የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር
ባለሥልጣን

ADDIS ABABA CITY
CONSTRUCTION PERMIT
AND CONTROL AUTHORITY

2431
13 01 /2016 ዓ.ም

ቁጥር ግፈቁሀ/3020 /2016ዓ.ም

1345/16
13/01/2016

ቦሌ 27/ሃ/ሀ/4

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለሁሉም የክፍለ ከተማ ጽ/ቤት
አ.አ

ጉዳዩ፡- <u>የተሸሻለ መመሪያ ተግባራዊ እንድታደርጉ ስለማሳወቅ ይሆናል</u>።

ከከተማ አስተዳደሩ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በ2016 በጀት ዓመት በአደረጃጀት ፣ በአሰራር፣ በቴክኖሎጂ እና በሰው ኃብት ሪፎርም በማድረግ ወደ ትግበራ ምዕራፍ መግባቱ ይታወቃል።

በዚህም መሠረት የተሻሻለውን የህንፃ መመሪያ ተግባራዊ እንድታደርጉ ከዚህ ጋር ተያይዞ ደብዳቤ ጋር -- ገፅ የተላከ መሆኑን አሳስባለሁ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን
Addis Ababa City Administration Building Permit & Control Authority

ከሠላምታ ጋር

አውራሪስ ከበደ በቀለ (ኢ/ር)
ዋና ዳይሬክተር
Awraris Kebede Bekele(Eng)
General Director

<u>ግልባጭ</u>፣

በግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

- ለዋና ዳይሬክተር
- ለም/ዋና ዳይሬክተር/3ቱም ዘርፍ/
- ለግንባታ ፈቃድ ዳይሬክቶሬት
- ለግንባታ ክትትልና ቁጥጥርዳይሬክቶሬት
- ለመጠቀሚያ ፈቃድና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ፋይል

92 ቀለደ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
BUREAU OF JUSTICE

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration
Bureau of Justice

በአዲስ አበባ ከተማ
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን
የህግ ጉዳዮች ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት
የአባሪ ብዛት
ስም ፈትሂያ ፈርማ

Date---20/2/16

Ref.No---ጉ/ፍ/ቁ/ሰ/2/101

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ለግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፡- **ረቂቅ መመሪያን ይመለከታል**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህንጻ ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት አስተያየት እንድንሰጥበት የላካችሁልን ረቂቅ መመሪያ ከሕጎች ጋር ያለውን መጣጣም በመፈተሸና የሚስተካለሉትን በማስተካከል የሕግ ቅርጽ እንዲያዝ በማድረግ መልሰን የላክን መሆኑን እየገለጽን መመሪያው ጸድቆ ወደ ተግባር ከመገባቱ በፊት ተቋሙ ተጠሪ ለሆነለት ለበላይ ኃለፊ እንዲያውቁት በማድረግ እንዲሁም በፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት ተገቢውን በማሟላት ለፌደራል ፍትህ ሚኒስቴር በማቀረብ እንድታስመዘግቡ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አሰፋ መብራቴ አዲሴ
ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ

- ለቢሮ ኃላፊ /ለአለሽ/
- ለምክትል ቢሮ ኃላፊ (ረቂቅ ሥርፀትና ምክር መስጠት ዘርፍ)
- ለህግ ጥናትና ምርምር ረቂቅ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት (

ፍትህ ቢሮ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ረቂቅ ድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

☎0115585850 /0115501356
✉ 15052
www.aaba.gov.et
https://youtube.com/channel/UC5072xwmW6V4RsyAMB6jmBg
Addis Ababa Bureau of Attorney
@Addis_Attorney
aaattorneybureau@gmail.com
t.me/AAbureauofattorney

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የህንጻ መመሪያ ቁጥር ---------/2016

በከተማው ተፈፃሚነት የሚኖረው ምቹ የግንባታ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እና የግንባታ የሥራ ሂደቶችና ዝርዝር አፈፃፀም ለአገልግሎት ሰጪም ሆነ ለተገልጋዩ ግልጽ በማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት እና በፌዴራል መንግስት የወጣውን የኢትዮጵያ ሕንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ጋር የተጣጣመ የህንጻ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከከተማው አስተዳደር መዋቅራዊ ፕላን መርሆች፣ የአፈፃፀም ስልቶች እና ከመሰረተ ልማት ቅንጅት፤ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ስርዓት ጋር እንዲጣጣምና የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት የሚያስችል የአፈፃፀም ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡





ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመርያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህንጻ መመሪያ ቁጥር ... /2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጉም**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. 'ሚኒስቴር" ማለት የኢፌዲሪ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ነዉ፤
   2. 'ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነዉ፤
   3. 'አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ፤
   4. 'ባለስልጣን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤
   5. "ጽህፈት ቤት" ማለት የክፍለ ከተማና የወረዳ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽህፈት ቤት ነው፤
   6. "የደንብ ማስከበር ባለሥልጣን" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ሲሆን በክፍለ ከተማ እና በወረዳ የሚገኘው ደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤት ነው፤
   7. "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ነው፤
   8. "ደንብ" ማለት የሕንፃ አዋጅን ለማስፈፀም የወጣው የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 243/2003 ነው፤
   9. "ስታንዳርድ" ማለት የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ስታንዳርድ ነው፤
   10. "የኘላን መረጃ" በአንድ ቦታ ሊገነቡ የሚችሉ ወይንም ለቦታው የተፈቀዱ የመሬት አጠቃቀም አገልግሎት አይነቶችን፣ ለቦታው የተፈቀደ የህንፃ ከፍታን፣ በቦታውና በአካባቢው የሚያልፉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን የአየር ክልከላ ክልልን (አቪዬሽን ክልል) ጨምሮ፣ ነባራዊ እና የታቀዱ መጠኖችን ወይንም ስፋቶች፣ ወዘተ የሚያሳይ ስልጣን ባለው አካል የሚሰጥ መረጃ ነው፤

11. **"የፕላን ስምምነት"** ማለት ስልጣን ባለው አካል ለህንጻ ግንባታ የቀረበ የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን ከከተማዉ ፕላን ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የጽሁፍ ስምምነት ነዉ፤

12. **"ግንባታ"** ማለት ማንኛውም ከመሬት በታች፣ከመሬት ላይ እና በላይ የሚገነባ አዲስ ህንጻ፣ መጠለያ፣ አጥር፣ እንዲሁም ነባር ህንጻ ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ነው፤

13. **"የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን"** ማለት የአንድን ሕንፃ መጠን ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃ የሚሰራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴ የማያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርክቴክቸር፣ የእስትራክቸር፣ የሳኒቴሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ መካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችንም ንድፍ ሊያካትት ይችላል፤

14. **"የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን ማሻሻያ"** ማለት በነባሩ ፕላን ለህንፃው ምድብ የተጠየቁ ፕላኖችን ወይም ዲዛይኖችን ትንታኔ ሙሉ በሙሉ መከለስ ሳያስፈልግ የግንባታ ዲዛይንና የከተማ ፕላን ህግጋትን ጠብቆ የሚደረግ ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ነው፤

15. **"መሠረታዊ ግንባታ"** ማለት የአንድ ግንባታ ሙሉ መዋቅር፣ የውጭና የውስጥ ግድግዳ ሥራ፣ የውጭ በርና መስኮት ስራና የጣሪያ ልባስ ስራ የተጠናቀቀለት ሕንፃ ግንባታ ነው፤

16. **"የግንባታ ዋና አገልግሎት ወይም ዋና ግንባታ"** ማለት ለጥበቃ ለአደጋ መከላከያና የመጠባበቂያ ኃይል አቅርቦት፣ ለግቢ ውስጥ መተላለፊያ፣ ለመንገድ፣ ለአጥርና ግንባታው ለሚሰጠው አገልግሎት ድጋፍ እንዲሰጡ ከሚገነቡት ግንባ ታዎች ውጪ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለሚሰጠው ቀዳሚ አገልግሎት ታስቦ የሚገነባ ግንባታ ነው፤

17. **"ጊዜያዊ ግንባታ"** ማለት የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚገነባ እና የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ የሚነሳ ግንባታ ነው፤

18. **"ገንቢ"** ማለት የግንባታ ደረጃውን የሚመጥንና ግንባታውን ለመስራት ውል የወሰደ የሥራ ተቋራጭ ወይም ለአነስተኛ ግንባታዎች ግለሰብ ባለሙያ ወይም ባለሙያ የሆነ የግንባታው ባለቤት ነው፤

19. “የሕንፃ ሹም” ማለት የህንጻ እዋጁን የማስፈጸሚያ ደንቡን እና ይህንን መመሪያ የሚያስፈጽም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል የተሾመ ሰው ነው፤

20. “ሪል እስቴት” ማለት ለሽያጭ፣ ለኪራይ፣ ወይም ለሊዝ አገልግሎት እንዲውል የተገነባ የመኖሪያ ሕንጻ ነው፤

21. የህንጻ ምድብ" ማለት የአስተዳደሩን እርከን ሳይመለከትና ሳይወሰን የሕንጻ ከፍታ እና የህንጻ አገልግሎት ባህሪይ ብቻ ለመግለጽ የሚጠቅም ስያሜ ነው፤

22. "ምድብ "ሀ" ሕንፃ" ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ከ7 ሜትር ወይም ከዚያ በታች የሆነ ባለ አንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም ማናቸውም ከሁለት ፎቅ በታች የሆነ የግል መኖሪያ ቤት ነው፤

23. "ምድብ "ለ"ሕንፃ" ማለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ከ7ሜትር በላይ የሆነ ወይም ባለሁለት ፎቅና ከሁለት ፎቅ በላይ የሆነና በምድብ "ሐ" የማይሸፈን ሕንፃ ወይም "ምድብ "ሀ" የተመደበ እንደሪል እስቴት ያሉ የቤቶች ልማት ነው፤

24. "ምድብ "ሐ" ሕንፃ" ማለት የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ ፣የፋብሪካ ወይም የወርክ ሾፕ ሕንፃ ወይም ከመሬት እስከ መጨረሻው ወለል ከፍታ ከ12 ሜትር በላይ የሆነ ማናቸውም ሕንፃ ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ የተካተቱትን ማስተካከያዎች ያካትታል፤

25. “የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ” ማለት በርካታ እና የተለያዩ ተጠቃሚዎችን የሚስብ እንደ ቲያትር ቤት፣ የሕዝብ ቤተ መፃሕፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ መዝናኛ፣ የትምህርት ተቋም፣ የህክምና አገልግሎት ሞስጫ፣ የገበያ ማእከል እና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ህዝብ የሚገለገልበት ሕንፃ ነው፤

26. “የሕንፃ ስጋት ደረጃ” ማለት በህንጻ ላይ ብልሽት ወይም ጉዳት ቢከሰት በሰው ህይወት፣ በአካባቢ እና ኢኮኖሚ ላይ የሚደርስ ስጋት ግምገማ ነው፤

27. “ዝቅተኛ (ዝ)” ህንጻ ስጋት ደረጃ” ማለት የሪል እስቴት እና ኮንክሪት ጣራ ያለው ህንጻን ሳይጨምር ማንኛውም አንድ ፎቅ (G+0) የሆነ ለግል አገልግሎት የሚውል የምድብ “ሀ” ሕንፃ ሆኖ በሕንፃው ላይ ብልሽት ወይም ጉዳት ቢከሰት ዝቅተኛ ደረጃ ያለው የስጋት ተጽዕኖ የሚያስከትል ነው፤

28. **"ዝቅተኛ እስከ መካከለኛ (ዝመ)" ሕንፃ ስጋት ደረጃ"** ማለት ማንኛውም የመኖሪያ ያልሆነ የምድብ "ለ" ሁለት ፎቅ (G+1) ሕንፃ ሆኖ አደገኛ ላልሆኑ እቃዎች ማከማቻነት፣ ለአነስተኛ እቃዎች መጋዘንነት፣ ለጋራዥ፣ ለእንስሳት ማቆያ፣ ለበረትና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች የሚውል እና በሕንፃው ላይ ብልሽት ወይም ጉዳት ቢከሰት ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ ያለው የስጋት ተጽዕኖ የሚያስከትል ነው፤

29. **"መካከለኛ እስከ ከፍተኛ (መከ)" ሕንፃ ስጋት ደረጃ"** ማለት የሪል እስቴት እና ኮንክሪት ጣራ ያለው ሕንፃን ሳይጨምር ማንኛውም ሁለት ፎቅ (G+1) የሆነ ለግል አገልግሎት የሚውል የምድብ "ለ" ሕንፃ ሆኖ፣ በህንጻው ላይ ብልሽት ወይም ጉዳት ቢከሰት ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያለው የስጋት ተጽዕኖ የሚያስከትል ነው፤

30. **"ከፍተኛ (ከ)" ሕንፃ ስጋት ደረጃ"** ማለት ማንኛውም የምድብ "ለ" እና "ሐ" ሕንፃ ሆኖ ለህዝብ አገልግሎት፣ ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ እና ማህበራዊ አገልግሎት የሚውል ወይም በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ "ዝ"፣ "ዝመ"፣ "መከ" እና "በከ" ውስጥ ያልተካተ ሆኖ በሕንፃው ላይ ብልሽት ወይም ጉዳት ቢከሰት ከፍተኛ ደረጃ ያለው የስጋት ተጽዕኖ የሚያስከትል ነው፤

31. **"በጣም ከፍተኛ (በከ)" ሕንፃ ስጋት ደረጃ"** ማለት ማንኛውም የምድብ "ሐ" ሕንፃ ሆኖ ለህዝብ አገልግሎት፣ ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ እና ማህበራዊ አገልግሎት የሚውል፣ ከፍተኛ የሰው ቁጥር (ከ500 በላይ) የሚያስተናግድ፣ እንዲሁም በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ "ዝ"፣ "ዝመ"፣ "መከ"፣ እና "ከ" ውስጥ ያልተካተተ ማንኛውም ህንጻ ሆኖ በሕንፃው ላይ ብልሽት ወይም ጉዳት ቢከሰት በጣም ከፍተኛ ደረጃ ያለው የስጋት ተጽዕኖ የሚያስከትል ነው፤

32. **"ወለል"** ማለት የምድር፣ ከምድር በላይ እና መሬት ውስጥ ያለ የህንጻ ወለል ነዉ፤

33. **"የወለል ብዛት"** ማለት ከመሬት በታች፣መሬት ላይና ከመሬት በላይ ያሉ የቆጥ ወለሎችን ሳይጨምር አንድ ግንባታ ያሉት አጠቃላይ የወለል ብዛት ነው፤

34. **"ተካፋች"** ማለት በማንኛውም ግንባታ ግድግዳ፣ ጣሪያ ወይም ወለል ላይ የሚገነባ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚከፈት መስኮት ወይም በር ነው፤

35. "የቆጥ ወለል ማለት በአንድ ወለል ከፍታ ውስጥ ያለና የታችኛውን ወለል 40 በመቶ የማይበልጥ ስፋት ያለው ወለል ነው፤

36. "የሕንፃ ተቆጣጣሪ" ማለት በከተማው አስተዳደር ክልል የሚካሄዱ ግንባታዎችን ሕጋዊነት እና የተሰጠን ፈቃድ በመመልከት በቅርብ የሚቆጣጠር ባለሙያ ነው፤

37. "መደበኛ ክትትል" ማለት በግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን መስሪያ ቤት በህጋዊ የግንባታ ፈቃዱ እርከን መሰረት ከመጀመሪያ እስከ ፍፃሜ ድረስ በግንባታው ላይ በባለስልጣኑ የሚከናወን አስገዳጅ ክትትል ነው፤

38. "ድንገተኛ ቁጥጥር" ማለት በሕንጻ ሹሙ ወይም በሸሙ የተሰየመው አካል በቁጥጥር ማስታወቂያ ከቀረበባቸው የሥራ እርከኖች ውጪ የሚደረግ ድንገተኛ የቁጥጥር ጉብኝት ነው፤

39. "የመጨረሻ ቁጥጥር" ማለት ግንባታው በተጠናቀቀና የመጠቀሚያ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ በቀረበበት ሕንፃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር ነው፤

40. "ከፍተኛ ማምረቻ ተቋም" ማለት በከተማ አስተዳደሩ ለማምረቻ በተከለለ ቦታ የሚገነቡ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ምርቶችን ሊያመርቱ የሚችሉ፤እንዲሁም በአካባቢው ላይ ተፅኖ ሊያደርሱ የሚችሉ የማምረቻ ተቋማት ነው፤

41. "ቀለም" ማለት የህንጻ የውጭ አካል ላይ የሚገኝ ማንኛውም የግንባታ ቁስ ቀለም ነው፤

42. "የህንጻ የውጭ ቀለም" ማለት በህንጻው ውጫዊ አካል ላይ የሚገኝ እንዲሁም ከመንገድ በኩል የሚታይ ማንኛውም ቁስ የሚኖረው ቀለም ነው፤

43. "የአዲስ አበባ ከተማ የህንጻ ቀለም ስታንዳርድ" ማለት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ህንጻዎች እንዲኖራቸው የተመረጡ ቀለማት የህንጻ ቀለማት ናቸው፤

44. "የህንጻ የፊት ለፊት ገጽ" ማለት በመንገድ በኩል የሚገኝ የህንጻው ቅርጽ ወይም ግድግዳ አካል ነው፤

45. "የህንጻ ላይ ማስታወቂያ" ማለት ማንኛውም በህንጻው ላይ የሚደረግ የንግድ ምልክት፣ የማስታወቂያ ቦርድ ወይም ባነር እንዲሁም ዲጂታል ስክሪን ነው፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

46. "የተፈጥሮ ቁስ" ማለት ድንጋይ፣ ማርብል፣ ግራናይት፣ እና እንጨት የመሳሰለ የግንባታ ግብዐት ነው፤

47. "የህንጻ ቁስ" ማለት በህንጻው የውጭ አካል ላይ የሚገኝ የግድግዳ፣ የመስታወት፣ የልባስ፣ የውቅር አካል፣ የፍሬም፣ የጣራ ሽፋን እና ተያያዥ ቁስ የሚሰራበት የግንባታ ግብአት ነው፤

48. **ከግንባታ የተወሰደ ማሻሻያ ፈቃድ'' ማለት** ግንባታው ከተጠናቀቀ በኃላ የግንባታ አካላት እንዲሁም ቁሳቁሶች፣ መለኪያዎች ወዘተ... በዲዛይኑ ላይ በማካተት የሚቀርብ የንድፍ አይነት ነው፤

49. "ባለቤት" ማለት የህንጻው ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ነው፤

50. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

51. በአዋጁ እና በደንቡ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በዚህ መመርያም ተፈጸሚነት ይኖራቸዋል፡፡

3. <u>የያታ አገላለጽ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ያታ የተደነገገው የሴትንም ያታ ያካትታል፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ በማንኛውም ግንባታ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

2. ይህ መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡-

ሀ) አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተሰጠ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ በመካሄድ ለይ በሚገኝ በማንኛውም ሕንፃ፣

ለ) ከሀገር ደንነት ጋር በተያያዘ የሕንፃ አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ሕንፃ ላይ፤

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ) አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በወጣ የህንፃ ግንባታ ፈቃድ መሠረት በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሆኖ ግንባታ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ከሆነ፣

ለ) አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የተጠናቀቀና አዋጁ ከፀና በኋላ የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት ወይንም የማፍረስ ጥያቄ በሚቀርብበት ሕንፃ ላይ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ተፈፃሚ እንዲሆንበት ማድረግ ይችላል።

ክፍል ሁለት

የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ማመልከቻ

5. የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ማመልከቻ አቀራረብ

በባለሥልጣኑና በጽፈት ቤቶች የሚሰጥ የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት በአዋጁ፣ በደንቡ እና በኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ መሠረት እንደሚከተለው የሚከናወን ይሆናል፡-

1. ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፤
2. ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ቅጽ-001 ማመልከቻ በመሙላት በባለስልጣኑ ድረ-ገጽ ወይም በአካል ቀርቦ የአገልግሎት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፤
3. የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን በሚቀርብበት ወቅት መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ የማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ በግልፅ መዘርዘር አለባቸው፤
4. ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ፕላኖች እና ማስረጃዎች፡-
   ሀ) ለሁሉም የህንጻ ምድቦች ተቀባይነት ያለው የይዞታ ባለመብትነት ማስረጃ ቅጂ፣
   ለ) ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሕንፃ ግንባታ የሚካሄድበትን ቦታ የሚያሳይ ከከተማው ፕላን ላይ የተወሠደ አካባቢውን የሚያሳይ የተሟላ የፕላን ስምምነት መረጃ፣
   ሐ) የኮንክሪት ጣሪያ ለሌላቸው የምድብ "ሀ" ህንፃዎች የአርክቴክቸር፤ የኤሌክትሪክ የግንባታ ዲዛይኖች ወይም ፕላኖች፣
   መ) የኮንክሪት ጣሪያ ላላቸው የምድብ "ሀ" ህንፃዎች የአርክቴክቸር፤ የስትራክቸር የኤሌክትሪክ የግንባታ ዲዛይኖች ወይም ፕላኖች፣
   ሠ) ለሕንፃ ምድብ "ለ" የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪክ የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላኖች፤ ትንታኔ፣ ሪፖርት እና የአፈር ምርመራ ሪፖርት፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

ረ) ለሕንፃ ምድብ "ሐ" የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪክ፣የእሳት አደጋ መከላከያ የግንባታ ዲዛይን/ፕላን፣ ትንታኔ፣ ሪፖርት እና ሁለትና ከሁለት ወለል በላይ ከፍታ ላላቸው የአፈር ምርመራ ሪፖርት፣ ኤሌክትሮ መካኒካል ዲዛይን ለሚያስፈልጋቸው ህንጻዎች ሙሉ የዲዛይን መረጃ፣

ሰ) ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የህንጻውን ጠቅላላ የወለል ስፋት ከውጪ የግድግዳ ጠርዝ የሚለካ ሆኖ የሁሉንም የወለል ስፋት በመደመር የሚሰላ ወይም ጥቅል ወጪ ግምት፣

ሸ) አስረኛው መሪ ፕላን ከመፅደቁ በፊት ግንባታ ፈቃድ አውጥተው ወደ ግንባታ የገቡ አልሚዎች ግንባታው ከተጀመረ በኋላ ተጨማሪ ወለል ለመጨመር ከፈለጉ እና የህንፃው ውቅር ተጨማሪውን መሸከም እንደሚችል ከተረጋገጠ በመሪ ፕላኑ የተቀመጠውን ዝቅተኛውን የወለል ምጣኔ ባያሟላም ወደዝቅተኛው እየተጠጋ በመሆኑ አገልግሎት እንዳያገኙ ይደረጋል፤ ሆኖም ባለው ክፍት ቦታ ላይ በይዞታው ውስጥ ተጨማሪ ብሎክ መገንባት ከተፈለገ የመዋቅራዊውን ፕላን ህግጋቶች መጠበቅ እና መሟላት ይኖርበታል፣

ቀ) ለከፍተኛ ማምረቻ ተቋማት ከአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማምረቻው በአካባቢው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ በማጥናት አሉታዊ ተጽእኖ ካለው ተጽእኖውን ለመቀነስ መካተት ያለበትን የግንባታ አይነት የሚተነትን የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ፣

በ) በአደባባይ፤ መንገዶች ላይ ወይም በከተማው ውስጥ ባሉ የህዝብ መተላለፊያ ቦታዎች የሚተከሉ የሃውልት፣ ቅርጻ ቅርጽ እና ቋሚ የመታሰቢያ ግንባታዎች በሁሉም አቅጣጫ ያለውን ገጽ የሚያሳይ ንድፍና የተሸካሚ አካላትን ስትራክቸራል ዲዛይን፣

ተ) አሳንሰር እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን የሚጠቀሙ ህንፃዎች የመካኒካል ቬንትሌሽን እና ኤር ኮንዲሽኒንግ የግንባታ ዲዛይኖች ወይም ፕላኖች እና ትንታኔዎች፣

ቸ) በአዋሳኝ ባሉ ሥፍራዎች የሚገኙ ዋና መንገዶችና የታወቁ ቦታዎችን ሥም የሚገልጹ መረጃዎች፣

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

ጎ) በአዋሳኝ ቦታዎች የሚገኙ ግንባታዎች ከመሬት በላይ እና በታች ያላቸው የወለል ብዛት፣ ከጋራ ወሰን ያላቸው ርቀት እና ከምድር ወለል በታች ያላቸው ጥልቀት፣

ኀ) የአማካሪ ግዴታ መግቢያ ቅጽ 010 መሰረት በአማካሪ ደረጃ ለሚሰሩ ዲዛይኑን ባዘጋጀው ባለሙያ የተፈረመ እና ማህተም ያረፈበት፣

ኘ) ለሁሉም የህንፃ ምድቦች የህንፃውን ፕላን ያዘጋጁ ባለሙያዎች ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤ በዘመኑ የታደሰ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣

አ) በአማካሪ ድርጅት ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ፕላኖች የድርጅቱ ማህተም ያረፈበትና ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቅጂ የሚመሳከር፣

ከ) ዲዛይኖች በንኡስ አማካሪ የሚሰራ ከሆነ በንኡስ አማካሪ ደረጃ ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላኖች የንኡስ አማካሪው ማህተም ያረፈበት የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂና የሚመሳከር፣

ኸ) የማሻሻያ ፈቃድ ከሆነ የቀድሞው የጸደቀውን የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት እና የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን እንዲሁም ክትትል የተደረገበት የመስክ ሪፖርት ወይም የመስክ ደብተር፤ የማሻሻያ ፈቃድ ከወለል ጭማሪ ዉጭ ቀድሞ አገልግሎቱን ባገኘበት ማዕከል የሚሰጥ ሆኖ ቀድሞ የተሰጣቸዉ የፈቃድ ጊዜ ካልተጠናቀቀ በወቅቱ የቀረቡ ሰነዶችን የአማካሪና የባለሙያ ፈቃድና ኢንሹራንስ/ከቀድሞ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣ ዕዳና ዕገዳ ማጣሪያ፣ የፕላን ስምምነት ድጋሚ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፣

ወ) በቀረበው ዲዛይን መሰረት የመድን ዋስትና ሽፋን፤

5. ለአዋሳኝ ቦታዎች የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ በአንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት ቅፅ 009 አጎራባቹን በማስሞላት የሚቀርብ ይሆናል፤

6. የግንባታ ፈቃድ በተጠየቀበት ይዞታ የሚገኝ የአጐራባች ባለይዞታ፣ ይዞታውን በሚመለከት የሚቀርብለትን ቅፅ መሙላት ይኖርበታል፤

7. የሚቀርቡ ፕላኖች መዘጋጀት የሚኖርባቸው በዲዛይን ባለሙያዎች እና አማካሪዎች ምዝገባ መመሪያ መሠረት የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚያሟሉና እና

ባለሙያዎችን ለመመዝገብና ለመፍቀድ ሥልጣን በተሰጠው አካል በተመዘገቡ ባለሙያዎች መሆን ይኖርባቸዋል፤

8. የዲዛይን አማካሪ ደረጃን በተመለከተ ሚኒስቴሩ ባወጣው ደንብ እንዲሁም ባለስልጣኑ ባወጣው መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤
9. የከተማው መዋቅራዊ ፕላን መጽደቅ በፊት የግንባታ ፈቃድ የተሰጠው በማንኛውም ምክንያት የግንባታ ፕላን ለውጥ ወይም ማሻሻያ ለማድረግ ሲቀርብ በፈቃዱ ጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታው ቤዝመንት ካለው መሰረት አልቆ ቤዝመንት ኮለን ከተጠናቀቀ እና ቤዝመንት ከሌለው የምድር ወለል ኮለን ስራ ካልተጠናቀቁ በስተቀር የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ በጸደቀው የመሪ ፕላን መስፈርት መሰረት እንደ አዲስ የሚታይ ይሆናል፤
10. ነባር ወይንም ጅምር ግንባታ ጋር በማያያዝ ወይንም በማስተሳሰር ወይንም የህንጻ ከፍታ በመቀጠል ለማሻሻል የሚቀርብ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ከሆነ ከሚቀርበው የዲዛይን ሰነድ ጋር የነባሩ ህንጻ የአፈር አይነት ጥናት፣ የመሰረት አይነትና ጥልቀት፣ የተሰራበት ዓመተ ምህረት፣ ቀድሞ የተገነባው መሰረት እና ሌሎች ተዛማጅ መዋቅራዊ አካላት ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ እና ከላይ የተጠቀሱትን የነባሩን ህንጻ የዲዛይን መረጃ መሰረት በማድረግ አዲስ የስትራክቸራል ዲዛይን ትንታኔ መቅረብ አለበት፤ ሆኖም በቀረበው ትንታኔ እና ከመሬት በታች እና በላይ በተገነባውና በተሸፈነው መዋቅራዊ አካላት ግንባታ መካከል ሊኖር በሚችል የመጠን ልዩነት ወይንም በሌላ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ችግር የዲዛይን አማካሪው ኃላፊነት ይወስዳል።

6. <u>የኘላን ወይም የግንባታ ዲዛይን አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም የግንባታ ዲዛይን የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርዶችን፣ የህንጻ አዋጅ፣ የህንጻ ደንብ እና የህንጻ መመሪያን በማሟላት ተጠቃሚውንና የአካባቢውን ማህብረሰብ ደህንነት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፤
2. በከተማው ውስጥ ማንኛውም ግንባታ ለማካሄድ በቅድሚያ የግንባታ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፤
3. የግንባታ ፈቃድ ጉዳይ በግንባታው ባለቤት ወይንም በህጋዊ ወኪል ወይንም ንድፉን ባዘጋጀው አማካሪ ወይም ባለሙያ ብቻ አቅራቢነት መካሄድ ይችላል፤ ሆኖም የግንባታ ፈቃዱ ወጪ ሆኖ የሚሰጠው ለባለቤት ወይንም ለህጋዊ ወኪል ብቻ ነው፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

4. በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡ ነገር ግን አንድ አይነት ስታንዳርድ ፕላን ያላቸው ግንባታዎች የየራሳቸው የግንባታ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፤
5. የፕላን መለኪያዎች በሜትሪክ ሲስተም እና በግራፊክስ ስታንዳርድ የልኬት አፃፃፍ መቅረብ አለባቸው፤
6. የሚቀርቡ የግንባታ ዲዛይኖች ወይም ፕላኖች በ 3 ቅጂ ሆነው እንደአስፈላጊነቱ ቢያንስ በA3 መጠን እና ቢበዛ በA1 መጠን የተዘጋጁ ሆነው በፕላን ኮፒ ወይም በብሉ ፕሪነት ወይም በባለ 80 ግራም ነጭ ወረቀት ንድፍ መሆን ይኖርበታል፤
7. የጽሑፉ ሰነድ በA4 መጠን መሆን አለበት፤ ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ከሶፍት ኮፒ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የሕንፃ ሹሙ ሊጠይቅ ይችላል፤
8. በግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን ወይም በንድፍ መግለጽ ያልቻሉ ዝርዝር መግለጫዎች በፕላኑ ላይ በጽሑፍ መመልከት ይኖርባቸዋል፤
9. ለሁሉም ሕንፃዎች የወለሉ ከፍተኛ የጎን ስፋት ከ30 ሜትር የማይበልጥ ከሆነ ፕላኖቹ በ1፡50 ሚዛን እንዲሁም የሳይት ፕላኖቹ በ1፡200 ሚዛን እንዲሁም የወለሉ ከፍተኛ የጎን ስፋት ከ30 ሜትር በላይ ከሆነ ፕላኖቹ በ1፡100 ሚዛን እንዲሁም የሳይት ፕላኖቹ በ1፡500 ሚዛን መዘጋጀት ይኖርበታል፤
10. ዝርዝር ፕላን ለሚዘጋጅላቸው ንድፎች በ1፡10፣ 1፡20፣ ወይም 1፡25 ሚዛን ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፤
11. ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ፕላኖች ዝርዝር የፕላን ምድቡ የሚጠይቀውን በማሟላት መለኪያቸው በሜትሪክ ሲስተም ወጥ ሆኖ መግለጽ ይኖርበታል፤
12. ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ዲዛይኖች ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉት የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት የተዘጋጁ መሆን አለባቸው።።

7. <u>የፕላን ስምምነት</u>

1. አዲስ፣ ተጨማሪ እና የማሻሻያ ግንባታ ለማከናወን እንዲሁም ከግንባታ የተወሰደ ፈቃድ የሚፈልግ ሰው የህንፃውን ዲዛይን ከማዘጋጀቱ በፊት የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፤
2. የፕላን ስምምነት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በቅጽ 003 መሠረት ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፤

3. በማመልከቻ ቅጹ ላይ ተሞልቶ የሚቀርብ ጥያቄ በነባር ይዞታ ላይ ለአዲስ ግንባታ የሚጠየቅ ስምምነት ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ቅጂ፣ የሊዝ ይዞታ ላይ ከሆነ ደግሞ የሊዝ ውሉን በተጨማሪ የሚያያዝ ሲሆን፤ ለነባር ግንባታ ማሻሻያ ከሆነ፡-

   ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ቅጂ፡-

   ለ) የተፈቀደበትን የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት

   ሐ) ለግንባታ ፕላን ማሻሻያ አገልግሎት የሚጠየቅ ከሆነ የመስክ ደብተር ወይም ሪፖርት ከቅጽ-003 ጋር ተያይዞ

   መ) የሊዝ ይዞታ ከሆነ የሊዝ ውሉን አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

4. የፕላን ስምምነቱ በከተማው መዋቅራዊ ፕላን ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፤

5. በፕላን ስምምነት መረጃ ላይ ተጨማሪ በከተማዋ የህንጻ ቀለም ስታንዳርድ መሰረት የህንጻ ቀለማት ኮዶች ምርጫና መጠሪያ ተጠቅሶ የሚሰጥ ይሆናል፤

6. የፕላን ስምምነቱ በሚመለከተው ባለሙያ እና ኃላፊ ተፈርሞ እና በመስሪያ ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለጠያቂው አካል መሰጠት ይኖርበታል፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት የተሰጠ የፕላን ስምምነት ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ለ12 ወራት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡





8. <u>የኘላን መግምግሚያ ጊዜ</u>

1. ማንኛውም ለግንባታ ሥራ የተዘጋጁ ኘላኖች ለየሕንጻ ምድቡ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መግምገም አለባቸው፤
2. ለአንድ የሕንጻ ዓይነት የተዘጋጁ የግንባታ ዲዛይኖች ወይም ፕላኖችን ለመግምገም በአማካይ የሚያስፈልገው ጊዜ፡-
   ሀ) ከሪልስቴት ውጪ ላለ በምድብ "ሀ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች የመግምገሚያ ጊዜ ከ5 የሥራ ቀናት ያልበለጠ፣
   ለ) በምድብ "ለ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች መግምገሚያ ጊዜ ከ7 የሥራ ቀናት ያልበለጠ፣
   ሐ) በምድብ "ሐ" ስር ለሚካተት ሕንፃ እና በምድብ "ለ" ውስጥ ለሚካተቱ የሪል እስቴት ህንጻዎች ኘላኖች የመግምገሚያ ጊዜ ከ21 የሥራ ቀናት የበለጠ መሆን የለበትም፤
3. ከፕሮጀክቱ ስፋት ወይም ውስብስብነት የተነሳ ተጨማሪ ጊዜ ለሚሸ ስራዎች የህንጻ ሸ.ሙ ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ ቅጽ 24 በመሙላት መጠየቅ ይኖርበታል፤
4. ለግምገማ የሚቀርብ ዲዛይን መሻሻል የሚስፈልገው ከሆነ መሻሻል ያለበትን በማመልከት ለአመልካቹ በእርማት መስጫ ቅጽ ተገልጸ ይሰጠዋል፤
5. የሃይማኖት ተቋማት፣ የዲፕሎማቲክ ተቋማት፣ አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ግንባታዎች እና በመንግስት ባለቤትነት የሚከናወኑ ግንባታዎች በባለስልጣኑ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይስተናገዳሉ፤
6. ለባለስልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ ማመልከቻ ከቀረበ ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ ይሰጣል፤ ሆኖም የተጠቀሰውን የውሳኔ ማሳወቂያ ጊዜ በየግንባታው ዓይነት ሊቀርቡ የሚችሉትን ከፍተኛ ግንባታዎች ከግምት በማስገባት የተሰጠ የጊዜ ጣሪያ እንጂ እንደ ፕሮጀክቱ መጠን በተነጻጻሪ ከተሰጠው የጊዜ ጣሪያ በፊት ውሳኔ የሚሰጥባቸው ናቸው፤

ሰንጠረዥ፡-1፡ ለግንባታ ፈቃድ አገልግሎት የፕላን መገምገሚያ ጊዜ

ተ.ቁ	የግንባታ ፈቃድ አይነት (አዲስ፣ ማሻሻያ፣ የአገልግሎት ለውጥ)	የወለል ብዛት (የህንጻ ምድብ)	የይዞታ ስፋት (ሜትር ካሬ)	ለምርመራ የሚወስደው ከፍተኛ ቀን						ድምር
				አርክቴክቸራል	ስትራክቸራል	ኤሌክትሪካል	ሳኒቴሪ	መካኒካል	ኳንቲቲ	
1	የፕላን ስምምነት መረጃ	በሁሉም	---	-	-	-	-	-	-	2 ሰዓት
2	ነጠላ መኖሪያ ቤት	ምድብ "ሀ"	---	2	-	1	-	-	-	3ቀን
3	ነጠላ መኖሪያ ቤት	ምድብ "ለ"	---	3	2	1	1	-	-	7ቀን
4	የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ እና ሪል እስቴት	ምድብ "ሐ"	---	7	4	3	3	2	2	21ቀን
5	ማምረቻና ማከማቻ	ምድብ "ሐ"	---	7	4	3	3	2	2	21ቀን
6	የእድሳት ፈቃድ	-	---	-	-	-	-	-	-	2ቀን
7	የማፍረስ ፈቃድ	-	---	-	-	-	-	-	-	2ቀን
8	ልዩ ከግንባታ የተወሰደ አስ.ቢ.ልት ፈቃድ (ስፔሻል አስቢውልት)	በሁሉም	---	9	-	-	-	-	-	9ቀን
9	ከግንባታ የተወሰደ አዝ ቢሙልት ፈቃድ	በሁሉም	---	3	2	2	2	-	-	9ቀን
10	የስም ለውጥ	በሁሉም	---	1	1	1/2	1/2	-	-	3ቀን
11	ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ	-	---	-	-	-	-	-	-	2ቀን
12	የምሽት ግንባታ ፈቃድ	-	---	-	-	-	-	-	-	2ቀን
13	የግንባታ መጀመሪያ ማራዘሚያ	በሁሉም	---	3	-	-	-	-	-	3ቀን



9. <u>ግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን ስለማፀደቅ</u>

1. የሕንፃ ሹሙ የቀረበውን የፕሮጀክቱን ዲዛይንና ሰነድ ከመሪ ፕላኑ እና ከኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ መስፈርቶች ጋር በማገናዘብና በመመርመር የተሟላ ሆኖ ሲያገኘው በግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጽ 002 ላይ የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ ሥር የሚገኙትን መረጃዎች ሞልቶ ያፀድቃል፤ የፀደቁትን ሰነዶች በአንደኛው ኮፒ ላይ "ተፈቅዷል" የሚል ማህተም፤ በሁለተኛው ኮፒ ላይ "ለክትትል ብቻ "የሚል ማህተም ተደርጎባቸው ለአመልካቹ ይሰጣሉ፣ ሦስተኛው ኮፒ "ቀሪ" ተብሎ ከፋይል ጋር ይያያዛል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የፀደቀ የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን የግንባታ ፈቃድ ቁጥር እና የፀደቀበትን ቀን የያዘና የሕንፃ ሹሙ ወይም የተሰየመው አካል ፊርማ እና ማሕተም ያረፈበት መሆን ይኖርበታል፤

3. የግንባታ ፈቃድ የማያስከለክሉና እርማት ተደርጎባቸው የሚታለፉ ግድፈቶች፡-

ሀ) በስትራክቸር ዲዛይን ላይ ለውጥ የማያመጡ እና የተዘነጉ ንድፎች፣

ለ) በግንባታ ሂደት ላይ ተጽእኖ የማይፈጥሩ የተዘነጉ ልኬቶች ማስተካከያ የተደረገባቸው፣

ሐ) በግንባታ ፈቃድ የተቀመጡ ሌሎች ግዴታዎችን ለመወሰንና የክፍሎችን ስፋት እና አጠቃቀም ለመወሰን የግድ መመልከት ካለባቸው በስተቀር የተዘነጉ የመጠቀሚያ ቁስ ንድፍ ወይም ማጠናቀቂያ፤

4. ደረጃ በደረጃ ወይም በየምእራፉ ለመግንባት የቀረበ ፕላን፡-

ሀ) የመጀመሪያው የግንባታ ደረጃ ዝቅተኛውን የመሪ ፕላን መስፈርት እና ከመሪ ፕላኑ ዝቅተኛ የሕንፃ ከፍታ ሳያንስ የግንባታ ፈቃዱ ሊሰጥ ወይም ሊፀድቅ ይችላል፤

ለ) ዝቅተኛውን የመሪ ፕላን መስፈርት እና ከመሪ ፕላኑ ዝቅተኛ የሕንፃ ከፍታ የማይገደዱ አገልግሎቶች የብሎኮችን ብዛት ደረጃ በደረጃ በመወሰን የግንባታ ፈቃዱ ሊሰጥ ወይም ሊፀድቅ ይችላል፤

ሐ) ለክትትልና ለመጠቀሚያ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ ያመች ዘንድ በግንባታ ፈቃድ ሰነድ ላይ ደረጃ በደረጃ ለመገንባት የታቀደው በግልፅ ተለይቶ በሚፈቀደው ፕላን ላይ መመልከት ይኖርበታል፣

መ) ደረጃ በደረጃ በመገንባት ሂደት የተወሰነ የግንባታ ክፍል አገልግሎት እየሰጠ ቀሪው ግንባታ የሚካሄድ በመሆኑ የህንጻው ተጠቃሚዎች እና ሌላው በአካባቢው እንቅስቃሴ በሚያደርጉት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በፍቃድ አሰጣጥ ላይ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤ በግንባታ ወቅት በአካበቢው የሚንቀሳቀስን ሰው ከአደጋ ለመከላከል ገንቢው ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ አለበት፤ በግንባታ ወቅት በሚደርስ አደጋ ገንቢው፤ አማካሪው እና ባለቤቱ በጋራ ወይም በተናጠል ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፣

ሠ) ደረጃ በደረጃ በመገንባት ሂደት ወቅት በዚህ ንዑስ አንቀፅ ከተራ ፊደል (ሀ) እስከ (መ) የተገለፁት እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ ቀደም የተጠናቀቀው ህንጻ አካል ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች መቋረጥ አለባቸው፣

ረ) አገልግሎቱ ሳይቋረጥ መገንባት ከተፈለገ መሰረታዊ የመዋቅር አካላት ስራዎች መጠናቀቃቸውን እና የውጭ ግድግዳ አካል ግንባታ የአካባቢውን እንቅስቃሴ የማያውክ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣

ሰ) አሰሪው ወይም ባለቤቱ የቀጣይ ምዕራፍ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ለክትትልና መጠቀሚያ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እንዲያመች ለሕንጻ ሹሙ ወይም ለተሰየመው አካል በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፣

5. ግንባታ ለመጀመር በግንባታ ፈቃድ ወቅት የሚቀርቡ እና በግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ወቅት በድጋሚ የማይጠየቁ ቅድመ-ሁኔታዎች፡-

ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቅጂ፣

ለ) የሊዝ ባለ ይዞታዎች የሊዝ ውል ቅጂ፣

ሐ) የግንባታ ፈቃድ ሰርተፊኬት ቅጂ፣

መ) የፀደቀ ፕላን ወይም ዲዛይን ቅጂ፣

ሠ) የግንባታ ስራ የዋጋ ዝርዝር /ቢኦኪው፤ ናቸው፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፈቃድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ስር የተዘረዘሩ ሰነዶች በግንባታ ፈቃድ ወቅት እንዲሟሉ በማድረግ አንድ ቅጂ ግንባታ እንዲጀመር ለግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ወይም ቡድን ይላካል፤
7. የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ክፍል በንዑስ አንቀፅ (5) የተጠቀሱ ሰነዶችን ማቅረብ ሳያስፈልግ የአማካሪ እና ስራ ተቋራጭ የተሟላ መረጃ እና የመድን ዋስትና እንዲያቀርቡ በማድረግ የመጀመሪያ እርካን አገልግሎት ይሰጣል፡፡

ቀ) የውቅር አካላትን የማያናጉና አርክቴክቸራል ቅርፁን የማይቀይሩ የውስጥ ቀለም ቅብ፣ ስታንዳርዱን የጠበቀ መስታወት መቀየር፣ ቀላል ክብደት ባላቸው የሚገነቡ የውስጥ ማከፋፈያ ግድግዳዎች፣ ነባር የመብራትና የሳኒታሪ መገጣጠሚያዎችን የመለወጥ ሥራ ናቸው።

12.<u>የግንባታ ፈቃድ</u>

1. የፀደቀ የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን እንደ ግንባታ ፈቃድ ያገለግላል፤
2. የግንባታ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የግንባታ ሥራዎች፡-
   ሀ) አዲስ የግንባታ ሥራ፣
   ለ) ከውስጥ የቀለም ቅብ እና የማጠናቀቂያ ሥራዎች ውጪ ያሉ የጥገና እና የእድሳት ስራዎች፣
   ሐ) ግንባታ የማስፋፋት እና የማሻሻል ሥራ፣
   መ) ግንባታ የማፍረስ ሥራ፣
   ሠ) የሕንፃ አገልግሎት ለውጥ፣
   ረ) የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ፈቃድ፣
   ሰ) 40 ፐርሰንት የነባር ግንባታ ግዜዜዊ ማሻሻያ፣
   ሸ) የጊዜያዊ ግንባታ፣
   ቀ) የምሽት ግንባታ ስራ፣
   በ) ከግንባታ የተወሰደ ማሻሻያ ፈቃድ፣
   ተ) ልዩ ከግንባታ የተወሰደ ፈቃድ፤ ናቸው፤
3. ቀደም ሲል የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ በተለያየ ሁኔታ እንዲለወጥ ሲወሰን በአዲስ ተተክቶ ለባለይዞታው ይሰጣል፣
4. በአንቀጽ 13 ንኡስ አንቀጽ (2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ እንቅስቃሴ ተጀምሯል የሚባለው የመሠረት ቁፋሮና ለመሠረት ግንባታ የሚያስፈልግ ብረት አቅርቦት ዝግጅት ሲጀመር ነው፤
5. ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊታገድ ይችላል፡-
   ሀ) ግድፈት እያለበት በስህተት የፀደቀ ፕላን ሆኖ ሲገኝ፣
   ለ) የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ የተሳሳተ መረጃ ከያዘ፣
   ሐ) ግንባታው ተቀባይነት ካለው ገደብ በላይ የሆነ የአካባቢ ብክለት የሚያስከትል መሆኑ ሲደረስበት፣

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
ፈቃድና ቁጥጥር ባለ/ሥልጣን

10.<u>ፕላን ውድቅ ስለማድረግ</u>

1. ከህንፃ አዋጁ፣ ከማስፈፀሚያ ደንቡና ከኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ እንዲሁም ከዚህ መመሪያ ጋር የማይጣጣም የግንባታ ፕላን በህንፃ ሹሙ ውድቅ ይደረጋል፤
2. ለምርመራ የቀረበው ዲዛይን የግንባታ ፈቃድ መስፈርትና የኢትዮጵያን ህንጻ ስታንዳርድ የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱ የተከለከለበትን ምክንያት ዝርዝር በግንባታ ፈቃዱ መጠየቂያ ቅጽ ላይ ተሞልቶና "አልተፈቀደም" የሚል ማህተም ተደርጐበት ለባለጉዳዩ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

11.<u>በግንባታ ወቅት ፕላንን ስለማሻሻል</u>

1. በግንባታ ወቅት የዲዛይን ማሻሻያ ስራ ሲያስፈልግ የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ 22 በመሙላት የተሻሻለውን የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን፣ ግንባታ ከመካሄዱ በፊት ጥያቄውን ለህንጻ ሹሙ ወይም ለተሰየመው አካል በማቅረብ መጽደቅ ይኖርበታል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በህንጻ ሹሙ ወይም በተሰየመው አካል መጽደቅ ሳያስፈልጋቸው የግንባታ ሥራ ለውጥ ማሳወቂያ ቅጽ 17 በመሙላት እና በማሳወቅ መሻሻል የሚችሉ የፕላን አካላትና ዲዛይኖች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) በፕላን ላይ የሰፈሩ የልኬት ጉድለት ወይም ስህተት፣

ለ) የውስጥ ማከፋፈያ ግድግዳ የተጨማሪ ጭነት በማይፈጥር ቁሳቁስ መለወጥ፣

ሐ) የኤሌትሪክ ነጥቦች ሳይቀየሩ የሚደረግ የኤሌክትሪክ መስመር አቅጣጫ ለውጥ ስራ፣

መ) የክፍል ውስጥ ማሥጌጥ ሥራ፣ የግቢ ማስዋብ ሥራ፤

ሠ) በግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን ላይ በከፊል ወይም በጥቅል የተገለፀና ዝርዝር መስፈርታቸው ወይም መለኪያቸው ያልተካተተ ስታንዳርድ ያላቸው የፋብሪካ ውጤቶች፣

ረ) በንድፍ ላይ በግንባታ ወቅት በመሐንዲሱ እንደሚወሰኑ የተገለጹ ሌሎች ስራዎች፣

ሰ) የውስጥ ክፍሎች የወለል ንጣፍ ሥራ፣ ከሕዝብ መገልገያ ውጪ ለሆኑ ሕንጻዎች

ሸ) የጣሪያ ልባስ ቁስ፣ የኮርኒስ፣ የአሸንዳና ጎረንዳዮ ቁሳቁስ ለውጥ፣

መ) አሰሪው ከተፈቀደለት ዲዛይን ውጪ እየሰራ ቢገኝ፣

6. በግንባታ ቦታ ላይ የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ ወይም የግንባታ ፈቃድ ቁጥር የያዘ የማስታወቂያ ሰሌዳ በግልጽ ቦታ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡

13.<u>የግንባታ ፈቃድ የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ</u>

በአስተዳደሩ እና በአልሚው መካከል የተገባ የግንባታ መጀመሪያ እና ማጠናቀቂያ የተለየ የጊዜ ገደብ ውል ከሌለ በስተቀር አንድ ግንባታ የግንባታ ፈቃዱ ጸድቆ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ዉስጥ ግንባታዉን መጀመርና በ5 ዓመት ዉስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡

14.<u>የጊዜ ገደብ</u>

በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ግንባታዉ ካልተጀመረ የግንባታ ፈቃዱ አያገለግልም፤ ሆኖም ግን ስድስት ወራት ያለፈው የግንባታ ፈቃድ በወቅቱ ካለው የከተማ ፕላን ህግጋት፣ ደንብ እና ሌሎች ተያያዥ ህጎችን እስካሟላ ድረስ የግንባታ መጀመሪያ ማራዘሚያ ፎርም ሞልቶ ሲጠይቅ በሀንዳ ሹሙ ታይቶ ሊራዘምለት ይችላል፡፡ ለሊዝ ባለይዞታዎች ግን በሊዝ ደንቡ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

15.<u>የግንባታ ፈቃድ ስለመጠየቅ</u>

1. ማንኛውም ሰው አዲስ፣ ተጨማሪ ማሻሻያ፣ ከግንባታ የተወሰደ፣ የአገልግሎት ለውጥ፣ ጊዜያዊ ግንባታ፣ የመጠቀሚያ ፈቃድ ወይም የማፍረስ ሥራ ለማከናወን ሲያቅድ በቅድሚያ የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፤

2. አዲስ፣ ተጨማሪ ማሻሻያ፣ ከግንባታ የተወሰደ፣ የመጠቀሚያ ፈቃድ፣ የአገልግሎት ለውጥ፣ ጊዜያዊ ግንባታ ወይም የማፍረስ ሥራ ለማከናወን የሚቀርብ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ለአዲስ ማስፋፊያ፣ ለማሻሻያ ግንባታ ወይም ከግንባታ የተወሰደ በቅፅ 001፤ ለግንባታ እድሳት ፈቃድ በቅፅ 005" ለግንባታ ማፍረስ ፈቃድ ቅጽ 006፣ ለአገልግሎት ለውጥ ቅጽ 007፣ ለጊዜያዊ ግንባታ ቅጽ 020 በመሙላት የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ እና የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በሃላፊ ተፈርሞ እና የድርጅቱ ማህተም አርፎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፤

3. በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡ አንድ ዓይነት ስታንዳርድ ፕላኖች ያላቸው ግንባታዎች የየራሳቸው የግንባታ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

16.የወሰን ላይ ግንባታ

1. የአዋሳኝ ቦታዎች መረጃ የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ ቅፅ 009 አጎራባቹን በማስሞላት የሚቀርብ ይሆናል፣ አጎራባቹ በማሳወቂያው መሰረት መረጃውን የመሙላት ግዴታ ያለበት ሲሆን ማሳወቂያ ቅጹን እንዲሞላ በተሰጠው በሦስት ተከታታይ ቀናት ሞልቶ ለግንቢው ካልመለሰ መረጃውን ለመሙላት ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ግንቢው ኃላፊነት በመውሰድ እና በቅጽ 009 ቁጥር 3 ላይ የአዋሳኝን ቅድሚያ ስምምነት ሳይጠየቅበት ግዴታ በመግባት የሚካሄድ የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ በሚለው ላይ ግዴታ ገብቶ የግንባታ ፈቃድ መውሰድ ይችላል፤
2. የወሰን ላይ ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት ወሰንተኛ የሆኑ ተጎራባቾች ግንባታው ለደህንነታቸው አስጊ ያለመሆኑን እና ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ ተወስዶ እየተከናወነ መሆኑን በመመልከት ማረጋገጥ ይችላሉ፤
3. ማንኛውም ሰው በሚሰራው ግንባታ ምክንያት የአዋሳኝ ነባር ግንባታ ደህንነት አደጋ ላይ የማይወድቅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤
4. ማንኛውም የግንባታ አካል ወይም ተንጠልጣይ ወለል ቄምር ከ2.00 ሜትር ርቀት በታች ከወሰን ተጠግቶ የሚገኝ ከሆነ ወሰን ላይ እንዳለ ግንባታ ይቆጠራል፤
5. አንድ ግንቢ ወሰን ላይ እንዲገነባ ፈቃድ ቢሰጠውም ማንኛውም ተካፋች ከወሰን መራቅ ያለበትን ርቀት ጠብቆ መገንባት አለበት፤
6. ወሰን ላይ የሚገነባ የምግብ ማብሰያ እና መሰል አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ግድግዳ የእሳት ቃጠሎን በተሻለ ሁኔታ መከላከል በሚችል ድፍን የግድግዳ ቁስ መገንባት አለባቸው፤
7. አስቀድሞ ወሰን ላይ የገነባ ወሰንተኛ ያገኘውን ወሰን ላይ የመገንባት መብት ወይ ጥቅም የኋላ ግንቢውም በተመሳሳይ መልኩ ወሰን ላይ የመገንባት እና የመዋቅራዊ ፕላኑ የህንፃ ከፍታ ህግጋት ጠብቆ ህንፃ መገንባት ይችላል፤
8. ከወሰንተኛ ግንባታ ጋር የተያያዘ እና የጋራ የሆነ ጣሪያ ወይም ግድግዳ ካለው፤ በአዋሳኝ ያለን ግንባታ ለማሻሻል፤ ለማደስም ሆነ ለማፍረስ የጋራ የሆነውን ግንባታ ባለበት እንደጠበቀ፤ በማሻሻያው ግንባታ ማፍረስ ሂደት የህንፃው ደህንነት ለመጠበቅ ግዴታ በመግባት በፈቃዱ መሰረት መፈፀም ይቻላል፤
9. ማንኛውም ወሰን ላይ የሚገነባ ህንፃ ዲዛይን ጥናት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ታሳቢዎች ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፤ ማንኛውም ግንባታ የምድር በታች

ወለል ቢኖረውም ባይኖረውም ከወሰን 2 ሜትርና ከዚያ በታች ተጠግቶ የሚገነባ ከሆነ፡-

ሀ) ለፈቃድ የሚቀርበው ስትራክቸራል ዲዛይን የወሰንተኛውን ነባር የህንፃ መዋቅር ይዘት ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፤ ይህም በሚቀርበው የዲዛይን ሰነድ የወሰንተኛውን ነባር የህንፃ መጠን ለምሳሌ ጭነት ከግምት ያስገባበትን ማመልከት አለበት፣

i. ከመሬት በታች ያለው የመሰረት ዓይነት፣

ii. ከመሬት በታች ያለው የወለል ብዛት፣

iii. ከመሬት በታች ያለው የመሰረት ጥልቀት፣

iv. የወሰንተኛ ነባር ህንፃ ከወሰን ያለው ርቀት ጨምሮ መዘርዘር አለበት፤

ለ) በአመልካች ሊሰራ በታቀደው ግንባታ ምክንያት በወሰንተኛ ነባር ግንባታ ደህንነት ላይ ምንም ዓይነት መናጋት እንዳይፈጠር በቁፋሮና በግንባታ ሂደት መወሰድ የሚኖርበት የጥንቃቄ ግንባታ ንድፍ ለፈቃድ ከሚቀርበው ሰነድ ጋር ቀርቦ ፈቃድ ማገኘት አለበት፤

10. ከወለል ከ1.70 ሜትር በላይ ከፍ ባለ ዝግ ወይም ተካፋች መስኮት በተገጠመለት በኩል ያለ ግንባታ ከወሰን ቢያንስ በ1.50 ሜትር ርቀት መገንባት አለበት፣ ከ1.70 ሜትር በታች መስኮት ያለው የግንባታ ገጽ ከወሰን ቢያንስ 2.00 ሜትር መራቅ አለበት፤

11. በማያሳዩ ውፍረታቸው ከ5 ሳ.ሜ. የማያንስ የመስታወት ግርግዳ መጠቀም ይቻላል፤ ይህም በሚቀርበው ዲዛይን ላይ በግልጽ መጠቀስ ሲኖርበት ወሰን ላይ የተሰራ ከሆነ ወሰንተኛው እንደ ማንኛውም ድፍን የግድግዳ አካል አስጠግቶ ሊሰራበት ስለማይከለከል የብርሃን ማስገቢያ መስፈርት ለሚጠየቅበት ተጨማሪ ወይም አማራጭ የብርሃን ምንጭ ማመልከት አለበት፤

12. በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ተግባር ያለው ማምረቻ ወይም ወርክሾፕ ሞተሩ ከወሰን ቢያንስ 6 ሜትር መራቅ አለበት፤

13. ማንኛውም ተካፋች ከወሰን ሊኖረው የሚገባው ርቀት በመስፈርቱ መሰረት መጠበቅ ያለበት ሲሆን በወሰንና በተካፋች መካከል መኖር የሚገባው ርቀት በአዋሳኞች የጋራ ስምምነት ሊቀየር አይችልም፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፈቃድና ማህደር
የማንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር ባለሥልጣን

14. ከመንገድ መራቅ ካለበት ርቀቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ካልተመራ ክፍት ቦታ ወይም ተመርቶ ካልተሰራበት ወይም መንገድ የሚዋሰን ማንኛውም ግንባታ ለመገንባት አዋሳኝን ማሳወቅ አያስፈልግም፤

15. ማንኛውም ሠው ግንባታውን እስከ ወሠን አስጠግቶ ማከናወን ይችላል ሆኖም ወሠን ላይ ለመገንባት ያቀደ ሰው፤

ሀ) ግንባታው ተጀምሮ እስኪጠናቀቀ ድረስ በአጐራባቹ ላይ አደጋና ችግር በማያስከትል ሁኔታ መከናወን አለበት፣

ለ) በማንኛውም ጊዜ ወሰንተኛው ግንባታውን እንዲከታተል መፍቀድ አለበት፣

ሐ) በማንኛውም የወሰን ላይ ግንባታ ሂደት ለሚፈጠር ችግር ገንቢው እና አማካሪው ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፣

መ) በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገቧቸውን ጥንቃቄዎች ተወስደው ያልታሰበ ችግር ቢፈጠር ገንቢው፣ ባለቤቱና እና አማካሪው አስፈላጊው የእርምት እርምጃ መወሰድ አለባቸው፣

ሠ) አማካሪው በተፈቀደው የወሰን ላይ ግንባታ ዲዛይን መሰረት ግንባታው ስለመከናወኑ ኃላፊነት አለበት፣

ረ) በወሰን ላይ ግንባታ የመሰረት ቁፋሮ ሲከናወን በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ ES-3965 አኩፔሽናል ሄልዝ ኤንድ ሴፍቲ ክፍል ክፍል 6 መሰረት መከናወን አለበት፤

16. የሕዝብ መፀዳጃ ግንባታ ከወሰን 2.5 ሜትር ርቆ መገንባት አለበት፤

17. የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ከጣሪያው ከፍታ አንድ ሜትር ከፍ ማለትና ከወሰን ቢያንስ 1 ሜትር መራቅ ይኖርበታል፤

18. በአዋሳኝ መንገድ የቆሻሻ ፍሳሽ መሥመር ከሌለ ወይም የቦታ ተፈጥሮአዊ ተዳፋት የህንጻ አቀማመጥ የማይፈቅድ ከሆነ ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ ማስወገጃ ጉድጓድ ወይም ሲስፑል ሴፕቲክ ታንክ የውስጥ ጉድጓድ ገጽ ከማንኛውም ወሰን 150 ሳ.ሜ. ርቆ በይዞታ ውስጥ መገንባት ይችላል፤ ሆኖም የታችኛውና የላይኛው ሶሌታ አርማታ እንዲሁም ግድግዳው ውሀ የማያሰርግ ሆኖ የተሰራና የመዋቅር ዲዛይኑ ከቀረበና በሚመለከተው አካል ከተፈቀደ ከወሰን እስከ 50 ሳ.ሜ ተጠግቶ መስራት ይቻላል፤

19. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ማስተንፈሻ ቱቦ መውጫ ከወሰን በአንድ ሜትር ርቀት መተከል አለበት፡፡

17.<u>የፅድሳት ፈቃድ</u>

1. በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገቡና ታሪካዊ እሴት ያላቸው ሕንጻዎች ለማደስ በቅድሚያ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፤
2. ማንኛውም የግንባታ እድሳት ለማግኘት የሚፈለግ ሰው ፈቃድ ለማግኘት ለባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ ለተሰየመው አካል የግንባታ እድሳት ማመልከቻ ቅጽ 005 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፤
3. የግንባታ እድሳት ማመልከቻ ቅጽ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ ፣ በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በድርጅቱ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፤
4. ለመኖሪያ ቤቶች የሚደረግ እድሳት የቁስ ለውጥ ቢኖረውም ባይኖረውም ፕላን ማቅረብ ሳያስፈልግ የእድሳቱ ፈቃድ የሚሰጥ ይሆናል፣ ፈቃዱ ሲሰጥ የግንባታው ሁለንም ገጾች ልኬት እና የተሰራበት ቁስ በፈቃድ ክፍሉ ባለሙያ በመስክ ተወስዶ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ መቀመጥ ይኖርበታል። ሆኖም ግን የእድሳት ስራው በቅርስነት የተመዘገበ ግንባታ ላይ የሚከናወን ከሆነ የእድሳት ስራውን ፕላን እና ከቅርስ መዝጋቢው አካል የድጋፍ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፤
5. ለማንኛውም ቤት ወይም ህንፃ የእድሳት ፈቃድ የባለ አንድ ወለል (G+0) ነባር ህንፃ እድሳት ፈቃድን በተመለከተ የእድሳት ፍቃድ ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት በነበረበት የሚታደስ ከሆነ የቁስ ለውጥ ቢደረግም ባይደረግም ወደ ጎን ሳይሰፋ እና የቆጥ ወለል ሳይጨምር ዝቅተኛውን የክፍል ቁመት በመጠበቅ የሚታደስ ከሆነ በማሳወቅ ብቻ ከታች በተጠቀሱት መስፈርቶች መሰረት መስተናገድ ይቻላል፡-
    ሀ) የማመልከቻ ቅፅ 005 በፅሁፍ መቅረብ አለበት፣
    ለ) ሊታደስ የታሰበው ቤት የመጠንና የቁስ አይነት በቅፅ ላይ በግልፅ መቀመጥ አለበት፣
    ሐ) የአገልግሎት ክፍያ መከፈል አለበት፣
6. በህዝብ መገልገያ ህንጻዎች ላይ የሚከናወን እና መዋቅራዊ አምዶችን የሚነካ እድሳት ስራ ለማከናወን የእድሳት ስራውን ፕላን በማቅረብ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን

የእድሳት ስራው ተገቢው የደህንነት ጥንቃቄ እርምጃዎች በመውሰድ የሚከናወን ይሆናል፤

7. ከ2 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእድሳት ፈቃድ የሚሰጥባቸው የግንባታ ዓይነቶች፤-

    ሀ) መወጣጫ ለሚጠይቁና ሁለት ወለል እና በላይ ለሆኑ ለመኖሪያ እና ለህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የቀለም ቅብ ወይም ሌሎች የማጠናቀቂያ ስራዎች ዕድሳት ስራ፤

    ለ) አዲስ የደጋፊ ግንብ ሥራ፤

8. ከግንባታ እድሳት መጠየቂያ ቅጽ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሠነዶች፡-

    ሀ) ከዋናው ጋር የተመሳከረ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣ ይዞታው በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም ቤቶች ኮርፖሬሽን የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል ቅጂ እንዲሁም የመንግስት ቤቶችን በተመለከተ የፌደራል ቤቶች ከከተማው አስተዳደር ጋር በሚገቡት ውል መሰረት ይፈጸማል፤

    ለ) ለዕድሳት ስራዎች የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

        i. የሚታደሰውን የህንጻ አካል ገጽና ቁስ ነባር ሁኔታና የህንጻውን አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍና ፎቶ ዝርዝር መግለጫ፤

        ii. ከእድሳት ጠያቂው አካል ጋር ቁስ ለውጠ ለሰራበት ካሳ ላለመጠየቅ ግዴታ የገባበት ውል፤

        iii. በአማካሪ ድርጅት ወይም በንኡስ አማካሪ ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ፕላኖች የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት እና እና የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የሚመሳከር፤

        iv. ግድግዳ ወይም ጣሪያ የሚጋሩ ወሰንተኞች ካሉ በሚጋሩት ወሰን በኩል ስለሚካሄደው የእድሳት ስራ የወሰንተኛውን ንብረት ደህንነት ያገናዘበ ጥናት መቅረብ ይኖርበታል፤

9. ከዕድሳት ፈቃድ ቅጽ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች ተሟልተው ሲቀርቡ ብቻ ማመልከቻው እንደቀረበ ይቆጠራል፤ ለአመልካች የማመልከቻ መቀበያ ማረጋገጫ እና የግንባታ ዕድሳት ፈቃድ መውሰጃ ቀጠሮ መስጫ ፎርም ወዲያው ይሰጠዋል፤
10. የግንባታ ዕድሳት ፈቃድ ጠያቂው በቅጹ ላይ የሞላው መረጃ ትክክለኛ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ማመልከቻው ወይም ፈቃዱ ተሰርዞ ከፋይሉ ጋር ይያያዛል፤ በዕድሳት ግንባታ ላይ ያለ ከሆነም ግንባታው ወዲያው እንዲቆም እና በፈቃድ ጠያቂው ኪሳራ ተገቢው እርምት እንዲወሰድ ይደረጋል፤ በተሳሳተ መረጃ ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም ችግር ፈቃድ ጠያቂው ኃላፊነት ይወስዳል፤
11. የአጥር ዕድሳት በመሪ ፕላኑ ወይም በውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ላይ የተቀመጠውን የመንገድ ስፋት በመጠበቅ የሚፈቀድ ይሆናል፤ የአጥር ዕድሳት ስራ የመሪ ፕላኑ ላይ የተቀመጠውን የመንገድ ስፋት የማይጠብቅ ከሆነ የመሪ ፕላኑ ወይም የውስጥ ለውስጥ መንገድ እስኪተገበር ድረስ በነበረበት ቁስ ብቻ የሚፈቀድ ይሆናል፤
12. የአጥር ዕድሳት አጥሩ ቀድሞ ከነበረበት ቦታ እንዲቀየር የሚጠይቅ ቢሆንም በዕድሳት ድንጋጌ እና የአገልግሎት ክፍያ መሰረት የሚፈቀድ ይሆናል፤ ሆኖም ከሌሎች ግንባታዎች ጋር የሚቀርብ የአጥር ዕድሳት ጥያቄ በግንባታ ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ መሰረት የሚፈቀድ ይሆናል፤
13. የአጥር ዕድሳት ስራ የአጥር ስታንዳርድ መስፈርትን እንደጠበቀ ሆኖ የአጥሩን ግንባታ ቁስ መቀየርን ሊያካትት ይችላል፤
14. በአንድ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ ከአንድ በላይ የቤት ባለቤቶች ለመኖራቸው በተጠቀሰበት ሁኔታ የሚቀርብ የአጥር ዕድሳት ጥያቄ የሁሉም የቤት ባለቤቶች በዕድሳት ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ላይ በጋራ አመልካችነት ሲያመለክቱ የሚፈቀድ ይሆናል፤ ሆኖም ይዞታውን ውስጥ ለውስጥ በአጥር ለማካፈል የሚቀርብ ጥያቄን አይመለከትም፤
15. ጸድቆ የተሰጠ የዕድሳት ፈቃድ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፤
16. እድሳት የተጠየቀበት ማንኛውም ቤት የመሪ ፕላን ወይም የውስጥ ለውስጥ መንገድ ቢነካውም ወይም የፕላን ተቃርኖ ቢኖረውም ለግምት በሚያመች ሁኔታ በሁሉም አቅጣጫ አስፈላጊ የሆነውን የቤቱን አካል ፎቶ በማንሳት፣ የቤቱን ሙሉ ልኬት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

በንድፍ በመስራት፣ ነባር ቤቱን አጠቃላይ ይዘት በመግለጽ፤ ከእድሳት ጠያቂው አካል ጋር ቁስ ለውጦ ለሰራበት ብቻ ካሳ ላለመጠየቅ ግዴታ የገባበትን ውል በማያያዝ፣ ህንጻ ሹሙ ወይም የተሰየመ አካል ቦታው ድረስ በመሄድና በማረጋገጥ የእድሳት ፈቃድ ይሰጣል፤

17. እድሳት የተጠየቀበት ማንኛውም የግንባታ እድሳት መሰረት እና መዋቅር ካለው መሰረት እና መዋቅሩ ሳይፈርስ፤ መሰረትና መዋቅር ከሌለው ደግሞ ፈርሶ ወይም ሳይፈርስ፤ ግንባታው ያረፈበት ስፋትና ርዝመት ለውጥ ሳይኖረው፤ ቀድሞ የነበረበትን ቦታ ሳይቀይር፤ ከፍተኛውን የወለል ከፍታ ሳያልፍና የቆጥ ወለል ሳይጨምር፤ በተሻለና የአካባቢውን ውበት ወይም ገጽታ በማያበላሽ መልኩ፣ የግንባታ ቁስ ለውጥ ማድረግ፣ የበርና መስኮት መጠን ብቻ በመቀየር የግንባታ ፈቃድ መመሪያ ህግጋትን አሟልቶ መፈቀድ አለበት፤

18. ዕድሳት የተሰጠው ማንኛውም ግንባታ፣ ዕድሳት ካደረገበት ቀን አንስቶ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ከቆየ፣ ቦታው ለልማት ከተፈለገ ዕድሳት ለተደረገበት የካሳ ክፍያ ይከፈላል፤ የዕድሳት ፈቃድ የወሰደ ባለቤት ወይም ተቋም የዕድሳት ስራ ከማከናወኑ በፊት ፈቃድ ለሰጠው አካል የዕድሳት ስራውን ሊጀምር እንደሆነ በአካል ቀርቦ ማሳወቅ አለበት፤

19. ተነጻጻሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያላቸዉ ባለይዞታዎች የእድሳት ፈቃድ ለማግኘት በተናጠል አገልግሎቱን መጠየቅ ይችላሉ፤ ነገር ግን ማስፋፊያና አዲስ ግንባታ ለመገንባት ከፈለጉ የሁሉንም ባለይዞታዎች ይሁንታ ማግኘት አለበት፤

20. ህንጻ ሹሙ ወይም የተሰየመው አካል የቀረበውን የእድሳት ጥያቄን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በማየት ወይም የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ከሌለው መረጃውን ከጂአይኤስ ወይም የ1997 ላይን ማፕ ላይ በማየት በቂ ካልሆነም በአካል በቦታው ተገኝቶ ሊያረጋግጥ ይችላል፤

21. በእድሳት ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ወቅት እድሳት ጠያቂው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ካለው ሰነዱ ላይ ያለው መረጃ ገዢ ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ከሌለው ደግሞ በተዋረድ የጂአይኤስ እና የ1997 ላይን ማፕ ላይ ያሉት መረጃዎች ገዢ ይሆናሉ፤

22. እድሳት የተጠየቀበት ቤት በአርሶ አደር ማህበር ክልል ውስጥ የሆነ እንደሆነ እና በጂአይኤስ ወይም የ1997 ላይን ማፕ ላይ የማይታይ ከሆነ በአዲስ አበባ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤ የልማት ተነሺ አርሶ አደር መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት

ጽህፈት ቤት ወይም ከሚመለከተው አካል ነባር መሆኑ አስመስክሮ የሚሰጠው ፈቃድ ከይዞታ ባለቤትነት ጋር የማይገናኝ መሆኑ ተገልጸ ይፈቀዳል።

18.<u>የግንባታ ማፍረስ ፈቃድ</u>

1. ማንኛውም ግንባታ ለማፍረስ የሚፈልግ ሰው ፈቃድ ለማግኘት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 006 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፤
2. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በድርጅቱ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፤
3. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች ተሟልተው ከግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ጋር መቅረብ አለባቸው፡-
   ሀ) ቦታው በአመልካች ስም የተመዘገበ ለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ፣
   ለ) ከሚፈርሰው ህንፃ ጋር ተያይዘው የነበሩ የመብራትና የውሃ አገልግሎቶች መቋረጣቸውን ወይንም መነሳታቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ፣
   ሐ) ህንጻው ከእዳና እገዳ ውል ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣
   መ) ግድግዳ ወይም ጣሪያ የሚጋሩ ወሰንተኞች ካሉ በሚጋሩት ወሰን በኩል ስለሚካሄደው የማፍረስ ሥራ የወሰንተኛውን ንብረት ደህንነት ያገናዘበ ጥናት፤
   ሠ) በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገቡና ታሪካዊ እሴት ያላቸው ሕንጻዎች ለማፍረስ በቅድሚያ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ስምምነት፤
   ረ) ህንጻው ሁለት ወለልና ከዚያ በላይ ከሆነ የተመዘገቡና የዘመኑን ፈቃድ ያደሰ የስራ ተቋራጭ የግንባታ ማፍረስ ስራ ውል መቅረብ ይኖርበታል፤
4. ከግንባታ ማፍረስ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ጋር ተፈላጊ አባሪ ሰነዶች ተሟልቶ ከቀረበ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ይሰጣል፤
5. የማፍረሻ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የማፍረስ ስራውን ካጠናቀቀ በኋላ ለመጨረሻ ቁጥጥር ለጽህፈት ቤቱ ሪፖርት በማድረግ በፈቃዱ መሰረት ግንባታው መፍረሱ በጽህፈት ቤቱ መረጋገጥ አለበት፤
6. ከተጎራባች የሚጋሩት ግድግዳ ወይም ጣሪያ ካለ፣ ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) ተራ ፊደል (መ) በቀረበው ጥናት መሰረት የቀሪ ግንባታውን

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ደህንነት ለመጠበቅ የግባውን ግዴታ የሚዘረዝር የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ ቅጽ 009 ለአጎራባቹ እንዲደርሰው ያደርጋል፤

7. የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ የደረሰው ወሰንተኛ በማፍረስ ሥራ ወቅት ግንቢውን በግዴታ ውስ ላይ ከተጠቀሰው ውጭ በመፈፀሙ ወይም በሌላ ምክንያት የጎባር ህንፃ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር ተፈጽሟል በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ሲኖር ወዲያውኑ የግንባታ ስራውን በማስቆም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ ውሳኔ ይሰጣል፤
8. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ የሚያገለግለው ለሶስት ወራት ብቻ ነው፤ በተጨማሪ የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ እንደ ህንፃው ዓይነት እና ውስብስበነት ጊዜው በከተማው አስተዳደር ወይም በሕንጻ ሹሙ ወይም በተሰየመው አካል ሊራዘም ይችላል፤
9. የግንባታ ማፍረስ ስራ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ "ኢኤስ-3965 አኩፔሽናል ሃልዝ ኤንድ ሴፍቲ" ክፍል 8 መሰረት መከናወን አለበት።

19.<u>ከግንባታ የተወሰደ ማሻሻያ ፈቃድ</u>

1. ከግንባታ የተወሰደ የግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽ 022 ሞልቶ የጥላን ስምምነት፣ ቀደም ሲል የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሠነድ፤ የግንባታ ተቆጣጣሪው ማሻሻያ እንዲያደርግ ያረጋገጠበትን ሰነድ በማያያዝ እና የማሻሻያ ዲዛይን ሠነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት፤
2. ከቦታው ተዳፋትነት ምክንያት ከሚፈጠር ለውጥ፣ ተጨማሪ ወለል መስራት፣ ተጓዳኝ የጥላን ህግጋት የሚያፋልሱ እና የመዋቅራዊ አምድ ዘንግ መጨመር ውጭ ያሉትን አነስተኛ ለውጦች በግንባታ የተወሰደ ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ መልክ ግንባታው እየተካሄደ መፈቀድ ይችላል፤
3. ከግንባታ የተወሰደ የግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የግንባታ ተቆጣጣሪው ባረጋገጠው እና ማሻሻያውን እንዲያደርግ ባስቀመጠለት ጊዜ ገደብ ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ በተገለጸው አግባብ ማሻሻያውን አቅርቦ ማጸደቅ አለበት፤
4. ማንኛውም የመስክ ሪፖርት የሚረጋገጠው በግንባታ ተቆጣጣሪ ባለሙያ እንዲሁም

በግንባታ ተቆጣጣሪ ኃላፊ በማፀደቅ መሆን አለበት፡፡

20.ልዩ ከግንባታ የተወሰደ ፈቃድ

1. ልዩ ከግንባታ የተወሰደ የግንባታ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽ 022 ሞልቶ የፕላን ስምምነት አያይዞ ማቅረብ አለበት፤
2. በከተማው አስተዳደር ተለይተው የሚታወቁ የቀድሞ ህንጻዎች ግንባታ "ልዩ ከግንባታ የተወሰደ ግንባታ ፈቃድ ዲዛይን ወይም ፕላን አቅርበው ማጸደቅ ይችላሉ፤
3. ልዩ ከግንባታ የተወሰደ ግንባታ ፈቃድ የሚጠየቁ ፕላኖች ወይም ዲዛይኖች ከወቅታዊ የፕላን ህግጋት መቃረናቸው ወይም መጣጣማቸው በምስክር ወረቀት ላይ ተገልፆ ይሰጣቸዋል፤
4. ልዩ ከግንባታ የተወሰደ ግንባታ ፈቃድ የሚቀርበው የአርክቴክቸራል ፕላን ወይም ዲዛይን ሆኖ፤ ለመጠቀሚያ ፈቃድ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

21.የምሽት ግንባታ ሥራ ፈቃድ

1. ማንኛውንም ከምሽቱ 1 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው የምሽት ግንባታ ሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 029 በመሙላት ማመልከት ይኖርበታል፤
2. የምሽት መገንቢያ ፈቃድ ሲጠየቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፤
   ሀ) የአካባቢውን ነዋሪ ፀጥታ የማያናጋ መሆኑን ማረጋገጥ፤
   ለ) ለህገወጥ ግንባታ አመቺ ሁኔታ የማይፈጥር እና ተቆጣጣሪ መገኘት ያለበት አይነት የግንባታ ሥራ አለመሆኑን ማረጋገጥ፤
   ሐ) የግንባታ ማስጠንቀቂያ ወይም ማስቆሚያ ትእዛዝ ያልተሰጠበት መሆኑ መረጋገጥ፤
   መ) በቀን ቢከናወን በሰውና ተሽከርካሪ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና ሊፈጥር የሚችል ዓይነት ስራ መሆኑን፤
   ሠ) የወሰን ላይ ግንባታ አለመሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤
3. የሕንጻ ሹም በምሽት ለመገንባት ከሚጠየቁ ሥራዎች ውሰጥ ሊፈቀዱ የሚችሉትን ስራዎችና በተጓዳኝ መወሰድ የሚኖርበትን ጥንቃቄ በመዘርዘር ፈቃድ መስጠት ይችላል፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

4. የምሽት ግንባታ ፈቀድ ያለው ገንቢ ግንባታውን በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማከናወን ይኖርበታል፤ ያለምሽት ግንባታ ፈቀድ የምሽት ግንባታ ማከናወን አይፈቀድም፤
5. የሕንጻ ሹም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምሽት ግንባታ ሥራ እንዲበረታታ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት አለበት፤
6. የግንባታ ተቆጣጣሪ መደበኛ ክትትል የሚደረግበትን ግንባታ በምሽት ተገኝቶ እንዲያረጋግጥ አይገደድም፤
7. የምሽት መገንቢያ ፈቃድ የሚያገለግለው የህዝብ መጠቀሚያ ተቋም ለሶስት ወራት ነው፤ ሆኖም የተፈቀዱትን ስራዎች ባለበት ለመቀጠል በተጨማሪ 30 ቀናት ያለክፍያ ፈቃዱ ተራዝሞ ሊፈቀድ ይችላል፤
8. በማንኛውም የምሽት ግንባታ እንቅስቃሴ ወቅት ለሚፈጠረው አደጋ ባለቤቱ፣ ስራ ተቋራጭ እና አማካሪው ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፤ አደጋ ከተፈጠረ ገንቢው ወዲያውኑ በሚቀጥለው ቀን በአካል በባለስልጣኑ ወይም በጽህፈት ቤቱ በመገኘት ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

22. <u>ማንኛውም የነባር ቤት ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ</u>

1. ከስልታዊ የኢንቨስትመንት ቦታዎች ውጪ ያሉና በአምስት አመትና በላይ በመልሶ ማልማት የተያዙ ቦታዎች ውስጥ ሆነው በሁለት አመት ጊዜ እንደማይፈርሱ በሚመለከተው አካል ከተረጋገጠ፤እራሱን ችሎ በሚለማ ቦታ ላይ ለግል መኖሪያ ቤት ብቻ ከተነፃፃሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ውጪ የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤
2. የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ በመሪ ፕላኑ የመሬት አጠቃቀም መስፈርት መሰረት የሚፈቀድ ቢሆንም በመሪ ፕላኑ የህንጻ ከፍታ መሰረት እንዲቀርብ አይገደድም፤ የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ ከምድር በላይ ጀምሮ ከአንድ ወለል በላይ ሊፈቀድ አይችልም፤
3. የመሪ ፕላኑ የወለል ይዞታ ስፋት ምጥን እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ይዞታ ካለው ነባር ግንባታ የወለል ስፋት ለአንድ ጊዜ ብቻ እስከ 40% ለማስፋፋት የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ መጠየቅ ይቻላል፤ ይህም በየትኛውም ጊዜ በአንድ ይዞታ ላይ ሊኖር የሚችለው የማስፋፊያ ጥያቄዎች ጥቅል ድምር ጣሪያ ሲሆን አጠቃላይ

የወለል ሽፋን ጥምርታ ገደብ እስካላለፈ ድረስ መሆን አለበት፤ የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ የከተማ ፕላን ያስቀመጠውን ከመንገድ መራቅ ያለበትን ርቀት ጠብቆ መፈቀድ አለበት፤

4. የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የማመልከቻ ቅጹን ሞልቶ፣ የፕላን ስምምነት፣ የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ከዚህ ቀደም ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሰነድና የማሻሻያ ዲዛይን ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፤ ከዚህ ቀደም ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሰነድ ከሌለው ደግሞ ከማሻሻያ ዲዛይን ሰነዶች ጋር የነባሩን ቤት ዲዛይን ማቅረብ አለበት፤
5. የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ ዲዛይኑ መቅረብ ያለበት ደረጃውን በሚመጥን እና ለዘመኑ የታደሰ የዲዛይን የሙያ ፈቃድ ያለዉ ባለሙያ ወይም አማካሪ ድርጅት መሆን ይኖርበታል፤
6. በአማካሪ ድርጅት ወይም በንኡስ አማካሪ ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ ፕላኖች የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣ እና ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የባለሙያ የሚመሳከር፤
7. የጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ በሚቀርብበት ነባር ይዞታ ላይ ያለ ነባር ቤት በሙሉ በግልጽ ተለይቶ በዲዛይኑ ላይ መታየት ይኖርበታል፤
8. በይዞታ ውስጥ የግንባታ ፈቃድ ድንብና መመሪያን የማይጠብቁ ተነጣጥለው የተሰሩ ነባር ግንባታዎችን ወይም የማሻሻያው ግንባታ ከነባር ግንባታ ጋር ተያይዞ የሚሰራ ከሆነ፤ ነባር ግንባታዎቹ በነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ ላይ ተመልክተው ነገር ግን ፈቃዱ እንደማያካትታቸው በግልጽ በፈቃዱ ላይ ተጠቅሶ መጻፍ አለበት፤
9. በልዩ ሁኔታ የጥበቃ ቤት የሚያስፈልጋቸው የግል መኖሪያ ቤቶች አነስተኛውን የክፍል ከፍታ ስታንዳርድ ሳይበልጥ እና 2.00 ሜትር በ 2.00 ሜትር የክፍል ስፋት ሳይበልጥ እንዲሁም የከተማ ፕላን ያስቀመጠውን ከመንገድ መራቅ ያለበትን ርቀት ጠብቆ በነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ መልክ ሊፈቀድ ይችላል፤
10. የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው።።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለ/ሥልጣን

23.የአገልግሎት ለውጥ ስለማድረግ

1. የህንፃ ሽሙ ከአዋጁ፣ ከማስፈፀሚያ ደንብ፣ ከህንጻ ኮድ እና ሌሎች አግባብነት ካለቸው ሕጎች ጋር እስከተጣጣመ ድረስ የህንፃ አገልግሎት ለውጥ ማድረግ ይችላል፤
2. ማንኛውም ባለይዞታ በሕንፃው ላይ የአገልግሎት ለውጥ ሲያቅድ ሥራው ከመጀመሩ በፊት የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፤
3. ማንኛውም ባለይዞታ የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ ሲያቅድ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ 007 መሙላት እና የፕላን ስምምነት ሰነድ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤
4. የአገልግሎት ለውጥ ለማከናወን ሲጠየቅ ባለይዞታው ሕንፃው የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ እና ለአገልግሎት ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ለሚሰራው ስራ የሚያስፈልጉትን ፕላኖች እና የስራ ዝርዝር አያይዞ ማቅረብ አለበት፤
5. ማንኛውም የአገልግሎት ለውጥ ሥራ የሚያከናውን ሰው ሥራውን ማከናወን የሚኖርበት የፕሮጀክት ግምቱን መሰረት በማድረግ ደረጃው በሚመጥን የሥራ ተቋራጭ መሆን ይኖርበታል፤
6. ማንኛውም ባለይዞታ በአገልግሎት ለውጥ ስራ ላይ የማፍረስ ሥራ ሲያከናውን በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያስከትልና ማንኛውንም እንቅስቃሴ እንዳያስተጓጉል ቅድመ ጥናት ማድረግ ይኖርበታል፤ ሥራውን ሲያከናውንና ሲያጠናቅቅ ፍርስራሹን በማስወገድና ቦታውን በማስተካከል ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ አለበት::

24.ጊዜያዊ ግንባታ

1. ማንኛውም ጊዜያዊ ግንባታ የሚያካሂድ ሰው ግንባታውን ለማከናወን የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤
2. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ጥያቄ መቅረብ ያለበት የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 020 በመሙላት ይሆናል፤
3. ለጊዜያዊ ግንባታ ለቀረበ ማመልከቻ የሕንፃ ሽሙ ግንባታው በህንፃ አዋጁ፣ ደንቡና በዚህ መመሪያ መሠረት እንዲከናወን ጊዜያዊ ፈቃድ ይሰጣል፤
4. የጊዜያዊ ግንባታ አገልግሎት በጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ ላይ የተጠቀሰው አገልግሎት ይሆናል፤

5. ተጓዳኝ፤ ወቅታዊ እና ኮንትራታዊ ጊዜያዊ ግንባታ በቀላሉ ሊነቃቀል በሚችል ቁስ የሚገነባ እና የአካባቢውን ውበት እና የተጠቃሚውን ደህንነት በጠበቀ መልኩ መሰራት ይኖርበታል፤
6. ለተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ የሚገነባ የአጥሩ ቁመት 2 ሜትር በኤጋ ቆርቆሮ የመሰራት ሆኖ ሰማያዊ በነጭ ቀለም በቁመቱ መቀባት አለበት፣ ሆኖም በቀለም አቀባብ ከሚፈጠር ቅርጽ /ፓተርን/ በስተቀር የማስታወቂያ ጹሁፎችን መቀባት አይቻልም፤
7. ለወቅታዊ ጊዜያዊ ግንባታ የሚተከሉ መጠለያዎች የተለየ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር በመተላለፊያ መንገዶች ላይ መሆን የለበትም፤
8. አውቶቡስ ማቆሚያ፣ የህዝብ ስልክ መከለያ፣ ለአነስተኛ ጥቃቅን ንግድ ዘርፎች እና የከተማ ግብርና የዶሮ እርባታ፣ ከብት እርባታ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ከሚመለከተው አካል ፀድቆ የቀረበ ቦታውን የሚያሳይ የፕላን ፎርማት እና የግንባታ ዲዛይን መቅረብ አለበት፤
9. የጊዜያዊ ግንባታ የመጠቀሚያ ዘመን ሲያበቃ ግንባታውን በጊዜያዊ ግንባታው ባለቤት ወጪ ተነስቶና ቦታው በነበረበት ሁኔታ ተስተካክሎ መለቀቅ አለበት፤
10. ጊዜያዊ ግንባታ ህንጻ ቁመት ከአንድ ወለል ወይም ከመሬት በላይ ያለው አጠቃላይ ከፍታ ከ 5.00 ሜትር መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም ለተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ በግንባታ ባህሪያቸው የተለዩና ውስብስብ ለሆኑ ህንፃዎች ህንፃ ሹሙ ወይም አስተዳደሩ በልዩ ሁኔታ ከ5.00 ሜትር በላይ ሊፈቅድ ይችላል፤
11. ተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ በመኪና ወይም በእግረኛ ክልል ሆኖ በዋና መንገድ በሆነ ይዞታ ላይ ለመገንባት በቅድሚያ ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የስምምነት ደብዳቤ መቅረብ አለበት፤
12. በአርሶ አደር ይዞታ ክልል ውስጥ የሚገኝ የግብርና የዶሮ እርባታ፣ ከብት እርባታ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ከሚመለከተው አካል የይዞታው ባለቤት መሆኑን አስመስክሮ እና የመሬት ግብር ደረሰኝ በማያያዝ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ አገልግሎት ማግኘት ይችላል የግዜ ቆይታውም፡-

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፈቃድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ሥምሪት ባለሥልጣን

ሀ) ለአርሶ አደር በይዞታው ክልል ውስጥ ጊዜያዊ ግንባታ መጀመሪያ ግዜ 6 ወር ይሆናል፤

ለ) በአርሶ አደር በይዞታው ክልል ውስጥ የሚገኝ ግብርና የጊዜያዊ ግንባታ የከተማው መዋቅራዊ ፕላን የመሬት አጠቃቀም መሰረት ለአረንጓዴ በተከለሉ በእርሻ ይዞታቸው ላይ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፤

13. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (12) አፈጻጸም ግንባታው ጊዜያዊ በመሆኑ ቋሚ ያልሆነ ወይም በቀላሉ ሊነቃቀሉ በሚችሉ ቁስ ተጠቅሞ መገንባት ይገባዋል፣ግንባታው ሲፈርስም ካሳ አይጠየቅበትም ወይም አይከፈልበትም፡፡ በዚህም መሠረት፡-

ሀ) ከ1,000 ካሬ በታች ላሉ ይዞታዎች የይዞታው ስፋት 80 በመቶ ያልበለጠ፣

ለ) ከ1,001 እስከ 2,000 ካሬ ሜትር ላሉ ይዞታዎች የይዞታው 70 በመቶ ያልበለጠ፣

ሐ) ከ2,001 እስከ 3,000 ካሬ ሜትር ላሉ ይዞታዎች የይዞታው 50 በመቶ ያልበለጠ፣

መ) ለ3,001 እስከ 4,000 ካሬ ሜትር ላሉ ይዞታዎች የይዞታው 25 በመቶ ያልበለጠ፣

ሠ) ከ4,001 እስከ 5000 ካሬ ሜትር ላሉ ይዞታዎች የይዞታው 20 በመቶ ያልበለጠ፣

ረ) ከ5001 ካሬ ሜትር በላይ ላሉ ይዞታዎች የይዞታው 20 በመቶ ያልበለጠ ነገር ግን አጠቃላይ ግንባታው ከ2000 ካሬ ሜትር በላይ መብለጥ የለበትም፤

14. ቦታው ለሌላ ልማት መንግስት ከፈለገው ግንባታዉ ጊዜያዊ በመሆኑ ካሳ አይጠየቅበትም፤

15. አርሶ አደሩ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ከሚመለከተው አካል የይዞታው ባለቤት መሆኑን አስመስክሮ እና የመሬት ግብር ደረሰኝ በማያያዝ በተጨማሪም የከተማ ግብርና ጊዜያዊ ፈቃድ የተጠየቀበት ቦታ ካሳ ያልተከፈለበት እና መሬት ባንክ ያልገባ መሆኑን ከመሬት አስተዳደር ቢሮ ማረጋገጫ በማቅረብ የጊዜያዊ

ግንባታ ፈቃድ አገልግሎት ማግኘት ይችላል፤

16. ለአጥር ጊዜያዊ ግንባታ ዙሪያውን 2 ሜትር ቁመት አጥር በእንጨትና በቆርቆሮ ቁስ መገንባት ይችላል።

25. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ አቀራረብ እና የጊዜ ገደብ

1. ለኮንትራታዊ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ 020 ጋር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፣ የጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ እና የጊዜያዊውን ግንባታ አርክቴክቸራልና እንደአስፈላጊነቱ የስትራክቸራል እና ኤሌክትሪካል ንድፍ ተያይዞ መቅረብ አለበት፣ የግንባታው የጊዜ ገደብ በጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተጠቀሰው ዘመን ይሆናል፤
2. ለተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፣ የዋናው ግንባታ ፈቃድ ኮፒ እና የጊዜያዊ ግንባታውን የቦታ አቀማመጥ እንዲሁም ወደ ግቢ መውጫ መግቢያውን የሚያሳይ ንድፍ መቅረብ አለበት፣ የግንባታው የጊዜ ገደብ የግንባታው መጠናቀቅ ወይንም የግንባታ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ይሆናል፤
3. ለወቅታዊ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ጋር ጊዜያዊ ግንባታው የተፈለገበትን ምክንያት በመግለጽ መቅረብ ይኖርበታል፤ የዚህ ግንባታ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ በከተማው አስተዳደር የሚወሰን ሆኖ የጊዜ ገደቡ ከ7 ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

26. የህንጻ ሹም

1. በከተማው አስተዳደር ከንቲባ ወይም በተወከለው ወይም ለከተማው ተጠሪ በሆነለት የክፍለ ከተማና ወረዳ አስተዳዳር አካል የሚሾም ሕንፃ ሹም፣ በአርክቴክቸር፣ በሲቪል ምህንድስና፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ ሙያ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሆኖ በዲዛይን ዝግጅትና ምርመራ ወይም በግንባታ ሥራ ክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች አግባብነት ያለው ልምድ ሊኖረው ይገባል፤
2. የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ወይም የተወከለው ወይም ከተማው ተጠሪ በሆነለት የክፍለ ከተማና ወረዳ አስተዳዳሪ አካል የሚሾም የህንፃ ሹም ለመሾም ከትምህርትና ከሙያ ዝግጅት መሥፈርት ምዝናው በተጨማሪ፡-

   ሀ) በሥራ ዘመኑ የነበረው የሥራ አፈፃፀም፣



ለ) መልካም ሥነምግባር ያለው እና ለተለያዩ ሱሶች ተገዥ ያልሆነ፣

ሐ) የማቀድ፣ የማደራጀት፣ የማስተባበር እና የመምራት ችሎታ ያለው፣

መ) ተግባቢና ቀና አመለካከት ያለው፣

ሠ) በቡድን የመስራት እና የባለቤትነት ስሜት ያለው፣

ረ) ደንበኛ ተኮር የሆነና የግንኙነት ችሎታ ያለው፣

ሰ) የማወቅ ፍላጎት ያለውና ችግር ፈቺ የሆነ፣

ሸ) በሙያው ትጉህና ሰርቶ የማሰራት ችሎታ ያለው መሆን ይኖርበታል፤

3. የህንፃ ሹም በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገነቡ፣ ከከተማ ክልል ውጭ ሆነው ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው እና እንዲቆጣጠራቸው የተወከለባቸው ሕንፃዎች ላይ በሕንፃ አዋጁ በማስፈፀሚያ ደንቡና በዚህ መመሪያና በሌሎች ሕጐች መሠረት እየተገነቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋል፤
4. የሕንፃ ሹሙ በህንጻ አዋጁ በህንጻ ደንብ እና በዚህ መመሪያ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ሆነው የተገኙ ግንባታዎች እንዲቆሙ፣ እንዲስተካከሉ ወይም እንዲፈርሱ ማዘዝ ይችላል፤
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕንፃ ሹሙ አስተዳደራዊ መቀጮ በመጣል እና ማስተካከያ መደረጉን በማረጋገጥ የግንባታ ማስቀጠያ ውሣኔ ይሰጣል፤
6. የህንፃ ሹሙ ተጠሪነት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ነው፤
7. የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሕንፃ አዋጁ፣ በማስፈፀሚያ ደንቡና በዚህ መመሪያ የተሰጡትን መብትና ግዴታዎች ያላከበረን የህንፃ ሹም አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከሥራ ያግዳል፣ ያሰናብታል፣ እንደየጥፋቱ ደረጃ በህግ ተጠያቂ ያደርጋል፤
8. የሕንፃ ሹሙ ቁጥጥር በሚያደርግባቸው የአስተዳደሩ አካባቢዎች አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው የተደረጉ ሕንፃዎችን በመመልከት እንዲመረመሩና አስጊ ሆነው ከተገኙ በአፋጣኝ እንዲስተካከሉ ወይም ተገቢው የሙያ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ እንዲፈርሱ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል።

27.<u>አገልግሎት መግዛት</u>

1. የሕንፃ ሹሙ በአስተዳደሩ ውስጥ አንድን የተወሰነ ሥራ ለመሥራት የሚችል ባለሙያ የማያገኝ ሲሆን ወይም ሥራውን በሶስተኛ ወገን እንዲሰራ በሚመለከተው አካል ሲወሰን ይህንን ሥራ ሊሰራ ከሚችል አካል ጋር አግባብ ባለው የከተማ አስተዳሩ ሕግ መሠረት በመዋዋል ሊያሰራ ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተዋውሎ የሚሠራ ባለሙያ ሥራውን በአዋጁ በደንቡ እና መመሪያ እና በውሉ መሠረት የማከናወን ኃላፊነት አለበት፤
3. የሕንፃ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተዋውሎ የሚሠራው ባለሙያ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤
4. በሦስተኛ ወገን እንዲከናወን የተደረገን ሥራ የማፅደቅ ኃላፊነት የሕንፃ ሹሙ ይሆናል፡፡

28.<u>የይግባኝ ሰሚ ቦርድ</u>

1. የከተማ አስተዳደሩ በሕንፃ አዋጅ፣ ደንብና በዚህ መመሪያ መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚችል ሙያዊ ብቃት ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፤
2. ለተቋቋመው ቦርድ የከተማው ከንቲባ ሰብሳቢ ይሰይማል፤
3. የቦርዱ አባላት፡-
   ሀ) ቴክኒካል ጉዳዮችን ለማየት ሙያውና የሥራ ልምድ ያላቸው፣
   ለ) በግንባታ ፈቃድና ክትትል አገልግሎት አሠጣጥ ሥራ ላይ ተሳትፎ የሌላቸው፣
   ሐ) በመልካም ሥነ-ምግባር የሚታወቁ፣
   መ) በከባድ ዲሲፒሊን ወይም በወንጀል ጥፋት ተከሰው ያልተቀጡ መሆን ይኖርባቸዋል፤
4. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ ከከተማ አስተዳደሩ ወይም ከተሰየመው አካል እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት የተውጣጡ ቁጥራቸው እንደጉዳዩ ውስብስብነት እና ከተማው ደረጃ የሚወሰን ሆኖ ከ5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል፤
5. የቦርዱ የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል፤
6. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አባላት ስብጥርና የሥራ ድርሻ እንደሚከተለው ይሆናል፡-
   ሀ) አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይም በከንቲባ የሚወከል ... ሰብሳቢ፤
   ለ) የስራና ክህሎት ቢሮ ..... አባል፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር ኤጀንሲ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ሐ) የሥራ ተቋራጮች ማህበር ተወካይ ..... አባል፤

መ) የፕላንና ልማት ቢሮ ..... አባል፤

ሠ) የኮንስትራክሽን አማካሪዎች ማህበር ..... አባል፤

ረ) የዲዛይን እና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ ..... አባል፤

ሰ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ..... አባል፤

ሸ) የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ድምጽ የሌለው ..... ፀሐፊ፤

7. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ የቴክኒክ ጉዳዮችን የሚመረምር የቴክኒክ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤
8. ማንኛውም ሰው በሕንፃ ሽሙ በተሰጠ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታ ካለው የህንፃ ሽሙ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በደረሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ቦርድ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

29.<u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

1. ግንባታዎችን በተመለከተ በሕንፃ ሽም በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፤
2. አቤቱታ በደረሰው በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የሚመለከትበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በመወሰን ለአመልካቹ ከአምስት የሥራ ቀናት በፊት ያሳውቃል
3. ለሚቀርብለት የይግባኝ አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤ ሆኖም የጉዳዩ ባህሪ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ የውሳኔው ጊዜ ለአንድ ተጨማሪ ወር ሊራዘም ይችላል፤
4. በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሌሎች ባለሙያዎችን እገዛ መጠየቅ ይችላል፤
5. ቴክኒክ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤
6. በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ለአመልካቹ እና ለህንጻ ሽሙ በጽሁፍ ያሳውቃል፤
7. ቦርዱ ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ይሆናል፤
8. የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በግንባታ ፈቃድ ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ 027 ይሆናል።

30. **<u>የቦርዱ ሰብሳቢ ተግባራትና ኃላፊነት</u>**

1. ቦርዱን በበላይነት ይመራል፤
2. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ አባላቱ ከመካከላቸው ስብሰባን የሚመራ ሊመርጡ ይችላሉ፤
3. ቦርዱ የሚመራበትን የሥራ መመሪያ ከቦርዱ አባላት ጋር ያዘጋጃል፣
4. አቤቱታዎችን ይቀበላል፤
5. አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም ውሣኔ በድምፅ ብልጫ እንዲከናወን ያደርጋል፤ የቦርዱ አባላት የሚሰጡት ድምፅ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን አሸናፊ ይሆናል፤
6. ቦርዱ የሚሰጠውን ውሣኔ ለአቤቱታ አቅራቢው፣ ለሕንፃ ሹሙ እና ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ባለስልጣን በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፤
7. በፍርድ ቤት ሲጠየቅ የውሳኔው ቅጂ ይሰጣል፤
8. የቦርዱን በጀት በማዘጋጀት ለከተማ አስተዳደሩ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡

31. **<u>የቦርዱ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. የስብሰባ አጀንዳና ቃለ ጉባዔ እየያዘና በአግባቡ እያዘጋጀ አባላቱ እንዲፈርሙበት ያደርጋል፤
2. አስፈላጊ መረጃዎች እና ሰነዶች በስብሰባ ወቅት ተሟልተው እንዲገኙ ያደርጋል፤
3. ቦርዱ የተሟሉ ሰነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፤
4. ከቦርዱ ሰብሳቢ በሚሠጠው መመሪያ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል፤
5. የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፤
6. አቤቱታ የቀረበባቸውን ሰነዶች እና ለምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል፤
7. ውሳኔ የተሰጠባቸውንና ሌሎች ሠነዶችን መዝግቦ በጥንቃቄ ይይዛል፤
8. በሕንፃ አዋጁ፣ በደንቡና በዚህ መመሪያ የተመለከቱት በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ቅሬታ ያለው ሰው ጉዳዩ እንዲታይለት ለቦርዱ በቅጽ 019 መሠረት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡



ክፍል ሶስት

የመሬት አጠቃቀም

32.ስለመሬት አጠቃቀም

1. ማንኛውም ግንባታ የከተማው ኘላን ቢሮ ያስቀመጠውን የመሬት አጠቃቀምና የህንጻ ከፍታ፣ የአየር መመላለሻ ገደብ እንዲሁም ተጓዳኝ ህግጋትን ማሟላት ይኖርበታል፤
2. በአንድ የመኖሪያ ይዞታ ተነጣጥለው በተሰሩ ሁለት ብሎኮች ወይንም በከፊል በተያያዙ ሁለት ብሎኮች መካከል በትይዩ በተሠሩ ሁለት የግድግዳ ገጾች፡-
   ሀ) አንዱ የግድግዳ ገጽ ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በታች ተካፋች ካለው ቢያንስ 2.50 ሜትር፣
   ለ) አንዱ የግድግዳ ገጽ መስኮት ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በላይ ተካፋች ካለው 1.5 ሜትር መራቅ ይኖርበታል፣
   ሐ) በሁለቱም የግድግዳ ገጾች ተካፋዮች ምንም ተካፋች ከሌለ አጣብቀው መስራት ይችላሉ፤
3. ከወለል ከ1.7 ሜትር በላይ ከፍ ባለ ዝግ ወይም ተካፋች መስኮት በተገጠመለት በኩል ያለ ግንባታ ከወሰን 1.5 ሜትር ርቀት መገንባት አለበት፤ ከዚህ ውጪ የትኛውም ዓይነት ግንባታ መስኮት ያለው የግንባታ ገፅ ከወሰን ቢያንስ 2 ሜትር መራቅ አለበት፡፡

33.ስለዲዛይኖች

1. ማንኛውም የህንፃ ዲዛይን የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን መሰረት በማድረግ ደህንነቱ የተረጋገጠ ሆኖ መሰራት አለነት፤
2. ማንኛውም ህንፃ ለሚገኝበት ምድብ የሚያስፈልጉ ፕላኖች በአንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤
3. ማንኛውም ፕላን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የዲዛይን ንድፍ የወረቀት መጠን መሠረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤
   ሀ) A0 - 841 x1189 ሚ.ሜ፣ A1 - 841 x 594 ሚ.ሜ፣ A2 - 420 x 594 ሚ.ሜ፣
   ለ) A3 - 297x 420 ሚ.ሜ፡፡

34. አርክቴክቸራል ዲዛይን

1. ንድፎች በአርክቴክቸራል ዲዛይን ተካተው እና አንዳስፈላጊነቱ ከሪፖርት ጋር ተያይዘው የቦታ አቀማመጥ ኘላን በሳይት ፕላኑ የሚከተሉት መቅረብ ይኖርባቸዋል፡-
   ሀ) ሊሠራ ወይም ሊሻሻል የታቀደውን ሕንፃ አቀማመጥ፣
   ለ) ሕንጻው ከወሰን ከመንገድና ከሌሎች ነባር ግንባታዎች ያለውን ርቀት፣
   ሐ) የመዳረሻ መንገዱ ስያሜና ወደ ህንፃው መግቢያ አመልካች ምልክት፣
   መ) በይዞታው ላይ የነባር ግንባታ ካለ የነባር ግንባታው አቀማመጥ፣
   ሠ) የተፈጥሮ መሬት ተዳፋት ኘላን እና የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ቦታ ወይም ከዋናው ፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ጋር የሚያገናኝ ከሆነ የማስወገጃ መስመር፣
   ረ) የጣሪያ የተፋሰስ አቅጣጫ እና የተዳፋት መጠን እንዲሁም በልኬት የተጠቀሰ የመኪና ማቆሚያ፣ የሰሜን አቅጣጫ አመልካች ምልክት፣
   ሰ) አረንጓዴ ቦታዎችን አግባብነት ባላቸው የከተማ ፕላን እና ማስፈጸሚያ የህግ ማዕቀፎች በሚያስቀምጡት መስፈርት መሰረት፤
   ሸ) ወደ አጥር ግቢ የሚያስገባ በር የሚያሳይ፣
   ቀ) ለህዝብ መጠቀሚያ ተቋም የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ ማስቀመጫ በሚል መካተት ይኖርባቸዋል፡
2. የወለል ኘላን በተመለከተ የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡-
   ሀ) የህንጻው ሁሉም ወለሎች የወለል ኘላን መዘጋጀት አለበት፤ ፍፁም ተመሳሳይ ወለል ያላቸው በሚል ተጠቅልሎ ሊቀርብ ይችላል፣
   ለ) የቆጥ ወለል ካለ ለብቻው መታየት አለበት፣
   ሐ) ከተፈጥሮ መሬት ያለዉ ከፍታ መገለፅ አለበት፤
   መ) አምዶችን የሚያመላክት ስም መቀመጥ አለበት፤
   ሠ) ወለሉ ላይ የተቀመጡ ክፍሎች ስም፣ የክፍል ስፋት እና የወለል ቁስ መቀመጥ አለበት፤
   ረ) ከእያንዳንዱ ክፍል በተጨማሪ በወለሉ ዙሪያ ልኬቶች መቀመጥ አለባቸዉ፤
   ሰ) ፕላኖቹ ተነባቢ ሆነዉ መቀመጥ አለባቸዉ፤
3. የተቆረጠ የቁምኘላን የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-
   ሀ) ቢያንስ የጣሪያ ውቅር፣ የምድር በታች ወለል፣ ሁለትና ከዚያ በላይ ያሉ ወለሎችን የሚያገናኝ ክፍተት እና የመወጣጫ ደረጃ የሚያሳይ መሆን

አለበት፣

ለ) ከመሬት በታች፣ ከመሬት ላይ እና ከመሬት በላይ ያለውን ዝርዝር አሰራሩን የሚገልጽ የወለል፣ የግርግዳ፣ የተካፋች እና የጣሪያ ቁስ መቀመጥ አለበት፣

ሐ) ከመሬት በታች፣ ከመሬት ላይ እና ከመሬት በላይ ያለውን የክፍል ስያሜ እና የውስጥ ለውስጥ ልኬት መቀመጥ አለበት፤

4. የውጭ ገፅታ ንላን የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የሁሉንም የህንፃ ገፅታዎች የሚያሳይ መሆን አለበት፣

ለ) ሙሉ በሙሉ የማይታይና በሌላ ሕንፃ የተሸፈነ የውጭ ገፅታ በተቆረጠ የቁም ገጽታ ንላን መታየት አለበት፣

ሐ) በሁሉም የሕንፃ ገፆች ላይ የሚገነባበት የግንባታ እቃ መፃፍ አለበት፣

መ) መስኮቶች ከተፈጥሮ ወለል ያላቸዉ ከፍታ እና መስኮቱ ካለበት ወለል ያለዉ ከፍታ መገለፅ አለበት፣

ሠ) በዉጪ ገጽታ በኩል የሚቀመጡ መስታዎቶች ወይም ከመስታወት የተሰሩ የዉጪ ግድግዳዎች አንጸባራቂ አለመሆናቸው መገለጽ አለበት፣

ረ) ግልፅ ባልሆኑ እና ተጨማሪ የጎላ ንድፍ በሚጠይቁ የዲዛይን አካላት ላይ ዝርዝር ፕላን መዘጋጀት አለበት፣

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) ለተገለጹት የወለል ከፍታቸው ከተፈጥሮ ምድር በላይ ወይም በታች መመልከት አለበት፣

ሰ) ዲዛይን አጽዳቂው የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል፣

ረ) የውጭ ግድግዳ ቀለም ሊቀባባቸው የሚችላቸው የግድግዳ አካላቶች ተለይው በቀለም ኮድ መሰረት የውጭ ገፅታ በዝርዝር ሀተታ በፅሁፍ መገለፅ አለበት።

35.<u>የህንጻ ቀለም ዲዛይን ስታንዳርድ</u>

የህንጻ የውጭ ገፅታ ቀለም ኮድና ስታንዳርድን በተመለከተ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የወጣውን የህንጻ የውጭ ገፅታ ቀለም ኮድና ስታንዳርድ አጠቃቀም ተፈፃሚ ይሆናል።

መጠን፣ርዝመት፣ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፤

10. የህንጻ ከመሰረት በታችና በላይ ባሉ የስትራክቸራል ዲዛይኖች ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት የሚመለከታቸው ክፍሎች እንደየአስፈላጊነታቸው በአግባቡ ተጠቅመው ዲዛይኑን መከናወኑን እና በዲዛይን ሪፖርት ውስጥም በዝርዝር መካተታቸውን መታየት ይኖርባቸዋል፤
11. የህንጻ ስትራክቸራል ዲዛይን ዲዛይን በሚደረግበት ወቅት ህንጻው የሚገነባበት አካባቢ እንደአስፈላጊነቱ ተሻሽሎ ስራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት የመሬት መንቀጥቀጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም ክንውኑ በዝርዝር መታየት ይኖርበታል፤
12. የህንጻ ስትራክቸራል ዲዛይን ከመሰረት ስራው ጀምሮ እስከ ጣሪያው ስራ በስራ ላይ በዋሉ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት መከናወን ይኖርባቸዋል፤ ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል፡፡

37. <u>ፍዘታዊ ስሌት</u>

ለአንድ ኘሮጀክት ዲዛይን ምርመራ የሚቀርብ ስታቲካል ስሌት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

1. የግንባታውን ዲዛይን አጠቃላይ መነሻና ታሳቢዎችን የሚዘረዝር መግቢያ ያለው፤
2. ለዲዛይን የተጠቀመበትን የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ የሚጠቅስ፤
3. የሁሉም የግንባታ አካላት ስታቲካል ስሌት የሚያሳይ፤
4. ዲዛይኑ የተዘጋጀበት ፕሮግራም የሚጠቅስ መሆን ይኖርበታል፡፡

38. <u>ስለአፈር ምርመራ</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት በአፈር ምርመራ ጥናት ተካትተው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የመሠረት አፈር ምርመራ መከናወን ያለበት ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተመዝግቦ ፈቃድ በተሰጠው ኩባንያ ወይም ድርጅት መሆን አለበት፤
2. የአንድ ኘሮጀክት የግንባታ ቦታ የአፈር ጥናት ተካሂዶ የሚቀርብ የላቦራቶሪ ውጤት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣

ሀ) ለምርመራ የሚጠቀምበትን የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ ማጣቀሻ፣

ለ) የአፈር ምርመራና የመሸከም ውጤት መግለጫ፣

ሐ) የመሠረት ዲዛይን ዓይነት አማራጭ ጥቆማ፣

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር ኮሚሽነር ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

36.ስትራክቸራክል ዲዛይን

ከዘ.ህ በታች የተመለከቱት በስትራክቸራል ዲዛይን ተካትተው መቅረብ አለባቸው፡-

1. የሶሌታ ዲዛይን ንድፍ፣ ሶሌታውንና ሶሌታው የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ በፕላን እና በሁለቱም የቁም አቅጣጫ የሚያሳይ ንድፍ እና የብረት መጠን፣ ርዝመት፣ ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የሚገልጽ መሆን አለበት፤
2. የወጋግራ ዲዛይን ንድፍ ወጋግራው የሚኖረውን የብረት አቀማመጥና በሁለቱም የቁም እና አግድም አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍና የብረት መጠን መግለጫ ሰንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፤
3. የኮለም ዲዛይን ንድፍ፣ የኮለም አግድሚዊ ቁርጥ እይታ እና ኮለሙ የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እና የሚኖረውን የብረት መጠን፣ርዝመት፣ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የሚገልፅ መሆን አለበት፤
4. የመሠረት ዲዛይን ንድፍ፣ለየመሠረቱ ዓይነት የፕላን፤የቁም ገጽታ እና መሠረቱ የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እንዲሁም የሚኖረውን የብረት መጠን ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፤
5. ክብደት ተሸካሚ ግድግዳ የአርማታ ግድግዳ እንዲኖረው በሚገደድበት የህንፃ አካል በአግድማዊ እይታ እና ግድግዳው የሚኖረው የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እና የሚኖረውን የብረት መጠን፣ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሰንጠረዥ የሚገለፅ መሆን አለበት፤
6. ደጋፊ ግንብ ፣ደጋፊ ግንብ እንዲኖረው በሚገደድበት የሕንፃ አካል የአግድምና የቁም ገፅታ እና ግንቡ የሚኖረውን አቀማመጥ ስፋትና መጠን የሚያሳይ ንድፍ እና የአርማታ ግድግዳ ከሆነ የሚኖረውን የብረት መጠን ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የሚገልፅ መሆን አለበት፤
7. የተገጣጣሚ አካላት ንድፍ፣ በተገጣጣሚ የሕንፃ አካላት ለሚሠራ ህንፃ የሁሉም የህንፃ አካላት ፕላንና የመገናኛ ዝርዝር ፕላን መዘጋጀት አለበት፤
8. የጣሪያ ከንች ውቅር፣የከንች ፕላን የቁም ገፅታና ከተሸካሚ መዋቅሮች ጋር ያለውን ትስስር የሚያሳይ ንድፍ የያዘ መሆን አለበት፤
9. ሌሎች መዋቅራዊ ይዘት ያላቸው የግንባታ ክፍሎች ለምሳሌ ደረጃ፣ፍሳሽ ማጠራቀሚያ፣ውሃ ማጠራቀሚያና መስቀያ ወዘተ አቀማመጥ ስፋትና መጠን የሚያሳይ ንድፍ እና የአርማታ ግንባታ ከሆነ የሚኖረውን የብረት

የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Justice Bureau

መ) ሌሎች የተለዩ ከምድር በታች ያሉ የህንፃ አካላት ዲዛይን አሠራር ጥቆማ የያዘ፣

ሠ) ግንባታው የሚያርፍበት ቦታ የአፈር መደርመስ አደጋ የሚገጥመው ከሆነ ለአፈር መደርመስ መከላከያ አማራጭ ዘዴዎችን ጥቆማ፣

ረ) ከሪፖርት ጋር የብቃት ማረጋገጫ እና የታደሰ የንግድ ፈቃድ ቅጂ ከዋናው ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤ ተያይዞ መቅረብ አለበት፣

ሰ) የአፈር ምርመራውን ውጤት መሰረት አድርጎ ሰነድ የሚያዘጋጅ አማካሪ ወይም ባለሙያ አጠቃላይ ለሚፈጠረው ችግርና ለውጥ ኃላፊነት ይወስዳል።

39.<u>ስለህንጻ ሳኒተሪ ዲዛይን</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት በሳኒታሪ ዲዛይን ጥናት መካተት አለባቸው፡-

1. የሁሉም ወለሎች የንፁህ ውኃ አቅርቦት ፕላን፤
2. የሁሉም ወለሎች የፍሳሽ ማስወገጃ ፕላን፤
3. የጣሪያ ፍሳሽ እና የዝናብ ውኃ ማስወገጃ ፕላን፤
4. የሳይት ሳኒተሪ ዲዛይን ፕላን የውጭ ንፁህ ውሀ አቅርቦት፣ ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ማጣሪያ የዝናብ ውሀ ማስወገጃ ያጠቃልላል፤
5. ለህዝብ መገልገያ ለሆኑ ህንፃዎች ወይም በምድብ "ሐ" ስር የተካተቱ ህንጻዎች የሁሉም ወለሎች የእሳት መከላከያ ፕላን፤
6. በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱትን ሥራዎች የሚያካትት የሳኒተሪ ዲዛይን ሪፖርትና ማጣቀሻ ኮድ መገለጽ አለበት፤
7. የህንጻ ሳኒተሪ ዲዛይን ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት ዲዛይኑ መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም በዝርዝር መታየት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል።

40.<u>ኤሌክትሪካል ዲዛይን</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱት በኤሌክትሪካል ዲዛይን ጥናት ተካተው መዘጋጀት አለባቸው፡-

1. የወለል ፕላኖች የኤሌክትሪክ ዲዛይን ንድፍ፣ የኤሌክትሪክ ገመድ የሚሳብባቸው ቱቦዎች፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ገመድ የሚዘረጋባቸው ምሶሶዎችና መብራቶች፣ የኤሌክትሪክ መስመር ጭነት ማጠቃለያና የሳይት ፕላን ጭነት

መካተት አለበት፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘጋጁትን ስራዎች የሚያካትት የኤሌክትሪካል ዲዛይን ሪፖርትና ማጣቀሻ በኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ መሰረት መገለጽ አለበት፤
3. የህንጻ ኤሌክትሪካል ዲዛይን ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት ዲዛይኑ መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም በዝርዝር መታየት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል፡፡

41.<u>ስለመካኒካል ዲዛይን</u>

1. በመካኒካል ዲዛይን ጥናት ውስጥ የቦይለር የውሃ ማሞቂያ፣የአየር ማስተካከያ)፣ የአሳንሰር መግለጫ እንዲሁም ግፊት ዲዛይን፣ ሪፖርትና መግለጫ መቅረብ አለበት፤
2. የህንጻ መካኒካል ቬንትሌሽን እና ኤር ኮንዲሽኒንግ ዲዛይን አግባብነት ባለው እና በተሻሻለው የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት መሰራት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል፡፡

42.<u>የእሳት መከላከያ ስርዓት ንድፍ እና የማምለጫ ስርዓት</u>

ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ በሚቀርበው የህንጻ ዲዛይን ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ ፕላን ከዚህ በታች በተመለከቱት መስፈርት መሰረት አካትቶ ማቅረብ አለበት፡-

1. የማምለጫ በሮች እና በሁሉም የመውጫ በሮች ላይ የተሰየመው ስያሜ፤
2. የሁሉም ማምለጫ በሮች ግለሰብን የመያዝ አቅም፤
3. የማምለጫ መንገዶች በተለያየ የመስመር አይነት ወይም ቀለም ማመላከት፤
4. የማምለጫ መንገዶች ላይ የተመላከተ የጉዞ ርቀት እና ከፍተኛውን የጉዞ ርቀት ከመጨረሻው የክፍል ጥግ እስከ ማምለጫ በሮች ድረስ ያለውን ማመላከት፤
5. የአደጋ ጊዜ መወጣጫ ደረጃ፣ በሮችና መተላለፊያዎች መጠንና ቀጥተኛነት ደረጃውን የጠበቀ እና ከመሰናክል ነፃ መሆን፤
6. ግንባታው እሳትን መቋቋም ያለበት ሰዓት፤
7. ጠቋሚ ምልክቶች የሚተከሉበት ቦታና አይነታቸው ማለትም በቀን፣ በማታና መብራት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ City Bureau

በሌለበት ጊዜ ሊታይ የሚችለበት ሁኔታ በተገናዘበ መልኩ፤

8. በየወለሉ የሚቀመጥ ውሃ መርጫ ጥቅል ከውኃ መርጫው ጋር የተገናኘ ውኃ ማጠራቀሚያ እና መብራት በማይኖርበት ጊዜ ሊኖር ስለሚገባው አማራጭ የኃይል ምንጭ፤
9. የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ደወል፤
10. የአደጋ ጊዜ መቆያ ክፍል፤
11. በግድግዳ ላይ የሚንጠለጠሉ ተንቀሳቃሽ እሳት ማጥፊያዎች አቀማመጥና ከግንባታው አገልግሎት አንፃር ሊነሳ ከሚችለው እሳት ዓይነት ጋር ያለው አግባብነት፤
12. መብረቅ መከላከያ፤
13. የመገልገያ ቁሳቁሶች አቀማመጥና የተሰሩበት ቁስ ደረጃ በአደጋ ጊዜ ሊደረስ የሚችለውን አደጋ የሚያባብስ አለመሆኑን ማረጋገጫ፤
14. ለምግብ ማብሰያ ክፍል፣ ቦይለር ክፍልና ወርክሾኘ ከዋናው ግንባታ በተለየ የሚደረግ ጥንቃቄ፤
15. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እስከ (14) ከተገለፁት በተጨማሪ ለማምረቻና ማከማቻ ተቋማት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-
    ሀ) የመውጫ በሮች ቁጥር የሠራተኛ ብዛት እና የአጠቃላይ ግንባታው ወለል ስፋት መጠን፣
    ለ) እንደማምረቻ ወይም ማከማቻው ባህርይ ጪስ ጠቋሚ፣ ነበልባል ጠቋሚ፣ ሙቀት ጠቋሚ፣ መሣሪያዎች መታየት፣
    ሐ) እንደማምረቻ ወይም ማከማቻው ባህርይ በራሱ ጊዜ የሚሰራ የውሀ መርጫ እና የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ደወል ሊኖረው ይገባል፤
16. በዚህ አንቀፅ ንዑስ ከአንቀፅ (1) እስከ (15) ከተገጹት በተጨማሪ የፈሳሽ ነዳጅና ቡታጋዝ ማከማቻ ተቋም የሚከለተውን ማሟላት አለበት፡-
    ሀ) ፊክሲድ ፎም ኢንስታሌሽን ያላቸው፣
    ለ) ከሌሎች ተቋማት በተናጠል የተገነባ፣
    ሐ) እሳትን ለመከላከል በራሱ ጊዜ የሚሰራ የውሀ መርጫ ፣
    መ) የፈሳሽ ነዳጅ ቃጠሎ ማጥፊያ ኬሚካል፣
17. የእሳት አደጋውን ለመከላከል የሚችል በቂ የውኃ ማጠራቀሚያ ጋን ከመጠባበቂያ የኃይል ምንጭ አቅርቦት ጋር፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር

18. የአካባቢ የፍሳሽ መስመር ከግቢው ከሚወጣ የፍሳሽ ነዳጅ መጠበቂያ ማካተት ይኖርበታል፤
19. ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ ዲዛይን እና ግንባታ ሂደቱ የእሳት አደጋ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ሲሆን በዲዛይን ወቅት የእሳት አደጋ ማምለጫና የህንጻው መዋቅራዊ አካላት እሳትን መቋቋም ስለመቻላቸው በተሻሻለው የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት መሰራት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል።

43.<u>አርክቴክቸር ወይም ስነ ህንፃ</u>

1. የህንፃ ዲዛያኖች ከህንፃ አዋጁ፣ ደንቡ፣ መመሪያውና ስታንዳርዱ ጋር የተገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤
2. የማንኛውም ህንፃ ፕላኑ ሲሠራ ተቀባይነት ያላቸውን ስታዳርድ መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፤
3. የዲዛይን ፕሮግራም ሲዘጋጅ የአሰሪውን ፍላጐት የሚሰጠውን አገልግሎት እና ለኘሮጀክቱ የተያዘውን በጀት ወይም አቅም ያገናዘ በመሆን ይኖርበታል፤
4. በዲዛይን ዝግጅት ህንጻው ሊሰጠው የታሰበው አገልግሎትና የቦታ አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊነትንና አዋጪነትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፤
5. ለማንኛውም ህንፃ እንዲገጠም የሚመረጥ አሳንሰር መወሰን ያለበት የተጠቃሚውን ቁጥር ፣የአገልግሎት አይነት እና ምቹነትን መሰረት በማድረግ ይሆናል፤
6. የፕላን አግድም ልኬት የሚነሳው ካልተለሰነው የግድግዳ ጠርዝ ነው፤
7. የወለል ስፋት በግድግዳ የተያዘውንና በተቀባሪ ቁምሳጥን የተያዘውን ቦታ አያካትትም።

44.<u>የዲዛይን ስታንዳርዶች</u>

1. ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ሕንፃ የዲዛይን ስታንዳርዶች ማለትም የክፍል፣ የተካፋች፣ የመተላለፊያ፣ በር፣ መስኮት፣ ባልኮኒ፣ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ አሳንሰር ስታንዳርዶች ከሕንፃ አዋጁ ደንብና ከዚህ መመሪያ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር የተገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤
2. ለማንኛውም ተሸከርካሪ የማቆያ ቦታ እንደ ከተማው እድገት እና መልካምድራዊ አቀማመጥ በከተማ ፕላን ህግጋት መሠረት ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፤ የቤት

ውስጥ የመኪና ማቆሚያ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የመኪና ማቆሚያው ዝቅተኛ የክፍል ቁመት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፤

ሀ) እስከ 10 ለሚደርሱ መኪናዎች 2.10 ሜትር፤

ለ) ከ10 እስከ 30 ለሚደርሱ 2.30 ሜትር፤

ሐ) ከ30 እስከ 70 ለሚደርሱ 2.50 ሜትር፤

መ) ከ70 በላይ 2.60 ሜትር፤

3. የቆጥ ወለል የክፍል ቁመት አጠቃላይ ድምር ከ6 ሜትር ከበለጠ እንደ ሁለት ወለል ይታሰባል፤
4. የክፍል ቁመት ከ6 ሜትር በላይ የሆነ ግንባታ ወለል ብዛት የሚሰላው የክፍሉን አጠቃላይ ቁመት ለ3 በማካፈልና የሚገኘውን ውጤት ወደ ዝቅተኛው ስሌት በማስጠጋት ይሆናል፤
5. የጣሪያ ላይ ክፍሎች ወለል ስፋት የደረጃ መወጣጫ እና የአሳንሰሩን ወለል ስፋት ድምር ሳይበልጥ ሌሎች ለህዝብ አገልግሎት መስጫነት የማይውሉ ክፍሎች ሊኖሩት ይችላል፣ከዚህ ስፋት በላይ ክፍሎች ያሉት የጣሪያ ወለል እንደ አንድ ወለል ይታሰባል፤
6. ማምረቻ ወይም ማከማቻ ወይም የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ ከሆኑ ግንባታዎች ውጭ የዛኒጋባ ጣሪያ ከፍታው ክፈፍ ሳይጨምር ከ2.8 ሜትር በላይ የሆነ ጣሪያ እንደ አንድ ወለል ይታሰባል፡፡

45.<u>የግል መኖሪያ ቤት የዲዛይን ስታንዳርዶች</u>

1. ማንኛውም የመኖሪያ ቤት የክፍል ስፋት ከ6 ካ.ሜትር ማነስ የሌለበት ሲሆን የየትኛውም ግድግዳ ወርድ ከ2 ሜትር ማነስ አይችልም፤ሆኖም የመጸዳጃ፤ልዩ የአገልግሎት አይነት ያላቸውና በሚገጠምላቸው መሳሪያ ባህሪ ስፋታቸው የሚወሰን ክፍሎች ከ6 ካሬ ሜትር ስፋትና ከ2ሜትር ወርድ አንሰው ሊሰሩ ይችላሉ፤
2. ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ህንጻ ከወለል እስከ ኮርኒስ ያለው አነስተኛው የክፍል ቁመት ከ2.50ሜትር በታች መሆን የለበትም፤
3. ስላሽ ኮርኒስ ላላቸው የመኖሪያ ቤት ክፍሎች ሰው ሊጠጋበት በሚችልበት በዝቅተኛው በኩል ያለው የክፍል ቁመት ከ2.0 ሜትር ማነስ የለበትም፤
4. መኝታ ክፍል ለአንድ ሰው 6 ካሬ ሜትር ሲሆን እንደ ሳሎን የሚያገለግል ከሆነ ከ12 ካሬ ሜትርማነስ የለበትም፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

46.<u>የተካፋች ስታንዳርድ</u>

1. ማንኛውም ተካፋች ከይዞታ ወደ ውጭ መከፈት አይችልም፣
2. ወደ ግቢ መግቢያ ቢያንስ ለመኖሪያ 3 ሜትር መጠበቅ ይኖርበታል፣
3. የመፀዳጃና ባልኮኒ የበር ስፋት ከ70 ሳ.ሜ እንዲሁም ቁመት ከ210 ሳ.ሜ ያነሰ መሆን የለበትም።

47.<u>የመታላለፊያ ስታንዳርድ ደረጃ እና ኮሪደር</u>

1. ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኮሪደር እና የውስጥ ደረጃዎች ከ90 ሳ.ሜትር ያነሰ መሆን የለበትም፤
2. በአንድ ተከታታይነት ባለው የመወጣጫ ደረጃ የተለያዩ የመርገጫ ስፋት ወይም የመወጣጫ ከፍታ መጠን መጠቀም አይቻልም፤ሆኖም ወደ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ወይም ወደ ማሽን ክፍል ወይም ለተመሳሳይ አገልግሎት ለዋለ ክፍሎች የሚያደርስ ደረጃ ከሆነ ከተጠቀሰው መጠን የተለየ ሊሆን ይችላል፤
3. ማንኛውም የመኖሪያ ቤት የውስጥ ደረጃዎች ስፋት ከ25 ሳንቲ ሜትር ማነስ እና የደረጃዎች ቁመት ከ18 ሳንቲ ሜትር መብለጥ የለበትም።

48.<u>በር እና መስኮት</u>

1. ብርሃን የሚያስገባ ተካፋች ስፋት ከክፍሉ የወለል ስፋት ቢያንስ 15% መሆን አለበት፤
2. የበር ስፋት የተጣራ 80 ሳ.ሜ እና ቁመት የተጣራ 200 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፤
3. የፊት መስታወት ዓይነት ወይንም ተመሳሳይ ውጤት እንዲኖረው የተደረገ መስታወት ለግንባታ የውጭ አካል አገልግሎት መጠቀም አይቻልም፤
4. ለመኖሪያ አገልግሎት ለሚውል ህንፃ ዋና መግቢያ በር ስፋት ደግሞ ከ120 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፤
5. የኩሽና፣ የሳሎን እና የመኝታ ክፍል የበር ስፋት ከ90 ሳ.ሜ ቁመት ከ2.1 ሜትር ማነስ የለበትም።

49.<u>ባልኮኒ ስታንዳርድ</u>

የባልኮኒ መደገፊያ የፍርግርጉ ስፋት ከ0.11 ሜትር መብለጥ የለበትም፤ መደገፊያ ቁመቱ ከ1.05 ሜትር ማነስ የለበትም።

50.<u>ሳኒተሪ ስታንዳርድ</u>

የመኖሪያ ቤት መፀዳጃ ከመታጠቢያ ጋር መዘጋጀት አለበት።

51.ኤሌክትሪካል ስታንዳርድ

1. መብራቶቹ ህንጻው ሊሰጠው ከታሰበው አገልግሎት አንፃርና የክፍሎቹ አቀማመጥ በቂ የብርሀን አቅርቦት፤
2. ማንኛውም የኤሌክትሪክ እቃ ዲዛይኑን ባዘጋጀው ባለሙያ /በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል፡፡

52.የአጥር ስታንዳርድ

1. የአጥር ከፍታ የሚለካው ከተፈጥሮ የምድር ወለል ጀምሮ ነው፤
2. በሁለት አዋሳኞች መካከል የሚገነባው አጥር ከፍተኛው የግንብ ቁመት 2.5 ሜትር መብለጥ የለበትም፤
3. ከውስጥ ለውስጥ መንገድ የሚዋሰን አጥር ወደ ውስጥ በማያሳይ ቁስ ወይንም ግንብ ከተሰራ ቁመቱ ለመኖሪያ 1.50 ሜትር፣ ለድርጅት 90 ሳ.ሜ. ነው፤ ሆኖም ለመኖሪያ ቢያንስ 75 ፐርሰንት ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ እስከ 2.00 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፤
4. ከውስጥ ለውስጥ ውጭ ለሆነ መንገድ ባለይዞታው ከዋናው መንገድ በኩል በሚዋሰነው ድንበር ላይ የሚገነባው አጥር ከፍታ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት መሆን አለበት፤ ሆኖም በሌሎቹ አዋሳኞች በኩል ያለው በመደበኛ የአጥር ስታንዳርድ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፤
5. ለመኖሪያ 70 ሳ.ሜ. ሆኖ ቢያንስ 75% ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ እስከ 1.50 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፤
6. ለቢሮ እና ለሌሎች የንግድ ተቋማት 70 ሳ.ሜ.፤
7. ለማምረቻ፣ ማከማቻ እና ማህበራዊ ተቋማት 80% ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ በመገንባት እስከ 1.50 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፤
8. ለኢምባሲዎችና ለዲፕሎማቲክ ተቋማት እስከ 2.50 ሜትር በድፍን ቁስ መስራት የሚቻል ሲሆን ተቋሙ በሚያቀርበው የደህንነት መጠበቂያ ዘዴ ምርጫ እስከ 3.00 ሜትር ከፍታ መሸፈን ይቻላል፤
9. ለአጥር የተከለለ ዕጽዋት ቅርንጫፍ ወይም ሌላ አካል ከይዞታ ውጭ ወደ መንገድም ሆነ አዋሳኝ ማለፍ የለበትም፤ ቁመቱም ለአጥር ከተፈቀደው ከፍታ በላይ መሆን አይችልም፡፡



53.ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ዝግጅቶች ስታንዳርድ

1. ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሚሆን መልኩ መገንባት ወይም አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች ሊሟላለት ይገባል፤
2. ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆን ከሕንፃ አዋጁ ደንብና ከዚህ መመሪያ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር የተገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤
3. ከ12 ሜትር ቁመት በላይ ላላቸው ለህዝብ መገልገያ ህንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች አሳንሰር በሕንፃው ውስጥ መገጠም ይኖርበታል። ነገር ግን ከ20 ሜትር ቁመት በታች ላላቸው ለመኖሪያ ህንፃዎች አሳንሰር እንዲኖራቸው አይገደዱም፤
4. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ20 ሜትር በታች ቁመት ያላቸው መኖሪያዎችና አፓርትመንቶች የደረጃዉ ስፋት ከ1.20 ሜትር በላይ ከሆነ ዋናዉን ደረጃ እንደ አደጋ ጊዜ መዉጫ ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ ነገር ግን ደረጃው እና በደረጃው አካባቢ የሚገኘው ግድግዳ ሆነ በር የተሰራበት ቁስ ዓይነት እሳት መቋቋም የሚችል መሆን አለበት።

ክፍል አራት

ግንባታ ስለመጀመርና ክትትል

54.ግንባታ ስለመጀመርና ክትትል

ማንኛውም ገንቢ፡-

1. ግንባታውን ለመጀመር የመጀመሪያ እርከን ማሳወቂያ መውሰድ ይኖርበታል፤ የመጀመሪያ እርከን ማሳወቂያ አገልግሎት ለማግኘት አልሚው የአማካሪ እና የስራ ተቋራጭ ድርጅት የተሟላ ሰነድ እና የመድን ዋስትና አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፤
2. የግንባታ የመጀመሪያ እርከን ማሳወቂያ አገልግሎት ሲሰጥ ባለሙያው ግንባታ የሚከናወንበት ቦታ ለግንባታ ስራ ዝግጁ መሆኑን እና በአጎራባች ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤
3. የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ክፍያ እንደ ደረጃው ወይም የእርከኖች ድምር ባለቤቱ ይከፍላል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ ከ (1) አስከ (3) የተጠቀሱት መሚላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ መስክ በመውጣት፡-
   ሀ) በይዞታው ውስጥ ሊገነባ የታሰበው አንድ ህንጻ ብቻ ከሆነ ግንባታው በሚያርፍበት ቦታ ላይ ምንም አይነት ቋሚ ግንባታ ያለመኖሩ፣
   ለ) በይዞታው ውስጥ ሊገነባ የታሰበው ከአንድ ህንጻ ወይም ብሎክበላይ ከሆነ ግንባታውን ሊጀምር እና ሊያሳርፍ ባቀደውብሎክ ላይ ምንም አይነት ቋሚ ግንባታ ያለመኖሩ፣
   ሐ) በይዞታው የወሰን ላይ ችካል መኖሩን፣
   መ) በየደረጃው ግንባታው በተፈቀደለት መሠረት መከናወኑን፣
   ሠ) በመጀመርያ እርከን ወቅት የተመዘገቡት ገንቢና አማካሪ በሥራ ላይ መሆናቸውን እና ተገቢውን ባለሙያ በመስክ መድበው እያሰሩ መሆኑን ክትትል ይደረግበታል፤
   ረ) ግንባታ ተጀመረ የሚባለዉ በቦታው ላይ ለመስራት ከተፈቀደው ግንባታ ቢያንስ የመሰረት ስራ መስራትና የኮለን ግንባታ ለማከናወን የሚያስችለ የኮለን ብረቶች የማቆም ስራ ሲጠናቀቅ ነው፤
5. ለክትትል ተብሎ የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ግንባታው በሚካሄድበት ቦታ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ በግልጽ ቦታ ላይ መቀመጥ አለበት፤
6. የግንባታ ሥራ ተጀምሮ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ ገደብ ካለፈ የግንባታ ማጠናቀቂያ ማራዘሚያ ፈቃድ አገልግሎት የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር በሚያደርገው አካል የሚራዘም ይሆናል፡፡ የግንባታ ማጠናቀቂያ ማራዘሚያ ጊዜ አገልግሎት ሲሰጥ የግንባታዉን ጥቅል ወጭ ግምት 0.05% ያህል መቀጮ ለአንድ ጊዜ ከፍሎ እስከ አንድ ዓመት ይራዘማል። የሚራዘመው ጊዜ ከአንድ አመት በላይ ከሆነ በከተማ አስተዳደሩ ወይም በተሰየመዉ አካል ተጨማሪ ቅጣት ሊጣል ይችላል፤
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚጣለው ቅጣት የግንባታዉን ጥቅል ወጭ ግምት 2% መብለጥ የለበትም የግንባታ ጥቅል ዋጋዉ የግንባታ ፈቃድ ሲወስድ የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ላይ የተጠቀሰዉ ዋጋ ይሆናል፤
8. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) እና (7) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
ቦ/ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

አስተዳደሩ ወይም የተሰየመው አካል ግንቢው አሳማኝ ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ ቅሬታውን ሊመለከት ይችላል።

55.<u>ትእዛዝ አለማክበር</u>

1. ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ የአዋጁን፣ የደንቡንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ማክበር ይኖርበታል፤
2. በአዋጁና በደንቡ የተቀመጡተን ድንጋጌዎች እና ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት፡-
   ሀ) ፍቃድ የተሰጠበት የግንባታ ፈቃድ ፕላን ማመልከቻ ኮፒ በግንባታ ቦታ አለመገኘት፣
   ለ) የውስጥ አደረጃጀት ወይም የግንባታ ቅድመ ዝግጅት ሳያሟሉ ሥራ መጀመር፣
   ሐ) የተሰጡ የማስተካከያ ትእዛዞችን ካጠናቀቁ በኋላ አለማስታወቅ፣
   መ) የተሰጡ ትእዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን፣
   ሠ) ከግንባታ ክልል ውጪ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሠረት አለማንሳት፣
   ረ) ካለ ተቆጣጣሪ ማሰራት፣
   ሰ) ካለማስታወቂያ ሥራ መጀመር፣
   ሸ) ያለ ፈቃድ እድሳት ማድረግ፣
   ቀ) ያለፈቃድ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን፣
   በ) ያለፈቃድ የማፍረስ ሥራ ማከናወን፣
   ተ) በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አለመውሰድ፣
   ቸ) የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም፤
   ነ) የግንባታ የውጭ ገጽታዎችን በተፈቀደው ስታንዳርድ ቀለም መሰረት ያለመሰራት፤ የመሳሰሉትን ተግባራት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ትእዛዝ እንዳላከበረ ይቆጠራል፤
3. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) የተመለከቱትን የማያከብር ሆኖ ከተገኘ በሕንፃ ሹሙ በሚሰጥ የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ ቅጽ 014 መሰረት ትእዛዝ ግንባታው እንዲቆም፣ ወይም እንዲፈርስ ወይም እንዲስተካከል ደርጋል፤
4. በግንባታ ወቅት ማንኛውንም በህንፃ ሹሙ ወይም በሚወክለው አካል የሚሰጥ

ትእዛዝን አለመቀበልና አለማክበር ግንቢው፣ አማካሪው እና የህንፃው ባለቤት በግልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል።

56.<u>ስለማስታወቂያ</u>

1. ማንኛውንም በምድብ "ለ" እና "ሐ" የሚገኝ ሕንፃ ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የየሥራው እርከን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስታወቂያ የሥራ እርከኑን ከመጀመሩ 5 የሥራ ቀናት አስቀድሞ የግንባታ ሥራ ማሳወቂያ ቅጽ 025 ሞልቶ ለሕንፃ ሹሙ በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፤
2. ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ህንጻዎች ለአዲስ ግንባታ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው የሚገቡ የስራ እርከኖች የሚከተሉት ናቸው፣
   ሀ) ግንባታ ለመጀመር ማንኛውም የቅየሳ ስራ ተጠናቆ ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት፣
   ለ) የመሠረት ቁፋሮ ከተጠናቀቀና የመሰረት ብረቶችና ፎርምወርክ በቦታቸው ከተቀመጡ በኋላ፣
   ሐ) የምድር ወለል ብረቶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃና የሀርድ ኮር ሙሌት ከተከናወነ በኋላ፣
   መ) የወለል ቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶችና ፎርም ወርክ ስራ ከተከናወነ በኋላ፣
   ሠ) የፎቁ ወለል ብረቶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የኤሌክትሪካል መስመር ዝርጋታና የፎርም ወርክ ስራ እንዲሁም የቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶችና ፎርምወርክ ከተከናወነ በኋላ፣
   ረ) የውሃ አቅርቦት፣ የሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ተጠናቆ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ፣
   ሰ) የጣሪያ ስላብ ወይም ሶሌታ ማጠናቀቂያ ወይም የጣሪያ ሽፋን ስራ ከመከናወኑ በፊት፣
   ሸ) እንደ ሥራው ዓይነት እና የአሠራር ዘዴ በሕንፃ ሹሙ የሚጠየቁ ተጨማሪ እርከኖች፤
3. የሕንፃ ሹም ማስታወቂያ ለቀረበበት የሥራ እርከን በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባታው ቦታ በመገኘት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፤
4. ለነባር ግንባታ ማሻሻያ እና ማስፋፊያ ሥራ እንደ ሥራው ዓይነት ወይም እንደሚከናወነው ተግባር ማስታወቂያ የሚቀርብበትን የሥራ እርከን የሕንፃ ሹሙ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ለግንቢው ያሳውቃል፤

5. መደበኛ ክትትል በሚደረግባቸው የግንባታ ደረጃዎች ግንቢው ለሚመለከተው የክትትል ክፍል ሳያሳውቅና ስራን ለመቀጠል ፈቃድ ሳያገኝ ማከናወን የለበትም፤
6. የግንባታ መስፋፋትን እና የህንጻ ከፍታን የማያካትት የዲዛይን ለውጥ ማስታወቂያ የደረሰው የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ክፍል በሰነዱ ላይ የተመለከተው ለውጥ የማይፈቀድ ወይም በቅድሚያ የግንባታ ፈቃድ እንዲወጣ የሚጠይቅ ከሆነ ማስታወቂያ በደረሰው በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለግንባታው ባለቤት ወይም ለአማካሪው ወይም ለተቋራጩ ማሳወቅ አለበት፡፡

57.<u>ስለ ተቆጣጣሪዎች</u>

1. ማንኛውም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል ማንነቱን የሚገለጽ መታወቂያ የያዘ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ወይም ግንባታ በሚከናወንበት በማንኛውም ጊዜ በግንባታው ቅጥር ግቢ ተገኝቶ የቁጥጥር ሥራ ማከናወን ይችላል ያከናወነውን የቁጥጥር ተግባር የሰጠውን ትእዛዝ በግንባታ መከታተያ ቅጽ 013 በመሙላት ለሕንጻ ሹሙ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፤
2. በማንኛውም ወቅት ወደ የትኛውም ይዞታ ለክትትልና ቁጥጥር ተግባር የሚንቀሳቀስ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በእለቱ ወደ ግንባታ ቦታ መግባት ያስፈለገበትን ምክንያት እና በግንባታ ቦታ ተገኝቶ ያከናወነውን የቁጥጥር ስራ ዝርዝር፣ የተገኘውን ውጤትና የሰጠውን ለተቆጣጣሪዎች በተለየ እና በግንባታ ቦታ በሚቀመጥ የቁጥጥር መዝገብ ላይ ሞልቶ በማስፈረምና በመፈረም ቅጂውን ለግንባታው ባለቤት ወይንም በግንባታው ቦታ ለሚገኝ ተጠሪ መስጠት አለበት፣ የቁጥጥር መዝገብ ተከታታይ ዋና እና ቀሪ የገጽ ቁጥር፣ የትዕዛዝ መስጫ ቦታ፣ የስኬች መስሪያ ቦታ፣ ለተቆጣጣሪ ለስራ ተቋራጭና እና ለአማካሪ የፊርማ ቦታ የያዘ መሆን ይኖርበታል፤
3. የሕንጻ ተቆጣጣሪው የሕንፃ አዋጁን፤ የሕንጻ ደንቡን፤ ይህን መመሪያ እና ተጓዳኝ ሕጐችንና ውሎችን በመተላለፍ የሚካሄድ ግንባታ እንዲቆም ትእዛዝ መስጠት ይችላል፤ የማስቆሚያ ትእዛዝ የሚሰጠው ዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ በተመለከተው መሠረት እና የግንባታ ማስቆሚያ ቅጽ 015 በመሙላት ይሆናል፤
4. ያለምንም የፅሑፍ ማስታወሻ የሚደረግ የግንባታ ቦታ ጉብኝትም ሆነ የሚሰጥ የቃል ትእዛዝ ህጋዊነት አይኖረውም፤

5. የህንፃ ሹሙ ወይም የሚወክለው አካል ከግንባታው ባለቤት የግንባታውን ክትትልና ቁጥጥር ሥራ አስመልክቶ ለሚቀርብለት ማስታወቂያ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ ቅጽ 016 በመሙላት መልስ መስጠት ይኖርበታል፤
6. ማንኛውም ተቆጣጣሪ በክትትል የስራ ሂደት ከስልጣኑ እርከን ክልል ውጭ ባለ ቦታ እና የግንባታ ደረጃ የሚያጋጥመውን ከፈቃድ ውጭ የሚደረግ የግንባታ እንቅስቃሴ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት የግንባታ ሂደት ማሳወቂያ ቅጽ ሞልቶ መላክ አለበት፡፡

58.<u>ስለቁሳቁስ</u>

1. የሕንፃ ሹም በግንባታ ሥፍራ የተቀመጠ ወይም በሕንፃው ሥራ ላይ የዋለ ግብዓት በናሙና ፍተሻ ውጤቱ ተቀባይነት ካጣ እንዲወገድ ወይንም በአጠቃቀሙ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፤
2. በግንባታ ግብዓት ጥራት ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም አደጋ ወይንም ጉድለት የግንባታው ባለቤት፣ ገንቢው እና አማካሪው ሃላፊነት አለበት፤
3. የሕንፃ ሹሙ ለግንባታው ያገለግላሉ ተብለው የተቀመጡ ወይም ሥራ ላይ የዋሉ የግንባታ ቁሳቁሶች የጥራት ጉድለት እንዳለባቸው በእይታም ሆነ በግንባታ ቦታ በሚደረግ ፍተሻ ካረጋገጠ እንዲወገድ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፤
4. የግንባታ ቁጥጥር የሚያደርጉ ባለሙያዎች ለግንባታ የሚቀርበውን ቁሳቁስ ጥራቱንናየደረጃ መስፈርቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤
5. የሕንፃ ሹሙ ማንኛውም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ለግንባታ ግብዓትለሚውሉ ቁሳቁሶች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊጠይቅ ይችላል፣
6. በእየርከኑ ለሚከናወኑ የኮንክሪት ስራዎች የኮንክሪት ናሙና መወሰድ አለበት፣ የተወሰዱት የኮንክሪት ናሙናዎች ቀነ ገደባቸውን ጠብቆ ፈቃድ ባለው ላብራቶሪ በማስመርመር ውጤቱን ለተቆጣጣሪው አካል ማሳወቅ አለበት፤
7. አዲስ የፈጠራ ግንባታ ቁሶችን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ቁሱ ከሁሉም የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር ጥራቱንና መስፈርቱን የጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ መጠቀም ይቻላል፡፡



59.<u>የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር</u>

1. ለማንኛውም ምድብ የሕንፃ ዓይነቶች የሚጠየቁ ዲዛይኖች ለሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ አማካሪ ድርጅቶች ወይም በልዩ የተደራጁ አማካሪ ኢንተርፕራይዞች መሠራት አለባቸው እንዲሁም ማንኛውም ግንባታ ለዲዛይን ስራ ብቻ ሳይሆን ለግንባታ ክትትል ቁምር አማካሪን በመቅጠር በአማካሪው ኃላፊነት ማሰራት አለበት፤
2. በአማካሪ ድርጅት ወይንም በኢንተርፕራይዞች የሚቀጠሩ የዲዛይን ባለሙያዎች እና በልዩ የተደራጁ ኢንተርፕራይዝ ባለሙያዎች የዲዛይን ሥራ ለማከናወን የተመዘገቡና ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የባለሙያ ምስክር ወረቀት፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የያዙ መሆን አለበት፤
3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የሚቀጠሩ የዲዛይን ባለሙያዎች ሚኒስቴሩ ለዲዛይን እና ለቁጥጥር ሥራ ያወጣውን ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት አለባቸው፤
4. ለማንኛውም የሕንፃ ምድብ ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ እና በልዩ የተደራጁ ኢንተርፕራይዝ አማካሪዎች በበጀት ዓመቱ የታደሰ የባለሙያ የምስክር ወረቀት ባላቸው ባለሙያዎች ቁጥጥሩ መደረግ ይኖርበታል፤
5. ማንኛውም የተመዘገበ የዲዛይን አማካሪ ድርጅት ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት ለሰራው ፕላንና የሥራ ዝርዝር ወይንም ሁለቱንም አገልግሎት በጣምራ ሲያከናውን ሊደርሱ ለሚችሉ ጉዳቶች እና ግድፈቶች ከታወቀ የመድህን ድርጅት የጉዳት ማካካሻ ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡

60.<u>የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮች ስለመቅጠር</u>

1. ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው ፈቃድ ያለውና የፈቃድ ዘመኑ የታደሰ የሥራ ተቋራጭ መቅጠር ይኖርበታል፤
2. የግንባታ ባለሙያዎቹ የግንባታ ሥራ ለማከናወን የተመዘገቡና የሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላቸው መሆን አለባቸው፤
3. የግንባታው ባለቤት ግንባታውን የሚያካሂድለት ሥራ ተቋራጭ መቅጠር ያለበት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች እና ሥራ ተቋራጮች ምዝገባ መመሪያ መሠረት ይሆናል፤
4. የግንባታው ባለቤት ግንባታውን የሚያካሂድለትን የሥራ ተቋራጭ የግንቢ

ግዴታመግቢያ ቅጽ 012 በማስሞላት ለሕንፃ ሹሙ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

5. በማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክት በተቋራጭ መመደብ ያለበት ባለሙያ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች እና ሥራ ተቋራጮች ምዝገባ መመሪያ መስፈርት ማሟላት አለበት፤
6. ማንኛውም በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማራ ባለሙያ ሲቀየር የሥራ ተቋራጩ ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፣ ተቋራጩና አማካሪው ሲቀየር ደግሞ ባለቤቱ፣ተቋራጩና አማካሪው ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል ውል መቋረጡን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣ የተጠቀሰውን የማሳወቂያ ቀናት ተላልፎ በሚገኝ እና በሚደረሰው ጉዳት ተቋራጩ አማካሪው እና ባለቤቱ በጋራ ወይም በግል ኃላፊነት ይወስዳሉ፤
7. የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ውለታ የገባ የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራ ፈቃድ ቅጂ በግንባታ ቦታ ማስቀመጥ አለበት፤
8. ማንኛውም የተመዘገበና ሕጋዊ ፈቃድ ያለው የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የገንቢ ግዴታ ቅጽ 012 መሙላት አለበት፡፡

ክፍል አምስት

በህንፃ ግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች

61.ስለደህንነት ጥንቃቄዎች

1. የሕንፃዎች ግንባታ በሚከናወንበት ጊዜ ጊዜያዊ ወለሎች፣ ማረፊዎች፣ ፎርምዎርኮች እና ደህንነት መጠበቂያ መረቦች ሥራው ለሚቆይበት ጊዜ ሁሉ መዘርጋት ይኖርባቸዋል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የደህንነት መጠበቂያ መረቦች መጠቀም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ጊዜያዊ ወለል ሥራው በሚሰራበት ከፍታ ልክ መዘርጋት ይኖርበታል፤
3. በሥራ ቦታዎች ሠራተኞች ለሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ከሚያስፈልጉ ክፍተቶች በስተቀር የስራ ቦታዎችን ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍኑ ጊዜያዊ ወለሎች እንዲኖሩ መደረግ ይኖርበታል፣ ክፍተቶቹም በሚገባ ሊከለሉ ይገባል፤
4. አደጋ ሊያስከትል የሚችል እያንዳንዱ የወለል ክፍተት፣ በአስተማማኝ ሁኔታ መሸፈን ወይም መከለል ይኖርበታል፣ ለክፍተት በተጋለጡ ጎኖች ሁሉ ከለላ ድጋፍ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

እና የእግር መደገፊያ ጣውላ ሊኖር ይገባል፣ ወይም ከክፍተቱ በታች ለእያንዳንዱ ክፍተት የሚያገለግል የደህንነት መረብ ሊዘረጋ ይገባል፤

5. በሥራ ቦታዎች ላይ ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች ሊወድቁ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል፡-

   ሀ) ሠራተኞች ለአደጋ ወደተጋለጡ ቦታዎች እንዳይገቡ ለመከላከል እንዲቻል ቦታዎቹ መዘጋት ወይም መከለል የሚኖርባቸው ሆኖ በተጨማሪም በሁሉም የሥራ ቦታዎች ጎኖች እና አቅራቢያዎች ጎልተው የሚታዩ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች መቀመጥ ይኖርበታል፣

   ለ) ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች ሊወድቁ በሚችሉባቸው ቦታዎች የመቅለቢያ መድረኮች ሊኖሩ ይገባል፣ መድረኮቹም፣ ከሕንፃው ውጭ ከ3 ሜትር ባላነሰ ርቀት ሊዘረጉ እና ፊታቸውን ወደ ሕንፃው አቅጣጫ አድርገው ወደ ውስጥ ማዘንበል ይኖርባቸዋል፣

6. የግንባታ ሥራዎች በሰዎች እና በንብረት ላይ የሚደርሱ አደጋዎች እና ጉዳቶችን እንዲሁም የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል እንዲቻል መወሰድ ያለባቸውን ወይንም ለሕይወት ጠንቅ የሚሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች እንዳይደርሱ ጥንቃቄን ግምት ውስጥ በማስገባት መገንባት ይኖርባቸዋል፤

7. የሕንፃዎች ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት ወደ ወሰንተኛ ይዞታ እና ወደ መንገድ የሚወድቅ፣ የሚራገፍ ፣ የሚበን እና የሚንጠባጠብ የግንባታ ቁሳቁስ እና መሳሪያ እንዳይኖር ተገቢው መከላከያ መደረግ አለበት፤

8. በመንገድ ዳር በሚሠሩ ሕንፃዎች አካባቢ ቁሳቁሶች ከላይ ወድቀው ከሥር የሚንቀሳቀስውን መንገደኛ እንዳይጐዱ ከጠንካራ ቁሳቁስ የተዘጋጀ መከለከያ አጥር መዘጋጀት ይኖርበታል፤

9. ከግንባታ ቦታ የሚወጡ እና ወደ ግንባታ በሚደረግ የመጫን ማውረድ እንቅስቃሴ ምክንያት በመንገድና ከይዞታ ውጪ በአካባቢው ላይ የሚወድቀውንና የሚራገፈውን ቁስና ተረፈ ግንባታ ገንቢው በራሱ ወጪ የማፅዳት ኃለፊነት አለበት፤

10. ልዩ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር አንድን የግንባታ ቁስ ከይዞታ ውጭ ማከማቸት አይፈቀድም፤

11. በግንባታ ወቅት ጤናን እና ድህንነትን ለማረጋገጥ በግንባታው ሂደት ላይ

የሚሳተፉት በሙሉ በስራ ላይ የዋለውን የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ "ES 3965 አኩፔሽናል ሄልዝ ኤንድ ስተንዳርድ" መሰረት ስራቸውን ማከናወን አለባቸው፤

12. የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሰራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት እንደ ስራው አይነት መውሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄ ተገቢው ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት፤
13. የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሰራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ አሰፈላጊ አልባሳት ማሟላት አለበት፤አማካሪውም ይህ መሟላቱን መከታተል ይኖርበታል፤ እንዲሁም የህንጻ ሹሙም ተወካይ ሁሉም አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ማረጋገጥ አለበት፤ ያልተሟላ ከሆነ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ይገባዋል፤
14. ማንኛውም ከአንድ ወለል በላይ የሚገነባ የህዝብ መጠቀሚያ ህንፃ ግንባታው ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሴፍቲ ባለሞያ ሊኖር ይገባል፤
15. የሴፍቲ ባለሞያው የሴፍቲ ፕላን ተዘጋጅቶ በዚሁ አግባብ እየተሰራ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

62.<u>በግንባታ ወቅት መደረግ የሚገባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች</u>

ማንኛውም ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት፡-

1. በግንባታው አካባቢ ያሉት የመሠረተ ልማት አውታሮች አገልግሎት ከመስጠት መስተጓጎል የለባቸውም፤
2. የአዋሳኝ ህንፃዎች ደህንነት መጠበቁ መረጋገጥ ይኖርበታል፤
3. በሜካኒካል መሣሪያዎች ጉድለት ወይም ብልሽት ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስ መሣሪያዎቹ በትክክል መሥራታቸው በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፤
4. ህንፃው ዙሪያ የወዳደቁ ማቴሪያሎች እና ቆሻሻዎች እንዲሁም ያለአግባብ የተከማቹ ብናኝ አደገኛ ኬሚካሎች መወገድ አለባቸው፤
5. በሕንፃ ግንባታ ቦታ ላይ በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት አንዳያደርስ ከለላ መኖር አለበት፤
6. ከደረሱ አደጋዎች በመነሣት መንሴያቸውን መተንተን ምልክታ ማካሄድና የናሙና ፍተሻ በማድርግ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

63. **<u>መወጣጫዎች እና መሰላሎች</u>**

1. ማንኛውም መወጣጫ መሸከም በሚገባው ክብደት መጠን መሠረት ዲዛይን ተደርጐ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ለማንኛውም ከምድር በላይ ስድስት ፎቅ እና በላይ ለሆነ ህንጻ ግንባታ የሚውሉ መወጣጫ በተለምዶ ጥቅም ላይ ከሚውሉት አጠና እና ጣውላ ቁስ ውጪ በተገጣጣሚና ተነቃቃይ ብረት ቁስ የተሰሩ መሆን ይኖርባቸዋል፤
2. በመወጣጫው ድጋፎች ጥብቅ መሠረት ወይም ደፎች እንዲኖራቸው እና መወጣጫው የድጋፍ መያ[1] እንዲኖረው ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፤
3. በመወጣጫው ላይ የሚገኙ የሥራ መድረኮች ስፋት ከ50 ሳ.ሜ ያነሰ መሆን የለበትም፤
4. በመወጣጫው ሥር የሚዘጋጀው ጣውላ፣ ብረት ወይም አጠና ጠንካራ እና ሰዎችን እና እቃን የማይጥልና የማያንጠባጥብ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፤
5. የመወጣጫ ድልድሎችን ለመስራት ጥቅም ላይ የሚውለው የእንጨት ዓይነት አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት ጥንካሬአቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፤
6. ቀጥተኛ በሆኑት የፊት እና የኋላ የመወጣጫ ድጋፎች መካከል ያለው ርቀት ከ85 ሳ.ሜ የማያንስ ሆኖ በአንድ ጣውላ ስፋት የሚበልጥ ክፍተት እንዳይፈጠር ተጨማሪ ጣውላዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፤
7. የሚሰካኩ በወጣጫዎችዲዛይን የሚደረጉት፣ የሚመረቱት እና አገልግሎት ላይ የሚውሉት አምራች በሚሰጡት መግለጫ መሠረት መሆን ይኖርበታል፤
8. መወጣጫዎች መዘርጋት ወይም መፈታት የሚኖራቸው በሥራው ልምድ ባላቸው ሰዎች ወይም ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ተቆጣጣሪነት መሆን አለበት፤
9. ጉዳት የደረሰበት ወይም የላላ የመወጣጫ አካል ተገቢው እድሳት ተደርጎለት በአስተማማኝ ሁኔታ እስካልተጠናከረ ድረስ አገልግሎት ላይ መዋል የለበትም፤
10. በግንባታ ቦታ ላይ የሚገኝ መወጣጫ ከአደጋ የተጠበቀ መሆኑ በአሠሪው ወይም በሠራተኞቹ የእለት ከእለት ቁጥጥር ሊደረግለት ይገባል፤
11. በመወጣጫ ድልድሉ ላይ የሚቀመጠው እቃ መወጣጫው መሸከም ከሚችለው አቅም በላይ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፤
12. መወጣጫዎች ቀጥ ብለው እና ተስተካክለው መዘርጋት ያለባቸው ሲሆን ከሕንፃው አካል ጋር በእያንዳንዱ 4.5 ሜትር ከፍታ እንዲሁም በየ6 ሜትሩ ርቀት አግድም መታሰር አለባቸው፤

13. ተንቀሳቃሽ መሰላል መሳይ መወጣጫዎች ከመሬት ወለል ከ5 ሜትር በላይ ለሚሰራ ስራ ጥቅም ላይ መዋል የሌለባቸው ሆኖ ከ5 ሜትር በታች ለሚሠራ ሥራ በአንድ ጊዜ ከሁለት ሠራተኞች በላይ ሊገለገሉባቸው አይገባም፡፡

64.<u>ስለመሰላሎች</u>

1. የእንጨት መሰላሎች አስተማማኝ በሆነ ጥንካሬ የተሰሩ እና በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት የሚደርስባቸውን ጫና መሸከም የሚችሉ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤
2. ከእንጨት የተሰሩ መሰላሎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ቀለም የተቀቡ መሆን ይገባቸዋል፤
3. ከቦታ ወደ ቦታ ሊዘዋወሩ የሚችሉ ተንቀሳቃሽ መሰላሎች አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት ተገቢው ፍተሻ ሊደረግላቸው ይገባል፤
4. የላሉ ወይም የተሰበሩ ወይም የጎደሉ መወጣጫዎች ወይም የተሰነጠቁ የጎን ቋሚዎች ያሏቸው መሰላሎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ አይፈቀድም፤
5. የተንቀሳቃሽ መሰላል የጎን ቋሚዎች የታችኛው ጫፎች ጠንካራ በሆነ እና በተደላደለ መደብ ላይ ማረፍ የሚኖርባቸው ሆነው የጎን ቋሚዎቹ የላይኛው ጫፍ የሚሸከመውን ክብደት ለመደገፍ በሚችል በቂ ጥንካሬ ባለው ደጋፊ አካል እንዲገፉማድረግ ይገባል፤
6. ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ነጠላ ወይም ተደራራቢ ወይም ተቀጣጣይ መሰላሎች እንዳይንሸራተቱ ተንሸራታች ያልሆነ መደብ እንዲኖራቸው ወይም እንዲያያዙ ወይም እንዲታሰሩ መደረግ ይኖርባቸዋል፤
7. የኤሌትሪክ ፍሰት ባለበት አካባቢ የሚያገለግሉ መሰላሎች ኤሌክትሪክ የማያስተላልፉ ዓይነት ሆነው በመሰላሎቹ እና በኤሌትሪክ አስተላላፊዎቹ መካከል በቂ ክፍት ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤
8. ከብረት የተሰሩ መሰላሎች ወይም በእንጨት ተሰርተው በሽቦ የተጠናከሩ መሰላሎች በሃይል የተሞላ የኤሌክትሪክ መሣሪያ በአለበት ቦታ ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፤
9. የመሰላሎች ርዝመት ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት መሆን ይኖርበታል፤

   ሀ) ለባለድጋፍ መሰላሎች ወይም ተቀጣይ ለሆኑ ባለድጋፍ መሰላሎች፣

   ለ) ለነጠላ መሰላሎች 9 ሜትር፣

   ሐ) ሁለት ተቀጣጣይ ክፍሎች ላሏቸው ተቀጣጣይ መሰላሎች 14.6 ሜትር እና

   መ) ከሁለት ተቀጣጣይ ክፍሎች በላይ ላሏቸው ተቀጣጣይ መሰላሎች 20 ሜትር፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር

10. ከ6 ሜትር በላይ ቁመት ያላቸው እንዳይንቀሳቀሱ ተደርገው የተተከለ መሰላሎች፣

ሀ) ከ6 ሜትር ያልበለጠ ርቀት ያላቸው መቆሚያዎች እንዲኖራቸው መደረግ ይኖርበታል፣

ለ) ከመሰላሉ የታችኛው ክፍል ከ2.5 ሜትር በላይ ለሆነ ከፍታ ሠራተኞች እንዳይወድቁ ለመከላከል የሚስችል የደህንነት መጠበቂያ አጥር (ኬጅ) ሊኖረው ይገባል፣

11. የማይንቀሳቀሱ መሰላሎች መተከል ያለባቸው በየመሐከላቸው የ3 ሜትር ርቀት እንዲኖር ተደርጎ ሆኖ ከላይ እስከታች ያለው አካላቸው ይህን ርቀት መጠበቅ ይኖርበታል፤

12. በተተከለ መሰላሎች ላይ ከሚገኙ መወጣጫዎች በስተጀርባ በትንሹ 1.75 ሜትር ስፋት ያለው ቦታ በቋሚነት እንዲኖር ማድረግ ይገባል፤

13. ከመሰላሎቹ በላይ መወጣጫዎች እንዳይኖሩ ሆኖ የጎን ቋሚዎቹ ከመሰላሎቹ ማረፊያ በላይ 90 ሳ.ሜ እስከሚቀረው ድረስ መቀጠል ይኖርባቸዋል፤

14. የደህንነት ባለሞያው በግንባታ ወቅት ለሰራተኛ ደህነት ሲባል የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን መወጣጫዎችና መሰላሎችን ወደ ስራ ከመግባቱ በፊት ደህነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

65. <u>የማፍረስ ሥራ</u>

1. አንድ ሕንፃ በሚፈርስበት ጊዜ ተያያዥ የሆኑ የቋሚ ግንባታ አካላት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን መሐንዲሱ ካላረጋገጠ በስተቀር ሙሉ ለሙሉ መደገፍ አለባቸው፤

2. አንድ ሕንፃን ለማፍረስ ሲወሰን በቋሚው የግንባታ አካል ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሥራዎች ካሉ የማፍረስ ሥራው ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ መቋረጥ አለባቸው፤

3. የማፍረስ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ሠራተኞችን ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ መስታወቶች እና ክፈፎቻቸው በቅድሚያ መነሳት ይኖርባቸዋል፤

4. የአንድ ሕንፃ የማፍረስ ሥራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከላይ ወደ ታች መከናወን ይኖርበታል፣ ግድግዳዎችም አደገኛ ወይም ያልተረጋጋ በሆነ ሁኔታ ቆመው እንዲቀሩ መደረግ የለበትም፤

5. ግድግዳዎች ወይም ሌሎች የግድግዳ ክፍሎች የወለል ጋ የመሸከም አቅም ባላገናዘበ

ሁኔታ በሕንፃው ወለል ላይ እንዲወድቁ ወይም በወለሉ ላይ እንዲቆዩ መደረግ የለበትም፤

6. ማንኛውም ሠራተኛ ከታች በሚገኙ ወለሎች ላይ እንዳይገኙ ካልተደረገ ወይም ወደ ወለሎቹ መግባት ካልተከለከለ በስተቀር በወለሉ ላይ ከሚገኝ ክፍተት ጀምሮ በ3 ሜትር ርቀት ውስጥ የሚገኝ የውስጥ ወይም የውጭ ግድግዳ እንዲፈርስ ከመደረጉ በፊት ከወለሉክፍተት በታች የሚሆን ጣውላ እንዲኖር መደረግ አለበት፤
7. የሚፈርሱ ቁሶች ከሕንፃው ላይ በጥንቃቄ እንዲወርዱ ሆነው ባግባቡ መከማቸት እና መወገድ ይኖርባቸዋል፤
8. ፍርስራሽ ማቴሪያሎች እና ሌሎች ቆሻሻዎች በወለሎች ወይም ከሕንፃው ውጭ በቅርብ ርቀት ላይ መጣል የለባቸውም፤
9. ከከፍተኛ ወለሎች ላይ ፍርስራሽ ማቴሪያሎች ወደ መሬት ሲወረወሩ ማቴሪያሉ እንዲወድቅ በሚፈለግበት ቦታ ሠራተኞች እንዳይገቡ ቦታው መከለል ወይም መዘጋት ይኖርበታል፣ በተጨማሪም በአካባቢው ላይ የማስጠንቀቂያ ምልክት መደረግ ይኖርበታል፤
10. አንድ ሕንፃ በሚፈርስበት ጊዜ ፍርስራሽ ሸክላዎች ወይም ሌሎች የደቀቁ ፍርስራሾችን ለማስወገድ የሚያስችል ማንሸራተቻ ወይም ማስተላለፊያ ሊኖረው ይገባል፤
11. ማንሸራታቻዎቹ ወይም ማስተላለፊያዎቹ ባልተቋረጠ ሁኔታ በህንፃው ላይ ሊዘረጉ የሚችሉት ሕንፃዎቹ ከሁለት ወለል ያልበለጠ እንደሆነ ብቻ ነው፤
12. ከእያንዳንዱ ማስተላለፊያ በታች መዝጊያዎች ወይም ማገጃዎች እንዲገጠሙ እና በማንሸራታቻ የመውጫ አፎች አጠገብ "ተንሸራታች ማቴሪያል" የሚል የማስጠንቀቂያ ምልክት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

66. <u>ስለ ክፍታ እና የጣሪያ ላይ ሥራዎች</u>

1. ሰራተኞች ከወለል ከ3 ሜትር በላይ ክፍታ ላይ የሚሰሩ ሆኖ ሲገኝ የመጠንጠልጠያ ገመዶች፣ የደህንነት መጠበቂያ ቀበቶዎች ወይም የአደጋ መከላከያ መረቦች መቅረብ ይኖርበታል፤
2. ሠራተኞች ሊወድቁ ወይም ሊንሸራተቱ የሚችሉበት በወለል ላይ የሚገኝ ክፍት ቦታ በከለላ ድጋፍ እና በእግር መደገፊያ ጣውላ መሸፈን ወይም መከደን ይኖርበታል፤
3. በማንኛውም በክፍታ ቦታ ላይ የመገንባት ወይም የማፍረስ ሥራ የሚሰራ ሠራተኛ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን
ፈቃድና ማህደር

ከአደጋ መከላከል የሚያስችሉ የጭንቅላት፣ የእጅ እና የእግር መጠበቂያ ማቴሪያሎችን መጠቀም ይኖርበታል።

67.<u>የጣሪያ ላይ ሥራዎች</u>

1. ማንኛውም የጣሪያ ሥራ በቅድሚያ የታቀደና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግለት ይገባል፤
2. በጣሪያ ሥራ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሠራተኛ የፊዚካላዊ እና ሳይኮሎጂካዊ ብቃት ያለው፣ በጣሪያ ሥራ ላይ በቂ እውቀት እና የሥራ ልምድ ያለው መሆን ይገባዋል፤
3. የጣሪያ ሥራ የሠራተኞችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል የአየር ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ መቋረጥ ይኖርበታል፤
4. ለጣሪያ ሥራ የሚውሉ የመንሸቀቀያ እንጨቶች፣ መረማመጃዎች እና የጣሪያ መሰላሎች ከቋሚ ግንብ ጋር በአስተማማኝ ሁኔታ መታሰር ይኖርባቸዋል፤
5. የጣሪያ ተሸካሚዎች ወይም ድጋፎች ከጣሪያው ቁልቁለማነት/ ዝቅዝቃት ጋር እንዲገጥሙ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተደገፉ መሆን ይገባቸዋል፤
6. በጣሪያው ጠርዝ ዙሪያ መንበርከክ ወይም ቁጢጥ ማለት ሲያስፈልግ ሠራተኛው በደህንነት መጠበቂያ ገመድ መጠቀም ይኖርበታል፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ በመካከሉ ድጋፍ መኖር አለበት፤
7. በጣሪያ ላይ ለሚገኙ ክፍት ቦታዎች መዝጊያ ክዳኖች በሙሉ ጠንካራ ከሆነ ቁሳቁስ የተሰሩ ሆነው በትክክል መገጠም ይኖርባቸዋል፤
8. በቁልቁለታማ ጣሪያዎች ላይ ለሚከናወኑ ሥራዎች አስተማማኝ እና ተስማሚ የመንሸቀቀያ ጣውላዎች ወይም የጣሪያ መሰላሎች ተዘጋጅተው በተገቢው ቦታ እንዲቀመጡ መደረግ ይኖርበታል፤
9. ረዥም ጊዜ ለሚወስዱ የጣሪያ ሥራዎች ሠራተኛውን ከአደጋ መከላከል የሚያስችሉ ጠንካራ የሆኑ ማገጃዎች ወይም ከለላ ድጋፎች እና እግር እንዳይንሸራተት የሚከላከሉ ጣውላዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤
10. አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ ጣሪያዎች ወይም ተሰባሪ ጣሪያዎች ባሏቸው ሕንፃዎች ላይ ወደ ጣሪያው መውጫ አካባቢ የማስጠንቀቂያ ጽሁፍ በግልጽ በሚታይ መልኩ እንዲኖር መደረግ ይኖርበታል።

68.<u>የመሬት ውስጥ ሥራዎች</u>

1. ማንኛውም የቁፋሮ እና የመሬት ውስጥ ሥራዎች በሚከናወኑበት ወቅት በሠራተኞች ላይ የመውደቅ፣ የአፈር መናድ፣ የውሃ ሙላት እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ አደጋዎች እንዳይደርሱ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፤
2. ከመሬት በታች ለሚከናወኑ የቁፋሮ ሥራዎች ብርሃን እና አየር ለማስገባት የሚስችሉ ክፍተቶች መኖራቸውን እና የአደጋ ጊዜ መውጫ መንገድ መዘጋጀቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፤
3. በመሬት ውስጥ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ መሥመሮች በኢትዮጵያ የሕንፃ ኮድ እና ስታንዳርድ በተቀመጡት የአሰራር ስርዓቶች መሰረት ይሆናል፤
4. ትላልቅ የቁፋሮ እና የመሬት ውስጥ ሥራዎች ሲከናወኑ የእለት ከእለት ቁጥጥር እና ክትትል በተቆጣጣሪ መሐንዲሱ መደረግ ይኖርበታል፡፡

69.<u>የቁፋሮ ሥራ</u>

1. ማንኛውም የቁፋሮ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች መረጋገጥ አለባቸው፣
   ሀ) የሚፈለገው የቁፋሮ ሥራ በሚገባ የታቀደ እና የአቆፋፈር ዘዴው በግልጽ ተለይቶ የተቀመጠ መሆን ይኖርበታል፣
   ለ) የመሬቱ የተፈጥሮ ሁኔታ በተገቢው ባለሙያ ተመርምሮ መታወቅ ይኖርበታል፣
   ሐ) የሚካሄደው የቁፋሮ ሥራ በአካባቢው ላይ የሚገኙትን ሕንፃዎች፣ መንገዶች እና ሌሎች የመሰረት ልማት አውታሮችን የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
   መ) በቁፋሮ ወቅት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የውሃ መስመሮች፣ ከመሬት በታች የቆሻሻ መውረጃ መስመሮች ወይም ቱቦዎች፣ እና የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያዎች በሚመለከተው አካል ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፣
   ሠ) ቁፋሮ የሚካሄድበት ቦታ በጎጂ ኬሚካሎች ወይም ጉዳት ሊያመጡ በሚችሉ አደገኛ ቁሶች ያለመበከሉ በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፣
   ረ) የተቆፈሩ ጉድጓዶች ጎን በሠራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ከከባድ ዝናብ፣

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር

ከመሬት መንሸራተት እና ከፈንጂዎች መፈንዳት በኋላ በተገቢው ባለሙያ ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፣

ሰ) የተቆፈረውን ጉድጓድ እንዲናድ ወይም እንዲንሸራተት የሚያደርጉ ከባድ መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎች እንዲሁም የማምረቻ ተቋማት በአካባቢው መቀመጥ ወይም መተከል አይኖርባቸውም፣

ሸ) እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች የተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ እንዳይገቡ የመከለያ አጥሮች እና የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያዎች ተዘጋጅተው መተከል ይኖርባቸዋል፣

2. ከሚቆፈረው ቦታ በቅርብ ርቀት እስከ ሁለት ሜትር የሚገኙ ዛፎች፣ ቋጥኞች እና ሌሎች ቁሶች የቁፋሮ ስራ ከመጀመሩ በፊት መነሳት ወይም መወገድ ይኖርባቸዋል፤

3. ማንኛውም ሠራተኛ ከ1 ሜትር በላይ ጥልቀት ባለው ቁፋሮ ውስጥ እንዲገባ የሚፈቀድለት፡-

ሀ) የተቆፈሩ ጉድጓዶች ጎን አደጋ እስከማያስከትል ቦታ ድረስ እንዲያዘነብሉ ሲደረግ፣

ለ) በተቆፈረው ጉድጓድ ጎኖች ብረቶችን በመትከል፣ ድጋፎችን በመስራት ወይምወሽመጠችን ወይም ቦዮችን በመስራት ጥበቃ ሲደረግላቸው እና

ሐ) ሠራተኞች በሌሎች አስተማማኝ ዘዴዎች የተጠበቁ ሆነው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፤

4. በሚቆፈረው ቦታ አቅራቢ የሚገኙ የሕንፃዎች መሠረቶች ሊሸረሸሩ ይችላሉ ተብሎ ሲገመት የቁፋሮው ሥራ በአጫጭር ክፍልፋዮች እንዲሰራ እና የህንፃዎቹ ግድግዳዎች በአስተማማኝ ሁኔታ መደገፍ ወይም መታሰር ይኖርባቸዋል፤

5. ሠራተኞች ከ1.2 ሜትር በላይ ጥልቀት ባላቸው የተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ሲገቡ በቅርብ ርቀት በሚገኙ ቦታዎች መሰላሎች እንዲኖሩ መደረግ ይኖርበታል፣ መሰላሎቹ ከተቆፈረው ጉድጓድ የታችኛው አካል ጀምሮ ከጉድጓዱ አናት በላይ ከ90 ሳ.ሜ ባላነሰ ከፍታ መዘርጋት ይኖርበታል፤

6. በተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ የሠራተኞችን መውደቅ ለመከላከል ጉድጓዶቹ

አስተማማኝ በሆኑ ድጋፎች ወይም ማገጃዎች መከለል አለባቸው፤

7. በቁፋሮ ወቅት ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሣሪያዎቹ ከመንደርደራያዎች ላይ ተንሸራተው እንዳይወድቁ በመንደርደረያዎቹ ላይ ጠርዞች መሠራት ይኖርበታል፤

8. በተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ለመግባት እና ከቁፋሮው የሚወጡ ማቴሪያሎችን ለማስወገድ ሲፈለግ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፤

9. ወደ ተቆፈሩ ጉድጓዶች ለመግባት የሚያገለግሉ መረማመጃዎች፡-

   ሀ) ከጠንካራ ጣውላ ወይም ላሜራ ወይም ተመሣሣይ ጥንካሬ ካላቸው ቁሳቁስ የተሰሩ ሆነው ከ60 ሳ.ሜ ያላነሰ ስፋት ሊኖራቸው ይገባል፤

   ለ) ከድልድል በላይ ከ1.2 ሜትር በላይ ጥልቀት ካላቸው ከለላ ወይም አጋጅ ድጋፎች መሰራት ይኖርበታል፤

   ሐ) ድልድሎቹ በስድስት ሜትር ቁመት ውስጥ ከአንድ የበለጡ ሆነው ሲገኙ መረማመጃዎቹ በችካሎች መጠናከር ይኖርባቸዋል፤

10. ማንኛውም በቁፋሮ ሥራ ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ከቁፋሮው የወጣውን ማቴሪል ከተቆፈሩ ጉድጓዶች ጠርዝ ጀምሮ በ1.2 ሜትር ርቀት ውስጥ ማከማቸት አይኖርበትም፤

11. ከተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ የወጡትን ማቴሪሎች ለማስወገድ ጥቅም ላይ የሚውሉ የማዘለያ እቃዎች ወይም ባልዲዎች የመደገፊያ አካላቸው እንዳይነቀሉ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

70. <u>ስለ ኬሚካሎች</u>

1. በግንባታ ቦታ ላይ በሠራተኛው ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በየጊዜው ሊመረመሩ እና ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፤

2. በሥራ ቦታ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በተቻለ መጠን አደጋ ሊያደርሱ በማይችሉ ተለዋጭ ቁሶች እንዲተካ ማድረግ ያስፈልጋል፤

3. አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በአንድ የሥራ ቦታ የሚገኙ ከሆነ በሠራተኞች ጤንነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል የሚያስችሉ ርምጃዎች መወሰዳቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፤ የሚወሰዱት እርምጃዎች፡-

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር ኮሚሽን ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ሀ) የሥራ ቦታን በተስማሚ ሁኔታ ዲዛይን ማድረግ እና ሥራው ዙሪያውን ዝግ በሆነበት ሁኔታ እንዲሰራ ወይም እንዲከለል ማድረግ፣

ለ) ለአደጋ የሚጋለጡትን ሠራተኞች ወይም ለአደጋ የሚያጋልጠው ሥራ የሚሰራበትን ጊዜ መቀነስ፣

ሐ) የነፍስ ወከፍ የመከላከያ አልባሳትን መጠቀም፣

መ) ተቀጣጣይ እና አንፀባራቂ ቁሶችን እንዲሁም ለመግልገያነት የሚውሉ ኬሚካሎችን ከሥራ ቦታ አካባቢ ማራቅ የመሳሰሉትን ያካትታል፤

71.<u>ስለ ፈንጂዎች</u>

1. በሥራ ቦታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፈንጂዎች በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ያለው ካልሆነ በስተቀር ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፤
2. ማናቸውም በግንባታ ሥራ ላይ ፈንጂ የማፈንዳት ሥራዎች መከናወን የሚችሉት በፈንጂ ተቆጣጣሪ አካላት በሚወጡ መመሪያዎች እና ደንቦች መሠረት ይሆናል፤
3. የፈንጂ ማፈንዳት ሥራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ የፈንጂ ተቆጣጣሪ ባለሙዎች ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ ይኖርባቸዋል።

72.<u>መርዛማ ቁሳቁሶች</u>

በግንባታ ሥራዎች ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገር ግን ለጤና ጎጂ የሆኑትን እንደ ሲሚንቶ፣ ላይም፣ የምስጥ ማጥፊያ ኬሚካል፣ ቶክሲክ የሆኑ ቀለሞች፣ ፖሊሽ ማፅጂያ ማድረጊያ አሲድ፣ የሆኑትን ቁሳቁሶች አጠቃቀም እና አያያዝ ላይ በቂ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

73.<u>ስለ አልባሳት</u>

1. በማንኛውም በግንባታ ቦታ ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ከዚህ በታች የተመለከቱትን የግንባታ ቦታ የአደጋ መከላከያ አልባሳት መጠቀም ይኖርበታል፡-

ሀ) ጭንቅላት መከላከያ ቆብ፣

ለ) የሥራ ጫማ፣

ሐ) የሥራ ልብስ ማድረግ ይኖርበታል፣

2. ማንኛውም በግንባታ ቦታ ላይ ጉብኝት የሚያደርግ ሰው የጭንቅላት መከላከያ ቆብ ማድረግ ይኖርበታል፤
3. ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ አሠሪ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከቱትን አልባሳት በሥራ ቦታው ላይ እንዲገኙ እና ሠራተኞችም

የማድረግ ግዴታ አለበት፤

4. ማንኛውም አሠሪ በሥሩ የሚተዳደሩ ሠራተኞች በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከቱትን አልባሳት በሥራ ቦታቸው ላይ መጠቀማቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፤
5. በማንኛውም ሥራ ቦታ ላይ ሠራተኞች ለግል ንብረቶቻቸው ማቆያ የሚያገለግል ቁም ሳጥን ለእያንዳንዱ ሠራተኛ በአሠሪው ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡

74.<u>የእሳት አደጋ ስለ መከላከል</u>

1. ሁሉም አውቶማቲክ መርጫ መከላከያ መሣሪያ የተገጠመላቸውን ጨምሮ የሥራ ቦታዎች ከጥንቃቄ ጉድለት የሚከሰቱ እሳቶችን ለመከላከል እና ለማጥፋት የሚያስችሉ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሊኖራቸው ይገባል፤
2. እነዚህ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሙሉ ለሙሉ ተሞልተው እና አገልግሎት መስጠት በሚያስችላቸው ሁኔታ ተዘጋጅተው በተመደበላቸው ቦታ ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፤
3. አገልግሎት ላይ የሚውሉ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሥልጣን ባለው አካል ፈቃድ የተሰጣቸው መሆን ይገባቸዋል፤
4. የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች የእሳት አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ ሊደረስባቸው በሚችሉ ግልጽ እና ከመሰናክል ነፃ በሆኑ አካባቢዎች በሚገኙ መስቀያዎች ወይም ድጋፍ ባላቸው ማስቀመጫዎች ላይ መሰቀል ወይም መቀመጥ ይኖርባቸዋል፤
5. የእሳት ማጥፊያ መሣሪዎች በተመደበላቸው ቦታ መገኘታቸውን፣ በአካላቸው ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩን እና አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን ለማረጋጥ የሚያስችል ምርመራ ከአንድ ዓመት ባላነሰ ጊዜ ውስጥመሣሪያዎቹ በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ ሊደረግላቸው ይገባል፣
6. የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ የመሣሪያዎቹ ዓይነት፣ የሚሰጡት አገልግሎት እና በትክክል መጠቀም የሚያስችሉ መመሪያዎች በሚታዩ እና በቀላሉ በሚነበቡበት ሁኔታ ተጽፈው መለጠፍ ይኖርባቸዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የመንግስት ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

75.<u>ስለ እሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች</u>

1. በማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ሕንፃ በእሳት አደጋ ጊዜ ሠራተኞች እንዲያመልጡ የሚያስችሏቸው መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፤
2. ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ በእሳት አደጋ ጊዜ ከአደጋ ነጻ ወደ ሆነው ቦታ ለመውጣትና ለማምለጥ የሚያስችሉ በእያንዳንዱ ፎቅ ላይ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ "ኢኤስ 3964 ፋየር ፕሪቪዎሽንስ ዱሪንግ ቢውልዲንግ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ወርክ ኤንድ ዩዝ" መሰረት የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፤
3. ሁሉም የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች በተገቢው መንገድ ጥበቃ የተደረገላቸው እና ማንኛውም እንቅስቃሴ ከሚገድቡ ወይም ከሚያውኩ መሰናክሎች ነፃ መሆን አለባቸው፤
4. ተንሸራታች ከሆኑ በሮች በስተቀር ሁሉም የሕንፃው በሮች ወደ ውጭ እንዲከፈቱ ሆነው መሰራት ይኖርባቸዋል፤
5. ሠራተኞችን ከሕንፃው ውስጥ ወይም ሕንፃው ከሚገኝበት ግቢ ለመውጣት የሚስችሉ በሮች በቀላሉ እንዳይከፈቱ በሚያደርጋቸው ሁኔታ መቆለፍ ወይም መታሰር የለባቸውም፤
6. በማናቸውም ክፍሎች ውስጥ የሚከማቹ እቃዎች በክፍሉ ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የእሳት አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት ለማምለጥ የሚያስችላቸው ነፃ የመተላለፊያ መንገድ እንዲኖር በሚያስችል ሁኔታ መዘጋጀት ወይም መደራጀት ይኖርባቸዋል፤
7. ማንኛውም በሕንፃ ውስጥ የሚገኝ ሠራተኛ በእሳት አደጋ ጊዜ ለማምለጥ የሚያስችለውን መንገድ እና በአደጋ ጊዜ መከተል ስለሚኖርበት ስርዓት ተገቢው ሥልጠና ማግኘት ይኖርበታል።

76.<u>ስለ ተቀጣጣይ ቁሳቁሶች</u>

1. የተቀጣጣይነት ባህርይ ያላቸው የግንባታ ቁሳቁሶች ለእሳት በሚጋለጡ ቦታዎች መከማቸት አይኖርባቸውም፤
2. በግንባታ ሥራ ውስጥ በቀላሉ በእሳት የሚቀጣጠሉ ቁሶችን ወይም ፈሳሾችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

ሀ) ተቀጣጣይ ነገሮች እንዳይቀጣጠሉ ለመከላከል የሚያስችል ቁጥጥር እና ክትትል

ሊደረግባቸው ይገባል፣

ለ) ተቀጣጣይ ቁሶችን ለመሸከም፣ ለማስተላለፍ እና ለማከማቸት የሚያገለግሉ የመያዣ እቃዎች በጥንቃቄ መጠበቅ እና መታሰር ይኖርባቸዋል።

77.ስለ የመጀመሪያ እርዳታ አሠጣጥ

1. በማንኛውም የሥራ ቦታ ላይ የመጀመሪያ የእርዳታ አገልግሎት መስጫ ቁሳቁስ ክፍል በአሰሪው መደራጀት ይኖርበታል፤
2. በሥራ ቦታ ውስጥ የመጀመሪያ የህክምና መስጫ ቦታን የሚያመለክቱ ምልክቶች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች መለጠፍ ወይም መተከል ይኖርበታል፤
3. በሥራ ቦታ ላይ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም ጉዳት በተመለከተ አግባብ ባለው መ/ቤት ተዘጋጅቶ በተፈቀደ ፎርም መመዝገብ ይኖርበታል፣ አሠሪውም በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት መመዝገቡን የማረጋገጥ እና የምዝገባ ዝርዝሩን ወደ ሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፤
4. ማንኛውም አሠሪ በሥራ ቦታ ላይ በከባድ ሕመም ወይም አደጋ የተጎዳን ሠራተኛ ወደ ሕክምና ተቋም የመውሰድ ሃላፊነት አለበት፤
5. በግንባታ ቦታዎች ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎት የሚሠጡ የሕክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት ተቋማት አድራሻዣው መመልከት አለባቸው።

78.ስለ አደጋ ማምለጫ መንገዶች

1. ማናቸውም የሥራ ቦታዎች ለሥራው እንደየሥራው አካባቢ ተገቢ የሆኑ እና ከአደጋ የተጠበቁ የመግቢያ እና የመውጪያ መንገዶች ሊኖራቸው ይገባል፤
2. በሥራ ቦታ የሚገኙ ሠራተኞች፣ መሣሪያዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ከአደጋ በተጠበቀ ሁኔታ ሊንቀሳቀሱ በሚችሉበት ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው፤
3. በአዳራሾች ወይም በሌሎች ክፍሎች የሚገኙ መተላለፊያዎች እና በየሕንፃው ውስጥ ከክፍል ወደ ክፍል ለመዘዋወሪያ ወይም ለመውጫ እና መግቢያ የሚያገለግሉ መተላለፊያዎች እንደአስፈላጊነቱ በወለል ምልክቶች እንዲለዩ መደረግ ይኖርበታል፤
4. ድንገተኛ አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት እና መደበኛ የመውጫ መንገዶች አደገኛ ሆነው ሲገኙ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ሲገኝ ለማምለጥ የሚያስችሉ የድንገተኛ አደጋ ማምለጫ ዘዴዎች በቅድሚያ ሊዘጋጁ ይገባል፤
5. የአደጋ መውጫ በሮች ወይም መንገዶች ፈጣን የመውጫ አገልግሎት እንዲሰጡ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
ሥርዓት ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

በሚያስችል ሁኔታ ሊዘጋጁ፣ ምልክት ሊደረግባቸው እና ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል፣

6. የአደጋ ጊዜ መውጫ በሮች መከፈት የሚኖርባቸው የበሮቹ ውዝዋዜ በሚፈልገው የቦታ ስፋት ወደ ያዙ ወለሎች እና፣ የደረጃ ማረፊያዎች በኩል ሆኖ ወደ ሁለቱ ተቃራኒ አቅጣጫዎች የሚወዛወዙ በሮች ሲገጠሙ አሳልፎ ለማየት በሚያስችል ክፍተት መሆን ይገባቸዋል።

79.<u>ስለ ሠራተኞች እና የሥራ ቦታዎች ደህንነት አጠባበቅ</u>

1. የታወቀ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ችግር ያለበት ሰው በግንባታ ሥራ ላይ እንዲመደብ መደረግ የለበትም፤
2. ማንኛውም የግንባታ አሰሪ ወይም ተቆጣጣሪ ወይም ሠራተኛ በሰዎች ጤንነት እና ደህንነት ላይ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ አሰካሪ መጠጦች ጥጦ ከተገኘ ወደ ሥራ ቦታ መግባት ወይም ሥራው ወደሚገኝበት ቦት ላይ መቆየት አይፈቀድም፤
3. ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚገኝ ሠራተኛ በሠራተኞች ላይ አደጋሊያስከትል በሚችል መልኩ እንደ ግብግብ፣ አላስፈላጊ ሩጫ እና ዝላይ እንዲሁም ቀልዶችን በሰዎች ላይ መሞከር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ረብሻ ላይ መሳተፍ የለበትም፤
4. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታው ላይ ደህንነቱን እና ጤንነቱን ለመጠበቅ የተሰጡትን መሣሪያዎች በአግባቡ መያዝ እና መጠቀም ይኖርበታል፤
5. አሠሪው የሠራተኞቹ ደህንነት እና ጤንነት ሊያስጠብቁ የሚችሉ የመከላከያ መሣሪያዎች እና ሌሎች አልባሳት እንዲያገኙ ማድረግ እና በስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ይገባዋል።

80.<u>የሥራ ቦታዎች ደህንነት</u>

1. ማንኛውም አሠሪ የሥራ ቦታዎች በሠራተኞች ደህንነት እና ጤንነት እንዲሁም በሕብረተሰቡ እና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ማድረግ ይኖርበታል፤
2. አሠሪው በሁሉም የሥራ ቦታዎች የደህንነት መጠበቂያ ሥነ-ስርአቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን በየጊዜው ማረጋገጥ ይኖርበታል፤
3. ማንኛውም የሥራ ቦታ ከቆሻሻ የፀዳ እና በጽዳት የሚጠበቅ መሆንይኖርበታል፤
4. ማንኛውም የሥራ ቦታ ለወንዶች እና ሴት ሠራተኞች መገልገያ የሚሆኑ እና በተለያየ ቦታ የተገነቡ ጊዜያዊ የመታጠቢያ እና የንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፤
5. ማንኛውም የሥራ ቦታ ከመንግስት ዋና ምንጭ ወይም በሚመለከተው አካል ፍቃድ

ካገኘ ሌላ የተለየ ምንጭ የተገኘ በቂ እና ለጤና ተስማሚ የሆነ የመጠጥ ውሃ ሊኖረው ይገባል፤

6. በሥራ ቦታዎች የሚገኙ ለእሳት አደጋ እና ለበሽታ የሚያጋልጡ ደረቅ ቆሻሻዎች በወቅቱ መወገድ አለባቸው፤
7. በግንባታው አካባቢ ብክለት እንዳይከሰት ጊዜያዊ የፍሳሽ ማከማቻ እና ማስወገጃ መዘጋጀት አለበት፤
8. ህዝብ በሚተላለፍበት መንገድ የሚከማች የግንባታ ቁሳቁስ ከከተማው አስተዳደር ፈቃድ ካልተሠጠ በስተቀር ማከማቸት አይፈቀድም፤
9. ከሀምሣ እና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች በሚሠሩባቸው ማናቸውም የሥራ ቦታዎች የደህንነት እና የጤንነት ሁኔታዎችን የሚከታተል የደህንነት መኮንን ሊኖር ይገባል፣ የደህንነት መኮንኑ፤

   ሀ) የሥራ ቦታ የደህንነት እና ጤንነት አጠባበቅ የሙያ ሥልጠና የተሰጠው ሊሆን ይገባል፣

   ለ) ከሥራ ተቆጣጣሪዎች ጋር በመመካከር በአሠሪው የተቀመጡትን የደህንነት እና ጤንነት ተግባራትን ያከናውናል፤ በሰራተኞች መተግበሩንም ይቆጣጠራል፡፡

81. <u>የሚደርሱ አደጋዎችን ስለ መመዝገብ እና ማሳወቅ</u>

1. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም የደረሰበትን አደገኛ ሁኔታ ለአሰሪው ወይም ለተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፤
2. በሥራ ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎች እና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች እንዲሁም አደገኛ ክስተቶች ተመዝግበው ለዚሁ ሥራ በተመደበ ሰው በአግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል፤
3. በሥራ ቦታ ላይ ተመዝግበው የተያዙ መረጃዎች ተጠብቀው የሚቆዩበት ጊዜ ቢያንስ ከ10 ዓመት ቢበዛ ደግሞ ከ20 ዓመት መብለጥ የለበትም፤
4. ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚደርስ አደጋ በ 3 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ አለበት፣ ሪፖርቱ የሚከተሉትን የሚካትት ይሆናል፡-

   ሀ) የአደጋውን መፈጠር እና የአደጋውን ባህሪይ ዓይነት፣

   ለ) አደጋው የደረሰብትን ጊዜ እና ቦታ፣

   ሐ) አደጋው የደረሰበት ሠራተኛ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር

መ) የአሠሪው ድርጅት ሙሉ ስም እና አድረሻ፣

ሠ) ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የህክምና እርዳታ ማግኘት ያለማግኘቱን፣ ካገኘ ሕክምና ያደረገለትን ሐኪም ስምና አድራሻ፤

5. አደጋው የሞት አደጋን የሚስከትል ሆኖ ሲገኝ በስልክ ወይም በማናቸውም ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች አደጋው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል።

ክፍል ስድስት

ስለ ህንጻ መጠቀሚያ ፍቃድ

82.የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ

1. በምድብ "ሐ" ስር ለሚካተቱ ህንፃዎች የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ በቅጽ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፤

2. የማመልከቻው ቅፅ በሕንፃው ባለቤት ወይም በህጋዊ ወኪሉ ወይም የመንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረት ከሆነ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጐ መቅረብ አለበት፤

3. ለሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚቀርብ የማመልከቻ ቅጽ፡-

ሀ) የግንባታውን ባለቤት ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ለ) ግንባታው የሚገኝበትን አድራሻ፣

ሐ) የህንፃውን የአገልግሎት ዓይነት፣

መ) የግንባታውን ፈቃድ ቁጥር፣

ሠ) ግንባታው የተጀመረበትንና የተጠናቀቀበትን ቀን፣እና

ረ) ህንጻው በጥላኑ መሠረት ስለመሠራቱ ቁጥጥሩን ያደረገው የተመዘገበ ባለሙያ ያረጋገጠበትን ማስረጃ ወይም በጥላኑ ወይም አርክቴክቸራል ዲዛይን መሰረት ስለመሰራቱ እና ርክክብ ስለመፈፀሙ በባለቤቱ በደብዳቤ የተሰጠ ማረጋገጫ፣ ማካተት አለበት፤

4. ለአዲስ ግንባታ ከማመልከቻው ቅፅ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች፡-

ሀ) የግንባታ ፈቃድ፣

ለ) የግንባታ ክትትል ደብተር፣

ሐ) ግንባታው መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ አማካሪ መሐንዲስና የሕንፃው ባለቤት የተፈራረሙበት የርክክብ ሠነድ፤ ወይም ርክክብ መፈረሙን ማረጋገጫ ደብዳቤ፣

መ) የጸደቀ አርክቴክቸራል ዲዛይን ቅጂ፣

ሠ) በክትትልና ቁጥጥር ስለማለፉ ከፋይሉ ጋር የሚቀርቡ ሠነዶች፣ ለክትትልና ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሠኝ ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

ረ) ግንባታው በክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ውስጥ ካላለፈ ክትትልና ቁጥጥር ከሚያደርገው የስራ ክፍል በህጉ መሰረት ተገቢውን ቅጣት ተቀጥቶ ሪፓርት/ ደረሰኝ ይዞ ማቅረብ አለበት፤

5. ለነባር ሕንፃ የአገልግሎት ለውጥ፣ ማስፋፋያ ወይንም ማሻሻያ በማድረግ ለሚቀርብ የመጠቀሚያ ፈቃድ፡-

ሀ) የቀድሞ የመጠቀሚያ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፣

ለ) የተፈቀዱ አርክቴክቸራል ፕላኖች

ሐ) በተፈቀደው ፕላን መሠረት መጠናቀቁን የሚገልፅ የርክክብ ሠነድ መቅረብ ይኖርበታል፤

6. ደረጃ በደረጃ ወይም በየምዕራፉ ለሚደረግ ግንባታ የደረጃ በደረጃ ፈቃድ፣ የመጀመሪያው ደረጃ መጠናቀቁን የሚገልጽ ተቆጣጣሪዎቹ በፊርማቸው ያረጋገጡበት ሠነድ መቅረብ ይኖርበታል፣ የመጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጠው ህንጻ ሹም ወይም የተሰየመው አካል የተጠናቀቀው የመጀመሪያ ደረጃ ግንባታ የመሪ ፕላኑን አነስተኛ የወለል ምጣኔ ወይም ዝቅተኛ ፋር መስፈርት መጠበቁን አረጋግጦ የመጠቀሚያ ፈቃድ መስጠት አለበት፤

7. በከፊል ተከናውኖ ለሚቀርብ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ጥያቄ የግንባታው ደረጃ ዝቅተኛውን የወለል ምጣኔ ያሟላ መሆን የሚገባው ሲሆን ፈቃዱ ለአገልግሎት ዝግጁ ለሆኑት ወለሎች ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፤

8. የህንፃ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት የግንባታ ፈቃድ አውጥተውም ሆነ ሳያወጡ የተጠናቀቀ ነባር ግንባታ ወይም "ልዩ ከግንባታ የተወሰደ" የመሪ ፕላኑን መስፈርት ባያሟላም የመጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ፣ የቦታውን ፕላን መረጃ እና

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

የተጠናቀቀውን ግንባታ ሙሉ የፀደቀ አርክቴክቸራል ንድፍ ለሚያቀርብ አመልካች ባለስልጣኑ ወይም ጽህፈት ቤቱ አጣርቶ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈል በማድረግ የነባር ግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤

9. ደረጃ በደረጃ ተፈቅዶ የሚገነባ ግንባታ እና/ወይም በከፊል ለተከናወነ ግንባታ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን እድሳቱም በየዓመቱ የሚከናወን ይሆናል፤

10. በህንጻ አዋጅ መሰረት የሕንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አስገዳጅ የሚሆነው ለምድብ "ሐ" ግንባታዎች ሲሆን ለምድብ "ሀ" እና ለምድብ "ለ" ግንባታዎች የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ መውሰድ አስገዳጅ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ተገልጋዩ አገልግሎቱን ከጠየቀ ቅድመ-ሁኔታዎችን አሟልቶ አገልግሎቱን ማግኘት ይችላል፤

11. ሙሉ በሙሉ ለተጠናቀቀ ግንባታ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላቱን በማረጋገጥ በየሁለት አመቱ የሚታደስ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፤

12. የስም ዝውውር የተደረገባቸው ይዞታዎች፤ በግንባታው ፕላን እና በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መካከል የስም ልዩነት ሲፈጠር የስም ዝውውር የተደረገበት ማስረጃ ወይም የግዥ ውል፣ የፍርድ ቤት ውሳኔ፣ የስጦታ ውል እንዲቀርብ በማድረግ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይሰጣል፤

13. ነባሩ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በአዲሱ በመሬት ይዞታ መረጃና ምዝገባ ተቋም በሚሰጠው ካርታ ሲተካ ምትክ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤ የቀረበው ፈቃድ የእድሳት ጊዜ ያለፈበት ከሆነ ፈቃዱ ታድሶ በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጥ ሲሆን ፈቃዱ የእድሳት ጊዜው ካላለፈበት ደግሞ የመህንዲስ አገልግሎት እንዲከፈል በማድረግ ምትክ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤

14. አክሲዮኖች ወይም ሪልእስቴቶች በእናት ካርታ የተገነባ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጠው የግንባታ ፈቃድ ባገኙበት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መሰረት ነው፤ አባላት በተናጠል በየወለሉ ተሰጥቷቸው ለሚያቀርቡት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች ግን በየወለሉ የተናጠል የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት

አይቻልም፡፡ ሆኖም ግን ህንጻው ጊዜው ያላበቃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ያለው ከሆነ በህንጻው ላይ የተናጠል ካርታ ያላቸው ተገልጋዮች ለሚፈልጉት አካል ህንጻው የመጠቀሚያ ፈቃድ ያለው መሆኑ ተገልጾ በደብዳቤ ሊጻፍላቸው ይችላል፤

15. በአንድ ይዞታ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ነባር ግንባታዎች አቀማመጥና በመካከላቸው ያለው ርቀት የግንባታ ፈቃድ መስፈርትን የማያሟሉ ከሆነ በተናጠል ለሚያሟላው ብሎክ ብቻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤ ሆኖም የግንባታ ፈቃድ መስፈርትን ባለማሟላቱ ምክንያት ውድቅ የተደረገው ብሎክ በንድፉ ላይ ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት ጋር በማመልከት በመጠቀሚያ ፈቃዱ የማይካተት መሆኑ በግልጽ መጠቀስ አለበት፤

16. የመጠቀሚያ ፈቃድ የቀረበበት የነባር ግንባታ የአርክቴክቸራል ንድፍ ወይም አስ ቢውልት ሙሉ በሙሉ መሬት ላይ ባለው የግንባታ ይዘት መሰረት ንድፉ መቅረብ አለበት፤ መሬት ላይ ባለው የግንባታ ይዘት መሰረት በትክክል መቅረቡን ለማጣራት ከሚደረገው ከመጀመሪያው የመስክ ጉብኝት ውጭ በትክክል ባለመቅረቡ በሚደረገው ለእያንዳንዱ ምልልስ ተጨማሪ ክፍያ በተመኑ መሰረት ይከፈላል፤

17. ከህንጻ አዋጅ በፊት የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ ተገንብተው ከተጠናቀቁ እና ይህን የሚያስረዳ ህጋዊ ማስረጃ የግንባታ ርክክብ ሰነድ፤ መንግስታዊ አገልግሎት ክፍያዎች፤ የኪራይ ውል ካቀረቡ የግንባታ ክትትል ደብተር እና የግንባታ ርክክብ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልጋቸው የፕላን ስምምነት፤ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፣ የግንባታ አርክቴክቸራል ፕላን ንድፍ ብቻ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተገቢ ክፍያዎችን ከፍለው አገልግሎት የሚያገኙ ይሆናል፤

18. የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይወስዱ ጥቅም ላይ የዋሉ ግንባታዎች ቅድመ-ሁኔታዎችን በማሟላት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፈቃድ እንዲያወጡ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሚሰጣቸው ሲሆን በማስጠንቀቂያው መሰረት ቀርበው ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፡፡ በተሰጠው ጊዜ ገደብ ፈቃድ ካላወጡ ህንጻው ለተጠቃሚው ደህንነት ስጋት እንዳለው ተቆጥሮ የንግድ ፈቃዱ እንዲታገድ እና ህንጻው በኪራይ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለሚመለከታቸው አካል/ተቋማት መረጃው ይተላለፋል፤

19. የመጠቀሚያ ፈቃድ የሚያስከለክሉ ምክንያቶች፡-

ሀ) ግንባታው ከፕላን ውጭ የተስፋፋ ከሆነ ወይም በተጓዳኝ የተገነቡ ግንባታዎች

ካለ፡ት፣

ለ) የመጠቀሚያ ፈቃድ መስፈረት የማያሟላ ከሆነ፣

ሐ) በግንባታ ውስጥ እና ውጭ የእሳት አደጋ መከላከያ ስርዓትን ያለማደራጀት እና የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ እና አቅጣጫ አመልካች ምልክቶች በተገቢው ቦታ ላይ አለመትከል ወይም አለመለጠፍ፣

መ) ከይዞታ ውጭ የተደረገ ማስፋፋት፣

ሠ) ግንባታ ላይ የዋለው ቁስ ባህሪ የአካባቢውን ነዋሪ ወይም የህንጻውን ተገልጋይ ወይም የአካካባቢውን ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚያውክ ወይም የሚገታ መሆን፤

20.የሕንፃ ሽ.ሙ ወይም የተሰየመው አካል ደህንነቱ አሰጊ አለመሆኑን ለተረጋገጠ እና በከፊል ለተጠናቀቀ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፤ በከፊል ለተጠናቀቀ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጥ የሚከተለ.ትን መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-

ሀ) ጥቅም ላይ ከሚውለ.ት የህንጻ ክፍሎች ውጭ ያለው የህንጻው ቀሪ አካል ግንባታ ስራ መቆሙን፣

ለ) ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት የህንጻ ወለሎች ደረጃቸው የድጋፍ መያዣ ሙ.ለ. ለሙ.ለ. መገጠማቸውን እና ያልተጠናቀቁ የህንጻው ፎቆች ጥቅም ላይ ለማዋል ከታሰቡት ለመለየት ጊዜያዊ ከለላ የተደረገላቸው ስለመሆኑ፣

ሐ) የህንጻው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከፍሳሽ ማስወገጃ ጋር መገናኘ.ቱን እና ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት መጸዳጃ ቤቶች ሙ.ለ. ለሙ.ለ. መጠናቀቃቸውን፣

መ) የህንጻው የውሃ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል ለታሰበው ሙ.ለ. ለሙ.ለ. መጠናቀቁንና ውሃ መዳረሱን፣

ሠ) የህንጻው የኤሌክትሪክ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል በታሰቡት ክፍሎች ላይ ሙ.ለ. ለሙ.ለ. መጠናቀቁን፣ መዳረሱን እንዲሁም ጥቅም ላይ የማይውለው የህንጻ ክፍል የኤሌክትሪክ አደጋ እንዳያዳርስ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረጉን፣

ረ) የህንጻው ያልተጠናቀቀ ክፍል ለማጠናቀቅ በሚደረገው ሂደት ህንጻውን በሚጠቀሙ እና በህንጻው በኩል በሚያልፉ መንገደኞች ላይ አደጋ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዩኒቲ ቢሮ Addis Ababa City Administration Unity Bureau

እንዳያደርስ መወሰድ የሚገባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች መወሰዳቸውን፣

ሰ) የህንፃው የእሳት አደጋ ጊዜ ማምለጫዎች መጠናቀቃቸውንና ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን፣

ሸ) ህንጻው ለአካል ጉዳተኞች ከእንቅፋት የጸዳ መዳረሻ መንገድ ገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ያደረገ መሆኑን፣

ቀ) የእሳት አደጋ መከላከያ ስፕሪክለር ካለው በአግባቡ መገጠሙንና መሰራቱን፣

በ) የህንጻው ለእሳት አደጋ መከላከያ የሚሆን ውሃ አቅርቦት ፓንፕ መገጠሙንና መሰራቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

21.አገልግሎቱ ያበቃ ወይም በወቅቱ ያልታደሰ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ እንደ ፈቃድ አያገለግልም፡፡

83.<u>የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ስለሚችልባቸው ምክንያቶች</u>

1. ግድፈት እያለበት በስህተት የፀደቀ ከሆነ፤
2. ተገልጋዩ ያቀረበው ማመልከቻ የተሳሳተ ወይም ሀሰተኛ መረጃ ከያዘ፤
3. ግንባታው የደህንነት ስጋት እንዳለበት በተጨባጭ ማስረጃ ተረጋግጦ ከቀረበ፤
4. የተሳሳተ የመስክ ሪፖርት በባለሙያ ከቀረበ፤
5. ግንባታው ከተፈቀደው ዲዛይን ውጭ ጥቅም ላይ ከዋለ የህንጻው መጠቀሚያ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ህንጻው አገልግሎት ላይ እንዳይውል የንግድ ፈቃዳቸው እንዲታገድ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይቻላል፡፡



ክፍል ሰባት

የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን

84.የውሃ አቅርቦት

1. ማንኛውም ህንጻ ለተገልጋዩ በቂና ንጹህ የውሃ አቅርቦት እንዲኖረው ተደርጎ መሰራት አለበት፤
2. በቂ የውሃ አቅርቦት እና ስርጭት ማለት ለእያንዳንዱ ሰው ለመጠጥ፣ ለገላ መታጠቢያ፣ ለልብስ እና መገልገያ እቃዎች ማጠቢያ፣ ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለመጸዳጃ ቤት አገልግሎት፣ ለአትክልት ማጠጫ የሚበቃ ሊሆን ይገባል፤
3. ለሰዎች አገልግሎት የሚውል የማንኛውም ህንጻ የውሃ አቅርቦት እና ጥራት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስታንደርዶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፤
4. ለምድብ "ሐ" ህንጻ ተጠቃሚዎች የሚውል የተጠቃሚውን ፍጆታ ሊያሟላ የሚችል የውሃ አቅርቦትና ለመጠባበቂያ የሚውል በቂ የውሃ መከማቻ ሊኖረው ይገባል፤
5. ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሚዘጋጁ የውሃ አቅርቦት መስመሮች ዲዛይኖች እና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ቁጠባዊ የውሃ አጠቃቀምን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፤
6. የውሃ መጠራቀሚያ ገንዳዎችና የስርጭት መስመሮች ለቁጥጥርና ለጽዳት ተደራሽ ሆነው መገንባት አለባቸው፤
7. የውሃ አቅርቦት ሳኔቴሽን የግንባታ እና ስርጭት ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች እና በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን መስፈርት ሊከናወን ይገባል።

85.የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ

1. አንድ ግንባታ በሚካሄድበት አቅራቢያ የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ካለ የከተማው መስተዳድር ወይም የሚመለከተው አካል በማስፈቀድ የሚገነባውን ሕንጻ የቆሻሻ መስመር ከአካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት ይችላለ፤
2. አንድ ግንባታ በአካባቢው የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከሌለ በግቢ ውስጥ ፍሳሽን ለማስወገድ ተቀባይነት ባለውና የሚመለከታቸውን አካላት መስፈርቶች እንዲያሟላ ተደርጎ መሰራት አለበት፤
3. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መሥመር በአዋሳኝ መንገድ ላይ የሚገኝ ከሆነ በአቅራቢያው ባለ ሌላ መንገድ ላይ ከሚገኝ መሥመር ጋር መገናኘት ይችላል፤

4. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ፍሳሹን ወደ አፈር ውስጥ እንዳይሰርግ ወይም እንዳያሳልፍ ሆኖ መገንባት አለበት፡፡

86. <u>ጎርፍ ውሀ ወይም የዝናብ ውሃ አወጋገድ</u>

1. ማንኛውም ባለይዞታ በግቢው ውስጥ የሚፈጠርን የዝናብ ውሀ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጎርፍ ውሀ ማስወገጃ መስመር ማገናኘት አለበት፤
2. ለጎርፍ አደጋ በተጋለጡ ቦታዎች የሚከናወን ግንባታ የጎርፍ መከላከያ ያለው ሆኖ መገንባት አለበት፤
3. ወሰን ተጠግቶ የሚሰራ ቤት ጣራ ፍሳሽ ወደራስ ይዞታ አቅጣጫ መሆን አለበት፤ የጣራውን ፍሳሽ ወደ ወሰንተኛው አቅጣጫ አድርጎ ለመገንባት ማንኛውንም የጣራ ፍሳሽና ጠፈጠፍ እንዲከላከል ተደርጎ ከተሰራ 60 ሳ.ሜ ከፍታ ባለው መሸፈኛ ግድግዳው ተከልሎ መሰራት አለበት፤
4. የዝናብ ውሀ አወጋገድ ሥርዓት ውሃው በቀላሉ ሊወገድ በሚችልበትና ውሃ በማያቁርበት ሁኔታ እና የወሰንተኛን ነባር ግንባታ ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ መገንባት አለበት፤
5. የዝናብ ውሃ ማስወገጃ በአዋሳኝ መንገድ ላይ ከሚገኝ ጎርፍ ማስወገጃ መረብ ጋር መገናኘት አለበት፤ሆኖም ከቦታው ተፈጥሯዊ ተዳፋት አንፃር የሚዘረጉ የፍሳሽ መስመሮች በመዳረሻ መንገድ በኩል ለማውጣት የማይቻል ከሆነ ፍሳሹ ሊሄድ በሚችልበት በኩል ባለ የተጎራባች ይዞታ አሳልፎ ማገናኘት ይቻላል፤ ይህም ፍሳሹን ተቀብለው ላሳለፈው ተጎራባች አመቺ በሆነ አቅጣጫ መሆን ያለበት ሲሆን ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የማይሄድ ከሆነ ስታንዳርዱን ጠብቆ በአመልካች ወይም አሳላፊው ወጪ ይገነባል፤ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የሚሄድ ከሆነ እያንዳንዱ ባለይዞታ የየራሱን ወጪ ይሸፍናል፤
6. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተጨማሪ ግንባታዎች በማድረግ ተዳፋቱን ወደ ራስ ይዞታ በኩልበመቀየር ወይም በጥልቀት በመቆፈር መስመሩን በራስ ይዞታ ላይ መዘርጋት ካልተቻለ በተጎራባች ይዞታ ማሳለፍ ይቻላል፤ ሆኖም በቦታው ልዩ የመሬት አቀማመጥና በአዋሳኝ ካሉት ነባር ግንባታዎች ነባራዊ ይዘት ምክንያት በተናጠል መታየት የሚኖርባቸውን ፍሳሽ መስመር ግንባታ ይዘት እና አቅጣጫ የህንፃ ሹሙ ውሳኔ ይሰጣል፡-

ሀ) ከ50 ሳ.ሜ በታች ሙሌት፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ባለሥልጣን

ለ) ከ150 ሳ.ሜ ጥልቀት እና ከ20 ሜትር ርዝመት በታች ቁፋሮ፣

7. አንድ ይዞታ ብቻ አቋርጦ ለሚሄድ የዝናብ ውሃ ፍሳሽ መስመር ቢያንስ በ20 ሳ.ሜ የኮንክሪት ቱቦ ወይም ቦይ መሰራት አለበት፤ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ ለሚሄድ የቱቦው መጠን እንደ ርዝመቱ የሚጨምር ይሆናል፤ ሆኖም መስመሩ በ2% ተዳፋት፣ በ40 ሳ.ሜ ጥልቀት እና በየ25 ሜትር ርዝመት ወይንም በማንኛውም የመስመር እጥፋት ላይ የመቆጣጠሪያ ገንዳ እንዲኖረው ሆኖ መሰራት አለበት፤
8. በተዳፋታማ ቦታ ላይ የሚገኙ ቤቶች የዝናብ ውኃን አንዱ ከሌላው ተቀብለው የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል፤
9. በዝናብ ውሃ መስመር ሌላ ቆሻሻ ፍሳሽ መልቀቅ አይፈቀድም፣ ከዝናብ ውሃ ጋር በሚመጣ ቆሻሻ ምክንያት መስመሩን የማጽዳት ሃላፊነት የአሳላፊው ሲሆን ተቀባዩ አሳላፊውን ለዚህ ጉዳይ ወደ ግቢው እንዲገባ የመፍቀድና የመስመሩን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

87.<u>ኢንዱስትሪ ዝቃጭ</u>

1. ማንኛውንም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ በቅድሚያ ሳይታከምና ጎጂ አለመሆኑ በሚመለከተው ሳይረጋገጥ ወደ ማንኛውም ፍሳሽ ማስተላለፊያ መለቀቅ የለበትም፤
2. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ የሚያመነጭ ተቋም ወይም ድርጅት አወጋገዱን በተመለከተ ለአካባቢ ባለሥልጣን ወይም ለሚመለከተው አካል ጥናቱን አቅርቦ ፈቀድ ማግኘት ይኖርበታል፤
3. የኢንዱስትሪ ዝቃጮችን ለማከምና ወደ ማንኛውም የፍሳሽ ማስወገጃ ለመልቀቅ፣ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፤
4. የኢንዱስትሪ ዝቃጮቹ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ መያዝና ጎጂነት ያላቸው ንጥረ ነገሮች ተጣርተው እና ታክመው መለቀቅ ይኖርበታል፤
5. ዝቃጭ የሚያመነጭ፣ ተቋማት በከተማው አስተዳደርና በሚመለከተው አካል የአካባቢ ብክለትን እንዳያስከትሉ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል።

88.<u>የውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ</u>

1. ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል መመሪያና ፈቃድ ውጭ ማንኛውም ሰው ውሃ አልባ ቆሻሻዎችን በየትኛውም ሥፍራና መስመር ማስወገድ ወይም እንዲወገድ ማድረግ የለበትም፤
2. የከተማው አስተዳደር ውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎችን የሕዝቡን ጤንነት

በጠበቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፤

3. ኬሚካል ወይም ዝግ ቆሻሻ ማስወገጃ በሚኖርበት ጊዜ ቆሻሻውን ከእቃው ለማስወገድ በአስተዳደሩ ተቀባይነት ባለው አወጋገድ ዘዴ መከናወን ይኖርበታል፡፡

89.<u>የእሳት ማጥፊያ ተከላ</u>

1. ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ለእሳት አደጋ መከላከል የሚረዱ መሣሪያዎች የሚተከሉበትን የሚያሳይ ፕላን መቅረብና በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፤
2. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች ተከላ በፕላኑና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት መከናወንና በተከላ ወቅትም ከትትል ሊደረግበት ይገባል፤
3. የመሣሪያዎቹ ተከላ እንደተጠናቀቀ ፍተሻ መደረግና መስራታቸው በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፤
4. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎቹ የጥራት ደረጃ በሚመለከተው አካል ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፤
5. በውኃ ለሚሠሩ የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች የውኃ ማከማቻ ሊኖራቸው ይገባል፤
6. የውኃ መስመር ደረጃውን በጠበቀ የውኃ ማስተላለፊያ ቧንቧ መዘርጋት ይኖርበታል፤
7. የውኃ ማጠራቀሚያ ጋኑም ሆነ መስመሮቹ ለቁጥጥር የሚያመቹ መሆን አለበት፡፡

90.<u>የእሣት መከላከያ የውሃ አቅርቦት</u>

1. የእሣት መከላከያ የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ በቅድሚያ ለከተማው አስተዳደር በማመልከቻ መጠየቅ አለበት፤
2. የከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ እስኪደርስ ድረስ ለትላልቅና ለምድብ "ሐ" ህንፃዎች መጠባበቂያ የሚሆን ከተገቢው መሣሪያ ጋር የውሃ አቅርቦት ሊኖር ይገባል፤
3. የተቋሞች ወይም ድርጅቶች የእሣት መከላከያ መሣሪያውና የውሃው አጠቃቀም ከከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ መስፈርቶችና ሕጐች ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባዋል፤
4. አስተዳዳሩ እሣት ለመከላል የሚቀርበውን የውሃ አቅርቦት ጥያቄ እንደ ህንፃው ዓይነት፣ ከፍታው የሕንፃው ስፋት መሠረት የውሃ አቅረቦትን ሊወስን ይችላል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ሪከርድና ማህደር

ክፍል ስምንት

የህንፃ ስጋት ደረጃ

91.የህንጻ ምድብ እና የስጋት ደረጃ

1. ለግንባታ ፈቃድ፣ የግንባታ ክትትልና የመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲረዳ 'ዝ'፣ 'መዝ'፣ 'መክ'፣ 'ክ' እና 'በክ' ተብለው የተሰየሙ የህንጻዎች የስጋት ደረጃ ምደባዎች ወጥተዋል፤
2. በዚህ አንቀጽ መሰረት ሁሉም ሕንፃዎች የህብረተሰብ ህይወት፤ የአካባቢ ደህንነትን፣ የኢኮኖሚ ተጽዕኖን እና ሌሎች በዚህ መመሪያ አባሪ ላይ የተመለከቱ ዝርዝር መለኪያዎችን መሰረት በማድረግ 'ዝ'፣ 'መዝ'፣ 'መክ'፣ 'ክ' እና 'በክ' ተብለው በተሰየሙ የሕንፃ ስጋት ደረጃዎች ምድብ ስር ይፈረጃሉ፤
3. በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ 'ዝ' እና 'መዝ' ስር የሚወድቅ ሕንፃ፡-
   ሀ) የጂኦቴክኒካል ጥናት ወይም የአፈር ምርመራ እና
   ለ) ለግንባታ ክትትል አላማ ድርጅት ወይም የተመዘገበ አማካሪ ባለሙያ መቅጠር አይጠበቅበትም፤
4. በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ 'ዝ' ስር የሚወድቅ ሕንፃ በባለስልጣኑ የሚደረግ መደበኛ ክትትል አይመለከተውም፤
5. በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ 'መዝ' እና 'መክ' ምድብ ስር የሚወድቅ ሕንፃ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ
   ሀ) የመሰረት ስራ ሲሰራ እና
   ለ) ከሀገር ደህንነት ጋር በተያያዘ የህንጻ አዋጁ ተፈጻሚ እንዳይሆንበት በሚንስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ህንጻ መደበኛ ክትትል አይመለከተውም፤
6. በህንጻ ስጋት ደረጃ ምድብ 'ዝ'፤ እና 'መዝ' ስር ለሚወድቁ ሕንፃዎች የዲዛይን ወይም ፕላን ማስፀደቅ ማመልከቻዎች የአፈር ምርመራ ማስረጃ አይቀርብም።

92.የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ

1. ከኢትዮጵያ ውጪ ተሰርተው የሚቀርቡ ዲዛይኖች በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ህጎች እና መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፤
2. በአማካሪ ድርጅት የሚቀርብ አርክቴክቸራል ዲዛይን የአርክቴክቸራል ዲዛይን እርማት መስጫ በዚህ መመሪያ መሰረት በማድረግ መሰራቱን የድርጅቱን

ማህተም በማድረግ አረጋግጦ ያቀርባል፤

3. የተሰጠውን እርማት ያልተቀበለ አማካሪ ዲዛይኑን የመረመረው ባለሙያ ጋር በመቅረብ ተጨማሪ ማብራሪያ ወይንም አስተያየት መጠየቅና መረዳት ይችላል፤ እርማት የሰጠውም ባለሙያ ያልተሟላውን የመዋቅራዊ ፕላን፣ የሕንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ወይንም የኢትዮጵያ ህንጻ ደረጃዎችን በመግለፅ በፅሁፍ መልስ ይሰጣል፤
4. የቁፋሮ ጥልቀታቸው ከ3.50 ሜትር በላይ ለሆኑ ግንባታዎች የአፈር መከላከያን በተመለከተ አማካሪ ድርጅቱ የግንባታ ቦታውን እና በዙሪያው ያሉ ግንባታዎችን ታሳቢ ያደረገ የመከላከያ አይነት ጥናትና ንድፍ ለባለስልጣኑ ያቀርባል፤ ባለስልጣኑም የቀረበውን ገምግሞ ያጸድቃል።

93. <u>የግንባታ ክትትል እና ቁጥጥር</u>

በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶች ቢኖሩም ማንኛውም የግንባታ የመጀመሪያ እርከን ማሳወቂያ አገልግሎት የሚፈልግ ሰው ወይም አካል ለህንጻ ስጋት ደረጃ ምድብ 'ዝ' እና 'መዝ' የግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ መቅጠር አይኖርበትም፤

94. <u>መደበኛ ክትትል</u>

1. ከግል መኖሪያ ቤት ውጭ ያለ ግንባታን የሚመለከት ሆኖ ማንኛውም በምድብ "ለ" እና "ሐ" የሚገኝ ሕንፃ ግንባታ ለመገንባት የሚያስችል የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የየሥራው እርከን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስታወቂያ የሥራ እርከኑን ከመጀመሩ ከ5 የሥራ ቀናት በፊት የሚሰጠውን ቅጽ በመሙላት ማቅረብ ይኖርበታል፤
2. ማንኛውም በስጋት ደረጃ 'ዝ' ምድብ ስር የሚወድቅ ሕንጻ የግንባታ ስራ መደበኛ ክትትል አይደረግበትም፤
3. ማንኛውም በስጋት ደረጃ 'መዝ' እና 'መከ' ምድብ ስር የሚወድቅ ሕንጻየግንባታ ስራ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ መደበኛ ክትትል የሚደረግበት ለሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን ይህም፤
   ሀ) የመሰረት ስራ ሲከናወን እና፣
   ለ) የመሰረት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚፈፀም ይሆናል፣
4. ማንኛውም በስጋት ደረጃ 'ከ' እና 'በከ' ምድብ ስር የሚወድቅ ሕንጻ በዚህ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሪከርድና ማህደር

አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተቀመጠው መደበኛ የህንጻ እርከን ክትትል የሚደረግበት ይሆናል፤

5. በግንባታ ወቅት ለሚደረጉ ጥቃቅን የዲዛይን ማሻሻያዎች የግንባታ አማካሪው ለተሻሻለው ንድፍ/ሰነድ በማቅረብ ወይም የክትትል ባለሙያው በመስክ ደብተሩ ላይ ማስታወሻ በማስፈር እንዲቀጥሉ ይደረጋል፤ ማሻሻያዎቹ የሚከተሉት መርሆችንና መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል፤

ሀ) ከግንባታ ፈቃድ ህግጋት ጋር የተጣጣመ መሆን፤

ለ) ከተፈቀደው የግንባታህላፊነት እየወሰደና ክትትል ለሚያደርገው ባለሙያ ወይም የስራ ክፍል በጽሁፍ ሰነድ አንፃር ተደራራቢ የመዋቅር እና የይዘት ለውጥ ሊያስከትል የማይችል መሆኑን ማረጋገጥ፡

ሐ) በተገቢው ሁኔታ መመዝገብና ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላም የዲጂታል አዝ-ቢዩልት ንድፎች እና የግንባታ ቦታ ማህደሩ የመጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻው አካል ሆነ፣

መ) የግንባታ ቁስ የኮንክሪት እና የብረት ፍተሻና ምርመራ የግንባታ ክትትል ሂደት አንድ ክፍል እና የመጨረሻ ሰነዱ አካል ይሆናል፤

6. የሚከተሉት ለውጦች እንደ ጥቃቅን ማሻሻያ የሚቆጠሩ ይሆናል፡-

ሀ) የብረት ቁጥርና አይነትን የጠበቀ የአደራደር ስፋት ለውጥ፣ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ የብረት አይነት ለውጥ፣

ለ) የህንጻ ከፍታ ወሰኑን የጠበቀ ተመጣጣኝ የወለል (ስላብ) አይነት ለውጥ፤

ሐ) የቁፋሮ ጥልቀት ፣

መ) የአፈር መከላከያ ዲዛይን ለውጥ፣

- አደጋው የሞት አደጋን የሚስከትል ሆኖ ሲገኝ በስልክ ወይም በማናቸውም ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች አደጋው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፣

ክፍል አራት

1. የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ

1.1. በምድብ"ሐ" ስር ለሚካተቱ ህንፃዎች የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ በቅጽ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

1.2. የማመልከቻው ቅፅ በሕንፃው ባለቤት ወይም በህጋዊ ወኪሉ ወይም የመንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረት ከሆነ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጐ መቅረብ አለበት፣

1.3. ለሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚቀርብ የማመልከቻ ቅጽ፡-

ሀ) የግንባታውን ባለቤት ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ለ) ግንባታው የሚገኝበትን አድራሻ፣

ሐ) የህንፃውን የአገልግሎት ዓይነት፣

መ) የግንባታውን ፈቃድ ቁጥር፣

ሠ) ግንባታው የተጀመረበትንና የተጠናቀቀበትን ቀን፤

ረ) ህንጻው በፕላኑ መሠረት ስለመሠራቱ ቁጥጥሩን ያደረገው የተመዘገበ ባለሙያ ያረጋገጠበትን ማስረጃ ወይም በፕላኑ መሰረት ስለመሰራቱ እና ርክክብ ስለመፈፀሙ በባለቤቱ በደብዳቤ የተሰጠ ማረጋገጫ፣ ማካተት አለበት።

1.4. ከማመልከቻው ቅፅ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች፡-

1.4.1. ለአዲስ ግንባታ (እድሳት)፣

ሀ) የግንባታ ፈቃድ፤

ለ) የግንባታ ክትትል ደብተር፤

ሐ) ግንባታው መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ አማካሪ መሐንዲስና የሕንፃው ባለቤት የተፈራረሙበት የርክክብ ሠነድ/ ወይም ርክክብ መረፀሙን ማረጋገጫ ደብዳቤ፤

መ) ህንጻው የፕላን ማሻሻል ወይም ለውጥ ከተደረገ የተሻሻለውን አካቶ የተዘጋጀ ወይም የተከለሰ ፕላን ቅጂ፣

ሠ) በክትትልና ቁጥጥር ስለማለፉ ከፋይሉ ጋር የሚቀርቡ ሠነዶች፣ ለክትትልና ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ የከፈለበት ደረሠኝ ተያይዞ መቅረብ አለበት። ግንባታው በክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ውስጥ ካላለፈ ክትትልና ቁጥጥር ከሚያደርገው የስራ ክፍል /ዳይሬክቶሬት ወይም ቡድን/ በህጉ መሰረት ተገቢውን ቅጣት ተቀጥቶ ሪፖርት/ ደረሰኝ ይዞ ማቅረብ አለበት፤

1.4.2. ለነባር ሕንፃ ያገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት በማድረግ ለሚቀርብ የመጠቀሚያ ፈቃድ፣

ሀ) የአገልግሎት ለውጥ ፈቃድ የፕላን ስምምነት፣

ለ) ለአገልግሎት ለውጥ የተፈቀዱ ፕላኖች

ሐ) በተፈቀደው ፕላን መሠረት መጠናቀቁን የሚገልፅ የርክክብ ሠነድ/ ርክክብ በወቅቱ መደረጉን የሚገልጽ ደብዳቤ መቅረብ ይኖርበታል።

1.5. ደረጃ በደረጃ ወይም በየምዕራፉ ለሚደረግ ግንባታ የደረጃ በደረጃ ፈቃድ፣ የመጀመሪያው ደረጃ መጠናቀቁን የሚገልጽ ተቆጣጣሪዎቹ በፊርማቸው ያረጋገጡበት ሠነድ መቅረብ ይኖርበታል፣ የመጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጠው ህንጻ ሹም ወይም የተሰየመው አካል የተጠናቀቀው የመጀመሪያ ደረጃ ግንባታ የመሪ ፕላኑን አነስተኛ የወለል ምጣኔ (Min-FAR) መስፈርት መጠበቁን አረጋግጦ የመጠቀሚያ ፈቃድ መስጠት አለበት፤

1.6. በከፊል ተከናውኖ ለሚቀርብ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ጥያቄ የግንባታው ደረጃ ዝቅተኛውን የወለል ምጣኔ ያሟላ መሆን የሚገባው ሲሆን ፈቃዱ ለአገልግሎት ዝግጁ ለሆኑት ወለሎች ብቻ የሚሰጥ ይሆናል፤

1.7. የህንፃ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት የግንባታ ፈቃድ አውጥተውም ሆነ ሳያወጡ የተጠናቀቀ ነባር ግንባታ ወይም "ልዩ ከግንባታ የተወሰደ" የመሪ ፕላኑን መስፈርት ባያሟላም የመጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ ፎርም በመሙላት የቦታውን ፕላን መረጃ እና የተጠናቀቀውን ግንባታ ሙሉ የፀደቀ አርክቴክቸራል ንድፍ እንዲቀርብ በማድረግ የአገልግሎት ክፍያ ከፍሎ የነባር ግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤

1.8. ደረጃ በደረጃ ተፈቅዶ የሚገነባ ግንባታ እና/ወይም በከፊል ለተከናወነ ግንባታ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን እድሳቱም በየዓመቱ የሚከናወን ይሆናል፤

1.9. ደረጃ በደረጃ ወይም በከፊል ለተጠናቀቁ የህንጻዎች የሚሰጥ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ/ዕድሳት፤ ግንባታው የቀረው የማጠናቀቂያ /Finishing/ ስራ፣ የሊፍት ገጠማ፤ የአደጋ ጊዜ ማምለጫ እና በፕላን ማሻሻያ ተካተው ሊፈቀዱ የሚችሉ መጠነኛ ተጓዳኝ ስራዎች ብቻ ከሆነ ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ፈቃድ/የዕድሳት አገልግሎት ያገኛል፤

1.10. በህንጻ አዋጅ መሰረት የሕንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አስገዳጅ የሚሆነው ለምድብ "ሕ" ግንባታዎች ሲሆን ለምድብ "ሀ" እና ለምድብ "ለ" ግንባታዎች የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ መውሰድ አስገዳጅ አይደለም፤

1.11. ሙሉ በሙሉ ለተጠናቀቀ ህንጻ (የህንጻ ግንባታ ስራ እስከ ማጠናቀቂያ ስራዎች፣ የፍሳሽ፣ የኤሌክትሪክ፣ የአደጋ መከላከያና ማምለጫ፣ አሳንሰር፣ የአካል ጉዳታኛ መወጣጫ Ramp፣ የደረጃ handrail፣ ... ወዘተ በተሟላ መልኩ ዲዛይኑን ጠብቆ የተሰራ ህንጻ) በየአራት አመቱ የሚታደስ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጠዋል።

1.12. የስም ዝውውር የተደረገባቸው ይዞታዎች፤ በግንባታው ፕላን እና በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መካከል የስም ልዩነት ሲፈጠር የስም ዝውውር የተደረገበት ማስረጃ (የግዥ ውል፣ የፍ/ቤት ውሳኔ፣ የስጦታ...ወዘተ) እንዲቀርብ በማድረግ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይሰጣል፤

1.13. ነባሩ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በአዲሱ በመሬት ይዞታ መረጃና ምዝገባ ተቋም በሚሰጠው ካርታ ሲተካ ምትክ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል። የቀረበው ፈቃድ የእድሳት ጊዜ ያለፈበት ከሆነ ፈቃዱ ታድሶ በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጥ ሲሆን ፈቃዱ የእድሳት ጊዜው ካላለፈበት ደግሞ የመሀንዲስ አገልግሎት እንዲከፈል በማድረግ ምትክ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤

1.14. አክሲዮኖች/ሪልእስቴቶች...ወዘተ በእናት ካርታ የተገነባ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጠው የግንባታ ፈቃድ ባገኙበት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መሰረት ሲሆን አባላት በተናጠል በየወለሉ ተሰጥቷቸው ለሚያቀርቡት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታዎች ግን በየወለሉ የተናጠል የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት አይቻልም። ሆኖም ግን ህንጻው ጊዜው ያላበቃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ያለው ከሆነ በህንጻው ላይ የተናጠል ካርታ ያገኙ ተገልጋዮች ለሚፈልጉት አካል ህንጻው የመጠቀሚያ ፈቃድ ያለው መሆኑ ተገልጾ በደብዳቤ ሊጻፍላቸው ይችላል።

1.15. ለህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የግንባታ ክትትል ማስረጃዎች ወይም የግንባታ ክትትል ቅጣት አፈጻጸም የህንጻ አዋጅ 624/2001ን ለማስፈፀም በወጡ የህንጻ ደንብ 243/2003 እና የህንጻ መመሪያ ቁጥር 5/2003፣ መመሪያ ቁጥር 2/2010፣ መመሪያና ስታንዳርድ ቁጥር 3/2015 ከግምት ያስገባ ሆኖ በግንባታ ክትትል ዳይሬክቶሬት/ ቡድን መፈፀሙን ማገናዘብ ያስፈልጋል፤

1.16. ከህንጻ አዋጅ 624/2001 በፊት የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ የተገነቡ ግንባታዎች የግንባታ ክትትል ደብተር እና የግንባታ ርክክብ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልጋቸው የጥላን ስምምነት፤ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፣ የግንባታ አርክቴክቸራል ጥላን ንድፍ ብቻ እንዲያቀርቡ በማድረግ ተገቢ ክፍያዎችን ከፍለው አገልግሎት የሚያገኙ ይሆናል፤

1.17. የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳይወስዱ ጥቅም ላይ የዋሉ ግንባታዎች ቅድመ-ሁኔታዎችን በማሟላት በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ፈቃድ እንዲያወጡ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሚሰጣቸው ሲሆን በማስጠንቀቂያው መሰረት ቀርበው ፈቃድ መውሰድ ይገባቸዋል። በተሰጠው ጊዜ ገደብ ፈቃድ ካላወጡ ህንጻው ለተጠቃሚው ደህንነት ስጋት እንዳለው ተቆጥሮ የንግድ ፈቃዱ እንዲታገድ እና ህንጻው በኪራይ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለሚመለከታቸው አካል/ተቋማት መረጃው ይተላለፋል፤

1.18. የመጠቀሚያ ፈቃድ የሚያስከለክሉ ምክንያቶች፡-

1.18.1. ግንባታው ከጥላን ውጭ የተስፋፋ ከሆነ ወይም በተጓዳኝ የተገነቡ ግንባታዎች ካሉት፤

1.18.2. የመጠቀሚያ ፈቃድ መስፈረት የማያሟላ ከሆነ፤

1.18.3. በግንባታ ውስጥ እና ውጭ የእሳት አደጋ መከላከያ ስርዓትን ያለማደራጀት እና የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ እና አቅጣጫ አመልካች ምልክቶች በተገቢው ቦታ ላይ አለመትከል ወይም አለመለጠፍ፤

1.18.4. ከይዞታ ውጭ የተደረገ ማስፋፋት፤

1.18.5. ግንባታ ላይ የዋለው ቁስ ባህሪ የአካባቢውን ነዋሪ ወይም የህንጻውን ተገልጋይ ወይም የአካካባቢውን ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚያውክ ወይም የሚገታ መሆን፤

1.19. የሕንፃ ሹሙ ወይም የተሰየመው አካል ደህንነቱ አሰጊ አለመሆኑን ለተረጋገጠ እና በከፊል ለተጠናቀቀ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል። በከፊል ለተጠናቀቀ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጥ የሚከተሉትን መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

1.19.1. የህንጻው ዝቅተኛ የወለል ምጣኔ ስትራክቸራል ፍሬም መሰራቱ እና ጥቅም ላይ ለማዋል የታቀደው እርከን ለአገልግሎት ዝግጁ መሆኑ፤

1.19.2. ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት የህንጻ ወለሎች ደረጃቸው የድጋፍ መያዣ ሙሉ ለሙሉ መገጠማቸውን እና ያልተጠናቀቁ የህንጻው ፎቆች ጥቅም ላይ ለማዋል ከታሰቡት ለመለየት ጊዜያዊ ከለላ የተደረገላቸው ስለመሆኑ፤

1.19.3. የህንጻው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከፍሳሽ ማስወገጃ ጋር መገናኘቱን እና ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት መጸዳጃ ቤቶች ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቃቸውን፤

1.19.4. የህንጻው የውሃ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል ለታሰበው ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁንና ውሃ መዳረሱን፤

1.19.5. የህንጻው የኤሌክትሪክ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል በታሰቡት ክፍሎች ላይ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁን መዳረሱን እንዲሁም ጥቅም ላይ የማይውለው የህንጻ ከፍል የኤሌክትሪክ አደጋ እንዳያዳርስ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረጉን፤

1.19.6. ህንጻው ለአካል ጉዳተኞች ከእንቅፋት የጸዳ መዳረሻ መንገድ ገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ያደረገ መሆኑን፤

1.19.7. የእሳት አደጋ መከላከያ ስፕሪክለር ካለው በአግባቡ መገጠሙንና መስራቱን በማረጋገጥ፤

1.19.8. የህንጻው ለእሳት አደጋ መከላከያ የሚሆን ውሃ አቅርቦት እና የውሃ ፓንፕ መገጠሙንና መሰራቱን ማረጋገጥ ይኖርበቸዋል፤

1.20. አገልግሎቱ ያበቃ ወይም በወቅቱ ያልታደሰ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ እንደ ፈቃድ አያገለግልም፤

1.21. የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ሊታገድ እና/ ወይም ሊሰረዝ የሚችልባቸው ምክንያቶች፡-

1.21.1. ግድፈት እያለበት በስህተት የፀደቀ ከሆነ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፤

1.21.2. ተገልጋዩ ያቀረበው ማመልከቻ የተሳሳተ ወይም ሀሰተኛ መረጃ ከያዘ፤

1.21.3. ግንባታው የደህንነት ስጋት እንዳለበት በተጨባጭ ማስረጃ ተረጋግጦ ከቀረበ፤

1.21.4. የተሳሳተ የመስክ ሪፖርት በባለሙያ ከቀረበ፤

1.21.5. ግንባታው ከተፈቀደው ዲዛይን ውጭ አገልግሎት ላይ ከዋለ፤ የህንጻው መጠቀሚያ ፈቃድ ሊታገድ እና/ወይም ሊሰረዝ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ እንደ አስፈላጊነቱ ህንጻው አገልግሎት ላይ እንዳይውል የንግድ ፈቃዳቸው እንዲታገድ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ ይቻላል።

ሰንጠረዥ-5- የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የአገልግሎት ስታንዳርድ

ተ.ቁ	አገልግሎት	የሚወስደው ጊዜ	ምርመራ
1.	ሙሉ ለሙሉ ለተጠናቀቀ ህንጻ የሚሰጥ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ	7	የተሟላ መረጃ ከቀረበ
2.	ደረጃ በደረጃ/ በከፊል ለተከናወነ ህንጻ የሚሰጥ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ	7	የተሟላ መረጃ ከቀረበ

ክፍል አምስት

1.1. የአገልግሎት ክፍያና ቅጣት

1.2. የአገልግሎት ክፍያዎች

1.2.1. የፕላን ስምምነትና የግንባታ ፈቃድ ክፍያ

1) የፕላን ስምምነት ለማግኘት ጥያቄ ሲቀርብ ብር 300.00 የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ስምምነቱ ይሰጣል።
2) ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።
3) ለግንባታ ጥቅም ላይ የሚውሉት ፕላኖች በከተማው አስተዳደር ተዘጋጅተው የሚሰጡ ስታንዳርድ ፕላኖች ከሆኑ ፕላኖቹን ለማግኘት የሚፈጸመው ክፍያ እንደ ፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይቆጠራል።
4) የኘላን መገምገሚያ ክፍያ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሠረት የሚሰላ ሲሆን የፕሮጀክት ግምት የሚሰላው የሕንጻዎቹን ጠቅላላ የወለል ስፋት በካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ በማባዛት ይሆናል።

ሰንጠረዥ 6-፥ ለየፕሮጀክት ግምት የሚከፈል የፕላን መገምገሚያ ክፍያ አቀራረብ

ተ.ቁ	የፕሮጀክት ግምት /በብር/	የፕላን መገምገሚያ ክፍያ
1	እስከ 2,500,000	የፕሮጀክቱን ግምት(1/2000)
2	2,500,000 እስከ 5,000,000	1,250+{1/2500(የፕሮጀክቱን ግምት- 2,500,000)}
3	5,000,000 እስከ 10,000,000	2,250+{1/3000(የፕሮጀክቱን ግምት-5,000,000)}
4	10,000,000 እስከ 20,000,000	3,920+{1/3500(የፕሮጀክቱን ግምት- 10,000,000)}
5	20,000,000 እስከ 50,000,000	6,770+{1/4000(የፕሮጀክቱን ግምት- 20,000,000)}
6	ከ50,000,000 በላይ	14,270+{1/5000(የፕሮጀክቱን ግምት- 50,000,000)}

5) የሕንጻ ሹም ከሚመለከተው ተቋም በሚያቀርብለት ወቅታዊ የግንባታ የዋጋ ጥናት በመነሳት ለፕሮጀክት ግምት ስሌት የሚሆን የየህንጻ ምድቡን የካሬ ሜትር ዋጋ በማዘጋጀት ለከተማው አስተዳደር ወይንም ለተሰየመው አካል አቅርቦ ያፀድቃል። የተዘጋጀው የካሬ ሜትር ዋጋ እንደ አስፈላጊነቱ ሊከለስ ይችላል።
6) ለፕላን ግምገማ የቀረቡ የሕንፃ አሀዶች ተመሳሳይ ከሆኑ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ የሚሰላው የአንዱን ሕንፃ የግንባታ ሙሉ ዋጋ እና የሌሎቹን አሀዶቹ ጠቅላላ የግንባታ ዋጋ 10 በመቶ በመደመር ይሆናል።
7) ውድቅ የሆኑ ፕላኖች ተስተካክለው እንደገና ለማፀደቅ በሚቀርቡበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያው ክፍያ፡-ሀ) ለምድብ "ሀ" ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ ግማሽ፣ ለ) ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ 25 በመቶ ይሆናል።
8) ፕላኑ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ቀደም ሲል ይኸው ፕላን ውድቅ በተደረገበት ጊዜ ሳይታይ በታለፈ ግድፈት ምክንያት ከሆነ ተስተካክሎ የሚቀርበውን ፕላን ለመገምገም ክፍያ አይጠየቅም።

9) የፕላን ማሻሻያ ክፍያ ስትራክቸራል ፕላኑን እንዲለውጥ የሚያስገድድ ከሆነ ክፍያው በአዲስ ፕላን መገምገሚያ አከፋፈል መሠረት ይሆናል። ለሌሎች የፕላን ማሻሻያዎች የሚከፈለው የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ለአዲስ ፕላን መገምገሚያ የሚጠየቀው ክፍያ 25 በመቶ ይሆናል። የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ፥ለሁሉም የሕንፃ ዓይነቶች የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ መጠን ለፕላን መገምገሚያ የተከፈለው ክፍያ 10 በመቶ ይሆናል።

1.2.2. **የቁጥጥር ክፍያ**

1.2.2.1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5.1.35 መሠረት ማስታወቂያ ለቀረበባቸው የምድብ "ለ" እና "ሐ" ሕንፃዎች የሥራ እርከን ለሚደረግ ጉብኝት ወይም ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል።

1.2.2.2. የክትትል የአገልግሎት ክፍያ መደበኛ ክትትል ለሚደረግባቸው የሥራ እርከኖች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ በመሆኑ ተጨማሪ ክትትል እንዲደረግ በሚጠይቅ የግንባታ ደረጃ ተጨማሪ ክፍያ አይጠየቅም።

1.2.2.3. በቁጥጥር ማስታወቂያ ከቀረበባቸው የሥራ እርከኖች ውጪ ለሚደረግ ድንገተኛ የቁጥጥር ጉብኝት የቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ አይፈጸምባቸውም።

1.2.2.4. ለሕንፃ ግንባታ የሚደረግ የቁጥጥር ሥራ በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 16.3 ለተመለከቱት ሕንፃዎች በተቀመጡት የሥራ ደረጃዎች መሠረት ይሆናል።

1.2.2.5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 4 በተመለከተው መሠረት ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየምድቡ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ፥

(ሀ) ለምድብ ለ/ ህንፃ ብር 400፣

(ለ) ለምድብ ሐ/ ህንፃ ብር 800 ይሆናል።

1.2.2.6. ለማንኛውም ግንባታ የቁጥጥር ክፍያ የሚፈፀመው ቁጥጥር የሚደረግበትን የሥራ እርከን ለመጀመር ገንቢው የግንባታ ሥራ ማስታወቂያ ቅጽ 025 ሲያቀርብ ይሆናል።

1.2.2.7. የቁጥጥር አገልግሎት ክፍያው የተፈጸመበት ማስረጃ ወይም ደረሰኝ ቅጂ በግንባታ ፈቃድ ፋይል ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ ይኖርበታል።

1.2.2.8. የቁጥጥር ክፍያ የሚፈፀመው በፋይናንስ ሰርዓት ደንብና መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት ይሆናል፣ ከዚህ ውጭ የሚፈፀሙ ክፍያዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

1.2.3. **የዕድሳት፣ ጊዜያዊ ግንባታና የማፍረሻ ፈቃድ እና የመሃንዲስ አገልግሎት ክፍያ**

1.2.3.1. የመሃንዲስ አገልግሎት፣ የዕድሳት፣ ጊዜያዊ ግንባታና የማፍረሻ ፈቃድ በሚካሄድበት ወለል ስፋት ድምር የሚከፈል ይሆናል።

1.2.3.2. የእድሳት ፈቃድ በንዑስ አንቀፅ 2.14 በተገለፀው የዕድሳት ደረጃዎች መሰረት ለደረጃ አንድ እና ሁለት ብቻ የእድሳት አገልግሎት ክፍያ የሚከፈል ሲሆን ለደረጃ ሶስት ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም።

1.2.3.3. የዕድሳት፣ ጊዜያዊ ግንባታና የማፍረሻ ፈቃድ በተከፈለበት አገልግሎት ላይ ተጨማሪ የመሃንዲስ አገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም።

1.2.3.4. የመሃንዲስ አገልግሎት፣ የዕድሳት፣ ጊዜያዊ ግንባታና የማፍረሻ ፈቃድ ክፍያ በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት በተጠቀሰው የወለል ስፋት መሰረት ይሆናል።

ሰንጠረዥ -7-፥ በይዞታ ስፋት መሰረት የሚከፈል የመሃንዲስ አገልግሎት፣

ተ.ቁ	የይዞታ ስፋት መጠን (ሜትር ካሬ)	የክፍያ ተመን (ብር)
۱	እስከ ۱۰۰	500
2	۱۰۱- 500	۱000
3	501- ۱000	2000
4	۱001-3000	3000
5	3001-7000	5000
6	7001-۱0000	7000
7	۱0001-50000	۱0000
8	50001-۱00000	۱5000
9	ከ۱00001 በላይ	20000
۱0	የፍርድ ቤት ምላሽ አገልግሎት	በነጻ
۱۱	አቤቱታ	በነጻ

1.2.4. **የመጠቀሚያ ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ**

የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የአገልግሎት እና የመሀንዲስ አገልግሎት ክፍያዎች

ሰንጠረዥ፡-8-የአገልግሎት ክፍያ እና የመሀንዲስ የመስክ አገልግሎት ክፍያ

ተ.ቁ	የአገልግሎት ክፍያ አይነት	መለኪያ	የአገልግሎት ክፍያ ተመን በብር	
۱.	የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ	በካሬ ሜትር	ለመኖሪያ (አፓርትመንት)፤ ለቅይጥ ህንጻዎች፣ የአስተዳደር ህንጻዎች፣ እና ተመሳሳይ ህንጻዎች የአንድ ካሬ ዋጋ ۱2,200 ብር ጥቅል ግምቱ ተሰርቶ ክፍያው በህንጻ መመሪያ ቀመር መሰረት ይሆናል (ከታች በሰንጠረዥ---ባለው መሰረት ይሰላል)	
		በካሬ ሜትር	ለሆስፒታል፣ ለፋብሪካዎች፣ ለማከማቻ (እስቶሮች) እና ተመሳሳይ ህንጻዎችን የአንድ ሜትር ካሬ ዋጋ 20,000 ብር ጥቅል ግምቱ ተሰርቶ ክፍያው በህንጻ መመሪያ ቀመር መሰረት ይሆናል። (ከታች በሰንጠረዥ---ባለው መሰረት ይሰላል)	
2.	የመሀንዲስ አገልግሎት ክፍያ	በጥቅል ግምት (በብር)	**ጥቅል ግምት (በብር)**	**የክፍያ ተመን (በብር)**
			እስከ ۱0ሚ	۱,600
			ከ۱0ሚ እስከ 20ሚ	2,000
			ከ20ሚ እስከ 50ሚ	2,500
			ከ50ሚ እስከ ۱00ሚ	3,000
			ከ۱00ሚሎዮን በላይ	5,000
3	የህንጻ አገልግሎት ለውጥ	በብር	۱0,000	

ሰንጠረዥ፡-9- በፕሮጀክት ጥቅል ዋጋ ዝርዝር መሰረት የሚከፈል የመጠቀሚያ ፈቃድ ክፍያ (የስሌት ቀመር)

የኘሮጀክት ጥቅል ዋጋ /በብር/ ገደብ	**የመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ /ብር/**		
	የኘሮጀክት ዋጋ /በብር/	**የመጠቀሚያ ፈቃድ ክፍያ ስሌት (ቀመር)**	**የክፍያ መጠን ጣሪያ**
up to 2,500,000	2,500,000	project cost*۱/2000	۱250
2,500,000+_5,000,000	5,000,000	۱250+((project cost-2500000)/2500)	2250
5,000,000+_۱0,000,000	۱0,000,000	2250+((project cost-5,000,000)/4000)	3500
۱0,000,000+_20,000,000	20,000,000	3500+((project cost-۱0000000)/6000)	5347
20,000,000+_50,000,000	50,000,000	5350+((project cost-20000000)/8000	9۱00
50,000,000 and above	۱00,000,000	9۱00+((project cost-50000000)/۱0000)	۱4۱00

1.3. ተመላሽ ክፍያዎች

1.3.1. ተመላሽ ክፍያ የሚባለው አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ወይም ክፍያ የተፈፀመበት አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ወይም አገልግሎቱ ከሚጠይቀው በትርፍነት የተከፈለ ክፍያ ነው።

1.3.2. አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ እንዲመለስለት የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን ክፍያው የተፈጸመበትን የአገልግሎት ዓይነት እና ክፍያው ተመላሽ እንዲሆን የተጠየቀበትን ምክንያት በመግለጽ ክፍያ ከተፈጸመበት ደረሰኝ ኮፒ ጋር በማያያዝ ማመልከት አለበት።

1.3.3. ማንኛውንም ክፍያ አገልግሎት ያልተፈጸመበት መሆኑ ሲረጋገጥ ተመላሽ ይደረጋል።

1.3.4. ማንኛውም ሰው አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን በማመልከቻ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ 026 ሞልቶ የግለሰብ

1.3.5. ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ ተቋም ከሆነ የድርጅቱ ማህተም ተደርጎና በሃላፊ ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል።

1.3.6. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 5.1.6.2 መሠረት ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ክፍያው ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም።

1.3.7. የተመላሽ ክፍያ አፈጻጸም በፋይናንስ ክፍያ ደንብና መመሪያ እንዲሁም ስታንዳርድ መሰረት ይከናወናል።

1.4. መቀጮ

1.4.1. የከተማው አስተደደር/ባለስልጣኑ የዚህን መመሪያና ስታንዳርድ ድንጋጌዎች በሚተላለፍ አካል ላይ እንደ ሕንጻ ምድብና እንደ ጥፋቱ ዓይነት አስተዳደራዊ መቀጮ ይጥላል፣ የቅጣት ውሳኔው የሚተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ 021 በመሙላት መሆን ይኖርበታል። የጥፋቱ አይነትና የቅጣቱ መጠን በህንጻ ደንቡ አንቀጽ 44 መሰረት እንደሚከተለው ይሆናል።

ሰንጠረዥ -10-፡ ለየህንጻ ምድብ ለተሰራ ጥፋት የአስተዳደራዊ መቀጮ ክፍያ

ተ.ቁ	የጥፋት ዓይነቶች	የህንጻ ምድብ እና አስተዳደራዊ ቅጣት መጠን (ብር)		
		ምድብ ሀ	ምድብ ለ	ምድብ ሐ
1.	ፍቃድ የተሰጠበት የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ማመልከቻ ቅጂ በግንባታ ቦታ አለመገኘት	------	2000	3000
2. 3. 4.	የውስጥ አደረጃጀት/የግንባታ ቅድመ ዝግጅት/ሳያሟሉ ስራ መጀመር	------	2000	3000
5. 6. 7.	የተሰጡ የማስተካከያ ትዕዛዞችን ካጠናቀቁ በኃላ አለማስታወቅ	1000	2000	3000
8. 9. 10.	የተሰጡ ትዕዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን	1000	2000	3000
11. 12. 13. 14.	ከግንባታ ክልል ውጭ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሰረት አለማንሳት	1000	2000	3000
15.	ካለተቆጣጣሪ ማሰራት	------	3000	5000
16.	ካለማስታወቂያ ስራ መጀመር	----	2000	4000
17.	ያለ ፈቃድ ዕድሳት ማድረግ	2000	3000	5000
18.	ያለ ፈቃድ የማስፋፋት ሰራ ማከናወን	2000	3000	5000
19.	ያለ ፈቃድ የማፍረስ ስራ ማከናወን	2000	3000	5000
20.	በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አለመውሰድ	-----	3000	5000
21.	የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም	--------	-------	5000

1.4.2. ከዚህ በላይ በተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ያልተመለከቱ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ የህንፃ ሹሙ እንደጥፋቱ ክብደት በሠንጠረዡ ለየህንፃ ምድቡ ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ ተመጣጣኝ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት ይጥላል። እንዲሁም በተመሳሳይ መልኩ ከላይ ከተራ.ቁ 1 እስከ 11 የተዘረዘሩ ጥፋቶች እያሉ የግንባታ ስራን ሲያከናውን የተገኘ የስራ ተቋራጭም ሆነ አማካሪ ድርጅት በተመሳሳይ መልኩ እንደ ስራ ምድቡ አስተዳደራዊ ቅጣት መሰረት የሚቀጡ እና ሪከርድ እየተያዘ በተደጋጋሚ ለሦስተኛ በተመሳሳይ ጥፋት ውስጥ ከተገኘ የስራ ድርጅቱና አማካሪ ድርጅቱ ላይ የህንጻ ሹሙ የተሰጣቸው ፈቃድ በሚመለከተው ተቋም እንዲታገድ ሊያደርግ ይችላል።

1.4.3. የተፈጸመው ጥፋት በአዋጁ በተመለከቱት የወንጀል ድንጋጌዎች ስር የሚወድቅ ሆኖ ሲገኝ የሕንፃ ሹሙ ተገቢ ነው ብሎ የሚወስደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጥፊው ላይ የወንጀል ክስ እንዲቀርብበት ለሚመለከተው አካል መምራት አለበት።

1.4.4. የሚጣለው አስተዳደራዊ መቀጮ ከተደራራቢ ጥፋቶች ወይም የከተማው አስተዳደር ወይም የህንፃ አዋጅ ከሚደነግገው የገንዘብና የእሥራት ቅጣት ነፃ አያደርግም።

1.4.5. አስተዳደራዊ መቀጮ መክፈል የግንባታ ሥራውን የማስቆም፣ የማስነሳት ወይም የማፍረስ ርምጃዎችን ከመውሰድ የሚያግድ አይሆንም።

1.4.6. በአንድ ጊዜ ለሚፈፀሙ ተደራራቢ ጥፋቶች የቅጣቱ መጠን እንደ ሕንፃው ምድብ ለየጥፋቱ የተመለከተው ድምር ይሆናል።

ክፍል ስድስት

1. የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን

1.1. የውሃ አቅርቦት

1.1.1. ማንኛውም ህንጻ ለተገልጋዩ በቂና ንጹህ የውሃ አቅርቦት እንዲኖረው ተደርጎ መሰራት አለበት፣

1.1.2. በቂ የውሃ አቅርቦት እና ስርጭት ማለት ለእያንዳንዱ ሰው ለመጠጥ፣ ለገላ መታጠቢያ፣ ለልብስ እና መገልገያ እቃዎች ማጠቢያ፣ ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለመጸዳጃ ቤት አገልግሎት፣ለአትክልት ማጠጫ የሚበቃ ሊሆን ይገባል፣

1.1.3. ለሰዎች አገልግሎት የሚውል የማንኛውም ህንጻ የውሃ አቅርቦት እና ጥራት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስታንደርዶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፣

1.1.4. ለምድብ "ሐ" ህንጻ ተጠቃሚዎች የሚውል የተጠቃሚውን ፍጆታ ሊያሟላ የሚችል የውሃ አቅርቦትና ለመጠባበቂያ የሚውል በቂ የውሃ መከማቻ ሊኖረው ይገባል፣

1.1.5. ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሚዘጋጁ የውሃ አቅርቦት መስመሮች ዲዛይኖች እና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ቁጠባዊ የውሃ አጠቃቀምን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፣

1.1.6. የውሃ መጠራቀሚያ ገንዳዎችና የስርጭት መስመሮች ለቁጥጥርና ለጽዳት ተደራሽ ሆነው መገንባት አለባቸው፣

1.1.7. የውሃ አቅርቦት ሳኔቴሽን የግንባታ እና ስርጭት ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች እና በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን መስፈርት ሊከናወን ይገባል፣

1.2. የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ

1.2.1. አንድ ግንባታ በሚካሄድበት አቅራቢያ የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ካለ የከተማው መስተዳድር ወይም የሚመለከተው አካል በማስፈቀድ የሚገነባውን ሕንጻ የቆሻሻ መስመር ከአካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት ይችላል፣

1.2.2. አንድ ግንባታ በአካባቢው የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከሌለ በግቢ ውስጥ ፍሳሽን ለማስወገድ ተቀባይነት ባለውና የሚመለከታቸውን አካላት መስፈርቶች እንዲያሟላ ተደርጎ መሰራት አለበት፣

1.2.3. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መሥመር በአዋሳኝ መንገድ ላይ የሚገኝ ከሆነ በአቅራቢያው ባለ ሌላ መንገድ ላይ ከሚገኝ መሥመር ጋር መገናኘት ይችላል፣

1.2.4. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ፍሳሹን ወደ አፈር ውስጥ እንዳይሰርግ ወይም እንዳያሳልፍ ሆኖ መገንባት አለበት፣

1.3. ጎርፍ ውሀ ወይም የዝናብ ውሃ አወጋገድ

1.3.1. ማንኛውም ባለይዞታ በግቢው ውስጥ የሚፈጠርን የዝናብ ውሀ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጎርፍ ውሀ ማስወገጃ መስመር ማገናኘት አለበት፣

1.3.2. ለጎርፍ አደጋ በተጋለጡ ቦታዎች የሚከናወን ግንባታ የጎርፍ መከላከያ ያለው ሆኖ መገንባት አለበት፣

1.3.3. ወሰን ተጠግቶ የሚሰራ ቤት ጣራ ፍሳሽ ወደራስ ይዞታ አቅጣጫ መሆን አለበት። የጣራውን ፍሳሽ ወደ ወሰንተኛው አቅጣጫ አድርጎ ለመገንባት ማንኛውንም የጣራ ፍሳሽና ጠፈጠፍ እንዲከላከል ተደርጎ ከተሰራ 60 ሳ.ሜ ከፍታ ባለው መሸፈኛ ግድግዳው ተከልሎ መሰራት አለበት፣

1.3.4. የዝናብ ውሀ አወጋገድ ሥርዓት ውሃው በቀላሉ ሊወገድ በሚችልበትና ውሃ በማያቁርበት ሁኔታ እና የወሰንተኛን ነባር ግንባታ ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ መገንባት አለበት፣

1.3.5. የዝናብ ውሃ ማስወገጃ በአዋሳኝ መንገድ ላይ ከሚገኝ ጎርፍ ማስወገጃ መረብ ጋር መገናኘት አለበት።ሆኖም ከቦታው ተፈጥሯዊ ተዳፋት አንፃር የሚዘረጉ የፍሳሽ መስመሮች በመዳረሻ መንገድ በኩል ለማውጣት የማይቻል ከሆነ ፍሳሹ ሊሄድ በሚችልበት በኩል ባለ የተጎራባች ይዞታ አሳልፎ ማገናኘት ይቻላል። ይህም ፍሳሹን ተቀብሎ ላሳለፈው ተጎራባች አመቺ በሆነ አቅጣጫ መሆን ያለበት ሲሆን ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የማይሄድ ከሆነ ስታንዳርዱን ጠብቆ በአመልካች ወይም አሳላፊው ወጪ ይገነባል። ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የሚሄድ ከሆነ እያንዳንዱ ባለይዞታ የየራሱን ወጪ ይሸፍናል፣

1.3.6. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተጨማሪ ግንባታዎች በማድረግ ተዳፋቱን ወደ ራስ ይዞታ በኩል በመቀየር ወይም በጥልቀት በመቆፈር መስመሩን በራስ ይዞታ ላይ መዘርጋት ካልተቻለ በተጎራባች ይዞታ ማሳለፍ ይቻላል። ሆኖም በቦታው ልዩ የመሬት አቀማመጥና በአዋሳኝ ካሉት ነባር ግንባታዎች ነባራዊ ይዘት ምክንያት በተናጠል መታየት የሚኖርባቸውን ፍሳሽ መስመር ግንባታ ይዘት እና አቅጣጫ የህንፃ ሹሙ ውሳኔ ይሰጣል፣

1.3.6.1. ከ50 ሳ.ሜ በታች ሙሌት፣

1.3.6.2. ከ150 ሳ.ሜ ጥልቀት እና ከ20 ሜትር ርዝመት በታች ቁፋሮ፣

1.3.7. አንድ ይዞታ ብቻ አቋርጦ ለሚሄድ የዝናብ ውሃ ፍሳሽ መስመር ቢያንስ በ20 ሳ.ሜ የኮንክሪት ቱቦ ወይም ቦይ መሰራት አለበት። ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ ለሚሄድ የቱቦው መጠን እንደ ርዝመቱ የሚጨምር ይሆናል። ሆኖም መስመሩ በ2% ተዳፋት፣ በ40 ሳ.ሜ ጥልቀት እና በየ25 ሜትር ርዝመት ወይንም በማንኛውም የመስመር እጥፋት ላይ የመቆጣጠሪያ ገንዳ እንዲኖረው ሆኖ መሰራት አለበት፣

1.3.8. በተዳፋታማ ቦታ ላይ የሚገኙ ቤቶች የዝናብ ውኃን አንዱ ከሌላው ተቀብሎ የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል።

1.3.9. በዝናብ ውሃ መስመር ሌላ ቆሻሻ ፍሳሽ መልቀቅ አይፈቀድም፣ ከዝናብ ውሃ ጋር በሚመጣ ቆሻሻ ምክንያት መስመሩን የማጽዳት ሃላፊነት የአሳላፊው ሲሆን ተቀባዩ አሳላፊውን ለዚህ ጉዳይ ወደ ግቢው እንዲገባ የመፍቀድና የመስመሩን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

1.4. ኢንዱስትሪ ዝቃጭ

1.4.1. ማንኛውንም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ በቅድሚያ ሳይታከምና ጐጂ አለመሆኑ በሚመለከተው ሳይረጋገጥ ወደ ማንኛውም ፍሳሽ ማስተላለፊያ መለቀቅ የለበትም፣

1.4.2. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ የሚያመነጭ ተቋም ወይም ድርጅት አወጋገዱን በተመለከተ ለአካባቢ ባለሥልጣን ወይም ለሚመለከተው አካል ጥናቱን አቅርቦ ፈቀድ ማግኘት ይኖርበታል፣

1.4.3. የኢንዱስትሪ ዝቃጮችን ለማከምና ወደ ማንኛውም የፍሳሽ ማስወገጃ ለመልቀቅ፣ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፣

1.4.4. የኢንዱስትሪ ዝቃጮቹ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ መያዝና ጐጂነት ያላቸው ንጥረ ነገሮች ተጣርተው እና ታከመው መለቀቅ ይኖርበታል፣

1.4.5. ዝቃጭ የሚያመነጩ ተቋማት በከተማው አስተዳደርና በሚመለከተው አካል የአካባቢ ብክለትን እንዳያስከትሉ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፣

1.5. የውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ

1.5.1. ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል መመሪያና ስታንዳርድ ና ፈቃድ ውጭ ማንኛውም ሰው ውሃ አልባ ቆሻሻዎችን በየትኛውም ሥፍራና መስመር ማስወገድ ወይም እንዲወገድ ማድረግ የለበትም፤

1.5.2. የከተማው አስተዳደር ውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎችን የሕዝቡን ጤንነት በጠበቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፤

1.5.3. ኬሚካል ወይም ዝግ ቆሻሻ ማስወገጃ በሚኖርበት ጊዜ ቆሻሻውን ከእቃው ለማስወገድ በአስተዳደሩ ተቀባይነት ባለው አወጋገድ ዘዴ መከናወን ይኖርበታል።

1.6. የእሳት ማጥፊያ ተከላ

1.6.1. ለምድብ ሐ ሕንፃዎች ለእሳት አደጋ መከላከል የሚረዱ መሣሪያዎች የሚተከሉበትን የሚያሳይ ኘላን መቅረብና በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፣

1.6.2. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች ተከላ በኘላኑና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት መከናወንና በተከላ ወቅትም ከትትል ሊደረግበት ይገባል፣

1.6.3. የመሣሪያዎቹ ተከላ እንደተጠናቀቀ ፍተሻ መደረግና መስራታቸው በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፣

1.6.4. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎቹ የጥራት ደረጃ በሚመለከተው አካል ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

1.6.5. በውኃ ለሚሠሩ የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች የውኃ ማከማቻ ሊኖራቸው ይገባል፣

1.6.6. የውኃ መስመር ደረጃውን በጠበቀ የውኃ ማስተላለፊያ ቧንቧ መዘርጋት ይኖርበታል፣

1.6.7. የውኃ ማጠራቀሚያ ጋኑም ሆነ መስመሮቹ ለቁጥጥር የሚያመቹ መሆን አለበት፣

1.7. የእሣት መከላከል የውሃ አቅርቦት

1.7.1. የእሣት መከላከያ የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ በቅድሚያ ለከተማው አስተዳደር በማመልከቻ መጠየቅ አለበት፣

1.7.2. የከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ እስኪደርስ ድረስ ለትላልቅና ለምድብ "ሐ" ህንፃዎች መጠባበቂያ የሚሆን ከተገቢው መሣሪያ ጋር የውሃ አቅርቦት ሊኖር ይገባል፣

1.7.3. የተቋሞች ወይም ድርጅቶች የእሣት መከላከያ መሣሪያውና የውሃው አጠቃቀም ከከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ መስፈርቶችና ሕጐች ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባዋል፣

1.7.4. የከተማው አስተዳዳር እሣት ለመከላል የሚቀርበውን የውሃ አቅርቦት ጥያቄእንደ ህንፃው ዓይነት፣ ከፍታው የሕንፃው ስፋት መሠረት የውሃ አቅረቦትን ሊወስን ይችላል፤

ክፍል ሰባት

1. የህንጻ የስጋት ደረጃ እና የህንጻ ምድብ

1.1. የህንጻ የስጋት ደረጃ

1.1.1. ለግንባታ ፈቃድ፣ ክትትልና የመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲረዳ “ዝ”፣ “ዝመ”፣ “መከ”፣ “ከ” እና “በከ” ተብለው የተሰየሙ የህንጻዎች የስጋት ደረጃ ምደባዎች ወጥተዋል።

1.1.2. በአንቀጽ (i) መሰረት ሁሉም ሕንፃዎች የህብረተሰብ ህይወት፤ የአካባቢ ደህንነትን፣ የኢኮኖሚ ተጽዕኖን እና ሌሎች በዚህ መመሪያ አባሪ ላይ/በአሰራር ማንዋሉ ላይ የተመለከቱ ዝርዝር መለኪያዎችን መሰረት በማድረግ “ዝ”፣ “ዝመ”፣ “መከ”፣ “ከ” እና “በከ” ተብለው በተሰየሙ የሕንፃ ስጋት ደረጃዎች ምድብ ስር ይፈረጃሉ።

1.1.3. በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ “ዝ” እና “ዝመ” ስር የሚወድቅ ሕንፃ፤

1.1.3.1. የጂኦቴክኒካል ጥናት ወይም የአፈር ምርመራ እና

1.1.3.2. ለግንባታ ክትትል የተመዘገበ ባለሙያ/አማካሪ ድርጅት መቅጠር አይጠበቅበትም።

1.1.4. በሕንፃ ስጋት ደረጃ “ዝ” ምድብ ስር የሚወድቅ ሕንፃ በባለስልጣኑ የሚደረግ መደበኛ ክትትል አይመለከተውም።

1.1.5. በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ “ዝመ” እና “መከ” ምድብ ስር የሚወድቅ ሕንፃ በባለስልጣን አስገዳጅ መደበኛ ክትትል፥

1.1.6. የመሰረት ስራ ሲሰራ እና ሲጠናቀቀ ለመጠቀሚያ ፈቃድ ብቻ ይደረጋል፣

1.1.7. ከሀገር ደህንነት ጋር በተያያዘ የህንጻ አዋጁ ተፈጻሚ እንዳይሆንበት በሚንስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ህንጻ አስገዳጅ መደበኛ ክትትል አይመለከተውም።

1.1.8. በሕንፃ ስጋት ደረጃ ምድብ “ከ” እና “በከ” ስር የሚወድቅ ሕንፃ በአንቀጽ 14 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት የሚስተናገድ ይሆናል።

1.2. የህንጻ ስጋት ደረጃ ምድብ

ምድብ	የስጋት ደረጃ	ገለጻ	ክፍያ	ቁጥጥር እና የአሰራር ቅደም ተከተል	ጊዜ
ሀ	ዝ	**ፎቅ:** አንድ (1) **አገልግሎት:** ማንኛውም፣ ከመኖርያ ውጭ ብዛትና **የሰው ብዛት:** እስከ 30 ሰው **ከፍታ:** 7 ሜትርና ከዛ በታች **የውቅሮች ርቀት:** እስከ 7 ሜትር	በፎቅ ወለል አጠቃላይ ስፋት ላይ ተመስርቶ ይሰላል	✓ ለግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ መቅጠር አይኖርበትም። ✓ የአፈር ምርመራ፣ የስትራክቸራል እና የሳኒተሪ ዲዛይን አይጠየቅም። ✓ አስገዳጅ ክትትል በባለስልጣኑ ግንባታው ሲጠናቀቀ ለመጠቀሚያ ፈቃድ ብቻ ይደረጋል። ✓ ተጨማሪ የእርከን መደበኛ ክትትል አያስፈልገውም።	5 የስራ ቀናት
	ዝ	**ፎቅ:** አንድ (1) **አገልግሎት:** መኖርያ፣ ከሪል እስቴት ውጭ **የሰው ብዛት:** እስከ 30 ሰው **ከፍታ: 7** ሜትርና ከዛ በታች			
ለ	ዝመ	**ፎቅ:** ሁለት (2) **አገልግሎት:** አደገኛ ላልሆኑ እቃዎች ማስቀመጫ መጋዘን, አነስተኛ እቃ ማስቀመጫዎች፣ ጋራጅ፣ የከብት በረት እና የመሳሰሉት **የሰው ብዛት:** ከ0 እስከ 30 **ከፍታ:** እስከ 7 ሜትር **የውቅሮች ርቀት:** ገደብ የለውም	በፎቅ ወለል አጠቃላይ ስፋት ላይ ተመስርቶ ይሰላል	✓ ለግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ መቅጠር አይኖርበትም። ✓ የአፈር ምርመራ አይጠየቅም። ✓ አስገዳጅ መደበኛ ክትትል በባለስልጣኑ ግንባታው ሲጀምር በመሰረት ስራና ሲጠናቀቀ ለመጠቀሚያ ፈቃድ ብቻ ይደረጋል። ✓ ተጨማሪ የእርከን መደበኛ ክትትል አያስፈልገውም።	13 የስራ ቀናት
	መከ	**ፎቅ:** ሁለት (2) **አገልግሎት:** ማንኛውም፣ ከሪል እስቴት ውጭ **የሰው ብዛት:** ከ31 እስከ 100 **ከፍታ:** 7 ወይም፣ ከ7 ሜትር በላይ እና ከ12 ሜትር በታች **የውቅሮች ርቀት:** ገደብ የለውም		✓ ለግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ መቅጠር ይኖርበታል። ✓ የአፈር ምርመራ ይጠየቃል። ✓ አስገዳጅ መደበኛ ክትትል በባለስልጣኑ ግንባታው ሲጀምር በመሰረት ስራና ሲጠናቀቀ ለመጠቀሚያ ፈቃድ ብቻ ይደረጋል። ✓ ተጨማሪ የእርከን መደበኛ ክትትል አያስፈልገውም።	
	ከ	**ፎቅ:** ከሶስት እስከ አራት (3-4) **አገልግሎት:** ማንኛውም **የሰው ብዛት:** ከ31 እስከ 100 **ከፍታ:** ከ7 ሜትር በላይ እና ከ12 ሜትር በታች **የውቅሮች ርቀት:** ገደብ የለውም		✓ ለግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ መቅጠር ይኖርበታል። ✓ የአፈር ምርመራ ይጠየቃል። ✓ አስገዳጅ መደበኛ ክትትል በባለስልጣኑ በግንባታው ወቅት ለሁሉም እርከን ይደረጋል።	
	ከ	**ፎቅ:** ከአምስት እስከ እስራ ዘጠኝ (5-23) **አገልግሎት:** የንግድ, ኢንዱስትሪ እና የሕዝብ ህንጻ, ወይን ሪል እስቴት **የሰው ብዛት:** ከ100 እስከ 500 **ከፍታ:** ከ12 ሜትር በላይ እስከ 70 ሜትር **የውቅሮች ርቀት:** ገደብ የለውም	በፎቅ ወለል አጠቃላይ ስፋት ላይ ተመስርቶ ይሰላል	✓ ለግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ መቅጠር ይኖርበታል። ✓ የአፈር ምርመራ ይጠየቃል። ✓ አስገዳጅ መደበኛ ክትትል በባለስልጣኑ በግንባታው ወቅት ለሁሉም እርከን ይደረጋል።	21 የስራ ቀናት

ምድብ	የስጋት ደረጃ	ገለጻ	ክፍያ	ቁጥጥር እና የአሰራር ቅደም ተከተል	ጊዜ
ሐ	በከ	**ፎቅ:** ገደብ የለውም **አገልግሎት:** የንግድ፣ የኢንዱስትሪ እና የሕዝብ መገልገያ፣ እና ከፍተኛና የአደገኛ እቃዎች መጋዘን፣ ወይም እስከ 23 ፎቅ የሚደርስ የሪል እስቴት ልማት **የሰው ብዛት:** ከ500 ሰው በላይ		✓ ለግንባታ ክትትል አማካሪ ድርጅት ወይም ባለሙያ መቅጠር ይኖርበታል። ✓ የአፈር ምርመራ ይጠየቃል። ✓ አስገዳጅ መደበኛ ክትትል በባለስልጣኑ በግንባታው ወቅት ለሁሉም እርከን	

		ከፍታ: ከ12 ሜትር በላይ **የውቅሮች ርቀት**: ገደብ የለውም		ይደረጋል።	

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያና ስታንዳርድ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፥ በከተማ ደረጃ የሚሰራባቸው ልዩ ልዩ መመሪዎች ያዘጋጃል።ለየሕንፃ ምድቦቹ የሚያገለግሉ በከተማ ደረጃ የዲዛይን እና የኮንስትራክሽን ስታንዳርዶችን፣ የዲዛይን፣ የኮንስትራክሽን እና የቁጥጥር ዘዴ፣ መመሪያና ስታንዳርዶዎች እንዲሁም የአሰራር ማንዋሎች ያዘጋጃል። መመሪያና ስታንዳርድ በከተማው ላይ ተከብሮ መፈጸሙን ይቆጣጠራል።

2. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

2.1. ከዚህ በፊት አገልግሎት ላይ የነበሩ የህንጻ መመሪያ ቁጥር 02/2010 እና የሕንፃ ስጋት ደረጃ መመሪያ ቁጥር 02/2012 በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ የተሻሩ ይሆናሉ፣

2.2. ማንኛውም ከዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ጋር የሚጋጩ መመሪያዎች፣ ልማዳዊ ድርጊቶችና አሰራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፣

2.3. ሆኖም ማንኛውም የዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ድንጋጌዎች ከህንጻ አዋጁ፣ ደንቡ እና ከአገሪቱ የህንጻ ኮድና ስታንዳርድ ጋር የሚጋጭ ከሆነ የአዋጁ፣ ደንቡ እና የኢትዮጵያ የህንፃ ኮድና ስታንዳርድ ድንጋጌዎች ገዢ ይሆናሉ።

3. መመሪያና ስታንዳርድን ስለማሻሻል

የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መመሪያና ስታንዳርዱን ያሻሽላል።

4. መመሪያና ስታንዳርዱ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያና ስታንዳርድ ጥቅምት / 2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት 01/2015 ዓ.ም

ስጦታው አካለ (ኢ/ር)

የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር

ልዩ ልዩ ቅጾች

1. የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ..... ቅፅ 001
2. የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት..... ቅፅ 002
3. የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ..... ቅፅ 003
4. የመጀመሪያ ግንባታ ክትትል እርከን ማሳወቂያ ..... ቅፅ 004
5. የግንባታ እድሳት ፈቃድ መጠየቂያ..... ቅፅ 005
6. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ..... ቅፅ 006
7. የአገልግሎት ለውጥ መጠየቂያ ማመልከቻ ..... ቅፅ 007
8. የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ..... ቅፅ 008
9. የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ..... ቅፅ 009
10. የአማካሪ ግዴታ መግቢያ ..... ቅፅ 010
11. የአሠሪ ግዴታ መግቢያ..... ቅፅ 011
12. የገንቢ ግዴታ መግቢያ ..... ቅፅ 012
13. የግንባታ መከታተያ ቅጽ..... ቅፅ 013
14. የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ ..... ቅፅ 014
15. የግንባታ ማስቆሚያ ..... ቅፅ 015
16. የግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ ..... ቅፅ 016
17. የግንባታ ሥራ ለውጥ ተጨማሪ ማሳወቂያ..... ቅፅ 017
18. የግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ መጠየቂያ..... ቅፅ 018
19. የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ..... ቅፅ 019
20. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ..... ቅፅ 020
21. የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ /ደንብ ማስከበር/..... ቅፅ 021
22. የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ..... ቅፅ 022
23. የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ..... ቅፅ 023
24. ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቂያ ..... ቅፅ 024
25. የግንባታ ሥራ እርከን ማሳወቂያ..... ቅፅ 025
26. አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ መጠየቂያ ..... ቅፅ 026
27. ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ ..... ቅፅ 027
28. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ..... ቅፅ 028
29. የምሽት መገንቢያ ፍቃድ..... ቅፅ 029
30. የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ምስክር ወረቀት..... ቅፅ 030
31. የግንባታ ማራዘሚያ ማስጀመሪ ምስክር ወረቀት.....ቅፅ 031



ጥቅምት/2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ



ግንቦት 2014 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

የህንጻ መመሪያና ስታንዳርድ

ቁጥር 127/2014



መግቢያ

ክፍል አንድ

1. ጠቅላላ 01
   1.1አጭር ርዕስ 01
   1.2ትርጎሜ..... 01
   1.3የተፈፃሚነት ወሰንና መመሪያ ማሻሻል..... 05

ክፍል ሁለት

2. የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ማመልከቻና አቀራረብ..... 06
3. የፕላን ስምምነት..... 11
4. የፕላን መገምገሚያ ጊዜ..... 12
5. የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ስለማፀደቅ..... 15
6.ፕላን ውድቅ ስለማድረግ..... 16
7. በግንባታ ወቅት ፕላንን ስለማሻሻል..... 17
8. ግንባታ ፈቃድ..... 17
9. የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ..... 19
10.የግንባታ ፈቃድ ስለመጠየቅ..... 21
11.የሕንፃ ሹም 38
12.አገልግሎት መግዛት..... 40
13.የይግባኝ ሰሚ ቦርድ..... 40
14.የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር..... 43
15.ትዕዛዝ ስለማክበር..... 46
16.ስለማስታወቂያ..... 47
17.ስለተቆጣጣሪዎች..... 48
18.ቁሳቁስ..... 50
19.የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ..... 51
20.የአገልግሎት ክፍያ እና ቅጣት..... 55
21.ተመላሽ ክፍያዎች..... 60
22.መቀጮ..... 61
23.ጊዜያዊ ግንባታ..... 63
24.የአገልግሎት ለውጥ ስለማድረግ..... 65
25.የተመዘገቡ ባለሙያዎችን (አማካሪ) ስለመቅጠርና የጉዳት ማካካሻ ዋስትና..... 66
26.የተመዘገቡ የስራ ተቋራጮችን ስለመቅጠር..... 67

ክፍል ሶስት

27.የመሬት አጠቃቀምና ተጓዳኝ ጥናቶች..... 70
28.ዲዛይኖች..... 72
29.አርክቴክቸር ወይም ስነ ህንፃ..... 80
30.የግል መኖሪያ ቤት የዲዛይን ስታዳርዶች..... 82
31.ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ዝግጅቶች ስታንዳርድ..... 85

ክፍል አራት

32.በህንፃ ግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች..... 86
33.መወጣቻዎች እና መሰላሎች..... 88
34.የማፍረስ ስራ..... 92
35.ስለከፍታ እና የጣሪያ ላይ ስራዎች..... 93
36.የመሬት ውስጥ ስራዎች..... 95
37.የቁፋሮ ስራ..... 95
38.ስለኬሚካሎች፣ ፈንጂዎች እና መርዛማ ቁሶች..... 98
39.ስለ አልባሳት..... 99
40.የእሳት አደጋ ስለ መከላከ..... 100
41.ስለ መጀመሪያ እርዳታ አሰጣጥ..... 102
42.ስለ አደጋ ማምለጫ መንገዶች 103
43.ስለ ሰራተኛ እና የስራ ቦታዎች ደህንነት አጠባበቅ 104
44.የሚደርሱ አደጋዎችን ስለመመዝገብ እና ማሳወቅ..... 105

ክፍል አምስት

45. የውሃ አቅርቦትና እና ሳኒቴሽን..... 107
46.የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ..... 107
47.የጎርፍ ውሃ ወይም የዝናብ ውሃ አወጋገድ..... 108
48.ኢንዱስትሪ ዝቃጭ..... 109
49.የውሃ አልባ ቆሻሻ መስወገጃ..... 110
50.የእሳት ማጥፊያ ተከላ..... 110
51.የእሳት መከላከል የውሃ አቅርቦት..... 111
52.የኮንስትራክሽን ቢሮ ስልጣንና ተግባር..... 112

ልዩ ልዩ ቅጾች

1. የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ..... ቅፅ 001
2. የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት..... ቅፅ 002
3. የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ..... ቅፅ 003
4. የግንባታ እርከን ማሳወቂያ ..... ቅፅ 004
5. የግንባታ እድሳት ፈቃድ መጠየቂያ..... ቅፅ 005
6. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ..... ቅፅ 006
7. የአገልግሎት ለውጥ መጠየቂያ ማመልከቻ ..... ቅፅ 007
8. የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ..... ቅፅ 008
9. የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ..... ቅፅ 009
10. የአማካሪ ግዴታ መግቢያ ..... ቅፅ 010
11. የአሠሪ ግዴታ መግቢያ..... ቅፅ 011
12. የገንቢ ግዴታ መግቢያ ..... ቅፅ 012
13. የግንባታ መከታተያ ቅጽ..... ቅፅ 013
14. የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ ..... ቅፅ 014
15. የግንባታ ማስቆሚያ ..... ቅፅ 015
16. የግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ ..... ቅፅ 016
17. የግንባታ ሥራ ለውጥ ተጨማሪ ማሳወቂያ..... ቅፅ 017
18. የግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ መጠየቂያ..... ቅፅ 018
19. የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ..... ቅፅ 019
20. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ..... ቅፅ 020
21. የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ /ደንብ ማስከበር/..... ቅፅ 021
22. የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ..... ቅፅ 022
23. የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ..... ቅፅ 023
24. ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቂያ ..... ቅፅ 024
25. የግንባታ ሥራ እርከን ማሳወቂያ..... ቅፅ 025
26. አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ መጠየቂያ ..... ቅፅ 026
27. ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ ..... ቅፅ 027
28. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ..... ቅፅ 028
29. የምሽት መገንቢያ ፍቃድ..... ቅፅ 029
30.የግንባታ ማስጀመሪያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት..... ቅፅ 030
31.የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ምስክር ወረቀት..... ቅፅ 031
32.የግንባታ ማራዘሚያ ማስጀመሪ ምስክር ወረቀት..... ቅፅ 032

1. መግቢያ

በአገራችን በመካሔድ ላይ ያለው የግንባታ ሥርዓት ባለው እና ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲመራ ለማድረግ፣ የሕዝብን ጤንነትና ደህንነትና ብልጽግና ለማረጋገጥና በመላ ሀገሪቱ ተፈፃሚነት የሚኖረው ምቹ የግንባታ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እንዲሁም የግንባታ የሥራ ሂደቶችና ዝርዝር አፈፃፀም ለአገልግሎት ሰጪም ሆነ ለተገልጋዩ ግልጽ በማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት በፌዴራል መንግስት የወጣውን የኢትዮጵያ ሕንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ እንዲሁም በከተማ አስተዳደሩ የወጣ የሕንጻ መመሪያ ቁጥር 2//2010 መኖሩ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ የከተማው እድገት ፈጣን በመሆኑ፣ ከተማዋ የአለም አቀፍ ዲፕሎማቶች መገኛ እና የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ በመሆኟ፣ ከተማውን ለነዋሪዎች ምቹና የህንጻ ደህንነት ስጋት የሌለባት ማድረግ በማስፈለጉ የፌደራል የህንጻ ቁጥር 624/2001፣ የህንጻ ደንብ ቁጥር 243/2003 እና መመሪያ ቁጥር 5/2003ን መነሻ በማድረግ የአዲስ አበባ ከተማ የህንጻ መመሪያ ቁጥር 2/2010ን ማሻሻል አስፈልጓል። በመሆኑም ባለስልጣኑ በማቋቋሚያ አዋጅ 74/2014 በተሰጠው ስልጣን መሰረት መመሪያውን አሻሽሏል።

ይህ መመሪያ በአገር አቀፍ የህንጻ ህግጋት እና የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን በውጤታማነት ለማስፈፀም እና የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ስርዓት፣ ከህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ እንዲሁም ከተማዋ ራሱን የቻለ መለያ ስታንዳርድ የህንጻዎች የውጭ ቀለም የሚመራበት አሰራርን ግልጽና ውጤታማ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። መመሪያው የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የተሻሻለ መመሪያ ቁጥር 127/2014 ተብሎ ወጥቷል።

2. **መመሪያውን ለማዘጋጀት ያስፈለገበት አላማ፡-**

- **ግልጽነት፣ ተጠያቂነትን፣ ምላሽ ሰጭነትና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ፤**
- **በመመሪያ ቁጥር 2/2010 ያልተዳሰሱ የግንባታ እና የህንጻ ውጭ ገጽ ስታንዳርዶችን ማካተት በማስፈለጉ፤**
- **በተለያየ ጊዜ የወጡ ሰርኩላሮችን ለማካተት እና በአሰራር የታዩ ክፍተቶችን ለመመላት፤**
- **የህንጻ ጥራትና ደህንነትን ለማሻሻል እና የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን በውጤታማነት ለማስፈጸም፤**
- **ተጋልጋዩን እርካታ በማረጋገጥ እና ልማትን ለማፋጠን፤ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡**

ክፍል አንድ

1. ጠቅላላ

1.1. አጭር ርዕስ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር የህንጻ መመሪያና ስታንዳርድ ቁጥር 127/2014 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1.2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ፍቺ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ውስጥ፡-

1.2.1. "ሚኒስቴር" ማለት የኢፌዲሪ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነዉ

1.2.2. "ከተማ"፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነዉ፤

1.2.3. "አስተዳደር"፡- ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ፤

1.2.4. ባለስልጣን፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

1.2.5. ጽ/ቤት፡- ማለት በክ/ከተማና የወረዳ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ነው፡፡

1.2.6. "ይዞታ"፡- ማለት አግባብ ካለው አካል በተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ የተያዘ ቦታ ነው፡፡

1.2.7. "የደንብ ማስከበር አገልግሎት"፡- ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር አገልግሎትና በክፍለ ከተማ እና በወረዳ የሚገኘው ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ነው፤

1.2.8. "የኘላን መረጃ"፡- በአንድ ቦታ ሊገነቡ የሚችሉ ወይንም ለቦታው የተፈቀዱ የመሬት አጠቃቀም አገልግሎት አይነቶችን፣ ለቦታው የተፈቀደ የህንፃ ከፍታን፣ በቦታውና በአካባቢው የሚያልፉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን የአየር ክልከላ ክልልን (አቪዬሽን

ክልል) ጨምሮ፣ ነባራዊ እና የታቀዱ መጠኖችን ወይንም ስፋቶች፣ ወዘተ የሚያሳይ ስልጣን ባለው አካል የሚሰጥ መረጃ ነው፤

1.2.9. “የፕላን ስምምነት”፡- ማለት ስልጣን ባለው አካል ለህንጻ ግንባታ የቀረበ የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ከከተማዉ ፕላን ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የጽሁፍ ስምምነት ነዉ፤

1.2.10. "ግንባታ"፡- ማንኛውም ከመሬት በታች፣ከመሬት ላይ እና በላይ የሚገነባ አዲስ ህንጻ፣ መጠለያ፣ አጥር፣ እንዲሁም ነባር ህንጻ ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ማለት ነው፡፡

1.2.11. “የግንባታ ዲዛይን/ፕላን”፡- የአንድን ሕንፃ መጠን ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃ የሚሰራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴ የማያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርክቴክቸር፣ የእስትራክቸር፣ የሳኒቴሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ መካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችንም ንድፍ ሊያካትት ይችላል፡፡

1.2.12. “የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ማሻሻያ”፡- ማለት በነባሩ ፕላን ለህንፃው ምድብ የተጠየቁ ፕላኖችን/ዲዛይኖችን ትንታኔ ሙሉ በሙሉ መከለስ ሳያስፈልግ የግንባታ ዲዛይንና የከተማ ፕላን ህግጋትን ጠብቆ የሚደረግ ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ነው፤

1.2.13. “መሠረታዊ ግንባታ”፡- ማለት የአንድ ግንባታ ሙሉ መዋቅር፣ የውጭና የውስጥ ግድግዳ ሥራ፣ የውጭ በርና መስኮት ስራና የጣሪያ ልባስ ስራ የተጠናቀቀለት ሕንፃ ግንባታ ነው፡፡

1.2.14. “የግንባታ ዋና አገልግሎት/ዋና ግንባታ”፡- ማለት ለጥበቃ ለአደጋ መከላከያና የመጠባበቂያ ሃይል አቅርቦት፣ ለግቢ ውስጥ መተላለፊያ፣ ለመንገድ፣ ለአጥርና ግንባታው ለሚሰጠው አገልግሎት ድጋፍ እንዲሰጡ ከሚገነቡት ግንባታዎች ውጪ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለሚሰጠው ቀዳሚ አገልግሎት ታስቦ የሚገነባ ግንባታ ነው፡፡

1.2.15. “ጊዜያዊ ግንባታ”፡- ማለት የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚገነባ እና የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ የሚነሳ ግንባታ ማለት ነው፡፡

1.2.16. “ገንቢ”፡- ማለት የግንባታ ደረጃውን የሚመጥንና ግንባታውን ለመስራት ውል የወሰደ የሥራ ተቋራጭ ወይም ለአነስተኛ ግንባታዎች ግለሰብ ባለሙያ ወይም ባለሙያ የሆነ የግንባታው ባለቤት ነው ፤

1.2.17. “የሕንፃ ሹም”፡- ማለት የህንጻ አዋጁን የማስፈጸሚያ ደንቡን እና ይህንን መመሪያና ስታንዳርድ የሚያስፈጽም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል የተሾመ ሰው ማለት ነው፤

1.2.18. “ሪል እስቴት”፡- ማለት ለሽያጭ፣ ለኪራይ፣ ወይም ለሊዝ አገልግሎት እንዲውል የተገነባ የመኖሪያ ሕንጻ ነው፡፡

1.2.19. የህንጻ ምድብ፡- ማለት የአስተዳደሩን እርከን ሳይመለከትና ሳይወስን የሕንጻ ከፍታ እና የህንጻ አገልግሎት ባህሪይ ብቻ ለመግለጽ የሚጠቅም ስያሜ ነው፤

1.2.20. "ምድብ "ሀ" ሕንፃ "፡- ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ከ7 ሜትር ወይም ከዚያ በታች የሆነ ባለ አንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም ማናቸውም ከሁለት ፎቅ በታች የሆነ የግል መኖሪያ ቤት ነው፤

1.2.21. "ምድብ "ለ" ሕንፃ "፡- ማለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ከ7ሜትር በላይ የሆነ ወይም ባለሁለት ፎቅና ከሁለት ፎቅ በላይ የሆነና በምድብ "ሐ" የማይሸፈን ሕንፃ ወይም "ምድብ "ሀ" የተመደበ እንደሪል እስቴት ያሉ የቤቶች ልማት ነው፤

1.2.22. "ምድብ "ሐ" ሕንፃ"፡- ማለት የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ ፣የፋብሪካ ወይም የወርክ ሾፕ ሕንፃ ወይም ከመሬት እስከ መጨረሻው ወለል ከፍታ ከ12 ሜትር በላይ የሆነ ማናቸውም ሕንፃ ሲሆን፣ በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ የተካተቱትን ማስተካከያዎች ያካትታል፤

1.2.23. “የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ”፡- ማለት በርካታ እና የተለያዩ ተጠቃሚዎችን የሚስብ እንደ ቲያትር ቤት፣ የሕዝብ ቤተ መፃሕፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ መዝናኛ፣ የትምህርት ተቋም፣ የህክምና አገልግሎት መስጫ፣ የገበያ ማእከል፣ ቅይጥ ህንጻዎች፣

አፓርትመንቶች፣ ሞሎች እና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ህዝብ የሚገለገልበት ሕንፃ ነው፤"

1.2.24. "ወለል"፡- ማለት የምድር፣ ከምድር በላይ እና መሬት ውስጥ ያለ የህንጻ ወለል ማለት ነዉ፤

1.2.25. "የወለል ብዛት"፡- ማለት ከመሬት በታች፣መሬት ላይና ከመሬት በላይ ያሉ የቆጥ ወለሎችን ሳይጨምር አንድ ግንባታ ያሉት አጠቃላይ የወለል ብዛት ማለት ነው፤

1.2.26. "ተካፋች"፡- ማለት በማንኛውም ግንባታ ግድግዳ፣ ጣሪያ ወይም ወለል ላይ የሚገነባ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚከፈት መስኮት ወይም በር ነው፡፡

1.2.27. "ከፍተኛ ማምረቻ ተቋም"፡- ማለት በከተማ አስተዳደሩ ለማምረቻ በተከለለ ቦታ የሚገነቡ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ምርቶችን ሊያመርቱ የሚችሉ፤እንዲሁም በአካባቢው ላይ ተፅኖ ሊያደርሱ የሚችሉ የማምረቻ ተቋማት ማለት ነው፤

1.2.28. "የሕንፃ አዋጅ"፡- ማለት የኢትዮጵያ ሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ነው፤

1.2.29. "የሕንፃ ደንብ"፡- ማለት የሕንፃ አዋጅን ለማስፈፀም የወጣው የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 243/2003 ማለት ነው፤

1.2.30. "*መመሪያና ስታንዳርድ*"፡- ማለት የህንፃ ደንብን ለማስፈፀም የወጣ የተሻሻለው የህንጻ *መመሪያና ስታንዳርድ* ቁጥር 3/2014ነው፤

1.2.31. "ሰው"፡- ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

1.2.32. "ስታንዳርድ"፡- ማለት የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ስታንዳርድ ነው፡፡

1.2.33. "ቀለም" ማለት የህንጻ የውጭ አካል ላይ የሚገኝ ማንኛውም የግንባታ ቁስ ቀለም ነው፡፡

1.2.34. "የህንጻ የውጭ ቀለም" ማለት በህንጻው ውጫዊ አካል ላይ የሚገኝ እንዲሁም ከመንገድ በኩል የሚታይ ማንኛውም ቁስ የሚኖረው ቀለም ነው፡፡

1.2.35. “የአዲስ አበባ ከተማ የህንጻ ቀለም ስታንዳርድ” በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ህንጻዎች እንዲኖራቸው የተመረጡ ቀለማት የህንጻ ቀለማት ናቸው።

1.2.36. “የህንጻ የፊት ለፊት ገጽ” ማለት በመንገድ በኩል የሚገኝ የህንጻው ቅርጽ ወይም ግድግዳ አካል ነው።

1.2.37. “የህንጻ ላይ ማስታወቂያ” ማለት ማንኛውም በህንጻው ላይ የሚደረግ የንግድ ምልክት፣ የማስታወቂያ ቦርድ ወይም ባነር እንዲሁም ዲጂታል ስክሪን ነው።

1.2.38. “የተፈጥሮ ቁስ” ወይም “natural material” ማለት ድንጋይ፣ ማርብል፣ ግራናይት፣ እና እንጨት የመሳሰለ የግንባታ ግብዐት ነው።

1.2.39. “የህንጻ ቁስ” ማለት በህንጻው የውጭ አካል ላይ የሚገኝ የግድግዳ፣ የመስታወት፣ የልባስ (cladding) ፣ የውቅር አካል፣ የፍሬም፣ የጣራ ሽፋን እና ተያያዥ ቁስ የሚሰራበት የግንባታ ግብአት ነው።

1.2.40. “ባለቤት” ማለት የህንጻው ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ነው።

*በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ላይ የሌሉት ትርጓሜዎች በኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

1.3. የተፈጻሚነት ወሰንና መመሪያና ስታንዳርድ ማሻሻል

1.3.1. ይህ መመሪያና ስታንዳርድ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል

I. ይህ መመሪያና ስታንዳርድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ በማንኛውም ግንባታ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

II. ይህ መመሪያና ስታንዳርድ ግንቦት --- ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

III. ይህንን መመሪያና ስታንዳርድ የማሻሻል ሥልጣን የአዲስ አበባ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

1.3.2 ይህ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፣

I. አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተሰጠ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ በመካሄድ ለይ በሚገኝ በማንኛውም ሕንፃ፣

II. ከሀገር ደንነት ጋር በተያያዘ የሕንፃ አዋጁ ተፈፃሚ እዳይሆንበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰኑ ሕንፃ፣

1.3.3 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1.3.2 ድንጋጌ ቢኖርም፣

I. አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በወጣ የህንፃ ግንባታ ፈቃድ መሠረት በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሆኖ ግንባታ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ከሆነ፣

II. አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የተጠናቀቀና አዋጁ ከፀና በኋላ የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት ወይንም የማፍረስ ጥያቄ በሚቀርብበት ሕንፃ ላይ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ተፈፃሚ እንዲሆንበት ማድረግ ይችላል፡፡

ክፍል ሁለት

2.1 የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ማመልከቻ አቀራረብ

በባለሥልጣኑ የማዕከል፣ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ጽ/ቤቶች የሚሰጡ የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ከዚህ በታች ከአንቀፅ 2.1 - 4.5 በተመለከተው መሠረት ይህን መመሪያና ስታንዳርድ፣ የሕንፃ ደንቡንና የሕንፃ አዋጁን ድንጋጌዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ መሠረት በማድረግ ይከናወናሉ፤

2.1 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፡፡

2.2 የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ በቀረበበት በማንኛውም የግንባታ ዲዛይን ሂደት ወቅት የእዳና እገዳ መረጃ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

2.3 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ 001 በመሙላት እና የፕሮጀክቱን ኘላን በማያያዝ በአካል ወይም በድህረ ገፅ አማካኝነት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

2.4 የግንባታ ዲዛይን/ ኘላን በሚቀርብበት ወቅት መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ የማስታወቂያ ሠሌዳ ላይ በግልፅ መዘርዘር አለባቸው፣

2.5 ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ኘላኖች እና ማስረጃዎች፡-

2.5.1 ለሁሉም የህንጻ ምድቦች ተቀባይነት ያለው የይዞታ ባለመብትነት ማስረጃ ቅጂ፣

2.5.2 ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሕንፃ ግንባታ የሚካሄድበትን ቦታ የሚያሳይ ከከተማው ኘላን ላይ የተወሠደ አካባቢውን የሚያሳይ የተሟላ የፕላን ስምምነት መረጃ፣

2.5.3 የኮንክሪት ጣሪያ ለሌላቸው የምድብ “ሀ“ ህንፃዎች የአርክቴክቸር፤ የኤሌክትሪክ የግንባታ ዲዛይኖች/ፕላኖች፤

2.5.4 የኮንክሪት ጣሪያ ላላቸው የምድብ "ሀ" ህንፃዎች የአርክቴክቸር፤ የስትራክቸር የኤሌክትሪክ የግንባታ ዲዛይኖች/ፕላኖች፤

2.5.5 ለሕንፃ ምድብ "ለ" የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪክ የግንባታ ዲዛይን/ፕላኖች፤ ትንታኔ፣ሪፖርት እና የአፈር ምርመራ ሪፖርት፤

2.5.6 ለሕንፃ ምድብ "ሐ" የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪክ፣የእሳት አደጋ መከላከያ የግንባታ ዲዛይን/ፕላን፣ ትንታኔ፣ ሪፖርት እና ሁለትና ከሁለት ወለል በላይ ከፍታ ላላቸው የአፈር ምርመራ ሪፖርት፣ኤሌክትሮ መካኒካል ዲዛይን ለሚያስፈልጋቸው ህንጻዎች ሙሉ የዲዛይን መረጃ፤

2.5.7 ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የህንጻውን ጠቅላላ የወለል ስፋት ከውጪ የግድግዳ ጠርዝ የሚለካ ሆኖ የሁሉንም የወለል ስፋት በመደመር የሚሰላ ወይም ጥቅል ወጪ ግምት፤

2.5.8 ለከፍተኛ ማምረቻ ተቋማት ከአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ማምረቻው በአካባቢው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽእኖ በማጥናት አሉታዊ ተጽእኖ ካለውም ተጽእኖውን ለመቀነስ መካተት ያለበትን የግንባታ አይነት የሚተነትን የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ያቀርባል፡፡

2.5.9 በአደባባይ፤ መንገዶች ላይ ወይም በከተማው ውስጥ ባሉ የህዝብ መተላለፊያ ቦታዎች የሚተከሉ የሃውልት፣ ቅርጻቅርጽ እና ቋሚ የመታሰቢያ ግንባታዎች በሁሉም አቅጣጫ ያለውን ገጽ የሚያሳይ ንድፍና የተሸካሚ አካላትን ስትራክቸራል ዲዛይን ያቀርባል፡፡

2.5.10 አሳንሰር እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን የሚጠቀሙ ህንፃዎች የመካኒካል ቬንትሌሽን እና ኤር ኮንዲሽኒንግ የግንባታ ዲዛይኖች/ፕላኖች እና ትንታኔዎች ይቀርባል፡፡

2.5.11 በአዋሳኝ ባሉ ሥፍራዎች የሚገኙ ዋና መንገዶችና የታወቁ ቦታዎችን ሥም የሚገልጹ መረጃዎች፣

2.5.12 በአዋሳኝ ቦታዎች የሚገኙ ግንባታዎች ከመሬት በላይ እና በታች ያላቸው

የወለል ብዛት፣ ከጋራ ወሰን ያላቸው ርቀት እና ከምድር ወለል በታች ያላቸው ጥልቀት፤

2.5.13 የአማካሪ ግዴታ መግቢያ ቅጽ 010 መሰረት በአማካሪ ደረጃ ለሚሰሩ ዲዛይኑን ባዘጋጀው ባለሙያ የተፈረመ እና ማህተም ያረፈበት፤

2.5.14 ለሁሉም የህንፃ ምድቦች የህንፃውን ፕላን ያዘጋጁ ባለሙያዎች ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤ በዘመኑ የታደሰ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፤

2.5.15 በአማካሪ ድርጅት ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ ፕላኖች የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት እና በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ቅጂ፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የባለሙያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤

2.5.16 ዲዛይኖች በንኡስ አማካሪ/Outsourcing/ የሚሰራ ከሆነ በንኡስ አማካሪ ደረጃ ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ ፕላኖች የንኡስ አማካሪው ማህተም ያረፈበት በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ቅጂ፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፤ የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የባለሙያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤

2.5.17 የማሻሻያ ፈቃድ ከሆነ የቀድሞው የጸደቀውን የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት እና የግንባታ ዲዛይን/ፕላን እንዲሁም ክትትል የተደረገበት የመስክ ሪፖርት ወይም የመስክ ደብተር፤ የማሻሻያ ፈቃድ ከወለል ጭማሪ ዉጭ ቀድሞ አገልግሎቱን ባገኘበት ማዕከል የሚሰጥ ሆኖ ቀድሞ የተሰጣቸዉ የፈቃድ ጊዜ ካልተጠናቀቀ በወቅቱ የቀረቡ ሰነዶችን (የአማካሪና የባለሙያ ፈቃድና ኢንሹራንስ/ከቀድሞ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ/፣ ዕዳና ዕገዳ ማጣሪያ፣ የፕላን ስምምነት ወ.ዘ.ተ) ድጋሚ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፤

2.5.18 በቀረበው ዲዛይን መሰረት የመድን ዋስትና ሽፋን፤

2.5.19 አራት ወራት ያላለፈው የዕዳና ዕገዳ ማጣሪያ ደብዳቤ ከሚመለከተዉ የመሬት ተቋም መቅረብ ይኖርበታል፤

2.6 የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ በአንቀጽ 10.2 መሰረት ቅፅ 009 አጎራባቹን በማስሞላት የሚቀርብ ይሆናል፤

2.7 የግንባታ ፈቃድ በተጠየቀበት ይዞታ የሚገኝ የአጐራባች ባለይዞታ፣ ይዞታውን በሚመለከት የሚቀርብለትን ቅፅ መሙላት ይኖርበታል፤

2.8 የሚቀርቡ ፕላኖች መዘጋጀት የሚኖርባቸው በዲዛይን ባለሙያዎች እና አማካሪዎች ምዝገባ መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚያሚሉና እና ባለሙያዎችን ለመመዝገብና ለመፍቀድ ሥልጣን በተሰጠው አካል በተመዘገቡ ባለሙያዎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

2.9 የዲዛይን አማካሪ ደረጃን በተመለከተ የፌዴራል ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ባወጣው ደንብ እንዲሁም የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣው መመሪያና ስታንዳርድ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

2.10 ከመሪ ፕላኑ መጽደቅ በፊት የግንባታ ፈቃድ የተሰጠው በማንኛውም ምክንያት የግንባታ ፕላን ለውጥ ወይም ማሻሻያ ለማድረግ ሲቀርብ በፈቃዱ ጊዜ ገደብ ውስጥ የግንባታው ዋና አገልግሎት/ ዋና ግንባታ የምድር በታች ወይንም የምድር ወለል የመዋቅር አካላት ካልተጠናቀቁ በስተቀር የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ በጸደቀው የመሪ ፕላን መስፈርት መሰረት እንደ አዲስ የሚታይ ይሆናል፡፡

2.11 ነባር ወይንም ጅምር ግንባታ ጋር በማያያዝ ወይንም በማስተሳሰር ወይንም የህንጻ ከፍታ በመቀጠል ለማሻሻል የሚቀርብ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ከሆነ ከሚቀርበው የዲዛይን ሰነድ ጋር የነባሩ ህንጻ የአፈር አይነት ጥናት፣ የመሰረት አይነትና ጥልቀት፣ የተሰራበት ዓመተ ምህረት፣ ቀድሞ የተገነባው መሰረት እና ሌሎች ተዛማጅ መዋቅራዊ አካላት ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ እና ከላይ የተጠቀሱትን የነባሩን ህንጻ የዲዛይን መረጃ መሰረት በማድረግ አዲስ የስትራክቸራል ዲዛይን ትንታኔ/structural design analysis/ መቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም በቀረበው ትንታኔ /analysis/ እና ከመሬት በታች እና በላይ በተገነባውና

በተሸፈነው መዋቅራዊ አካላት ግንባታ መካከል ሊኖር በሚችል የመጠን ልዩነት ወይንም በሌላ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ችግር የዲዛይን አማካሪው ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

2.2 የኘላን/የግንባታ ዲዛይን አቀራረብ፡-

2.2.1 የማንኛውም ግንባታ ዲዛይን የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርዶችን፣ የህንጻ አዋጅ፣ የህንጻ ደንብ እና የህንጻ መመሪያና ስታንዳርድን በማሟላት ተጠቃሚውንና የአካባቢውን ማህብረሰብ ደህንነት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡

2.2.2 በከተማው ውስጥ ማንኛውም ግንባታ ለማካሄድ በቅድሚያ የግንባታ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም በንዑስ አንቅጽ 10.4 የተዘረዘሩት ስራዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለደረጃ ሶስት የእድሳት አይነት እድሳት ለማከናወን ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልግ የሚሰራውን ስራ ዝርዝር የግንባታ እድሳት ቅጽ 05 በመሙላት ለጽ/ቤቱ በማሳወቅ እድሳት ማከናወን ይቻላል፡፡

2.2.3 በንዑስ አንቀጽ 2.2.2 ላይ የተዘረዘሩትን ስራዎች ከተጠቀሰው መጠን በላይ ወይም የተጠቀሰውን መጠን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ለመስራት የግንባታ ፈቃድ መውጣት አለበት፡፡

2.2.4 የግንባታ ፈቃድ ጉዳይ በግንባታው ባለቤት ወይንም በህጋዊ ወኪል ወይንም ንድፉን ባዘጋጀው አማካሪ ወይም ባለሙያ ብቻ አቅራቢነት መካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም የግንባታ ፈቃዱ ወጪ ሆኖ የሚሰጠው ለባለቤት ወይንም ለህጋዊ ወኪል ብቻ ነው፡፡

2.2.5 በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡ ነገር ግን አንድ አይነት ስታንዳርድ ፕላን ያላቸው ግንባታዎች የየራሳቸው የግንባታ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

2.2.1 ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርብ ዲዛይንና ተዛማጅ ሠነድ በአስተዳደሩ የሥራ ቋንቋ ወይም በእንግሊዘኛ የተፃፈ መሆን አለበት፣

2.2.2 የፕላን መለኪያዎች በሜትሪክ ሲስተም እና በግራፊክስ ስታንዳርድ የልኬት አፃፃፍ መቅረብ አለባቸው፣

2.2.3 የሚቀርቡ የግንባታ ዲዛይኖች/ፕላኖች በ 3 ቅጂ ሆነው እንደአስፈላጊነቱ ቢያንስ በA3 መጠን እና ቢበዛ በA1 መጠን የተዘጋጁ ሆነው በፕላን ኮፒ (BlUE print) ወይም

በባለ 80 ግራም ነጭ ወረቀት ንድፍ መሆን ይኖርበታል፣

2.2.4 የጽሑፉ ሰነድ በA4 መጠን መሆን አለበት፤ ለምድብ "ለ" እና "ሐ" የኤሌክትሮኒክስ ኮፒ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የሕንፃ ሹሙ ሊጠይቅ ይችላል፣

2.2.5 በግንባታ ዲዛይን/ፕላን ወይም በንድፍ መገለጽ ያልቻሉ ዝርዝር መግለጫዎች በፕላኑ ላይ በጽሑፍ መመልከት ይኖርባቸዋል፣

2.2.6 ለሁሉም ሕንፃዎች የወለሉ ከፍተኛ የጎን ስፋት ከ30 ሜትር የማይበልጥ ከሆነ ፕላኖቹ በ1፡50 ሚዛን እንዲሁም የሳይት ፕላኖቹ በ1፡200 ሚዛን እንዲሁም የወለሉ ከፍተኛ የጎን ስፋት ከ30 ሜትር በላይ ከሆነ ፕላኖቹ በ1፡100 ሚዛን እንዲሁም የሳይት ፕላኖቹ በ1፡500 ሚዛን መዘጋጀት ይኖርበታል፣

2.2.7 ዝርዝር ፕላን (detail plan) ለሚዘጋጅላቸው ንድፎች በ1፡10፣ 1፡20፣ ወይም 1፡25 ሚዛን ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

2.2.8 ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ፕላኖች ዝርዝር የፕላን ምድቡ የሚጠይቀውን በማሟላት መለኪያቸው በሜትሪክ ሲስተም ወጥ ሆኖ መገለጽ ይኖርበታል፣

2.2.9 ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ዲዛይኖች ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉት የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፤

3. የፕላን ስምምነት

3.1 አዲስ፣ተጨማሪ እና የማሻሻያ ግንባታ ለማከናወን እንዲሁም ከግንባታ የተወሰደ (As-Built) ፈቃድ የሚፈልግ ሰው የህንፃውን ዲዛይን ከማዘጋጀቱ በፊት የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፣

3.2 የፕላን ስምምነት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ በቅጽ 003 መሠረት ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

3.3 በማመልከቻ ቅጹ ላይ ተሞልቶ የሚቀርብ ጥያቄ በነባር ይዞታ ላይ ለአዲስ ግንባታ የሚጠየቅ ስምምነት ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ቅጂ፣የሊዝ ይዞታ ላይ ከሆነ ደግሞ የሊዝ ውሉን በተጨማሪ የሚያያዝ ሲሆን፤ ለነባር ግንባታ ማሻሻያ ከሆነ፡-

3.3.1 የይዞታ ማረጋገጫ ቅጂ፣

3.3.2 የተፈቀደበትን የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት

3.3.3 የግንባታ ማስጀመሪያ ምስክር ወረቀት እና የመስክ ደብተር ወይም ሪፖርት

3.3.4 የሊዝ ይዞታ ከሆነ የሊዝ ውሉን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

3.4 የፕላን ስምምነቱ በከተማው መሪ ፕላን ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣

3.5 በፕላን ስምምነት መረጃ ላይ የከተማዋ ስታንዳርድ የህንጻ ቀለማት ኮዶች ምርጫና መጠሪያ ተጠቅሶ የሚሰጥ ይሆናል፤

3.6 የፕላን ስምምነቱ በሚመለከተው ባለሙያ እና ኃላፊ ተፈርሞ እና በመ/ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ ለጠያቂው አካል መሰጠት ይኖርበታል፣

3.7 ከላይ በንኡስ አንቀጽ 3.6 በተመለከተው መሠረት የተሰጠ የፕላን ስምምነት ወጪ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ለ12 ወራት ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

4. የኘላን መገምገሚያ ጊዜ

4.1 ማንኛውም ለግንባታ ሥራ የተዘጋጁ ኘላኖች ለየሕንጻ ምድቡ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መገምገም አለባቸው፣

4.2 ለአንድ የሕንጻ ዓይነት የተዘጋጁ የግንባታ ዲዛይኖችን/ፕላኖችን ለመገምገም በአማካይ የሚያስፈልገው ጊዜ፤

4.2.1 ከሪልስቴት ውጪ ላለ በምድብ “ሀ” ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ5 የሥራ ቀናት ያልበለጠ፣

4.2.2 በምድብ “ለ” ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች መገምገሚያ ጊዜ ከ7 የሥራ ቀናት ያልበለጠ፣

4.2.3 በምድብ “ሐ” ስር ለሚካተት ሕንፃ እና በምድብ “ለ” ውስጥ ለሚካተቱ የሪል እስቴት ህንጻዎች ኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ21 የሥራ ቀናት የበለጠ መሆን

የለበትም፡፡

4.3 ከፕሮጀክቱ ስፋት ወይም ውስብስብነት የተነሳ ተጨማሪ ጊዜ ለሚሹ ስራዎች የህንጻ ሹመ ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ ቅጽ 24 በመሙላት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

4.4 ለግምገማ የሚቀርብ ዲዛይን መሻሻል የሚስፈልገው ከሆነ መሻሻል ያለበትን በማመልከት ለአመልካቹ በእርማት መስጫ ቅጽ ተገልጾ ይሰጠዋል፡፡

4.5 ባለስልጣኑ ወይም ጽ/ቤቱ ማመልከቻ በቀረበ ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም የተጠቀሰውን የውሳኔ ማሳወቂያ ጊዜ በየግንባታው ዓይነት ሊቀርቡ የሚችሉትን ከፍተኛ ግንባታዎች ከግምት በማስገባት የተሰጠ የጊዜ ጣሪያ እንጂ እንደ ፕሮጀክቱ መጠን በተነጻጻሪ ከተሰጠው የጊዜ ጣሪያ በፊት ውሳኔ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡

ተ.ቁ	የግንባታው አይነት	የወለል ስፋት	የይዞታ ስፋት በሜ.ካ.	ለምርመራ የሚፈጀው ከፍተኛ ቀን					
				አርክቴክቸራል	ስትራክቸራል	ኤሌክትሪካል	ሳኒተሪ	መካኒካል	ድምር
1.	ነጠላ መኖሪያ ቤት	1	ማንኛውም	3	-	2	-	-	5
2.	ነጠላ መኖሪያ ቤት	/2	"	3	2	1	1	-	7
3.	የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ	ማንኛ ውም	"	8	5	3	3	2	21
4.	ማምረቻና ማከማቻ	"	"	8	5	3	3	2	21
5.	የእድሳት ፈቃድ	"	"	3				-	3
6.	የማፍረስ ፈቃድ	"	"	3				-	3
7.	ከግንባታ የተወሰደ ማሻሻያ	"	"	8	5	3	3	2	21
8.	ልዩ ከግንባታ የተወሰደ	"	"	9	-	-	-	-	9
9.	ጊዜያዊ ግንባታ	"	"	3	-	-	-	-	3

ሰንጠረዥ 4.5 ለአንድ የሕንጻ ዓይነት የተዘጋጁ የግንባታ ዲዛይኖችን/ፕላኖችን ለመገምገም በአማካይ የሚያስፈልገው ጊዜ

5. የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ስለማፀደቅ

5.1 የሕንፃ ሹመ በንዑስ አንቀጽ 4.5 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሠረት የቀረበውን

የኘሮጀክቱን ዲዛይንና ሰነድ ከመሪ ኘላኑ እና ከኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ መስፈርቶች ጋር በማገናዘብና በመመርመር የተሟላ ሆኖ ሲያገኝ በግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጽ 002 ላይ የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ ሥር የሚገኙትን መረጃዎች ሞልቶ ያፀድቃል፡፡ የፀደቁትን ሰነዶች በአንደኛው ኮፒ ላይ "ተፈቅዷል" የሚል ማህተም፤ በሁለተኛው ኮፒ ላይ "ለክትትል ብቻ " የሚል ማህተም ተደርጎባቸው ለአመልካቹ ይሰጣሉ፣ ሦስተኛው ኮፒ "ቀሪ" ተብሎ ከፋይል ጋር ይያያዛል፣

5.2 ከላይ በአንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 5.1 በተመለከተው መሠረት የፀደቀ የግንባታ ዲዛይን/ፕላን የግንባታ ፈቃድ ቁጥር እና የፀደቀበትን ቀን የያዘና የሕንፃ ሹመ ወይም የተሰየመው አካል ፊርማ እና ማሕተም ያረፈበት መሆን ይኖርበታል፣

5.3 የግንባታ ፈቃድ የማያስከለክሉና እርማት ተደርጎባቸው የሚታለፉ ግድፈቶች ፡-

5.3.1 በስትራክቸር ዲዛይን ላይ ለውጥ የማያመጡ እና የተዘነጉ ንድፎች፣

5.3.2 በግንባታ ሂደት ላይ ተጽእኖ የማይፈጥሩ የተዘነጉ ልኬቶች ማስተካከያ የተደረገባቸው፣

5.3.3 በግንባታ ፈቃድ የተቀመጡ ሌሎች ግዴታዎችን ለመወሰንና የክፍሎችን ስፋት እና አጠቃቀም ለመወሰን የግድ መመልከት ካለባቸው በስተቀር የተዘነጉ የመጠቀሚያ ቁስ ንድፍ/Furnishing/

5.4 ደረጃ በደረጃ ወይም በየምእራፉ ለመገንባት የቀረበ ፕላን፡-

5.4.1 የመጀመሪያው የግንባታ ደረጃ ዝቅተኛውን የመሪ ፕላን መስፈርት እና ከመሪ ኘላኑ ዝቅተኛ የሕንፃ ከፍታ ሳያንስ የግንባታ ፈቃዱ ሊሰጥ ወይም ሊፀድቅ ይችላል፣

5.4.2 ዝቅተኛውን የመሪ ፕላን መስፈርት እና ከመሪ ኘላኑ ዝቅተኛ የሕንፃ ከፍታ የማይገደዱ አገልግሎቶች የብሎኮችን ብዛት ደረጃ በደረጃ በመወሰን የግንባታ ፈቃዱ ሊሰጥ ወይም ሊፀድቅ ይችላል፣

5.4.3 ለክትትልና ለመጠቀሚያ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ ያመች ዘንድ በግንባታ ፈቃድ ሰነድ ላይ ደረጃ በደረጃ ለመገንባት የታቀደው በግልፅ ተለይቶ በሚፈቀደው ፕላን ላይ መመልከት ይኖርበታል፣

5.4.4 ደረጃ በደረጃ በመገንባት ሂደት የተወሰነ የግንባታ ክፍል አገልግሎት እየሰጠ ቀሪው ግንባታ የሚካሄድ በመሆኑ የህንጻው ተጠቃሚዎች እና ሌላው በአካባቢው እንቅስቃሴ በሚያደርጉት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በፍቃድ አሰጣጥ ላይ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ በግንባታ ወቅት በአካበባው የሚንቀሳቀስን ሰው ከአደጋ ለመከላከል ገንቢው ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ በግንባታ ወቅት በሚደርስ አደጋ ገንቢው፤ አማካሪው እና ባለቤቱ በጋራ ወይም በተናጠል ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡

5.4.5 ደረጃ በደረጃ በመገንባት ሂደት ወቅት ከላይ የተገለፁት እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ ቀደም የተጠናቀቀው ህንጻ አካል ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች መቋረጥ አለባቸው፡፡ አገልግሎቱ ሳይቋረጥ መገንባት ከተፈለገ መሰረታዊ የመዋቅር አካላት ስራዎች መጠናቀቃቸውን እና የውጭ ግድግዳ አካል ግንባታ የአካባቢውን እንቅስቃሴ የማያውክ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

5.4.6 አሰሪው/ባለቤቱ የቀጣይ ምዕራፍ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ለክትትልና መጠቀሚያ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እንዲያመች ለሕንጻ ሹመ ወይም ለተሰየመው አካል በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡

6. ፕላን ውድቅ ስለማድረግ

6.1 ከህንፃ አዋጁ፣ ከማስፈፀሚያ ደንቡና ከኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ እንዲሁም ከዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ጋር የማይጣጣም የግንባታ ፕላን በህንፃ ሹመ ውድቅ ይደረጋል፣

6.2 ለምርመራ የቀረበው ዲዛይን የግንባታ ፈቃድ መስፈርትና የኢትዮጵያን ህንጻ ስታንዳርድ የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱ የተከለከለበትን ምክንያት ዝርዝር በግንባታ ፈቃዱ መጠየቂያ ቅጽ ላይ ተሞልቶና "አልተፈቀደም" የሚል ማህተም ተደርጐበት ለባለጉዳዩ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

7. በግንባታ ወቅት ፕላንን ስለማሻሻል

በግንባታ ወቅት የዲዛይን ማሻሻያ ስራ ሲያስፈልግ የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ 22 በመሙላት የተሻሻለውን የግንባታ ዲዛይን/ፕላን፣ ግንባታ ከመካሄዱ በፊት ጥያቄውን ለህንጻ ሹሙ ወይም ለተሰየመው አካል በማቅረብ መጽደቅ ይኖርበታል። ሆኖም በህንጻ ሹሙ ወይም በተሰየመው አካል መጽደቅ ሳያስፈልጋቸው የግንባታ ሥራ ለውጥ ማሳወቂያ ቅጽ 17 በመሙላት እና በማሳወቅ መሻሻል የሚችሉ የፕላን አካላትና ዲዛይኖች የሚከተሉት ናቸው፡-

7.1 በፕላን ላይ የሰፈሩ የልኬት ጉድለት ወይም ስህተት፣

7.2 የውስጥ ማከፋፈያ ግድግዳ የተጨማሪ ጭነት በማይፈጥር ቁሳቁስ መለወጥ፣

7.3 የኤሌትሪክ ነጥቦች ሳይቀየሩ የሚደረግ የኤሌክትሪክ መስመር አቅጣጫ ለውጥ ስራ፣

7.4 የክፍል ውስጥ ማሥጌጥ ሥራ፣

7.5 በግንባታ ዲዛይን/ፕላን ላይ በከፊል ወይም በጥቅል የተገለፀና ዝርዝር መስፈርታቸው ወይም መለኪያቸው ያልተካተተ ስታንዳርድ ያላቸው የፋብሪካ ውጤቶች፣

7.6 በንድፍ ላይ በግንባታ ወቅት በመሐንዲሱ እንደሚወሰኑ የተገለጹ ሌሎች ስራዎች፣

7.7 የውስጥ ክፍሎች የወለል ንጣፍ ሥራ፣ከሕዝብ መገልገያ ውጪ ለሆኑ ሕንጻዎች

7.8 የጣሪያ ልባስ ቁስ፣ የኮርኒስ፣ የአሸንዳና ጎረንዳዮ ቁሳቁስ ለውጥ፣

7.9 የግቢ ማስዋብ ሥራ፤

7.10 የውቅር አካላትን የማያናጉና አርክቴክቸራል ቅርፁን (form) የማይቀይሩ የውስጥ ቀለም ቅብ፣ ስታንዳርዱን የጠበቀ መስታወት መቀየር፣ ቀላል ክብደት ባላቸው የሚገነቡ የውስጥ ማከፋፈያ ግድግዳዎች፣ ነባር የመብራትና የሳኒታሪ መገጣጠሚያዎችን የመለወጥ ሥራ ናቸው።

8. የግንባታ ፈቃድ

8.1 የፀደቀ የግንባታ ዲዛይን (ፕላን) እንደ ግንባታ ፈቃድ ያገለግላል፣

8.2 የግንባታ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የግንባታ ሥራዎች፡-

8.2.1 አዲስ የግንባታ ሥራ፣

8.2.2 ከውስጥ የቀለም ቅብ እና የማጠናቀቂያ ሥራዎች ውጪ ያሉ የጥገና እና የእድሳት ስራዎች፤

8.2.3 ግንባታ የማስፋፋት እና የማሻሻል ሥራ፣

8.2.4 ግንባታ የማፍረስ ሥራ፣

8.2.5 የሕንፃ አገልግሎት ለውጥ፣

8.2.6 የጊዜያዊ ግንባታ፤

8.2.7 የአጥር ግንባታ ስራ፤ በማሳወቂያ ከሚሰራው ውጭ ላሉ፤

8.2.8 የምሽት ግንባታ ስራ፤

8.2.9 ከግንባታ የተወሰደ (AS-Built) ማሻሻያ ፈቃድ፤

8.2.10. ልዩ ከግንባታ የተወሰደ (Special AS-Built) ፈቃድ፤ ናቸው፡፡

8.3 ቀደም ሲል የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ በተለያየ ሁኔታ እንዲለወጥ ሲወሰን በአዲስ ተተክቶ ለባለይዞታው ይሰጣል፣

8.4 በአንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 9.2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የግንባታ እንቅስቃሴ ተጀምሯል የሚባለው የመሠረት ቁፋሮና ለመሠረት ግንባታ የሚያስፈልግ ብረት አቅርቦት ዝግጅት ሲጀመር ነው፡፡

8.6 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊታገድ ይችላል፣

8.6.1 ግድፈት እያለበት በስህተት የፀደቀ ፕላን ሆኖ ሲገኝ፣

8.6.2 የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ የተሳሳተ መረጃ ከያዘ፣

8.6.3 ግንባታው ተቀባይነት ካለው ገደብ በላይ የሆነ የአካባቢ ብክለት የሚያስከትል መሆኑ ሲደረስበት፤

8.6.4 አሰሪው ከተፈቀደለት ዲዛይን ውጪ እየሰራ ቢገኝ፣

8.7 በግንባታ ቦታ ላይ የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ ወይም የግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር የያዘ የማስታወቂያ ሰሌዳ በግልጽ ቦታ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡

9. የግንባታ ፈቃድ የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ

9.1 አንድ የግንባታ ፈቃድ እንዲያገለግል በተሰጠበት የጊዜ ገደብ ውስጥ መሠረታዊ የግንባታ ሥራ ካልተጠናቀቀ የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ቅጽ 23 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብና ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

9.2 የጊዜ ገደብ

9.2.1 በአስተዳደሩ እና በአልሚው መካከል የተገባ የግንባታ መጀመሪያ እና ማጠናቀቂያ የተለየ የጊዜ ገደብ ውል ከሌለ በስተቀር ጸድቆ ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ የሚያገለግለው ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 9.3 ለተመለከተው ጊዜ ድረስ ይሆናል፡፡

9.2.2 በተራ ቁጥር 9.3 የተመለከተው ጊዜ ፈቃዱ አገልግሎት የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ጣሪያ ሆኖ በአስተዳደሩ እና በአልሚው መካከል የተገባ የግንባታ መጀመሪያ እና ማጠናቀቂያ የተለየ የጊዜ ገደብ ውል ከሌለ በስተቀር ለማንኛውም የግንባታ ደረጃ ግንባታው ፈቃድ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካልተጀመረ የግንባታ ፈቃዱ አያገለግልም፡፡ ሆኖም ግን ስድስት ወራት ያለፈው የግንባታ ፈቃድ በወቅቱ ካለው የከተማ ፕላን ህግጋት፣ ደንብ እና ሌሎች ተያያዥ ህጎችን እስካሟላ ድረስ የግንባታ ማስጀመሪያ ማራዘሚያ ፎርም ሞልቶ ባቀረበው መሰረት በህንጻ ሹመ ታይቶ ሊራዘምለት ይችላል፡፡

9.3 የጊዜ ገደብ ሰንጠረዥ

የግንባታ ፈቃድ የአገልግሎት ማብቂያ ዘመን በግንባታ ፈቃድ ሰነድ ላይ ከዚህ በታች የተመለከተው የጊዜ ጣሪያ እና በአንቀጽ 9.2 የተጠቀሰው የአገልግሎት ዘመን ይኖረዋል፡፡

የግንባታ ደረጃ	የግንባታ አይነት	ፈቃድ የሚጸናበት የጊዜ ጣሪያ
አነስተኛ	ለአንድ ወለል ነጠላ መኖሪያ ቤቶች	1 ዓመት
መካከለኛ	• የምድር በታች ሳይቆጠር እስከ አራት ወለል እና ከዚያ በታች ለሆነ ነጠላ የመኖሪያ ህንጻ	3 ዓመት
ከፍተኛ	• ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ግንባታዎች • ከዚህ በታች በተጠቀሰው ዝርዝር መሰረት ለሚቀርቡ ተቋማት 1. የመኖሪያ ቤት በአንድ ጊዜ እስከ መቶ ነጠላ ቤቶችና ከዚያ በላይ፤ 2. ለትምህርት ቤት ተቋማት እስከ ሁለተኛ ከፍተኛ ደረጃ እና ከዚያ በላይ፤ 3. ለጤና ማዕከል እስከ ከፍተኛ ልዩ ክሊኒክ እና ከዚያ በላይ፤ 4. ለቤተ መጻህፍትና ለሁለገብ አዳራሾች እስከ 500 ሰው የሚይዙ እና ከዚያ በላይ፤ 5. ለስፖርት ሜዳዎችና ማዕከል እስከ 500 ሰው የሚይዙ እና ከዚያ በላይ፤ 6. አጠቃላይ መካከለኛ እና አነስተኛ የማምረቻ እና ማከማቻ ተቋማት፤ 7. በዓለም ወይም በሀገር ወይም በከተማ አቀፍ ደረጃ ለሚገነቡ የትራንስፖርት መናኸሪያ ተቋማት 8. የዲፕሎማቲክ ተቋማት 9. ከላይ በአነስተኛ እና በመካከለኛ ደረጃ ከተጠቀሱት ውጭ ላሉ ግንባታዎች	5 ዓመት

ሰንጠረዥ 9.3፡- ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የግንባታ ደረጃ የጊዜ ገደብ የሚገልጽ

10. የግንባታ ፈቃድ ስለመጠየቅ

10.1 አጠቃላይ

10.1.1 ማንኛውም ሰው አዲስ" ተጨማሪ" የማሻሻያ፣ከግንባታ የተወሰደ/As-Built/፣ የአገልግሎት ለውጥ፣ ጊዜያዊ ግንባታ፣የመጠቀሚያ ፈቃድ ወይም የማፍረስ ሥራ ለማከናወን ሲያቅድ በቅድሚያ የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል ፣

10.1.2 አዲስ" ተጨማሪ" የማሻሻያ፣ከግንባታ የተወሰደ/As-Built/፣የመጠቀሚያ ፈቃድ፣ የአገልግሎት ለውጥ፣ ጊዜያዊ ግንባታ ወይም የማፍረስ ሥራ ለማከናወን የሚቀርብ የግንባታ ፈቃድ ጥያቄ ለአዲስ ለማስፋፊያ፣ ለማሻሻያ ግንባታ ወይም ከግንባታ የተወሰደ /As-Built/ በቅፅ 001፤ ለግንባታ እድሳት ፈቃድ በቅፅ 005" ለግንባታ ማፍረስ ፈቃድ ቅጽ 006፣ ለአገልግሎት ለውጥ ቅጽ 007፣ ለጊዜያዊ ግንባታ ቅጽ 020 በመሙላት የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ እና የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በሃላፊ ተፈርሞ እና የድርጅቱ ማህተም አርፎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል።

10.1.3 በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡ አንድ ዓይነት ስታንዳርድ ፕላኖች ያላቸው ግንባታዎች የየራሳቸው የግንባታ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፣

10.2 የወሰን ላይ ግንባታ

10.2.1 የአዋሳኝ ቦታዎች መረጃ የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ ቅፅ 009 አጎራባቹን በማስሞላት የሚቀርብ ይሆናል፤ አጎራባቹ በማሳወቂያው መሰረት መረጃውን የመሙላት ግዴታ ያለበት ሲሆን ማሳወቂያ ቅጹን እንዲሞላ በተሰጠው በሦስት ተከታታይ ቀናት ሞልቶ ለገንቢው ካልመለሰ መረጃውን ለመሙላት ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ገንቢው ኃላፊነት በመውሰድ እና በቅጽ-009 ቁጥር 3 ላይ የአዋሳኝን ቅድሚያ ስምምነት ሳይጠየቅበት ግዴታ በመግባት የሚካሄድ የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ በሚለው ላይ ግዴታ ገብቶ የግንባታ ፈቃድ መውሰድ ይችላል።

10.2.2 የወሰን ላይ ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት ወሰንተኛ የሆኑ ተጎራባቾች ግንባታው ለደህንነታቸው አስጊ ያለመሆኑን እና ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ ተወስዶ እየተከናወነ

መሆኑን በመመልከት ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

10.2.3 ማንኛውም ሰው በሚሰራው ግንባታ ምክንያት የአዋሳኝ ነባር ግንባታ ደህንነት አደጋ ላይ የማይወድቅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

10.2.4 ማንኛውም የግንባታ አካል ወይም ተንጠልጣይ ወለል ጭምር ከ2.00 ሜትር ርቀት በታች ከወሰን ተጠግቶ የሚገኝ ከሆነ ወሰን ላይ እንዳለ ግንባታ ይቆጠራል::

10.2.5 አንድ ግንባታው ወሰን ላይ እንዲገነባ ፈቃድ ቢሰጠውም ማንኛውም ተካፋች ከወሰን መራቅ ያለበትን ርቀት ጠብቆ መገንባት አለበት፡፡

10.2.6 ወሰን ላይ የሚገነባ የምግብ ማብሰያ እና መሰል አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ግድግዳ የእሳት ቃጠሎን በተሻለ ሁኔታ መከላከል በሚችል ድፍን የግድግዳ ቁስ መገንባት አለባቸው፡፡

10.2.7 አስቀድሞ ወሰን ላይ የገነባ ወሰንተኛ ያገኘውን ወሰን ላይ የመገንባት መብት/ጥቅም የኋላ ገንቢውም በተመሳሳይ መልኩ ወሰን ላይ የመገንባት እና የመሪ ፕላኑ የህንፃ ከፍታ ህግጋት ጠብቆ ህንፃ መገንባት ይችላል፡፡

10.2.8 ከወሰንተኛ ግንባታ ጋር የተያያዘ እና የጋራ የሆነ ጣሪያ ወይም ግድግዳ ካለው፤ በአዋሳኝ ያለን ግንባታ ለማሻሻል፤ ለማደስም ሆነ ለማፍረስ የጋራ የሆነውን ግንባታ ባለበት እንደጠበቀ፤በማሻሻያው ግንባታ ማፍረስ ሂደት የህንፃው ደህንነት ለመጠበቅ ግዴታ በመግባት በፈቃዱ መሰረት መፈፀም ይቻላል፡፡

10.2.9 ማንኛውም ወሰን ላይ የሚገነባ ህንፃ ዲዛይን ጥናት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ታሳቢዎች ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡፡ ማንኛውም ግንባታ/የምድር በታች ወለል ቢኖረውም ባይኖረውም/ከወሰን 2 ሜትርና ከዚያ በታች ተጠግቶ የሚገነባ ከሆነ፡-

ሀ. ለፈቃድ የሚቀርበው ስትራክቸራል ዲዛይን የወሰንተኛውን ነባር የህንፃ መዋቅር ይዘት ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ይህም በሚቀርበው የዲዛይን ሰነድ የወሰንተኛውን ነባር የህንፃ መጠን ለምሳሌ ጭነት /load/ ከግምት ያስገባበትን ማመልከት አለበት፡፡

1. ከመሬት በታች ያለው የመሰረት ዓይነት
2. ከመሬት በታች ያለው የወለል ብዛት
3. ከመሬት በታች ያለው የመሰረት ጥልቀት
4. የወሰንተኛ ነባር ህንፃ ከወሰን ያለው ርቀት ጨምሮ መዘርዘር አለበት፡፡

ለ. በአመልካች ሊሰራ በታቀደው ግንባታ ምክንያት በወሰንተኛ ነባር ግንባታ ደህንነት ላይ ምንም ዓይነት መናጋት እንዳይፈጠር በቁፋሮና በግንባታ ሂደት መወሰድ የሚኖርበት የጥንቃቄ ግንባታ ንድፍ ለፈቃድ ከሚቀርበው ሰነድ ጋር ቀርቦ ፈቃድ ማገኘት አለበት፡፡

10.2.10 ከወለል ከ1.70 ሜትር በላይ ከፍ ባለ ዝግ ወይም ተካፋች መስኮት በተገጠመለት በኩል ያለ ግንባታ ከወሰን ቢያንስ በ1.50 ሜትር ርቀት መገንባት አለበት፣ከ1.70 ሜትር በታች መስኮት ያለው የግንባታ ገጽ ከወሰን ቢያንስ 2.00 ሜትር መራቅ አለበት፣

10.2.11 አየር ማስገቢያ ሳይኖረው ብርሃን ብቻ የሚያስገባ ግንባታ ወሰን ላይ ለመሥራት ለዚሁ ተብለው በተዘጋጁና አሳልፈው በማያሳዩ ውፍረታቸው ከ5 ሳ.ሜ የማያንስ የመስታወት ግርግዳ መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህም በሚቀርበው ዲዛይን ላይ በግልጽ መጠቀስ ሲኖርበት ወሰን ላይ የተሰራ ከሆነ ወሰንተኛው እንደ ማንኛውም ድፍን የግድግዳ አካል አስጠግቶ ሊሰራበት ስለማይከለከል የብርሃን ማስገቢያ መስፈርት ለሚጠየቅበት ተጨማሪ ወይም አማራጭ የብርሃን ምንጭ ማመልከት አለበት፣

10.2.12 በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ ተግባር ያለው ማምረቻ ወይም ወርክሾኘ ሞተሩ ከወሰን ቢያንስ 6 ሜትር መራቅ አለበት፣

10.2.13 ማንኛውም ተካፋች ከወሰን ሊኖረው የሚገባው ርቀት በመስፈርቱ መሰረት መጠበቅ ያለበት ሲሆን በወሰንና በተካፋች መካከል መኖር የሚገባው ርቀት በአዋሳኞች የጋራ ስምምነት ሊቀየር አይችልም፡፡

10.2.14 ከመንገድ መራቅ ካለበት ርቀቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ካልተመራ ክፍት ቦታ ወይም ተመርቶ ካልተሰራበት ወይም መንገድ የሚዋሰን ማንኛውም ግንባታ ለመገንባት አዋሳኝን ማሳወቅ አያስፈልግም፡፡

10.2.15 ማንኛውም ሠው ግንባታውን እስከ ወሠን አስጠግቶ ማከናወን ይችላል ሆኖም ወሠን ላይ ለመገንባት ያቀደ ሰው፡፡

10.2.15.1 ግንባታው ተጀምሮ እስኪጠናቀቀ ድረስ በአጐራባቹ አደጋና ችግር በማያስከትል ሁኔታ መከናወን አለበት፡፡

10.2.15.2 በማንኛውም ጊዜ ወሰንተኛው ግንባታውን እንዲከታተል መፍቀድ አለበት፡፡

10.2.15.3 በማንኛውም የወሰን ላይ ግንባታ ሂደት ለሚፈጠር ችግር ገንቢው እና አማካሪው ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡

10.2.15.4 በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ተወስደው ያልታሰበ ችግር ቢፈጠር ገንቢው፣ ባለቤቱና እና አማካሪው አስፈላጊው የእርምት እርምጃ መወሰድ አለባቸው፡፡

10.2.15.5 አማካሪው በተፈቀደው የወሰን ላይ ግንባታ ዲዛይን መሰረት ግንባታው ስለመከናወኑ ኃላፊነት አለበት፤

10.2.15.6 በወሰን ላይ ግንባታ የመሰረት ቁፋሮ ሲከናወን በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ ES-3965 OCCUPATIONAL HEALTH AND SAFETY ክፍል 6 መሰረት መከናወን አለበት፡፡

10.2.16 የሕዝብ መፀዳጃ ግንባታ ከወሰን 2.5 ሜትር እርቆ መገንባት አለበት፣

10.2.17 የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ከጣሪያው ከፍታ አንድ ሜትር ከፍ ማለትና ከወሰን ቢያንስ 1 ሜትር መራቅ ይኖርበታል፣

10.2.18 በአዋሳኝ መንገድ የቆሻሻ ፍሳሽ መሥመር ከሌለ ወይም የቦታ ተፈጥሮአዊ ተዳፋት የህንጻ አቀማመጥ የማይፈቅድ ከሆነ ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ ማስወገጃ ጉድጓድ /ሲስፑል/ ሴፕቲክ ታንክ የውስጥ ጉድጓድ ገጽ ከማንኛውም ወሰን 150 ሳ.ሜ. ርቆ በይዞታ ውስጥ መገንባት ይችላል፡፡ ሆኖም የታችኛውና የላይኛው ሶሌታ አርማታ እንዲሁም ግድግዳው ውሀ የማያሰርግ ሆኖ የተሰራና የመዋቅር ዲዛይኑ ከቀረበና በሚመለከተው አካል ከተፈቀደ ከወሰን አስከ 50 ሳ.ሜ ተጠግቶ መስራት ይቻላል፣

10.2.19 የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ማስተንፈሻ ቱቦ መውጫ ከወሰን በአንድ ሜትር ርቀት መተከል አለበት፣

10.3 የፅድሳት ፈቃድ

10.3.1 በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገቡና ታሪካዊ እሴት ያላቸው ሕንጻዎች ለማደስ በቅድሚያ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፣

10.3.2 ማንኛውም የግንባታ እድሳት ለማግኘት የሚፈለግ ሰው ፈቃድ ለማግኘት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል የግንባታ እድሳት ማመልከቻ ቅጽ 005 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፣

10.3.3 የግንባታ እድሳት ማመልከቻ ቅጽ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ ፣በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በድርጅቱ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል ፣

10.3.4 ለመኖሪያ ቤቶች የሚደረግ እድሳት የቁስ ለውጥ ቢኖረውም ባይኖረውም ፕላን ማቅረብ ሳያስፈልግ የእድሳቱ ፈቃዱ የሚሰጥ ይሆናል፤ ፈቃዱ ሲሰጥ የግንባታው ሁሉንም ገጾች ልኬት እና የተሰራበት ቁስ በፈቃድ ክፍሉ ባለሙያ በመስክ ተወስዶ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ መቀመጥ ይኖርበታል። ሆኖም ግን የእድሳት ስራው በቅርስነት የተመዘገበ ግንባታ ላይ የሚከናወን ከሆነ የእድሳት ስራውን ፕላን እና ከቅርስ መዝጋቢው አካል የድጋፍ ማስረጃ በማቅረብ ይኖርበታል።

10.3.5 በህዝብ መገልገያ ህንጻዎች ላይ የሚከናወን እና መዋቅራዊ አምዶችን የሚነካ እድሳት ስራ ለማከናወን የእድሳት ስራውን ፕላን በማቅረብ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን የእድሳት ስራው ተገቢው የደህንነት ጥንቃቄ እርምጃዎች በመውሰድ የሚከናወን ይሆናል።

10.3.6 ከግንባታ እድሳት መጠየቂያ ቅጽ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሠነዶች፤

ሀ) ከዋናው ጋር የተመሳከረ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣ ይዞታው በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወይም ቤቶች ኮርፖሬሽን የተያዘ ከሆነ የኪራይ ውል ቅጂ እንዲሁም የመንግስት ቤቶችን በተመለከተ የፌደራል ቤቶች ከከተማው አስተዳደር ጋር በሚገቡት

ውል መሰረት ይፈጸማል፡፡

ለ) ከታች በንዑስ አንቀፅ 10.4 በተገለፀው የዕድሳት ደረጃዎች መሰረት ለደረጃ አንድ ብቻ ለተጠቀሱት የዕድሳት ስራዎች የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

- የግለሰብ ቤት ከሆነ የዕዳና ዕገዳ መረጃ፤
- የሚታደሰውን የህንጻ አካል ገጽና ቁስ (Elevation and Building Material) ነባር ሁኔታና የህንጻውን አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍና ፎቶ(existing building picture) ዝርዝር መግለጫ፤
- ከእድሳት ጠያቂው አካል ጋር ቁስ ለውጦ ለሰራበት ካሳ ላለመጠየቅ ግዴታ የገባበት ውል፣
- በአማካሪ ድርጅት ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ ፕላኖች የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት እና በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ቅጂ፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የባለሙያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤
- ዲዛይኖች በንኡስ አማካሪ/Outsourcing/ የሚሰራ ከሆነ በንኡስ አማካሪ ደረጃ ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ ፕላኖች የንኡስ አማካሪው ማህተም ያረፈበት በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ቅጂ፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፤ የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የባለሙያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤
- ግድግዳ ወይም ጣሪያ የሚጋሩ ወሰንተኞች ካሉ በሚጋሩት ወሰን በኩል ስለሚካሄደው የእድሳት ስራ የወሰንተኛውን ንብረት ደህንነት ያገናዘበ ጥናት መቅረብ ይኖርበታል፣

ሐ) ከታች በንዑስ አንቀፅ 10.4 በተገለፀው የዕድሳት ደረጃዎች መሰረት ለደረጃ ሁለት ብቻ ለተጠቀሰው የዕድሳት ስራዎች የእድሳት ስራውን የሚገልጽ ስኬች ወይም ንድፍ መቅረብ አለበት፤

10.3.7 ከዕድሳት ፈቃድ ቅጽ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች ተሟልተው ሲቀርቡ ብቻ ማመልከቻው እንደቀረበ ይቆጠራል፡፡ ለአመልካች የማመልከቻ መቀበያ ማረጋገጫ እና የግንባታ ዕድሳት ፈቃድ መውሰጃ ቀጠሮ መስጫ ፎርም ወዲያው ይሰጠዋል፡፡

10.3.8 የደረጃ 1 እና ደረጃ 2 የዕድሳት ስራዎች በአንድ ፈቃድ ከተጠየቁ በደረጃ አንድ የውሳኔ ማሳወቂያ ጊዜ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

10.3.9 የግንባታ ዕድሳት ፈቃድ ጠያቂው በቅጹ ላይ የሞላው መረጃ ትክክለኛ ያለመሆኑ ሲረጋገጥ ማመልከቻው ወይም ፈቃዱ ተሰርዞ ከፋይሉ ጋር ይያያዛል፡፡ በዕድሳት ግንባታ ላይ ያለ ከሆነም ግንባታው ወዲያው እንዲቆም እና በፈቃድ ጠያቂው ኪሳራ ተገቢው እርምት እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡ በተሳሳተ መረጃ ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም ችግር ፈቃድ ጠያቂው ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

10.3.10 የአጥር ዕድሳት በመሪ ፕላኑ ወይም በውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ላይ የተቀመጠውን የመንገድ ስፋት በመጠበቅ የሚፈቀድ ይሆናል፡፡ የአጥር ዕድሳት ስራ የመሪ ፕላኑ ላይ የተቀመጠውን የመንገድ ስፋት የማይጠብቅ ከሆነ የመሪ ፕላኑ ወይም የውስጥ ለውስጥ መንገድ እስኪተገበር ድረስ በነበረበት ቁስ ብቻ የሚፈቀድ ይሆናል፡፡

10.3.11 የአጥር ዕድሳት አጥሩ ቀድሞ ከነበረበት ቦታ እንዲቀየር የሚጠይቅ ቢሆንም በዕድሳት ድንጋጌ እና የአገልግሎት ክፍያ መሰረት የሚፈቀድ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከሌሎች ግንባታዎች ጋር የሚቀርብ የአጥር ዕድሳት ጥያቄ በግንባታ ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ መሰረት የሚፈቀድ ይሆናል፡፡

10.3.12 የአጥር ዕድሳት ስራ የአጥር ስታንዳርድ መስፈርትን እንደጠበቀ ሆኖ የአጥሩን ግንባታ ቁስ መቀየርን ሊያካትት ይችላል፡፡

10.3.13 በአንድ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ ከአንድ በላይ የቤት ባለቤቶች ለመኖራቸው በተጠቀሰበት ሁኔታ የሚቀርብ የአጥር ዕድሳት ጥያቄ የሁሉም

የቤት ባለቤቶች በዕድሳት ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ላይ በጋራ አመልካችነት ሲያመለክቱ የሚፈቀድ ይሆናል፡፡ ሆኖም ይዞታውን ውስጥ ለውስጥ በአጥር ለማካፈል የሚቀርብ ጥያቄን አይመለከትም፡፡

10.3.14 ጸድቆ የተሰጠ የዕድሳት ፈቃድ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡

10.3.15 በንዑስ አንቀፅ 10.4 በተገለፀው የዕድሳት ደረጃዎች መሰረት ለደረጃ አንድ ብቻ እድሳት የተጠየቀበት ማንኛውም ቤት የመሪ ፕላን ወይም የውስጥ ለውስጥ መንገድ ቢኖሀውም ወይም የፕላን ተቃርኖ ቢኖረውም ለግምት በሚያመች ሁኔታ በሁሉም አቅጣጫ አስፈላጊ የሆነውን የቤቱን አካል ፎቶ በማንሳት፣ የቤቱን ሙሉ ልኬት በንድፍ በመስራት፣ ነባር ቤቱን አጠቃላይ ይዘት በመግለጽ፤ ከእድሳት ጠያቂው አካል ጋር ቁስ ለውጦ ለሰራበት ብቻ ካሳ ላለመጠየቅ ግዴታ የገባበትን ውል በማያያዝ፣ ህንጻ ሹሙ ወይም የተሰየመ አካል ቦታው ድረስ በመሄድና በማረጋገጥ የእድሳት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

10.3.16 በንዑስ አንቀፅ 10.4 በተገለፀው የዕድሳት ደረጃዎች መሰረት ለደረጃ አንድ ብቻ እድሳት የተጠየቀበት ማንኛውም የግንባታ እድሳት መሰረት እና መዋቅር ካለው መሰረት እና መዋቅሩ ሳይፈርስ፤ መሰረትና መዋቅር ከሌለው ደግሞ ፈርሶ ወይም ሳይፈርስ፤ ግንባታው ያረፈበት ስፋትና ርዝመት ለውጥ ሳይኖረው፤ ቀድሞ የነበረበትን ቦታ ሳይቀይር፤ ከፍተኛውን የወለል ከፍታ ሳያልፍና የቆጥ ወለል ሳይጨምር፤ በተሻለና የአካባቢውን ውበት ወይም ገጽታ በማያበላሽ መልኩ፣ የግንባታ ቁስ ለውጥ ማድረግ፣ የበርና መስኮት መጠን ብቻ በመቀየር የግንባታ ፈቃድ መመሪያና ስታንዳርድ ህግጋትን አሟልቶ መፈቀድ አለበት፡፡

10.3.17 በንዑስ አንቀፅ 10.4 በተገለፀው የዕድሳት ደረጃዎች መሰረት ለደረጃ አንድ ብቻ ዕድሳት የተሰጠው ማንኛውም ግንባታ፣ ዕድሳት ካደረገበት ቀን አንስቶ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ከቆየ፣ ቦታው ለልማት ከተፈለገ ዕድሳት ለተደረገበት የካሳ ክፍያ ይከፈላል፡፡ የዕድሳት ፈቃድ የወሰደ ባለቤት ወይም ተቋም የዕድሳት ስራ ከማከናወኑ በፊት ፈቃድ ለሰጠው አካል የዕድሳት ስራውን ሊጀምር እንደሆነ በአካል ቀርቦ ማሳወቅ አለበት፡፡

10.3.18 ተነጻጻሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያላቸዉ ባለይዞታዎች የእድሳት ፈቃድ ለማግኘት በተናጠል አገልግሎቱን መጠየቅ ይችላሉ፤ ነገር ግን

ማስፋፊያና አዲስ ግንባታ ለመገንባት ከፈለጉ የሁሉንም ባለይዞታዎች የሁንታ ማግኘት አለበት፡፡

10.4 የዕድሳት ደረጃዎች

ደረጃ 1፣

❖ ከ3 የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእድሳት ፈቃድ የሚሰጥባቸው የግንባታ ዓይነቶች፣

ሀ. ነባሩን ግንባታ በመቀየር የሚሰራ የአዲስ ግድግዳ ግንባታ እና ዕድሳት ስራ፣

ለ. ግድግዳው ሳይፈርስ ልባሱን የማደስ ስራ /እንደ ግርፍና ልስን ሥራ ዓይነት/፣

ሐ. የጣሪያው መዋቅር ፈርሶ የጣሪያ ልባስ ዕድሳት፣

መ. የመስኮትና በር መጠን እንዲሁም የቁስ ለውጥ ኖሮት የዕድሳት ስራ፣

ሠ. የመሪ ፕላን መስፈርት ጠብቆ እና ቁስ ለውጦ የሚሰጥ ማንኛውንም አይነት የአጥር ዕድሳት ስራ፣

ረ. መወጣጫ (Scaffolding) ለሚጠይቁና ሶስት ወለል እና በላይ ለሆኑ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የቀለም ቅብ ወይም ሌሎች የማጠናቀቂያ ስራዎች ዕድሳት ስራ፤

ሰ. አዲስ የደጋፊ ግንብ ሥራ፣

ደረጃ 2፣

❖ የዕድሣት ጥያቄ በተጠየቀ ከአንድ የስራ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የሚሰጥባቸው የዕድሳት ስራ አይነቶች፣

ሀ. የጣሪያው መዋቅር ሳይፈርስ ከ20 ካሬ ሜትር ስፋት በላይ የጣሪያ ልባስ ዕድሳት፣

ለ. የፍሳሽ መስመር ጥገና፣

ሐ. እስከ G+1 ድረስ ላለ የህዝብ መጠቀሚያ ተቋም ቀለም ቅብ፣

መ. ከ40 ካሬ ሜትር በላይ ለሆነ የግቢ ወለል ንጣፍ፣

ሠ. የአሌክትሪክ መስመር ጥገና

ረ. የመስኮትና በር መጠን እንዲሁም የቁስ ለውጥ ሳይኖር የዕድሳት ስራ ፣

ሰ. አጠቃላይ ከመሬት በታችና በላይ ያለው መጠን ከ2.5 ሜ.ኩ. በልጦ ከመሬት በላይ ቁመቱ ከ40 ሳ.ሜ. ርዝመቱ ከ5.00 ሜትር በላይ የሆነ ደጋፊ የግንብ ጥገና፤

ሸ. የመሪ ፕላን መስፈርት መንገድ ሳይጠብቅ እና ቁስ ሳይለውጥ ቀድሞ በነበረበት ቦታ የሚሰጥ ማንኛውንም አይነት የአጥር ዕድሳት ስራ፣

በ. የቁስ ለውጥ ሳይኖር ከመሬት በላይ ቁመቱ ከ90 ሳ.ሜ. ስፋቱ ከ3.5 ካ.ሜ የበለጠ ግድግዳን ማደስ፣

ደረጃ 3፣

❖ ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልግ ነገር ግን የዕድሳት ቅጽ በመሙላት ሥራው ከመሠራቱ አንድ ቀን በፊት በጽ/ቤቱ ድህረ ገጽ ወይም በአካል በመቅረብ ለጽ/ቤቱ በማሳወቅ ብቻ መሰራት ያለባቸው የዕድሳት ሥራዎች፣

ሀ. የህዝብ መጠቀሚያ ላልሆኑ ግንባታዎች ተቋም ቀለም ቅብ፣

ለ. የግድግዳ ወረቀት የመለጠፍ ስራ፤

ሐ. የመስታወት የመቀየር ሥራ፣

መ. ያረጁ ቋሚ የመገልገያ እቃዎችን መቀየር ስራ ለምሳሌ የውሃ ማጠራቀሚያ ወይም የማጠቢያ ገንዳ፣ ወይም የሽንት ቤት መጠቀሚያዎችን፣

ሠ. እስከ 40 ካሬ ሜትር እና 40 ካሬ ሜትር ለሆነ የግቢ ወለል ንጣፍ እና የወደቀ አጥርን ባለበት የማንሳትና የማስተካከል ሥራ፣

ረ. የቁስ ለውጥ ሳይኖር ከመሬት በላይ ቁመቱ 90 ሳ.ሜ. እና ከ90 ሳ.ሜ. እንዲሁም ስፋቱ 3.5 ካ.ሜ. እና ከ3.5 ካ.ሜ ያልበለጠ ግድግዳን ማደስ፣

ሰ. አጠቃላይ ከመሬት በታችና በላይ ያለው መጠን 2.5 ሜ.ኩ. እና ከ2.5 ሜ.ኩ. ሳይበልጥ ከመሬት በላይ ቁመቱ 40 ሳ.ሜ እና ከ40 ሳ.ሜ. በላይ ያልሆነ እንዲሁም ርዝመቱ 5.00 ሜትር እና ከ5.00 ሜትር በላይ ያልሆነ ደጋፊ የግንብ ጥገና፤

ሸ) የጣሪያው መዋቅር ሳይፈርስ 20 ካሬ ሜትር እና ከ20 ካሬ ሜትር ስፋት በታች የጣሪያ ልባስ ዕድሳት፣

10.4.1 ህንጻ ሹሙ ወይም የተሰየመ አካል የቀረበውን የእድሳት ጥያቄን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በማየት አለበለዚያ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ከሌለው መረጃውን ከGIS ወይም የ1997 Line Map ላይ በማየት በቂ ካልሆነም በአካል በቦታው ተገኝቶ ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡

10.4.2 በእድሳት ፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ወቅት እድሳት ጠያቂው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ካለው ሰነዱ ላይ ያለው መረጃ ገዢ ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ከሌለው ደግሞ በተዋረድ የGIS እና የ1997 Line Map ላይ ያሉት መረጃዎች ገዢ ይሆናሉ፡፡

10.4.3 እድሳት የተጠየቀበት ቤት በአርሶ አደር ማህበር ክልል ውስጥ የሆነ እንደሆነ እና በGIS ወይም የ1997 Line Map ላይ የማይታይ ከሆነ በአዲስ አበባ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የልማት ተነሺ አርሶ አደር መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ጽ/ቤት ወይም ከሚመለከተው አካል ነባር መሆኑ አስመስክሮ የሚሰጠው ፈቃድ ከይዞታ ባለቤትነት ጋር የማይገናኝ መሆኑ ተገልጾ ይፈቀዳል።

10.5 የግንባታ ማፍረስ ፈቃድ

10.5.1 ማንኛውም ግንባታ ለማፍረስ የሚፈልግ ሰው ፈቃድ ለማግኘት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 006 በመሙላት ጥያቄ ማቅረብ አለበት፣

10.5.2 የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ በመንግስታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተያዘ ወይም የሚተዳደር ከሆነ በድርጅቱ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጎበት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፣

10.5.3 የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች ተሟልተው ከግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ጋር መቅረብ አለባቸው፡-

ሀ. ቦታው በአመልካች ስም የተመዘገበ ለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ፣

ለ. ከሚፈርሰው ህንፃ ጋር ተያይዘው የነበሩ የመብራትና የውሃ አገልግሎቶች መቋረጣቸውን ወይንም መነሳታቸውን የሚገልጽ ማረጋገጫ፣

ሐ. ህንጻው ከእዳና እገዳ ውል ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

መ. ግድግዳ ወይም ጣሪያ የሚጋሩ ወሰንተኞች ካሉ በሚጋሩት ወሰን በኩል ስለሚካሄደው የማፍረስ ሥራ የወሰንተኛውን ንብረት ደህንነት ያገናዘበ ጥናት፤

ሠ. በታሪካዊ ቅርስነት የተመዘገቡና ታሪካዊ እሴት ያላቸው ሕንጻዎች ለማፍረስ በቅድሚያ ከሚመለከተው መስሪያ ቤት ስምምነት፤

ረ. ህንጻው ሁለት ወለልና ከዚያ በላይ ከሆነ የተመዘገቡና የዘመኑን ፈቃድ ያደሰ የስራ

ተቋራጭ GC/BC ደረጃ 7 እና በላይ የግንባታ ማፍረስ ስራ ውል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

10.5.4 ከግንባታ ማፍረስ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ ጋር ተፈላጊ አባሪ ሰነዶች ተሟልቶ ከቀረበ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

10.5.5 የማፍረሻ ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የማፍረስ ስራውን ካጠናቀቀ በኋላ ለመጨረሻ ቁጥጥር ለጽ/ቤቱ ሪፖርት በማድረግ በፈቃዱ መሰረት ግንባታው መፍረሱ በጽ/ቤቱ መረጋገጥ አለበት፡፡

10.5.6 ሙሉ ለሙሉ ለሚፈርስ ግንባታ የማፍረሻ ፈቃድ የተሰጠበት ግንባታ ሰነድ ቅጂ፣ የከተማው መሬት ልማትና ከተማ ማደስ ኤጀንሲ ወይም ለይዞታ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽ/ቤት ወይም ለማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ወይም ለሚመለከተው መስሪያ ቤት እና ለፕላን ኮሚሽን ይተላለፋል፡፡

10.5.7 ከተጎራባች የሚጋሩት ግድግዳ ወይም ጣሪያ ካለ፣ ፈቃድ ጠያቂው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (10.5.3) (መ) በቀረበው ጥናት መሰረት የቀሪ ግንባታውን ደህንነት ለመጠበቅ የገባውን ግዴታ የሚዘረዝር የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ ቅጽ 009 ለአጎራባቹ እንዲደርሰው ያደርጋል፣

10.5.8 የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ የደረሰው ወሰንተኛ በማፍረስ ሥራ ወቅት ገንቢውን በግዴታ ውሉ ላይ ከተጠቀሰው ውጭ በመፈፀሙ ወይም በሌላ ምክንያት የነባር ህንፃ ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር ተፈጽሟል በማለት የሚያቀርበው አቤቱታ ሲኖር ወዲያውኑ የግንባታ ስራውን በማስቆም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ ውሳኔ ይሰጣል፣

10.5.9 የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ የሚያገለግለው ለሶስት ወራት ብቻ ነው፤ በተጨማሪ የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ እንደ ህንፃው ዓይነት እና ውስብስበነት ጊዜው በከተማው አስተዳደር ወይም በሕንጻ ሹሙ ወይም በተሰየመው አካል ሊራዘም ይችላል፣

10.5.10 የግንባታ ማፍረስ ስራ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ "ES-3965 OCCUPATIONAL HEALTH AND SAFETY" ክፍል 8 መሰረት መከናወን አለበት፡፡

10.6 ከግንባታ የተወሰደ (As-Built) ማሻሻያ ፈቃድ

10.6.1 ከግንባታ የተወሰደ (As-Built) ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽ 001 ሞልቶ የፕላን ስምምነት፣ ቀደም ሲል የተሰጠ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሠነድ፤ የግንባታ ተቆጣጣሪው ማሻሻያ እንዲያደርግ ያረጋገጠበትን ሰነድ በማያያዝ እና የማሻሻያ ዲዛይን ሠነዶች አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

10.6.2 ከቦታው ተዳፋትነት ምክንያት ከሚፈጠር ለውጥ፣ ተጨማሪ ወለል መስራት፣ ተጓዳኝ የፕላን ህግጋት የሚያፋልሱ እና የመዋቅራዊ አምድ ዘንግ (Axis) መጨመር ውጭ ያሉትን አነስተኛ ለውጦች በግንባታ የተወሰደ (As-Built) ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ መልክ ግንባታው እየተካሄደ መፈቀድ ይችላል፡፡

10.6.3 ከግንባታ የተወሰደ (As-Built) ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የግንባታ ተቆጣጣሪው ባረጋገጠው እና ማሻሻያውን እንዲያደርግ ባስቀመጠለት ጊዜ ገደብ ውስጥ ከላይ በአንቀጽ 10.6 ንዑስ አንቀጽ 10.6.2 ላይ በተገለጸው አግባብ ማሻሻያውን አቅርቦ ማጸደቅ አለበት፡፡

10.6.4 ማንኛውም የመስክ ሪፖርት የሚረጋገጠው በግንባታ ተቆጣጣሪ ባለሙያ እንዲሁም በግንባታ ተቆጣጣሪ ኃላፊ በማፀደቅ መሆን አለበት፡፡

10.6.5 ማንኛውም ከግንባታ የተወሰደ (As-Built) ግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ሰው እስከ 3 ወር ድረስ የግንባታ ፈቃዱን ማ ጸደቅ አለበት፡፡

10.7 ልዩ ከግንባታ የተወሰደ (Special As-Built) ፈቃድ

10.7.1 ልዩ ከግንባታ የተወሰደ (As-Built) ግንባታ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀውን ቅጽ 001 ሞልቶ የፕላን ስምምነት አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

10.7.2 በከተማው አስተዳደር ተለይተው የሚታወቁ የቀድሞ ህንጻዎች ግንባታ "ልዩ ከግንባታ የተወሰደ (As-Built)" ግንባታ ፈቃድ ዲዛይን/ፕላን አቅርበው ማጸደቅ ይችላሉ፤

10.7.3 "ልዩ ከግንባታ የተወሰደ (As-Built)" ግንባታ ፈቃድ የሚጠየቁ ፕላኖች/ዲዛይኖች ከወቅታዊ የፕላን ህግጋት መቃረናቸው ወይም መጣጣማቸው በምስክር ወረቀት ላይ ተገልፆ ይሰጣቸዋል፤

10.7.4 "ልዩ ከግንባታ የተወሰደ (As-Built)" ግንባታ ፈቃድ የሚቀርበው የአርክቴክቸራል ፕላን/ዲዛይን ሆኖ፤ ለመጠቀሚያ ፈቃድ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፤

10.8 የምሽት ግንባታ ሥራ ፈቃድ

10.8.1 ማንኛውንም ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው የምሽት ግንባታ ሥራ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 029 በመሙላት ማመልከት ይኖርበታል፣

10.8.2 የምሽት መገንቢያ ፈቃድ ሲጠየቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላት ይኖርባቸዋል፤

ሀ) የአካባቢውን ነዋሪ ፀጥታ የማያናጋ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ለ) ለህገወጥ ግንባታ አመቺ ሁኔታ የማይፈጥር እና ተቆጣጣሪ መገኘት ያለበት አይነት የግንባታ ሥራ አለመሆኑ ማረጋገጥ፣

ሐ) የግንባታ ማስጠንቀቂያ ወይም ማስቆሚያ ትእዛዝ ያልተሰጠበት መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

መ) በቀን ቢከናወን በሰውና ተሸከርካሪ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና ሊፈጥር የሚችል ዓይነት ስራ መሆኑን፤

ሠ) የወሰን ላይ ግንባታ አለመሆኑን፤

10.8.3 የሕንጻ ሹም በምሽት ለመገንባት ከሚጠየቁ ሥራዎች ውስጥ ሊፈቀዱ የሚችሉትን ስራዎችና በተጓዳኝ መወሰድ የሚኖርበትን ጥንቃቄ በመዘርዘር ፈቃድ መስጠት ይችላል፣

10.8.4 የምሽት ግንባታ ፈቀድ ያለው ገንቢ ግንባታውን በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማከናወን ይኖርበታል፣ ያለምሽት ግንባታ ፈቀድ የምሽት ግንባታ ማከናወን

አይፈቀድም፣

10.8.5 የሕንጻ ሹም በንዑስ አንቀጽ 10.8.2 የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምሽት ግንባታ ሥራ እንዲበረታታ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት አለበት፡፡

10.8.6 የግንባታ ተቆጣጣሪ መደበኛ ክትትል የሚደረግበትን ግንባታ በምሽት ተገኝቶ እንዲያረጋግጥ አይገደድም፡፡

10.8.7 የምሽት መገንቢያ ፈቃድ የሚያገለግለው የህዝብ መጠቀሚያ ተቋም ለሶስት ወራት ነው፡፡ ሆኖም የተፈቀዱትን ስራዎች ባሉበት ለመቀጠል በተጨማሪ 30 ቀናት ያለክፍያ ፈቃዱ ተራዝሞ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

10.8.8 በማንኛውም የምሽት ግንባታ እንቅስቃሴ ወቅት ለሚፈጠረው አደጋ ባለቤቱ፣ ስራ ተቋራጭ እና አማካሪው ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ፡፡ አደጋ ከተፈጠረ ገንቢው ወዲያውኑ በሚቀጥለው ቀን በአካል በባለስልጣኑ ወይም በጽ/ቤቱ በመገኘት ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

10.9 የመኖሪያ ቤት ነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ

10.9.1 ከስልታዊ የኢንቨስትመንት ቦታዎች ውጪ ያሉና በአምስት አመትና በላይ በመልሶ ማልማት የተያዙ ቦታዎች ውስጥ ሆነው በሁለት አመት ጊዜ እንደማይፈርሱ በሚመለከተው አካል ከተረጋገጠ፤እራሱን ችሎ በሚለማ ቦታ ላይ ለግል መኖሪያ ቤት ብቻ ከተነፃፃሪ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ውጪ የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

10.9.2 የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ በመሪ ፕላኑ የመሬት አጠቃቀም መስፈርት መሰረት የሚፈቀድ ቢሆንም በመሪ ፕላኑ የህንጻ ከፍታ መሰረት እንዲቀርብ አይገደድም፡፡ የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ ከምድር በላይ ጀምሮ ከአንድ ወለል በላይ ሊፈቀድ አይችልም፡፡

10.9.3 የመሪ ፕላኑ የወለል ይዞታ ስፋት ምጥን እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ይዞታ ካለው ነባር ግንባታ የወለል ስፋት እስከ 40% ለማስፋፋት የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ መጠየቅ ይቻላል፤ ይህም በየትኛውም ጊዜ በአንድ ይዞታ ላይ ሊኖር የሚችለው

የማስፋፊያ ጥያቄዎች ጥቅል ድምር ጣሪያ ሲሆን አጠቃላይ የወለል ሽፋን ጥምርታ ገደብ እስካላለፈ ድረስ መሆን አለበት፡፡ የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ የከተማ ፕላን ያስቀመጠውን ከመንገድ መራቅ ያለበትን ርቀት ጠብቆ መፈቀድ አለበት፡፡

10.9.4 የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው የማመልከቻ ቅጹን ሞልቶ፣ የፕላን ስምምነት፣ የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ከዚህ ቀደም ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሰነድና የማሻሻያ ዲዛይን ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ ከዚህ ቀደም ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ ሙሉ ሰነድ ከሌለው ደግሞ ከማሻሻያ ዲዛይን ሰነዶች ጋር የነባሩን ቤት ዲዛይን ማቅረብ አለበት፡፡

10.9.5 የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ ዲዛይኑ መቅረብ ያለበት ደረጃውን በሚመጥን እና የዘመኑን ግብር በሚከፍል የዲዛይን ባለሙያ ወይም አማካሪ መሆን ይኖርበታል፤

10.9.6 በአማካሪ ድርጅት ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ ፕላኖች የድርጅቱ ማህተም ያረፈበት እና በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ቅጂ፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ፤ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የባለሙያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤

10.9.7 ዲዛይኖች በንኡስ አማካሪ/Outsourcing/ የሚሰራ ከሆነ በንኡስ አማካሪ ደረጃ ለሚሰሩ የግንባታ ዲዛይን/ ፕላኖች የንኡስ አማካሪው ማህተም ያረፈበት በዘመኑ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ ቅጂ፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ፤ የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ እንዲሁም ዲዛይኑን የሰሩት ባለሙያዎች የዲዛይን ባለሙያ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የባለሙያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቅጂ ከዋና ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤

10.9.8 የጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ በሚቀርብበት ነባር ይዞታ ላይ ያለ ነባር ቤት በሙሉ በግልጽ ተለይቶ በዲዛይኑ ላይ መታየት ይኖርበታል፡፡

10.9.9 በይዞታ ውስጥ የግንባታ ፈቃድ ድንብና መመሪያና ስታንዳርድን የማይጠብቁ ተነጣጥለው የተሰሩ ነባር ግንባታዎችን ወይም የማሻሻያው ግንባታ ከነባር ግንባታ ጋር ተያይዞ የሚሰራ ከሆነ፤ ነባር ግንባታዎቹ በነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ

ፈቃድ ላይ ተመልክተው ነገር ግን ፈቃዱ እንደማያካትታቸው በግልጽ በፈቃዱ ላይ ተጠቅሶ መጻፍ አለበት፡፡

10.9.10 በልዩ ሁኔታ የጥበቃ ቤት የሚያስፈልጋቸው የግል መኖሪያ ቤቶች አነስተኛውን የክፍል ከፍታ ስታንዳርድ ሳይበልጥ እና 2.00 ሜትር በ 2.00 ሜትር የክፍል ስፋት ሳይበልጥ እንዲሁም የከተማ ፕላን ያስቀመጠውን ከመንገድ መራቅ ያለበትን ርቀት ጠብቆ በነባር ግንባታ ጊዚያዊ ማሻሻያ ፈቃድ መልክ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

10.9.11 የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ፈቃድ የሚያገለግለው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡

10.10 የአገልግሎት ለውጥ ስለማድረግ

10.10.1 የህንፃ ሹሙ ከአዋጁ፣ ከማስፈፀሚያ ደንቡ፤ ከህንጻ ኮድ እና ከዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ጋር እስከተጣጣመ ድረስ የህንፃ አገልግሎት ለውጥ ማድረግ ይችላል፤

10.10.2 ማንኛውም ባለይዞታ በሕንፃው ላይ የአገልግሎት ለውጥ ሲያቅድ ሥራው ከመጀመሩ በፊት የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፣

10.10.3 ማንኛውም ባለይዞታ የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ ሲያቅድ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ 007 መሙላት እና የፕላን ስምምነት ሰነድ አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

10.10.4 የአገልግሎት ለውጥ ለማከናወን ሲጠየቅ ባለይዞታው ሕንፃው የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ እና ለአገልግሎት ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ለሚሰራው ስራ የሚያስፈልጉትን ፕላኖች እና የስራ ዝርዝር አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

10.10.5 ማንኛውም የአገልግሎት ለውጥ ሥራ የሚያከናውን ሰው ሥራውን ማከናወን የሚኖርበት የፕሮጀክት ግምቱን መሰረት በማድረግ ደረጃው በሚመጥን የሥራ ተቋራጭ መሆን ይኖርበታል፣

10.10.6 ማንኛውም ባለይዞታ በአገልግሎት ለውጥ ስራ ላይ የማፍረስ ሥራ ሲያከናውን በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያስከትልና ማንኛውንም እንቅስቃሴ እንዳያስተጓጉል ቅድመ ጥናት ማድረግ ይኖርበታል፣ ሥራውን ሲያከናውንና ሲያጠናቅቅ ፍርስራሹን በማስወገድና ቦታውን በማስተካከል ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ አለበት፣

11. የህንጻ ሹም

11.1 በከተማው አስተዳደር ከንቲባ ወይም በተወከለው ወይም ለተማው ተጠሪ በሆነለት የክፍለ ከተማና ወረዳ አስተዳዳር አካል የሚሾም ሕንፃ ሹም፣ በአርክቴክቸር፣ በሲቪል ምህንድስና፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ ሙያ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ሆኖ በዲዛይን ዝግጅትና ምርመራ ወይም በግንባታ ሥራ ክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች አግባብነት ያለው ልምድ ሊኖረው ይገባል፣

11.2 የከተማው አስተዳደር ከንቲባ ወይም የተወከለው ወይም ከተማው ተጠሪ በሆነለት የክፍለ ከተማና ወረዳ አስተዳዳሪ አካል የሚሾም የህንፃ ሹም ለመሾም ከትምህርትና ከሙያ ዝግጅት መሥፈርት ምዝናው በተጨማሪ፣

11.2.1 በሥራ ዘመኑ የነበረው የሥራ አፈፃፀም፣

11.2.2 መልካም ሥነምግባር ያለው እና ለተለያዩ ሱሶች (ለአልኮልና ለአደገኛ ሱሶች) ተገዥ ያልሆነ፣

11.2.3 የማቀድ፣ የማደራጀት፣ የማስተባበር እና የመምራት ችሎታ ያለው፣

11.2.4 ተግባቢና ቀና አመለካከት ያለው፣

11.2.5 በቡድን የመስራት እና የባለቤትነት ስሜት ያለው፣

11.2.6 ደንበኛ ተኮር የሆነና የግንኙነት ችሎታ ያለው፣

11.2.7 የማወቅ ፍላጎት ያለውና ችግር ፈቺ የሆነ፣

11.2.8 በሙያው ትጉህና ሰርቶ የማሰራት ችሎታ ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡

11.3 የህንፃ ሹም በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገነቡ፣ ከከተማ ክልል ውጭ ሆነው ይህ መመሪያና ስታንዳርድ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው እና እንዲቆጣጠራቸው የተወከለባቸው ሕንፃዎች ላይ በሕንፃ አዋጁ በማስፈፀሚያ ደንቡና በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ እንዲሁም በሌሎች ሕጐች መሠረት እየተገነቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋል፣

11.4 የሕንፃ ሹመ በህንጻ አዋጁ 624/2001፣ በህንጻ ደንብ 243/2003 እና በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ሆነው የተገኙ ግንባታዎች እንዲቆሙ፣ እንዲስተካከሉ ወይም እንዲፈርሱ ማዘዝ ይችላል፣

11.5 ከዚህ በላይ በንኡስ አንቀጽ (11.4) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕንፃ ሹመ አስተዳደራዊ መቀጮ በመጣል እና ማስተካከያ መደረጉን በማረጋገጥ የግንባታ ማስቀጠያ ውሣኔ ይሰጣል፣

11.6 የህንፃ ሹመ ተጠሪነት ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ነው፡፡ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሕንፃ አዋጁ፣ በማስፈፀሚያ ደንቡና በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ የተሰጡትን መብትና ግዴታዎች ያላከበረን የህንፃ ሹም አግባብ ባለው ህግ መሠረት ከሥራ ያግዳል፣ ያሰናብታል፣ እንደየጥፋቱ ደረጃ በህግ ተጠያቂ ያደርጋል፣

11.7 የሕንፃ ሹመ ቁጥጥር በሚያደርግባቸው የአስተዳደሩ አካባቢዎች አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያና ስታንዳርድ ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው የተደረጉ ሕንፃዎችን በመመልከት እንዲመረመሩና አስጊ ሆነው ከተገኙ በአፋጣኝ እንዲስተካከሉ ወይም ተገቢው የሙያ ሪፖርት ከቀረበ በኋላ እንዲፈርሱ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፣

12. አገልግሎት መግዛት

12.1 የሕንፃ ሹመ በአስተዳደሩ ውስጥ አንድን የተወሰነ ሥራ ለመሥራት የሚችል ባለሙያ የማያገኝ ሲሆን ይህንን ሥራ ሊሰራ ከሚችል አማካሪ ድርጅት ጋር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በመዋዋል ሊያሰራ ይችላል፡፡

12.2 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 12.1 መሠረት ተዋውሎ የሚሠራ ባለሙያ ሥራውን በአዋጁ በደንቡ እና መመሪያና ስታንዳርድ እና በውሉ መሠረት የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

12.3 የሕንፃ ሹመ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 12.1 መሠረት ተዋውሎ የሚሠራው ባለሙያ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

12.5 በሦስተኛ ወገን እንዲከናወን የተደረገን ሥራ የማፅደቅ ኃላፊነት የሕንፃ ሹመ ይሆናል፡፡

13 የይግባኝ ሰሚ ቦርድ

13.1 የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሕንፃ አዋጅ፣ ደንብና በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚችል ሙያዊ ብቃት ያለው የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ያቋቁማል፡፡ ለሚቋቋመው ቦርድ፤

13.1.1 ሰብሳቢና ፀሐፊ ይሰይማል፣

13.1.2 የሥራ ዘመን ይወስናል፣

13.2. የቦርዱ አባላት፣

13.2.1 ቴክኒካል ጉዳዮችን ለማየት ሙያውና የሥራ ልምድ ያላቸው፣

13.2.2 ከግንባታ ፈቃድ አሠጣጥና ክትትል ጋር ግንኙነት የሌላቸው፣

13.2.3 በመልካም ስነምግባር የሚታወቁ፣

13.2.4 በዲሲፒሊን ጥፋት ተከሰው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፣

13.3 የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ ከከተማ አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል እና ከሚመለከታቸው ተቋማት የተውጣጡ ቁጥራቸው እንደጉዳዩ ውስብስብነት እና እንደ ከተማው ደረጃ የሚወሰን ሆኖ ከ5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል፡፡

13.4 የቦርዱ የሥራ ዘመን ከከተማ አስተዳደሩ የሥራ ዘመን ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

13.5 የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አባላት ስብጥርና የሥራ ድርሻ እንደሚከተለው ይሆናል፣

13.5.1 አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ/በከንቲባ የሚወከል---------- ሰብሳቢ

13.5.2 የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን----------ፀሐፊ

13.5.2 የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ.....አባል፣

13.5.3 የሥራ ተቋራጮች ማህበር ተወካይ.....አባል፣

13.5.4 የፍትህ ቢሮ .....አባል፣

13.5.5 የኮንስትራክሽን አማካሪዎች ማህበር.....አባል፣

13.5.6 የፕላን ኮሚሽን.....አባል፣

13.5.7 ነዋሪዎች ፎረም .....አባል፡፡

ማሳሰቢያ፡- የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ የቴክኒክ ጉዳዮችን የሚመረምር የቴክኒክ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

13.6 ማንኛውም ሰው በሕንፃ ሹመ በተሰጠ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታ ካለው የህንፃ ሹመ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በደረሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ቦርድ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

13.7 የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

1. ቦርዱ ግንባታዎችን በተመለከተ በሕንፃ ሹም በተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረል፡፡
2. የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አቤቱታ በደረሰው በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የሚመለከትበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በመወሰን ለአመልካቹ ከአምስት የሥራ ቀናት በፊት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. ቦርዱ ለሚቀርብለት የይግባኝ አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም የጉዳዩ ባህሪ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ የውሳኔው ጊዜ ለአንድ ተጨማሪ ወር ሊራዘም ይችላል፡፡
4. ቦርዱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሌሎች ባለሙያዎችን እገዛ መጠየቅ ይችላል፡፡
5. ቦርዱ ቴክኒክ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
6. ቦርዱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ለአመልካቹ እና ለህንጻ ሹመ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

13.8 የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ለቦርዱ አባላት አበል ሊከፍል ይችላል፡፡

13.9 ቦርዱ ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ይሆናል፡፡

13.10 የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በግንባታ ፈቃድ ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ 027 ይሆናል፣

13.11 የቦርዱ ሰብሳቢና ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባራት፣

ሀ) ቦርዱን በበላይነት ይመራል፣

ለ) ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ከአባላቱ ውስጥ ስብሰባውን የሚመራ በአስተዳደሩ ወይም የተሰየመው አካል የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን እንዲወክል ያደርጋል፣

ሐ) ቦርዱ የሚመራበትን የሥራ መመሪያና ስታንዳርድ ከቦርዱ አባላት ጋር ያዘጋጃል፣

መ) አቤቱታዎችን ይቀበላል፣

ሠ) አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም ውሣኔ በድምፅ ብልጫ እንዲከናወን ያደርጋል፤ የቦርዱ አባላት የሚሰጡት ድምፅ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን አሸናፊ ይሆናል

ረ) ቦርዱ የሚሰጠውን ውሣኔ ለአቤቱታ አቅራቢው፣ ለሕንፃ ሹመ እና ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በጽሁፍ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

ሰ) በፍርድ ቤት ሲጠየቅ የውሳኔው ቅጂ ይሰጣል፣

ቀ) የቦርዱን በጀት በማዘጋጀት ለከተማ አስተዳደሩ አቅርቦ ያጸድቃል፣

13.12 የቦርዱ ፀሐፊ ሥልጣንና ተግባር፡-

ሀ) የስብሰባ አጀንዳና ቃለ ጉባዔ እየያዘና በአግባቡ እያዘጋጀ አባላቱ እንዲፈርሙበት ያደርጋል፣

ለ) አስፈላጊ መረጃዎች እና ሰነዶች በስብሰባ ወቅት ተሟልተው እንዲገኙ ያደርጋል፣

ሐ) ቦርዱ የተሟሉ ሰነዶች እና መዛግብቶች እንዲኖሩት ያደርጋል፣

መ) ከቦርዱ ሰብሳቢ በሚሠጠው መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት አጀንዳ ያዘጋጃል፣

ሠ) የቦርዱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣

ረ) አቤቱታ የቀረበባቸውን ሰነዶች እና ለምርመራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መዝግቦ

ይይዛል፣

ሰ) ውሳኔ የተሰጠባቸውንና ሌሎች ሠነዶችን መዝግቦ በጥንቃቄ ይይዛል፣

13.13. በሕንፃ አዋጁ፣ በደንቡና በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ የተመለከቱት በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ቅሬታ ያለው ሰው ጉዳዩ እንዲታይለት ለቦርዱ በቅጽ 019 መሠረት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣

14. የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር

14.1 አጠቃላይ

ማንኛውም የግንባታ ማስጀመሪያ የሚፈልግ ሰው ወይም አካል፡-

14.1.1 የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ

14.1.2 የይዞታ ማረጋገጫ ቅጂ

14.1.3 ለስራው የሚመጥን የስራ ተቋራጭ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሰነዶች ማሟላት አለበት፤

ሀ) በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ ከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ለ) የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ ከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ሐ) የግብር ከፋይ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ወረቀት ቅጂ፤ከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

መ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ሠ) በገንቢው የተቀጠረው ለፕሮጀክቱ የሚመጥን ሳይት መሃንዲስ ላይሰንስ እና የግብር ከፋይ ምስክር ወረቀት ቅጂ ከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ረ) ለፕሮጀክቱ የሚመጥን የመድን ዋስትና ሽፋን (Contractor all Risk)

ሰ) ከሥራ ተቋራጭ ጋር የተደረገ የሥራ ስምምነት ሆኖ የሀገሪቱን የኮንስትራክሽን ህግ ውል የጠበቀ ኮፒ (General condition of contract

and special condition of contract) /እንደ ደረጃው/

ሸ) ለህዝብ መጠቀሚያ ህንፃ ጠቅላላ ዝርዝር የዋጋ ግምት (Bill of Quantity)፤ ሆኖም ዝርዝር የዋጋ ግምቱን ያዘጋጀው አማካሪ ድርጅት ትክክለኛ ግምት ስለማቅረቡ ሀላፊነት ይወስዳል፡፡

ቀ) የአሰሪና የገምቢ ግዴታ ውል

14.1.4 ለስራው የሚመጥን አማካሪ ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሰነዶች ማሟላት አለበት፤

ሀ) በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ቅጂ ከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ለ) የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ሐ) የግብር ከፋይ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ወረቀት ቅጂ ከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

መ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቅጂ ከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ሠ) በአማካሪው የተቀጠረው ለፕሮጀክቱ የሚመጥን ሳይት መሃንዲስ ላይሰንስ እና የግብር ከፋይ ምስክር ወረቀት ቅጂከዋናው ጋር የሚመሳከር፤

ረ) ለፕሮጀክቱ የሚመጥን የመድን ዋስትና ሽፋን (Professional Indemnity)

ሰ) የአሰሪና የአማካሪ ግዴታ ውል ሆኖ የሀገሪቱን የኮንስትራክሽን ህግ ውል የጠበቀ ኮፒ (General condition of contract and special condition of contract) /እንደ ደረጃው/

14.1.5 የሚፈርስ ግንባታ ካለ የማፍረሻ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ባለቤቱ ያቀርባል፤

14.1.6 የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ክፍያ (Inspection fee) /እንደ ደረጃው/ ወይም የእርከኖች ድምር የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ክፍያ ባለቤቱ ይከፍላል፡፡

14.1.7 ከላይ የተጠቀሱት መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ መስክ በመውጣት

ሀ. በይዞታው ውስጥ ሊገነባ የታሰበው አንድ ህንጻ ብቻ ከሆነ ግንባታው በሚያርፍበት ቦታ ላይ ምንም አይነት ቋሚ ግንባታ ያለመኖሩ፤

ለ. በይዞታው ውስጥ ሊገነባ የታሰበው ከአንድ ህንጻ ወይም ብሎክበላይ ከሆነ ግንባታውን ሊጀምር እና ሊያሳርፍ ባቀደውብሎክ ላይ ምንም አይነት ቋሚ ግንባታ ያለመኖሩ፤

ሐ. በይዞታው የወሰን ላይ ችካል መኖሩን

መ. በየደረጃው ግንባታው በተፈቀደለት መሠረት መከናወኑን

ሠ. በማስጀመሪያ ወቅት የተመዘገቡት ገንቢና አማካሪ በሥራ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ረ. ግንባታ ተጀመረ የሚባለዉ የግንባታዉን መሰረት እና የምድር ወለል ወይም ህንጻዉ የምድር ዉስጥ ወለል ካለዉ የመጀመሪያዉ የምድር ዉስጥ ወለል ሶሌታ ሲሞላ ነዉ፡፡

14.1.8 “ለክትትል” ተብሎ የተሰጠውን የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ግንባታው በሚካሄድበት ቦታ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ በግልጽ ቦታ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡ የግንባታ ጊዜዉ ከተጠናቀቀ በኋላ ተጨማሪ የግንባታ ጊዜ ካስፈለገ ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ወር የግንባታዉን ጥቅል ወጭ ግምት 0.1% ያህል መቀጮ ከፍሎ ለአንድ ዓመት ይራዘምለታል፡፡ ከአንድ አመት በላይ ከሆነ ከ0.1% ተጨማሪ በከተማ አስተዳደሩ ወይም በተሰየመዉ አካል ተጨማሪ ቅጣት ሊጣል ይችላል፡፡

15. ትእዛዝ አለማክበር

15.1 ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ የአዋጁን፣ የደንቡንና የዚህን መመሪያና ስታንዳርድ ድንጋጌዎች ማክበር ይኖርበታል፣

15.2 በአዋጁና በደንቡ የተቀመጡተን ድንጋጌዎች እና ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት

15.2.1 ፍቃድ የተሰጠበት የግንባታ ፈቃድ/ፕላን ማመልከቻ ኮፒ በግንባታ ቦታ አለመገኘት

15.2.2 የውስጥ አደረጃጀት /የግንባታ ቅድመ ዝግጅት/ ሳያሟሉ ሥራ መጀመር

15.2.3 የተሰጡ የማስተካከያ ትእዛዞችን ካጠናቀቁ በኋላ አለማስታወቅ

15.2.4 የተሰጡ ትእዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን

15.2.5 ከግንባታ ክልል ውጪ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሠረት አለማንሳት

15.2.6 ካለ ተቆጣጣሪ ማሰራት

15.2.7 ካለማስታወቂያ ሥራ መጀመር

15.2.8 ያለ ፈቃድ እድሳት ማድረግ

15.2.9 ያለፈቃድ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን

15.2.10 ያለፈቃድ የማፍረስ ሥራ ማከናወን

15.2.11 በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አለመውሰድ

15.2.12 የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም፤

15.2.13 የግንባታ የውጭ ገጽታዎችን በተፈቀደው ስታንዳርድ ቀለም መሰረት ያለመስራት፤ የመሳሰሉትን ተግባራት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ትእዛዝ እንዳላከበረ ይቆጠራል፡፡

15.3. ማንኛውም ሰው ከላይ በንኡስ አንቀጽ 15.1 እና 15.2 የተመለከቱትን የማያከብር ሆኖ ከተገኘ በሕንፃ ሹመ በሚሰጥ የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ ቅጽ 014 መሰረት ትእዛዝ ግንባታው እንዲቆም፣ ወይም እንዲፈርስ ወይም እንዲስተካከል ደርጋል፣

15.4 በግንባታ ወቅት ማንኛውንም በህንፃ ሹመ ወይም በሚወክለው አካል የሚሰጥ ትእዛዝን አለመቀበልና አለማክበር ገንቢው፣ አማካሪው እና የህንፃው ባለቤት በግልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፣

16. ስለማስታወቂያ

16.1 ማንኛውንም በምድብ “ለ" እና “ሐ" የሚገኝ ሕንፃ ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የየሥራው እርከን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስታወቂያ የሥራ እርከኑን ከመጀመሩ 5 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ለሕንፃ ሹመ በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

16.2 ማንኛውም የፀደቀ የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ያለው ሰው የግንባታ ማስታወቂያ ለቀረበበት የሥራ እርከን ሥራው ከመጀመሩ በፊት ከላይ በንኡስ አንቀጽ 16.1 በተመለከተው መሠረት ለሕንፃ ሹመ የግንባታ ሥራ ማሳወቂያ ቅጽ 025 ሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

16.3 ለምድብ “ለ" እና “ሐ" ህንጻዎች ለአዲስ ግንባታ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው የሚገቡ የስራ እርከኖች የሚከተሉት ናቸው፣

16.3.1 ግንባታ ለመጀመር ማንኛውም የቅየሳ ስራ ተጠናቆ ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት፤

16.3.2 የመሠረት ቁፋሮ ከተጠናቀቀና የመሰረት ብረቶችና ፎርምወርክ በቦታቸው ከተቀመጡ በኋላ፤

16.3.3 የምድር ወለል ብረቶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃና የሀርድ ኮር ሙሌት ከተከናወነ በኋላ፤

16.3.4 የወለል ቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶችና ፎርም ወርክ ስራ ከተከናወነ በኋላ፤

16.3.5 የየፎቁ ወለል ብረቶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የኤሌክትሪካል መስመር ዝርጋታና የፎርም ወርክ ስራ እንዲሁም የቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶችና ፎርምወርክ ከተከናወነ በኋላ፤

16.3.6 የውሃ አቅርቦት፣ የሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ተጠናቆ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ፤

16.3.7 የጣሪያ ስላብ (ሶሌታ) ማጠናቀቂያ ወይም የጣሪያ ሽፋን ስራ ከመከናወኑ በፊት፤

16.3.8 እንደ ሥራው ዓይነት እና የአሠራር ዘዴ በሕንፃ ሹመ የሚጠየቁ ተጨማሪ

እርከኖች፡፡

16.4 የሕንፃ ሹም ማስታወቂያ ለቀረበበት የሥራ እርከን በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባታው ቦታ በመገኘት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

16.5 ለነባር ግንባታ ማሻሻያ እና ማስፋፊያ ሥራ እንደ ሥራው ዓይነት ወይም እንደሚከናወነው ተግባር ማስታወቂያ የሚቀርብበትን የሥራ እርከን የሕንፃ ሹሙ ለገንቢው ያሳውቃል፣

16.6 መደበኛ ክትትል በሚደረግባቸው የግንባታ ደረጃዎች ገንቢው ለሚመለከተው የክትትል ክፍል ሳያሳውቅና ስራን ለመቀጠል ፈቃድ ሳያገኝ ማከናወን የለበትም፤

16.7 የግንባታ መስፋፋትን እና የህንጻ ከፍታን የማያካትት የዲዛይን ለውጥ ማስታወቂያ የደረሰው የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ክፍል በሰነዱ ላይ የተመለከተው ለውጥ የማይፈቀድ ወይም በቅድሚያ የግንባታ ፈቃድ እንዲወጣ የሚጠይቅ ከሆነ ማስታወቂያ በደረሰው በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለግንባታው ባለቤት ወይም ለአማካሪው ወይም ለተቋራጩ ማሳወቅ አለበት፤

17. ስለ ተቆጣጣሪዎች

17.1 ማንኛውም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል ማንነቱን የሚገለጽ መታወቂያ የያዘ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ወይም ግንባታ በሚከናወንበት በማንኛውም ጊዜ በግንባታው ቅጥር ግቢ ተገኝቶ የቁጥጥር ሥራ ማከናወን ይችላል ያከናወነውን የቁጥጥር ተግባር የሰጠውን ትእዛዝ በግንባታ መከታተያ ቅጽ 13 በመሙላት ለሕንጻ ሹሙ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል ፣

17.2 በማንኛውም ወቅት ወደ የትኛውም ይዞታ ለክትትልና ቁጥጥር ተግባር የሚንቀሳቀስ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በእለቱ ወደ ግንባታ ቦታ መግባት ያስፈለገበትን ምክንያት እና በግንባታ ቦታ ተገኝቶ ያከናወነውን የቁጥጥር ስራ ዝርዝር፣ የተገኘውን ውጤትና የሰጠውን ለተቆጣጣሪዎች በተለየ እና በግንባታ ቦታ በሚቀመጥ የቁጥጥር መዝገብ ላይ ሞልቶ በማስፈረምና በመፈረም ቅጂውን ለግንባታው ባለቤት ወይንም በግንባታው ቦታ ለሚገኝ ተጠሪ መስጠት አለበት፣ የቁጥጥር መዝገብ ተከታታይ ዋና እና ቀሪ የገጽ ቁጥር፣ የትዕዛዝ መስጫ ቦታ፣ የስኬች

መስሪያ ቦታ፣ ለተቆጣጣሪ ለስራ ተቋራጭና እና ለአማካሪ የፊርማ ቦታ የያዘ መሆን ይኖርበታል፣

17.3 የሕንጻ ተቆጣጣሪው የሕንፃ አዋጁን፤ የሕንጻ ደንቡን፤ ይህን መመሪያና ስታንዳርድ እና ተጓዳኝ ሕጐችንና ውሎችን በመተላለፍ የሚካሄድ ግንባታ እንዲቆም ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ የማስቆሚያ ትእዛዝ የሚሰጠው በአንቀጽ 17.2 ላይ በተመለከተው መሠረት እና የግንባታ ማስቆሚያ ቅጽ 015 በመሙላት ይሆናል፣

17.4 ያለምንም የፅሑፍ ማስታወሻ የሚደረግ የግንባታ ቦታ ጉብኝትም ሆነ የሚሰጥ የቃል ትእዛዝ ህጋዊነት አይኖረውም፣

17.5 የህንፃ ሹመ ወይም የሚወክለው አካል ከግንባታው ባለቤት የግንባታውን ክትትልና ቁጥጥር ሥራ አስመልክቶ ለሚቀርብለት ማስታወቂያ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ ቅጽ 016 በመሙላት መልስ መስጠት ይኖርበታል፣

17.6 ማንኛውም ተቆጣጣሪ በክትትል የስራ ሂደት ከስልጣኑ እርከን ክልል ውጭ ባለ ቦታ እና የግንባታ ደረጃ የሚያጋጥመውን ከፈቃድ ውጭ የሚደረግ የግንባታ እንቅስቃሴ ለሚመለከተው መስሪያ ቤት የግንባታ ሂደት ማሳወቂያ ቅጽ ሞልቶ መላክ አለበት፡፡

18. ቁሳቁስ

18.1 የሕንፃ ሹም በግንባታ ሥፍራ የተቀመጠ ወይም በሕንፃው ሥራ ላይ የዋለ ግብዓት በናሙና ፍተሻ ውጤቱ ተቀባይነት ካጣ እንዲወገድ ወይንም በአጠቃቀሙ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

18.2 በግንባታ ግብዓት ጥራት ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም አደጋ ወይንም ጉድለት የግንባታው ባለቤት፣ ገንቢው እና አማካሪው ሃላፊነት አለበት፡፡

18.3 ከላይ በአንቀጽ 18.1 እና 18.2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሕንፃ ሹመ ለግንባታው ያገለግላሉ ተብለው የተቀመጡ ወይም ሥራ ላይ የዋሉ የግንባታ ቁሳቁሶች የጥራት ጉድለት እንዳለባቸው በእይታም ሆነ በግንባታ ቦታ በሚደረግ ፍተሻ ካረጋገጠ እንዲወገድ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግ ትእዛዝ መስጠት

ይችላል፣

18.4 የግንባታ ቁጥጥር የሚያደርጉ ባለሙያዎች ለግንባታ የሚቀርበውን ቁሳቁስ ጥራቱንናየደረጃ መስፈርቱን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፣

18.5 የሕንፃ ሹሙ ማንኛውም ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የሚገቡ ለግንባታ ግብዓትለሚውሉ ቁሳቁሶች የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሊጠይቅ ይችላል፣

18.6 በእየርከኑ ለሚከናወኑ የኮንክሪት ስራዎች የኮንክሪት ናሙና መወሰድ አለበት፣ የተወሰዱት የኮንክሪት ናሙናዎች ቀነ ገደባቸውን ጠብቆ ፈቃድ ባለው ላብራቶሪ በማስመርመር ውጤቱን ለተቆጣጣሪው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

18.7 አዲስ የፈጠራ ግንባታ ቁሶችን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ቁሱ ከሁሉም የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር ጥራቱንና መስፈርቱን የጠበቀ መሆኑ ከተረጋገጠ መጠቀም ይቻላል፡፡

19. የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ

19.1. በምድብ “ሐ" ስር ለሚካተቱ ህንፃዎች የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ በቅጽ ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣

19.2. የማመልከቻው ቅፅ በሕንፃው ባለቤት ወይም በህጋዊ ወኪሉ ወይም የመንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረት ከሆነ በድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ተፈርሞና ማህተም ተደርጐ መቅረብ አለበት፣

19.3. የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት አይነቶች፡-

ሀ. ሙሉ በሙሉ ለተጠናቀቀ ህንጻ የሚሰጥ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ፤

ለ. ደረጃ በደረጃ ለሚከናወን ወይም/እና በከፊል ለተጠናቀቀ ህንጻ የሚሰጥ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ፤

ሐ. የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት፤

19.4. ለሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚቀርብ የማመልከቻ ቅጽ፡-

ሀ) የግንባታውን ባለቤት ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ለ) ግንባታው የሚገኝበትን አድራሻ፣

ሐ) የህንፃውን የአገልግሎት ዓይነት፣

መ) የግንባታውን ፈቃድ ቁጥር፣

ሠ) ግንባታው የተጀመረበትንና የተጠናቀቀበትን ቀን፣እና

ረ) ህንጻው በፕላኑ መሠረት ስለመሠራቱ ቁጥጥሩን ያደረገው የተመዘገበ ባለሙያ ያረጋገጠበትን ማስረጃ፣ ማካተት አለበት፡፡

19.5. ከማመልከቻው ቅፅ ጋር ተያይዘው መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች፡-

19.5.1. ለአዲስ ወይም ለእድሳት የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ጥያቄ፡-

ሀ) የግንባታ ፈቃድ ምስክር ወረቀት፤

ለ) አርክቴክቸራል ፕላን ንድፍ ቅጂ፤

ሐ) የግንባታ ክትትል ሠነድ፤

መ) በግንባታው ባለቤት እና አማካሪ ድርጅቱ የተፈረመ የርክክብ ሠነድ፡፡ የርክክብ ሰነድ ማቅረብ ካልተቻለ ባለቤቱ ግንባታውን ስለመረከቡ ማረጋገጫ ደብዳቤ ያቀርባል፤

19.5.2. ለነባር ሕንፃ የአገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት በማድረግ ለሚቀርብ የመጠቀሚያ ፈቃድ፣

ሀ) የአገልግሎት ለውጥ ፈቃድ የፕላን ስምምነት፣

ለ) ለአገልግሎት ለውጥ የተፈቀዱ ፕላኖች ወይም ዝርዝር ሥራዎች

ሐ) በተፈቀደው ፕላን መሠረት መጠናቀቁን የሚገልፅ የርክክብ ሠነድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የርክክብ ሰነድ ማቅረብ ካልተቻለ ባለቤቱ ግንባታውን ስለመረከቡ ማረጋገጫ ደብዳቤ ያቀርባል፤

19.6. መጠነኛ ለውጥ ኖሯቸው የግንባታ ማሻሻያ የሚያስልጋቸው ግንባታዎች የደህንነት ስጋት የማያስከትሉ መሆኑ ተረጋግጦ፤ የፕላን ማሻሻያውን አሰርተው እስኪያቀርቡ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የሚያገኙ ይሆናል፡፡

19.7. በከፊል ተከናውኖ ለሚቀርብ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ጥያቄ የግንባታው ደረጃ ዝቅተኛውን የወለል ምጣኔ ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ ግንባታው ለአገልግሎት ዝግጁ ለሆኑበት ወለሎች ብቻ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃዱ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

19.8. የህንፃ አዋጅ ከመፅደቁ በፊት የግንባታ ፈቃድ አውጥተውም ሆነ ሳያወጡ የተጠናቀቀ ነባር ግንባታ ወይም “ልዩ ከግንባታ የተወሰደ” የመሪ ፕላኑን መስፈርት ባያሟላም የመጠቀሚያ ፈቃድ ማመልከቻ፤ የቦታውን ፕላን መረጃ እና የፀደቀ አርክቴክቸራል ንድፍ በማቅረብ የግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ያገኛል፡፡

19.9. ደረጃ በደረጃ ተፈቅዶ የሚገነባ ግንባታ እና/ወይም በከፊል ለተከናወነ ግንባታ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን እድሳቱም በየዓመቱ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የእድሳት ማብቂያ ጊዜው በአንቀጽ 19.10 መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

19.10. ደረጃ በደረጃ ወይም በከፊል ለተገነባ ግንባታ የሚሰጥ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የእድሳት አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ የግንባታ ፈቃዱ የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ቀሪው ግንባታ ያልተከናወነው በሚታወቅ ምክንያት ከሆነ ለምሳሌ በጤና ችግር፣ በአገራዊ ግንባታ ሊያስተጓጉል በሚችል ምክንያት፣ በይዞታ/ግንባታ ክርክር፣ በፍርድ ቤትና ሌሎች ዕግዶች ወይም መሰል አሳማኝ ምክንያቶች ከሆነ የመጠቀሚያ ፈቃዱ የሚሰጥ/የሚታደስ ይሆናል፡፡

19.11. ደረጃ በደረጃ ወይም በከፊል ለተጠናቀቁ የህንጻዎች የሚሰጥ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ/ዕድሳት፤ግንባታው የቀረው የማጠናቀቂያ /Finishing/ ስራ እና የሊፍት ገጠማ ስራዎች ከሆነ ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ፈቃድ/የዕድሳት አገልግሎት የሚያገኝ ይሆናል፡፡ አገልግሎቱም በግንባታ ፈቃዱ ማብቂያ ጊዜ አይገደብም፡፡ ሆኖም ግን ገንቢው የአገልግሎት ክፍያውን ሃያ አምስት በመቶ ቅጣት እንዲቀጣ በማድረግ አገልግሎቱ ይሰጣል፡፡

19.12. በህንጻ አዋጅ መሰረት የሕንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አስገዳጅ የሚሆነው ለምድብ “ሐ” ግንባታዎች ብቻ ሲሆን በምድብ “ሀ” እና “ለ” ውስጥ የሚገኙ እና ለመኖሪያነት አገልግሎት እየዋሉ የሚገኙ ወይም ወደ ህዝብ መገልገያነት ያልተለወጡ ግንባታዎች የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አያስፈልጋቸውም፤

19.13. የህዝብ መገልገያ ያልሆኑና አነስተኛ ቁጥር ያለው ተገልጋይ የሚገለገልባቸው እንደ ህጻናት መዋያ፣ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ክሊኒኮች፣ ፋርማሲዎች፣ የመኖሪያ ቤት ግንባታዎች/ህንጻዎች ሆነው (High Density Mixed Residence የመሬት አጠቃቀም ላላቸው ከ30 በመቶ በላይ የግንባታ ወለል መጠን ያለወጡ እንዲሁም Middium/ Low Density Mixed Residence የመሬት አጠቃቀም ላላቸው ደግሞ ከ40 በመቶ በላይ የግንባታ ወለል መጠን አገልግሎት ያለወጡ) ግንባታዎች የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አያስፈልጋቸውም፤

19.14. በምድብ “ሀ” እና “ለ” ውስጥ ይገኙ የነበሩ እና ወደ ህዝብ መገልገያነት የተለወጡ ግንባታዎች ከሚመለከተው ተቋም የአገልግሎት ለውጥ አድርገው እስኪመጡ ድረስ የፕላን ስምምነት እንዲያቀርቡ በማድረግና የተደረገው የአገልግሎት ለውጥ ከመዋቅራዊ ፕላኑ ጋር የሚጣጣም ከሆነ ለአንድ ጊዜ ብቻ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ለአንድ ዓመት ይሰጣቸዋል፤

19.15. ሙሉ በሙሉ ለተጠናቀቀ ግንባታ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላቱን በማረጋገጥ በየሁለት አመቱ የሚታደስ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፤

19.16. የስም ዝውውር የተደረገባቸው ይዞታዎች፤ በግንባታው ፕላን እና በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መካከል የስም ልዩነት ሲፈጠር የስም ዝውውር የተደረገበት ማስረጃ (የግዥ ውል፣ የፍ/ቤት ውሳኔ፣ የስጦታ...ወዘተ) እንዲቀርብ በማድረግ ጊዜያዊ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይሰጣል፤

19.17. ነባሩ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በአዲሱ በመሬት ይዞታ መረጃና ምዝገባ ተቋም በሚሰጠው ካርታ ሲተካ ምትክ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ የቀረበው ፈቃድ የእድሳት ጊዜ ያለፈበት ከሆነ ፈቃዱ ታድሶ በአዲሱ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጥ ሲሆን ፈቃዱ የእድሳት ጊዜው ካላለፈበት ደግሞ የመሀንዲስ አገልግሎት እንዲከፈል በማድረግ ምትክ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

19.18. ለህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት የግንባታ ክትትል ማስረጃዎች እና የግንባታ ክትትል ቅጣት አፈጻጸም በሚመለከት፡-

19.18.1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከወጣው የህንጻ መመሪያ ቁጥር 1/97 በፊት የተገነቡ ግንባታዎች ከመመሪያው በፊት ስለመገንባቱ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ ወይም 1997 የመስመር ካርታ ላይ መታየቱን በማረጋገጥ፤ የግንባታ ማስጀመሪያ፣ የግንባታ ክትትል ወረቀት፣ የግንባታ ርክክብ ሰነድ መጠየቅ ሳያስፈልግ ሌሎች የአገልግሎት ቅድመ-ሁኔታዎች ብቻ እንዲሟሉ በማድረግ አገልግሎቱ ይሰጣል፤

19.18.2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከወጣው የህንጻ መመሪያ ቁጥር 1/97 እና በፌደራል በወጣው የህንጻ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ግንባታቸው የተከናወኑ ህንጻዎች ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ ወይም 2003 የመስመር ካርታ ላይ የሚታይ መሆኑን በማረጋገጥ በመመሪያ ቁጥር 1/97 መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፤

19.18.3. በፌደራል በወጣው የህንጻ መመሪያ ቁጥር 5/2003 እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣው የህንጻ መመሪያ ቁጥር 2/2010 መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ግንባታቸው የተከናወኑ ህንጻዎች በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ይስተናገዳሉ፤

19.18.4. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከወጣው የህንጻ መመሪያ ቁጥር 2/2010 እና በበህንጻ መመሪያ 3/2014 መካከል ለተገነቡ ግንባታዎች በመመሪያ (2/2010) መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፤

19.18.5. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከወጣው የህንጻ መመሪያ ቁጥር 3/2014 በኃላ ለተገነቡ ግንባታዎች ማስረጃ የሚጠየቀው ሌላ ተለዋጭ መመሪያ እስካልወጣ ድረስ በዚሁ በመመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፤

19.19. በአንድ ይዞታ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ነባር ግንባታዎች አቀማመጥና በመካከላቸው ያለው ርቀት የግንባታ ፈቃድ መስፈርትን የማያሟሉ ከሆነ በተናጠል ለሚያሟላው ብሎክ ብቻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም የግንባታ ፈቃድ መስፈርትን ባለማሟላቱ ምክንያት ውድቅ የተደረገው ብሎክ በንድፉ ላይ ተቀባይነት ያላገኘበት ምክንያት ጋር በማመልከት በመጠቀሚያ ፈቃዱ የማይካተት መሆኑ በግልጽ መጠቀስ አለበት፡፡

19.20. የመጠቀሚያ ፈቃድ የቀረበበት የነባር ግንባታ የአርክቴክቸራል ንድፍ /AS-BUILT/ ሙሉ በሙሉ መሬት ላይ ባለው የግንባታ ይዘት መሰረት ንድፉ መቅረብ አለበት፡፡ መሬት ላይ ባለው የግንባታ ይዘት መሰረት በትክክል መቅረቡን ለማጣራት ከሚደረገው ከመጀመሪያው የመስክ ጉብኝት ውጭ በትክክል ባለመቅረቡ በሚደረገው ለእያንዳንዱ ምልልስ ተጨማሪ ክፍያ በተመነ መሰረት ይከፈላል፡፡

19.21. የመጠቀሚያ ፈቃድ የሌላቸው ነባር ግንባታዎች ከግንባታ ፈቃድ ወይም አፈጻጸም ወይም ከግንባታ ፈቃድ ደንብና መመሪያና ስታንዳርድ ውጭ የተከናወነ ግንባታ ቢኖር እና ይህም በመሪ ፕላኑ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚኖረው ከሆነ ባለስልጣኑ ወይም ጽ/ቤቱ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስድ ለሚመለከተው የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ያሳውቃል፡፡

19.22. የመጠቀሚያ ፈቃድ የሚያስከለክሉ ምክንያቶች፡-

19.22.1. ግንባታው ከግንባታ ፈቃድ ደንብና መመሪያና ስታንዳርድ ውጭ የተገነባ ሲሆን በተጓዳኝ የተገነቡ ጊዜያዊ ግንባታዎችን አለማንሳት፤

19.22.2. የመጠቀሚያ ፈቃድ መስፈረት የማያሟላ ከሆነ፤

19.22.3. በግንባታ ውስጥ እና ውጭ የእሳት አደጋ መከላከያ ስርዓትን ያለማደራጀት እና የአደጋ ጊዜ ጠቋሚ እና አቅጣጫ አመልካች ምልክቶች በተገቢው ቦታ ላይ አለመትከል ወይም አለመለጠፍ፤

19.22.4. ከይዞታ ውጭ የተደረገ ማስፋፋት፤

19.22.5. ግንባታ ላይ የዋለው ቁስ ባህሪ የአካባቢውን ነዋሪ ወይም የህንጻውን ተገልጋይ ወይም የአካካባቢውን ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚያውክ ወይም የሚገታ መሆን፤

19.23. የሕንፃ ሹመ ወይም የተሰየመው አካል ደህንነቱ አስጊ አለመሆኑን ለተረጋገጠ እና በከፊል ለተጠናቀቀ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በከፊል ለተጠናቀቀ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጥ የሚከተሉትን መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

19.23.1. የህንጻው ዝቅተኛ የወለል ምጣኔ ስትራክቸራል ፍሬም መሰራቱ እና ጥቅም ላይ ለማዋል የታቀደው እርከን ለአገልግሎት ዝግጁ መሆኑ፤

19.23.2. ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት የህንጻ ወለሎች ደረጃቸው የድጋፍ መያጣ ሙሉ ለሙሉ መገጠማቸውን እና ያልተጠናቀቁ የህንጻው ፎቆች ጥቅም ላይ ለማዋል ከታሰቡት ለመለየት ጊዜያዊ ከለላ የተደረገላቸው ስለመሆኑ፤

19.23.3. የህንጻው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከፍሳሽ ማስወገጃ ጋር መገናኘቱን እና ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት መጸዳጃ ቤቶች ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቃቸውን፤

19.23.4. የህንጻው የውሃ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል ለታሰበው ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁንና ውሃ መዳረሱን፤

19.23.5. የህንጻው የኤሌክትሪክ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል በታሰቡት ክፍሎች ላይ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁን መዳረሱን እንዲሁም ጥቅም ላይ የማይውለው የህንጻ ከፍል የኤሌክትሪክ አደጋ እንዳያደርስ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረጉን፤

19.23.6. የህንጻው ያልተጠናቀቀ ክፍል ለማጠናቀቅ በሚደረገው ሂደት ህንጻውን በሚጠቀሙ እና በህንጻው በኩል በሚያልፉ መንገደኞች ላይ አደጋ እንዳያደርስ መወሰድ የሚገባቸው በ "ES 3965 OCCUPATIONAL HEALTH AND SAFETY" መሰረት የደህንነት ጥንቃቄዎች መወሰዳቸውን፤

19.23.7. ህንጻው በዲዛይኑና በ "ES 3964 FIRE PRECAUTIONS DURING BUILDING CONSTRUCTION DESIGN, WORKS AND USE" እና በ "ES 3963 BUILDING SPATIAL DESIGN" ስታንዳርዶች መሰረት

የእሳት አደጋ ጊዜ ማምለጫዎች መጠናቀቃቸውንና ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን ፈትሾ በማረጋገጥ፤

19.23.8. ህንጻው ለአካል ጉዳተኞች ከእንቅፋት የጸዳ መዳረሻ መንገድ ገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ያደረገ መሆኑን፤

19.23.9. የህንጻው አመላካች የሆኑ ምልክቶች አገልግሎት ሲሰጡ በታቀዱት ሁሉ መቀመጣቸውንና አገልግሎት ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ፤

19.23.10. የእሳት አደጋ መከላከያ ስፕሪክለር ካለው በአግባቡ መገጠሙንና መስራቱን በማረጋገጥ፤

19.23.11. የህንጻው የውሃ መከላከያ አቅርቦትና ለእሳት አደጋ መከላከያ የሚሆን ውሃ አቅርቦት የሚሆን ውሃ ፓንፕ መገጠሙንና መሰራቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

19.24. አገልግሎቱ ያበቃ ወይም በወቅቱ ያልታደሰ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ እንደ ፈቃድ አያገለግልም፤

19.25. የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ሊታገድ እና/ ወይም ሊሰረዝ የሚችልባቸው ምክንያቶች፡-

19.25.1. ግድፈት እያለበት በስህተት የፀደቀ ከሆነ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፤

19.25.2. ተገልጋዩ ያቀረበው ማመልከቻ የተሳሳተ ወይም ሀሰተኛ መረጃ ከያዘ፤

19.25.3. ግንባታው የደህንነት ስጋት እንለበት በህንጻ ሹሙ ከታመነበት፤

19.25.4. የተሳሳተ የመስክ ሪፖርት በባለሙያ ከቀረበ፤

19.25.5. ግንባታው ከተፈቀደው ዲዛይን ውጭ ጥቅም ላይ ከዋለ፤

19.25.6. ህንጻው ከተፈቀደው የአገልግሎት ውጭ ጥቅም ላይ ከዋለ፤ የህንጻው መጠቀሚያ ፈቃድ ሊታገድ እና/ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

20. የአገልግሎት ክፍያና ቅጣት

20.1 የአገልግሎት ክፍያዎች

20.1.1 የፕላን ስምምነትና የግንባታ ፈቃድ ክፍያ

1) ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል፡፡

2) የፕላን ስምምነት ለማግኘት ጥያቄ ሲቀርብ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል የአገልግሎት ክፍያ ብር 300.00 በማስከፈል ስምምነቱን ይሰጣል፡፡

3) ለግንባታ ጥቅም ላይ የሚውሉት ፕላኖች በከተማው አስተዳደር ተዘጋጅተው የሚሰጡ ስታንዳርድ ፕላኖች ከሆኑ ፕላኖቹን ለማግኘት የሚፈጸመው ክፍያ እንደ ፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይቆጠራል፡፡

4) የኘላን መገምገሚያ ክፍያ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሠረት የሚሰላ ሲሆን የፕሮጀክት ግምት የሚሰላው የሕንጻዎቹን ጠቅላላ የወለል ስፋት በካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ በማባዛት ይሆናል፡-

ተ.ቁ	የፕሮጀክት ግምት /በብር/	የፕላን መገምገሚያ ክፍያ
1	እስከ 2,500,000	የፕሮጀክቱን ግምት(1/2000)
2	2,500,000 እስከ 5,000,000	1,250+{1/2500(የፕሮጀክቱን ግምት-2,500,000)}
3	5,000,000 እስከ 10,000,000	2,250+{1/3000(የፕሮጀክቱን ግምት-5,000,000)}
4	10,000,000 እስከ 20,000,000	3,920+{1/3500(የፕሮጀክቱን ግምት-10,000,000)}
5	20,000,000 እስከ 50,000,000	6,770+{1/4000(የፕሮጀክቱን ግምት-20,000,000)}
6	ከ50,000,000	14,270+{1/5000(የፕሮጀክቱን ግምት-50,000,000)}

ሰንጠረዥ20.1.1፡- ለየፕሮጀክት ግምት የሚከፈል የፕላን መገምገሚያ ክፍያ አቀራረብ

5) የሕንጻ ሹም ከሚመለከተው ተቋም በሚያቀርብለት ወቅታዊ የግንባታ የዋጋ ጥናት በመነሳት ለፕሮጀክት ግምት ስሌት የሚሆን የየህንጻ ምድቡን የካሬ ሜትር ዋጋ በማዘጋጀት ለከተማው አስተዳደር ወይንም ለተሰየመው አካል አቅርቦ ያፀድቃል፡፡ የተዘጋጀው የካሬ ሜትር ዋጋ እንደ አስፈላጊነቱ ሊከለስ ይችላል፡፡

6) በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ክፍል ስድስት በአንቀጽ 12 በተመለከተው መሠረት በግዥ በተገኘ የተመዘገበ ባለሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን የፕላን መገምገሚያ ዋጋ አሸናፊው ባቀረበው ዝቅተኛ ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

7) ለፕላን ግምገማ የቀረቡ የሕንፃ አሀዶች ተመሳሳይ ከሆኑ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ የሚሰላው የአንዱን ሕንፃ የግንባታ ሙሉ ዋጋ እና የሌሎቹን አሀዶቹ ጠቅላላ የግንባታ ዋጋ 10 በመቶ በመደመር ይሆናል፡፡

8) ውድቅ የሆኑ ፕላኖች ተስተካክለው እንደገና ለማፀደቅ በሚቀርቡበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያው ክፍያ፡-

ሀ) ለምድብ “ሀ” ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ ግማሽ፤

ለ) ለምድብ “ለ” እና “ሐ” ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ 25 በመቶ፤

ይሆናል፡፡

9) ፕላኑ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ቀደም ሲል ይኸው ፕላን ውድቅ በተደረገበት ጊዜ ሳይታይ በታለፈ ግድፈት ምክንያት ከሆነ ተስተካክሎ የሚቀርበውን ፕላን ለመገምገም ክፍያ አይጠየቅም፡፡

10) የፕላን ማሻሻያ ክፍያ ስትራክቸራል ፕላኑን እንዲለውጥ የሚያስገድድ ከሆነ ክፍያው በአዲስ ፕላን መገምገሚያ አከፋፈል መሠረት ይሆናል፡፡ ለሌሎች የፕላን ማሻሻያዎች የሚከፈለው የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ለአዲስ ፕላን መገምገሚያ የሚጠየቀው ክፍያ 25 በመቶ ይሆናል፡፡

11) የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ፡-

ለሁሉም የሕንፃ ዓይነቶች የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ መጠን ለፕላን መገምገሚያ የተከፈለው ክፍያ 10 በመቶ ይሆናል፡፡

12) ማንኛውም የእዳና እገዳ የሚያስፈልገው የግንባታ ሂደት፤ የእዳና እገዳ ማጣሪያ የግንባታው ባለቤት 100 ብር የሚከፍል ሲሆን ባለስልጣኑ ወይም ፅ/ቤቱ ለሚመለከተው ተቋም የከፈለውን ክፍያ በማሳወቅ የእዳና እገዳ ማጣሪያ ደብዳቤ በ3 ቀናት ውስጥ እንዲቀርብለት ያደርጋል፡፡

20.1.2 የቁጥጥር ክፍያ

20.1.2.1 በአንቀጽ 16 በንኡስ አንቀፅ 16.3 እና 16.4 መሠረት ማስታወቂያ ለቀረበባቸው የምድብ "ለ» እና "ሐ» ሕንፃዎች የሥራ እርከን ለሚደረግ ጉብኝት ወይም ቁጥጥር የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፣

20.1.2.2 የክትትል የአገልግሎት ክፍያ መደበኛ ክትትል ለሚደረግባቸው የሥራ እርከኖች የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ በመሆኑ ተጨማሪ ክትትል እንዲደረግ በሚጠይቅ የግንባታ ደረጃ ተጨማሪ ክፍያ አይጠየቅም፣

20.1.2.3 በቁጥጥር ማስታወቂያ ከቀረበባቸው የሥራ እርከኖች ውጪ ለሚደረግ ድንገተኛ የቁጥጥር ጉብኝት የቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ አይፈጸምባቸውም፣

20.1.2.4 ለሕንፃ ግንባታ የሚደረግ የቁጥጥር ሥራ በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ አንቀጽ 16 ንኡስ አንቀጽ 16.3 ለተመለከቱት ሕንፃዎች በተቀመጡት የሥራ ደረጃዎች መሠረት ይሆናል።

20.1.2.5 በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 4 በተመለከተው መሠረት ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየምድቡ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ፤

(ሀ) ለምድብ ለ/ ህንፃ ብር 400፣

(ለ) ለምድብ ሐ/ ህንፃ ብር 800 ይሆናል።

20.1.2.6 ለማንኛውም ግንባታ የቁጥጥር ክፍያ የሚፈፀመው ቁጥጥር የሚደረግበትን የሥራ እርከን ለመጀመር ገንቢው የግንባታ ሥራ ማስታወቂያ ቅጽ 025 ሲያቀርብ ይሆናል፣

20.1.2.7 የቁጥጥር አገልግሎት ክፍያው የተፈጸመበት ማስረጃ ወይም ደረሰኝ ቅጂ በግንባታ ፈቃድ ፋይል ውስጥ ተያይዞ መቀመጥ ይኖርበታል፣

20.1.2.8 የቁጥጥር ክፍያ የሚፈፀመው በፋይናንስ ሰርዓት ደንብና መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት ይሆናል፣ ከዚህ ውጭ የሚፈፀሙ ክፍያዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፣

20.1.3 የዕድሳት ፈቃድ፣ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ፣ የማፍረሻ ፈቃድ እና የመሃንዲስ አገልግሎት ክፍያ

20.1.3.1 የመሃንዲስ አገልግሎት፤ የዕድሳት ፈቃድ፤ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ፣ የማፍረሻ ፈቃድ በሚካሄድበት ወለል ስፋት ድምር የሚከፈል ይሆናል፡፡

20.1.3.2 የእድሳት ፈቃድ በንዑስ አንቀፅ 10.4 በተገለፀው የዕድሳት ደረጃዎች መሰረት ለደረጃ አንድ እና ሁለት ብቻ የእድሳት አገልግሎት ክፍያ የሚከፈል ሲሆን ለደረጃ ሶስት ምንም አይነት የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም፡፡

20.1.3.3 የዕድሳት ፈቃድ፤ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ እና የማፍረሻ ፈቃድ በተከፈለበት አገልግሎት ላይ ተጨማሪ የመሃንዲስ አገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም፡፡

20.1.3.4 የመሃንዲስ አገልግሎት፤ የዕድሳት ፈቃድ፤ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ፣ የማፍረሻ ፈቃድ ክፍያ በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት በተጠቀሰው የወለል ስፋት መሰረት ይሆናል፡፡

ተ.ቁ	የወለል ስፋት በካሬ ሜትር	የክፍያ መጠን
1	እስከ 100	200
2	101- 500	400
3	501- 1000	800
4	ከ1000 በላይ	1600

ሰንጠረዥ20.1.3.4፡- በወለል ስፋት መሰረት የሚከፈል የመሃንዲስ አገልግሎት፤ የዕድሳት ፈቃድ፤ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ፣ የማፍረሻ ፈቃድ ክፍያ መጠን

20.1.4 የመጠቀሚያ ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ

20.1.4.1 ደረጃ በደረጃ ተገንብቶ የመጠቀሚያ ፈቃድ ለሚሹ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ እድሳት ለሚፈልጉ ባለይዞታዎች ከታች በሰንጠረዝ 20.1.4.4 በተጠቀሰው መሰረት ለጠየቁበት ደረጃ ጥቅል ዋጋ ይሰላል፡፡

20.1.4.2 መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖራቸው ልዩ ከግንባታ የተወሰደ የመጠቀሚያ ፈቃድ ለሚጠይቁ ባለይዞታዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ ክፍያ ከታች በሰንጠረዝ 20.1.4.4 መሰረት ይሆናል፡፡

20.1.4.3 ጊዜያዊ የመጠቀሚያ ፈቃድ የወሰደ ገንቢ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ቋሚ የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመውሰድ ቢፈልግ በመጀመሪያ ለጊዜያዊ መጠቀሚያ ፈቃድ ከከፈለው ተጨማሪ የመሀንዲስ አገልግሎት ክፍያ ብቻ ይከፍላል፡፡ ከአንድ ዓመት ጊዜ ገደብ በላይ ከሆነ በሰንጠረዥ 20.1.4.4 መሰረት ይከፍላል፡፡

20.1.4.4 የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ክፍያ በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት በተጠቀሰው የፕሮጀክት ጥቅል ዋጋ መሰረት ይሆናል፡፡

የኘሮጀክት ጥቅል ዋጋ /በብር/ ገደብ	የመጠቀሚያ ፈቃድ አገልግሎት ክፍያ /ብር/		
	የኘሮጀክት ዋጋ /በብር/	የመጠቀሚያ ፈቃድ ክፍያ ስሌት	የክፍያ መጠን ጣሪያ
up to 2,500,000	2500000	project cost*1/2000	1250
2,500,000+__5,000,000	5000000	1250+((project cost-2500000)/2500)	2250
5,000,000+__10,000,000	10,000,000.00	2250+((project cost-5,000,000)/4000)	3500
10,000,000+__20,000,000	20000000	3500+((project cost-10000000)/6000)	5347
20,000,000+__50,000,000	50000000	5350+((project cost-20000000)/8000	9100
50,000,000 and above	100000000	9100+((project cost-50000000)/10000)	14100

ሰንጠረዥ20.1.4.4፡- በፕሮጀክት ጥቅል ዋጋ ዝርዝር መሰረት የሚከፈል የመጠቀሚያ ፈቃድ ክፍያ

21.ተመላሽ ክፍያዎች

21.1 ተመላሽ ክፍያ የሚባለው አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ወይም ክፍያ የተፈፀመበትአገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ወይም አገልግሎቱ ከሚጠይቀው በትርፍነት የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡

21.2 አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ እንዲመለስለት የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን ክፍያው የተፈጸመበትን የአገልግሎት ዓይነት እና ክፍያው ተመላሽ እንዲሆን የተጠየቀበትን ምክንያት በመግለጽ ክፍያ ከተፈጸመበት ደረሰኝ ኮፒ ጋር በማያያዝ ማመልከት አለበት፡፡

21.3 ማንኛውንም ክፍያ አገልግሎት ያልተፈጸመበት መሆኑ ሲረጋገጥ ተመላሽ ይደረጋል፣

21.4 ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን በማመልከቻ ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ 26 ሞልቶ የግለሰብ ከሆነ በአመልካቹ ተፈርሞ፣ የመንግስታዊ፣ የሕዝባዊ እና የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሆነ የድርጅቱ ማህተም ተደርጎ እና በሃላፊ ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል፣

21.5 ክፍያው የተፈፀመበትን የአገልግሎት ዓይነት በመጥቀስ፣

21.6 የክፍያ ቅጂ ደረሰኝ በማያያዝ፣

21.7 ተመላሽ እንዲሆን የተጠየቀበትን ምክንያት በግልጽ በመፃፍ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

21.8 በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 21.2 መሠረት ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርብ ጥያቄ ክፍያው ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፣

21.9 የተመላሽ ክፍያ አፈፃፀም በፋይናንስ ደንብና መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት ይከናወናል፣

22. መቀጮ

22.1 የከተማው አስተደደር የዚህን መመሪያና ስታንዳርድ ድንጋጌዎች በሚተላለፍ አካል ላይ እንደ ሕንጻ ምድብና እንደ ጥፋቱ ዓይነት አስተዳደራዊ መቀጮ ይጥላል፣ የቅጣት ውሳኔው የሚተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ ቅጽ 021 በመሙላት መሆን ይኖርበታል። የጥፋቱ አይነትና የቅጣቱ መጠን በህንጻ ደንቡ አንቀጽ 44 መሰረት እንደሚከተለው ይሆናል።

ተ.ቁ	የጥፋት ዓይነቶች	የህንጻ ምድብ እና አስተዳደራዊ ቅጣት መጠን (ብር)		
		ምድብ ሀ	ምድብ ለ	ምድብ ሐ
1	ፍቃድ የተሰጠበት የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ማመልከቻ ቅጂ በግንባታ ቦታ አለመገኘት	------	2000	3000
2	የውስጥ አደረጃጀት/ የግንባታ ቅድመ ዝግጅት/ ሳያሟሉ ስራ መጀመር	------	2000	3000
3	የተሰጡ የማስተካከያ ትዕዛዞችን ካጠናቀቁ በኃላ አለማስታወቅ	1000	2000	3000
4	የተሰጡ ትዕዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን	1000	2000	3000
5	ከግንባታ ክልል ውጭ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሰረት አለማንሳት	1000	2000	3000
6	ካለተቆጣጣሪ ማሰራት	------	3000	5000
7	ካለማስታወቂያ ስራ መጀመር	------	2000	4000
8	ያለ ፈቃድ ዕድሳት ማድረግ	2000	3000	5000
9	ያለ ፈቃድ የማስፋፋት ሰራ ማከናወን	2000	3000	5000
10	ያለ ፈቃድ የማፍረስ ስራ ማከናወን	2000	3000	5000
11	በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አለመውሰድ	-----	3000	5000
12	የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም	------	-----	5000

ሰንጠረዥ22.1፡- ለየህንጻ ምድብ ለተሰራ ጥፋት የአስተዳደራዊ መቀጮ ክፍያ

22.2 ከዚህ በላይ በተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ያልተመለከቱ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ የህንፃ ሹመ እንደጥፋቱ ክብደት በሠንጠረዡ ለየህንፃ ምድቡ ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ ተመጣጣኝ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት ይጥላል፡፡ እንዲሁም በተመሳሳይ መልኩ ከላይ ከተራ.ቁ 1 እስከ 11 የተዘረዘሩ ጥፋቶች እያሉ የግንባታ ስራን ሲያከናውን የተገኘ የስራ ተቋራጭም ሆነ አማካሪ ድርጅት በተመሳሳይ መልኩ እንድ ስራ ምድቡ አስተዳደራዊ ቅጣት መሰረት የሚቀጡ እና ሪከርድ እየተያዘ በተደጋጋሚ ለሦስተኛ በተመሳሳይ ጥፋት ውስጥ ከተገኘ የስራ ድርጅቱና አማካሪ ድርጅቱ ላይ የህንጻ ሹመ የተሰጣቸው ፈቃድ በሚመለከተው ተቋም እንዲታገድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

22.3 የተፈጸመው ጥፋት በአዋጁ በተመለከቱት የወንጀል ድንጋጌዎች ስር የሚወድቅ ሆኖ ሲገኝ የሕንፃ ሹመ ተገቢ ነው ብሎ የሚወስደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጥፊው ላይ የወንጀል ክስ እንዲቀርብበት ለሚመለከተው አካል መምራት አለበት፡፡

22.4 የሚጣለው አስተዳደራዊ መቀጮ ከተደራራቢ ጥፋቶች ወይም የከተማው አስተዳደር ወይም የህንፃ አዋጅ ከሚደነግገው የገንዘብና የእሥራት ቅጣት ነፃ አያደርግም፣

22.5 አስተዳደራዊ መቀጮ መክፈል የግንባታ ሥራውን የማስቆም፣ የማስነሳት ወይም የማፍረስ ርምጃዎችን ከመውሰድ የሚያግድ አይሆንም፣

22.6 በአንድ ጊዜ ለሚፈፀሙ ተደራራቢ ጥፋቶች የቅጣቱ መጠን እንደ ሕንፃው ምድብ ለየጥፋቱ የተመለከተው ድምር ይሆናል፣

23. ጊዜያዊ ግንባታ

23.1 አጠቃላይ

23.1.1 ማንኛውም ጊዜያዊ ግንባታ የሚያካሂድ ሰው ግንባታውን ለማከናወን የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፣

23.1.2 የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ጥያቄ መቅረብ ያለበት የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ቅጽ 020 በመሙላት ይሆናል፣

23.1.3 ለጊዜያዊ ግንባታ ለቀረበ ማመልከቻ የሕንፃ ሹመ ግንባታው በህንፃ አዋጁ፣ ደንቡና በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት እንዲከናወን ጊዜያዊ ፈቃድ ይሰጣል፣

23.1.4 የጊዜያዊ ግንባታ አገልግሎት በጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ ላይ የተጠቀሰው አገልግሎት ይሆናል፣

23.1.5 ተጓዳኝ፤ ወቅታዊ እና ኮንትራታዊ ጊዜያዊ ግንባታ በቀላሉ ሊነቃቀል በሚችል ቁስ የሚገነባ እና የአካባቢውን ውበት እና የተጠቃሚውን ደህንነት በጠበቀ መልኩ መሰራት ይኖርበታል፣

23.1.6 ለተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ የሚገነባ አጥር ለአካባቢው ውበት በሚሰጥ ቁሳቁስ መገንባትና ተስማሚ ቀለም መቀባት አለበት፣ ሆኖም በቀለም አቀባብ ከሚፈጠር ቅርጽ /Pattern/ በስተቀር የማስታወቂያ ጹሁፎችን መቀባት አይቻልም፣

23.1.7 ለወቅታዊ ጊዜያዊ ግንባታ የሚተከሉ መጠለያዎች የተለየ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር በመተላለፊያ መንገዶች ላይ መሆን የለበትም፣

23.1.8 አውቶቡስ ማቆሚያ፣ የህዝብ ስልክ መከለያ፣ ለአነስተኛ ጥቃቅን ንግድ ዘርፎች እና የከተማ ግብርና (የዶሮ እርባታ፣ ከብት እርባታ ወዘተ.) የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ከሚመለከተው አካል ፀድቆ የቀረበ ቦታውን የሚያሳይ የፕላን ፎርማት እና የግንባታ ዲዛይን መቅረብ አለበት፣

23.1.9 የጊዜያዊ ግንባታ የመጠቀሚያ ዘመን ሲያበቃ ግንባታውን በጊዜያዊ ግንባታው ባለቤት ወጪ ተነስቶና ቦታው በነበረበት ሁኔታ ተስተካክሎ መለቀቅ አለበት፣

23.1.10 ጊዜያዊ ግንባታ ህንጻ ቁመት ከአንድ ወለል ወይም ከመሬት በላይ ያለው አጠቃላይ ከፍታ ከ 5.00 ሜትር መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም ለተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ በግንባታ ባህሪያቸው የተለዩና ውስብስብ ለሆኑ ህንፃዎች ህንፃ ሹመ ወይም አስተዳደሩ በልዩ ሁኔታ ከ5.00 ሜትር በላይ ሊፈቅድ ይችላል ።

23.1.11 ተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ በመኪና ወይም በእግረኛ ክልል ሆኖ በዋና መንገድ በሆነ ይዞታ ላይ ለመገንባት በቅድሚያ ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የስምምነት ደብዳቤ መቅረብ አለበት።

23.1.12 በአርሶ አደር ማህበር ክልል ውስጥ የሚገኝ ግብርና (የዶሮ እርባታ፣ ከብት እርባታ ወዘተ.) የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት በአዲስ አበባ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ

ቢሮ የልማት ተነሺ አርሶ አደር መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ጽ/ቤት ወይም ከሚመለከተው አካል የይዞታው ባለቤት መሆኑን አስመስክሮ እና የመሬት ግብር ደረሰኝ በማያያዝ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ አገልግሎት ማግኘት ይችላል፡፡

23.2 የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ አቀራረብ እና የጊዜ ገደብ፤

23.2.1 ለኮንትራታዊ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ 020 ጋር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፣ የጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫ እና የጊዜያዊውን ግንባታ አርክቴክቸራልና እንደአስፈላጊነቱ የስትራክቸራል እና ኤሌክትሪካል ንድፍ ተያይዞ መቅረብ አለበት፣ የግንባታው የጊዜ ገደብ በጊዜያዊ ይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተጠቀሰው ዘመን ይሆናል፣

23.2.2 ለተጓዳኝ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ጋር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ፣ የዋናው ግንባታ ፈቃድ ኮፒ እና የጊዜያዊ ግንባታውን የቦታ አቀማመጥ እንዲሁም ወደ ግቢ መውጫ መግቢያውን የሚያሳይ ንድፍ መቅረብ አለበት፣ የግንባታው የጊዜ ገደብ የግንባታው መጠናቀቅ ወይንም የግንባታ ፈቃድ የጊዜ ገደብ ይሆናል፣

23.2.3 ለወቅታዊ ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ከግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ጋር ጊዜያዊ ግንባታው የተፈለገበትን ምክንያት በመግለጽ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የዚህ ግንባታ የአገልግሎት ጊዜ ገደብ በከተማው አስተዳደር የሚወሰን ሆኖ የጊዜ ገደቡ ከ7 ቀን መብለጥ የለበትም፣

24. የአገልግሎት ለውጥ ስለማድረግ

24.1 የህንፃ ሹሙ ከአዋጁ፣ ከማስፈፀሚያ ደንቡ፤ ከህንጻ ኮድ እና ከዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ጋር እስከተጣጣመ ድረስ የህንፃ አገልግሎት ለውጥ ማድረግ ይችላል፤

24.2 ማንኛውም ባለይዞታ በሕንፃው ላይ የአገልግሎት ለውጥ ሲያቅድ ሥራው ከመጀመሩ በፊት የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ ይኖርበታል፣

24.3 ማንኛውም ባለይዞታ የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ ሲያቅድ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ 007 መሙላት እና የፕላን ስምምነት ሰነድ አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

24.4 የአገልግሎት ለውጥ ለማከናወን ሲጠየቅ ባለይዞታው ሕንፃው የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ እና ለአገልግሎት ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ለሚሰራው ስራ የሚያስፈልጉትን ፕላኖች እና የስራ ዝርዝር አያይዞ ማቅረብ አለበት፣

24.5 ማንኛውም የአገልግሎት ለውጥ ሥራ የሚያከናውን ሰው ሥራውን ማከናወን የሚኖርበት የፕሮጀክት ግምቱን መሰረት በማድረግ ደረጃው በሚመጥን የሥራ ተቋራጭ መሆን ይኖርበታል፣

24.6 ማንኛውም ባለይዞታ በአገልግሎት ለውጥ ስራ ላይ የማፍረስ ሥራ ሲያከናውን በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያስከትልና ማንኛውንም እንቅስቃሴ እንዳያስተጓጉል ቅድመ ጥናት ማድረግ ይኖርበታል፣ ሥራውን ሲያከናውንና ሲያጠናቅቅ ፍርስራሹን በማስወገድና ቦታውን በማስተካከል ወደ ነበረበት ሁኔታ መመለስ አለበት፣

25. የተመዘገቡ ባለሙያዎችን (አማካሪ) ስለመቅጠርና የጉዳት ማካካሻ ዋስትና

25.1 የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር

25.1.1 ለማንኛውም ምድብ የሕንፃ ዓይነቶች የሚጠየቁ ዲዛይኖች ለሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ አማካሪ ድርጅቶች ወይም በልዩ የተደራጁ አማካሪ ኢንተርፕራይዞች መሠራት አለባቸው እንዲሁም ማንኛውም ግንባታ ለዲዛይን ስራ ብቻ ሳይሆን ለግንባታ ክትትል ጭምር አማካሪን በመቅጠር በአማካሪው ኃላፊነት ማሰራት አለበት፤

25.1.2 በአማካሪ ድርጅት ወይንም በኢንተርፕራይዞች የሚቀጠሩ የዲዛይን ባለሙያዎች እና በልዩ የተደራጁ ኢንተርፕራይዝ ባለሙያዎች የዲዛይን ሥራ ለማከናወን የተመዘገቡና ለበጀት ዓመቱ የታደሰ የባለሙያ ምስክር ወረቀት፣የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቁጥር የያዙ መሆን አለበት፤

25.1.3 በአንቀጽ 25.1 ንኡስ አንቀጽ 25.1.2 መሠረት የሚቀጠሩ የዲዛይን ባለሙያዎች የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለዲዛይን እና ለቁጥጥር ሥራ ያወጣውን ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት አለባቸው፣

25.1.4 ለማንኛውም የሕንፃ ምድብ ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየሥራው በሚመጥኑ

የተመዘገቡ እና በልዩ የተደራጁ ኢንተርፕራይዝ አማካሪዎች በበጀት ዓመቱ የታደሰ የባለሙያ የምስክር ወረቀት ባላቸው ባለሙያዎች ቁጥጥሩ መደረግ ይኖርበታል፡፡

25.1.5 ማንኛውም የተመዘገበ የዲዛይን አማካሪ ድርጅት ወደ ሥራ ከመግባቱ በፊት ለሰራው ፕላንና የሥራ ዝርዝር ወይንም ሁለቱንም አገልግሎት በጣምራ ሲያከናውን ሊደርሱ ለሚችሉ ጉዳቶች እና ግድፈቶች ከታወቀ የመድህን ድርጅት የጉዳት ማካካሻ ዋስትና ማቅረብ አለበት፣

25.1.6 የዋስትናው ዓይነትና መጠን በደንቡ አንቀጽ 19 ንኡስ አንቀጽ 6 በተመለከተው መሰረት እንደሚከተለው ይሆናል፣

ተ.ቁ	የህንጻ ምድብ	የፕሮጀክት ግምት/ብር/	የዋስትና መጠን(የፕሮጀክቱን ግምት)	የዋስትና መጠን ጣሪያ/ብር/	የዋስትና ጊዜ	የዋስትና አቀራረብ
1	ከሪል እስቴት ውጭ ያሉ የምድብ "ለ" ህንጻዎች	5,000,000	10 በመቶ	500,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድህን ድርጅት፤ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
2	ለሪል እስቴት እና ለምድብ "ሐ" ህንጻዎች	2,500,000	20 በመቶ	500,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድህን ድርጅት፤ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
		10,000,000	15 በመቶ	1,500,000		
		20,000,000	10 በመቶ	2,000,000		

ሰንጠረዥ12.1.6፡- ለሕንጻ ምድብ አይነት በአማካሪ የሚቀርብ የዋስትና ዓይነትና መጠን አቀራረብ

25.1.7 ለዋስትና መጠን ስሌት የሚሆነው የፕሮጀክት ዋጋ ግምት የሚሰላው በህንጻውጠቅላላ ስፋት እና የህንጻ ሹመ አዘጋጅቶ በሚያቀርበው እና በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚጸድቀው የየምድቡ ዝርዝር የዋጋ ግምት ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡

25.1.8 የፕሮጀክት ዋጋ ለህንጻ ምድቡ በተመለከቱት ሁለት ዋጋዎችመካከል ሲሆን የዋስትና መጠኑ የሚሰላበት የላይኛውን መቶኛ ተመጣጣኝ መለኪያ ንጽጽር

(prorate) በኘሮጀክት ዋጋ በማብዛት ይሆናል።

26. የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮች ስለመቅጠር

ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው ፈቃድ ያለውና የፈቃድ ዘመኑ የታደሰ የሥራ ተቋራጭ መቅጠር ይኖርበታል፣

26.1 የግንባታ ባለሙያዎቹ የግንባታ ሥራ ለማከናወን የተመዘገቡና የሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ ምስክር ወረቀት እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው መሆን አለባቸው፣

26.2 የግንባታው ባለቤት ግንባታውን የሚያካሂድለት ሥራ ተቋራጭ መቅጠር ያለበት የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ባወጣው የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች እና ሥራ ተቋራጮች ምዝገባ መመሪያና ስታንዳርድ መሠረት ይሆናል፣

26.3 የግንባታው ባለቤት ግንባታውን የሚያካሄድለትን የሥራ ተቋራጭ የገንቢ ግዴታመግቢያ ቅጽ 012 በማስሞላት ለሕንፃ ሹመ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

26.4 በማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክት በተቋራጭ መመደብ ያለበት ባለሙያ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች እና ሥራ ተቋራጮች ምዝገባ መመሪያና ስታንዳርድ መስፈርት ማሟላት አለበት፣

26.5 ማንኛውም በግንባታ ሥራ ላይ የተሠማራ ባለሙያ ሲቀየር የሥራ ተቋራጩ ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፣ ተቋራጩና አማካሪው ሲቀየር ደግሞ ባለቤቱ፣ተቋራጩና አማካሪው ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል ውል መቋረጡን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣ የተጠቀሰውን የማሳወቂያ ቀናት ተላልፎ በሚገኝ እና በሚደረሰው ጉዳት ተቋራጩ አማካሪው እና ባለቤቱ በጋራ ወይም በግል ኃላፊነት ይወስዳሉ።

26.6 የግንባታ ሥራውን ለማከናወን ውለታ የገባ የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራ ፈቃድ ቅጂ በግንባታ ቦታ ማስቀመጥ አለበት፣

26.7 ማንኛውም የተመዘገበና ሕጋዊ ፈቃድ ያለው የሥራ ተቋራጭ የግንባታ ሥራ

ከመጀመሩ በፊት የገንቢ ግዴታ ቅጽ 012 መሙላት አለበት፣

26.8 ማንኛውም ውል የገባ የግንባታ ስራ ተቋራጭ በውለታ ሰነዱ መሰረት ጥራቱ ተጠብቆ ግንባታው ለመከናወኑ እና በስራ ጥራትና ጉድለቶች ለሚደርሱ ጉዳቶች የግንባታ ስራው ከተጠናቀቀ በኃላ ቢያንስ ለ1 ዓመት የሚቆይ የጉዳት ማካሻ ዋስትና በደንቡ አንቀጽ 20 ንኡስ አንቀጽ 6 መሰረት እንደሚከተለው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ተ.ቁ	የህንጻ ምድብ	የፕሮጀክት ግምት/ብር/	የዋስትና መጠን (የፕሮጀክቱን ግምት)	የዋስትና መጠን ጣሪያ/ብር/	የዋስትና ጊዜ	የዋስትና አቀራረብ
1	ከሪል እስቴት ውጭ ያሉ የምድብ "ለ" ህንጻዎች	10,000,000	20 በመቶ	500,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድህን ድርጅት፤ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
2	ለሪል እስቴት እና ለምድብ "ሐ" ህንጻዎች	10,000,000	30 በመቶ	500,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድህን ድርጅት፤ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
		15,000,000	25 በመቶ	3,750,000		
		25,000,000	20 በመቶ	5,000,000		

ሰንጠረዥ26.8፡- ለሕንጻ ምድብ አይነት በተቋራጭ የሚቀርብ የዋስትና ዓይነትና መጠን አቀራረብ

26.9 አነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ የሆኑ ግንባታዎች በህንጻ ግንባታ ላይ የተደራጁና የስራ ተቋራጭ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች በመቅጠር ማሰራት ይቻላል፡፡

ክፍል ሶስት

27. የመሬት አጠቃቀም እና ተጓዳኝ ጥናቶች

27.1 አጠቃላይ

27.1.1 ማንኛውም ግንባታ የከተማው ኘላን ኮሚሽን ያስቀመጠውን የመሬት አጠቃቀምና የህንጻ ከፍታ፣የአየር መመላለሻ ገደብ (Aviation zone) እንዲሁም ተጓዳኝ ህግጋትን ማሟላት ይኖርበታል፣

27.1.2 በአንድ የመኖሪያ ይዞታ ተነጣጥለው በተሰሩ ሁለት ብሎኮች ወይንም በከፊል በተያያዙ ሁለት ብሎኮች መካከል በትይዩ በተሠሩ ሁለት የግድግዳ ገጾች፣

27.1.2.1 አንዱ የግድግዳ ገጽ ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በታች ተካፋች ካለው ቢያንስ 2.50 ሜትር፣

27.1.2.2 አንዱ የግድግዳ ገጽ መስኮት ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በላይ ተካፋች ካለው 1.5 ሜትር መራቅ ይኖርበታል።

27.1.2.3 በሁለቱም የግድግዳ ገጾች ተካፋዮች ቢያንስ 1.5 ሜትር ከፍተት መኖር አለበት፣

27.1.3 በአንድ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋም ይዞታ ውስጥ ተነጣጥለው በተሰሩ ሁለት ብሎኮች ወይንም በከፊል በተያያዙ ሁለት ብሎኮች መካከል በትይዩ በተሠሩ ሁለት የግድግዳ ገጾች እንደሚከተለው ይሆናል፡-

27.1.3.1 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በጀርባ ወይም በፊት ለፊት በኩል ሁለቱም የግድግዳ ገጾች ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በታች ተካፋች ካለው ቢያንስ 6.00ሜትር፤

27.1.3.2 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በጀርባ ወይም በፊት ለፊት በኩል አንዱ የግድግዳ ገጽ ብቻ ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በታች ተካፋች ካለው ቢያንስ 3.00ሜትር፤

27.1.3.3 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በጀርባ ወይም በፊት ለፊት በኩል አንዱ ወይም ሁለቱም የግድግዳ ገጽ ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በላይ ተካፋች ካለው/ካላቸው ቢያንስ 1.50ሜትር፤

27.1.3.4 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በጀርባ በኩል በሁለቱም የግድግዳ ገጽ ተካፋች ከሌለ ተካፋዮቹ ቢያንስ 1.50ሜትር ወይም ሁለቱም የግድግዳ ተካፋዮች ተጣብቀው መሰራት አለባቸው፡፡

27.1.3.5 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በሁለቱም ጎኖች በኩል ሁለቱም የግድግዳ ገጾች ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በታች ተካፋች ካላቸው ቢያንስ 4.00ሜትር፤

27.1.3.6 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በሁለቱም ጎኖች በኩል አንዱ የግድግዳ ገጽ ብቻ ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በታች ተካፋች ካለው ቢያንስ 2.00ሜትር፤

27.1.3.7 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በሁለቱም ጎኖች በኩል አንዱ ወይም ሁለቱም የግድግዳ ገጽ ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በላይ ተካፋች ካለው/ካላቸው ቢያንስ 1.50ሜትር፤

27.1.3.8 ከዋና አገልግሎት ህንጻ በሁለቱም ጎኖች በኩል በሁለቱም የግድግዳ ገጽ ተካፋች ከሌለ ተካፋዮቹ ቢያንስ 1.50ሜትር ወይም ሁለቱም የግድግዳ ተካፋዮች ተጣብቀው መሰራት አለባቸው፡፡

27.1.4 በአንድ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋም ይዞታ ስር አንድ የዋና አገልግሎት ህንጻ ውስጥ ለአየር እና ለብርሃን አገልግሎት ተብለው በከፊል ለተከፈቱ የግድግዳ ገጾች መራቅ ያለበት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

27.1.4.1 አንዱ የግድግዳ ገጽ ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በታች ተካፋች ካለው ቢያንስ 2.50 ሜትር፣

27.1.4.2 አንዱ የግድግዳ ገጽ መስኮት ከወለል በላይ ከ1.7 ሜትር በላይ ተካፋች ካለው 1.5 ሜትር መራቅ ይኖርበታል፡፡

27.1.5 ከህንፃ የፊት ለፊት ገጽታ በኩል ወይም ከዋናው የመዳረሻ መንገድ በኩል ወይም ከዚህ ውጭ ያለ በአዋሳኝ መንገድ በኩል ያለው ርቀት በአንቀጽ 27.1.1 በተገለጸው መሰረት ይሆናል፡፡

28. ዲዛይኖች

28.1 አጠቃላይ

28.1.1 ማንኛውም የህንፃ ዲዛይን የከተማውን መሪ ፕላን መሰረት በማድረግ ደህንነቱ የተረጋገጠ ሆኖ መሰራት አለነት፤

28.1.2 ማንኛውም የህንፃ ለሚገኝበት ምድብ የሚያስፈልጉ ፕላኖች በአንቀፅ 25 ንዑስ አንቀፅ (25.1) መሰረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤

28.1.3 ማንኛውም ፕላን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የዲዛይን ንድፍ የወረቀት መጠን መሠረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

A0 - 841 x1189 ሚ.ሜ፣ A1 - 841 x 594 ሚ.ሜ፣ A2 - 420 x 594 ሚ.ሜ፣

A3 - 297x 420 ሚ.ሜ፣

28.2 አርክቴክቸራል ዲዛይን

ከዚህ በታች የተመለከቱት ንድፎች በአርክቴክቸራል ዲዛይን ተካተው እና እንዳስፈለጊነቱ ከሪፖርት ጋር ተያይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

ሀ) **የቦታ አቀማመጥ ኘላን** (site plan)፣ በሳይት ፕላኑ ላይ በዋነኛነት መካተት ያለባቸው፡-

- ሊሠራ / ሊሻሻል የታቀደውን ሕንፃ አቀማመጥ፣
- ሕንጻው ከወሰን ከመንገድና ከሌሎች ነባር ግንባታዎች ያለውን ርቀት፣
- የመዳረሻ መንገዱ ስያሜና ወደ ህንፃው መግቢያ አመልካች ምልክት፣
- በይዞታው ላይ የነባር ግንባታ ካለ የነባር ግንባታው አቀማመጥ፣
- የተፈጥሮ መሬት ተዳፋት ኘላን (contour plan) እና የፍሳሽ ማጠራቀሚያ ቦታ ወይም ከዋናው ፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ጋር የሚያገናኝ ከሆነ የማስወገጃ መስመር
- የጣሪያ የተፋሰስ አቅጣጫ እና የተዳፋት መጠን እንዲሁም በልኬት የተጠቀሰ የመኪና ማቆሚያ፣የሰሜን አቅጣጫ አመልካች ምልክት መካተት ይኖርባቸዋል፣
- አረንጓዴ ቦታዎችን አግባብነት ባላቸው የከተማ ፕላን እና ማስፈጸሚያ የህግ

ማዕቀፎች በሚያስቀምጡት መስፈርት መሰረት፤

- ወደ አጥር ግቢ የሚያስገባ በር የሚያሳይ
- ለህዝብ መጠቀሚያ ተቋም የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ ማስቀመጫ ቦታ /Solid Waste Container/ SWC በሚል መካተት ይኖርባቸዋል፣

ለ) የወለል ኘላን (Floor Plan)

- የህንጻው ሁሉም ወለሎች የወለል ኘላን መዘጋጀት አለበት፣
- ፍፁም ተመሳሳይ ወለል ያላቸው (Typical floor) በሚል ተጠቅልሎ ሊቀርብ ይችላል፣
- የቆጥ ወለል (mezzanine floor) ካለ ለብቻው መታየት አለበት፣
- ከተፈጥሮ መሬት ያለዉ ከፍታ መገለፅ አለበት፡፡
- አምዶችን (COLUMN) የሚያመላክት ስም መቀመጥ አለበት (AXIS NAME)
- ወለሉ ላይ የተቀመጡ ክፍሎች ስም፣ የክፍል ስፋት እና የወለል ቁስ መቀመጥ አለበት፡፡
- ከእያንዳንዱ ክፍል በተጨማሪ በወለሉ ዙሪያ ልኬቶች መቀመጥ አለባቸዉ፡፡
- ፕላኖቹ ተነባቢ ሆነዉ መቀመጥ አለባቸዉ፡፡

ሐ) የተቆረጠ የቁምኘላን (Section)

- የተቆረጠ የቁም ኘላን (Section) ቢያንስ የጣሪያ ውቅር፣የምድር በታች ወለል፣ሁለትና ከዚያ በላይ ያሉ ወለሎችን የሚያገናኝ ክፍተት (open wall) እና የመወጣጫ ደረጃ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡
- የተቆረጠ የቁም ኘላን (Section) ከመሬት በታች፣ ከመሬት ላይ እና ከመሬት በላይ ያለውን ዝርዝር አሰራሩን የሚገልጽ የወለል፣ የግርግዳ፣ የተካፋች እና የጣሪያ ቁስ መቀመጥ አለበት፡፡
- ከመሬት በታች፣ ከመሬት ላይ እና ከመሬት በላይ ያለውን የክፍል ስያሜ እና የውስጥ ለውስጥ ልኬት መቀመጥ አለበት፡፡

መ) የውጭ ገፅታ ኘላን (Elevation)

- የውጭ ገፅታ ኘላን የሁሉንም የህንፃ ገፅታዎች የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡
- ሙሉ በሙሉ የማይታይና በሌላ ሕንፃ የተሸፈነ የውጭ ገፅታ በተቆረጠ የቁም ገጽታ ኘላን (Sectional Elevation) መታየት አለበት፣

- በሁሉም የሕንፃ ገፆች ላይ የሚገነባበት የግንባታ እቃ መፃፍ አለበት፡፡
- መስኮቶች ከተፈጥሮ ወለል ያላቸዉ ከፍታ እና መስኮቱ ካለበት ወለል ያለዉ ከፍታ መገለፅ አለበት፡፡
- በዉጪ ገጽታ በኩል የሚቀመጡ መስታዎቶች ወይም ከመስታወት የተሰሩ የዉጪ ግድግዳዎች አንጸባራቂ አለመሆናቸው መገለጽ አለበት፡፡
- “አዲስ አበባ የሀገሪቷና የአፍሪካ መዲና እንደመሆኗ መጠን ደረጃዋን የሚመጥን በአረንጓዴ ልማት፣ በመሰረተ-ልማትና በህንጻዎች የራሷ የሆነ ስታንዳርድ እና በቀለም የሚገለጽ ብራንድ እንዲኖራት፡

    - የአረንረንጓዴ ልማት የአርባን ዲዛይን ቅርጽ/Pattern/ ይዞ እንዲለማ ማድረግ ይኖርበታል
    - ህንጻዎች በሁሉም አቅጣጫ በዉጭ ገጽታ በኩል የሚገነባበት የማጠናቀቂያ ቁስ ወይም የሚቀባ ቀለም ከከተማዉ ዲዛይን(Urban Design) እና ሞርፎሎጂ(Morphology) ጋር የተጣጣመ፣ አካባቢን የማይረብሽ እንዲሁም ለከተማዉ/ለአካበቢዉ ከተወሰነዉ ዓይነትና ቀለም ዉጭ መሆን የለበትም፤
    - የሚገነቡ መሰረተ-ልማቶች (መንገድ፣ ድልድዮች፣ የመንገድ መብራቶች፣ የትራፊክ ምልክቶች ወዘተ) አለም አቀፋዊ ሰታንዳርድ ሊኖራቸዉና ከህንጻዎችና ከአረንጓዴ ልማቱ ጋር የተናበቡ መሆን ይኖርባቸዋል፤

- **የህንጻ ቀለም ዲዛይን ስታንዳርድ፡ የህንጻ ቀለም አይነት**
    - ለህንጻ የውጭ ቀለም ዲዛይን ማስተግበሪያ የሚያገለግለው ስታንዳርድ RAL የሚባለው የአውሮፓ የቀለም ማዛመጃ ስርዐት ነው፡፡
    - ለህንጻ የውጭ ቀለም ዲዛይን መጠቀም የሚቻለው በRAL ስታንዳርድ የቀለም ክልል (range) ውስጥ ለአካባቢው የተፈቀደውን የቀለም አይነት ብቻ ነው፡፡

- **የህንጻ ቀለም አጠቃቀም**

  - ከላይ የተጠቀሰዉ እነደተጠበቀ ሆኖ የተቀመጠው የቀለም አይነት በህንጻው የውጭ አካል ላይ የሚገኝ ማንኛውም ከተፈጥሮ ቁስ ውጭ የሆነ የህንጻ ቁስ ላይ ተግባራዊ ይሆናል።
  - ህንጻው የሚቀባው የወለም አይነት በመመሪያና ስታንዳርድ የተፈቀደውን እና ለአካባቢው የተወሰነውን የቀለም አይነት ነው፤ የአካባቢው ቀለም ዝርዝር በሚወጣው የቀለም ስታንዳርድ ይወሰናል።
  - ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ህንጻ ከተማ አስተዳደሩ በሚያወጣው የአፈጻጸም እርከን አቅጣጫ የቀለም ዲዛይኑን የሚተገብር ይሆናል።
  - ማንኛውም በግንባታ ላይ ያለ ወይም አዲስ ግንባታ ይህ መመሪያና ስታንዳርድ ው ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የቀለም ዲዛይኑን ተግባራዊ ያደርጋል።

- **የህንጻ የመጀመሪያ ወለል**

  - ከላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለህንጻው የመጀመሪያ ወለል ላይ ማንኛውም አይነት በቀለም ያልተገደቡ የተፈጥሮ ቁስ እንዲሁም የህንጻ ቁስ ግንባታ ግብአት መጠቀም ይቻላል።
  - ማንኛውም ህንጻ በመጀመሪያው ወለል ላይ ከ2 ካሬ.ሜ ያላነሰ ስፋት ያለው ቦታ በወለል ወይም ግድግዳው ላይ ለአረንጋዴ ልማት ማዋል አለበት።

- **የህንጻ ማስታወቂያ ስታንዳርድ**
  - የህንጻ ባለቤት ለህንጻው ዋና ስም እንዲሁም ተከራይ ለሆነ የንግድ ቤት ስም በተዘጋጀው የውጭ ማስታወቂያ ስታንዳርድ መሰረት ተዘጋጅቶ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤
  - ለማንኛዉም የንግድ ሱቅ ወይም ቢሮ ስምና ምልክት የሚውል የማስታወቂያ ዕሁፍ መጠን ከህንጻው ጎልቶ የሚታይ መሆን የለበትም፤ የጽሁፉ መደብም በአንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀፅ ፫ ላይ የተቀመጠው የህንጻው የውጭ የቀለም አይነት ክልል ውስጥ መሆን አለበት።

- የህንጻውን የውጭ ገጽ አካላት ላይ የሚሰቀል ማስታወቂያ ይዘቱ የነዋሪውን ወግና ባህል ያከበረ በመሆን የሚገባው ሲሆን መጠኑ ደግሞ በውጭ ማስታወቂያ ስታንዳርድ ላይ በሚቀመጠው መሰረት ይወሰናል፡፡

ሠ) ግልፅ ባልሆኑ እና ተጨማሪ የጎላ ንድፍ በሚጠይቁ የዲዛይን አካላት ላይ ዝርዝር ፕላን (Detail plan) መዘጋጀት አለበት፡፡

ረ) ከላይ ለ፣ሐ እና መ ለተገለጹት የወለል ከፍታቸው ከተፈጥሮ ምድር በላይ ወይም በታች መመልከት አለበት፣

ሰ) በዚህም መሰረት ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል፡፡

28.3 ስትራክቸራል ዲዛይን

ከዚህ በታች የተመለከቱት በስትራክቸራል ዲዛይን ተካትተው መቅረብ አለባቸው፣

ሀ/ የሶሌታ ዲዛይን ንድፍ፣ሶሌታውንና ሶሌታው የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ በኘላን እና በሁለቱም የቁም አቅጣጫ የሚያሳይ ንድፍ እና የብረት መጠን፣ርዝመት፣ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ (Bar schedule) የሚገልጽ መሆን አለበት፣

ለ/ የወጋግራ (Beam) ዲዛይን ንድፍ ወጋግራው የሚኖረውን የብረት አቀማመጥና በሁለቱም የቁም እና አግድም አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍና የብረት መጠን መግለጫ ሰንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፣

ሐ/ የኮለም ዲዛይን ንድፍ፣የኮለም አግድማዊ ቁርጥ እይታ Horizontal cross section) እና ኮለሙ የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እና የሚኖረውን የብረት መጠን፣ርዝመት፣ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የሚገልፅ መሆን አለበት፣

መ/ የመሠረት ዲዛይን ንድፍ፣ለየመሠረቱ ዓይነት የኘላን፤የቁም ገጽታ እና መሠረቱ የሚኖረውን የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እንዲሁም የሚኖረውን የብረት መጠን ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፣

ሠ/ ክብደት ተሸካሚ ግድግዳ (shear wall) የአርማታ ግድግዳ እንዲኖረው በሚገደድበት የህንፃ አካል በአግድማዊ እይታ (Horizontal cross section) እና ግድግዳው የሚኖረው

የብረት አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ እና የሚኖረውን የብረት መጠን፣ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሰንጠረዥ የሚገለፅ መሆን አለበት፣

ረ/ ደጋፊ ግንብ (Retaining wall) ፣ደጋፊ ግንብ እንዲኖረው በሚገደድበት የሕንፃ አካል የአግድምና የቁም ገፅታ (Horizontal vertical cross section) እና ግንቡ የሚኖረውን አቀማመጥ ስፋትና መጠን የሚያሳይ ንድፍ እና የአርማታ ግድግዳ ከሆነ የሚኖረውን የብረት መጠን ርዝመት ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የሚገልፅ መሆን አለበት፣

ሰ/ የተገጣጣሚ አካላት ንድፍ፣ በተገጣጣሚ የሕንፃ አካላት ለሚሠራ ህንፃ የሁሉም የህንፃ አካላት ፕላንና የመገናኛ ዝርዝር ፕላን (Detail plan) መዘጋጀት አለበት፣

ሸ/ የጣሪያ ክንች ውቅር፣የክንች ኘላን የቁም ገፅታና ከተሸካሚ መዋቅሮች ጋር ያለውን ትስስር የሚያሳይ ንድፍ የያዘ መሆን አለበት፣

ቀ/ ሌሎች መዋቅራዊ ይዘት ያላቸው የግንባታ ክፍሎች ለምሳሌ ደረጃ፣ፍሳሽ ማጠራቀሚያ፣ውሃ ማጠራቀሚያና መስቀያ ወዘተ አቀማመጥ ስፋትና መጠን የሚያሳይ ንድፍ እና የአርማታ ግንባታ ከሆነ የሚኖረውን የብረት መጠን፣ርዝመት፣ርቀትና ብዛት መግለጫ ሠንጠረዥ የያዘ መሆን አለበት፡

በ/ የህንጻ ከመሰረት በታችና በላይ ባሉ የስትራክቸራል ዲዛይኖች ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት የሚመለከታቸው ክፍሎች እንደየአስፈላጊነታቸው በአግባቡ ተጠቅመው ዲዛይኑን መከናወኑን እና በዲዛይን ሪፖርት ውስጥም በዝርዝር መካተታቸውን መታየት ይኖርባቸዋል፡፡

ቨ) የህንጻ ስትራክቸራል ዲዛይን ዲዛይን በሚደረግበት ወቅት ህንጻው የሚገነባበት አካባቢ እንደአስፈላጊነቱ ተሻሽሎ ስራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት የመሬት መንቀጥቀጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም ክንውኑ በዝርዝር መታየት ይኖርበታል፡፡

ተ/ የህንጻ ስትራክቸራል ዲዛይን ከመሰረት ስራው ጀምሮ እስከ ጣሪያው ስራ በስራ ላይ በዋሉ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት መከናወን ይኖርባቸዋል፤ ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት

መሰራቱን ያረጋግጣል፡፡

28.4 ፍዘታዊ ስሌት (statical calculation)

ለአንድ ኘሮጀክት ዲዛይን ምርመራ የሚቀርብ ስታቲካል ስሌት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

ሀ) የግንባታውን ዲዛይን አጠቃላይ መነሻና ታሳቢዎችን የሚዘረዝር መግቢያ ያለው፣

ለ) ለዲዛይን የተጠቀመበትን የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ የሚጠቅስ፣

ሐ) የሁሉም የግንባታ አካላት ስታቲካል ስሌት statical Calculation የሚያሳይ፣

መ) ዲዛይኑ የተዘጋጀበት ፕሮግራም (SoftWare) የሚጠቅስ መሆን ይኖርበታል፣

28.5 የአፈር ምርመራ ውጤት፣

ከዚህ በታች የተመለከቱት በአፈር ምርመራ ጥናት ተካትተው መቅረብ አለባቸው፣

28.5.1 የመሠረት አፈር ምርመራ መከናወን ያለበት ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተመዝግቦ ፈቃድ በተሰጠው ኩባንያ ወይም ድርጅት መሆን አለበት፤

28.5.2 የአንድ ኘሮጀክት የግንባታ ቦታ የአፈር ጥናት ተካሂዶ የሚቀርብ የላቦራቶሪ ውጤት የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣

ሀ/ ለምርመራ የሚጠቀምበትን የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ ማጣቀሻ፣

ለ/ የአፈር ምርመራና የመሸከም ውጤት መግለጫ፣

ሐ/ የመሠረት ዲዛይን ዓይነት አማራጭ ጥቆማ፣

መ/ ሌሎች የተለዩ ከምድር በታች ያሉ የህንፃ አካላት ዲዛይን አሠራር ጥቆማ የያዘ፤

ሠ/ ግንባታው የሚያርፍበት ቦታ የአፈር መደርመስ አደጋ የሚገጥመው ከሆነ ለአፈር መደርመስ መከላከያ አማራጭ ዘዴዎችን ጥቆማ፤

ረ/ ከሪፖርት ጋር የብቃት ማረጋገጫ እና የታደሰ የንግድ ፈቃድ ቅጂ ከዋናው ሰነድ ጋር የሚመሳከር፤ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

ሰ/ የአፈር ምርመራውን ውጤት መሰረት አድርጎ ሰነድ የሚያዘጋጅ አማካሪ ወይም ባለሙያ አጠቃላይ ለሚፈጠረው ችግርና ለውጥ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

28.6 የህንጻ ሳኒተሪ ዲዛይን

ከዚህ በታች የተመለከቱት በሳኒታሪ ዲዛይን ጥናት መካተት አለባቸው፣

ሀ/ የሁሉም ወለሎች የንፁህ ውኃ አቅርቦት ፕላን፣

ለ/ የሁሉም ወለሎች የፍሳሽ ማስወገጃ ፕላን፣

ሐ/ የጣሪያ ፍሳሽ እና የዝናብ ውኃ ማስወገጃ ፕላን፣

መ/ የሳይት ሳኒተሪ ዲዛይን ፕላን (የውጭ ንፁህ ውሀ አቅርቦት፣ ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ማጣሪያ የዝናብ ውሀ ማስወገጃ ያጠቃልላል)

ሠ/ ለህዝብ መገልገያ ለሆኑ ህንፃዎች ወይም በምድብ ሐ ስር የተካተቱ ህንጻዎች የሁሉም ወለሎች የእሳት መከላከያ ፕላን፣

ረ/ ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች የሚያካትት የሳኒተሪ ዲዛይን ሪፖርትና ማጣቀሻ ኮድ መገለጽ አለበት፡

ሰ/ የህንጻ ሳኒተሪ ዲዛይን ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት ዲዛይኑ መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም በዝርዝር መታየት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል፡፡

28.7 ኤሌክትሪካል ዲዛይን

ከዚህ በታች የተመለከቱት በኤሌክትሪካል ዲዛይን ጥናት ተካተው መዘጋጀት አለባቸው፣

ሀ/ የወለል ፕላኖች የኤሌክትሪክ ዲዛይን ንድፍ፣ የኤሌክትሪክ ገመድ የሚሳብባቸው ቱቦዎች፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮኒክስ ገመድ የሚዘረጋባቸው ምሶሶዎችና መብራቶች፣ የኤሌክትሪክ መስመር ጭነት ማጠቃለያና የሳይት ፕላን ጭነት መካተት አለበት፣

ለ/ ከላይ የተጠቀሱትን ስራዎችን የሚያካትት የኤሌክትሪካል ዲዛይን ሪፖርትና ማጣቀሻ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ መገለጽ አለበት፣

ሐ/ የህንጻ ኤሌክትሪካል ዲዛይን ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት ዲዛይኑ መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም በዝርዝር መታየት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል።

28.8 የመካኒካል ዲዛይን

ሀ/ በመካኒካል ዲዛይን ጥናት ውስጥ የቦይለር (የውሃ ማሞቂያ፣የአየር ማስተካከያ (air condition)፣ የአሳንሰር መግለጫ እንዲሁም ግፊት (pump) ዲዛይን፣ ሪፖርትና መግለጫ መቅረብ አለበት፣

ለ/ የህንጻ መካኒካል ቬንትሌሽን እና ኤር ኮንዲሽኒንግ ዲዛይን አግባብነት ባለው እና በተሻሻለው የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት መሰራት ይኖርባቸዋል፤ እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል።

28.9 የእሳት መከላከያ ስርዓት ንድፍ እና የማምለጫ ስርዓት

28.9.1 ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ በሚቀርበው የህንጻ ዲዛይን ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ ፕላን ከዚህ በታች በተመለከቱት መስፈርት መሰረት አካትቶ ማቅረብ አለበት፤

1/ የማምለጫ በሮች እና በሁሉም የመውጫ በሮች ላይ የተሰየመው ስያሜ፤

2/ የሁሉም ማምለጫ በሮች ግለሰብን የመያዝ አቅም፤

3/ የማምለጫ መንገዶች በተለያየ የመስመር አይነት ወይም ቀለም ማመላከት፤

4/ የማምለጫ መንገዶች ላይ የተመላከተ የጉዞ ርቀት እና ከፍተኛውን የጉዞ ርቀት ከመጨረሻው የክፍል ጥግ እስከ ማምለጫ በሮች ድረስ ያለውን ማመላከት፤

5/ የአደጋ ጊዜ መወጣጫ ደረጃ፣ በሮችና መተላለፊያዎች መጠንና ቀጥተኛነት ደረጃውን የጠበቀ እና ከመሰናክል ነፃ መሆን፣

6/ ግንባታው እሳትን መቋቋም ያለበት ሰዓት፣

7/ ጠቋሚ ምልክቶች የሚተከሉበት ቦታና አይነታቸው (በቀን፣ በማታና መብራት በሌለበት ጊዜ ሊታይ የሚችለበት ሁኔታ በተገናዘበ መልኩ)፣

8/ በየወለሉ የሚቀመጥ ውሃ መርጫ ጥቅል ከውኃ መርጫው ጋር የተገናኘ ውኃ ማጠራቀሚያ እና መብራት በማይኖርበት ጊዜ ሊኖር ስለሚገባው አማራጭ የኃይል ምንጭ፣

9/ የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ደወል፣

10/ የአደጋ ጊዜ መቆያ ክፍል፣

11/ በግድግዳ ላይ የሚንጠለጠሉ ተንቀሳቃሽ እሳት ማጥፊያዎች አቀማመጥና ከግንባታው አገልግሎት አንፃር ሊነሳ ከሚችለው እሳት ዓይነት ጋር ያለው አግባብነት፣

12/ መብረቅ መከላከያ፣

13/ የመገልገያ ቁሳቁሶች አቀማመጥና የተሰሩበት ቁስ ደረጃ በአደጋ ጊዜ ሊደረስ የሚችለውን አደጋ የሚያባብስ አለመሆኑን ማረጋገጫ፣

14/ ለምግብ ማብሰያ ክፍል፣ቦይለር ክፍልና ወርክሾኘ ከዋናው ግንባታ በተለየ የሚደረግ ጥንቃቄ፣

28.9.2 ከላይ በተራ ቁጥር 1 እስከ 14 ከተገለፁት በተጨማሪ ለማምረቻና ማከማቻ ተቋማት፣

1/ የመውጫ በሮች ቁጥር የሠራተኛ ብዛት እና የአጠቃላይ ግንባታው ወለል ስፋት መጠን፣

2/ እንደማምረቻ ወይም ማከማቻው ባህርይ ጪስ ጠቋሚ፣ ነበልባል ጠቋሚ፣ ሙቀት ጠቋሚ፣ መሣሪያዎች መታየት፣

3/ እንደማምረቻ ወይም ማከማቻው ባህርይ በራሱ ጊዜ የሚሰራ የውሀ መርጫ /sprinkler/ እና የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ደወል ሊኖረው ይገባል።

28.9.3 ከላይ በአንቀፅ 28.9.1 ከተገጹት በተጨማሪ የፈሳሽ ነዳጅና ቡታጋዝ ማከማቻ ተቋም

1/ fixed foam installation ያላቸው፣

2/ ከሌሎች ተቋማት በተናጠል የተገነባ፣

3/ እሳትን ለመከላከል በራሱ ጊዜ የሚሰራ የውሀ መርጫ (sprinkler)፣

4/ የፈሳሽ ነዳጅ ቃጠሎ ማጥፊያ ኬሚካል (foam Compound & foam Monitor - trailer)፣

5/ የእሳት አደጋውን ለመከላከል የሚችል በቂ የውኃ ማጠራቀሚያ ጋን ከመጠባበቂያ የኃይል ምንጭ አቅርቦትጋር፣

6/ የአካባቢ የፍሳሽ መስመር ከግቢው ከሚወጣ የፍሳሽ ነዳጅ መጠበቂያ ማካተት ይኖርበታል።

28.9.4 ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ ዲዛይን እና ግንባታ ሂደቱ የእሳት አደጋ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ሲሆን በዲዛይን ወቅት የእሳት አደጋ ማምለጫና የህንጻው መዋቅራዊ አካላት እሳትን መቋቋም ስለመቻላቸው በተሻሻለው የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሰረት መሰራት ይኖርባቸዋል፤እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑን እና በስታንዳርዱ መሰረት መሰራቱን ያረጋግጣል።

29. አርክቴክቸር ወይም ስነ ህንፃ

29.1 የህንፃ ዲዛያኖች ከህንፃ አዋጁ፣ ደንቡ፣ መመሪያና ስታንዳርድ ውና ስታንዳርዱ ጋር የተገናዘበ መሆን ይኖርበታል፤

29.2 የማንኛውም ህንፃ ፕላኑ ሲሠራ ተቀባይነት ያላቸውን ስታዳርድ መሰረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

29.3 የዲዛይን ኘሮግራም ሲዘጋጅ የአሰሪውን ፍላጐት የሚሰጠውን አገልግሎት እና ለኘሮጀክቱ የተያዘውን በጀት /አቅም/ ያገናዘ በመሆን ይኖርበታል፣

29.4 በዲዛይን ዝግጅት ህንጻው ሊሰጠው የታሰበው አገልግሎትና የቦታ አጠቃቀም ኢኮኖሚያዊነትንና አዋጪነትን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፣

29.5 ለማንኛውም ህንፃ እንዲገጠም የሚመረጥ አሳንሰር መወሰን ያለበት የተጠቃሚውን ቁጥር ፣የአገልግሎት አይነት እና ምቹነትን መሰረት በማድረግ ይሆናል፤

29.6 የፕላን አግድም ልኬት የሚነሳው ካልተለሰነው የግድግዳ ጠርዝ ነው፤

29.7 የወለል ስፋት በግድግዳ የተያዘውንና በተቀባሪ ቁምሳጥን የተያዘውን ቦታ አያካትትም፤

29.2 የዲዛይን ስታንዳርዶች

29.2 አጠቃላይ

ሀ) ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ሕንፃ የዲዛይን ስታንዳርዶች ማለትም የክፍል፣የተካፋች፣ የመተላለፊያ፣ በር፣ መስኮት፣ባልኮኒ፣ ቆሻሻ ማስወገጃ፣ አሳንሰር ስታንዳርዶች ከሕንፃ አዋጁ ደንብና ከዚህ መመሪያና ስታንዳርድ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር የተገናዘበ መሆን ይኖርበታል።

ለ) ለማንኛውም ተሸከርካሪ የማቆያ ቦታ እንደ ከተማው እድገት እና መልካምድራዊ አቀማመጥ በከተማ ፕላን ህግጋት መሠረት ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፣ የቤት ውስጥ የመኪና ማቆሚያ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የመኪና ማቆሚያው ዝቅተኛ የክፍል ቁመት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፣

1. እስከ 10 ለሚደርሱ መኪናዎች 2.10 ሜትር፣

2. ከ10 እስከ 30 ለሚደርሱ 2.30 ሜትር፣

3. ከ30 እስከ 70 ለሚደርሱ 2.50 ሜትር፣

4. ከ70 በላይ 2.60 ሜትር፣

ሐ) የቆጥ ወለል የክፍል ቁመት አጠቃላይ ድምር ከ6 ሜትር ከበለጠ እንደ ሁለት ወለል ይታሰባል፣

መ) የክፍል ቁመት ከ6 ሜትር በላይ የሆነ ግንባታ ወለል ብዛት የሚሰላው የክፍሉን አጠቃላይ ቁመት ለ3 በማካፈልና የሚገኘውን ውጤት ወደ ዝቅተኛው ስሌት በማስጠጋት ይሆናል፣

ሠ) የጣሪያ ላይ ክፍሎች ወለል ስፋት የደረጃ መወጣጫ እና የአሳንሰሩን ወለል ስፋት ድምር ሳይበልጥ ሌሎች ለህዝብ አገልግሎት መስጫነት የማይውሉ ክፍሎች ሊኖሩት ይችላል፣ከዚህ ስፋት በላይ ክፍሎች ያሉት የጣሪያ ወለል እንደ አንድ ወለል ይታሰባል፣

ረ) ማምረቻ ወይም ማከማቻ ወይም የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ ከሆኑ ግንባታዎች ውጭ የዛኒጋባ ጣሪያ ከፍታው (ክፈፍ ሳይጨምር) ከ2.8 ሜትር በላይ የሆነ ጣሪያ እንደ አንድ ወለል ይታሰባል፣

30. የግል መኖሪያ ቤት የዲዛይን ስታንዳርዶች

ከዚህ በታች የተመለከቱት የዲዛይን ስታንዳርዶች የግል መኖሪያ ቤትን ብቻ ይመለከታሉ፡-

30.1 የክፍል ስታንዳርድ

ሀ) ማንኛውም የመኖሪያ ቤት የክፍል ስፋት ከ6 ካ.ሜትር ማነስ የሌለበት ሲሆን የየትኛውም ግድግዳ ወርድ ከ2 ሜትር ማነስ አይችልም፡፡ሆኖም የመጸዳጃ፤ልዩ የአገልግሎት አይነት ያላቸውና በሚገጠምላቸው መሳሪያ ባህሪ ስፋታቸው የሚወሰን ክፍሎች ከ6 ካሬ ሜትር ስፋትና ከ2ሜትር ወርድ አንሰው ሊሰሩ ይችላሉ፣

ለ) ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ህንጻ ከወለል እስከ ኮርኒስ ያለው አነስተኛው የክፍል ቁመት ከ2.50ሜትር በታች መሆን የለበትም፡፡

ሐ) ስላሽ ኮርኒስ ላላቸው የመኖሪያ ቤት ክፍሎች ሰው ሊጠጋበት በሚችልበት በዝቅተኛው በኩል ያለው የክፍል ቁመት ከ2.0 ሜትር ማነስ የለበትም፣

መ) መኝታ ክፍል ለአንድ ሰው 6 ካሬ ሜትር ሲሆን እንደ ሳሎን የሚያገለግል ከሆነ ከ12 ካሬ ሜትርማነስ የለበትም፣

30.2 የተካፋች ስታንዳርድ

ሀ) ማንኛውም ተካፋች ከይዞታ ወደ ውጭ መከፈት አይችልም፣

ለ) ወደ ግቢ መግቢያ ቢያንስ ለመኖሪያ 3 ሜትር መጠበቅ ይኖርበታል፣

ሐ) የመፀዳጃና ባልኮኒ የበር ስፋት ከ70 ሳ.ሜ እንዲሁም ቁመት ከ210 ሳ.ሜ ያነሰ መሆን የለበትም፣

30.3 የመታላለፊያ ስታንዳርድ/ ደረጃ እና ኮሪደር/

ሀ) ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኮሪደር እና የውስጥ ደረጃዎች ከ90 ሳ.ሜትር ያነሰ መሆን የለበትም፣

ለ) በአንድ ተከታታይነት ባለው የመወጣጫ ደረጃ የተለያዩ የመርገጫ ስፋት ወይም የመወጣጫ ከፍታ መጠን መጠቀም አይቻልም፣ሆኖም ወደ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ወይም ወደ ማሽን ክፍል ወይም ለተመሳሳይ አገልግሎት ለዋሉ ክፍሎች የሚያደርስ ደረጃ ከሆነ ከተጠቀሰው መጠን የተለየ ሊሆን ይችላል፣

ሐ) ማንኛውም የመኖሪያ ቤት የውስጥ ደረጃዎች ስፋት (Tread) ከ25 ሳንቲ ሜትር ማነስ እና የደረጃዎች ቁመት (Riser) ከ18 ሳንቲ ሜትር መብለጥ የለበትም፣

30.4 በር እና መስኮት

ሀ) ብርሃን የሚያስገባ ተካፋች ስፋት ከክፍሉ የወለል ስፋት ቢያንስ 15% መሆን አለበት፣

ለ) የበር ስፋት የተጣራ 80 ሳ.ሜ እና ቁመት የተጣራ 200 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

ሐ) የፊት መስታውት ዓይነት (mirror glass) ወይንም ተመሳሳይ ውጤት እንዲኖረው የተደረገ መስታወት ለግንባታ የውጭ አካል አገልግሎት መጠቀም አይቻልም፣

መ) ለመኖሪያ አገልግሎት ለሚውል ህንፃ ዋና መግቢያ በር ስፋት ደግሞ ከ120 ሳ.ሜ ማነስ የለበትም፣

ሠ) የኩሽና፣ የሳሎን እና የመኝታ ክፍል የበር ስፋት ከ90 ሳ.ሜ ቁመት ከ2.1 ሜትር ማነስ የለበትም፣

30.5 ባልኮኒ ስታንዳርድ

የባልኮኒ መደገፊያ የፍርግርጉ ስፋት ከ0.11 ሜትር መብለጥ የለበትም፣መደገፊያ ቁመቱ ከ1.05 ሜትር ማነስ የለበትም፣

30.6 ሳኒተሪ ስታንዳርድ

የመኖሪያ ቤት መፀዳጃ ከመታጠቢያ ጋር መዘጋጀት አለበት፣

30.7 ኤሌክትሪካል ስታንዳርድ

ሀ) መብራቶቹ ህንጻው ሊሰጠው ከታሰበው አገልግሎት አንፃርና የክፍሎቹ አቀማመጥ በቂ የብርሀን አቅርቦት፣

ለ) ማንኛውም የኤሌክትሪክ እቃ ዲዛይኑን ባዘጋጀው ባለሙያ/በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል፣

30.3 የአጥር ስታንዳርድ

ሀ) የአጥር ከፍታ የሚለካው ከተፈጥሮ የምድር ወለል ጀምሮ ነው፣

ለ) በሁለት አዋሳኞች መካከል የሚገነባው አጥር ከፍተኛው የግንብ ቁመት 2.5 ሜትር መብለጥ የለበትም፣

ሐ) ከውስጥ ለውስጥ መንገድ የሚዋሰን አጥር ወደ ውስጥ በማያሳይ ቁስ ወይንም ግንብ ከተሰራ ቁመቱ ለመኖሪያ 1.50 ሜትር፣ ለድርጅት 90 ሳ.ሜ. ነው፡፡ ሆኖም ለመኖሪያ ቢያንስ 75 ፐርሰንት ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ እስከ 2.00 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡

መ) ከውስጥ ለውስጥ ውጭ ለሆነ መንገድ ባለይዞታው ከዋናው መንገድ በኩል በሚዋሰነው ድንበር ላይ የሚገነባው አጥር ከፍታ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት መሆን አለበት፡፡ ሆኖም በሌሎቹ አዋሳኞች በኩል ያለው በመደበኛ የአጥር ስታንዳርድ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

1. ለመኖሪያ 70 ሳ.ሜ. ሆኖ ቢያንስ 75% ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ እስከ 1.50 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡

2. ለቢሮ እና ለሌሎች የንግድ ተቋማት 70 ሳ.ሜ.፤

3. ለማምረቻ፣ ማከማቻ እና ማህበራዊ ተቋማት 80% ወደ ውስጥ በሚያሳይ ቁስ በመገንባት እስከ 1.50 ሜትር ከፍ ማድረግ ይቻላል::

4. ለኢምባሲዎችና ለዲፕሎማቲክ ተቋማት እስከ 2.50 ሜትር በድፍን ቁስ መስራት የሚቻል ሲሆን ተቋሙ በሚያቀርበው የደህንነት መጠበቂያ ዘዴ ምርጫ እስከ 3.00 ሜትር ከፍታ መሸፈን ይቻላል፡፡

ሠ) ለአጥር የተከለለ ዕጽዋት ቅርንጫፍ ወይም ሌላ አካል ከይዞታ ውጭ ወደ መንገድም ሆነ አዋሳኝ ማለፍ የለበትም፡፡ ቁመቱም ለአጥር ከተፈቀደው ከፍታ በላይ መሆን አይችልም፡፡

31. ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ዝግጅቶች ስታንዳርድ

ሀ) ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሚሆን መልኩ መገንባት ወይም አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ የተመቻቹ ሁኔታዎች ሊሟላለት ይገባል፣

ለ) ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆን ከሕንፃ አዋጁ ደንብና ከዚህ መመሪያና ስታንዳርድ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር የተገናዘበ መሆን ይኖርበታል፣

ሐ) ከ4 ፎቅ በላይ ለሚኖራቸው የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች አሳንሰር በሕንፃው ውስጥ መገጠም ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን 20 ሜትር እና በታች ከፍታ ያላቸዉ የመኖሪያ ቤቶች እና አፓርትመንቶች አሳንሰር እንዲኖራቸው

አይገደዱም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከ20ሜትር በታች ቁመት ያላቸው መኖሪያዎችና አፓርትመንቶች የደረጃዉ ስፈት ከ1.20ሜትር በላይ ከሆነ ዋናዉን ደረጃ እንደ አደጋ ጊዜ መዉጫ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

ክፍል አራት

32. በህንፃ ግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች

32.1.አጠቃላይ

32.1.1 የሕንፃዎች ግንባታ በሚከናወንበት ጊዜ ጊዜያዊ ወለሎች፣ ማረፊዎች፣ ፎርምዎርኮች እና ደህንነት መጠበቂያ መረቦች ሥራው ለሚቆይበት ጊዜ ሁሉ መዘርጋት ይኖርባቸዋል፣

32.1.2 በአንቀጽ 32 ንኡስ አንቀጽ (32.1.1) የተመለከተውን የደህንነት መጠበቂያ መረቦች መጠቀም የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ጊዜያዊ ወለል ሥራው በሚሰራበት ከፍታ ልክ መዘርጋት ይኖርበታል፣

32.1.3 በሥራ ቦታዎች ሠራተኞች ለሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ከሚያስፈልጉ ክፍተቶች በስተቀር የስራ ቦታዎችን ሙሉ ለሙሉ የሚሸፍኑ ጊዜያዊ ወለሎች እንዲኖሩ መደረግ ይኖርበታል፣ ክፍተቶቹም በሚገባ ሊከለሉ ይገባል፣

32.1.4 አደጋ ሊያስከትል የሚችል እያንዳንዱ የወለል ክፍተት፣ በአስተማማኝ ሁኔታ መሸፈን ወይም መከለል ይኖርበታል፣ ለክፍተት በተጋለጡ ጎኖች ሁሉ ከለላ ድጋፍ እና የእግር መደገፊያ ጣውላ ሊኖር ይገባል፣ ወይም ከክፍተቱ በታች ለእያንዳንዱ ክፍተት የሚያገለግል የደህንነት መረብ ሊዘረጋ ይገባል፣

32.1.5 በሥራ ቦታዎች ላይ ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች (ማቴሪያሎች) ሊወድቁ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ፣

ሀ) ሠራተኞች ለአደጋ ወደተጋለጡ ቦታዎች እንዳይገቡ ለመከላከል እንዲቻል ቦታዎቹ መዘጋት ወይም መከለል የሚኖርባቸው ሆኖ በተጨማሪም በሁሉም የሥራ ቦታዎች ጎኖች እና አቅራቢያዎች ጎልተው የሚታዩ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች መቀመጥ ይኖርበታል፣

ለ) ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሶች ሊወድቁ በሚችሉባቸው ቦታዎች የመቅለቢያ መድረኮች ሊኖሩ ይገባል፣ መድረኮቹም፣ ከሕንፃው ውጭ ከ3 ሜትር ባላነሰ ርቀት ሊዘረጉ እና ፊታቸውን ወደ ሕንፃው አቅጣጫ አድርገው ወደ ውስጥ ማዘንበል ይኖርባቸዋል፣

32.1.6 የግንባታ ሥራዎች በሰዎች እና በንብረት ላይ የሚደርሱ አደጋዎች እና ጉዳቶችን እንዲሁም የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል እንዲቻል መወሰድ ያለባቸውን ወይንም ለሕይወት ጠንቅ የሚሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች እንዳይደርሱ ጥንቃቄን ግምት ውስጥ በማስገባት መገንባት ይኖርባቸዋል፣

32.1.7 የሕንፃዎች ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት ወደ ወሰንተኛ ይዞታ እና ወደ መንገድ የሚወድቅ፣ የሚራገፍ ፣ የሚበን እና የሚንጠባጠብ የግንባታ ቁሳቁስ እና መሳሪያ እንዳይኖር ተገቢው መከላከያ መደረግ አለበት፡፡

32.1.8 በመንገድ ዳር በሚሠሩ ሕንፃዎች አካባቢ ቁሳቁሶች ከላይ ወድቀው ከሥር የሚንቀሳቀስውን መንገደኛ እንዳይጐዱ ከጠንካራ ቁሳቁስ የተዘጋጀ መከለከያ አጥር መዘጋጀት ይኖርበታል፣

32.1.9 ከግንባታ ቦታ የሚወጡ እና ወደ ግንባታ በሚደረግ የመጫን ማውረድ እንቅስቃሴ ምክንያት በመንገድና ከይዞታ ውጪ በአካባቢው ላይ የሚወድቀውንና የሚራገፈውን ቁስና ተረፈ ግንባታ ገንቢው በራሱ ወጪ የማፅዳት ኃለፊነት አለበት፣

32.1.10 ልዩ ፈቃድ ከሌለ በስተቀር አንድን የግንባታ ቁስ ከይዞታ ውጭ ማከማቸት አይፈቀድም፣

32.1.11 በግንባታ ወቅት ጤናን እና ድህንነትን ለማረጋገጥ በግንባታው ሂደት ላይ የሚሳተፉት በሙሉ በስራ ላይ የዋለውን የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ "ES 3965 OCCUPATIONAL HEALTH AND STANDARD" መሰረት ስራቸውን ማከናወን አለባቸው፡፡

32.1.12 የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሰራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት እንደ ስራው አይነት መውሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄ ተገቢው ገንዛቤ ማስጨበጥ አለበት፡፡

32.1.13 የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሰራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ አሰፈላጊ አልባሳት ማሟላት አለበት፤አማካሪውም ይህ መሟላቱን መከታተል ይኖርበታል፤ እንዲሁም የህንጻ ሹሙም ተወካይ ሁሉም አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ማረጋገጥ አለበት፤ ያልተሟላ ከሆነ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ይገባዋል፡፡

32.1.14 ማንኛውም ከአንድ ወለል በላይ የሚገነባ የህዝብ መጠቀሚያ ህንፃ ግንባታው ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሴፍቲ ባለሞያ ሊኖር ይገባል፡፡

32.1.15 የሴፍቲ ባሞያው የሴፍቲ ፕላን ተዘጋጅቶ በዚሁ አግባብ እየተሰራ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

32.2 በግንባታ ወቅት መደረግ የሚገባቸው የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች

ማንኛውም ግንባታ በሚከናወንበት ወቅት፡-

32.2.1 በግንባታው አካባቢ ያሉት የመሠረተ ልማት አውታሮች አገልግሎት ከመስጠት መስተጓጎል የለባቸውም፣

32.2.2 የአዋሳኝ ህንፃዎች ደህንነት መጠበቁ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

32.2.3 በሜካኒካል መሣሪያዎች ጉድለት ወይም ብልሽት ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስ መሣሪያዎቹ በትክክል መሥራታቸው በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፣

32.2.4 ህንፃው ዙሪያ የወዳደቁ ማቴሪያሎች እና ቆሻሻዎች እንዲሁም ያለአግባብ የተከማቹ ብናኝ አደገኛ ኬሚካሎች መወገድ አለባቸው፣

32.2.5 በሕንፃ ግንባታ ቦታ ላይ በሰውና በእንስሳት ላይ ጉዳት አንዳያደርስ ከለላ መኖር አለበት፣

32.2.6 ከደረሱ አደጋዎች በመነሣት መንሴያቸውን መተንተን ምልክታ ማካሄድና የናሙና ፍተሻ በማድርግ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፣

33 መወጣጫዎች እና መሰላሎች

33.1 መወጣጫዎች (Scaffoldings)

33.1.1 ማንኛውም መወጣጫ (Scaffoldings) መሸከም በሚገባው ክብደት መጠን መሠረት ዲዛይን ተደርጐ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ለማንኛውም ከምድር በላይ ስድስት ፎቅ እና በላይ ለሆነ ህንጻ ግንባታ የሚውሉ መወጣጫ (Scaffoldings) በተለምዶ ጥቅም ላይ ከሚውሉት አጠና እና ጣውላ ቁስ ውጪ በተገጣጣሚና ተነቃቃይ ብረት ቁስ የተሰሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

33.1.2 በመወጣጫው (Scaffolding) ድጋፎች ጥብቅ መሠረት ወይም ደፎች እንዲኖራቸው እና መወጣጫው የድጋፍ መያ[1] እንዲኖረው ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፣

33.1.3 በመወጣጫው (Scaffolding) ላይ የሚገኙ የሥራ መድረኮች ስፋት ከ50 ሳ.ሜ ያነሰ መሆን የለበትም፣

33.1.4 በመወጣጫው (Scaffolding) ሥር የሚዘጋጀው ጣውላ፣ ብረት ወይም አጠና ጠንካራ እና ሰዎችን እና እቃን የማይጥልና የማያንጠባጥብ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፣

33.1.5 የመወጣጫ ድልድሎችን ለመስራት ጥቅም ላይ የሚውለው የእንጨት ዓይነት አገልግሎት ላይ ከመዋሉ በፊት ጥንካሬአቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፣

33.1.6 ቀጥተኛ በሆኑት የፊት እና የኋላ የመወጣጫ ድጋፎች መካከል ያለው ርቀት ከ85 ሳ.ሜ የማያንስ ሆኖ በአንድ ጣውላ ስፋት የሚበልጥ ክፍተት እንዳይፈጠር ተጨማሪ ጣውላዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፣

33.1.7 የሚሰካኩ በወጣጫዎች (Scaffolding) ዲዛይን የሚደረጉት፣ የሚመረቱት እና አገልግሎት ላይ የሚውሉት አምራ ች በሚሰጡት መግለጫ መሠረት መሆን ይኖርበታል፣

33.1.8 መወጣጫዎች መዘርጋት ወይም መፈታት የሚኖራባቸው በሥራው ልምድ ባላቸው ሰዎች ወይም ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች

ተቆጣጣሪነት መሆን አለበት፤

33.1.9 ጉዳት የደረሰበት ወይም የላላ የመወጣጫ አካል ተገቢው እድሳት ተደርጎለት በአስተማማኝ ሁኔታ እስካልተጠናከረ ድረስ አገልግሎት ላይ መዋል የለበትም፣

33.1.10 በግንባታ ቦታ ላይ የሚገኝ መወጣጫ ከአደጋ የተጠበቀ መሆኑ በአሠሪው ወይም በሠራተኞቹ የእለት ከእለት ቁጥጥር ሊደረግለት ይገባል፣

33.1.11 በመወጣጫ ድልድሉ ላይ የሚቀመጠው እቃ መወጣጫው መሸከም ከሚችለው አቅም በላይ እንዳይሆን ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፣

33.1.12 መወጣጫዎች ቀጥ ብለው እና ተስተካክለው መዘርጋት ያለባቸው ሲሆን ከሕንፃው አካል ጋር በእያንዳንዱ 4.5 ሜትር ከፍታ እንዲሁም በየ6 ሜትሩ ርቀት አግድም መታሰር አለባቸው፣

33.1.13 ተንቀሳቃሽ መሰላል መሳይ መወጣጫዎች ከመሬት ወለል ከ5 ሜትር በላይ ለሚሰራ ስራ ጥቅም ላይ መዋል የሌለባቸው ሆኖ ከ5 ሜትር በታች ለሚሠራ ሥራ በአንድ ጊዜ ከሁለት ሠራተኞች በላይ ሊገለገሉባቸው አይገባም፣

33.2 መሰላሎች

33.2.1 የእንጨት መሰላሎች አስተማማኝ በሆነ ጥንካሬ የተሰሩ እና በሚሰጡት አገልግሎት ምክንያት የሚደርስባቸውን ጫና መሸከም የሚችሉ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣

33.2.2 ከእንጨት የተሰሩ መሰላሎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ቀለም የተቀቡ መሆን ይገባቸዋል፣

33.2.3 ከቦታ ወደ ቦታ ሊዘዋወሩ የሚችሉ ተንቀሳቃሽ መሰላሎች አገልግሎት ላይ ከመዋላቸው በፊት ተገቢው ፍተሻ ሊደረግላቸው ይገባል፣

33.2.4 የላሉ ወይም የተሰበሩ ወይም የጎደሉ መወጣጫዎች ወይም የተሰነጠቁ የጎን ቋሚዎች ያሏቸው መሰላሎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ

አይፈቀድም፣

33.2.5 የተንቀሳቃሽ መሰላል የጎን ቋሚዎች የታችኛው ጫፎች ጠንካራ በሆነ እና በተደላደለ መደብ ላይ ማረፍ የሚኖርባቸው ሆነው የጎን ቋሚዎቹ የላይኛው ጫፍ የሚሸከመውን ክብደት ለመደገፍ በሚችል በቂ ጥንካሬ ባለው ደጋፊ አካል እንዲገፉማድረግ ይገባል፣

33.2.6 ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ነጠላ ወይም ተደራራቢ ወይም ተቀጣጣይ መሰላሎች እንዳይንሸራተቱ ተንሸራታች ያልሆነ መደብ እንዲኖራቸው ወይም እንዲያያዙ ወይም እንዲታሰሩ መደረግ ይኖርባቸዋል፣

33.2.7 የኤሌትሪክ ፍሰት ባለበት አካባቢ የሚያገለግሉ መሰላሎች ኤሌክትሪክ የማያስተላልፉ ዓይነት ሆነው በመሰላሎቹ እና በኤሌትሪክ አስተላላፊዎቹ መካከል በቂ ክፍት ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣

33.2.8 ከብረት የተሰሩ መሰላሎች ወይም በእንጨት ተሰርተው በሽቦ የተጠናከሩ መሰላሎች በሃይል የተሞላ የኤሌክትሪክ መሣሪያ በአለበት ቦታ ላይ መጠቀም የተከለከለ ነው፣

33.2.9 የመሰላሎች ርዝመት ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት መሆን ይኖርበታል፣

ሀ) ለባለድጋፍ መሰላሎች ወይም ተቀጣይ ለሆኑ ባለድጋፍ መሰላሎች 4.8

ለ) ለነጠላ መሰላሎች 9 ሜትር፣

ሐ) ሁለት ተቀጣጣይ ክፍሎች ላሏቸው ተቀጣጣይ መሰላሎች 14.6 ሜትር እና

መ) ከሁለት ተቀጣጣይ ክፍሎች በላይ ላሏቸው ተቀጣጣይ መሰላሎች 20 ሜትር፣

33.2.10 ከ6 ሜትር በላይ ቁመት ያላቸው እንዳይንቀሳቀሱ ተደርገው የተተከሉ መሰላሎች፣

ሀ) ከ6 ሜትር ያልበለጠ ርቀት ያላቸው መቆሚያዎች

እንዲኖራቸው መደረግ ይኖርበታል፣

ለ) ከመሰላሉ የታችኛው ክፍል ከ2.5 ሜትር በላይ ለሆነ ከፍታ ሠራተኞች እንዳይወድቁ ለመከላከል የሚስችል የደህንነት መጠበቂያ አጥር (ኬጅ) ሊኖረው ይገባል፣

33.2.11 የማይንቀሳቀሱ መሰላሎች መተከል ያለባቸው በየመሐከላቸው የ3 ሜትር ርቀት እንዲኖር ተደርጎ ሆኖ ከላይ እስከታች ያለው አካላቸው ይህን ርቀት መጠበቅ ይኖርበታል፣

33.2.12 በተተከሉ መሰላሎች ላይ ከሚገኙ መወጣጫዎች በስተጀርባ በትንሹ 1.75 ሜትር ስፋት ያለው ቦታ በቋሚነት እንዲኖር ማድረግ ይገባል፣

33.2.13 ከመሰላሎቹ በላይ መወጣጫዎች እንዳይኖሩ ሆኖ የጎን ቋሚዎቹ ከመሰላሎቹ ማረፊያ በላይ 90 ሳ.ሜ እስከሚቀረው ድረስ መቀጠል ይኖርባቸዋል፣

ማሳሰቢያ፡- የደህንነት ባለሞያው በግንባታ ወቅት ለሰራተኛ ደህነት ሲባል የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን መወጣጫዎችና መሰላሎችን ወደ ስራ ከመገባቱ በፊት ደህነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

34. የማፍረስ ሥራ

34.1 አንድ ሕንፃ በሚፈርስበት ጊዜ ተያያዥ የሆኑ የቋሚ ግንባታ አካላት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን መሐንዲሱ ካላረጋገጠ በስተቀር ሙሉ ለሙሉ መደገፍ አለባቸው፣

34.2 አንድ ሕንፃን ለማፍረስ ሲወሰን በቋሚው የግንባታ አካል ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሥራዎች ካሉ የማፍረስ ሥራው ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ መቋረጥ አለባቸው፣

34.3 የማፍረስ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ሠራተኞችን ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ መስታወቶች እና ክፈፎቻቸው በቅድሚያ መነሳት ይኖርባቸዋል፣

34.4 የአንድ ሕንፃ የማፍረስ ሥራ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከላይ ወደ ታች መከናወን ይኖርበታል፣ ግድግዳዎችም አደገኛ ወይም ያልተረጋጋ በሆነ ሁኔታ ቆመው እንዲቀሩ መደረግ የለበትም

34.5 ግድግዳዎች ወይም ሌሎች የግድግዳ ክፍሎች የወለሉን የመሸከም አቅም ባላገናዘበ ሁኔታ በሕንፃው ወለል ላይ እንዲወድቁ ወይም በወለሉ ላይ እንዲቆዩ መደረግ የለበትም፣

34.6 ማንኛውም ሠራተኛ ከታች በሚገኙ ወለሎች ላይ እንዳይገኙ ካልተደረገ ወይም ወደ ወለሎቹ መግባት ካልተከለከለ በስተቀር በወለሉ ላይ ከሚገኝ ክፍተት ጀምሮ በ3 ሜትር ርቀት ውስጥ የሚገኝ የውስጥ ወይም የውጭ ግድግዳ እንዲፈርስ ከመደረጉ በፊት ከወለሉክፍተት በታች የሚሆን ጣውላ እንዲኖር መደረግ አለበት፣

34.7 የሚፈርሱ ቁሶች ከሕንፃው ላይ በጥንቃቄ እንዲወርዱ ሆነው ባግባቡ መከማቸት እና መወገድ ይኖርባቸዋል፣

34.8 ፍርስራሽ ማቴሪያሎች እና ሌሎች ቆሻሻዎች በወለሎች ወይም ከሕንፃው ውጭ በቅርብ ርቀት ላይ መጣል የለባቸውም፣

34.9 ከከፍተኛ ወለሎች ላይ ፍርስራሽ ማቴሪያሎች ወደ መሬት ሲወረወሩ ማቴሪያሉ እንዲወድቅ በሚፈለግበት ቦታ ሠራተኞች እንዳይገቡ ቦታው መከለል ወይም መዘጋት ይኖርበታል፣ በተጨማሪም በአካባቢው ላይ የማስጠንቀቂያ ምልክት መደረግይኖርበታል፣

34.10 አንድ ሕንፃ በሚፈርስበት ጊዜ ፍርስራሽ ሸክላዎች ወይም ሌሎች የደቀቁ ፍርስራሾችን ለማስወገድ የሚያስችል ማንሸራተቻ ወይም ማስተላለፊያ ሊኖረው ይገባል፣

34.11 ማንሸራታቻዎቹ ወይም ማስተላለፊያዎቹ ባልተቋረጠ ሁኔታ በህንፃው ላይ ሊዘረጉ የሚችሉት ሕንፃዎቹ ከሁለት ወለል ያልበለጠ እንደሆነ ብቻ ነው፣

34.12 ከእያንዳንዱ ማስተላለፊያ በታች መዝጊያዎች ወይም ማገጃዎች እንዲገጠሙ እና በማንሸራታቻ የመውጫ አፎች አጠገብ “ተንሸራታች ማቴሪያል" የሚል የማስጠንቀቂያ ምልክት መቀመጥ ይኖርበታል፣

35. ስለ ከፍታ እና የጣሪያ ላይ ሥራዎች

35.1 የከፍታ ላይ ሥራዎች

35.1.1 ሠራተኞች ከወለል ከ3 ሜትር በላይ ከፍታ ላይ የሚሰሩ ሆኖ ሲገኝ የመጠንጠልጠያ ገመዶች፣ የደህንነት መጠበቂያ ቀበቶዎች ወይም የአደጋ መከላከያ መረቦች መቅረብ ይኖርበታል፣

35.1.2 ሠራተኞች ሊወድቁ ወይም ሊንሸራተቱ የሚችሉበት በወለል ላይ የሚገኝ ክፍት ቦታ በከለላ ድጋፍ እና በእግር መደገፊያ ጣውላ መሸፈን ወይም መከደን ይኖርበታል፣

35.1.2 በማንኛውም በከፍታ ቦታ ላይ የመገንባት ወይም የማፍረስ ሥራ የሚሰራ ሠራተኛ ከአደጋ መከላከል የሚያስችሉ የጭንቅላት፣ የእጅ እና የእግር መጠበቂያ ማቴሪያሎችን መጠቀም ይኖርበታል፣

35.2 የጣሪያ ላይ ሥራዎች

35.2.1 ማንኛውም የጣሪያ ሥራ በቅድሚያ የታቀደና ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግለት ይገባል፣

35.2.2 በጣሪያ ሥራ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም ሠራተኛ የፊዚካላዊ እና ሳይኮሎጂካዊ ብቃት ያለው፣ በጣሪያ ሥራ ላይ በቂ እውቀት እና የሥራ ልምድ ያለው መሆን ይገባዋል፣

35.2.3 የጣሪያ ሥራ የሠራተኞችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል የአየር ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ መቋረጥ ይኖርበታል፣

35.2.4 ለጣሪያ ሥራ የሚውሉ የመንሿቀቂያ እንጨቶች፣ መረማመጃዎች እና የጣሪያ መሰላሎች ከቋሚ ግንብ ጋር በአስተማማኝ ሁኔታ መታሰር ይኖርባቸዋል፣

35.2.5 የጣሪያ ተሸካሚዎች ወይም ድጋፎች ከጣሪያው ቁልቁለማነት/ዝቅዝቃት ጋር እንዲገጥሙ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተደገፉ መሆን ይገባቸዋል፣

35.2.6 በጣሪያው ጠርዝ ዙሪያ መንበርከክ ወይም ቁጢጥ ማለት ሲያስፈልግ ሠራተኛው በደህንነት መጠበቂያ ገመድ መጠቀም ይኖርበታል፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ በመካከሉ ድጋፍ መኖር አለበት፣

35.2.7 በጣሪያ ላይ ለሚገኙ ክፍት ቦታዎች መዝጊያ ክዳኖች በሙሉ ጠንካራ ከሆነ ቁሳቁስ የተሰሩ ሆነው በትክክል መገጠም ይኖርባቸዋል፣

35.2.8 በቁልቁለታማ ጣሪያዎች ላይ ለሚከናወኑ ሥራዎች አስተማማኝ እና ተስማሚ የመንሸቀቀያ ጣውላዎች ወይም የጣሪያ መሰላሎች ተዘጋጅተው በተገቢው ቦታ እንዲቀመጡ መደረግ ይኖርበታል፣

35.2.9 ረዥም ጊዜ ለሚወስዱ የጣሪያ ሥራዎች ሠራተኛውን ከአደጋ መከላከል የሚያስችሉ ጠንካራ የሆኑ ማገጃዎች ወይም ከለላ ድጋፎች እና እግር እንዳይንሸራተት የሚከላከሉ ጣውላዎች መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣

35.2.10 አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ ጣሪያዎች ወይም ተሰባሪ ጣሪያዎች ባሏቸው ሕንፃዎች ላይ ወደ ጣሪያው መውጫ አካባቢ የማስጠንቀቂያ ጽሁፍ በግልጽ በሚታይ መልኩ እንዲኖር መደረግ ይኖርበታል፣

36. የመሬት ውስጥ ሥራዎች

36.3.1 ጠቅላላ

36.3.1.1 ማንኛውም የቁፋሮ እና የመሬት ውስጥ ሥራዎች በሚከናወኑበት ወቅት በሠራተኞች ላይ የመውደቅ፣ የአፈር መናድ፣ የውሃ ሙላት እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ አደጋዎች እንዳይደርሱ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፣

36.3.1.2 ከመሬት በታች ለሚከናወኑ የቁፋሮ ሥራዎች ብርሃን እና አየር ለማስገባት የሚስችሉ ክፍተቶች መኖራቸውን እና የአደጋ ጊዜ መውጫ መንገድ መዘጋጀቱ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

36.3.1.3 በመሬት ውስጥ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ መሥመሮች በኢትዮጵያ የሕንፃ ኮድ እና ስታንዳርድ በተቀመጡት የአሰራር ስርዓቶች መሰረት ይሆናል።

36.3.1.4 ትላልቅ የቁፋሮ እና የመሬት ውስጥ ሥራዎች ሲከናወኑ የእለት ከእለት ቁጥጥር እና ክትትል በተቆጣጣሪ መሐንዲሱ መደረግ ይኖርበታል፣

37. የቁፋሮ ሥራ

37.1 ማንኛውም የቁፋሮ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች መረጋገጥ አለባቸው፣

ሀ) የሚፈለገው የቁፋሮ ሥራ በሚገባ የታቀደ እና የአቆፋፈር ዘዴው በግልጽ ተለይቶ የተቀመጠ መሆን ይኖርበታል፣

ለ) የመሬቱ የተፈጥሮ ሁኔታ በተገቢው ባለሙያ ተመርምሮ መታወቅ ይኖርበታል፣

ሐ) የሚካሄደው የቁፋሮ ሥራ በአካባቢው ላይ የሚገኙትን ሕንፃዎች፣ መንገዶች እና ሌሎች የመሰረት ልማት አውታሮችን የማይጎዳ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣

መ) በቁፋሮ ወቅት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የውሃ መስመሮች፣ ከመሬት በታች የቆሻሻ መውረጃ መስመሮች ወይም ቱቦዎች፣ እና የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያዎች በሚመለከተው አካል ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፣

ሠ) ቁፋሮ የሚካሄድበት ቦታ በጎጂ ኬሚካሎች ወይም ጉዳት ሊያመጡ በሚችሉ አደገኛ ቁሶች ያለመበከሉ በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፣

ረ) የተቆፈሩ ጉድጓዶች ጎን በሠራተኞች ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ከከባድ ዝናብ፣ ከመሬት መንሸራተት እና ከፈንጂዎች መፈንዳት በኋላ በተገቢው ባለሙያ ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፣

ሰ) የተቆፈረውን ጉድጓድ እንዲናድ ወይም እንዲንሸራተት የሚያደርጉ ከባድ መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎች እንዲሁም የማምረቻ ተቋማት በአካባቢው መቀመጥ ወይም መተከል አይኖርባቸውም፣

ሸ) እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች የተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ እንዳይገቡ የመከለያ አጥሮች እና የማስጠንቀቂያ ማስታወቂያዎች ተዘጋጅተው መተከል ይኖርባቸዋል፣

37.2 ከሚቆፈረው ቦታ በቅርብ ርቀት እስከ ሁለት ሜትር የሚገኙ ዛፎች፣ ቋጥኞች እና ሌሎች ቁሶች የቁፋሮ ስራ ከመጀመሩ በፊት መነሳት ወይም መወገድ ይኖርባቸዋል፣

37.3 ማንኛውም ሠራተኛ ከ1 ሜትር በላይ ጥልቀት ባለው ቁፋሮ ውስጥ እንዲገባ የሚፈቀድለት፣

ሀ) የተቆፈሩ ጉድጓዶች ጎን አደጋ እስከማያስከትል ቦታ ድረስ እንዲያዘነብሉ ሲደረግ፣

ለ) በተቆፈረው ጉድጓድ ጎኖች ብረቶችን በመትከል፣ ድጋፎችን በመስራት ወይምወሽመጦችን ወይም ቦዮችን በመስራት ጥበቃ ሲደረግላቸው እና

ሐ) ሠራተኞች በሌሎች አስተማማኝ ዘዴዎች የተጠበቁ ሆነው ሲገኙ ብቻ ይሆናል፣

37.4 በሚቆፈረው ቦታ አቅራቢ የሚገኙ የሕንፃዎች መሠረቶች ሊሸረሸሩ ይችላሉ ተብሎ ሲገመት የቁፋሮው ሥራ በአጫጭር ክፍልፋዮች እንዲሰራ እና የህንፃዎቹ ግድግዳዎች በአስተማማኝ ሁኔታ መደገፍ ወይም መታሰር ይኖርባቸዋል፣

37.5 ሠራተኞች ከ1.2 ሜትር በላይ ጥልቀት ባላቸው የተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ሲገቡ በቅርብ ርቀት በሚገኙ ቦታዎች መሰላሎች እንዲኖሩ መደረግ ይኖርበታል፣ መሰላሎቹ ከተቆፈረው ጉድጓድ የታችኛው አካል ጀምሮ ከጉድጓዱ አናት በላይ ከ90 ሳ.ሜ ባላነሰ ከፍታ መዘርጋት ይኖርበታል፣

37.6 በተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ የሠራተኞችን መውደቅ ለመከላከል ጉድጓዶቹ አስተማማኝ በሆኑ ድጋፎች ወይም ማገጃዎች መከለል አለባቸው፣

37.7 በቁፋሮ ወቅት ተንቀሳቃሽ መሣሪዎችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሣሪዎቹ ከመንደርደራያዎች ላይ ተንሸራተው እንዳይወድቁ በመንደርደረያዎቹ ላይ ጠርዞች መሠራት ይኖርበታል፣

37.8 በተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ ለመግባት እና ከቁፋሮው የሚወጡ ማቴሪያሎችን

ለማስወገድ ሲፈለግ ቀጥሎ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፣

37.9 ወደ ተቆፈሩ ጉድጓዶች ለመግባት የሚያገለግሉ መረማመጃዎች፣

ሀ) ከጠንካራ ጣውላ ወይም ላሜራ ወይም ተመሣሣይ ጥንካሬ ካላቸው ቁሳቁስ የተሰሩ ሆነው ከ60 ሳ.ሜ ያላነሰ ስፋት ሊኖራቸው ይገባል፣

ለ) ከድልድል በላይ ከ1.2 ሜትር በላይ ጥልቀት ካላቸው ከለላ ወይም አጋጅ ድጋፎች መሰራት ይኖርበታል.

ሐ) ድልድሎቹ በስድስት ሜትር ቁመት ውስጥ ከአንድ የበለጡ ሆነው ሲገኙ መረማመጃዎቹ በችካሎች መጠናከር ይኖርባቸዋል፣

37.10 ማንኛውም በቁፋሮ ሥራ ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ከቁፋሮው የወጣውን ማቴሪል ከተቆፈሩ ጉድጓዶች ጠርዝ ጀምሮ በ1.2 ሜትር ርቀት ውስጥ ማከማቸት አይኖርበትም፣

37.11 ከተቆፈሩ ጉድጓዶች ውስጥ የወጡትን ማቴሪሎች ለማስወገድ ጥቅም ላይ የሚውሉ የማዘለያ እቃዎች ወይም ባልዲዎች የመደገፊያ አካላቸው እንዳይነቀሉ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፣

38. ስለ ኬሚካሎች፣ ፈንጂዎች እና መርዛማ ቁሳቁሶች

38.1 ኬሚካሎች

38.1.1 በግንባታ ቦታ ላይ በሠራተኛው ጤናና ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በየጊዜው ሊመረመሩ እና ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፣

38.1.2 በሥራ ቦታ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በተቻለ መጠን አደጋ ሊያደርሱ በማይችሉ ተለዋጭ ቁሶች እንዲተካ ማድረግ ያስፈልጋል፣

38.1.3 አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ኬሚካላዊ ቁሶች በአንድ የሥራ ቦታ የሚገኙ ከሆነ በሠራተኞች ጤንነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል የሚያስችሉ ርምጃዎች መወሰዳቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፣ የሚወሰዱት ርምጃዎች፣

ሀ) የሥራ ቦታን በተስማሚ ሁኔታ ዲዛይን ማድረግ እና ሥራው

ዙሪያውን ዝግ በሆነበት ሁኔታ እንዲሰራ ወይም እንዲከለል ማድረግ፣

ለ) ለአደጋ የሚጋለጡትን ሠራተኞች ወይም ለአደጋ የሚያጋልጠው ሥራ የሚሰራበትን ጊዜ መቀነስ፣

ሐ) የነፍስ ወከፍ የመከላከያ አልባሳትን መጠቀም

መ) ተቀጣጣይ እና አንፀባራቂ ቁሶችን እንዲሁም ለመገልገያነት የሚውሉ ኬሚካሎችን ከሥራ ቦታ አካባቢ ማራቅ የመሳሰሉትን ያካትታል፣

38.2 ስለ ፈንጂዎች

39.1 በሥራ ቦታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፈንጂዎች በሚመለከተው አካል ተቀባይነት ያለው ካልሆነ በስተቀር ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፣

39.2 ማናቸውም በግንባታ ሥራ ላይ ፈንጂ የማፈንዳት ሥራዎች መከናወን የሚችሉት በፈንጂ ተቆጣጣሪ አካላት በሚወጡ መመሪያና ስታንዳርድ ዎች እና ደንቦች መሠረት ይሆናል፣

39.3 የፈንጂ ማፈንዳት ሥራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ የፈንጂ ተቆጣጣሪ ባለሙዎች ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ ይኖርባቸዋል፣

38.3 መርዛማ (toxic) ቁሳቁሶች

በግንባታ ሥራዎች ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገር ግን ለጤና ጎጂ የሆኑትን እንደ ሲሚንቶ፣ ላይም፣ የምስጥ ማጥፊያ ኬሚካል፣ ቶክሲክ የሆኑ ቀለሞች፣ ፖሊሽ (ማፅጂያ) ማድረጊያ አሲድ፣ የሆኑትን ቁሳቁሶች አጠቃቀም እና አያያዝ ላይ በቂ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፤

39. ስለ አልባሳት

39.1 በማንኛውም በግንባታ ቦታ ላይ የተሰማራ ሠራተኛ ከዚህ በታች የተመለከቱትን የግንባታ ቦታ የአደጋ መከላከያ አልባሳት መጠቀም ይኖርበታል፡-

39.1.1 የጭንቅላት መከላከያ ቆብ፣

39.1.2 የሥራ ጫማ፣

39.1.3 የሥራ ልብስ ማድረግ ይኖርበታል፣

39.2 ማንኛውም በግንባታ ቦታ ላይ ጉብኝት የሚያደርግ ሰው የጭንቅላት መከላከያ ቆብ ማድረግ ይኖርበታል፣

39.3 ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ አሠሪ በአንቀፅ 39 ንኡስ አንቀጽ 39.1 እና 10.8.2 የተመለከተቱትን አልባሳት በሥራ ቦታው ላይ እንዲገኙ እና ሠራተኞችም የማድረግ ግዴታ አለበት፣

39.4 ማንኛውም አሠሪ በሥሩ የሚተዳደሩ ሠራተኞች በአንቀፅ 39 በንኡስ አንቀጽ 39.1 የተመለከቱትን አልባሳት በሥራ ቦታቸው ላይ መጠቀማቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፣

39.5 በማንኛውም ሥራ ቦታ ላይ ሠራተኞች ለግል ንብረቶቻቸው ማቆያ የሚያገለግል ቁም ሳጥን ለእያንዳንዱ ሠራተኛ በአሠሪው ሊዘጋጅለት ይገባል፣

40. የእሣት አደጋ ስለ መከላከል

40.1ስለ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪዎች

40.1.1 ሁሉም (አውቶማቲክ መርጫ መከላከያ መሣሪያ የተገጠመላቸውን ጨምሮ) የሥራ ቦታዎች ከጥንቃቄ ጉድለት የሚከሰቱ እሳቶችን ለመከላከል እና ለማጥፋት የሚያስችሉ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሊኖራቸው ይገባል፣

40.1.2 እነዚህ ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሙሉ ለሙሉ ተሞልተው እና አገልግሎት መስጠት በሚያስችላቸው ሁኔታ ተዘጋጅተው በተመደበላቸው ቦታ ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣

40.1.3 አገልግሎት ላይ የሚውሉ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ሥልጣን ባለው አካል ፈቃድ የተሰጣቸው መሆን ይገባቸዋል፣

40.1.4 የእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች የእሳት አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ ሊደረስባቸው በሚችሉ ግልጽ እና ከመሰናክል ነፃ በሆኑ አካባቢዎች በሚገኙ መስቀያዎች ወይም ድጋፍ ባላቸው ማስቀመጫዎች ላይ መሰቀል ወይም መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣

40.1.5 የእሳት ማጥፊያ መሣሪዎች በተመደበላቸው ቦታ መገኘታቸውን፣ በአካላቸው ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩን እና አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን ለማረጋጥ የሚያስችል ምርመራ ከአንድ ዓመት ባላነሰ ጊዜ ውስጥመሣሪያዎቹ በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ ሊደረግላቸው ይገባል፣

40.1.6 የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ የመሣሪያዎቹ ዓይነት፣ የሚሰጡት አገልግሎት እና በትክክል መጠቀም የሚያስችሉ መመሪያና ስታንዳርድ ዎች በሚታዩ እና በቀላሉ በሚነበቡበት ሁኔታ ተጽፈውመለጠፍ ይኖርባቸዋል፣

40.2 ስለ እሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች

40.2.1 በማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ሕንፃ በእሳት አደጋ ጊዜ ሠራተኞች እንዲያመልጡ የሚያስችሏቸው መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፣

40.2.2 ማንኛውም የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ በእሳት አደጋ ጊዜ ከአደጋ ነጻ ወደ ሆነው ቦታ ለመውጣትና ለማምለጥ የሚያስችሉ በእያንዳንዱ ፎቅ ላይ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ "ES 3964 FIRE PRECAUTIONS DURING BUILDING CONSTRUCTION DESIGN WORKS AND USE" መሰረት የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች ሊኖሩት ይገባል።

40.2.3 ሁሉም የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች በተገቢው መንገድ ጥበቃ የተደረገላቸው እና ማንኛውም እንቅስቃሴ ከሚገድቡ ወይም ከሚያውኩ መሰናክሎች ነፃ መሆን አለባቸው፣

40.2.4 ተንሸራታች ከሆኑ በሮች በስተቀር ሁሉም የሕንፃው በሮች ወደ ውጭ እንዲከፈቱ ሆነው መሰራት ይኖርባቸዋል፣

40.2.5 ሠራተኞችን ከሕንፃው ውስጥ ወይም ሕንፃው ከሚገኝበት ግቢ ለመውጣት የሚስችሉ በሮች በቀላሉ እንዳይከፈቱ በሚያደርጋቸው ሁኔታ መቆለፍ ወይም መታሰር የለባቸውም፣

40.2.6 በማናቸውም ክፍሎች ውስጥ የሚከማቹ እቃዎች በክፍሉ ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የእሳት አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት ለማምለጥ የሚያስችላቸው ነፃ የመተላለፊያ መንገድ እንዲኖር በሚያስችል ሁኔታ መዘጋጀት ወይም መደራጀት ይኖርባቸዋል፣

40.2.7 ማንኛውም በሕንፃ ውስጥ የሚገኝ ሠራተኛ በእሳት አደጋ ጊዜ ለማምለጥ የሚያስችለውን መንገድ እና በአደጋ ጊዜ መከተል ስለሚኖርበት ስርዓት ተገቢው ሥልጠና ማግኘት ይኖርበታል፣

40.3 ስለ ተቀጣጣይ ቁሳቁሶች

40.3.1 የተቀጣጣይነት ባህርይ ያላቸው የግንባታ ቁሳቁሶች ለእሳት በሚጋለጡ ቦታዎች መከማቸት አይኖርባቸውም፣

40.3.2 በግንባታ ሥራ ውስጥ በቀላሉ በእሳት የሚቀጣጠሉ ቁሶችን ወይም ፈሳሾችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ሀ) ተቀጣጣይ ነገሮች እንዳይቀጣጠሉ ለመከላከል የሚያስችል ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፣

ለ) ተቀጣጣይ ቁሶችን ለመሸከም፣ ለማስተላለፍ እና ለማከማቸት የሚያገለግሉ የመያዣ እቃዎች በጥንቃቄ መጠበቅ እና መታሰር ይኖርባቸዋል፣

41. ስለ የመጀመሪያ እርዳታ አሠጣጥ

41.1 በማንኛውም የሥራ ቦታ ላይ የመጀመሪያ የእርዳታ አገልግሎት መስጫ ቁሳቁስ ክፍል በአሰሪው መደራጀት ይኖርበታል፣

41.2 በሥራ ቦታ ውስጥ የመጀመሪያ የህክምና መስጫ ቦታን የሚያመለክቱ ምልክቶች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች መለጠፍ ወይም መተከል ይኖርበታል፣

41.3 በሥራ ቦታ ላይ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም ጉዳት በተመለከተ አግባብ ባለው መ/ቤት ተዘጋጅቶ በተፈቀደ ፎርም መመዝገብ ይኖርበታል፣ አሠሪውም በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት መመዝገቡን የማረጋገጥ እና የምዝገባ ዝርዝሩን ወደ ሚመለከተው

አካል የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፣

41.4 ማንኛውም አሠሪ በሥራ ቦታ ላይ በከባድ ሕመም ወይም አደጋ የተጎዳን ሠራተኛ ወደ ሕክምና ተቋም የመውሰድ ሃላፊነት አለበት፣

41.5 በግንባታ ቦታዎች ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎት የሚሠጡ የሕክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት ተቋማት አድራሻገርው መመልከት አለባቸው፣

42. ስለ አደጋ ማምለጫ መንገዶች

42.1 ማናቸውም የሥራ ቦታዎች ለሥራው እንደየሥራው አካባቢ ተገቢ የሆኑ እና ከአደጋ የተጠበቁ የመግቢያ እና የመውጪያ መንገዶች ሊኖራቸው ይገባል፣

42.2 በሥራ ቦታ የሚገኙ ሠራተኞች፣ መሣሪያዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ከአደጋ በተጠበቀ ሁኔታ ሊንቀሳቀሱ በሚችሉበት ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው፣

42.3 በአዳራሾች ወይም በሌሎች ክፍሎች የሚገኙ መተላለፊያዎች እና በየሕንፃው ውስጥ ከክፍል ወደ ክፍል ለመዘዋወሪያ ወይም ለመውጫ እና መግቢያ የሚያገለግሉ መተላለፊያዎች እንደአስፈላጊነቱ በወለል ምልክቶች እንዲለዩ መደረግ ይኖርበታል፣

42.4 ድንገተኛ አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት እና መደበኛ የመውጫ መንገዶች አደገኛ ሆነው ሲገኙ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ሲገኝ ለማምለጥ የሚያስችሉ የድንገተኛ አደጋ ማምለጫ ዘዴዎች በቅድሚያ ሊዘጋጁ ይገባል፣

42.5 የአደጋ መውጫ በሮች ወይም መንገዶች ፈጣን የመውጫ አገልግሎት እንዲሰጡ በሚያስችል ሁኔታ ሊዘጋጁ፣ ምልክት ሊደረግባቸው እና ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል፣

42.6 የአደጋ ጊዜ መውጫ በሮች መከፈት የሚኖርባቸው የበሮቹ ውዝዋዜ በሚፈልገው የቦታ ስፋት ወደ ያዙ ወለሎች እና የደረጃ ማረፊያዎች በኩል ሆኖ ወደ ሁለቱ ተቃራኒ አቅጣጫዎች የሚወዛወዙ በሮች ሲገጠሙ አሳልፎ ለማየት በሚያስችል ክፍተት መሆን ይገባቸዋል፣

43. ስለ ሠራተኞች እና የሥራ ቦታዎች ደህንነት አጠባበቅ

43.1 የሠራተኞች ደህንነት

43.1.1 የታወቀ አካላዊ ወይም አእምሯዊ ችግር ያለበት ሰው በግንባታ ሥራ ላይ እንዲመደብ መደረግ የለበትም፣

43.1.2 ማንኛውም የግንባታ አሰሪ ወይም ተቆጣጣሪ ወይም ሠራተኛ በሰዎች ጤንነት እና ደህንነት ላይ አደጋ በማያስከትል ሁኔታ አሰካሪ መጠጦች ጠጥቶ ከተገኘ ወደ ሥራ ቦታ መግባት ወይም ሥራው ወደሚገኝበት ቦት ላይ መቆየት አይፈቀድም፣

43.1.3 ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚገኝ ሠራተኛ በሠራተኞች ላይ አደጋሊያስከትል በሚችል መልኩ እንደ ግብግብ፣ አላስፈላጊ ሩጫ እና ዝላይ እንዲሁም ቀልዶችን በሰዎች ላይ መሞከር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ረብሻ ላይ መሳተፍ የለበትም፣

43.1.4 ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታው ላይ ደህንነቱን እና ጤንነቱን ለመጠበቅ የተሰጡትን መሣሪያዎች በአግባቡ መያዝ እና መጠቀም ይኖርበታል፣

43.1.5 አሠሪው የሠራተኞቹ ደህንነት እና ጤንነት ሊያስጠብቁ የሚችሉ የመከላከያ መሣሪያዎች እና ሌሎች አልባሳት እንዲያገኙ ማድረግ እና በስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ይገባዋል፣

43.2 የሥራ ቦታዎች ደህንነት

43.2.1 ማንኛውም አሠሪ የሥራ ቦታዎች በሠራተኞች ደህንነት እና ጤንነት እንዲሁም በሕብረተሰቡ እና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ማድረግ ይኖርበታል፣

43.2.2 አሠሪው በሁሉም የሥራ ቦታዎች የደህንነት መጠበቂያ ሥነ-ስርኣቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን በየጊዜው ማረጋገጥ ይኖርበታል፣

43.2.3 ማንኛውም የሥራ ቦታ ከቆሻሻ የፀዳ እና በጽዳት የሚጠበቅ መሆንይኖርበታል፣

43.2.4 ማንኛውም የሥራ ቦታ ለወንዶች እና ሴት ሠራተኞች መገልገያ የሚሆኑ እና በተለያየ ቦታ የተገነቡ ጊዜያዊ የመታጠቢያ እና የንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፣

43.2.5 ማንኛውም የሥራ ቦታ ከመንግስት ዋና ምንጭ ወይም በሚመለከተው አካል ፍቃድ ካገኘ ሌላ የተለየ ምንጭ የተገኘ በቂ እና ለጤና ተስማሚ የሆነ የመጠጥ ውሃ ሊኖረው ይገባል፣

43.2.6 በሥራ ቦታዎች የሚገኙ ለእሣት አደጋ እና ለበሽታ የሚያጋልጡ ደረቅ ቆሻሻዎች በወቅቱ መወገድ አለባቸው፣

43.2.7 በግንባታው አካባቢ ብክለት እንዳይከሰት ጊዜያዊ የፍሳሽ ማከማቻ እና ማስወገጃ መዘጋጀት አለበት፣

43.2.8 ህዝብ በሚተላለፍበት መንገድ የሚከማች የግንባታ ቁሳቁስ ከከተማው አስተዳደር ፈቃድ ካልተሠጠ በስተቀር ማከማቸት አይፈቀድም፣

43.2.9 ከሀምሣ እና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች በሚሠሩባቸው ማናቸውም የሥራ ቦታዎች የደህንነት እና የጤንነት ሁኔታዎችን የሚከታተል የደህንነት መኮንን ሊኖር ይገባል፣ የደህንነት መኮንኑ፣

ሀ) የሥራ ቦታ የደህንነት እና ጤንነት አጠባበቅ የሙያ ሥልጠና የተሰጠው ሊሆን ይገባል፣

ለ) ከሥራ ተቆጣጣሪዎች ጋር በመመካከር በአሠሪው የተቀመጡትን የደህንነት እና ጤንነት ተግባራትን ያከናውናል፤ በሰራተኞች መተግበሩንም ይቆጣጠራል፣

44. የሚደርሱ አደጋዎችን ስለ መመዝገብ እና ማሳወቅ

44.1 ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም የደረሰበትን አደገኛ ሁኔታ ለአሰሪው ወይም ለተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

44.2 በሥራ ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎች እና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች እንዲሁም አደገኛ ክስተቶች ተመዝግበው ለዚሁ ሥራ በተመደበ ሰው በአግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል፣

44.3 በሥራ ቦታ ላይ ተመዝግበው የተያዙ መረጃዎች ተጠብቀው የሚቆዩበት ጊዜ ቢያንስ ከ10 ዓመት ቢበዛ ደግሞ ከ20 ዓመት መብለጥ የለበትም፣

44.4 ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚደርስ አደጋ በ3 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ አለበት፣ ሪፖርቱ የሚከተሉትን የሚካትት ይሆናል፣

45.4.1 የአደጋውን መፈጠር እና የአደጋውን ባህሪይ ዓይነት፣

45.4.2 አደጋው የደረሰብትን ጊዜ እና ቦታ፣

45.4.3 አደጋው የደረሰበት ሠራተኛ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

44.4.4 የአሠሪው ድርጅት ሙሉ ስም እና አድረሻ፣

44.4.5 ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የህክምና እርዳት ማግኘት ያለማግኘቱን፣ ካገኘ ሕክምና ያደረገለትን ሐኪም ስምና አድራሻ፣

44.5 አደጋው የሞት አደጋን የሚስከትል ሆኖ ሲገኝ በስልክ ወይም በማናቸውም ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች አደጋው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፣

ክፍል አምስት

45. የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን

45.1 የውሃ አቅርቦት

45.1.1 ማንኛውም ህንጻ ለተገልጋዩ በቂና ንጹህ የውሃ አቅርቦት እንዲኖረው ተደርጎ መሰራት አለበት፣

45.1.2 በቂ የውሃ አቅርቦት እና ስርጭት ማለት ለእያንዳንዱ ሰው ለመጠጥ፣ ለገላ መታጠቢያ፣ ለልብስ እና መገልገያ እቃዎች ማጠቢያ፣ ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለመጸዳጃ ቤት አገልግሎት፣ለአትክልት ማጠጫ የሚበቃ ሊሆን ይገባል፣

45.1.3 ለሰዎች አገልግሎት የሚውል የማንኛውም ህንጻ የውሃ አቅርቦት እና ጥራት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስታንደርዶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፣

45.1.4 ለምድብ "ሐ" ህንጻ ተጠቃሚዎች የሚውል የተጠቃሚውን ፍጆታ ሊያሟላ የሚችል የውሃ አቅርቦትና ለመጠባበቂያ የሚውል በቂ የውሃ መከማቻ ሊኖረው ይገባል፣

45.1.5 ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሚዘጋጁ የውሃ አቅርቦት መስመሮች ዲዛይኖች እና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ቁጠባዊ የውሃ አጠቃቀምን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፣

45.1.6 የውሃ መጠራቀሚያ ገንዳዎችና የስርጭት መስመሮች ለቁጥጥርና ለጽዳት ተደራሽ ሆነው መገንባት አለባቸው፣

45.1.7 የውሃ አቅርቦት ሳኔቴሽን የግንባታ እና ስርጭት ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች እና በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን መስፈርት ሊከናወን ይገባል፣

46. የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ

46.1 አንድ ግንባታ በሚካሄድበት አቅራቢያ የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ካለ የከተማው መስተዳድር ወይም የሚመለከተው አካል በማስፈቀድ የሚገነባውን ሕንጻ የቆሻሻ መስመር ከአካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት ይችላል፣

46.2 አንድ ግንባታ በአካባቢው የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከሌለ በግቢ ውስጥ ፍሳሽን ለማስወገድ ተቀባይነት ባለውና የሚመለከታቸውን አካላት መስፈርቶች እንዲያሟላ ተደርጎ መሰራት አለበት፣

46.3 የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መሥመር በአዋሳኝ መንገድ ላይ የሚገኝ ከሆነ በአቅራቢያው ባለ ሌላ መንገድ ላይ ከሚገኝ መሥመር ጋር መገናኘት ይችላል፣

46.4 የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ፍሳሹን ወደ አፈር ውስጥ እንዳይሰርግ ወይም እንዳያሳልፍ ሆኖ መገንባት አለበት፣

47. ጎርፍ ውሀ ወይም የዝናብ ውሃ አወጋገድ

47.1 ማንኛውም ባለይዞታ በግቢው ውስጥ የሚፈጠርን የዝናብ ውሀ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጎርፍ ውሀ ማስወገጃ መስመር ማገናኘት አለበት፣

47.2 ለጎርፍ አደጋ በተጋለጡ ቦታዎች የሚከናወን ግንባታ የጎርፍ መከላከያ ያለው ሆኖ መገንባት አለበት፣

47.3 ወሰን ተጠግቶ የሚሰራ ቤት ጣራ ፍሳሽ ወደራስ ይዞታ አቅጣጫ መሆን አለበት፡፡ የጣራውን ፍሳሽ ወደ ወሰንተኛው አቅጣጫ አድርጎ ለመገንባት ማንኛውንም የጣራ ፍሳሽና ጠፈጠፍ እንዲከላከል ተደርጎ ከተሰራ 60 ሳ.ሜ ከፍታ ባለው መሸፈኛ ግድግዳው ተከልሎ መሰራት አለበት፣

47.4 የዝናብ ውሀ አወጋገድ ሥርዓት ውሃው በቀላሉ ሊወገድ በሚችልበትና ውሃ በማያቁርበት ሁኔታ እና የወሰንተኛን ነባር ግንባታ ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ መገንባት አለበት፣

47.5 የዝናብ ውሃ ማስወገጃ በአዋሳኝ መንገድ ላይ ከሚገኝ ጎርፍ ማስወገጃ መረብ ጋር መገናኘት አለበት፡፡ሆኖም ከቦታው ተፈጥሯዊ ተዳፋት አንፃር የሚዘረጉ የፍሳሽ መስመሮች በመዳረሻ መንገድ በኩል ለማውጣት የማይቻል ከሆነ ፍሳሹ ሊሄድ በሚችልበት በኩል ባለ የተጎራባች ይዞታ አሳልፎ ማገናኘት ይቻላል፡፡ ይህም ፍሳሹን ተቀብሎ ላሳለፈው ተጎራባች አመቺ በሆነ አቅጣጫ መሆን ያለበት ሲሆን ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የማይሄድ ከሆነ ስታንዳርዱን ጠብቆ በአመልካች ወይም አሳላፊው ወጪ ይገነባል፡፡ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የሚሄድ ከሆነ እያንዳንዱ ባለይዞታ የየራሱን ወጪ ይሸፍናል፣

47.6 ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተጨማሪ ግንባታዎች በማድረግ ተዳፋቱን ወደ ራስ ይዞታ በኩልበመቀየር ወይም በጥልቀት በመቆፈር መስመሩን በራስ ይዞታ ላይ መዘርጋት ካልተቻለ በተጎራባች ይዞታ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ ሆኖም በቦታው ልዩ የመሬት አቀማመጥና በአዋሳኝ ካሉት ነባር ግንባታዎች ነባራዊ ይዘት ምክንያት በተናጠል መታየት የሚኖርባቸውን ፍሳሽ መስመር ግንባታ ይዘት እና አቅጣጫ የህንፃ ሹሙ ውሳኔ ይሰጣል፣

48.6.1 ከ50 ሳ.ሜ በታች ሙሌት፣

48.6.2 ከ150 ሳ.ሜ ጥልቀት እና ከ20 ሜትር ርዝመት በታች ቁፋሮ፣

47.7 አንድ ይዞታ ብቻ አቋርጦ ለሚሄድ የዝናብ ውሃ ፍሳሽ መስመር ቢያንስ በ20 ሳ.ሜ የኮንክሪት ቱቦ ወይም ቦይ መሰራት አለበት፡፡ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ ለሚሄድ የቱቦው መጠን እንደ ርዝመቱ የሚጨምር ይሆናል፡፡ ሆኖም መስመሩ በ2% ተዳፋት፣ በ40 ሳ.ሜ ጥልቀት እና በየ25 ሜትር ርዝመት ወይንም በማንኛውም የመስመር እጥፋት ላይ የመቆጣጠሪያ ገንዳ እንዲኖረው ሆኖ መሰራት አለበት፣

47.8 በተዳፋታማ ቦታ ላይ የሚገኙ ቤቶች የዝናብ ውኃን አንዱ ከሌላው ተቀብሎ የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

47.9 በዝናብ ውሃ መስመር ሌላ ቆሻሻ ፍሳሽ መልቀቅ አይፈቀድም፣ ከዝናብ ውሃ ጋር በሚመጣ ቆሻሻ ምክንያት መስመሩን የማጽዳት ሃላፊነት የአሳላፊው ሲሆን ተቀባዩ አሳላፊውን ለዚህ ጉዳይ ወደ ግቢው እንዲገባ የመፍቀድና የመስመሩን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

48. ኢንዱስትሪ ዝቃጭ

48.1 ማንኛውንም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ በቅድሚያ ሳይታከምና ጎጂ አለመሆኑ በሚመለከተው ሳይረጋገጥ ወደ ማንኛውም ፍሳሽ ማስተላለፊያ መለቀቅ የለበትም፣

48.2 ማንኛውም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ የሚያመነጭ ተቋም ወይም ድርጅት አወጋገዱን በተመለከተ ለአካባቢ ባለሥልጣን ወይም ለሚመለከተው አካል ጥናቱን አቅርቦ ፈቀድ ማግኘት ይኖርበታል፣

48.3 የኢንዱስትሪ ዝቃጮችን ለማከምና ወደ ማንኛውም የፍሳሽ ማስወገጃ ለመልቀቅ፣ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፣

48.4 የኢንዱስትሪ ዝቃጮቹ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ መያዝና ጉጂነት ያላቸው ንጥረ ነገሮች ተጣርተው እና ታክመው መለቀቅ ይኖርበታል፣

48.5 ዝቃጭ የሚያመነጩ ተቋማት በከተማው አስተዳደርና በሚመለከተው አካል የአካባቢ ብክለትን እንዳያስከትሉ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፣

49. የውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ

49.1 ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል መመሪያና ስታንዳርድ ና ፈቃድ ውጭ ማንኛውም ሰው ውሃ አልባ ቆሻሻዎችን በየትኛውም ሥፍራና መስመር ማስወገድ ወይም እንዲወገድ ማድረግ የለበትም፤

49.2 የከተማው አስተዳደር ውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎችን የሕዝቡን ጤንነት በጠበቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፤

49.3 ኬሚካል ወይም ዝግ ቆሻሻ ማስወገጃ በሚኖርበት ጊዜ ቆሻሻውን ከእቃው ለማስወገድ በአስተዳደሩ ተቀባይነት ባለው አወጋገድ ዘዴ መከናወን ይኖርበታል፡፡

50. የእሳት ማጥፊያ ተከላ

50.1 ለምድብ ሐ ሕንፃዎች ለእሳት አደጋ መከላከል የሚረዱ መሣሪያዎች የሚተከሉበትን የሚያሳይ ንላን መቅረብና በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፣

50.2 የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች ተከላ በንላኑና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት መከናወንና በተከላ ወቅትም ከትትል ሊደረግበት ይገባል፣

50.3 የመሣሪያዎቹ ተከላ እንደተጠናቀቀ ፍተሻ መደረግና መስራታቸው በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፣

50.4 የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎቹ የጥራት ደረጃ በሚመለከተው አካል ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

50.5 በውኃ ለሚሠሩ የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች የውኃ ማከማቻ ሊኖራቸው ይገባል፣

50.6 የውኃ መስመር ደረጃውን በጠበቀ የውኃ ማስተላለፊያ ቧንቧ መዘርጋት ይኖርበታል፣

50.7 የውኃ ማጠራቀሚያ ጋኑም ሆነ መስመሮቹ ለቁጥጥር የሚያመቹ መሆን አለበት፣

51. የእሣት መከላከል የውሃ አቅርቦት

51.1 የእሣት መከላከያ የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ በቅድሚያ ለከተማው አስተዳደር በማመልከቻ መጠየቅ አለበት፣

51.2 የከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ እስኪደርስ ድረስ ለትላልቅና ለምድብ "ሐ" ህንፃዎች መጠባበቂያ የሚሆን ከተገቢው መሣሪያ ጋር የውሃ አቅርቦት ሊኖር ይገባል፣

51.3 የተቋሞች ወይም ድርጅቶች የእሣት መከላከያ መሣሪያውና የውሃው አጠቃቀም ከከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ መስፈርቶችና ሕጐች ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባዋል፣

51.4 የከተማው አስተዳዳር እሣት ለመከላል የሚቀርበውን የውሃ አቅርቦት ጥያቄእንደ ህንፃው ዓይነት፣ ከፍታው የሕንፃው ስፋት መሠረት የውሃ አቅረቦትን ሊወስን ይችላል፤

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

52. የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው ይህን መመሪያና ስታንዳርድ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

52.1 በከተማ ደረጃ የሚሰራባቸው ልዩ ልዩ መመሪዎች ያዘጋጃል፣

52.2 ለየሕንፃ ምድቦቹ የሚያገለግሉ በከተማ ደረጃ የዲዛይን እና የኮንስትራክሽን ስታንዳርዶችን፣ የዲዛይን፣ የኮንስትራክሽን እና የቁጥጥር ዘዴ፤ መመሪያና ስታንዳርድ ዎች እና የአሰራር ማንዋሎች ያዘጋጃል፣

52.3 መመሪያና ስታንዳርድ በከተማው ላይ ተከብሮ መፈጸሙን ይቆጣጠራል፣

52.2 መመሪያና ስታንዳርድ ውን ስለማሻሻል

ከዚህ መመሪያና ስታንዳርድ በፊት ሲሰራባቸው የነበሩትን ሕንጻን ብቻ የተመለከተው የቀድሞ ህንጻ መመሪያ 2/2010 እና ሰርኩላሮች ሙሉ በሙሉ ተሽሮ በዚህ መመሪያና ስታንዳርድ ተተክቷል ሆኖም ይህ መመሪያና ስታንዳርድ ከህንጻ አዋጅ 624/2001፣ ከህንጻ ደንብ 243/2003 እና ከአገሪቱ የህንጻ ኮድና ስታንዳርድ ጋር የሚጋጭ ሀሳብ ካለው አዋጁ፣ ደንቡ እና የኢትዮጵያ የህንፃ ኮድና ስታንዳርድ ገዢ ይሆናሉ፡፡

የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን መመሪያና ስታንዳርድ ያሻሽላል፡፡

52.3 መመሪያና ስታንዳርዱ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያና ስታንዳርድ ከሰኔ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት 2014 ዓ.ም

ስጦታው አካለ (ኢንጂነር)
የአዲስ አበባ ከተማ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

ቅጽ 001

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

CONSTRUCTION PERMIT & CONTROL AUTORITY

የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ

በአመልካች የሚሞላ

1. ግንባታው የሚካሄድበት አድራሻ

ከተማ ..... ክፍለ ከተማ ..... ወረዳ/ቀበሌ .....

ልዩ መጠሪያ/መንገድ ..... የቤት ቁጥር ---------- የጎሎት ቁጥር ----------

2. የግንባታ ፈቃድ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

የመሠረተ ልማት ዓይነት ☐ ሌሎች ☐

3. የግንባታ ዓይነት

አዲስ ግንባታ ☐ ማሻሻያ/ማስፋፊያ ☐ የግንባታ ፈቃድ ማራዘሚያ ☐

ግንባታው የሚካሄድበት ሁኔታ በአንድ ጊዜ ☐ ደረጃ በደረጃ ☐

ካባር ከሆነ የቀድሞው የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ ፈቃድ የወጣበት ቀን ☐

የግንባታው ጥቅል ግምትወጪ ☐ የወለል ብዛት ☐

ከመሬት በላይ ያለው ከፍታ በሜትር ☐ ከምድር በታች የወለል ብዛት ☐

ከምድር በታች ያለው ጥልቀት በሜትር ☐

የወሰን ላይ የግንባታ ይዘት ዝርዝር መግለጫ

.....

.....

.....

4. የአማካሪው ድርጅት

ሥም ☐ ደረጃ ☐ አድራሻ ☐ ስ.ቁ ☐

የዲዛይኑ ዝርዝር መግለጫ

ለግንባታ ፈቃድ የቀረበ የዲዛይን ዓይነት

የዲዛይኑ ዓይነት	ዲዛይኑን ያዘጋጀው ባለሙያ ስም	የባለሙያው የምዝገባ ቁጥር	ስልክ ቁጥር
አርክቴክቸራል			
ስትራክቸራል			
ኤሌትሪካል			
ሳኒታሪ			
ሜካኒካል			

5. እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ ኢንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የግንባታ ፈቃዱ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ።

የግንባታ ፈቃድ ጠያቂው ስም ስልክ ቁጥር

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፊርማ

ቀን

7. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

ለምርመራ የቀረበ ሠነድ (የ× ምልክት ያድርጉ)

የህንፃ ምድብ ሀ ለ ሐ

የፕላን መረጃ	ገጽ	ኤሌክትሪካል	ገጽ	የወሰን ስምምነት መረጃ	ገጽ
አርክቴክቸራል	ገጽ	ሳኒታሪ	ገጽ	የባለሙያ ማዬታ	ገጽ
ስትራክቸራል	ገጽ	ሜካኒካል	ገጽ	የሊዝ/ይዞታ ውል	ገጽ

ስታቲካል ካልኩሌሽንና

የአፈር ምርመራ /ጥራዝ ጥቅል ግምት ወጪ ሌላ/ዓይነቱ ይገለጽ

የመዳረሻ መንገድ የይዞታው ስፋት

የቀረበው ሠነድ ለግንባታ ፈቃድ የተሟላ ነው አይደለም

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁ.

ፈቃዱን መቀበያ ቀጠሮ 1 2

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ፊርማ

ቀን ሰዓት

ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
CONSTRUCTION PERMIT & CONTROL AUTORITY

ሴሪ ቁጥር.....

የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት (ለመረጃ እና ከቀሪ ፋይል ጋር የሚያያዝ)

1.የባለይዞታው ስም

የካርታ ቁጥር

2. ግንባታው የሚገኝበት

አድራሻ ክ.ከ ወረዳ/ቀበሌ ብሎክ ቁ.

ፕሎት ቁ. የቤት ቁ. የካዳስተር ቁ.

የመንገድ/ጎዳና ስም ኮርድኔት X Y

3. የህንፃዉ አገልግሎት ዝርዝር የተፈቀደ የመኖሪያ ምጣኔ በመቶኛ

4. የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ከመሬት በታች

5. የህንጻዉ ቁመት ከመሬት በላይ በሜትር ከምድር በታች ጥልቀት በሜትር

6. የግንባታው ጥቅል ግምት ወጪ ነጠላ ዋጋ

7. አረንጓዴ ቦታ ስፋት በሜ.ካ

8. የይዞታዉ ስፋት የተጣራ የይዞታዉ ስፋት ጠቅላላ የወለል ስፋት ድምር የመኪና ማቆሚያን ጨምሮ

የወለል ምጣኔ(የመኪና ማቆሚያን ሳይጨምር)

	በፊትለፊት	በስተግራ	በስተቀኝ	በስተኋላ
የመንገድ ስፋት				
ህንጻዉ ከመንገዱ ጠርዝ ያለዉ ርቀት				

9 .ፈቃድ የተሰጠበት ጥናት(መዋቅራዊ ፕላን፣ አካባቢ ፕላን ወይም ሌላ) ይጠቀስ

10. የግንባታው ዓይነት አዲስ ማሻሻያ የአገልግሎት ለውጥ የመኪና ማቆሚያ ብዛት

ግንባታው የሚካሄድበት ሁኔታ በአንድ ጊዜ ደረጃ በደረጃ

11. የግንባታ ፈቃዱ ላይ ያለኝ ውሳኔ / አስተያየት/

.....

.....

.....

12. የአማካዉ ድርጅት ስም ደረጃ

13. የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት አካል የሆኑ አባሪ ሠነዶች

አርክቴክቸራል ☐ ገጽ ስትራክቸራል ☐ ገጽ ኤሌክትሪካል ☐ ገጽ የሊዝ ውል ኮፒ ☐ ገጽ

ሳኒተሪ ☐ ገጽ መካኒካል ☐ ገጽ የኤሌክትሪካል ጥራዝ ☐ ገጽ

የባለሙያ ግዴታ ቅጽ ☐ ገጽ የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ ☐ ገጽ የሳኒተሪ ጥራዝ ☐ ገጽ

የስታቲካል ካልኩሌሽን ☐ ጥራዝ የአፈር ምርመራ ☐ ጥራዝ

የተመሳከረና የታደሰ የባለሙያዎች ፈቃድ እና ቲን ቁጥር ☐ ገጽ ኢንሹራንስ ☐ ገጽ

የሳይት ሪፖርት ☐ ገጽ

የአፈር መከላከያ ዘዴ ☐ ገጽ

14. ዕዳና ዕገዳ የወጣበት ቀን ☐ የፕላን ስምምነቱ የተሰጠበት ቀን ☐

የቀድሞ ግንባታ ፈቃድ ቁ. ☐ የተፈቀደበት ቀን ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁ. ☐ የተፈቀደበት ቀን ☐

የዚህ ፈቃድ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ☐

አርክቴክቸራል መርማሪ

ፊርማ.....

ስም.....

ቀን .....

ስትራክቸራል መርማሪ

ፊርማ.....

ስም.....

ቀን .....

ኤሌክተሪካል መርማሪ

ፊርማ.....

ስም.....

ቀን .....

ሳኒተሪ መርማሪ

ፊርማ.....

ስም.....

ቀን .....

መካኒካል መርማሪ

ፊርማ.....

ስም.....

ቀን .....

ማሳሰቢያ

- ይህ ቅጽ ያለ ዋናዉ የምስክር ወረቀት እንደ ግንባታ ፈቃድ አየገለግልም።
- በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ አንዱ ለክትትል፣ ሁለተኛዉ ከቀሪ ፋይል ጋር የሚያያዝ ሲሆን፣ ሶስተኛዉ ከመረጃ ሰነድ ጋር ለፕላን ኮሚሽን የሚላክ ይሆናል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
CONSTRUCTION
PERMIT & CONTROL AUTORITY

. ቁጥር መልቅግፈቁባ .....
Serial No.
ቀን.....

ሴሪ ቁጥር.

የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

1. የባለይዞታው ስም
2. ግንባታው የሚገኝበት አድራሻ፡ ክፍለ ከተማ ወረዳ የቤት ቁ. ስልክ ቁ
የካርታ ቁጥር
ፕሎት ቁ. የካዳስተር ቁ. የመንገድ/ጎዳና ስም
3. የግንባታው አገልግሎት ኮኦርድኔት x
Y-
4. አጠቃላይ የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ከመሬት በታች
5. የግንባታው ጥቅል ግምት ወጪ ነጠላ ዋጋ
7. የግንባታው ዓይነት
የተፈቀደ የመኪና ማቆሚያ ብዛት የተፈቀደ የመኖሪያ ምጣኔ በመቶኛ -- የወለል ምጣኔ/FAR
8. የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ/አስተያየት
.....

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለተገለፀው ግንባታ የቀረበው ሠነድ ተመርምሮ ግንባታው በህንፃ አዋጅ ፤ ደንብ እና መመሪያ መሠረት እንዲካሄድ፣

9. የግንባታ ምስክር ወረቀት አካል የሆኑ አባሪ ሠነዶች

አርክቴክቸራል ገጽ ስትራክቸራል ገጽ ኤሌክትሪካል ገጽ ሳኒተሪ ገጽ መካኒካል

የግንባታ ፈቃድ ቁ. የዚህ ፈቃድ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ

የግንባታ ፈቃዱን ያረጋገጠው ኃላፊ

ፊርማ .....
ስም .....
ቀን .....

የግንባታ ፈቃዱን ያፀደቀው ሕንፃ ሹም

ፊርማ .....
ስም .....
ቀን .....

ማሳሰቢያ

1. ይህ ቅጽ በአንድ ኦርጅናል እና በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ ‹‹ተፈቅዷል››ና ‹‹ለክትትል›› ከሚሉ ሁለት የዲዛይን ሠነድ ኮፒዎች ጋር ለግንባታው ባለቤት የሚሰጥ ሲሆን አንድ ኮፒ ከፋይል ጋር የሚያያዝ ይሆናል።አራቱም ባለሙያዎች የፈረሙበት 2 ገፅ የዲዛይን ዝርዝር ቅፅ ከቀሪ እና መረጃ ሰነዶች ጋር ተያይዟል።
2. ይህ ቅጽ በሕንፃ ሹሙ ተፈርሞ በመ/ቤቱ ማህተም ካልተረጋገጠ ዋጋ አይኖረውም።
3 በዚህ ይዞታ ላይ ከዚህ በፊት ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ በዚህ ተተክቷል።
4 የግንባታ መጀመሪያ ጊዜ በተመለከተ ለነባር ይዞታዎች ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ሲሆን ለሊዝ ይዞታዎች ደግሞ በሊዝ ውሉ ወይም በሊዝ መመሪያ መሰረት ይሆናል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
CONSTRUCTION PERMIT & CONTROL AUTORITY

የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ

1. በአመልካች የሚሞላ

ሴሪ ቁ.....
ቀን ...../...../2010ዓ.ም

1.1 ግንባታው የሚካሄድበት ይዞታ አድራሻ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡- ክፍለ ከተማ ____ ኣዲሱ ወረዳ ____

ልዩ መጠሪያ/መንገድ ____ የቤት ቁጥር ____

የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር /የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር/ ____

የይዞታ ማረጋገጫ አይነት፡- የነባር ይዞታ ☐ ሊዝ ይዞታ ☐ የተሰጠበት ቀን ____

ይዞታ ማረጋገጫ ላይ የተጠቀሰው ባለቤት ስም ____

1.2 የፕላን ስምምነቱ የተጠየቀበት ነባር የግንባታ አገልግሎት

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ አፓርታማ ☐ ማከማቻ ☐
ማምረቻ ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐ ሌሎች ____

1.3 ፕላን ስምምነቱ የተጠየቀበት የግንባታ አይነት

አዲስ ☐ ማሻሻያ/ማስፋፊያ ☐ የአገልግሎት ለውጥ ☐ ሌላ ____

1.4 የፕላን ስምምነት የተጠየቀበት ግንባታ አዲስ ከሆነ የታቀደው ግንባታ፡-

ሙሉ ለሙሉ በአንዴ የሚገነባ ☐ ደረጃ በደረጃ የሚገነባ ☐

የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ____ የወለል ብዛት ከመሬት በታች ____

1.5 የፕላን ስምምነት የተጠየቀበት ግንባታ ማሻሻያ/ማስፋፊያ/የአገልግሎት ለውጥ ከሆነ፡-

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ____ ግንባታ ፈቃድ የወጣበት ቀን ____

የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ____ የወለል ብዛት ከመሬት በታች ____

1.6 እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የፕላን ስምምነት ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ እንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የፕላን ስምምነቱ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ።

1.7 የፕላን ስምምነት ጠያቂው፡-

ባለቤት ከሆነ፣ ስም ____

በውክልና ከሆነ፣ ስም ____

ስልክ ቁጥር ____ ሞባይል ____

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ካለ ____

ፊርማ ____ ቀን ...../...../2010ዓ.ም ሰዓት ____

ማህተም

ገጽ 01/02

2. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ የፕላን መረጃ፡- ለምርመራ የቀረበ ሰነድ- ለባለጉዳይ የሚሰጥ ☐ ቀሪ ፋይል ☐

2.1 ግንባታው የሚካሄድበት ይዞታ አድራሻ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፡- ክፍለ ከተማ _____ አዲሱ ወረዳ _____

ልዩ መጠሪያ/መንገድ --- የቤት ቁጥር _____

የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር /የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር/:- _____

የይዞታ ማረጋገጫ አይነት:- የነባር ይዞታ ☐ የሊዝ ይዞታ ☐ የተሰጠበት ቀን _____

የሊዝ ይዞታ ከሆነ፡- የዲዛይን ማስገቢያ የመጨረሻው ቀን _____

የግንባታ መጀመሪያ የመጨረሻው ቀን _____

ይዞታ ማረጋገጫ ላይ የተጠቀሰው ባለቤት ስም _____

መረጃ፡- ብሎክ ቁ. _____ ፓርሴል ቁ. _____ X _____ Y _____

የካዳስተር ቁጥር ------- በሰነድ የተረጋገጠ የይዞታ ስፋት _____

2.2 የመሪ ፕላን መስፈርት መረጃ/ Master Plan/፡-

ይዞታው የሚገኝበት መደብ _____

የህንፃ ከፍታ በሜትር/Building Height/፡- አነስተኛ/Lowest/ _____ ከፍተኛው/Highest/ _____

ለይዞታው የተመደበ የመሬት አጠቃቀም _____

FAR/Flooor area ratio/፡-አነስተኛ/Lowest/ _____ ፍተኛው/Highest/ _____ መዳረሻ መንገድ፡-

ደረጃ _____ ፤ስፋት በሜትር _____ ፤የተጣራ የይዞታ ስፋት _____

የአየር ማመላለሻ ክልል ካለው፡- ክልል _____ የሚገነባበት ከፍተኛው የህንጻ ጣሪያ _____

ተጨማሪ መግለጫ _____

2.3 በይዞታው ላይ ወይም አጠገብ የተዘረጋ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት አውታር

የውሃ መስመር ☐ የፍሳሽ ማስወገጃ ☐ የኤሌክትሪክ መስመር ☐ የቴሌ መስመር ☐

ተጨማሪ መግለጫ _____

2.4 የፕላን ስምምነት መረጃ ሰጪ እና አጽዳቂ፡-

መረጃውን የሰጠው ባለሙያ ስም _____

ፊርማ _____ ቀን _____

ያፀደቀው ኃላፊ ስም _____

ፊርማ _____ ቀን _____

የፕላን መረጃ ቁ. _____

ማህተም

3. በፕላን ስምምነት ጠያቂው የሚሞላ

እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የፕላን ስምምነት ጠያቂ ከዚህ በላይ የተሰጠውን መረጃ አግባብና ህጋዊ ለሆነ አገልግሎት ለመጠቀም፤ ለፈቃድ የማቀርበውን ዲዛይን በዚህ መረጃ መሠረት በማድረግ እንዲሁም በዚህ የፕላን ስምምነት ቅጽ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የፕላን ስምምነቱን መቀበሌን አረጋግጣለሁ፡፡

የፕላን ስምምነት ጠያቂው ስም _____ ቀን _____

ፊርማ _____ ሰዓት _____ የገጽ ብዛት _____

ማሳሰቢያ. ይህ መረጃ እንደ ይዞታ ማረጋገጫነት አያገለግልም፤ የፕላን ስምምነት ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት ብቻ ያገለግላል፡፡ ለነባር ይዞታ የግንባታ መጀመሪያ ስድስት ወራት ነው፡፡ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር/ፋይል ጋር ይያያዛል፡፡

ገጽ 02/02

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
CONSTRUCTION PERMIT & CONTROL AUTORITY

የግንባታ እርከን ማሳወቂያ

1. አድራሻ

የባለቤት ሥም ____ ክ/ከ ____ ወረዳ/ቀበሌ ____

የኘሎት ቁጥር ____

የቤት ቁ. ____ የግንባታው አገልግሎት ____ የሕንፃ ምድብ ____

የግንባታ ፈቃድ ቁ. ____ የወለል ብዛት ____ ከመሬት በላይ ____ ከመሬት በታች ____

የግንባታው ጥቅል ግምት ____ ግብር ከፋይ መ.ቁ ____

የሥራ ተቋራጭ ____ ደረጃ ____ ተቆጣጣሪ ____

የምዝገባ ቁ. ____ አማካሪ ____ ዘርፍና ደረጃ ____

2. ግንባታው ያለበት ደረጃ /የሥራ እርከን

……

……..

ግንባታው ደረጃ ከመሬት በላይ……ከመሬት በታች……

3. የባለሙያው አስተያየት

……

……..

ያዘጋጀው ባለሙያ ሥም ____ ፊርማ ____

ያፀደቀው ህንጻ ሹም ሥም ____ ፊርማ ____

የፈቃድ ቁጥር ____ ቀን ____

ማሳሰቢያ

- መደበኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግንባታ ደረጃዎች 1. ግንባታ ለመጀመር ማንኛውም የቅየሳ ስራ ተጠናቆ ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት፣ 2. የመሠረት ቁፋሮ ከተጠናቀቀ እና የመሠረት ብረቶችና በቦታቸው ከተቀመጡ በኋላ፣ 3. የምድር ወለል ብረቶች የፍሳሽ ማስወገጃና የሀርድ ኮር ሙሌት ከተከናወነ በኋላ፣ 4. የወለል ቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶችና ፎርምወረክ ስራ ከተከናወነ በኋላ፣5.የየፎቁ ወለል ብረቶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የኤልክትሪክ መስመር ዝርጋታና የፎርም ወርክ ስር እንዲሁም የቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶችና ፎርምወርክ ከተከናወነ በኋላ፣6.የውሃ አቅርቦት፣የሳኒተሪ፣የኤሌክትሪክ እና ኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ተጠናቆ ፍሳሽ በሚደረግበት ጊዜ፣7.የጣሪያ ስላብ (ሶሌታ) ማጠናቀቂያ ወይም የጣሪያ ሽፋን ስራ ከመከናወኑ በፊት፣8.እንደ ስራው ዓይነት እና የአሰራር ዘዴ በህንፃ ሹሙ የሚጠየቁ ተጨማሪ እርከኖች፤
- በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ክትትል እንዲደረግ ለክትትል ክፍሉ በቅድሚያ ማሳወቅ ያስፈልጋል።
- በእያንዳንዱ ደረጃ በግንባታ ክትትል ሂደት የግንባታ ተቆጣጣሪዎች የሚሰጡት የቃል ትዕዛዝ ህጋዊነት የለውም።

የግንባታ እድሳት ፈቃድ መጠየቂያ

በአመልካች የሚሞላ

1. እድሳት የተጠየቀበት ቤት አድራሻ

ክ/ከተማ ____ ወረዳ/ቀበሌ ____ የመንገድ/ጎዳና ስም ____

የቤት ቁ. ____ የጎሎት ቁጥር ____

2. የቤቱ ባለቤት

የግል ____ የቀበሌ ____ የቤቶች ኤጀንሲ ____

የቤቱ አገልግሎት

ለመኖሪያ ____ ለቢሮ ____ ለሌላ ____

3. ለእድሳት ፈቃድ የተጠየቀ ሥራ

ግድግዳ እድሳት ____ የጣሪያ ሙሉ ልባስ እድሳት ____ የጣሪያ ልባስ ከፊል እድሳት ____

የፍሳሽ መስመር ____ የኤሌትሪክ መስመር ጥገና ____ የቀለም ቅብ ____

የቁስ ለውጥ እና እድሳት ____ የድጋፍ ግንብ ሥራ ____ የአጥር እድሳት ሥራ ____

ሌሎች ____

4. ጣሪያና ግድግዳ የሚጋሩ ወሰንተኞች አሉ ____ የሉም ____

ካሉ የወሰንተኞች ዝርዝር መግለጫ

……

……..

……

5. እድሳቱን ለማከናወን በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚፈርስ ግንባታ ካለ በዝርዝር ይጠቀስ

……

……..

……

6. **የግንባታው ባለቤት ስም** ስ.ቁ

አድራሻ ክልል ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ የቤ.ቁ.

የአመልካች ስም (ከግንባታው ባለቤት የተለየ ከሆነ) ስ.ቁ

የግንባታው ባለቤት የቤቶች ኤጀንሲ ወይም የቀበሌ ከሆነ የእድሳቱ ሥራ ስምምነት ማህተም ይደረግ

41.1.5. የእሳት ማጥፊያ መሣሪዎች በተመደበላቸው ቦታ መገኘታቸውን፣ በአካላቸው ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩን እና አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል ሁኔታ ላይ መገኘታቸውን ለማረጋጥ የሚያስችል ምርመራ ከአንድ ዓመት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ መሣሪያዎቹ በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ ሊደረግላቸው ይገባል፣

41.1.6. የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያዎች በሚቀመጡበት ወይም በሚሰቀሉበት ቦታ የመሣሪያዎቹ ዓይነት፣ የሚሰጡት አገልግሎት እና በትክክል መጠቀም የሚያስችሉ መመሪያዎች በሚታዩ እና በቀላሉ በሚነበቡበት ሁኔታ ተጽፈው መለጠፍ ይኖርባቸዋል፣

41.2. ስለ እሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች

41.2.1. ማንኛውም ሕንፃ በእሳት አደጋ ጊዜ ሠራተኞች እንዲያመልጡ የሚያስችሏቸው መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፣

41.2.2. በማንኛውም ህንፃ እያንዳንዱ ፎቅ ላይ በተለያዩ አቅጣጫዎች የተዘጋጁ ሁለት የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፣

41.2.3. ሁሉም የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች በተገቢው መንገድ ጥበቃ የተደረገላቸው እና ማንኛውም እንቅስቃሴ ከሚገድቡ ወይም ከሚያውኩ መሰናክሎች ነፃ መሆን አለባቸው፣

41.2.4. ተንሸራታች ከሆኑ በሮች በስተቀር ሁሉም የሕንፃው በሮች ወደ ውጭ እንዲከፈቱ ሆነው መሰራት ይኖርባቸዋል፣

41.2.5. ሠራተኞችን ከሕንፃው ውስጥ ወይም ሕንፃው ከሚገኝበት ግቢ ለመውጣት የሚስችሉ በሮች በቀላሉ እንዳይከፈቱ በሚያደርጋቸው ሁኔታ መቆለፍ ወይም መታሰር የለባቸውም፣

41.2.6. በማናቸውም ክፍሎች ውስጥ የሚከማቹ ዕቃዎች በክፍሉ ውስጥ የሚሰሩ ሠራተኞች የእሳት አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት ለማምለጥ የሚያስችላቸው ነፃ የመተላለፊያ መንገድ እንዲኖር በሚያስችል ሁኔታ መዘጋጀት ወይም መደራጀት ይኖርባቸዋል፣

41.2.7. ማንኛውም በሕንፃ ውስጥ የሚገኝ ሠራተኛ በእሳት አደጋ ጊዜ ለማምለጥ የሚያስችለውን መንገድ እና በአደጋ ጊዜ መከተል ስለሚኖርበት ስርዓት ተገቢው ሥልጠና ማግኘት ይኖርበታል፣

41.3. ስለ ተቀጣጣይ ቁሳቁሶች

41.3.1. የተቀጣጣይነት ባህርይ ያላቸው የግንባታ ቁሳቁሶች ለእሳት በሚጋለጡ ቦታዎች መከማቸት አይኖርባቸውም፣

41.3.2. በግንባታ ሥራ ውስጥ በቀላሉ በእሳት የሚቀጣጠሉ ቁሶችን ወይም ፈሳሾችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

ሀ) ተቀጣጣይ ነገሮች እንዳይቀጣጠሉ ለመከላከል የሚያስችል ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፣

ለ) ተቀጣጣይ ቁሶችን ለመሸከም፣ ለማስተላለፍ እና ለማከማቸት የሚያገለግሉ የመያዣ ዕቃዎች በጥንቃቄ መጠበቅ እና መታሰር ይኖርባቸዋል፣

42. ስለ የመጀመሪያ እርዳታ አሠጣጥ

42.1. በማንኛውም የሥራ ቦታ ላይ የመጀመሪያ የእርዳታ አገልግሎት መስጫ ቁሳቁስ ክፍል በአሰሪው መደራጀት ይኖርበታል፣

42.2. በሥራ ቦታ ውስጥ የመጀመሪያ የህክምና መስጫ ቦታን የሚያመለክቱ ምልክቶች በግልፅ በሚታዩ ቦታዎች መለጠፍ ወይም መተከል ይኖርበታል፣

42.3. በሥራ ቦታ ላይ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም ጉዳት በተመለከተ አግባብ ባለው መ/ቤት ተዘጋጅቶ በተፈቀደ ፎርም መመዝገብ ይኖርበታል፣ አሠሪውም በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት መመዝገቡን የማረጋገጥ እና የምዝገባ ዝርዝሩን ወደ ሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፣

42.4. ማንኛውም አሠሪ በሥራ ቦታ ላይ በከባድ ሕመም ወይም አደጋ የተጎዳን ሠራተኛ ወደ ሕክምና ተቋም የመውሰድ ሃላፊነት አለበት፣

42.5. በግንባታ ቦታዎች ለድንገተኛ አደጋ አገልግሎት የሚሠጡ የሕክምናና የአምቡላንስ አገልግሎት ተቋማት አድራሻገርው መመልከት አለባቸው፣

43. ስለ አደጋ ማምለጫ መንገዶች

43.1. ማናቸውም የሥራ ቦታዎች ለሥራው እንደየሥራው አካባቢ ተገቢ የሆኑ እና ከአደጋ የተጠበቁ የመግቢያ እና የመውጪያ መንገዶች ሊኖራቸው ይገባል፣

43.2. በሥራ ቦታ የሚገኙ ሠራተኞች፣ መሣሪያዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች ከአደጋ በተጠበቀ ሁኔታ ሊንቀሳቀሱ በሚችሉበት ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው፣

43.3. በአዳራሾች ወይም በሌሎች ክፍሎች የሚገኙ መተላለፊያዎች እና በየሕንፃው ውስጥ ከክፍል ወደ ክፍል ለመዘዋወሪያ ወይም ለመውጫ እና መግቢያ የሚያገለግሉ መተላለፊያዎች እንደአስፈላጊነቱ በወለል ምልክቶች እንዲለዩ መደረግ ይኖርበታል፣

43.4. ድንገተኛ አደጋ በሚፈጠርበት ወቅት እና መደበኛ የመውጫ መንገዶች አደገኛ ሆነው ሲገኙ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ሲገኝ ለማምለጥ የሚያስችሉ የድንገተኛ አደጋ ማምለጫ ዘዴዎች በቅድሚያ ሊዘጋጁ ይገባል፣

43.5. የአደጋ መውጫ በሮች ወይም መንገዶች ፈጣን የመውጫ አገልግሎት እንዲሰጡ በሚያስችል ሁኔታ ሊዘጋጁ፣ ምልክት ሊደረግባቸው እና ብርሃን ሊኖራቸው ይገባል፣

43.6. የአደጋ ጊዜ መውጫ በሮች መከፈት የሚኖርባቸው የበሮቹ ውዝዋዜ በሚፈልገው የቦታ ስፋት ወደ ያዙ ወለሎች እና የደረጃ ማረፊያዎች በኩል ሆኖ ወደ ሁለቱ ተቃራኒ አቅጣጫዎች የሚወዛወዙ በሮች ሲገጠሙ አሳልፎ ለማየት በሚያስችል ክፍተት መሆን ይገባቸዋል፣

44. ስለ ሠራተኞች እና የሥራ ቦታዎች ደህንነት አጠባበቅ

44.1. የሠራተኞች ደህንነት

44.1.1. የታወቀ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ችግር ያለበት ሰው በግንባታ ሥራ ላይ እንዲመደብ መደረግ የለበትም፣

44.1.2. ማንኛውም የግንባታ አሰሪ ወይም ተቆጣጣሪ ወይም ሠራተኛ በሰዎች ጤንነት እና ደህንነት ላይ አደጋ በሚያስከትል ሁኔታ አስካሪ መጠጦች ጠጥቶ ከተገኘ ወደ ሥራ ቦታ መግባት ወይም ሥራው ወደሚገኝበት ቦት ላይ መቆየት አይፈቀድም፣

44.1.3. ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚገኝ ሠራተኛ በሠራተኞች ላይ አደጋ ሊያስከትል በሚችል መልኩ እንደ ግብግብ፣ አላስፈላጊ ሩጫ እና ዝላይ እንዲሁም ቀልዶችን በሰዎች ላይ መሞከር ወይም በሌላ ተመሳሳይ ረብሻ ላይ መሳተፍ የለበትም፣

44.1.4. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታው ላይ ደህንነቱን እና ጤንነቱን ለመጠበቅ የተሰጡትን መሣሪያዎች በአግባቡ መያዝ እና መጠቀም ይኖርበታል፣

44.1.5. አሠሪው የሠራተኞቹ ደህንነት እና ጤንነት ሊያስጠብቁ የሚችሉ የመከላከያ መሣሪያዎች እና ሌሎች አልባሳት እንዲያገኙ ማድረግ እና በስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ይገባዋል፣

44.2. የሥራ ቦታዎች ደህንነት

44.2.1. ማንኛውም አሠሪ የሥራ ቦታዎች በሠራተኞች ደህንነት እና ጤንነት እንዲሁም በሕብረተሰቡ እና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ማድረግ ይኖርበታል፣

44.2.2. አሠሪው በሁሉም የሥራ ቦታዎች የደህንነት መጠበቂያ ሥነ-ስርኣቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን በየጊዜው ማረጋገጥ ይኖርበታል፣

44.2.3. ማንኛውም የሥራ ቦታ ከቆሻሻ የፀዳ እና በጽዳት የሚጠበቅ መሆን ይኖርበታል፣

44.2.4. ማንኛውም የሥራ ቦታ ለወንዶች እና ሴት ሠራተኞች መገልገያ የሚሆኑ እና በተለያየ ቦታ የተገነቡ ጊዜያዊ የመታጠቢያ እና የንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፣

44.2.5. ማንኛውም የሥራ ቦታ ከመንግስት ዋና ምንጭ ወይም በሚመለከተው አካል ፍቃድ ካገኘ ሌላ የተለየ ምንጭ የተገኘ በቂ እና ለጤና ተስማሚ የሆነ የመጠጥ ውሃ ሊኖረው ይገባል፣

44.2.6. በሥራ ቦታዎች የሚገኙ ለእሣት አደጋ እና ለበሽታ የሚያጋልጡ ደረቅ ቆሻሻዎች በወቅቱ መወገድ አለባቸው፣

44.2.7. በግንባታው አካባቢ ብክለት እንዳይከሰት ጊዜያዊ የፍሳሽ ማከማቻ እና ማስወገጃ መዘጋጀት አለበት፣

44.2.8. ህዝብ በሚተላለፍበት መንገድ የሚከማች የግንባታ ቁሳቁስ ከከተማው አስተዳደር ፈቃድ ካልተሠጠ በስተቀር ማከማቸት አይፈቀድም፣

44.2.9. ከሀምሣ እና ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች በሚሠሩባቸው ማናቸውም የሥራ ቦታዎች የደህንነት እና የጤንነት ሁኔታዎችን የሚከታተል የደህንነት መኮንን ሊኖር ይገባል፣ የደህንነት መኮንኑ፣

ሀ) የሥራ ቦታ የደህንነት እና ጤንነት አጠባበቅ የሙያ ሥልጠና የተሰጠው ሊሆን ይገባል፣

ለ) ከሥራ ተቆጣጣሪዎች ጋር በመመካከር በአሠሪው የተቀመጡትን የደህንነት እና ጤንነት ተግባራትን ያከናውናል፣ በሠራተኞች መተግበሩንም ይቆጣጠራል፣

45. የሚደርሱ አደጋዎችን ስለ መመዝገብ እና ማሳወቅ

45.1. ማንኛውም ሠራተኛ በሥራ ቦታ ላይ የደረሰበትን አደጋ ወይም የደረሰበትን አደገኛ ሁኔታ ለአሰሪው ወይም ለተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፣

45.2. በሥራ ምክንያት የሚደርሱ አደጋዎች እና በሥራ ምክንያት የሚመጡ በሽታዎች እንዲሁም አደገኛ ክስተቶች ተመዝግበው ለዚሁ ሥራ በተመደበ ሰው በአግባቡ መያዝ ይኖርባቸዋል፣

45.3. በሥራ ቦታ ላይ ተመዝግበው የተያዙ መረጃዎች ተጠብቀው የሚቆዩበት ጊዜ ቢያንስ ከ10 ዓመት ቢበዛ ደግሞ ከ20 ዓመት መብለጥ የለበትም፣

45.4. ማንኛውም በሥራ ቦታ ላይ የሚደርስ አደጋ በ3 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ አለበት፣ ሪፖርቱ የሚከተሉትን የሚካትት ይሆናል፣

45.4.1. የአደጋውን መፈጠር እና የአደጋውን ባህሪይ ዓይነት፣

45.4.2. አደጋው የደረሰብትን ጊዜ እና ቦታ፣

45.4.3. አደጋው የደረሰበት ሠራተኛ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣

45.4.4. የአሠሪው ድርጅት ሙሉ ስም እና አድረሻ፣

45.4.5. ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ የህክምና እርዳት ማግኘት ያለማግኘቱን፣ ካገኘ ሕክምና ያደረገለትን ሐኪም ስምና አድራሻ፣

45.5. አደጋው የሞት አደጋን የሚስከትል ሆኖ ሲገኝ በስልክ ወይም በማናቸውም ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች አደጋው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት መደረግ ይኖርበታል፣

አምስት
የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን

46. የውሃ አቅርቦት

46.1. ማንኛውም ህንጻ ለተገልጋዩ በቂና ንጹህ የውሃ አቅርቦት እንዲኖረው ተደርጎ መሰራት አለበት፣

46.2. በቂ የውሃ አቅርቦት እና ስርጭት ማለት ለእያንዳንዱ ሰው ለመጠጥ፣ ለገላ መታጠቢያ፣ ለልብስ እና መገልገያ እቃዎች ማጠቢያ፣ ለምግብ ማዘጋጃ፣ ለመጸዳጃ ቤት አገልግሎት፣ ለአትክልት ማጠጫ የሚበቃ ሊሆን ይገባል፣

46.3. ለሰዎች አገልግሎት የሚውል የማንኛውም ህንጻ የውሃ አቅርቦት እና ጥራት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስታንደርዶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፣

46.4. ለምድብ "ሐ" ህንጻ ተጠቃሚዎች የሚውል የተጠቃሚውን ፍጆታ ሊያሟላ የሚችል የውሃ አቅርቦትና ለመጠባበቂያ የሚውል በቂ የውሃ መከማቻ ሊኖረው ይገባል፣

46.5. ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የሚዘጋጁ የውሃ አቅርቦት መስመሮች ዲዛይኖች እና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ቁጠባዊ የውሃ አጠቃቀምን መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፣

46.6. የውሃ መጠራቀሚያ ገንዳዎችና የስርጭት መስመሮች ለቁጥጥርና ለጽዳት ተደራሽ ሆነው መገንባት አለባቸው፣

46.7. የውሃ አቅርቦት ሳኔቴሽን የግንባታ እና ስርጭት ዘዴዎች በኢትዮጵያ የህንጻ ኮድ ስታንዳርድ እና በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን መስፈርት ሊከናወን ይገባል፣

47. የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ

47.1. አንድ ግንባታ በሚካሄድበት አቅራቢያ የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ካለ የከተማው መስተዳድር ወይም የሚመለከተው አካል በማስፈቀድ የሚገነባውን ሕንጻ የቆሻሻ መስመር ከአካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት ይችላል ፣

47.2. አንድ ግንባታ በአካባቢው የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከሌለ በግቢ ውስጥ ፍሳሽን ለማስወገድ ተቀባይነት ባለውና የሚመለከታቸውን አካላት መስፈርቶች እንዲያሟላ ተደርጎ መሰራት አለበት፣

47.3. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ መሥመር በአዋሳኝ መንገድ ላይ የሚገኝ ከሆነ በአቅራቢያው ባለ ሌላ መንገድ ላይ ከሚገኝ መሥመር ጋር መገናኘት ይችላል፣

47.4. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ፍሳሹን ወደ አፈር ውስጥ እንዳይሰርግ ወይም እንዳያሳልፍ ሆኖ መገንባት አለበት፣

47.5. በአዋሳኝ መንገድ የቆሻሻ ፍሳሽ መሥመር ከሌለ ወይም የቦታ ተፈጥሮአዊ ተዳፋት የህንጻ አቀማመጥ የማይፈቅድ ከሆነ ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ ማስወገጃ ጉድጓድ /ሲስፑል/ ሴፕቲክ ታንክ የውስጥ ጉድጓድ ገጽ ከማንኛውም ወሰን 150 ሴ.ሜ. ርቆ በይዞታ ውስጥ መገንባት ይችላል፡፡ ሆኖም የታችኛውና የላይኛው ሶሌታ አርማታ እንዲሁም ግድግዳው ውሀ የማያሰርግ ሆኖ የተሰራና የመዋቅር ዲዛይኑ ከቀረበና በሚመለከተው አካል ከተፈቀደ ከወሰን አስከ 50 ሳ.ሜ ተጠግቶ መስራት ይቻላል፣

47.6. የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ገንዳ ማስተንፈሻ ቱቦ መውጫ ከወሰን በአንድ ሜትር ርቀት መተከል አለበት፣

48. የጎርፍ ውሀ ወይም የዝናብ ውሃ አወጋገድ

48.1. ማንኛውም ባለይዞታ በግቢው ውስጥ የሚፈጠርን የዝናብ ውሀ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የጎርፍ ውሀ ማስወገጃ መስመር ማገናኘት አለበት፣

48.2. ለጎርፍ አደጋ በተጋለጡ ቦታዎች የሚከናወን ግንባታ የጎርፍ መከላከያ ያለው ሆኖ መገንባት አለበት፣

48.3. ወሰን ተጠግቶ የሚሰራ ቤት ጣራ ፍሳሽ ወደራስ ይዞታ አቅጣጫ መሆን አለበት፡፡ የጣራውን ፍሳሽ ወደ ወሰንተኛው አቅጣጫ አድርጎ ለመገንባት ማንኛውንም የጣራ ፍሳሽና ጠፈጠፍ እንዲከላከል ተደርጎ ከተሰራ 60 ሳ.ሜ ከፍታ ባለው መሸፈኛ ግድግዳው ተከልሎ መሰራት አለበት፣

48.4. የዝናብ ውሀ አወጋገድ ሥርዓት ውሃው በቀላሉ ሊወገድ በሚችልበትና ውሃ በማያቁርበት ሁኔታ እና የወሰንተኛን ነባር ግንባታ ደህንነት በሚጠብቅ መልኩ መገንባት አለበት፣

48.5. የዝናብ ውሃ ማስወገጃ በአዋሳኝ መንገድ ላይ ከሚገኝ ጎርፍ ማስወገጃ መረብ ጋር መገናኘት አለበት፡፡ ሆኖም ከቦታው ተፈጥሯዊ ተዳፋት አንፃር የሚዘረጉ የፍሳሽ መስመሮች በመዳረሻ መንገድ በኩል ለማውጣት የማይቻል ከሆነ ፍሳሹ ሊሄድ በሚችልበት በኩል ባለ የተጎራባች ይዞታ አሳልፎ ማገናኘት ይቻላል፡፡ ይህም ፍሳሹን ተቀብሎ ላሳለፈው ተጎራባች አመቺ በሆነ አቅጣጫ መሆን ያለበት ሲሆን ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የማይሄድ ከሆነ ስታንዳርዱን ጠብቆ በአመልካች ወይም አሳላፊው ወጪ ይገነባል፡፡ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ የሚሄድ ከሆነ እያንዳንዱ ባለይዞታ የየራሱን ወጪ ይሸፍናል፣

48.6. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተጨማሪ ግንባታዎች በማድረግ ተዳፋቱን ወደ ራስ ይዞታ በኩል በመቀየር ወይም በጥልቀት በመቆፈር መስመሩን በራስ ይዞታ ላይ መዘርጋት ካልተቻለ በተጎራባች ይዞታ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ ሆኖም በቦታው ልዩ የመሬት አቀማመጥና በአዋሳኝ ካሉት ነባር ግንባታዎች ነባራዊ ይዘት ምክንያት በተናጠል መታየት የሚኖርባቸውን ፍሳሽ መስመር ግንባታ ይዘት እና አቅጣጫ የህንፃ ሹመ ውሳኔ ይሰጣል፣

48.6.1. ከ50 ሳ.ሜ በታች ሙሌት፣

48.6.2. ከ150 ሳ.ሜ ጥልቀት እና ከ20 ሜትር ርዝመት በታች ቁፋሮ፣

48.7. አንድ ይዞታ ብቻ አቋርጦ ለሚሄድ የዝናብ ውሃ ፍሳሽ መስመር ቢያንስ በ20 ሳ.ሜ የኮንክሪት ቱቦ ወይም ቦይ መሰራት አለበት፡፡ ከአንድ ይዞታ በላይ አቋርጦ ለሚሄድ የቱቦው መጠን እንደ ርዝመቱ የሚጨምር ይሆናል፡፡ ሆኖም መስመሩ በ2% ተዳፋት፣ በ40 ሳ.ሜ ጥልቀት እና በየ25 ሜትር ርዝመት ወይንም በማንኛውም የመስመር እጥፋት ላይ የመቆጣጠሪያ ገንዳ እንዲኖረው ሆኖ መሰራት አለበት፣

48.8. በተዳፋታማ ቦታ ላይ የሚገኙ ቤቶች የዝናብ ውኃን አንዱ ከሌላው ተቀብሎ የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

48.9. በዝናብ ውሃ መስመር ሌላ ቆሻሻ ፍሳሽ መልቀቅ አይፈቀድም፣ ከዝናብ ውሃ ጋር በሚመጣ ቆሻሻ ምክንያት መስመሩን የማጽዳት ሃላፊነት የአሳላፊው ሲሆን ተቀባዩ አሳላፊውን ለዚህ ጉዳይ ወደ ግቢው እንዲገባ የመፍቀድና የመስመሩን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

49. የኢንዱስትሪ ዝቃጭ

49.1. ማንኛውንም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ በቅድሚያ ሳይታከምና ጎጂ አለመሆኑ በሚመለከተው ሳይረጋገጥ ወደ ማንኛውም ፍሳሽ ማስተላለፊያ መለቀቅ የለበትም፣

49.2. ማንኛውም የኢንዱስትሪ ዝቃጭ የሚያመነጭ ተቋም ወይም ድርጅት አወጋገዱን በተመለከተ ለአካባቢ ባለሥልጣን ወይም ለሚመለከተው አካል ጥናቱን አቅርቦ ፈቀድ ማግኘት ይኖርበታል፣

49.3. የኢንዱስትሪ ዝቃጮችን ለማከምና ወደ ማንኛውም የፍሳሽ ማስወገጃ ለመልቀቅ፣ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ መገኘት አለበት፣

49.4. የኢንዱስትሪ ዝቃጮቹ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ መያዝና ጎጂነት ያላቸው ንጥረ ነገሮች ተጣርተው እና ታክመው መለቀቅ ይኖርበታል፣

49.5. ዝቃጭ የሚያመነጨ ተቋማት በከተማው አስተዳደርና በሚመለከተው አካል የአካባቢ ብክለትን እንዳያስከትሉ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፣

50. የውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ

50.1. ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል መመሪያና ፈቃድ ውጭ ማንኛውም ሰው ውሃ አልባ ቆሻሻዎችን በየትኛውም ሥፍራና መስመር ማስወገድ ወይም እንዲወገድ ማድረግ የለበትም፤

50.2. የከተማው አስተዳደር ውሃ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎችን የሕዝቡን ጤንነት በጠበቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይፈቅዳል፤

50.3. ኬሚካል ወይም ዝግ ቆሻሻ ማስወገጃ በሚኖርበት ጊዜ ቆሻሻውን ከዕቃው ለማስወገድ በአስተዳደሩ ተቀባይነት ባለው አወጋገድ ዘዴ መከናወን ይኖርበታል፡፡

51. የእሳት ማጥፊያ ተከላ

51.1. ለምድብ ለ እና ሐ ሕንፃዎች ለእሳት አደጋ መከላከል የሚረዱ መሣሪያዎች የሚተከሉበትን የሚያሳይ ንላን መቅረብና በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፣

51.2. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች ተከላ በንላኑና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት መከናወንና በተከላ ወቅትም ከትትል ሊደረግበት ይገባል፣

51.3. የመሣሪያዎቹ ተከላ እንደተጠናቀቀ ፍተሻ መደረግና መስራታቸው በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፣

51.4. የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎቹ የጥራት ደረጃ በሚመለከተው አካል ደረጃውን የጠበቀ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፣

51.5. በውኃ ለሚሠሩ የእሣት ማጥፊያ መሣሪያዎች የውኃ ማከማቻ ሊኖራቸው ይገባል፣

51.6. የውኃ መስመር ደረጃውን በጠበቀ የውኃ ማስተላለፊያ ቧንቧ መዘርጋት ይኖርበታል፣

51.7. የውኃ ማጠራቀሚያ ጋኑም ሆነ መስመሮቹ ለቁጥጥር የሚያመቹ መሆን አለበት፣

52. የእሣት መከላከል የውሃ አቅርቦት

52.1. የእሣት መከላከያ የውሃ አቅርቦትን በተመለከተ በቅድሚያ ለከተማው አስተዳደር በማመልከቻ መጠየቅ አለበት፣

52.2. የከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ እስኪደርስ ድረስ ለትላልቅና ለምድብ "ሐ" ህንፃዎች መጠባበቂያ የሚሆን ከተገቢው መሣሪያ ጋር የውሃ አቅርቦት ሊኖር ይገባል፣

52.3. የተቋሞች ወይም ድርጅቶች የእሣት መከላከያ መሣሪያውና የውሃው አጠቃቀም ከከተማው አስተዳደር የእሣት አደጋ መከላከያ መስፈርቶችና ሕጐች ጋር የተጣጣመ መሆን ይገባዋል፣

52.4. የከተማው አስተዳዳር እሣት ለመከላል የሚቀርበውን የውሃ አቅርቦት ጥያቄ እንደ ህንፃው ዓይነት፣ ከፍታው የሕንፃው ስፋት መሠረት የውሃ አቅረቦትን ሊወስን ይችላል፤

53. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

53.1. በአገር አቀፍ የሚሰራባቸው ልዩ ልዩ ኮዶችን ያዘጋጃል፣

53.2. ለየሕንፃ ምድቦቹ የሚያገለግሉ የዲዛይን እና የኮንስትራክሽን ስታንዳርዶችን፣ የዲዛይን፣ የኮንስትራክሽን እና የቁጥጥር ዘዴ መመሪያዎች ሞዴል ለክልሎች ያዘጋጃል፣

53.3. መመሪያው በክልሎችና በከተሞች ተከብሮ መፈጸሙን ይቆጣጠራል፣

53.4. ከሌሎች አግባብ ካላቸው የፌዴራል መንግሥቱ አካላት በጋር በመቀናጀት ክልሎችና ከተሞች መመሪያውን ለማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣

54. መመሪያውን ስለማሻሻል

54.1. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መመሪያውን ያሻሽላል።

55. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከግንቦት 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት 2003 ዓ.ም

መኩሪያ ኃይሌ
የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
ሚኒስትር

1. የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ .....ቅፅ 001
2. የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት.....ቅፅ 002
3. የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ.....ቅፅ 003
4. የግንባታ እርከን ማሳወቂያ .....ቅፅ 004
5. የግንባታ እድሳት ፈቃድ መጠየቂያ.....ቅፅ 005
6. የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ .....ቅፅ 006
7. የአገልግሎት ለውጥ መጠየቂያ ማመልከቻ ....ቅፅ 007
8. የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ.....ቅፅ 008
9. የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ .....ቅፅ 009
10. የአማካሪ ግዴታ መግቢያ .....ቅፅ 010
11. የአሠሪ ግዴታ መግቢያ.....ቅፅ 011
12. የገንቢ ግዴታ መግቢያ .....ቅፅ 012
13. የግንባታ መከታተያ ቅጽ.....ቅፅ 013
14. የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ .....ቅፅ 014
15. የግንባታ ማስቆሚያ .....ቅፅ 015
16. የግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ .....ቅፅ 016
17. የግንባታ ሥራ ለውጥ ተጨማሪ ማሳወቂያ.....ቅፅ 017
18. የግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ መጠየቂያ.....ቅፅ 018
19. የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ.....ቅፅ 019
20. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ.....ቅፅ 020
21. የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ /ደንብ ማስከበር/.....ቅፅ 021
22. የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ.....ቅፅ 022
23. የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ.....ቅፅ 023
24. ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቂያ .....ቅፅ 024
25. የግንባታ ሥራ እርከን ማሳወቂያ.....ቅፅ 025
26. አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ መጠየቂያ .....ቅፅ 026
27. ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ .....ቅፅ 027
28. የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት .....ቅፅ 028
29. የምሽት መገንቢያ ፍቃድ.....ቅፅ 029

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 001

አርማ

የ ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ

በአመልካች የሚሞላ

1. ግንባታው የሚካሄድበት አድራሻ

ከተማ ..... ክፍለ ከተማ ..... ወረዳ/ቀበሌ .....

ልዩ መጠሪያ/መንገድ ..... የቤት ቁጥር ---------- የኘሎት ቁጥር ----------

2. የግንባታ ፈቃድ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

የመሠረተ ልማት ዓይነት ☐ ሌሎች ☐

3. የግንባታ ዓይነት

አዲስ ግንባታ ☐ ማሻሻያ/ማስፋፊያ ☐ የግንባታ ፈቃድ ማራዘሚያ ☐

ነባር ከሆነ የቀድሞው የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ ፈቃድ የወጣበት ቀን ☐

የግንባታው ወጪ ☐ የወለል ብዛት ☐

ከመሬት በላይ ያለው ከፍታ በሜትር ☐ ከምድር በታች የወለል ብዛት ☐

ከምድር በታች ያለው ጥልቀት በሜትር ☐

የወሰን ላይ የግንባታ ይዘት ዝርዝር መግለጫ

……

……..

……

……..

4. የአማካሪው ድርጅት

ሥም ደረጃ አድራሻ ስ.ቁ

የዲዛይኑ ዝርዝር መግለጫ

ለግንባታ ፈቃድ የቀረበ የዲዛይን ዓይነት

የዲዛይኑ ዓይነት	**ዲዛይኑን ያዘጋጀው ባለሙያ ስም**	**የባለሙያው የምዝገባ ቁጥር**	**ስልክ ቁጥር**
አርክቴክቸራል			
ስትራክቸራል			
ኤሌትሪካል			
ሳኒታሪ			
ሜካኒካል			

5. እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ ኢንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የግንባታ ፈቃዱ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ።

የግንባታ ፈቃድ ጠያቂው ስም ስልክ ቁጥር

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፊርማ

ቀን

7. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

ለምርመራ የቀረበ ሠነድ (የ× ምልክት ያድርጉ)

የህንፃ ምድብ ሀ ለ ሐ

የፕላን መረጃ ☐ ገጽ ኤሌትሪካል ☐ ገጽ የወሰን ስምምነት መረጃ ☐ ገጽ

አርክቴክቸራል ☐ ገጽ ሳኒታሪ ☐ ገጽ የባለሙያ ማዬታ ☐ ገጽ

ስትራክቸራል ☐ ገጽ ሜካኒካል ☐ ገጽ የሊዝ/ይዞታ ውል ☐ ገጽ

ስታቲካል ካልኩሌሽንና
የአፈር ምርመራ /ጥራዝ/ ☐ ጥቅል ግምት ☐ ሌላ/ዓይነቱ ይገለጽ ☐

የመዳረሻ መንገድ ☐ የይዞታው ስፋት ☐

የቀረበው ሠነድ ለግንባታ ፈቃድ የተሟላ ነው ☐ አይደለም ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁ. ☐

ፈቃዱን መቀበያ ቀጠሮ 1 ☐ 2 ☐

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ☐ ፊርማ ☐

ቀን ☐ ሰዓት ☐

ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል፡

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 002

አርማ

የ ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

1. የባለይዞታው ስም ____ የካርታ ቁ. ____

አድራሻ ክ.ከ ____ ወረዳ/ቀበሌ ____ ስልክ ቁ. ____

የግብር ከፋይ መለያ ቁ. ____

2. ግንባታው የሚገኝበት

አድራሻ ክ.ከ ____ ወረዳ/ቀበሌ ____ ብሎክ ቁ. ____

ፕሎት ቁ. ____ የቤት ቁ. ____ የካዳስተር ቁ. ____

የመንገድ/ጎዳና ስም ____

3. የግንባታው አገልግሎት ____

4. የወለል ብዛት ____ ከመሬት በላይ ____ ከመሬት በታች ____

5. የግንባታው ወጪ ____

6. የተሰጠበት ቀን ____

7. የግንባታው ዓይነት አዲስ ____ ማሻሻያ ____ የአገልግሎት ለውጥ ____

8. የግንባታ ፈቃድ ውሳኔ

.....

.....

.....

.....

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለተገለፀው ግንባታ የቀረበው ሠነድ ተመርምሮ ግንባታው እንዲካሄድ

ተፈቅዷል ☐ አልተፈቀደም ☐

9. ያልተፈቀደበት ምክንያት

……

……..

……

10. የግንባታ ምስክር ወረቀት አካል የሆኑ አባሪ ሠነዶች

አርክቴክቸራል ☐ገጽ ስትራክቸራል ☐ገጽ ኤሌክትሪካል ☐ገጽ ሳኒታሪ ☐ገጽ

መካኒካል ☐ገጽ የባለሙያ ግዴታ ቅጽ ☐ገጽ የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ ☐ገጽ

የቀድሞ ግንባታ ፈቃድ ቁ. (ነባር ግንባታ ከሆነ) ☐ የዚህ ፈቃድ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁ. ☐ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን ☐

የግንባታ ፈቃድ መርማሪ ባለሙያ	የግንባታ ፈቃዱን ያፀደቀው ሃላፊ
ስም ……	ስም ……
ፊርማ ……..	ፊርማ ……
ቀን ……	ቀን ……

ማሳሰቢያ

1. ይህ ቅጽ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ ‹‹ተፈቅዷል›› እና ‹‹ለክትትል›› ከሚሉ ሁለት የዲዛይን ሠነድ ኮፒዎች ጋር ለግንባታው ባለቤት የሚሰጥ ሲሆን አንድ ኮፒ ከፋይል ጋር የሚያያዝ ይሆናል፡፡
2. ይህ ቅጽ በሃላፊ ተፈርሞ በመ/ቤቱ ማህተም ካልተረጋገጠ ዋጋ አይኖረውም፡፡
3 በዚህ ይዞታ ላይ ከዚህ በፊት ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ በዚህ ተተክቷል፡፡

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 003

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የፕላን ስምምነት መጠየቂያ ማመልከቻ

በአመልካች የሚሞላ

1. **ግንባታው የሚካሄድበት አድራሻ**

ከተማ ..... ክፍለ ከተማ ---------- ወረዳ/ቀበሌ .....

ልዩ መጠሪያ/መንገድ ..... የቤት ቁጥር ..... ኘሎት ቁጥር ----------

2. **የፕላን ስምምነቱ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት**

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

ሌሎች ☐

የህንፃው ከፍታ ከመሬት በላይ በሜትር ☐ ከመሬት በታች በሜትር ☐

የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ☐ ከመሬት በታች ☐

3. **የፕላን ስምምነት የተጠየቀበት የግንባታ ዓይነት**

አዲስ ግንባታ ☐ ማሻሻያ/ማስፋፊያ ☐ የአገልግሎት ለውጥ ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ የግንባታ ፈቃድ የወጣበት ቀን ☐ የግንባታው ወጪ ☐

4. **የፕላን ስምምነት የተጠየቀበት ግንባታ አዲስ ከሆነ**

ሙሉ ለሙሉ በአንደኛ የሚገነባ ☐ ደረጃ በደረጃ የሚገነባ ☐

የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ ቁጥር ☐

5. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

ለምርመራ የቀረበ ሠነድ

የግንባታው አድራሻ

መረጃ ብሎክ ቁ. ☐ **ፓርሴል ቁ.** ☐ **X** ☐ **Y** ☐

የመሪ ፕላን መስፈርት መረጃ ☐

ይዞታው የሚገኝበት መደብ ☐

ለይዞታው የተመደበ የመሬት አጠቃቀም ☐ **ማህበራዊና ማዘጋጃ ቤታዊ** ☐ **ቅይጥ** ☐

አረንህዴ ለባሽ ☐ **ማዕከል** ☐ **ማምረቻና ማከማቻ** ☐ **መናሃሪያ** ☐ **ለመጠባበቂያ** ☐

ሌላ ☐ **የህንፃ ከፍታ** ☐ **አነስተኛው** G+

ከፍተኛው G+ **ጣሪያ ከፍታው በሜትር** ☐ **የግንባታው ይዘት ንፅፅር** %

የመዳረሻ መንገድ ደረጃ ☐

በይዞታው ላይ ወይም አጠገብ የተዘረጋ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት አውታር መረጃ

የውሃ መስመር ☐ **የፍሳሽ ማስወገጃ** ☐ **የኤሌክትሪክ መስመር** ☐ **የቴሌ መስመር** ☐

ተጨማሪ መግለጫ ☐

የፕላን መረጃ ቁ. ☐ **ቀን** ☐

መረጃውን የሰጠው ባለሙያ ስም ☐ **ፊርማ** ☐

ያፀደቀው `ላፊ

ስም ☐ **ፊርማ** ☐

6. **እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የፕላን ስምምነት ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ ኢንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የፕላን ስምምነቱ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ።**

የፕላን ስምምነት ጠያቂው ስም ☐ **ስልክ ቁጥር** ☐

ሞባይል ☐ **የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ካለ** ☐

ፊርማ ☐

<u>ማሳሰቢያ</u>.ይህ መረጃ እንደይዞታ ማረጋገጫነት አያገለግልም 2. ለፍቃድ የሚቀርብ ዲዛይን በዚህ መረጃ መሠረት መሆን አለበት 3. ይህን መረጃ አግባብና ህጋዊ ለሆነ አገልግሎት የመጠቀም ሃላፊነት የፕላን መረጃ ጠያቂው ነው ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል፡

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 004

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ እርከን ማሳወቂያ

1. አድራሻ

የባለቤት ሥም ክ/ከ ወረዳ/ቀበሌ

የኘሎት ቁጥር

የቤት ቁ. የግንባታው አገልግሎት የሕንፃ ምድብ

የግንባታ ፈቃድ ቁ. የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ከመሬት በታች

የግንባታው ጥቅል ግምት ግብር ከፋይ መ.ቁ

የሥራ ተቋራጭ ደረጃ ተቆጣጣሪ

የምዝገባ ቁ. አማካሪ ዘርፍና ደረጃ

2. ግንባታው ያለበት ደረጃ /የሥራ እርከን

.....

.....

ግንባታው ደረጃ ከመሬት በላይ.....ከመሬት በታች.....

3. የኃላፊው አስተያየት

.....

.....

ያዘጋጀው ባለሙያ ሥም ፊርማ

ያጠደቀ ኃላፊ ሥም ፊርማ

የፈቃድ ቁጥር ቀን

ማሳሰቢያ

- መደበኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግንባታ ደረጃዎች 1. ግንባታ ለመጀመር ማንኛውም ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት፣ 2. የመሠረት ቁፋሮ ከተጠናቀቀ እና የመሠረት ብረቶችና ፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች በቦታቸው ከተቀመጡ በኋላ፣ 3. የምድር ወለል ከተጠናቀቀና የምድር ወለል ቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረት በቦታው ከተቀመጠ በኋላ፣ 4. የጣሪያ ሶሌታ ማጠናቀቂያ ወይም የጣሪያ ሽፋን ሥራ ከመከናወኑ በፊት ናቸው።
- በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ክትትል እንዲደረግ ለክትትል ክፍሉ በቅድሚያ ማሳወቅ ያስፈልጋል።
- በእያንዳንዱ ደረጃ በግንባታ ክትትል ሂደት የግንባታ ተቆጣጣሪዎች የሚሰጡት የቃል ትዕዛዝ ህጋዊነት የለውም።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 005

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ እድሳት ፈቃድ መጠየቂያ

በአመልካች የሚሞላ

1. እድሳት የተጠየቀበት ቤት አድራሻ

ክ/ከተማ | ወረዳ/ቀበሌ | የመንገድ/ጎዳና ስም

የቤት ቁ. | የኘሎት ቁጥር

2. የቤቱ ባለቤት

የግል | የቀበሌ | የቤቶች ኤጀንሲ

የቤቱ አገልግሎት

ለመኖሪያ | ለቢሮ | ለሌላ

3. ለእድሳት ፈቃድ የተጠየቀ ሥራ

ግድግዳ እድሳት | የጣሪያ ሙሉ ልባስ እድሳት | የጣሪያ ልባስ ከፊል እድሳት

የፍሳሽ መስመር | የኤሌትሪክ መስነር ጥገና | የቀለም ቅብ

የቁስ ለውጥ እና እድሳት | የድጋፍ ግንብ ሥራ | የአጥር እድሳት ሥራ

4. ጣሪያና ግድግዳ የሚጋሩ ወሰንተኞች አሉ | የሉም

ካሉ የወሰንተኞች ዝርዝር መግለጫ

……

……..

……

……..

5. እድሳቱን ለማከናወን በከፊልም ሆነ በሙሉ የሚፈርስ ግንባታ ካለ በዝርዝር ይጠቀስ

……

……..

……

……..

6. የግንባታው ባለቤት ስም ስ.ቁ

አድራሻ ክልል ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ የቤ.ቁ.

የአመልካች ስም (ከግንባታው ባለቤት የተለየ ከሆነ) ስ.ቁ

የግንባታው ባለቤት የቤቶች ኤጀንሲ ወይም የቀበሌ ከሆነ የእድሳቱ ሥራ ስምምነት ማህተም ይደረግ

7. እኔ የግንባታ ዕድሳት ፈቃድ ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን አገናዝቤ እና አንብቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ ተክክለኛ ያለሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ እና በዚህ ቅጽ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውንም የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የዕድሳት ፈቃድ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ።

ፊርማ ቀን ሰዓት

8. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

ቀጠሮ ቀን ዓ.ም.

መረጃ የተቀበለው ሰው ስም

ፊርማ ቀን ዓ.ም

የግንባታ ፈቃድ ቁ. [ ] የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁ. [ ]

የቤት ይዞታ ደብተር ቁ. [ ]

እድሳት የተጠየቁ ስራዎች ዝርዝር ……..
……..
……..
አባሪ ሰነድ ዝርዝር ……..
……..

ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለፀው የግንባታ እድሳት ሥራ ጥያቄ አባሪ ሆኖ በተያያዘው ……. ገጽ የእድሳት ንድፍ መሠረት እድሳቱ እንዲካሄድ

ተፈቅዷል [ ] አልተፈቀደም [ ]

9. ያልተፈቀደበት ምክንያት

……
……
……
……
……

10. የግንባታ ማሳወቂያ

የተላከላቸው ወሰንተኞች [ ] [ ] [ ]

የማፍረሻ ፈቃድ ቁ/ካለ [ ] የፅድሳት ፈቃድ ቁ. [ ]

የፈቃድ ሰጪው ባለሙያ ሥም [ ] የፈቃዱ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ [ ]

ፊርማ [ ] ቀን [ ] ሰዓት [ ]

<u>ማሳሰቢያ</u>

ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል፡፡

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 006

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ

በአመልካች የሚሞላ

1. ግንባታው የሚገኝበት አድራሻ

ከተማ ..... ክፍለ ከተማ ..... ወረዳ/ቀበሌ .....

ልዩ መጠሪያ/መንገድ ..... የቤት ቁጥር ..... ኘሎት ቁጥር ----------

2. የማፍረሻ ፈቃድ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

ሌሎች ☐

3. የማፍረሻ ፈቃድ የተጠየቀበት ግንባታ ይዞታ

የግል ይዞታ ☐ የመንግስት ይዞታ ☐ የድርጅት ይዞታ ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ ቁጥር ☐

የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁጥር ☐

4. ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑ ማስረጃ ከ .....ቀርቧል።

5. የማፍረሻ ፈቃድ የተጠየቀበት ግንባታ የወሰን ላይ ይዞታ ዝርዝር መግለጫ

……

……..

……

……..

6. የህንፃ ምድብ ሀ ☐ ለ ☐ ሐ ☐

7. የሚፈርሰው ቤት የወለል ከፍታ በሜትር ከመሬት በላይ ☐ ከመሬትበታች ☐

የወለል ስፋት በካ.ሜ ☐ ቤቱ የሚፈርሰው ሙሉ በሙሉ ☐ በከፊል ☐

የሚፈርሰው ቤት የተሠራበት ቁሳቁስ

ግድግዳው ☐ ጣሪያው ☐ ወለሉ ☐

8. የተዘረጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች

መብራት ☐ ውሃ ☐ ፍሳሽ ☐ ስልክ ☐ ሌሎች ☐

9. ግንባታው ማፍረስ ያስፈለገበት ምክንያት

……

……..

10. ጣራና ግድግዳ የሚጋሩ ወሰንተኞች አሉ ☐ የሉም ☐

ካሉ የወሰንተኛ ስም 1	☐	☐	☐
የሚዋሰኑበት አቅጣጫ1	☐	☐	☐

11. የተያያዘ የሚፈርሰው ግንባታ መረጃ

የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ ☐ ከእዳና እገዳ ነፃ መሆኑ ማስረጃ ☐ ፕላኖች አርክቴክቸራል ኮፒ ☐

ስትራክቸራል ኮፒ ☐ ኤሌትሪካል ኮፒ ☐ ሳኒታሪ ኮፒ ☐ ሌሎች ኮፒ ☐

12. እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ። ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ ኢንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የፕላን ስምምነቱ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ።

የአመልካች ስም ☐ ስልክ ቁጥር ☐

ሞባይል ☐ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ካለ ☐

የተያያዘ አባሪ ☐ ገፅ ፊርማ ☐

13. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

ቀጠሮ ☐ መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ☐

ፊርማ ☐ ቀን ☐ ሰዓት ☐

ለምርመራ የቀረበ ሠነድ

የሕንፃ ምድብ ሀ ☐ ለ ☐ ሐ ☐

የፕላን መረጃ ☐ ገጽ ኤሌትሪካል ☐ ገጽ የወሰን ስምምነት መረጃ ☐ ገጽ

አርክቴክቸራል ☐ ገጽ ሳኒታሪ ☐ ገጽ የባለሙያ ማዬታ ☐ ገጽ

ስትራክቸራል ☐ ገጽ ሜካኒካል ☐ ገጽ የሊዝ/ይዞታ ውል ☐ ገጽ

የመዳረሻ መንገድ ☐ የሚፈርሰው ግንባታ ይዞታ ስፋት ☐

የቀረበው ሠነድ ለማፍረሻ ፈቃድ የተሟላ ነው ☐ አይደለም ☐

የግንባታ ማፍረሻ ፈቃድ ቁጥር ☐ የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁጥር ☐

ፈቃድ መቀበያ ቀጠሮ 1 ☐ 2 ☐

የማፍረሻ ፈቃዱ ተፈቅዷል ☐ አልተፈቀደም ☐

የግንባታው ባለቤት ስም ☐ ስ.ቁ. ☐ ሞባይል ☐

የአመልካች ስም ግንባታው ባለቤት የተለየ ከሆነ ☐ ስ.ቁ. ☐ ሞባይል ☐

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ☐ ፊርማ ☐

ቀን ☐ ሰዓት ☐

መስመር መቋረጫ ፈቃድ ይያያዝ / ቅጅው ይያያዝ/

መብራት ☐ ውሃ ☐ ፍሳሽ ☐ ስልክ ☐

ከዘህ በላይ በዝርዝር የተገለፀውና አባሪ ሆኖ በተያያዘው .....ገፅ ንድፍ ለይ የተመለከተው ግንባታ እንዲፈርስ ☐

የግንባታው መፍረስ ማስታወቂያ የተላከላቸው ወሰንተኞች 1.

2. 3. 4.

ከተቋራጭ ጋር የተገባ የግንባታ ማፍረሻ ውል ደብደቤ ቁ. የማፍረሻ ፈቃድ ቁ.

ከእዳና እገዳ ማረጋገጫ ቁ. ቀን የፈቃድ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ

የፈቃድ ሰጪው ስም ፊርማ ቀን

የማፍረስ ስራው በፈቃዱ መሰረት ተጠናቋል ያረጋገጠው ባለሙያ

ፊርማ

ቀን

ማሳሰቢያ፣ **ይህ ቅጽ በ3 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለግንባታው ባለቤት 1ኮፒ ለፈቃድ ክፍል 1 ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል።ከግንባታ ማፍረስ በኋላ በ3ቀን ውስጥ ለማረጋገጫ ቁጥጥር ተግባር ፈቃዱን ለሰጠው ጽ/ቤት ባለቤቱ ቀርበው ማሳወቅ አለባቸው።**

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 007

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የአገልግሎት ለውጥ መጠየቂያ ማመልከቻ

በአመልካች የሚሞላ

1. **ግንባታው የሚገኝበት አድራሻ** ከተማ ..... ክፍለ ከተማ .....
   ቀበሌ/ወረዳ ..... ልዩ መጠሪያ/መንገድ ..... የቤት ቁጥር .....
   የኘሎተር ቁጥር ----------

2. **የአገልግሎት ለውጥ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት**

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

ሌሎች ☐

3. **የአገልግሎት ለውጥ የተጠየቀበት ግንባታ ይዞታ**

የግል ☐ የመንግስት ☐ የድርጅት ☐ ሌላ ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ የአገልግሎት ፈቃድ ቁ. ☐

የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ ቁጥር ☐

የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁጥር ☐

4. **የተጠየቀው የአገልግሎት ለውጥ ዓይነት** ☐

5. **የአገልግሎት ለውጥ ያስፈለገበት ምክንያት**

……

……..

……

……

6. የህንፃው የወለል ስፋት ☐ከመሬት በላይ ከፍታው በሜትር ☐መሬት በታች ጥልቀቱ በሜትር ☐

7. **ለአገልግሎት ለውጥ የተጠየቀበት መሻሻያ ፕላን ያዘጋጀው ባለሙያ/አማካሪ**

ሙሉ ስም ☐ **ደረጃ** ☐ **አድራሻ** ☐

ስ.ቁ. ☐

ለአገልግሎት ለውጥ የተዘጋጁ ዲዛይኖች ዓይነት

የዲዛይኑ ዓይነት	ዲዛይኑን ያዘጋጀው ባለሙያ ስም	የባለሙያው የምዝገባ ቁጥር	ስልክ ቁጥር
አርክቴክቸራል			
ስትራክቸራል			
ኤሌትሪካል			
ሳኒታሪ			
ሜካኒካል			

8. እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የአገልግሎት ለውጥ ጠያቂ ከዚህ በላይ የተመለከተውን መረጃ አንብቤና አገናዝቤ የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ ኢንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የፕላን ስምምነት እና የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የአገልግሎት ለውጥ ፈቃድ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ፡፡

የግንባታው ባለቤት ስም ☐ ስልክ ቁጥር ☐

የአመልካች ስም ግንባታው ባለቤትየተለየ ከሆነ ☐ ስልክ ቁጥር ☐

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ካለ ☐ ፊርማ ☐

9. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

የአገልግሎት ለውጥ የተጠየቀበት ህንፃ ምድብ ሀ ☐ ለ ☐ ሐ ☐

ቀጠሮ ☐

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ☐ ፊርማ ☐

ቀን ☐ ሰዓት ☐

የአገልግሎት ለውጥ የተጠየቀበት ህንፃ ከወሰን ያለው ርቀት

ወሰን ላይ የተሰራ ነው ☐ ከወሰን ከሁለት ሜትር በታች የተሰራ ነው ☐

ከወሰን በ3 ሜትር ክልል የተሰራ ነው ☐

የቀረበው ሠነድ ለአገልግሎት ለውጥ የተሟላ ነው ☐ አይደለም ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ የአገልግሎት ክፍያ ብር ☐

ስምምነቱን መቀበያ ቀጠሮ 1 ☐ 2 ☐

የአገልግሎት ለውጡ ተፈቅዷል ☐ አልተፈቀደም ☐

10. ያልተፈቀደበት ምክንያት

……

……..

……

……..

የፈቀደው/ያልፈቀደው ሃላፊ ስም ☐ ፊርማ ☐

ቀን ☐ ሰዓት ☐ የፕላን ስምምነት ቁጥር ☐

ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል፡

ሴሪ ቁጥር --------
ቅጽ 008

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ

በአመልካች የሚሞላ

1. አዳራሽ

የአመልካች ሥም ክ/ከ ቀበሌ/ወረዳ

የቤት ቁ. የግንባታ ፈቃድ ቁ.

የግንባታው አገልግሎት የኘሎት ቁጥር

2. የግንባታው ዓይነት

አዲስ ግንባታ ነባር ግንባታ ማሻሻያ ነባር ግንባታ ማስፋፋት

ግንባታ እድሳት ግንባታ ማፍረስ የመዳረሻ መንገድ ስፋት

ከመሬትበላይ ከፍታ በሜትር ከመሬት በታች ጥልቀት በሜትር

የአዋሳኝ ግንባታ ባለቤት

የግል የቀበሌ የቤቶች ኤጀንሲ

3. የወሰን ላይ ግንባታ ይዘት ማጠቃለያ እና የወሰንተኛ ስምምነት መግለጫ

በአመልካች የሚሞላ							
አዋሳኝ	አቅጣጫ	ሊሠራ የታቀደ የወሰን ላይ ግንባታ ዓይነት	የወሰንተኛ ሥም	የወሰንተኛ ነባር ግንባታ ወለል ብዛት	ነባር ግንባታው ከወሰን ያለው ርቀት በሜትር	አዲስ ግንባታው ከወሰን ያለው ርቀት በሜትር	
1	በስተግራ						
2	በስተቀኝ						
3							
4							
5							

4. የአመልካች የግዴታ መግለጫ

በሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2003 የሕንፃ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብና መመሪያ ..... መሠረት ከላይ ከተጠቀሰው ግንባታ አቅጣጫ ያሉና የሚመለከታቸው ወሰንተኞችን ንብረት የቅርብ ክትትል የሚጠይቅ መሆኑን በማወቅ ስለወሰንና ወሰንተኞች ትክክለኛ መረጃ መስጠቱንና በዚህ የግዴታ ቅጽ እና በግንባታ ፈቃዱ መሠረት የተጎራባችን ነባር ግንባታ ደህንነት በቁፋሮና በግንባታ ሂደት ለመጠበቅና ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ ግዴታ መግባቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

አመልካች | ፊርማ

ስ.ቁ | ቀን

5. የሥራ ክፍሉ ማረጋገጫ

ወሰንና ወሰንተኞችን አስመልክቶ አመልካች በሰጡት መረጃ መነሻነት እና በሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2003 የሕንፃ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብና መመሪያ መሠረት የቀረበው የግዴታ ዲዛይን በወሰንተኛ ነባር ግንባታ ደህንነት አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ተገቢው ጥንቃቄ በአመልካች እንዲወሰድ በግንባታ ፈቃድ አሠጣጥ ላይ አስፈላጊው እርምጃ የተወሰደ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

መርማሪ ባለሙያ | ፊርማ

ቀን

ማሳሰቢያ ፣ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል፡

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 009

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የወሰን ላይ ግንባታ ማሳወቂያ

በአመልካች የሚሞላ

1. አድራሻ

የአመልካች ሥም ክ/ከ ወረዳ/ቀበሌ

የቤት ቁ. የግንባታ ፈቃድ ቁ.

የግንባታው አገልግሎት የኘሎት ቁጥር

2. የግንባታው ዓይነት

አዲስ ነባር ግንባታ ማሻሻያ ነባር ግንባታ ማስፋፋት

ግንባታ እድሳት ግንባታ ማፍረስ የመዳረሻ መንገድ ስፋት

ከመሬትበላይ ከፍታ በሜትር ከመሬት በታች ጥልቀት በሜትር

አጠቃላይ የወለል ብዛት የምድር በታች የወለል ስፋት

የአዋሳኝ ግንባታ ባለቤት

የግል የቀበሌ የቤቶች ኤጀንሲ

3. የአዋሳኝን ቅድሚያ ስምምነት ሳይጠየቅበት ግዴታ በመግባት የሚካሄድ የወሰን ላይ ግንባታ መግለጫ

.....

.....

.....

.....

4. የወሰን ላይ ግንባታ ይዘት ማጠቃለያ እና የወሰንተኛ ስምምነት መግለጫ

በአመልካች የሚሞላ						በወሰንተኛ የሚሞላ የስምምነት መግለጫ	
አዋሳኝ	አቅጣጫ	ሊሠራ የታቀደ የወሰን ላይ ግንባታ ዓይነት	የወሰንተኛ ሥም	የወሰንተኛ ነባር ግንባታ ወለል ብዛት	ነባር ግንባታው ከወሰን ያለው ርቀት በሜትር	አመልካች የገቡትን ግዴታ ጠብቀው የተጠቀሰውን ግንባታ ወሰን ላይ እንዲገነቡ መስማማቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ	
						ሥም	ፊርማ
1	በስተግራ						
2	በስተቀኝ						
3							
4							
5							

5. የአመልካች የግዴታ መግለጫ

በግንባታ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር ..... መሠረት ከላይ ከተጠቀሰው ግንባታ አቅጣጫ ያሉና የሚመለከታቸው ወሰንተኞችን ስምምነት የቅርብ ክትትል የሚጠይቅ መሆኑን በማወቅ ስለወሰንና ወሰንተኞች ትክክለኛ መረጃ መስጠቴንና በዚህ የግዴታ ቅጽ እና በግንባታ ፈቃዱ መሠረት የተጎራባችን ነባር ግንባታ ደህንነት በቁፋሮና በግንባታ ሂደት ለመጠበቅና ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ ግዴታ መግባቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

አመልካች _____ ፊርማ _____

ስ.ቁ _____ ቀን _____

6. የሥራ ክፍሉ ማረጋገጫ

ወሰንና ወሰንተኞችን አስመልክቶ አመልካች በሰጡት መረጃ መሰረት እና በግንባታ ፈቃድ መመሪያ መሠረት የቀረበው የግዴታ ዲዛይን በወሰንተኛ ነባር ግንባታ ደህንነት አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳይኖረው ተገቢው ጥንቃቄ በአመልካች እንዲወሰድ በግንባታ ፈቃድ አሠጣጥ ላይ አስፈላጊው እርምጃ የተወሰደ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

መርማሪ ባለሙያ _____ ፊርማ _____

ቀን _____

ማሳሰቢያ

- **ይህ ቅጽ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ወሰንተኞች ብዛት ተዘጋጅቶ የወሰን ላይ ግንባታው በሚመለከታቸው ወሰንተኞች እና በአመልካቹ ተፈርሞና በመርማሪው ባለሙያ ፊርማ ፀድቆ 1 ኮፒ ለአመልካች፣ አንድ አንድ ኮፒ ለሚመለከታቸው ወሰንተኞች ይሰጣል፡፡ 1 ኮፒ ከፋይል ጋር ይያያዛል፡፡**
- **ከወሰንተኛ ነባር ግንባታ ደህንነት ጋር የተገናኘ የግንባታ አካል አመልካች በሚያከናውንበት ወቅት ወሰንተኛው ክትትል ለማድረግ እንዲችል አመልካች መፍቀድ አለበት፡፡**

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 010

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የአማካሪ ግዴታ መግቢያ

1. በአማካሪ የሚሞላ

የአማካሪ ዓይነት ግለሰብ ☐ **አማካሪ ድርጅት** ☐

2 የግንባታው ባለቤት ሥም ☐ የግንባታው አድራሻ ክ/ከ ☐

ቀበሌ/ወረዳ ☐ የቤ.ቁ ☐ የግንባታው አገልግሎት ☐

የኘሎት ቁጥር ☐

የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ☐ ከመሬት በታች ☐ የወለል ስፋት ☐

የካርታ ቁ. ☐ ጥቅል ወጪ ግምት ☐

3. የአማካሪ ድርጅት ሥም ☐ ዘርፍ ☐ ደረጃ ☐

ፈቃድ ቁ. ☐ ግብር ከ.መ.ቁ ☐ ክ.ከ ☐

ወረደወ ☐ የቴክኒክ ሃላፊ ☐ ስ.ቁ. ☐

የድርጅቱ ባለቤት ☐ ስ.ቁ. ☐ ሞባይል ☐

የመልካም ሥራ አፈፃፀም ቀርቧል ☐ አልቀረበም ☐

4. የአማካሪ ግዴታ

እኔ ሥሜ ከታች የተጠቀሰው አማካሪ ከላይ በዝርዝር የተጠቀሰውን ግንባታ ዲዛይን ለመስራት ከግንባታው ባለቤት ጋር በደረስነው ስምምነት መሠረት ለተለያዩ የግንባታ ዲዛይን የሙያ ዘርፎች በተቀመጠው እና ተቀባይነት ባለው ስታንዳርድ፣ በግንባታ ፈቃድ ደንብ ..... በተደነገገው እና በግንባታ ፈቃድ ቁጥር ..... በተቀመጠው መስፈርት መሠረት ዲዛይኑን ለማዘጋጀት ግዴታ የገባሁ መሆኔንና በዚሁ ባዘጋጀሁት ዲዛይን ምክንያት ለሚደርሰው ማንኛውም ችግር ሃላፊ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

4.1 አማካሪ ቢሮ | ቴክኒክ ኃላፊ | ፊርማ | ቀን

4.2 አርክቴክቸራል ዲዛይን

ስም | ምዝገባ ቁ. | ፊርማ | ቀን

4.3 ስትራክቸራል ዲዛይን

ስም | ምዝገባ ቁ. | ፊርማ | ቀን

4.4 ኤሌትሪካል ዲዛይን

ሥም | ምዝገባ ቁ. | ፊርማ | ቀን

4.5 ሳኒታሪ ዲዛይን

ሥም | ምዝገባ ቁ. | ፊርማ | ቀን

4.6 ሜካኒካል ዲዛይን

ሥም | ምዝገባ ቁ. | ፊርማ | ቀን

ማሳሰቢያ

- ደረጃውና የሙያ ዘርፉ ለሚፈቅድለትና በድርጅቱ ለተዘጋጁ ዲዛይኖች በሙሉ ድርጅቱ ጥቅል ሃላፊነት ይወስዳል።

- በግል እንዲዘጋጁ ለሚፈቀዱ ዲዛይኖች ለእያንዳንዱ የሙያ ዓይነት አጥኚው ግለሰብ በግል ሃላፊነት ይወስዳል።

- ይህ ቅጽ በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለግንባታው ባለቤት፣ 1ኮፒ ለአሠሪ፣ 1ኮፒ ከቀሪ ፋይይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 011

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የአሠሪ ግዴታ መግቢያ

በአሠሪ የሚሞላ

1. **የሥራ ተቋራጭ ዓይነት** ግለሰብ ☐ ድርጅት ☐

የግንባታው ባለቤት ሥም ☐ የግንባታው አድራሻ ክ/ከ ☐

ቀበሌ/ወረዳ ☐ የቤ.ቁ ☐ የግንባታው አገልግሎት ☐

የኘሎት ቁጥር ☐

የህንፃ ምድብ ሀ. ☐ ለ. ☐ ሐ. ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁ. ☐ የወለል ስፋት ☐ የካርታ ቁ. ☐

ጥቅል ወጪ ግምት ☐ የሥራ ተቋራጭ ሥም ☐

ዘርፍ ☐ ደረጃ ☐ ፈቃድ ቁ. ☐ ግብር ከ.መ.ቁ ☐

ክ.ከ ☐ ወረዳ ☐ የቴክኒክ ሃላፊ ☐

ስ.ቁ ☐ የድርጅቱ ባለቤት ☐ ስ.ቁ ☐

2. **የአሠሪ ግዴታ**

እኔ ሥሜ ከታች የተጠቀሰው አሠሪ ከላይ በዝርዝር የተጠቀሰውን ግንባታ በተፈቀደው ዲዛይንና የሥራ ዝርዝር መሠረት ግንባታውን ለማከናወን ግዴታ የገባሁ መሆኔንና በዚሁ በገነባሁት ግንባታ ምክንያት ለሚደርሰው ማንኛውም ችግር ሃላፊ መሆኔን በፊርማዬ እያረጋገጥሁ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ አቅርቤአለሁ።

አሠሪ ☐ ፊርማ ☐ ቀን ☐

አባሪ

የግንባታ ሥራ ውል ☐ ገጽ የውል ቀን ☐ የውል ቁ. ☐

የውል መጠን ብር ☐ የግንባታ ሥራ ፈቃድ ኮፒ ☐ ገጽ

የንግድፈቃድ ☐ ገጽ ሌላ ☐

ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ አቅርቤአለሁ ☐

ማሳሰቢያ

- **ይህ ቅጽ በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለግንባታው ባለቤት፣ 1 ኮፒ ለአሠሪ፣ 1 ኮፒ ከቀሪ ፋይል ጋር ይያያዛል።**

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 012

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የገንቢ ግዴታ መግቢያ

በግዴታ ገቢው የሚሞላ

1. ግንባታው የሚገኝበት አድራሻ

ከተማ ..... ክፍለ ከተማ .....

ቀበሌ/ወረዳ ..... ልዩ መጠሪያ/መንገድ ..... የቤት ቁጥር .....

የጎዳና/መንገድ ስም .....

2. የገንቢው/ሥራ ተቋራጭ አድራሻ

ሙሉ ስም

ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ የቤት ቁጥር

ስልክ ቁጥር ደረጃ የግብር ከፋይ መለያ ቁ.

3. የግንባታ ባለቤት አድራሻ

ሙሉ ስም

ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ የቤት ቁጥር

ስልክ ቁጥር የኘሎት ቁጥር

የገንቢ ግዴታ የተጠየቀበት የግንባታ አገልግሎት

የግል መኖሪያ ሱቅ ቢሮ ሆቴል ማምረቻ

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

ሌሎች ☐

የግንባታው አይነት አዲስ ☐ ማሻሻያ ☐ የግንባታ ማፍረስ ☐ ጊዜያዊ ግንባታ ☐ ሌላ ☐

4. የገንቢ ግዴታ የተጠየቀበት ግንባታ ይዞታ

የግል ☐ የመንግስት ☐ የድርጅት ☐ ሌላ ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ የግንባታ ፈቃድ የወጣበት ቀን ☐

የይዞታ ማረጋገጫ ሠነድ ቁጥር ☐

የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁጥር ☐

5. የገንቢው ግዴታ

ከላይ የተመለከተውን ግንባታ ለማከናወን ከግንባታው ባለቤት ጋር በደረስነው ስምምነት መሠረት የተፈቀደውን ፕላንና የሥራ ዝርዝር ጠብቄ ለመሥራት ግዴታ የገባሁ ሲሆን ከግንባታ ፈቃድ እና ከውለታ ውጭ ለሚከናወነው ስራ ተጠያ ቂ መሆኔን አረጋግጣለሁ

የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ቦንድ ቅጅ ቀርቧል ☐ አልቀረበም ☐

6. የገንቢው/ሥራ ተቋራጭ ስም ☐ የስልክ ቁጥር ☐

ፊርማ ☐

7. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

……

……

……

……

ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 013

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ መከታተያ ቅጽ

በተቆጣጣሪው የሚሞላ

1. የባለቤት ሥም ክ/ከ ወረዳ/ቀበሌ

የቤት ቁ. የግንባታው አገልግሎት የግንባታ ፈቃድ ቁ.

የሕንፃ ምድብ ሀ ለ ሐ የኘሎት ቁጥር

የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ከመሬት በታች

ያለፈው ጉብኝት ቀን

ግንባታ መከታተያ ቁ. የጉብኝቱ ዓይነት መደበኛ በአቤቱታ

ግንባታውን የሚያከናውነው የሥራ ተቋራጭ ደረጃ ተቆጣጣሪ

የምዝገባ ቁ. አማካሪ ዘርፍና ደረጃ

የአማካሪ መሐንዲስ ምዝገባ ቁ.

2. አጠቃላይ በግንባታው ሂደት የታዩ ፡-

ይዞታውና ግንባታው

.....

.....

.....

.....

3. ፈቃድና ግንባታው

……

……..

……

……..

4. አሠሪ፣ አማካሪ እና ተቆጣጣሪ፡-

……

……..

……

……..

5. ሌሎች፡-

……

……..……

……

……..

6. ግንባታው ያለበት ደረጃ /የሥራ እርከን

……

……..

7. ካለፈው የክትትል ሪፖርት ያለው ልዩነት

……

……..

……

……..

8. የተቆጣጣሪው ሥም ☐ መታወቂያ ቁ. ☐ ፊርማ ☐

ቀን ☐

ማሳሰቢያ ፣መደበኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግንባታ ደረጃዎች

1. ግንባታ ለመጀመር ማንኛውም ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት፣
2. የመሠረት ቁፋሮ ከተጠናቀቀ እና የመሠረት ብረቶችና ፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች በቦታቸው ከተቀመጡ በኋላ፣
3. የምድር ወለል ከተጠናቀቀና የምድር ወለል ቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረት በቦታው ከተቀመጠ በኋላ፣
4. የጣሪያ ሶሌታ ማጠናቀቂያ ወይም የጣሪያ ሽፋን ሥራ ከመከናወኑ በፊት ናቸው።

በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ክትትል እንዲደረግ ለክትትል ክፍሉ በቅድሚያ ማሳወቅ ያስፈልጋል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 014

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ

የተቆጣጣሪው መግለጫ

1. **የባለቤት ሥም** ክ/ከ ወረዳ/ቀበሌ

የሕንፃ ምድብ ሀ ለ ሐ ኘሎት ቁጥር

የቤት ቁ. የግንባታው አገልግሎት የግንባታ ፈቃድ ቁ.

የወለል ብዛት ከመሬት በላይ ከመሬት በታች ያለፈው ጉብኝት ቀን

ግንባታ መከታተያ ቁ. የጉብኝቱ ዓይነት መደበኛ በአቤቱታ

የሥራ ተቋራጭ ደረጃ ተቆጣጣሪ

የምዝገባ ቁ. አማካሪ ዘርፍና ደረጃ

የአማካሪ መሐንዲስ ምዝገባ ቁ.

2. **አጠቃላይ ግንባታው ያለበት ደረጃ**

.....

.....

3. **ውሳኔ**

የግንባታ ማስቆሚያ ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ምክንያት

.....

.....

.....

.....

4. እርምት የሚጠይቀው ብሎክ መጠሪያ

……

……..

5. ባለቤቱ መውሰድ ያለበት የእርምት እርምጃ

……

……..

6. ግንባታው ያለበት ደረጃ

……

……..

7. የግንባታው ባለቤት ከላይ የተጠቀሱትን የእርምት እርምጃዎች በመውሰድ እስከ ……ቀን ዓ.ም ድረስ ማስጠንቀቂያውን ለሰጠው አካል ሪፖርት ካላደረገ እርምት የሚጠይቀው ግንባታ እንዲቆም የሚደረግ ሆኖ በቀጣይነትም በባለቤቱ ወጪ መንግስት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል።

የተቆጣጣሪው ሥም		መታወቂያ ቁ.		ፊርማ	
ያፀደቀው ሃላፊ		ፊርማ			
ማስጠንቀቂያውን የጠቀበለው		የሥራ ድርሻ			
ቁጥር		ቀን			

ማሳሰቢያ

ይህ ቅጽ በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለግንባታው ባለቤት፣ 1 ኮፒ ለመ/ቤቱ የግንባታ ፈቃድ ክፍል ሲሰጥ 1 ኮፒ ከፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 015

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ማስቆሚያ

1. የተቆጣጣሪው መግለጫ

የባለቤት ሥም ክ/ከ ወረዳ/ቀበሌ

ኘሎት ቁጥር

የቤት ቁ. የግንባታው አገልግሎት የግንባታ ፈቃድ ቁ.

መጨረሻ የተጎበኘበት ቀን ግንባታ መከታተያ ቁ.

2. የጉብኝቱ ዓይነት መደበኛ በአቤቱታ ድንገተኛ

1. የሥራ ተቋራጭ ዘርፍ / ደረጃ

የተቋራጭ መሃንዲስ ምዝገባ ቁ.

2. አማካሪ ደረጃ

የአማካሪ መሃንዲስ ምዝገባ ቁ.

3. የግንባታ ማቆሚያ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል አልተሰጠም

ከተሰጠ የተሰጠበት ቀን ቁጥር

4. አጠቃላይ ግንባታው ያለበት ደረጃ

.....

.....

5. ከፈቃድ ውጭ የሆነው ግንባታ ያለበት ደረጃ

……

……

6. ማስጠንቀቂያው ቀደም ሲል የተሰጠበት ሥራ ከሆነ ከማስጠንቀቂያው በኋላ የተደረገ ለውጥ ወይም ማስተካከያ

……

……

7. ውሳኔ

ግንባታው የሚቆምበት ምክንያት

……

……

……

……

በተለይ የሚቆመው ግንባታ/ሕንፃ

……

……

8. **ከዚህ በላይ የተመለከተው ግንባታ/ሕንፃ ከ ……. ቀን …….. ዓ.ም ጀምሮ እንዲቆም ተወስኗል። ከዚህ ዕለት ጀምሮ የግንባታው ባለቤት እንዲቆም ውሳኔ ያረፈበትን ግንባታ በማቆም እስከ …… ቀን --------- ዓ.ም ጀምሮ መወሰድ ያለበትን የእርምት እርምጃ በማድረግ ይህንን ትዕዛዝ ለሰጠው መ/ቤት ሪፖርት ማድረግ አለበት። ይህ ካልተፈፀመ የተገነባው ግንባታ እንዲፈርስ ውሳኔ ለሚመለከተው ክፍል ይላካል።**

የተቆጣጣሪው ሥም | **መታወቂያ ቁ.** | **ፊርማ**

ያፀደቀው ሃላፊ | **ፊርማ**

ማስጠንቀቂያውን የጠቀበለው | **የሥራ ድርሻ**

ቁጥር | **ቀን**

ማሳሰቢያ ፣

ይህ ቅጽ በ5 ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለግንባታው ባለቤት፣ 1 ኮፒ ለ …… ከተማ አስተዳደር፣ 1 ኮፒ ለክፍለ ከተማ ጽ/ቤት፣ 1 ኮፒ ለወረዳ ጽ/ቤት ይሰጣል። 1 ኮፒ ደግሞ ከፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 016

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ

1. የተቆጣጣሪው መግለጫ

የባለቤት ሥም ☐ ክ/ከ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐

የቤት ቁ. ☐ የግንባታው አገልግሎት ☐ የግንባታ ፈቃድ ቁ. ☐

የጎሎች ቁጥር ☐

ግንባታ ማስቆሚያ የተሰጠበት ቀን ☐ ቁጥር ☐ የማስተካከያ ቀነገደብ ☐

2. ግንባታው የቆመበት ምክንያት

.....

.....

3. በማስቆሚያው ትዕዛዝ መሠረት የተደረገ ማስተካከይ

.....

.....

4. የተደረገው ማስተካከያ

በቂና ግንባታውን መቀጠል ያስችላል ☐ በቂ አይደለም ☐

ምንም የእርምት እርምጃ አልተወሰደም ☐

5. ውሳኔ

በክትትል ሂደት የታየው እና በግንባታ ማስቆሚያ ቅጽ ላይ የተመለከተው ግድፈት እስከ ተጠቀሰው ቀነገደብ ድረስ እንዲስተካከል በተገለፀው መሠረት የግንባታው ባለቤት የወሰዱትን የእርምት እርምጃ በማጣራት ከዚህ በታች የተገለፀው ውሳኔ ተሰጥቷል። ይህ ውሳኔ ለሚመለከታቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች እንዲላክላቸው ተደርጓል።

ያዘጋጀው _____ ፊርማ _____

ያፀደቀው ሃላፊ _____ ፊርማ _____

ቁጥር _____ ቀን _____

ውሳኔውን የተቀበለው ሰው ሥም _____ የሥራ ድርሻ _____ ፊርማ _____

ማሳሰቢያ

ይህ ቅጽ በ5 ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለግንባታው ባለቤት፣ 1 ኮፒ ለ ..... ከተማ አስተዳደር፣ 1 ኮፒ ለክፍለ ከተማ ጽ/ቤት፣ 1 ኮፒ ለወረዳ ጽ/ቤት ይሰታል። 1 ኮፒ ደግሞ ከፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 017

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ሥራ ለውጥ ተጨማሪ ማሳወቂያ

በግንባታ ባለቤት፣ በአማካሪ ወይም በሥራ ተቋራጭ የሚሞላ

1. የባለቤት ሥም ክ/ከ ወረዳ/ቀበሌ

   የቤት ቁ. የግንባታው አገልግሎት የግንባታ ፈቃድ ቁ.

   የኘሎት ቁጥር

   የወለል ብዛት የሥራ ተቋራጭ ዘርፍ/ደረጃ

   የሳይት መሐንዲስ ምዝገባ ቁ.

   አማካሪ ዘርፍ/ደረጃ የአማካሪ መሐንዲስ

   ምዝገባ ቁ.

2. በግንባታው ፈቃድ ላይ ከተመለከተው የወለል ስፋት እና የሕንፃ ከፍታ ለውጥ ውጭ፣ በተሸካሚ መዋቅሩ ላይ ተጽዕኖ በሌላቸውና መዋቅራዊ ባልሆኑ አካላት ላይ የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎችን የማይቃረኑ የዲዛይን ለውጦችን በግንባታው ሂደት ለማድረግ የሚለወጠውን ሥራ ዓይነት እና ዝርዝር ይገለጽ፡፤

.....

.....

.....

.....

ከላይ የተገለፀው ሥራ የሚያሳይ አባሪ ንድፍ

አርክቴክቸራል ☐ ገጽ ስትራክቸራል ☐ ገጽ ሌላ ☐ ገጽ

መረጃውን የሞላው	የሥራ ድርሻ/ሃላፊነት	ፊርማ	ቀን

ማሳሰቢያ

- በግንባታ ሂደት በግንባታ ፈቃድ ላይ ከተመለከተው የወለል ስፋት፣ የግንባታ መስፋፋት እና የሕንፃ ከፍታ ለውጥ ለማድረግ በቅድሚ የግንባታ ፈቃድ መውጣት አለበት።
- በግንባታ ሂደት በግንባታ ፈቃድ ላይ ከተመለከተው የወለል ስፋት እና የሕንፃ ከፍታ ለውጥ ሳያደርግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና በተሸካሚ መዋቅሩ ላይ ተጽዕኖ በሌላቸው መዋቅራዊ ባልሆኑ አካላት ላይ የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች የማይቃረኑ ለውጦችን ማድረግ ይቻላል።
- የሚደረገው ለውጥ ግንባታው ከመደረጉ ከ2 የሥራ ቀን በፊት የሥራ ለውጥ ቅጽ 013 በመሙላት እና ንድፉን በማማያያዝ 1 ኮፒ ለመ/ቤቱ የክትትልና ቁጥጥር ክፍል መስጠት1 ኮፒ ከሣይት መቆጣጠሪያ መዝገብ ጋር መያያዝ አለበት።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 018

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ መጠየቂያ

በአመልካች የሚሞላ

1. ግንባታው የሚገኝበት አድራሻ

ከተማ ☐ ክፍለ ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐

የቤት ቁ. ☐ የጎዳና ሥም ☐

የኘሎት ቁጥር ☐

2. የነባር ግንባታ አገልግሎት (ቅይጥ አገልግሎቶች ካሉት በሚመለከታቸው ሁሉ ላይ የ x ምልክት ያድርጉ)

የሕንፃ ምድብ ሀ ☐ ለ ☐ ሐ ☐

የግል መኖሪያ ☐ ሱቅ/ንግድ ☐ ማምረቻ ☐ ማከማቻ ☐ ቢሮ ☐

አፓርታማ ☐ ሆቴል ☐ የጤና ተቋም ☐ ሌላ/ይጠቀስ ☐

ማምረቻ ከሆነ ዓይነቱ ይገለጽ ይዞታው ☐ የግል ☐ የመንግስት ☐ ሌላ ☐

ግንባታው የተጠናቀቀበት ቀን ☐ ዓ.ም ☐ የቀድሞው ግንባታ አለው ☐ የለውም ☐

ነባር ከሆነ የቀድሞው ☐ የግንባታ ፈቃድ ቁ. ☐ የግንባታው ወጪ ☐
ፈቃድ የወጣበት ቀን

የወለል ብዛት ☐ ከመሬት በላይ ከፍታው በሜትር ☐ ከመሬት በታች ጥልቀቱ በሜትር ☐

3. የወሰን ላይ ግንባታ ይዞታ መግለጫ

.....

.....

.....

.....

የሥራ ተቋራጭ ሥም ደረጃ አድራሻ ስ.ቁ

የአማካሪው ድርጅት ሥም ደረጃ አድራሻ ስ.ቁ

የዲዛይኑ ዓይነት	ክትትል ያደረገው ባለሙያ ስም	የምዝገባ ቁጥር	ስልክ ቁ
አርክቴክቸራል			
ስትራክቸራል			
ኤሌትሪካል			
ሳኒታሪ			
ሜካኒካል			

4. የግንባታ ማሻሻያ ፈቃድ የተሰጠባቸው የፕላን ዓይነት

አርክቴክቸራል ማሻሻያ የተሰጠበት ቀን የፈቃድ ቁ.

ስትራክቸራል " " " " "

ኤሌትሪካል " " " " "

ሳኒታሪ " " " " "

ሜካኒካል " " " " "

5. የተከለሰ ፕላን

የተከለሰው ዲዛይን	ያዘጋጀው ባለሙያ	የምዝገባ ቁጥር	ስ.ቁ.	ፊርማ

6. ከዚህ በላይ የተጠየቀውን አገናዝቤ እና አንብቤ የሰጠሁት መረጃ እውነትና ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ፣ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥና በዚህም ምክንያት ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ እና በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንናውንም የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመረዳት የመጠቀሚያ ፈቃድ እንዲሰጠን አመለክታለሁ::

የግንባታው ባለቤት ሥም ስ.ቁ የግብር ከፋይ ቁ.

አመልካች ከባለቤቱ የተለየ ከሆነ ስ.ቁ ፊርማ

ቀን

7. በፈቃድ ሰጪው ክፍል የሚሞላ

ለምርመራ የቀረበ ሠነድ

የፕላን መረጃ ገጽ ኤሌትሪካል ገጽ የወሰን ስምምነት መረጃ ገጽ

አርክቴክቸራል ገጽ ሳኒታሪ ገጽ የባለሙያ ግዴታ ገጽ

ስትራክቸራል ገጽ ሜካኒካል ገጽ የሊዝ/ይዞታ ውል ገጽ

የመዳረሻ መንገድ የሚፈርሰው ግንባታ ይዞታ ስፋት

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ቁ.

ፈቃድ መቀበያ ቀጠሮ 1 2

8. ያልተፈቀደበት ምክንያት

……

……

……

……

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ፊርማ

ቀን [ ] ሰዓት [ ]

የፈቀደው/ያልፈቀደው ሃላፊ ስም [ ] ፊርማ [ ]

ቀን [ ] ሰዓት [ ] የፕላን ስምምነት ቁጥር [ ]

ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር /ፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 19

አርማ

የ..... ክልል

የ..... ከተማ አስተዳደር

የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ

በአመልካች የሚሞላ

1. የአመልካች አድራሻ

ከተማ..... ክፍለ ከተማ ..... ወረዳ/ቀበሌ ..... የኘሎት ቁጥር ----------

የቤት ቁጥር ..... ስልክ ቁጥር .....

2. የግንባታ ቦታ አድራሻ

ከተማ ..... ክፍለ ከተማ ..... ወረዳ ---------- የቤት ቁጥር.....

3. የግንባታው አይነት

ለአዲስ ግንባታ ---------- ለአገልግሎት ለውጥ ..... ነባር ግንባታ ማሻሻያ .....

ለተጠየቀው ግንባታ አገልግሎት የፕላን ስምምነት አለ..... የለም.....

4. ጉዳዩ

.....

.....

.....

.....

ውሳኔ የተሰጠበት ቀን.....

የተያያዘ አባሪ .....ገጽ

የአመልካች ወይም ወኪል ሙሉ ስም ---------- ፊርማ ---------- ቀን----------

ሴሪ ቁጥር ---------
ቅጽ ...020

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ

በአመልካች የሚሞላ

1. **አድራሻ**

ከተማ ☐ ክ/ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐ የኘሎት ቁጥር ☐

የቤት ቁጥር ☐ የጐዳና ስም ☐

የተጠየቀው የግንባታ ዓይነት

ኮንትራታዊ ☐ ተጓዳኝ ☐ ወቅታዊ ☐ የነባር ግንባታ ጊዜያዊ ማሻሻያ ☐

የይዞታ ማረጋገጫ ቁጥር ☐ የውሉ ማብቂያ ቀን ☐ ስፋት ☐

የተጠየቀው አገልግሎት ☐

የባለቤቱ ስም ☐ ስ.ቁ ☐

2. ከላይ የተጠየቀውን አገናዝቤና አንብቤ ፣ የሰጠሁት መረጃ እውነትና ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ብሰጥ በዚህ ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ እና በዚህ ቀፅ ላይ ቢጠቀሰም ባይጠቀስም ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ ድንጋጌወች ተፈጻሚነቱን በመረዳትና ጊዜያዊ ግንባታ እንዲነሳ በሚደረግበት ወቅት ምንም አይነት ካሳ ልጠይቅበት እንደማልችል በማወቅ የጊዜያዊ ግንባታ እንዲሰጠኝ አመለክታለሁ

አመልካች ስም ..... ፊርማ ..... ቀን .....

በክፍሉ የሚሞላ

3. **የጊዜያዊ ግንባታ ጥያቄ አባሪ ሆኖ የተያያዘ** ☐ ገጽ

ፈቃድ መቀበያ ቀጠሮ 1 ☐ 2 ☐

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ☐ ፊርማ ☐

ሠዓት ☐ ቀን ☐

ማሳሰቢያ፣ ይሕ ቅጽ በ 2ኮፒ ተዘጋጅቶ 1ኮፒ ለአመልካች 1ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ ...021

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

የቅጣት ውሳኔ ማሳወቂያ /ደንብ ማስከበር/

የሕንፃው ባለቤት ☐ የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐

1. አድራሻ

ክፍለ ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐ የቤት ቁጥር ☐

የኘሎት ቁጥር ☐

የሕንፃ ምድብ ☐ ግንባታው የተጀመረበት ቀን ☐ ዓ.ም ☐

የሥራ ተቋራጭ ☐ አድራሻ ☐

ክ/ከተማ ☐ ቀበሌ ☐

አማካሪ ድርጅት ☐ አድራሻ ክፍለ ከተማ ☐ ቀበሌ ☐

የቤት ቁጥር ☐ ስ.ቁ ☐

2. የጥፋትዓይነት.....
.....
.....

3. በሕንፃ ደንብ ቁጥር ..... አንቀጽ ..... መሠረት ብር..... አስተዳደራዊ ቅጣት ተወስኗል። በመሆኑም የተወሰነውን ቅጣት ገቢ በማድረግ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ እናስታውቃለን የተወሰደውን የእርምት እርምጃ እንዲያስፈጽሙ ለደንብ ማስፈፀም የተላከላቸው መሆኑን እንገልጻለን።

የሕንፃ ቡም ፊርማ .....
ቀን .....

ማሳሰቢያ፣ ይሕ ቅፅ በ5 ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለግንባታው ባለቤት 1 ኮፒ ለከተማ አስተዳደር 1 ኮፒ ለክፍለ ከተማ እና 1 ኮፒ ለቀበሌ ደንብ ማስከበር 1 ኮፒ ከፋይል ጋር ይያያዛል ።

አርማ

ሴሪ ቁጥር ----------
ቅጽ 022

የ.....ክልል
የ.....ከተማ አስተዳደር

የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ

በአመልካች የሚሞላ

1. **ግንባታው የሚካሄድበት አድራሻ**

ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ/ ወረዳ

የቤት ቁጥር የጐዳና ስም የጎለት ቁጥር

የፕላን ማሻሻያ የተጠየቀው አገልግሎት

የግል መኖሪያ ሱቅ ቢሮ ሆቴል

ማምረቻ የትምህርት ተቋም ሌላ

የግንባታው ዓይነት

አዲስ ማሻሻያ ሌላ

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ፈቃድ የተሰጠበት ቀን

ፈቃድ የሚያበቃበት ጊዜ ግንባታው ያለበት ደረጃ

2. **የፕላን ማሻሻያ የተደረገበት ምክንያት**.....
.....

3. **የተሻሻለውን ፕላን ያዘጋጀው አማካሪ ድርጅት**

ሥም ደረጃ አድራሻ ስ/ቁ
የተሻለውዲዛይን ዝርዝር መግለጫ

የዲዛይን ዓይነት	ዲዛይኑን ያዘጋጀው/ያሻሻለው ባለሙያ	የባለሙያ ምዝገባ ቁጥር	ስልክ ቁጥር	ፊርማ
አርኪቴክቸራል				
ስትራክቸራል				
ኤሌክትሪካል				
ሳኒተሪ				
ሜካኒካል				

5. እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተገለፀው የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ከዚህ በላይ የተጠየቀውን አንብቤና አገናዝቤ፣የሰጠሁት መረጃ እውነት እና ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ፣ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ

ብሰጥ እና በዚህም ምክንያት ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ መሆኔን በማወቅ እንዲሁም በዚህ ማመልከቻ ቅጽ ላይ ቢጠቀስም ባይጠቀስም ማንኛውም የግንባታ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆን በመረዳት የፕላን ማሻሻያው እንዲፈቀድልኝ እጠይቃለሁ።

የጠያቂው ስም ☐ ስ.ቁ ☐

ፊርማ ☐

ቀን ☐

6. **በፈቃድ ሠጪው ክፍል የሚሞላ**
   የቀረበው ማስረጃ

   አርኪቴክቸራል ☐ ገጽ ሳኒተሪ ☐ ገጽ

   ስትራክቸራል ☐ ገጽ ሜካኒካል ☐ ገጽ

   ኤሌክትሪካል ☐ ገጽ የወሰን ላይ መረጃ ☐ ገጽ

   የባለሙያ ግዴታ ☐ ገጽ

ሌሎች ☐

የቀረበው ሠነድ የተሟላ ☐ አይደለም ☐

ፈቃድ መቀበያ ቀጠሮ 1 ☐ 2 ☐

ፕላን ማሻሻያ ው ተፈቅዷል ☐ አልተፈቀደም ☐

7. ያልተፈቀደበት ምክንያት……
   ……..……..

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ☐ ፊርማ ☐

ቀን ☐ ሠዓት ☐

ያፀደቀው ኃላፊ ስም ☐ ፊርማ ☐

ቀን ☐ ሠዓት ☐ የፕላን ስምምነት ቁጥር ☐

ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅጽ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካቹ ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር ጋር ይያያዛል ::

ሴሪ ቁጥር ----------

ቅጽ...023

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ጊዜ ማራዘሚያ ማመልከቻ

በአመልካች የሚሞላ

1. ግንባታው የሚካሄድበት አድራሻ

ከተማ ☐ ክ/ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐ የኘሎት ቁጥር ☐

የግንባታው ዓይነት አዲስ ☐ ማሻሻያ ☐

የግንባታ ፈቃድ የተጠየቀበት አገልግሎት

ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐

አፓርታማ ☐ መጋዘን ☐ የጤና ተቋም ☐ የትምህርት ተቋም ☐

ሌላ ☐

የሕንፃ ምድብ ለ ☐ ሐ ☐

የወለል ብዛት ከምድር በላይ ☐ ከምድር በታች ☐

የግንባታ ፈቃድ ቁጥር ☐ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን ☐

የፈቃድ ማብቂያ ጊዜ ☐ ቀን ☐ ዓ.ም

2. ግንባታው ያለበት ደረጃ .....

.....

...

3. የግንባታ ማራዘሚያ ጊዜ የተጠየቀበት ምክንያት

.....

...

……

የተጠየቀው ጊዜ

የጠያቂው ስም ስ.ቁ

ፊርማ ማህተም

ውሳኔ መቀበያ ቀጠሮ 1 2

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም

ፊርማ ቀን ዓ.ም ሰዓት

በክፍሉ የሚሞላ

4. የግንባታ ክትትል ባደረገው ባለሙያ የሚሞላ

ሕንፃው ያለበት የግንቦታ ደረጃ ….

የተከናወነው ግንባታ ……%

5. በቀረበው የማራዘሚያ ጥያቄ አስተያየት

……

……

ተቀባይነት አለው የለውም

ተቀባይነት ካለው ……ተጨማሪ የግንባታ ጊዜ…… ተፈቅዷል ።

የሕንፃ ሹም ሹም ……..

ፊርማ……

ቀን ……

ማሳሰቢያ፣ ይህ ቅፅ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ እና ተፈርሞ በመሥሪያ ቤቱ ማህተም ከተረጋገጠ በኋላ ለግንባታው ባለቤት 1 ኮፒ ከፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------

ቅጽ...024

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

ለፕላን ማምገማ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቂያ

1. ግንባታው ፈቃድ ክፍል ☐ ግንባታ ክትትል ክፍል ☐

የግንባታው ባለቤት ስም ☐ ክ/ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐ የቤት ቁጥር ☐

የግንባታው አድራሻ ክ/ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐ የኘሎት ቁጥር ☐

የሕንፃ ምድብ ለ ☐ ሐ ☐

የግንባታ አገልግሎት

ሱቅ ☐ ቢሮ ☐ ሆቴል ☐ ማምረቻ ☐ የትምህርት ተቋም ☐ ሌላ ☐

የግንባታው ዓይነት

አዲስ ☐ ማሻሻያ ☐ ጊዜያዊ

የግንባታው የወለል ብዛት ከምድር በታች ☐ ከምድር በላይ ☐ ከፍታው በሜትር ከምድር በታች ☐ ከምድር በላይ ☐

2. ተጨማሪ የማምገማ ጊዜ የተጠየቀበት

ምክንያት.....

.....

የተጠየቀው ተጨማሪ ጊዜ ☐

የሕንፃ ሹም ስም ☐ ፊርማ ☐ ቀን ☐ ዓ.ም ☐

3. የከተማ አስተዳደር ውሳኔ

.....

.....

የተፈቀደ ተጨማሪ ☐

የከተማ አስተዳደር ወይም የተሠየመ አካል ኃላፊ ሥም .....ፊርማ.....

ቀን .....

ማሳሰቢያ፣ ይሕ ቅፅ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለከተማ አስተዳደሩ 1 ኮፒ የግንባታ ፈቃድ ክፍል ከማህደር ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------

ቅጽ...025

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ሥራ እርከን ማሳወቂያ

የግንባታ ባለቤት ፣ የአማካሪ ወይም በሥራ ተቋራጭ የሚሞላ

1. የባለቤቱ ስም ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ

የቤት ቁጥር የሕንፃ ምድብ ፕሎት ቁጥር

የግንባታው ዓይነት

አዲስ ማሻሻያ የግንባታው አገልግሎት የግንባታ ፈቃድ ቁጥር

የግንባታው የወለል ብዛት ከምድር በላይ ከምድር በታች

የሥራ ተቋራጭ ደረጃ /ዘርፍ የምዝገባ ቁጥር የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር

አማካሪ ዘርፍ / ደረጃ ምዝገባ ቁጥር የግብር ከፋይ ቁጥር

2. የሚከናወነው የሥራ እርከን

.....

.....

የአገልግሎት ክፍያ ደረሠኝ ቁጥር

የጠያቂው ስም ስልክ ቁጥር ፊርማ

በግንባታ ክትትል ክፍል የሚሞላ

3. **የሥራ እርከን የሚታይበት** ቀጠሮ ቀን ዓ.ም

መረጃውን ያፀደቀው ኃላፊ ሥም

ፊርማ ቀን ዓ.ም

ይሕ ቅፅ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር/ፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------

ቅጽ 026

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ መጠየቂያ ቅጽ

በአመልካች የሚሞላ

1. **የአመልካች አድራሻ**

ከተማ ☐ ክ/ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐ የኘሎት ቁጥር ☐

የቤት ቁጥር ☐ የስልክ ቁጥር ☐

2. **ክፍያ የተፈፀመበት የአገልግሎት ዓይነት** .....

.....

.....

3. **ተመላሽ እንደሆን የተጠየቀበት ምክንያት** .....

.....

.....

የክፍያ ደረሠኝ ቁጥር ☐

የክፍያ መጠን ብር ☐

4. **የአመልካች ወይም የወኪል ሙሉ ስም** ☐ ፊርማ ☐ ቀን ☐

የተያያዘ አባሪ ☐ ገጽ

ቀጠሮ ☐

መረጃውን የተቀበለው ሰው ስም ☐

ፊርማ ☐ ቀን ☐ ሠዓት ☐

ማሳሰቢያ፣ ይሕ ቅፅ በ2 ኮፒ ተሞልቶ 1 ኮፒ ለአመልካች ሲሰጥ 2ኛው ኮፒ ከማህደር/ፋይል ጋር ይያያዛል።

ሴሪ ቁጥር ----------

ቅጽ.....027

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

ይግባኝ ሰሚ ቦርድ ውሳኔ ማሳወቂያ

1. የባለይግባኙ መረጃ

የግንባታው ባለቤት [ ] የግንባታ ፈቃድ ቁጥር [ ]

የአመልካች አድራሻ

ከተማ [ ] ክፍለ ከተማ [ ] ወረዳ/ቀበሌ [ ] የንሎት ቁጥር [ ]

የቤት ቁጥር [ ] ስልክ ቁጥር [ ]

2. የግንባታ አድራሻ

ከተማ [ ] ክ/ከተማ [ ] ወረዳ [ ]

የቤት ቁጥር [ ]

ውሳኔ የተሰጠበት ቀን [ ]

የቦርዱ ሊቀመንበር ስም [ ]

ፊርማ [ ]

ቀን [ ]

ማሳሰቢያ፣ ይሕ ቅፅ በ4 ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለአመልካች 1 ኮፒ ለከተማ አስተዳደር 1 ኮፒ ለግንባታ ፈቃድና ክትትል ክፍል 1 ኮፒ ከማህደር/ፋይል ጋር ይያያዛል ::

ሴሪ ቁጥር ----------

ቅጽ...028

አርማ

የ.....ክልል

የ.....ከተማ አስተዳደር

የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ የምስክር ወረቀት

1. የባለይዞታ ሥም ☐ የካርታ ቁጥር ☐

   የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ☐

   አድራሻ ክፍለ ከተማ ☐ ወረዳ/ቀበሌ ☐ የጎሎት ቁጥር ☐

   የመንገድ ጐዳና ሥም ☐

   የጊዜያዊ ግንባታ ዓይነት ☐

   ኮንትራታዊ ☐ ተጓዳኝ ☐ ወቅታዊ ☐ የነባር ግንባታ ☐ ጊዜያዊ ማሻሻያ ☐

2. **የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ውሳኔ**

   የሕንጻ ደንብ ቁጥር ☐ መሠረት የቀረበው የጊዜያዊ ግነባታ ፈቃድ ተመልርምሮ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

   ውሳኔ .....

   .....

   የተፈቀደው አገልግሎት ☐

3. **ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለፀዉ ገንባታ የቀረበው ሠነድ ተመርምሮ ግንባታው እንዲካሄድ**

   ተፈቅዷል ☐ አልተፈቀደም ☐

4. **ያልተፈቀደበት ምክንያት** .....

   .....

   የግንባታ ምስክር ወረቀት አካል አባሪ የሆኑት ሠነዶች

አርኪቴክቸራል ☐ ገጽ ሳኒተሪ ☐ ገጽ

ስትራክቸራል ☐ ገጽ ኤሌክትሪካል ☐ ገጽ

የፈቃድ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ..... ቀን ዓ.ም

የግንባታ ፈቃድ ቁ ☐ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን ☐

የግንባታ ፈቃድ መርማሪ ባለሙያ		የንግድ ፈቃድ ያፀደቀው ኃላፊ	
ስም		ስም	
ፊርማ		ፊርማ	
ቀን		ቀን	

ማሳሰቢያ፣ ይሕ ቅጽ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ "ተፈቅዷል" እና "ለክትትል" ከሚሉ ሁለት የዲዛይን ሠነድ ኮፒዎች ጋር ለግንባታ ባለቤት የሚሠጥ ሲሆን አንድ ኮፒ ከፋይል ጋር የሚያያዝ ይሆናል።

1. ይሕ ቅጽ በኃላፊው ተፈርሞ በመ/ቤቱ ማህተም ካልተረጋገጠ ዋጋ አይኖረውም ።
2. በዚህ ይዞታ ላይ ከዚህ በፊት ወጪ የተደረገ የግንባታ ፈቃድ በዚህ ተተክቷል።

ሴሪ ቁጥር ----------

ቅጽ...029



የ.....ክልል

የ.....ከተማ

የምሽት መገንቢያ ፍቃድ

1. **የግንባታ ባለቤት ስም**

አድራሻ ከተማ ክፍለ ከተማ

ወረዳ/ቀበሌ ስልክ ቁጥር

የግንባታው አድራሻ

ከተማ ክ/ከተማ

ቀበሌ/ወረዳ የቤት ቁጥር የኘሎት ቁጥር

የግንባታው ፍቃድ ቁጥር

ግንባታው የተጀመረበት ቀን የፍቃድ ጊዜው

የሚያበቃበት ቀን ዓ.ም

የግንባታው የወለል ብዛት ከምድር በታች

ከምድር በላይ

2. **በምሽት መገንባት ያስፈለገበት ምክንያት**

.....

.....

....

አመልካች ፊርማ

ቀን ስልክ ቁጥር

በከፍሉ የሚሞላ

3. **የግንባታ ፍቃድ ውሳኔ**

በሕንጻ አዋጅ ☐ **ደንብ ቁጥር** ☐ ***መመሪያ ቁጥር*** ☐

የቀረበው የግንባታ ፈቃድ ተመርምሮ ከዚህ በታች የተመለከተው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

……

……

……

4. **ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለጻውን ግንባታ እንዲካሄድ**

የግንባታ ፈቃድ የስፈለገበት ጊዜ ☐ ***መገንቢያ ፈቃድ ቁጥር*** ☐

ቀን ☐

የግንባታዉ ፈቃድ መርማሪ ☐ **የግንባታ ፈቃድ አጽዳቂው** ☐

ባለሙያ ☐ **ኃላፊ** ☐

ስም ☐ **ስም** ☐

ፊርማ ☐ **ፊርማ** ☐

ቀን ☐ **ቀን** ☐

ማሳሰቢያ፣ **ይህ ቅጽ በ2ኮፒ ተሠርቶ 1ኮፒ ለባለቤቱ አንድ ኮፒ ከፋይል ጋር ይያያዛል፡፡ ቅፀ በጎላፊ ተፈርሞ በማህተም ካልተረጋገጠ አያገለግልም ከዚህ በፊት ወጪ የተደረገ የምሽት ግንባታ ፈቃድ በዚህኛው ተተክቷል፡፡**


ፀ
ፈ
ቨ
ፐ
ፚ
ፘ
ተፈቅዷል
ለክትትል ብቻ

1





2





3





4





5





6





TO BE USED ONLY WITH BUILDING DIRECTIVE

PERMITTED

FOR
FOLLOW UP
ONLY

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ግንቦት ፷፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.50
Addis Ababa May 31, 2022

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፴፩/፪ሺ፲፩

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውጭ ማስታወቂያ ደንብ

ገፅ..... ፪ሺ፭፻፳፫

CONTENT

REGULATION NUMBER 131/2022
THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT
OUTDOOR ADVERTISEMENT REGULATION

Page.....2523

ደንብ ቁጥር ፻፴፩/፪ሺ፲፩

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውጭ ማስታወቂያ ደንብ

የውጭ ማስታወቂያን በሥርዓት በመምራት እና በማስተዳደር የአካባቢ ጥበቃን፣ የትራፊክ እንቅስቃሴን፣ የከተማውን ውበትና ገጽታ እንዲሁም የሕብረተሰቡን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ ለከተማው ኢኮኖሚ እድገትና መሪ ፕላን ተግባራዊነት አስተዋፅኦ የሚያደርግ በመሆኑ፤

በከተማው የሚተከሉ፣ የሚለጠፉ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚሰራጩ የውጭ ማስታወቂያዎች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲሰራጩ ለማድረግ አደረጃጀትና አሰራርን በማዘመን ተደራሽ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽና ጤናማ የውጭ ማስታወቂያ እንዲኖር እና ኢንዱስትሪው ሰፊ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት እና የሥራ እድል እንዲፈጥር ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአንዱ ዋጋ
Unit price

REGULATION NUMBER 131/2022

THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT OUTDOOR ADVERTISEMENT REGULATION

WHEREAS, it has been found necessary to facilitate environment protection, the traffic movement, protect the beauty and image of the city as well as uphold the rights and benefits of the community through appropriately managing outdoor advertisements;

WHEREAS, the income generated from the sector contributes to the economic development and the master plan implementation of the city;

WHEREAS, it has been found necessary to modernize organizations and systems to create accessible, efficient, transparent, and a healthy outdoor advertisements to enable the industry to create a wide range of trade, investment, and job opportunities to ensure the dissemination of quality outdoor advertisements that are erected, posted or disseminated in any manner in the city;

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፱/፪ሺ፬ አንቀፅ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፫፬/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፺፩ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውጭ ማስታወቂያ ደንብ ቁጥር ፻፴፩/፪ሺ፲፬ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. "አዋጅ" ማለት እንደ አግባብነቱ የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፱/፪ሺ፬ ወይም/እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፫፬/፪ሺ፲፬ ነው፤

፪. "ደንብ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤት የአገልግሎት ክፍያ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፲፯/፪ሺ፲፫ እና ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፻፴፬/፪ሺ፲፬ ነው፤

፫. "ባለሥልጣን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ነው፤

፬. "ፈቃድ ሰጪ" ማለት እንደ አግባብነቱ በየደረጃው ያለ የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ የግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ጽህፈት ቤት ነው፤

፭. "መዋቅራዊ ፕላን" ማለት በማህበራዊ፣ በምጣኔ ሀብታዊ እና በአካባቢያዊ ዘርፎች የተመጣጠነ የከተማ ልማት ለማስገኘት በሚያስችል መልኩ የከተማውን ፊዚካላዊ ዕድገትና ልማት በተመለከተ መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮችን የሚዘረዝርና ሕጋዊ ተፈፃሚነት ያለው ዐብይ የከተማ ፕላን ነው፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Article (3) of Article 36 of Advertisement Proclamation number 759/2012 and Article 91 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation number 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

Part One

General Provisions

1. Short Title

This Regulation may be cited as: **"The Addis Ababa City Government Outdoor Advertisement Regulation Number 131/2022."**

2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"Proclamation"** means the Advertisement Proclamation number 759/2012 or the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation number 74/2021 as per the context;
2. **"Regulation"** means the Addis Ababa City Government Public Offices Service Charge Regulation number 117/2021 and its amendment Regulation number 134/2022;
3. **"Authority"** means the Addis Ababa City Government Construction Permit and Regulatory Authority;
4. **"Licensing Organ"** means the construction permit and regulatory office at the sub-city or woreda level as per the context;
5. **"Structural Plan"** means a legally applicable main plan of the city that specifies requirements to be met regarding the physical development and growth of the city to ensure balanced urban development in the social, economic, and environmental sectors;

፮. "ዋና ዋና መንገድ" ማለት በከተማው መዋቅራዊ ኘላን ላይ ዋና መንገድ ወይም ዋና መጋቢ መንገድ ወይም ቀለበት መንገድ ተብሎ የተጠቀሰ መንገድ ነው፤

፯. "አደባባይ" ማለት በመንገድ መሃል ለትራፊክ መሽጋገሪያና ማዟዟሪያ የሚያገለግል ሆኖ ለተለያዩ ሀውልቶች፣ ቅርጻ-ቅርፆች፣ የውኃ ፋውንቴን ግንባታዎችና ለእጽዋት መትከያ የተተወ አረንጓዴ ቦታ ነው፤

፰. "ማስታወቂያ" ማለት የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ እንዲስፋፋ ወይም ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት ወይም ዓላማ እንዲተዋወቅ በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የንግድ ማስታወቂያ ሲሆን የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያንና የግል ማስታወቂያን ይጨምራል፤

፱. "የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ" ማለት የውጭ ማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስታወቂያውን በከፊል ወይም በሙሉ በመግለጽ ለህዝብ የሚነገር ወይም ለእይታ ግልጽ በሆነ ቦታ የሚካሄድ የማስታወቅ ስራ ነው፤

፲. "የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ" ማለት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሠራጭ መልዕክት ነው፤

፲፩. "የግል ማስታወቂያ" ማለት በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የአፋልጉኝ እና ሌላ መሰል ማስታወቂያን ያካትታል፤

፲፪. "የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ" ማለት፡-

ሀ) በቢል ቦርድ፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ፣ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የሚሰራጭ፣

6. **"Major Road"** means a road that is indicated as a major road or major supplementary road or ring road in the structural plan of the city;
7. **"Roundabout"** means a space used for traffic movement on a road having a preserved green area for the purpose of erecting monuments, sculptures, making fountains, and planting;
8. **"Advertisement"** means a commercial advertisement that is disseminated through outdoor advertisement means to promote the sale of products or services or to publicize the naming, emblem, trademark, or objective of the thereof, and it includes public service and private advertisements;
9. **"Outdoor Advertisement Work"** means an advertisement activity to partially or fully announce an advertisement for the public or that is carried out visibly for the public using outdoor advertisement methods
10. **"Public Service Advertisement"** means a message that is disseminated using outdoor advertisement methods for the purpose of the public;
11. **"Private Advertisement"** means a message of looking for a missing person and other similar advertisements that were disseminated through outdoor advertisement methods;
12. **"Outdoor Advertisement Distribution Methods"** means an advertisement that is:
    A. disseminated through billboards, notice boards, electronic screens, or films;

ለ) በሕንጻ፣ በግድግዳ፣ በጣራ ወይም በማናቸውም ስትራክቸር ወይም በትራንስፖርት ተሽከርካሪ፣ በተንሳፋፊ ፊኛ ወይም መሰል ነገር ላይ የሚሳል፣ የሚፃፍ፣ የሚለጠፍ ወይም የሚተከል፣

ሐ) በተንጠልጣይ ነገር፣ በፖስተር፣ በስቲከር፣ በተባዛ በራሪ ወረቀት፣ በብሮሸር፣ ሊፍሌት፣ ፍላየር የሚሰራጭ፣

መ) በድምጽ ካሴት፣ በድምፅ ማጉያ መሳሪያ የሚሰራጭ፣ ወይም

ሠ) በሌላ መሰል ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ሲሆን የመንገድ አቅጣጫ ጠቋሚ፣ የትራፊክና የአውቶቢስ ፌርማታ ምልክትን፣ የመንገድ ስምን ወይም ቁጥርንና መሰል የሕዝብ አገልግሎት መረጃ ሰጪ ምልክቶችን አይጨምርም፤

፲፫. "የውጭ ማስታወቂያ ሠሌዳ" ማለት በኤሌክትሪክ ወይም በብርሃን በሚሠራ የማስታወቂያ ሥራ የሚካሄድበት ወይም የሚታይበት ወይም ተለጣፊ ጽሑፍ፣ ምስል ወይም በሌላ ዘዴ የማስታወቂያ ሥራ የሚሠራበት ሠሌዳ ነው፤

፲፬. "የማስታወቂያ አሰራጭ" ማለት እንደ አንድ ንግድ ዘርፍ የንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት የማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲሁም የትራንስፖርት ተሽከርካሪን፣ የሕንፃ አካልን፣ የማስታወቂያ ሰሌዳ ፍሬምን፣ የማስታወቂያ መለጠፊያ ሳጥን ወይም ቦርድ ተክሎ በማከራየት ወይም ማናቸውም መሰል አገልግሎትን ለውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫነት እንዲውል በማድረግ የውጭ ማስታወቂያ የማሰራጨት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ነው፤

B. painted, written, posted, or erected on a building, wall, roof, or any structure or transport vehicles, balloons, or similar things;

C. disseminated using hanging objects, posters, stickers, flyers, brochures, and leaflets;

D. disseminated through audio cassettes and loudspeakers; or

E. disseminated through other similar methods, and it does not include street direction indicators, traffic and bus stop signs, street names or numbers, and other similar public service informative signs;

13. **"Outdoor Advertisement Board"** means a board used to carry out an advertisement work through electronic or lighting means or for the purpose of an advertisement utilizing stickers, pictures, or any other means;

14. **"Advertisement Promoter"** means a person that provides advertisement dissemination service by having a business license in the sector using various advertisement methods and transporting vehicles, building parts, notice boards, and erect notice posting boxes or boards and leasing the thereof, or using any other similar services for the purpose of outdoor advertisement;

፲፮.**"የማስታወቂያ አስነጋሪ"** ማለት በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት በማስታወቂያ አሰራጩ ወይም የራሱን ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት ማስታወቂያው የሚተዋወቅለት ሰው ነው፤

፲፯. **"የማስታወቂያ ወኪል"** ማለት በማስታወቂያ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፲፰.**"የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት"** ማለት የውጭ ማስታወቂያ መንገዶችን በመጠቀም ማስታወቂያ መትከል፣ መለጠፍ፣ መሳል፣ መፃፍ፣ ማስቀመጥ ወይም በማናቸውም መንገድ ማሰራጨትንና በድምፅ ማስተዋወቅን ይጨምራል፤

፲፱."**ከህዝብ መልካም ፀባይ ጋር የሚቃረን መልዕክት**" ማለት ፈቃድ ከተሰጠበት ውጭ ሆኖ ህዝብን ለአመጽ የሚያነሳሳ፣ ከህብረተሰቡ መልካም ጸባይ እና እሴቶች ጋር የማይጣጣም መልእክት ነው፤

፳.**"ስፖንሰር"** ማለት ፕሮግራምን ወይም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ስፖንሰር የሚያደርግ ሰው ነው፤

፳፩.**"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፫. <u>የጾታ አገላለጽ</u>

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

፬. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ በከተማው ውስጥ በሚገኙ የውጭ ማስታወቂያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፭. <u>ስለ ውጭ ማስታወቂያ መርህ</u>

የውጭ ማስታወቂያ ፍቃድ፣ ክትትልና የቁጥጥር ስርዓት የሚከተሉትን መርሆዎች መሰረት ማድረግ አለበት፡-

15. **"Advertiser"** means a person whose advertisement for a product, service, or company is being advertised by the advertisement promoter or by himself through outdoor advertisement dissemination methods;
16. **"Advertisement Agent"** means a person engaged in advertisement work;
17. **"Outdoor Advertisement Dissemination"** means the erecting, posting, painting, writing, and placing of advertisements using outdoor advertisement methods or disseminating same in any other means and it includes sound advertisement;
18. **"Message against Societal Norms"** means a message, which is not included in the issued license, that provokes the public for violence and is inconsistent with the morals and values of the society;
19. **"Sponsor"** means a person that sponsors a program or an advertisement dissemination method;
20. **"Person"** means any natural or juridical person.

3. <u>Gender Expression</u>

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

4. <u>Scope of Application</u>

This Regulation shall be applicable to those outdoor advertisements that are found in the city.

5. <u>Principles for Outdoor Advertisement</u>

The licensing, supervision and regulatory system of outdoor advertisement should be based on the following principles:

፩. ህግ፣ ባሕል፣ እምነት፣ ቋንቋና እሴት የማክበር መርህ፤ ማንኛውም በምስል፣ በቅርጽና በድምፅ የሚተላለፉ የውጭ ማስታወቂያዎች የፌደራል መንግስትና የከተማ አስተዳደሩን ህጎች፣ የህዝቡን ባህል፣ እምነት፣ ቋንቋና እሴቶች የማክበር፤

፪. የመሬት አጠቃቀም መርህ፤ የውጭ ማስታወቂያ የከተማውን ፕላን መሰረት ማድረግ አለበት፤

፫. የአከባቢ ጥበቃና ደህንነት መርህ፡-

ሀ) ኃይል የሚጠይቁ የውጭ ማስታወቂያዎች ኃይል ቆጣቢና የተንቀሳቃሽ ምስል አዳዲስ ቴክኖሎጂ እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣

ለ) የውጭ ማስታወቂያ የመንገድ ትራፊክ የማያውክና በነዋሪው ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆን አለበት፤

ሐ) የውጭ ማስታወቂያ ከአረንጓዴ ልማት ጋር ተጣጥሞ የሚሄድና የአካባቢ ጥበቃን የሚያጎለብት እንዲሆን ማድረግ፣

መ) የውጭ ማስታወቂያ ከድምፅ ብክለት የፀዳ፣ የማይረብሽና በተከለከለ ስፍራ እንዳይከናወን ማድረግ፡፡

፬. የከተማ ውበትና ፅዳት መርህ፡-

ሀ) የውጭ ማስታወቂያ ቅርፅ፣ መጠን፣ ገፅታ፣ ቀለም፣ ከአከባቢው የመሬት አጠቃቀምና ፕላን ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት፤

ለ) የውጭ ማስታወቂያ የከተማዋን ውበት የማያጎድፉ፣ የእይታ ብክለት የማያስከትልና የከተማውን ውበትና ገፅታ የሚጨምር መሆን አለበት፤

ሐ) አግባብ ያለው አካል የሚያወጣውን የውጭ ማስታወቂያ ጥራትና ደረጃን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

1.

the principle of respecting the law, culture, language, and values: any outdoor advertisement that is broadcasted through image, shapes, and sounds should respect the laws of the federal and the city government, and the culture, beliefs, language, and values of the society;

2. the principle of land utilization: outdoor advertisements should be based on the plan of the city;
3. the principle of environmental protection and safety:
   A. promote power saving and modern motion picture technologies for those outdoor advertisements that demand power;
   B. an outdoor advertisement should not affect the traffic movement and harm the residents;
   C. make sure that outdoor advertisement is implemented in harmony with green development and promotes environmental protection;
   D. ensure that an outdoor advertisement is free from sound pollution, does not disturb others, and will not be carried out in restricted areas.
4. the principle of city beautification and sanitation
   A. the shape, size, appearance, and colour of the outdoor advertisement should be consistent with the land utilization and plan of the local area;
   B. the outdoor advertisement should not harm the beauty of the city, cause visual pollution, and should contribute to the beauty and image of the city;
   C. should follow the quality and standard of an outdoor advertisement to be issued by the relevant organ.

ክፍል ሁለት

የውጭ ማስታወቂያ ሥራ መብት፤ ፈቃድ፤ ደረጃ እና ስርጭት

፮. በውጭ ማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት

አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

፩. ማንኛውም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ግለሰብ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመና በካፒታሉ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ ድርሻ የሌለበት የንግድ ድርጅት በውጭ ማስተዋወቅ ሥራ የመሰማራት መብት ይኖረዋል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ በውጭ ማስተዋወቅ ሥራ ላይ የመሰማራት መብት ይኖረዋል፡፡

፯. ስለውጭ ማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ

ማንኛውም በውጭ ማስታወቂያ የስራ ዘርፍ መሰማራት የሚፈልግ ሰው፡-

፩. የውጭ ማስታወቂያ አገልግሎት የንግድ ስራ ፍቃድ ማውጣት አለበት፤

፪. ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ወኪል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተደነገገውን አሟልቶ በውጭ ማስታወቂያ ስራ ለመስራት የውጭ ማስታወቂያ አገልግሎት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም የማስታወቂያ አስነጋሪው የራሱን ድርጅት ወይም ምርት ወይም አገልግሎት ለማስተዋወቅ የማስታወቂያ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማውጣት ሳያስፈልገው ከሚመለከተው አካል የውጭ ማስታወቂያ ይዘቱን በማረጋገጥ እና ከባለስልጣኑ የውጭ ማስታወቂያ የግንባታ ፈቃድ በማውጣት ማስተዋወቅ ወይም ማሰራጨት ይችላል፤

Part Two

The Right, Licensing, Level, and Distribution of Outdoor Advertisement Activity

6. The Right to Undertake Outdoor Advertisement Activity

Without prejudice to the provisions specified under other relevant laws:

1. Any Ethiopian national or a business company established according to Ethiopian laws and does not have the share of a foreign national in its capital shall have the right to undertake advertisement activity;
2. Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, any foreign national of Ethiopian origin shall have the right to undertake advertisement activity.

7. Licensing for Outdoor Advertisement Activity

Any individual who wants to engage in outdoor advertisement activity should:

1. obtain a business license for outdoor advertisement service;
2. any outdoor advertisement agent should meet the requirements stated under Article 6 of this Regulation and must obtain the business lice for outdoor advertisement service to undertake the activity;
3. notwithstanding the provisions stated under Sub-Article (1) and (2) of this Article, an advertiser can promote or disseminate his own company or product, or service by confirming the content of the outdoor advertisement by the relevant organ and obtaining a construction permit for the outdoor advertisement from the authority without the need to obtain an advertisement licensing and professional competence certificate;

፬. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በውጭ አገር ተዘጋጅቶ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ሊደረግ የሚችለው በማስታወቂያ ወኪል አማካኝነት ብቻ ነው፤

፭. የውጭ ማስታወቂያ ፍቃድ አሰጣጥና ዕድሳት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፰. <u>ስለውጭ ማስታወቂያ የጥራት ደረጃ</u>

ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ከመሰራጨቱ በፊት በባለሥልጣኑ እና በሚመለከተው አካል የሚወጣውን የብቃትና የጥራት ደረጃ መመሪያ የሚያሟላ መሆን አለበት።

፱. <u>ስለውጭ ማስታወቂያ ሥርጭት</u>

፩. በማንኛውም ሁኔታ የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት የሚቻለው በባለስልጣኑ ፈቃድ ብቻ ነው፤

፪. ዝርዝር አፈጻጸሙ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፲. <u>የውጭ ማስታወቂያ ስርጭትን ስለማቋረጥ</u>

፩. ማንኛውም ማስታወቂያ ከተፈቀደለት ይዘት ውጪ ሲሆን እና ለህግ ወይም ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ መልእክት እንደሚያስተላልፍ ከተረጋገጠ፣ በቅድሚያ የማስታወቂያው ባለቤት በአንድ ቀን ወይም በ፳፬ ሰዓት የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያነሳ የማስጠንቀቂያ ጽሁፍ እንዲደርሰዉ በማድረግ የማስታወቂያ ሥራው ይቋረጣል፤

፪. በደረሰው ማስጠንቀቂያ መሰረት ለማንሳት ፈቃደኛ ካልሆነ ባለስልጣኑ በራሱ ወጪ አንስቶ ንብረቱን በመውረስ ለማንሳት ያወጣውን ወጪ ከባለቤቱ በህግ ይጠይቃል፤ ከዚህ በተጨማሪም በከተማው ክልል በማንኛውም ቦታ ምርቱንም ሆነ አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ስራ ለመስራት ጥያቄ ቢያቀርብ ለአንድ ዓመት እንዳይሳተፍ ይደረጋል፤

4.

without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, any advertisement prepared abroad and brought to Ethiopia may be permitted to be distributed in Ethiopia only through an advertisement agent;

5. the issuance and renewal of license for the outdoor advertisement shall be specified through a directive to be issued by the authority.

8. <u>Quality Level of an Outdoor Advertisement</u>

Any outdoor advertisement must fulfill the competence and quality requirements stated under the directive issued by the authority and the relevant organ before it is disseminated.

9. <u>Distribution of an Outdoor Advertisement</u>

1. In any condition, the distribution of outdoor advertisements is only allowed under the permission of the authority.
2. The details for the implementation of the thereof shall be specified through a directive to be issued by the authority.

10. <u>Termination of Outdoor Advertisement Dissemination</u>

1. If any advertisement is opposite to the approved content and confirmed that it imparts a message which is against the law and public morality, the advertisement activity shall be terminated by first sending a warning notice for the owner of the advertisement to remove it within a day or 24 hours;
2. If the owner of the advertisement refuses to remove it as per the issued warning, the authority shall remove it at his own cost and demand the owner the expense for removing it legally by confiscating the property; in addition to this, if he submits a request for the advertisement of his products or services in any palace within the vicinity of the city, he shall be prohibited for one year;

፫. በማንኛውም ወቅት ሰሌዳው የተተከለበት ቦታ ለሌላ አገልግሎት ሲፈለግ ከፈቃድ ሰጪው በሚሰጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የማስታወቂያ ሰሌዳው ባለቤት እንዲያነሳ በማድረግ ማስታወቂያዉ ይቋረጣል፤

፬. ቦታዉ ለልማት ወይም ለማናቸውም የሕዝብ አገልግሎት ወይም ለሌላ አገልግሎት ተፈልጎ ሰሌዳዉ ሲነሳ የኪራይ ወይም የአገልግሎት ዘመኑ ያልተጠናቀቀ ከሆነ ለባለፈቃዱ የቀሪ ወራት ሂሳብ ተሰልቶ ይመለስለታል ወይም ምትክ ቦታ ይሰጠዋል፤ ሆኖም የኪራይ ዘመኑ የተጠናቀቀ ከሆነና በቀጣይ ማስተዋወቅ ከፈለገ ጥያቄው በአዲስ መልክ ይስተናገዳል፤

፭. ማንኛውም ሰው የተፈቀደለትን ማስታወቂያ ሥራ ለማቋረጥ ሲወስን ለፈቃድ ሰጪው በአስር ቀናት ውስጥ በጽሁፍ በማሳወቅ ማስታወቂያዉ እንዲቋረጥ ማድረግ ይኖርበታል፤ ለቀሪው የውል ጊዜ የተከፈለው ክፍያ ሳይመለስ ማስታወቂያዉ ይቋረጣል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

፮. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት በባለስልጣኑ ፈቃድ ተሰጥቷቸው በዚህ ደንብ ወይም ከስታንዳርድ ውጭ የተሰሩ ማስታወቂዎች በአምስት ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንዲነሱ ያደርጋል፤ የማስታወቂያው ባለቤት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላነሳ ባለሥልጣኑ በራሱ ወጪ አንስቶ ንብረቱን በመውረስ ለማፍረስ ያወጣውን ወጪ በህግ ይጠይቃል።

3. If the area where the advertisement board was erected is needed for another service at any time, the owner of the board shall remove it according to the period given by the licensing authority and the advertisement shall be terminated;

4. If the lease or service period for an advertisement board is not completed when the board is removed as the land is needed for development or any public service or another service, the cost for the remaining months shall be calculated and the owner will be refunded or he shall be entitled with a replacement land. However, if the lease period is over and he wants to continue the advertisement, his request shall be entertained as a new one;

5. When any person wants to terminate the approved advertisement activity, he should notify the licensing authority in writing within ten days to terminate the advertisement; the advertisement shall be terminated without refunding the payment made for the remaining contract period; the details shall be specified through a directive;

6. Those advertisements made without standards by the approval of the authority before the issuance of this Regulation shall be removed by giving a five days advance written notice; if the owner of the advertisement fails to remove it, the authority shall remove it at his own cost and demand the owner the expense for removing it legally by confiscating the property.

፲፩. <u>ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ ስለመስጠት</u>

፩. ለግንባታ፣ ለልማት ወይም ለማናቸውም የሕዝብ አገልግሎት የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ በማግኘት የተተከለ ወይም የተለጠፈ የውጭ ማስታወቂያ ያረፈበት ቦታ ለማስታወቂያ አስነጋሪው ሁኔታውን በማሳወቅና ተለዋጭ ቦታ ወይም የቀሪ ወራት ሂሳብ ተሰልቶ እንዲሰጠው በማድረግ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የማስታወቂያው ባለቤት ማስታወቂያውን እንዲያነሳ በማድረግ ማስታወቂያው ስርጭት ይቋረጣል፤ በዚህ ሁኔታ ለተነሳ ማስታወቂያ ካሳ አይከፈልም፤

፪. ከንግድ እና ከሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ ስርጭት ጋር በተያያዘ አዋጁን ወይም ይህን ደንብ በማስፈፀም ሂደት ውስጥ ተነፃፃሪ ፍላጎቶች ሲኖሩ ለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ ቅድሚያ መሰጠት ይኖርበታል።

፲፪. <u>ለውጭ ማስታወቂያ በጨረታ ስለሚሰጡ ቦታዎች</u>

፩. ለውጭ ማስታወቂያ መትከያነት በጨረታ የሚሰጡ ቦታዎች በፍትሃዊነትና በግልፅነት መሰጠት ይኖርባቸዋል፤

፪. በዋና መንገድ አካባቢ ለውጭ ማስታወቂያ መትከያ የተዘጋጁ ቦታዎች እና ሌሎች የከተማው አስተዳደር ንብረቶች የሆኑና ለውጭ ማስታወቂያ መትከያ የተዘጋጁ ቦታዎች በጨረታ የሚሰጡ ይሆናል፤

፫. ባለስልጣኑ በወረቀት የሚዘጋጅ ማስታወቂያ ሊለጠፍበት የሚችል የጋራ የማስታወቂያ ሰሌዳ ሊያዘጋጅ ወይም የማስታወቂያ ቦታዎችን እንደ አስፈላጊነቱ በጨረታ ወይም በቀጥታ ያለውድድር ሊሰጥ ይችላል፤

11.

<u>About Prioritizing the Public Interest</u>

1. When the area for which an approved outdoor advertisement has been erected or posted is needed for construction or development or any other public service, the owner of the advertisement shall be notified about the case and will be asked to remove the advertisement within the given period by providing him a replacement land or refunding the payment made for the remaining months and the dissemination of the advertisement shall be terminated; compensation will not be paid for the removal of advertisements in such circumstances;
2. When there are relative interests during the enforcement of the Proclamation or this Regulation regarding the dissemination of commercial or public service advertisements, priority should be given to public service advertisements.

12. <u>Places to be Auctioned for Outdoor Advertisement</u>

1. Places to be auctioned for the placement of outdoor advertisements should be offered in a just and transparent manner;
2. Places prepared for the erection of outdoor advertisements near main roads and other properties of the city governments and places prepared for the erection of outdoor advertisements shall be given through auction;
3. The authority may prepare common notice boards on which paper notices may be posted or may give notice spaces through auction or directly without competition as may be found necessary;

፬. ባለስልጣኑ በከተማው አስተዳደር ክልል ውስጥ ለውጭ ማስታወቂያ መትከያነት በዋና መንገድ አካባቢ የሚገኙ ቦታዎችን በጨረታ ለማቅረብ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ቦታዎችን ለጨረታ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

፭. የጨረታ አሸናፊ የሆነ ሰው በየዓመቱ ፈቃዱን እያሳደሰ የውል ዘመኑ እስከሚያበቃ ድረስ በበውጭ ማስታወቂያ መትከያ ቦታው ላይ ሊጠቀም ይችላል፤

፮. የውል ጊዜው የተጠናቀቀ የውጭ ማስታወቂያ መትከያ ቦታ የሚተላለፈው በድጋሚ ጨረታ በማውጣት ይሆናል፤

፯.ከዋና መንገድ ውጭ በሆኑ መንገዶች አካባቢ ለሚተከሉ የውጭ ማስታወቂያዎች እንደ አስፈላጊነቱ ያለ ጨረታ በአመልካቹ ጥያቄ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል።።

፲፫. <u>የውጭ ማስታወቂያን ስለማደስ፣ ስለማንሳት ወይም ስለመቀየር</u>

የማስታወቂያ አሰራጩ ወይም የራሱን ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት የሚያስተዋውቅ ሰው ፡-

፩. የውጭ ማስታወቂያውንና የማስታወቂያ መትከያ ቦታውን ደህንነትና ፅዳት መጠበቅ፣ መጠገንና ማደስ ይኖርበታል፤

፪. ከአገልግሎት ውጭ የሆነን፣ የጥራት ደረጃው የተጓደለን ወይም የስርጭት ቆይታ ጊዜው ያለፈበትን የውጭ ማስታወቂያ ማንሳት ይኖርበታል፤

፫. የስርጭት ቆይታ ጊዜው ያለፈበትን ለማስቀጠል ወይም ከአገልግሎት ውጪ የሆነን የውጭ ማስታወቂያ ለመቀየር ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤

፬. ለሕዝብ ጥቅም፣ ለግንባታና በሌላ በማናቸውም ምክንያት እንዲነሳ የተደረገን ነባር የውጭ ማስታወቂያ በሌላ ቦታ ለመትከል ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፤

4. The authority shall, in consultation with the relevant offices and stakeholders, cause the preparation of the places that will be used for the placement of outdoor advertisements around the main roads within the vicinity of the city government;

5. The bid winner shall renew his license annually and may use the place for outdoor advertisement until the end of the contract period;

6. A place having an expired contract for erecting an outdoor advertisement shall be transferred through auction;

7. A license shall be, as may be found necessary, given without auction, upon the request of an applicant, for outdoor advertisements to be erected on roads outside the main roads.

13. **<u>About Renewing, Removing, or Changing Outdoor Advertisements</u>**

An advertiser or a person who advertises his product, service or company should:

1. preserve the safety and cleanliness of the outdoor advertisement and the space for erecting it; carry out maintenance and renewal activities;
2. remove those outdoor advertisements that are out of service, fail to meet the set forth standards, or whose dissemination period is over;
3. obtain a permit to extend the dissemination of an outdoor advertisement whose period is over or to replace an outdoor advertisement that is out of service;
4. obtain a permit to erect an existing outdoor advertisement that was removed for the benefit of the public, construction, and any other reason in another place;

፭. ሌላ የውጭ ማስታወቂያ ለማሰራጨት ከፈቃድ ሰጪው ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

ክፍል ሶስት

የውጭ ማስታወቂያ፣ ይዘት፣ ቋንቋ እና ፊደል አጠቃቀም

፲፬. የውጭ ማስታወቂያ ይዘት

፩. ማናቸውም በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ የሚሰራጭ ማስታወቂያ፡-

ሀ) ማናቸውንም ሕግ ወይም መልካም ሥነ ምግባር የማይጻረር፣ አሳሳች ወይም ተገቢ ካልሆነ አገላለጽ ነፃ የሆነ፣

ለ) የሕብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ እሴት የሚያከብርና የሸማቹን ሕጋዊ ጥቅም የማይጎዳ፣

ሐ) የሚተዋወቀውን ምርት ወይም አገልግሎት እውነተኛ ባህርይ፣ ጥቅም፣ ጥራትና መሰል መረጃዎችን የሚገልጽ፣

መ) የሌሎችን ሰዎች ምርት ወይም አገልግሎት የማያንቋሽሽ፣

ሠ) የአገርን ክብርና ጥቅም የሚጠብቅ፣

ረ) የሙያ ሥነ ምግባርን የሚያከብር ይዘት ያለው መሆን አለበት፤

፪. የሚከተሉት የውጭ ማስታወቂያዎች ሕግን ወይም መልካም ሥነ-ምግባርን የሚጻረር ይዘት ወይም አቀራረብ እንዳላቸው ሆነው ይቆጠራሉ፡-

ሀ) ቋንቋን፣ ያታን፣ ዘርን፣ ብሔር ብሔረሰብን፣ ሙያን፣ ሐይማኖትን፣ እምነትን፣ ፖለቲካዊ ወይም ማህበራዊ አቋምን አስመልክቶ የሰው ልጅን ስብዕና፣ ነጻነት ወይም እኩልነት የሚጻረር ምስልን ወይም አገላለጽን የያዘ፣

obtain a permit from the licensing authority to disseminate another outdoor advertisement.

Part Three

The Content, Language, and letter Use of an Outdoor Advertisement

14. The Content of an Outdoor Advertisement

1. Any advertisement that will be broadcasted through an outdoor advertisement should:
   A. not violate any law or good moral and be free from any misleading and inappropriate expressions;
   B. respect the social and cultural values of the society and not harm the lawful interests of consumers;
   C. describe the true nature, benefit, quality, and other similar information of the product or service being advertised;
   D. not degrade the product or services of other individuals;
   E. protect the interest and dignity of the country;
   F. have content that respects professional ethics.
2. The following outdoor advertisements shall be considered as having content or expression that contravenes the law or good morals:
   A. contain images or expressions that violate the personality, liberty, or equality of human beings concerning their language, sex, race, nation-nationality, profession, religion, belief, political or social status;

ለ) የግለሰብን፣ የብሔር ብሔረሰብን ወይም የህዝብን መልካም ሥነ-ምግባር ወይም ሰብአዊ ክብርን እንዲሁም የድርጅትን መልካም ስምና ዝና የሚያጐድፍ፣

ሐ) ብሔራዊ ወይም የክልል ሰንደቅ ዓላማን፣ አርማን፣ ብሔራዊ መዝሙርን ወይም ገንዘብን የሚያንቋሽሽ ወይም የሚያዋርድ፣

መ) የአካል ጉዳተኛን፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደሙ ውስጥ ያለበትን ወይም በሌላ ህመም የተያዘ ሰውን ክብርና ሥነ ልቦና የሚነካ፣

ሠ) በጎብረተሰቡ መካከል አመጽ፣ የሀይል ተግባር፣ ሽብር፣ ግጭት ወይም የፍርሃት ስሜት እንዲፈጠር የሚያነሳሳ፣

ረ) የጎብረተሰቡን አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነት ወይም ደህንነት ለጉዳት የሚያጋልጥ ድርጊት እንዲፈፀም የሚያነሳሳ፣

ሰ) አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል የሚወሰነውን የድምጽ መጠን በመተላለፍ በማናቸውም ዓይነት የድምጽ ማጉያ አማካይነት አካባቢን በከፍተኛ ድምጽ በመበከል የሚነገር፣

ሸ) ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ የጽሁፍ መልዕክት፣ ምስል፣ ሥዕላዊ መግለጫ ወይም መሰል አቀራረብን የያዘ፣

ቀ) የግለሰብን ስም፣ ምስል ወይም ፎቶግራፍ ግለሰቡ ሳይፈቅድ የሚጠቀም ወይም በህግ ጥበቃ የሚደረግለትን የኪነ-ጥበብ ወይም የፈጠራ ሥራ የሚመለከተው ሰው ሳይፈቅድ የሚጠቀም፣

በ) ለትራፊክ ደህንነት ወይም ለአካባቢ ጥበቃ ተጻራሪ የሆነ፣

ተ) የመከላከያ ሠራዊት ወይም የፖሊስ የደንብ ልብስን ወይም ምልክትን በመጠቀም የሚቀርብ የንግድ ማስታወቂያ፣

B. harm the good behavior or human dignity of n individual, nation-nationality or people as well as defame the reputation of a company;

C. degrade the national or regional states' flag, emblem, national anthem, or currency;

D. undermine the dignity and emotional status of an individual with a physical disability, a person living with HIV/AIDS, or an individual suffering from other diseases;

E. instigate chaos, violence, terror, conflict, or fear in the society;

F. provoke to commit an action that endangers the physical and mental health as well as the safety of society;

G. cause sound pollution using any kind of sound amplifiers by violating the sound limit set by the relevant governmental organ;

H. contain written messages, images, graphic descriptions, or such other presentations that are contrary to good behavior;

I. using the name, image, or photo of an individual without his consent or using artistic or creative works that have legal protection without the authorization of the concerned party;

J. violate traffic safety or environmental protection procedures;

K. commercial advertisements presented by wearing the uniforms of the defense force or police or their insignia;

ቸ) በሌላ ህግ የተከለከለ ይዘት ወይም አቀራረብ የያዘ ወይም ማንኛውም ህግ እንዲጣስ የሚያነሳሳ የውጭ ማስታወቂያ፤

፫. የሚከተሉት ይዘት ያላቸው ማስታወቂያዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡-

ሀ) አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በአደንዛዥ ዕጽነት የተመደበን ማናቸውንም ዕፅ የሚመለከት፤

ለ) ያለሐኪም ትዕዛዝ የማይሰጥ ወይም በጥቅም ላይ የማይውል መድሀኒትን ወይም የህክምና መገልገያን ተጠቃሚው በቀጥታ እንዲጠቀም የሚገፋፋ፤

ሐ) ናርኮቲክ መድሐኒትን ወይም ሳይኮቴራፒክ ንጥረ ነገርን የሚመለከት፤

መ) የጦር መሳሪያ ማስታወቂያ፤

ሠ) የቁማር ማስታወቂያ፤

ረ) የህገ ወጥ ምርት ወይም አገልግሎት ማስታወቂያ፤

ሰ) የአራጣ አበዳሪ ማስታወቂያ፤

ሸ) የጥንቆላ ማስታወቂያ፤

ቀ) የሲጋራ ወይም የሌሎች የትምባሆ ውጤቶች ማስታወቂያ፤

በ) የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ ከተመዘገበ አካል ውጭ የሚደረግ የፖለቲካ ግብ ያለው ማስታወቂያ፤

ተ) የጫት፣ የሺሻ ማስታወቂያ፤

ቸ) የአልኮል ማስታወቂያ፤

ኀ) ሌሎች በህግ የተከለከሉ ማስታወቂያዎች፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (በ) የተደነገገው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት የሚያሰራጨውን የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅት የሚያሠራጨውን የአድራሻ ለውጥ፣ የሰብሰባ ጥሪ እና መሰል ማስታወቂያን የሚከለክል አይሆንም፡፡

L. contain contents or presentations that are prohibited by other laws or encourage the violation of any law.

3. It is prohibited to directly or indirectly disseminate advertisements that have the following contents using outdoor advertisements:

A. regarding the advertisement of any substance classified as a drug by the relevant governmental body;

B. advertisements that encourage consumers to directly use any medications that could not be used without prescriptions or unavailable ones or medical appliances;

C. advertisement of narcotic drugs or psychotropic substances;

D. advertisement of weapons;

E. advertisement of gambling;

F. advertisement of illegal products or services;

G. advertisement of usury;

H. advertisement of witchcraft;

I. advertisement of cigarettes or other tobacco products;

J. an advertisement having a political agenda except for those legally registered political parties;

K. advertisement of khat and shisha;

L. alcohol advertisements;

M. other advertisements prohibited by the law.

4. The provision stated under letter (J) of Sub-Article (2) of this Article shall not prohibit the election campaign advertisement to be disseminated by a political party that was registered according to the relevant laws or an election candidate and the advertisement of an address change, meeting announcement and other similar advertisements of a political party.

፲፭. <u>የውጭ ማስታወቂያ ቋንቋ እና ፊደል አጠቃቀም</u>

በማናቸውም መንገድ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ፡-

፩. በአገር ውስጥ ቋንቋ ወይም ፊደል የተጻፈ መሆን ይኖርበታል፤

፪. በውጭ ቋንቋ ወይም ፊደል ጭምር የተጻፈ ከሆነ የአገር ውስጥ ቋንቋው ወይም ፊደሉ ከውጭው ቋንቋ ወይም ፊደል አስቀድሞ ወይም ከላይ ሆኖ የተጻፈ መሆን አለበት፣

፫. በውጭ ቋንቋ ተተርጉሞ የቀረበ የውጭ ማስታወቂያ አቻ ትርጉም ከሕጋዊ ተርጓሚ ተቋም መቅረብ አለበት፤

፬. ከውጭ ቋንቋ የተወሰደው ቃል ማስታወቂያው በተሰራጨበት የአገሪቱ ቋንቋ ፍቺ ከሌለው በቀር የሀገር ውስጥ ቋንቋ ከውጭ አገር ቋንቋ ጋር በማቀላቀል በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት የተከለከለ ነው። ሆኖም ይህ ድንጋጌ የንግድ ስምና ምልክትን በውጭ ቋንቋ ከመጠቀም የሚያግድ አይደለም፤

፭. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (፩) እስከ (፬) የተመለከተው ድንጋጌ፡-

ሀ) በተባዙ የበራሪ ወረቀት ማስታወቂያዎች ወይም በብሮሸር፣ በሊፍሌት፣ በፍላየር ወይም በወረቀት ላይ በሚሰራጭ ማስታወቂያ፣

ለ) በምርት ማሸጊያ ወይም መያዣ ላይ በሚሰራጭ ማስታወቂያ እና

ሐ) በዲፕሎማቲክ እና መሰል አለም አቀፍ ተቋማት በሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

15.

<u>Language and Alphabet Utilization of Outdoor Advertisements</u>

An outdoor advertisement to be disseminated by any means should:

1. be written using the local language or alphabet;
2. if the advertisement is also written using a foreign language or alphabet, the local language or alphabet must be written before or above the foreign one;
3. an outdoor advertisement that was presented by translating from a foreign language should avail its equivalent translation from a legal translation office;
4. it is prohibited to mix a local language with a foreign language and disseminate an outdoor advertisement unless the term taken from the foreign language has no equivalent meaning in the local language that the advertisement is being broadcasted. However, this provision does not prevent the use of the naming and logo of a business in a foreign language;
5. the provisions specified from Sub-Article (1) to (4) of this Article shall not be applicable to advertisements to be disseminated:
   A. using fliers, brochures, leaflets, or using papers;
   B. on product packaging or containers;
   C. using outdoor advertisements of diplomatic and other international institutions.

ክፍል አራት

የውጭ ማስታወቂያ የጥራት ደረጃና ብቃት፣ ስርጭት እና የአገልግሎት ክፍያ

፲፮. የውጭ ማስታወቂያ የጥራት ደረጃና ብቃት

፩. ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ከመሰራጨቱ በፊት የብቃትና የጥራት ደረጃ መመሪያ የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፤

፪. ባለስልጣኑ በተለያዩ ቦታዎች ስለሚተከሉ ወይም ስለሚቀመጡ የውጭ ማስታወቂያዎች እና የተለያዩ የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶች ሲዘጋጁና ሲሰራጩ ሊከተሉት የሚገባውን የብቃትና የጥራት ደረጃ በመመሪያ ይወስናል፡፡

፲፯. የውጭ ማስታወቂያ የቆይታ ጊዜ

፩. በመሬት፣ በሕንፃ፣ በንግድ ድርጅት፣ በአጥር ወይም በማናቸውም መሰል አካል ላይ የሚተከል፣ የሚለጠፍ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ የቆይታ ጊዜ ማስታወቂያው የተዘጋጀበትን መሳሪያ እና ስምምነት መሰረት በማድረግ በባለስልጣኑ ይወሰናል፤

፪. የውጭ ማስታወቂያው ፈቃድ የሚጠናቀቅበት ጊዜ በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ መፃፍ ይኖርበታል፤

፫. ከአንድ ወቅታዊ ሁነት ጋር በተያያዘ ለአጭር ጊዜ የሚተከል፣ የሚለጠፍ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ወቅታዊ ሁነቱ ከመከናወኑ በፊት ከአንድ (፩) ወር በላይ እንዲሁም ወቅታዊ ሁነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከሰባት (፯) ቀናት በላይ መቆየት የለበትም፤ የማጠናቀቂያ ጊዜ ካለቀ የማስታወቂያ አሰራጩ አካል ማስታወቂያውን በማንሳት ቦታውን የማስረከብ ኃላፊነት አለበት፤

፬. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተደነገገው ድንጋጌ ለትርፍ ያልተቋቋመ የመንግስት መሥሪያ ቤት በሚያሰራጨው የሕዝብ ማስታወቂያ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

Part Four

The Quality and Standard Level, Distribution, and Service Charge of Outdoor Advertisement

16. The Quality and Standard Level of Outdoor Advertisement

1. Any outdoor advertisement should meet the quality and standard requirements before its distribution;
2. The authority shall determine the quality and standard requirements for outdoor advertisements that will be erected or placed in various areas and the preparation and dissemination methods of various outdoor advertisements.

17. Duration of an Outdoor Advertisement

1. The duration of an outdoor advertisement that will be erected, posted, or disseminated in any manner on land, buildings, business organizations, fences, or any similar structures shall be specified by the authority based on the material that the advertisement was prepared and the existing agreement;
2. The expiry date of the outdoor advertisement should be written on the advertisement board;
3. An outdoor advertisement that will be erected, posted, or disseminated in any manner for a short period concerning a current event should not be displayed more than one (1) month before its happening and more than seven (7) days after the event is over; the advertisement promoter shall have the responsibility to remove the advertisement and handing back the space when the time is over;
4. The provision stated under Sub-Article (3) of this Article shall not be applicable to public advertisements disseminated by non-profiting governmental offices.

፲፰. <u>የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ የቆይታ ጊዜ</u>

፩. አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶችን በመጠቀም የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ ማሰራጨት ይችላሉ፤

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚሰራጭ የምርጫ ውድድር የውጭ ማስታወቂያ፡-

ሀ) የቆይታ ጊዜው በሚመለከተው አካል በምርጫ ወቅት የሚወሰነው የምርጫ የቆይታ ጊዜ ይሆናል፤

ለ) የተወሰነው የምርጫ ቆይታ ጊዜ በተጠናቀቀ በ፴ ቀናት ውስጥ ማስታወቂያው መነሳት ይኖርበታል፤

ሐ) ማስታወቂያው ሌሎች ሕጎችንና የምርጫ ሕግን አክብሮ መሰራጨት ይኖርበታል።

፲፱. <u>የአገልግሎት ክፍያ እና የሚከፈልበት ጊዜ</u>

፩. የውጭ ማስታወቂያ በማናቸውም መንገድ ከመሰራጨቱ በፊት ለፈቃድ ሰጪው የአገልግሎት ክፍያ መከፈል አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ የአገልግሎት ክፍያዎች ለመሰብሰብ አመቺ ሆኖ ባገኘነው መንገድ ሌላ ሰው ሊወክል ይችላል፤

፫. በምስልና በፅሁፍ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ የክፍያ ተመን በማስታወቂያ ሰሌዳው ስፋት በሜትር ካሬና በቆይታ ጊዜው የሚሰላ ሲሆን፤ በድምፅ የሚተዋወቅ የውጭ ማስታወቂያ በሚወስደው ጊዜ የሚሰላ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

፬. የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ዓመቱን ጠብቆ የአገልግሎት እድሳት ማድረግ ይኖርበታል።

18. <u>Duration of Election Campaign Advertisement</u>

1. Political parties and candidates that are registered and active as per the law can use various outdoor advertisement methods to advertise their election campaign during the election period;
2. An election campaign outdoor advertisement that will be disseminated pursuant to Sub-Article (1) of this Article:
   A. the duration of the advertisement shall be that of the election period to be decided by the relevant organ during the election;
   B. The advertisement should be removed within 30 days after the end of the election period;
   C. The advertisement should be broadcasted in compliance with other laws and the election law.

19. <u>Service Charge and Payment Period</u>

1. The service charge must be paid to the licensing authority before the dissemination of an outdoor advertisement by any means;
2. Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the authority may employ convenient ways and delegate another person to collect service charges;
3. The payment rate for an outdoor advertisement to be disseminated using images and texts shall be calculated based on the width of the advertisement board in meter square and its duration; the outdoor advertisement to be broadcasted using voice shall be calculated as per the time it takes; the details shall be specified through a directive;
4. An individual who obtains an outdoor advertisement license should renew his service license annually.

፳. ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ስለመሆን

፩. የሃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የዲፕሎማቲክ መስሪያ ቤቶች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለእምነት ወይም ለዓላማ ማስፈጸሚያ እንዲውሉ በተፈቀዱላቸው ቦታዎች ወይም ንብረቶች ላይ የማስተዋወቅ ሥራ ቢያካሂዱ ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ናቸው፣

፪. የፖለቲካ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ድርጅት፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የመሳሰሉት ለአላማ ማስፈጸሚያ እንዲያውሉ ከተፈቀዱላቸው ቦታዎች ወይም ንብረቶች ውጭ የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ ለማካሄድ ሲጠይቁ፡-

ሀ) በህግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ በምርጫ ወቅት ምርጫን ለመወዳደር፣ የስብሰባ ጥሪ እና መሰል ማስታወቂያዎች ለማሰራጨት፣

ለ) መንግስታዊ ድርጅቶች ወይም ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ማስታወቂያዎች ለማሰራጨት፣

ሐ) ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ለህብረተሰቡ ወይም አለም አቀፋዊና አህጉራዊ ህብረትን ወይም ግንኙነት ለማጠናከር የሚውል የውጭ ማስታወቂያ ለማስተላለፍ ሲፈልጉ ለአፅድር ጊዜ ባለስልጣኑን በማስፈቀድ ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ይሆናሉ፣

20. Exemption from Service Charge

1. Religious institutions, political parties, non-benefiting non-governmental organizations, diplomatic institutions, and international organizations are exempted from service charges when they carry out advertisements on spaces or properties that are allowed to be used for religious purposes or to attain some kind of objective;
2. When political parties, governmental organizations, non-benefiting non-governmental organizations, international organizations or charity organizations and similar others submit a request to carry out an outdoor advertisement other than the spaces or properties that are allowed to be used to attain an objective shall be exempted from service charge for a short period by the permission of the authority:
   A. to disseminate election campaign, making meeting announcements and similar advertisements during an election period when it is a registered and active political party as per the law;
   B. to disseminate advertisements that have economical and social benefits for the society when it is governmental organizations or non-profiting non-governmental organizations or charities;
   C. to broadcast advertisements that strengthen community-based or international and continental cooperation or relations when it is international and continental organizations;

፫. በበጎ ፈቃደኝነት አካባቢዉን ያለማ ድርጅት ወይም ግለሰብ ባለማዉ አካባቢ ያለማውን መንከባከብ እንዳለ ሆኖ ስለ ድርጅቱ ወይም ሥራዉ የውጭ ማስተዋወቂያ የማሰራጨት ፈቃድ አውጥቶ ከከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር በሚያደርገው የውል ስምምነት የጊዜ ገደብ ድረስ ሲያሰራጭ ከክፍያ ነጻ ይሆናል፤ በዚሁ መሠረት፡-

ሀ) በበጎ ፈቃደኝነት ያለማው ሰው ቦታው ላይ ሌላ ሰው እሱን ተክቶ ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ሊወክል ወይም አሳልፎ ሊሰጥ አይችልም፤

ለ) የግንባታ፣ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የቀለምና መሰል ስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ግንባታው በሚከናወንበት ሕንፃ፣ ቦታ ወይም መሳሪያ ላይ ስማቸውንና ስራቸውን ለማስተዋወቅ የሚያስቀምጡት የውጭ ማስታወቂያ ከክፍያ ነጻ ይሆናል፤

ሐ) በባለሥልጣኑ ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ እንዲሆኑ የተወሰነለት ሰው የሚያሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ ከክፍያ ነፃ ይሆናል።

፳፩. <u>የአገልግሎት ክፍያ ስለመክፈል</u>

የዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ ድንጋጌ ቢኖርም ድርጅቶቹ ለዓላማ ማስፈጸሚያ ባልተፈቀዱላቸው ይዞታዎች ወይም ንብረቶች ላይ የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ቢያካሂዱ የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

፳፪. <u>የክፍያ ውሳኔ ማሳወቂያና ክስ አቀራረብ</u>

፩. ፈቃድ ሰጪው የአገልግሎት ክፍያውን ላልከፈለ ሰው የአገልግሎት ክፍያ ውሳኔ ማሳወቂያ እንዲደርሰው ማድረግ ይኖርበታል፤

፪. ከፈቃድ ሰጪው የውሳኔ ማሳወቂያ በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ክፍያ አጠቃሎ ያልከፈለ ወይም በ፲ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ቅሬታ ያላቀረበ ሰው ካለ ባለሥልጣን መሥያ ቤቱ ማስታወቂያው እንዲነሳ በማድረግ የአገልግሎት ክፍያውንና ማስታወቂያውን ለማንሳት ያወጣውን ወጪ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ መጠየቅ ይችላል።

3. An organization or individual that carries out voluntary development activities on a given space, while developing the area, shall be exempted from payment for disseminating an outdoor advertisement about his organization or work through obtaining a license and entering into a contract with the urban beautification and green development bureau for a specific period; According to this:

A. an individual that carries out voluntary development activity cannot delegate another person to disseminate an advertisement on the given space on his behalf or transfer the thereof;

B. the outdoor advertisements of construction, water, electric, painting, and other similar works contractors and consultants which will be placed on the undertaking construction building, space, or material to advertise their name and work shall be free from payment;

C. an individual who is exempted from service charge by the authority, his outdoor advertisement shall be from payment.

21. <u>Paying Service Charges</u>

Notwithstanding the provisions specified under Article 20 of this Regulation, the organizations are obliged to pay service charges if they disseminate outdoor advertisements on landholdings or properties that are not allowed to carry out an advertisement to attain a certain objective.

22. <u>Payment Decision Notification and Lawsuit</u>

1. The licensing authority should send a notification for a service charge decision for an individual who fails to do so;
2. If an individual fails to pay the required payment within 30 days or submit a complaint to the authority within 10 days of receiving the payment decision notification, the authority shall remove the advertisement and request the service charge and the expense for removing the advertisement by taking the case to the relevant court.

ክፍል አምስት

የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ አዘጋጅና አሠራጭ ግዴታና ኃላፊነት

፳፫. ስለ የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ግዴታ

፩. ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ አሰራጭ ወይም የራሱን ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት በውጭ ማስታወቂያ በማናቸውም መንገድ የሚያሰራጭ አካል በማስታወቂያ አስነጋሪው የቀረበለትን መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤

፪. የሚሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ሥነ-ምግባርን የሚጻረር ይዘት ወይም አቀራረብ የሌለው መሆኑን ማስታወቂያ አሰራጩ ባለሥልጣኑ ያዘጋጃውን የግዴታ ቅጽ በመፈረም ያረጋግጣል፡፡

፳፬. ስለ ውጭ ማስታወቂያ ሪከርድ ወይም ቅጂ

ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ አዘጋጅ፣ አሰራጭ ወይም አስነጋሪ፡-

፩. የአንድን የተተከለ፣ የተለጠፈ ወይም በማናቸውም መንገድ የተሰራጨ የውጭ ማስታወቂያን ቅጅ ወይም ሪኮርድ ቢያንስ ለ፮ ወራት ይዞ ማቆየት አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተያዘውን የማስታወቂያ ሪኮርድ፣ ቅጅና መረጃ ከዚህ ደንብ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ምክንያት አግባብ ያለው የመንግሥት አካል እንዲቀርብለት ሲጠይቅ በራሱ ወጭ ማቅረብ አለበት፡፡

፳፭. ቁጥጥር እንዲደረግ ስለመፍቀድ

ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ አሰራጭ ወይም አስነጋሪ በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና ደንቡን መሰረት አድርጎ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ለሚደረግ ቁጥጥር የአገልግሎት መስጫ ድርጅቱን ክፍት ማድረግና የሚጠየቀውን ሰነድ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

Part Five

Obligation and Responsibilities of an Advertiser, Advertisement Producer, and Advertisement Promoter

23. Obligation about Outdoor Advertisement Activities

1. Any outdoor advertisement promoter or organ that disseminates his own product, service, or company in any means through an outdoor advertisement shall have the obligation to verify the correctness of the information provided by the advertiser;
2. The advertisement promoter should verify, as per the provision specified under Sub-Article (1) of this Article, that the outdoor advertisement to be disseminated does not contain any content or presentation that violates good morals by signing the binding form prepared by the authority.

24. About a Record or Copy of the Outdoor Advertisement

Any producer, promoter, or advertiser of an outdoor advertisement shall:

1. keep the copy or record of an outdoor advertisement that was erected, posted, or disseminated by any means for 6 months at least;
2. avail the record, copy, and evidence of the advertisement maintained as per Sub-Article (1) of this Article to the relevant government organ at his own expense upon the request of it by the thereof concerning the implementation of this Regulation.

25. Approval for Inspection Activities

Any outdoor advertisement promoter or advertiser shall have the obligation to open his service-providing organization and present the required documents for inspection activities that will be carried out according to the Proclamation, this Regulation, and directives to be issued as per this Regulation.

፳፮. <u>የውጭ ማስታወቂያ አሰራጭ እና አስነጋሪ ኃላፊነት</u>

ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የአዋጁንና የዚህ ደንብ ድንጋጌን በመተላለፍ የተሰራጨ ማስታወቂያ በውጭ ማስታወቂያ ሥራ እና አሰራጩ ፈቃድ እንደተሰራጨ ተቆጥሮ እንደ ኃላፊነታቸው መጠን በአንድነት ወይም በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

<u>ክፍል ስድስት</u>
<u>በቅንጅትና በትብብር ስለመስራት</u>

፳፯. <u>በቅንጅትና በትብብር ስለመሥራት</u>

፩. ይህን ደንብ ለማስፈጸም ባለሥልጣኑ እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ የኮሚኒኬሽን ቢሮ፣ የደንብ ማክበር ባለሥልጣን እና የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በቅንጅትና በትብብር የመስራት ኃላፊነት አላባቸው፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት አስፈጻሚ አካላት ለውጭ ማስታወቂያ መትከያ ቦታዎች ዝግጅት፣ ለይዘትና አቀራረብ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ በሕግ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ማከናወን ይኖርባቸዋል፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተገለጹት አስፈጻሚ አካላት በተጨማሪ ለቅንጅት ስራው አስፈላጊ መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲታመንበት ሌሎች አስፈጻሚ ተቋማት በትብብር ጥምረቱ ውስጥ ተካተው እንዲሰሩ ይደረጋል፤

፬. የቅንጅት ስራውን የሚያስተባብረው ባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

26. <u>Responsibilities of Outdoor Advertisement Promoter and Advertiser</u>

Unless contrary evidence is submitted, the outdoor advertisement promoter and advertiser shall be jointly or individually held accountable to the extent of their responsibility for a broadcasted advertisement by violating the provisions of the proclamation and this Regulation by considering that it was disseminated by the approval of the outdoor advertisement promoter.

<u>Part Six</u>
<u>About Working in Coordination and Cooperation</u>

27. <u>About Working in Coordination and Cooperation</u>

1. The authority shall have the responsibility to work in a coordinated and cooperative manner with the Addis Ababa city government land development and management bureau, communication bureau, code enforcement authority, and environmental protection authority for the implementation of this Regulation;
2. The executive organs indicated under Sub-Article (1) of this Article shall carry out their duties and responsibilities given by the law for the preparation of spaces for erecting outdoor advertisements, content, and presentation inspection activities, and taking measures;
3. In addition to the executive organs stated under Sub-Article (1) of this Article, other executive institutions shall be included in the cooperation coalition and carry out activities when such has been considered necessary by the authority;
4. The authority oversees the coordination activities.

፳፰. በባለስልጣኑ ስለሚደራጅ ወይም ስለሚወከል አካል

ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች በስሩ በየደረጃው በተቋቋሙ አካላት እንዲከናወኑ ማድረግ ወይም ሥልጣንና ተግባሩን ማከናወን ለሚችል የከተማው አስተዳደር የሚመለከተው አካል ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በውክልና በመስጠት ማሰራት ይችላል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፱. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት።

፴. የውጭ ማስታወቂያን አለአግባብ ስለማስወገድ

ማንኛውም ሰው ፈቃድ በማግኘት የተተከለ፣ የተለጠፈ ወይም በማናቸውም መንገድ የተሰራጨ ሕጋዊ የውጭ ማስታወቂያን ሆነ ብሎ የማስታወቂያ አስነጋሪውን ለመጉዳት በማሰብ ማስወገድ የለበትም።

፴፩. አቤቱታ ስማቅረብ

፩. ከውጭ ማስታወቂያ ጋር በተያያዘ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተሰራጨ ማንኛውም ማስታወቂያ መብቱ የተጣሰ ሰው የማስታወቂያው ስርጭት ፈቃድ እንዲታገድለትና ማስታወቂያው እንዲወገድለት ለፈቃድ ሰጪው አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ሥልጣን ላለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብን የሚከለክል አይሆንም፣

፫. የአቤቱታ አቀራረብና አወሳሰን ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

28.

About an Organ to be Organized or Delegated by the Authority

The authority can totally or partially delegate its duties and responsibilities given to it by this Regulation to those organs that are established at every level hierarchically or to an organ of the city government that can carry out the duties and responsibilities. The details shall be specified through a directive.

Part Seven

Miscellaneous Provisions

29. Duty to Cooperate

Any person shall be duty-bound for the implementation of this Regulation.

30. About Inappropriate Removal of Outdoor Advertisements

Any person should not remove an authorized outdoor advertisement that is erected, posted, or disseminated in any manner in order to intentionally harm the advertiser.

31. Complaint Submittal

1. Any person whose rights have been violated in relation to a disseminated outdoor advertisement through violating the provisions of this Regulation may submit his complaints to the licensing authority for the suspension of the advertisement broadcasting license and the removal of the advertisement;
2. The provision stated under Sub-Article (1) of this Article shall not preclude the lodging of a suit to the relevant judicial organ;
3. The complaint submittal and decision-making procedure shall be specified through a directive to be issued by the authority.

፴፪. ይግባኝ ስለማቅረብ

፩. በፈቃድ ሰጪው ስር በየደረጃው ባሉ አስፈፃሚ አካላት ወይም በባለሥልጣኑ በተወከለ አካል በተሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ላይ አቤቱታ ያለው ሰው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በፅሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፤

፪. ፈቃድ ሰጪው የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው ከ፴ ቀናት ባነሰ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፤

፫. ሥልጣን ለተሰጠው የመንግሥት አካል ይግባኝ የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለስልጣኑ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

፴፫. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩. ይህ ደንብና ደንቡን መሰረት አድርጎ የሚወጣው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በሕግ መሰረት ፈቃድ ተሰጥቶት እና የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎበት የተተከለ፣ የተለጠፈ ወይም በማናቸውም መንገድ የተሰራጨ የውጭ ማስታወቂያ የአዋጁንና የደንቡን ድንጋጌዎች የሚያሟላ ከሆነ በዚህ ደንብ መሰረት ፈቃድ እንዳገኘ ይቆጠራል።

፪. ይህ ደንብና ደንቡን መሰረት አድርጎ የሚወጣው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም ፈቃድ ቢሰጠውም የአዋጁን፣ የደንቡንና ደንቡን መሰረት አድርጎ የሚወጣውን መመሪያ ድንጋጌዎች የማያሟላ የውጭ ማስታወቂያ የተከለ ወይም በማናቸውም መንገድ ያሰራጨ የማስታወቂያ አሰራጭ ፡-

32. About Submittal of an Appeal

1. Any person who has a complaint against a decision given by executive organs at every level under the licensing authority or an organ delegated by the authority could submit his complaint in writing to the authority within 15 working days upon receiving the decision;
2. The licensing authority should make its decision in less than 30 days upon receiving the complaint of the applicant;
3. Notwithstanding the right to submit an appeal to the relevant government organ, the decision made by the authority shall be a final one.

33. Transitional Provisions

1. If an outdoor advertisement that was erected, posted, or disseminated in any manner through having a license and paid service charges as per the law before the issuance of this Regulation and directive to be issued according to the thereof complies with the provisions of the Proclamation and the Regulation, it shall be considered as obtaining a license based on this Regulation;
2. If any advertisement promoter that has erected or disseminated an outdoor advertisement in any manner without having a license before the issuance of this Regulation or directive to be issued according to the thereof or does not comply with the provisions of the Proclamation, Regulation, and directive to be issued based on the Regulation despite having a license should:

ሀ) ይህ ደንብ ከፀናበት ጊዜ ወይም ደንቡን መሰረት አድርጎ የሚወጣው መመሪያ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በ፩ ወር ጊዜ ውስጥ የውጭ ማስታወቂያው እንዲሰራጭ ማመልከቻውን በፅሁፍ ለባለስልጣኑ ማቅረብ እና የተሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አሟልቶ ከተገኘ ማስታወቂያው እንዲሰራጭ የተፈቀደለትና የተመዘገበ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ መያዝ እና ለማስታወቂያው የተወሰነውን ክፍያ መክፈል አለበት።

ለ) የተሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ የዚህን ደንብና ደንቡን መሰረት አድርጎ የሚወጣውን መመሪያ ድንጋጌዎች ባለማሟላቱ እንዲሰራጭ ፈቃድ ካላገኘ ማስታወቂያውን ማንሳት ወይም ማስወገድ አለበት።

፫. ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ለውጭ አገር ዜጋ በውጭ ማስታወቂያ ሥራ እንዲሰማራ እና የሌሎችን ሰዎች የውጭ ማስታወቂያ እንዲያሰራጭ የተሰጠ ፈቃድ መሰረዝ ይኖርበታል፤

፬. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሰረት የውጭ ማስታወቂያ ስርጭት ፈቃዱ የተሰረዘበት የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ተክሎ ለሌላ ሰው የሚያከራየውን የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳ ፍሬም፣ የውጭ ማስታወቂያ መለጠፊያ ሳጥን ወይም ቦርድ ወይም መሰል የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መሳሪያ ወይም ተያያዥ ንብረቶችን በማንሳት መውሰድ ወይም ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ይችላል።

A. submit an application in writing to the authority to broadcast the outdoor advertisement within a month upon the regulation or the directive to be issued as per the regulation is in effect, and have evidence for the approval to disseminate the advertisement and its registration if the disseminated advertisement complied with the provisions of this Regulations; and make the required payment for the advertisement.

B. remove the advertisement if the disseminated outdoor advertisement did not obtain a license for dissemination due to its failure to comply with the provisions of this Regulation or directive to be issued as per the Regulation.

3. A license granted, before the issuance of this Regulation, for a foreign national to engage in an outdoor advertisement business and disseminate an outdoor advertisement of another individual should be revoked;

4. The foreign nation or company whose license has been revoked according to Sub-Article (3) of this Article can take the outdoor advertisement billboard frame, posting box or board, or similar materials or related properties used for outdoor advertisement purposes that were posted and leased before the issuance of this Regulation or transfer it to another person.

፴፬. አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ቅጣት

በማስታወቂያ አዋጁ ቁጥር ፯፻፶፱/፪ሺ፬ የተደነገገው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ፡-

፩. በዚህ ደንብ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ በሚከፈልበት ጊዜ ውስጥ የሚፈለግበትን የአገልግሎት ክፍያ በሙሉ ያልከፈለ ማንኛውም ሰው ክፍያውን ማጠናቀቅ ካለበት ከመጨረሻው ቀን በኋላ ክፍያውን ላዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ከሚፈለግበት የአገልግሎት ክፍያ ከመቶ አስር ፐርሰንት መቀጮ እየተጨመረበት ይከፍላል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሳይከፍል ከሁለት ወራት በላይ ከቆየ የግንባታ ፈቃድ ሰጭው የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳውን በማንሳት ይወርሳል፤ ያነሳበትንም ወጪ በህግ ይጠይቃል፣

፫. የዚህን ደንብ ወይም ሌሎች ህጐች ድንጋጌዎች ባለማክበር የውጭ ማስታወቂያ በደንብ ማስከበር ባለስልጣን አማካይነት የተነሳበትና ለዚሁ የወጣውን ወጪ የከፈለ ሰው በከተማው ክልል በማንኛውም ቦታ የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ወይም የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ ጥያቄ ቢያቀርብ ለአንድ ዓመት እንዳይስተናገድ ይታገዳል፣

፬. ለአጭር ጊዜ በፖስተር፣ በስቲከር፣ በባነር ለሚለጠፍና ለሚንጠለጠል እንዲሁም በብሮሸር፣ በሊፍሌት እና በበራሪ ወረቀት የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ በተጨማሪ ለሚቆየው ለእያንዳንዱ ቀን የአገልግሎት ክፍያው ሁለት እጥፍ ይከፈልበታል፡፡ ሆኖም የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ሳምንት የሚበልጥ ከሆነ ባለስልጣኑ በራሱ ወጪ ያነሳዋል፤ ወጪውንም የማስታወቂያዉ ባለቤት እንዲተካ ያደርጋል፣

34. Administrative Measure or Penalty

Notwithstanding the penalties specified under the Advertisement Proclamation Number 759/2004, any person that violates the provisions of this Regulation and commits an offense should:

1. pay the required total payment within the payment period of a service charge according to this Regulation shall pay a ten percent fine of the required service charge for each month for delay at the end of the last day of the stated payment period;
2. if the required payment according to Sub-Article (1) of this Article is not paid for more than two months, the construction permit licensing organ shall remove and confiscate the outdoor advertisement board; it shall demand its expenses for removal as per the law;
3. any person whose outdoor advertisement was removed by the code enforcement authority due to failure to comply with his Regulation and other laws and paid the penalties for thereof shall be suspended for one year for engaging in any outdoor advertisement business or having an outdoor advertisement license in any areas within the vicinity of the city;
4. the service payment for the permit of an outdoor advertisement to be disseminated for a short period using posters, stickers, and banners that will be posted and hung on as well as using brochures, leaflets, and fliers shall be two folds of the service charge for each day for the longer period it stays. However, if the duration of stay is more than a week, the authority shall remove it at its own expense; it shall demand the owner of the advertisement to cover the expense;

፭. ያለፈቃድ ወይም ከተፈቀደለት ሰዓት ውጭ በመኪና ላይ የማስታወቂያ ሥራ ሲሰራ የተገኘ አሽከርካሪ ብር ፩ሺ፮፻ (አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ይቀጣል፣ ማስታወቂያው በመኪናው ላይ የተለጠፈ ከሆነ እንዲያነሳ ይደረጋል፣

፮. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ ብር) መቀጮ ይከፍላል፣

፯. የዚህን ደንብ ድንጋጌ በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕጉ መሠረት የሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ በአደባባይ ወይም ሕዝብ በሚያየው ቦታ መልካም ሥነ-ምግባርን ወይም መልካም ጠባይን የሚነካ ድርጊት አስቦ የፈጸመ እንደሆነ፣ የተከለከለ የውጭ ማስታወቂያዎችን ያሰራጨ እና ገድብ የተደረገባቸውን ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ያደረገ ብር ፬ሺ (አራት ሺህ ብር) መቀጮ ይከፍላል፣

፰. በዚህ ደንብ የተሰጠውን ክልከላና ግዴታ ያልተወጣ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፣

፴፭. ስለተሻረ እና ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ሕግ

፩. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውጭ ማስታወቂያ ደንብ ቁጥር ፴፯/፪ሺ፫ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፪. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚቃረኑ የከተማው ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ያወጧቸው መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

5. a driver who is engaged in an advertising business using vehicles without a license or out of the permitted hours shall pay a fine of birr 1,600.00 (one thousand six hundred birr); if the advertisement was posted on the car, he shall be forced to remove it;
6. any individual that violates the provisions of this Regulation shall pay a fine of birr 2,000.00 (two thousand birr);
7. any person that violates the provisions of this Regulation and commits an offense, except those matters that incur criminal liability, that intentionally harms good morals or good behaviour, disseminates prohibited outdoor advertisements, and causes the dissemination of banned advertisements shall pay a fine of birr 4,000.00 (four thousand);
8. any official or employee that does not carry out the prohibitions and obligations specified under this Regulation shall be held accountable according to the relevant laws.

35. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Addis Ababa city government outdoor advertisement Regulation number 37/2011 is repealed by this Regulation.
Any mass media disseminating advertisements shall disseminate impartially and fairly advertisements submitted to it by advertisers and advertising agents.

30. Responsibilities of Advertiser, Advertising Agent and Advertisement Disseminator

Unless proved to the contrary, any advertisement disseminated in breach of the provisions of this Proclamation shall be presumed to have been conducted with the consent of the advertiser, advertising agent and advertisement disseminator, and they shall be jointly and severally liable according to their degree of responsibility.

PART EIGHT

MISCELLANEOUS PROVISIONS

31. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ ensure that advertisement is conducted in such a manner that contributes to the economic, social and political development of the country;

2/ in consultation with the appropriate bodies, issue competency requirement and code of conduct for advertising activity;

3/ examine and suspend any advertisement, other than outdoor advertisement, disseminated in violation of the provisions of this Proclamation, and order the dissemination of a counter advertisement;

4/ transmit to the appropriate government body any information relevant for the prosecution of any offender who disseminated an advertisement in violation of the provisions of this Proclamation;

5/ provide technical support to the appropriate regional bodies regarding the enforcement of this Proclamation with respect to outdoor advertisements;

6/ design strategies and provide support for developing the advertising profession and for making the sector self regulated.

፴፪. የሸማቾች ማኅበር

አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም የሸማቾች ማኅበር፡-

፩/ ይህን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ ከባለሥልጣኑና ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር ይተባበራል፤

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ በመተላለፍ በተሰራጨ ማስታወቂያ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን አባላቱን በመወከል የፍትሐ ብሔር ክስ የመመስረት መብት ይኖረዋል።

32. Consumers Association

Any consumers association established under the relevant law shall:

1/ cooperate with the Authority and the appropriate government bodies in the enforcement of this Proclamation;

2/ have the right to institute a civil suit on behalf of its members who have sustained damages as a result of an advertisement disseminated in violation of the provisions of this Proclamation.

፴፫. ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርብ አቤቱታ

፩/ ከውጭ ማስታወቂያ በስተቀር የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተሰራጨ ማንኛውም ማስታወቂያ መብቱ የተጣሰ ሰው የማስታወቂያው ስርጭት እንዲታገድለት ወይም የአፀፋ ማስታወቂያ እንዲወጣለት ማስታወቂያው ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ሥልጣን ላለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብን የሚከለክል አይሆንም።

33. Submission of Complaints to the Authority

1/ Any person whose rights are infringed by the dissemination of any advertisement, other than outdoor advertisement, in violation of the provisions of this Proclamation may submit complaints, within six months from the date of the dissemination of the advertisement, to the Authority to obtain an order of suspension of disseminating the advertisement or the dissemination of a counter advertisement.

2/ The provision of sub-article (1) of this Article may not be construed to preclude the institution of a suit with the competent judicial body.

፴፬. ቅጣት

፩/ በሌላ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፡-

ሀ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭(፩) እና (፪) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ አንቀጽ ፷(፩) መሠረት ይቀጣል፤

ለ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭(፫)፣ አንቀጽ ፭(፭)፣ አንቀጽ ፮(፪)፣ አንቀጽ ፮(፫)፣ አንቀጽ ፮(፬)፣ አንቀጽ ፲፣ አንቀጽ ፲፩፣ አንቀጽ ፲፪(፪)፣ አንቀጽ ፲፫፣ አንቀጽ ፲፫(፩)፣ አንቀጽ ፲፭(፩)፣ አንቀጽ ፲፭(፪)፣ አንቀጽ ፲፭(፫)፣ አንቀጽ ፲፮፣ አንቀጽ ፲፯፣ አንቀጽ ፲፰፣ አንቀጽ ፲፱፣ አንቀጽ ፳፫፣ አንቀጽ ፳፭፣ አንቀጽ ፳፮፣ አንቀጽ ፳፯፣ አንቀጽ ፳፱(፫)፣ አንቀጽ ፳፱፣ አንቀጽ ፳፱ ወይም አንቀጽ ፳፱ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፲ሺ በማያንስና ከብር ፭፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

34. Penalty

1/ Unless punishable with more severe penalty under other law, any person found guilty of violating:

a) Article 5(1) and (2) of this Proclamation shall be punishable in accordance with Article 60(1) of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686/2010;

b) Article 5(3), Article 5(5), Article 6(2), Article 6(3), Article 6(4), Article 10, Article 11, Article 12(2), Article 13, Article 15(1), Article 15(2), Article 15(3), Article 16, Article 17, Article 18, Article 19, Article 20, Article 21, Article 22, Article 23, Article 24, Article 26(3), Article 27, Article 28 or Article 29 of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr 10,000 and not exceeding Birr 100,000;

ሐ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፮(፩)፣ አንቀጽ ፯፣ አንቀጽ ፰፣ አንቀጽ ፱፣ አንቀጽ ፲፪(፩)፣ አንቀጽ ፲፬፣ አንቀጽ ፲፭(፬)፣ አንቀጽ ፲፭(፭)፣ አንቀጽ ፳፭(፩)፣ አንቀጽ ፳፭(፪) ወይም አንቀጽ ፳፭(፬) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፩፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

መ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፳፫(፩) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፴ሺ በማያንስና ከብር ፪፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው የገንዘብ መቀጮ በተጨማሪ ጥፋተኛ የሆነው ሰው ከሕገ ወጥ ማስታወቂያ ሥራው ያገኘው ገቢ ይወረሳል።

c) Article 6(1), Article 7, Article 8, Article 9, Article 12(1), Article 14, Article 15(4) , Article 15(5), Article 26(1), Article 26(2) or Article 26(4) of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr 20,000 and not exceeding Birr 150,000;

d) Article 25(1) of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr 30,000 and not exceeding Birr 250,000.

2/ In addition to the fine specified under sub-article (1) of this Article, the income obtained by the convicted person from the illegal advertisement activity shall be confiscated.

፴፭. ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ሕግ

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

35. Inapplicable Law

No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

፴፮. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፫/ ክልሎች የውጭ ማስታወቂያን በሚመለከት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ።

36. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

3/ Regions may issue regulations and directives necessary for the implementation of this Proclamation with respect to outdoor advertisements.

፴፯. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

37. Effective date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፭ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

Done at Addis Ababa, this 27th day of August, 2012.

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

በአዲስ አበባ ከተማ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

ADDIS ABABA CITY CONSTRUCTION PERMIT AND CONTROL AUTHORITY

የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ እና ክትትል ማስፈፀሚያ መመሪያ እና ስታንዳርድ ቁጥር 01/2015



ጥቅምት 01/2015
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ከተማ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት ርዕሰ ከተማ፣ የአፍሪካ መዲና እና የተለያዩ ዓለም አቀፍ፣ የመንግስትና የግል ተቋማት መቀመጫ እንደ መሆኗ ከተማዋ ፈጣን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ትገኛለች። ይህን ተከትሎ በመጠን፣ በዓይነትና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም እያደገና ተለዋዋጭ ሆኖ የመጣውን የውጭ ማስታወቂያ/Out-door Advertising/ አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ በሕግና ሥርዓት መምራት በማስፈለጉ፣

በውጭ ማስታወቂያ ዘርፍ ጤናማ ውድድር እንዲኖር በማድረግ ከዘርፉ የሚገውኝን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ/ገቢ የሚያስገኝና ለዜጎች የስራ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ለዘርፉ ምቹ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፣

የውጭ ማስታወቂያ በሥርዓት ካልተመራ የሕብረተሰቡን መብትና ጥቅም እንዲሁም የአገራችንና ከተማችንን ገጽታ ሊጎዳ ስለሚችል የአካባቢ ጥበቃን፣ የትራፊክ እንቅስቃሴን፣ የከተማችንን ውበትና ገጽታ ለመጠበቅ የጥራት ስታንዳርድ ማውጣት አስፍላጊ በመሆኑ፣ እንዲሁም የማስታወቂያ ወኪሎች፣ አሰራጮችና አስነጋሪዎችን መብት እና ግዴታን በግልጽ መወሰን በማስፈለጉ፣

የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሰልጣን በኢትዮጵያ ስለማስታወቂያ የወጣ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀጽ 36(3) ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተሰጠ ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014 እና በውጭ ማስታወቂያ ደንብ ቁጥር 131/2014 በተደነገገው መሰረት ለባለስልጣኑ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ይህን መመሪያ እና ስታንዳርድ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1.2 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥና ክትትል ማስፈፀሚያ መመሪያ እና ስታንዳርድ ቁጥር 01/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1.3 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፥

1. "**ሚኒስቴር**"፥ ማለት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነዉ።
2. "**ከተማ**"፥ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነዉ።
3. "**አስተዳደር**"፥ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ።
4. "**ባለስልጣን**"፥ ማለት የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው።
5. "**ጽ/ቤት**"፥ ማለት በክ/ከተማና የወረዳ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ነው።
6. **"የደንብ ማስከበር አገልግሎት"**፥ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር አገልግሎትና በክፍለ ከተማ እና ወረዳ የሚገኘው ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ነው።
7. **"ማስታወቂያ"** ማለት የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ እንዲስፋፋ ወይም ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት ወይም ዓላማ እንዲተዋወቅ በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የንግድ ማስታወቂያ ሲሆን የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያንና የግል ማስታወቂያን ይጨምራል።
8. **"የማስታወቂያ ስራ"** ማለት ማስታወቂያ ማዘጋጀትን፣ ማሠራጨትን እና ከማስታወቂያ ጋር ተያያዥነት ያለውን ሌላ ሥራ የሚያካትትሥራ ነው።
9. **"የውጭ ማስታወቂያ/ማስተዋወቅ ሥራ"**፥ ማለት አንድ ሰው አርማውን፣ ምልክቱን፣ ምርቱን፣ አገልግሎቱን፣ ስሙን፣ አድራሻውን፣ ወይም አላማውን እንዲሁም ከስተትን የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስታወቂያውን በከፊል ወይም በሙሉ በመግለጽ ለህዝብ የሚነገር ወይም ለእይታ ግልጽ በሆነ ቦታ የሚካሄድ የማስታወቅ ስራ ነው።
10. **"የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ ዘዴ/መንገድ"**፥ ማለት

    ሀ) በቢል ቦርድ፣ በማስታወቂያ ሰሌዳ፣ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የሚሰራጭ፣

ለ) በሕንጻ፣ በግድግዳ፣ በጣራ ወይም በማናቸውም ስትራክቸር ወይም በትራንስፖርት ተሽከርካሪ፣ በተንሳፋፊ ፊኛ ወይም መሰል ነገር ላይ የሚሳል፣ የሚፃፍ፣ የሚለጠፍ ወይም የሚተከል፣

ሐ) በተንጠልጣይ ነገር፣ በባነር፤በፖስተር፣ በስቲከር፣ በተባዛ በራሪ ወረቀት፣ በብሮሸር፣ ሊፍሌት፣ ፍላየር የሚሰራጭ፣

መ) በድምጽ ካሴት፣ በድምፅ ማጉያ መሳሪያ የሚሰራጭ፣ ወይም

ሠ) በሌላ መሰል ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ሲሆን የመንገድ አቅጣጫ ጠቋሚ፣ የትራፊክና የአውቶቢስ ፌርማታ ምልክትን፣ የመንገድ ስምን ወይም ቁጥርንና መሰል የሕዝብ አገልግሎት መረጃ ሰጪ ምልክቶችን አይጨምርም።

11. **“የማስታወቂያ ወኪል”**፥ ማለት አግባብ ባለው የሀገሪቱ ህግ መሠረት ፈቃድ አውጥቶ በማስታወቂያ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው።

12. **“የውጭ ማስታወቂያ አሰራጭ”**፥ ማለት እንደ አንድ የንግድ ዘርፍ የንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት የማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲሁም የትራንስፖርት ተሽከርካሪ፣ የህንጻ አካልን የማስታወቂያ ሰሌዳ ፍሬምን፣ የማስታወቂያ መለጠፊያ ሳጥንን ወይም ቢልቦርድ ተከሎ በማስለጠፍ ወይም ማናቸውንም መሰል አገልግሎትን ለውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫነት እንዲውል በማድረግ የውጭ ማስታወቂያ የማሰራጨት አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ወይም ድርጅት ነው።

13. **“የማስታወቂያ አስነጋሪ”**፥ ማለት ምርቱ፣ አገልግሎቱ፣ ስሙ፣ አርማው፣ የንግድ ምልክቱ ወይም አላማው የሚተዋወቅለት ሰው ወይም ድርጅት ማለት ነው።

14. **“ፈቃድ ሰጪ አካል”**፥ ማለት የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን እና በሥሩ ያሉ የክ/ከተማና የወረዳ ጽ/ቤቶችን ነው።

15. **“መሪ ፕላን”**፥ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መዋቅራዊ ፕላን ወይም የአካባቢ እድገት /LDP/ ፕላን ነው።

16. **”የህዝብ አገልግሎት“**፥ ማለት መንግስታዊ ተቋማት በሕግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚፈለግባቸውን የስብሰባ ጥሪ፣ ቅስቀሳ የመሳሰሉትን ማድረግን ያጠቃልላል።

17. **“ዋና መንገድ”**፥ ማለት በከተማው መሪ ፕላን ላይ ዋና መንገድ (PAS) ተብሎ የተጠቀሰ መንገድ ነው።

18. **“ዋና ዋና መንገድ”**፥ ማለት በከተማው መሪ ፕላን ላይ ዋና መንገድ (PAS) ወይም ዋና መጋቢ መንገድ (SAS) ወይም ቀለበት መንገድ (RR) ተብሎ የተጠቀሰ መንገድ ነው።

19. **“የውጭ ማስታወቂያ ሠሌዳ”**፥ ማለት በኤሌክትሪክ ወይም በብርሃን የሚሠራ ማስታወቂያ የሚለጠፍበት ሰሌዳ ወይም የማስታወቂያ ሥራ የሚካሄድበት ወይም የሚታይበት በተለጣፊ ጽሑፍ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በስእል ወይም በሌላ ዘዴ የማስታወቂያ ሥራ የሚሠራበት ሠሌዳ ነው።

20. **“አደባባይ”**፥ ማለት በመንገድ መሃል በትራፊክ መሽጋገሪያና ማዟዟሪያ የሚያገለግል ሆኖ ለተለያዩ ሀውልቶች፣ ቅርጻ-ቅርፆች፣ የውኃ ፋውንቴን ግንባታዎችና ለእጽዋት መትከያ የተተወ አረንጓዴ ቦታ ነው።

21. **“አደባባይ ዙሪያ”** ማለት በአደባባይ ዙሪያ በሚገኝ የእግረኛ መንገድ በውጭ በኩል ያለ ለውጭ ማስታወቂያ መትከያ የሚያገለግል ቦታ ነው።

22. **“የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት”**፥ ማለት የውጭ ማስታወቂያ መንገዶችን በመጠቀም ማስታወቂያ መትከል፣ መለጠፍ፣ መሳል፣ መፃፍ፣ ማስቀመጥ ወይም በማናቸውም መንገድ ማሰራጨትንና በድምፅ ማስተዋወቅን ይጨምራል።

23. **"ከህዝብ መልካም ፀባይ ጋር የሚቃረን መልዕክት"** ማለት ፈቃድ ከተሰጠበት ዉጭ ሆኖ ህዝብን ለአመጽ የሚያነሳሳ፣ ከህብረተሰቡ መልካም ጸባይ እና እሴቶች ጋር የማይጣጣም መልእክት ነው።

24. **“ስፖንሰር”**፥ ማለት ማንኛውም ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን በመጠቀም ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተከፈለበት ወይም የከፍያ ቃል የገባ ሰው ወይም ተቋም ማለት ነው።

25. **“የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ”**፥ ማለት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሠራጭ መልዕክት ነው።

26. **“የግል ማስታወቂያ”**፥ ማለት በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የአፋልጉኝ እና ሌላ መሰል ማስታወቂያን ያካትታል።

27. **“አዋጅ”**፥ ማለት የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 ማለት ነው።

28. **“ደንብ”**፥ ማለት የማስታወቂያ ደንብ ቁጥር 131/2014 ማለት ነው።

29. **“ደንብ”**፥ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአገልግሎት ክፍያ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 117/2013 ነው።

30. **“ባለቤት”**፥ ማለት የማስታወቂያ ስራ ድርጅት ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ነው።

31. **“ሰው”**፥ ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት/ዕውቅና የተሰጠው አካል ነው።

32. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

1.4 የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ እና ስታንዳርድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ በውጭ ማስታወቂያ ተግባር በሚመለከት በማናቸውም ሥራዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

/ስለ ውጭ ማስታወቂያ መመሪያ/

የውጭ ማስታወቂያ ሥራ መብት፣ ፈቃድ፣ ደረጃ እና ስርጭት

1.1 በውጭ ማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት

2.1.1 ማንኛውም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ግለሰብ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመና በካፒታሉ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ ድርሻ የሌለበት የንግድ ድርጅት በውጭ ማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት ይኖረዋል፣

2.1.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2.1.1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ በውጭ ማስታወቂያ ሥራ ላይ የመሰማራት መብት ይኖረዋል።

1.2 የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ

ማንኛውም በውጭ ማስታወቂያ ዘርፍ መሰማራት የሚፈልግ ሰው፥

1. የውጭ ማስታወቂያ አገልግሎት የንግድ ስራ ፍቃድ ማውጣት አለበት፣

2. ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ወኪል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2.1 የተደነገገውን አሟልቶ በውጭ ማስታወቂያ ስራ ለመስራት የውጭ ማስታወቂያ አገልግሎት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም የማስታወቂያ አስነጋሪው የራሱን ድርጅት ወይም ምርት ወይም አገልግሎት ለማስተዋወቅ የማስታወቂያ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ማውጣት ሳያስፈልገው ከሚመለከተው አካል የውጭ ማስታወቂያ ይዘቱን በማረጋገጥ እና ከባለስልጣኑ የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ በማውጣት ማስተዋወቅ ወይም ማሰራጨት ይችላል፣ ሆኖም የውጭ ማስታወቂያ አስነጋሪው ይህን ስራ መስራት የሚችለው፥

ሀ. በራሱ የመሬት ይዞታ ውስጥ ሲሆን፣

ለ. በራሱ የንግድ መኪኖች ላይ ሲሆን፣

ሐ. ለንግድ ስራ ከሌላ አካል በተከራየው የንግድ ቦታ ወይም የንግድ ቤት ላይ፣

መ. ሌሎች ለንግድ ስራ በተከራዩት ቦታ ወይም ቤት ላይ የራሱን ምርት/ አገልግሎት ለማስተዋወቅ የተስማሙበት ውል ሲኖር፣

4. ማንኛውም በውጭ አገር ተዘጋጅቶ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ሊደረግ የሚችለው በማስታወቂያ ወኪል አማካኝነት ብቻ ነው።

1.4 ስለውጭ ማስታወቂያ የጥራት ደረጃ

ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ከመሰራጨቱ በፊት በመመሪያውና በስታንዳርዱ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት።

1.5 ስለውጭ ማስታወቂያ ሥርጭት

በማንኛውም ሁኔታ የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት የሚቻለው በባለስልጣኑ እና በስሩ ባሉ በክ/ከተማ እና በወረዳ ፅ/ቤቶች ፈቃድ ብቻ ነው።

ክፍል ሶስት

የውጭ ማስታወቂያ ስርጭትን ስለማቋረጥ

1. ማንኛውም ማስታወቂያ ከተፈቀደለት ይዘት ውጪ ሲሆን፣ ለህግ ወይም ለህዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ መልእክት እንደሚያስተላልፍ በሚመለከተው አካል ከተረጋገጠ፣ በቅድሚያ የማስታወቂያው ባለቤት እስከ አንድ ቀን ወይም በ24 ሰዓት የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያነሳ የማስጠንቀቂያ ጽሁፍ እንዲደርሰዉ በማድረግ የማስታወቂያ ሥራው ይቋረጣል፣

2. በደረሰው ማስጠንቀቂያ መሰረት ለማንሳት ፈቃደኛ ካልሆነ ባለስልጣኑ በራሱ ወጪ አንስቶ ንብረቱን በመውረስ ለማንሳት ያወጣውን ወጪ ከባለቤቱ በህግ ይጠይቃል ከዚህ በተጨማሪም በከተማው ክልል በማንኛውም ቦታ ምርቱንም ሆነ አገልግሎቱን የማስተዋወቅ ስራ ለመስራት ጥያቄ ቢያቀርብ ለአንድ ዓመት እንዳይሳተፍ ይደረጋል፣

3. በማንኛውም ወቅት ሰሌዳው የተተከለበት ቦታ ለሌላ አገልግሎት ሲፈለግ ከፈቃድ ሰጪው በሚሰጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የማስታወቂያ ሰሌዳው ባለቤት እንዲያነሳ በማድረግ ማስታወቂያዉ ይቋረጣል፣

4. ቦታዉ ለልማት ወይም ለማናቸውም የሕዝብ አገልግሎት ወይም ለሌላ አገልግሎት ተፈልጎ ሰሌዳዉ ሲነሳ የኪራይ ወይም የአገልግሎት ዘመኑ ያልተጠናቀቀ ከሆነ ለባለፈቃዱ የቀሪ ወራት ሂሳብ ተሰልቶ ይመለስለታል ወይም ምትክ ቦታ ይሰጠዋል፣ ሆኖም የኪራይ ዘመኑ የተጠናቀቀ ከሆነና በቀጣይ ማስተዋወቅ ከፈለገ ጥያቄው በአዲስ መልክ ይስተናገዳል፣

5. ማንኛውም ሰው የተፈቀደለትን ማስታወቂያ ሥራ ለማቋረጥ ሲወስን ለፈቃድ ሰጪው በአስር ቀናት ውስጥ በጽሁፍ በማሳወቅ ማስታወቂያዉ እንዲቋረጥ ማድረግ ይኖርበታል፣ ለቀሪው የውል ጊዜ የተከፈለው ክፍያ ሳይመለስ ማስታወቂያዉ ይቋረጣል፣

6. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በባለስልጣኑ ፈቃድ ተሰጥቷቸው ከዚህ መመሪያ ወይም ከስታንዳርድ ውጭ የተሰሩ ማስታወቂዎች በአምስት ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንዲነሱ ያደርጋል፣ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ካላነሱ በራሱ ወጪ አንስቶ ንብረቱን በመውረስ ለማፍረስ ያወጣውን ወጪ በህግ ይጠይቃል።

7. በአንቀጽ3.4 የተደነገገው ቢኖርም ምትክ ቦታ የሚሰጠው ቀሪው የሊዝ ዘመን ከአንድ አመት በላይ ከሆነ ነው፤ ከአንድ አመትና ከአንድ አመት በታች የቀረው ከሆነ ለማስታወቂያው የከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ይመለስለታል፤ ወለድ አይታሰብበትም

8. ማስታወቂያው እስከ ተነሳበት ጊዜ ድረስ የሚፈለግበትን የአገልግሎት ክፍያ ይኸው የጊዜ ገደብ ከማብቃቱ በፊት በሙሉ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ሰነድ ለፈቃድ ሰጪው አካል በማቅረብ ምዝገባውን አሰርዞ ማስረጃ መውሰድ አለበት፤ ፈቃድ ሰጪው አካልም ሁኔታውን አጣርቶ በቀረበለት ጥያቄ መነሻ በአስር ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ ማስረጃ መስጠት አለበት

ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ ስለመስጠት

1. ለግንባታ፣ ለልማት ወይም ለማናቸውም የሕዝብ አገልግሎት የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ በማግኘት የተተከለ ወይም የተለጠፈ የውጭ ማስታወቂያን ለማስታወቂያ አስነጋሪው በማሳወቅና ተለዋጭ ቦታ ወይም የቀሪ ወራት ሂሳብ ተሰልቶ እንዲሰጠው በማድረግ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የማስታወቂያው ባለቤት ማስታወቂያውን እንዲያነሳ በማድረግ ማስታወቂያው ስርጭት ይቋረጣል፣ በዚህ ሁኔታ ለተነሳ ማስታወቂያ ካሳ አይከፈልም፣

2. ከንግድ እና ከሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ ስርጭት ጋር በተያያዘ ደንቡን እና መመሪያን በማስፈፀም ሂደት ውስጥ ተነፃፃሪ ፍላጎቶች ሲኖሩ ለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ ቅድሚያ መሰጠት ይኖርበታል።

ለውጭ ማስታወቂያ ቦታ ስለመፍቀድ

ለውጭ ማስታወቂያ የሚሰጡ ቦታወች በሁለት መንገድ ሊፈቀድ ይችላል። መንግስት ይዞታ የሆነ መሬት እና ንብረት ላይ የውጭ ማስታወቂያ ስራ በዋነኛነት የሚሰራበት ሲሆን አገልግሎቱን ለማሳለጥ በሚያመች ሁኔታ ለማከናወን በቀጥታ በምደባ እና በጨረታ የሚፈቀድ ይሆናል።

1. በጨረታ ለውጭ ማስታወቂያ ስራ የሚሰጡ ቦታወች

ሀ. ለውጭ ማስታወቂያ መትከያነት በጨረታ የሚሰጡ ቦታዎች በፍትሃዊነትና በግልፀኝነት መስጠት ይኖርባቸዋል፣

ለ. በዋና መንገድ ላይ ለውጭ ማስታወቂያ መትከያ የተዘጋጁ ቦታዎች እና ሌሎች የከተማው አስተዳደሩ ንብረት የሆኑና ለውጭ ማስታወቂያ መትከያ የተዘጋጁ ቦታዎች በጨረታ የሚሰጡ ይሆናል፣

ሐ. ባለስልጣኑ በወረቀት የሚዘጋጅ ማስታወቂያ ሊለጠፍበት የሚችል የጋራ የማስታወቂያ ሰሌዳ እንደ አስፈላጊነቱ በጨረታ ወይም በቀጥታ ያለውድድር ሊሰጥ ይችላል፣

መ. የውል ጊዜው የተጠናቀቀ የውጭ ማስታወቂያ መትከያ ቦታ የሚተላለፈው በድጋሚ ጨረታ በማውጣት ይሆናል፣

ሠ. በዋናነት ጨረታ የሚወጣባቸው ቦታወች፥

1. ዋና መንገዶች ላይ የሚገኙ ክፍት ቦታወች፣

2. በትልልቅ አደባባዮች ዙሪያ፣

3. በከተማ እና በክ/ከተማ ደረጃ በሚገኙ ፓርኮች፣

4. የቀላል ባቡር መስመር ድልድዮች፣

5. በቀላል ባቡር እና በከተማ አውቶቢስ ላይ የሚለጠፍ/የሚሰቀል/የሚተ ማስታወቂያ፣

6. ቁጥራቸው 50 እና ከዚያ በላይ የሆኑ የመንግስት ተሸከርካሪወች በአንድ ጊዜ ለማስታወቂያ ስራ ሲቀርቡ፣

2. በቀጥታ ለውጭ ማስታወቂያ ስራ በምደባ የሚፈቀዱ ቦታዎች

ከዋና መንገድ ውጭ በሆኑ መንገዶች ላይ ለሚተከሉ የውጭ ማስታወቂያዎች እንደ አስፈላጊነቱ ያለ ጨረታ በአመልካቹ ጥያቄ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል። እንዲሁም በሚከተሉት ቦታወች፣ ቋሚ አካል እና ተሸከርካሪወች ላይ በምደባ ይሰጣል።

ሀ. ለአቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች በማንኛውም ቦታ እስከ 500 ሜትር ራዲየስ፣

ለ. የቀላል ባቡር መስመር ኮንክሪት ምሰሶወች ላይ፣

ሐ. የእግረኛ እና መኪና መሸጋገሪያ ድልድዮች ላይ፣

መ. ማንኛውም ባለቤትነታቸው የመንግስት የሆኑ ንብረቶች ላይ፣

ሠ. ጨረታ ከሚወጣበት መሬት ውጭ በአሉት ክፍት ቦታዎች፣

ረ. አዳዲስ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለዘርፉ የላቀ ፋይዳ እንዲኖረው ለሚያደርጉ፣ የተሸለ ካፒታል ለሚያቀርቡ፣ የተሻለ የስራ እድል ለሚፈጥሩ እና በተሻለ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማሳየት ለሚችሉ አካላት በልዩ ሁኔታ በባለስልጣኑ ማኔጅመንት ሲወሰን፣

ሰ. ለልዩ ልዩ ፕሮግራሞች/ሁነቶች ለአጭር ጊዜ ለሚፈቀድ የውጭ ማስታወቂያ፣

ክፍል አራት

የውጭ ማስታወቂያ ይዘት፣ ቋንቋ እና ፊደል አጠቃቀም

1.6 የውጭ ማስታወቂያ ይዘትና አቀራረብ

1. ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ይዘት፥

ሀ. ማናቸውንም ሕግ ወይም መልካም ሥነ-ምግባርን የማይፃረር አሳሳች ወይም ተገቢ ካልሆነ አገላለጽ ነጻ የሆነ፣

ለ. የጎብረተሰቡን ማጎበራዊና ባህላዊ እሴትን የሚያከብርና ሕጋዊ ጥቅም የማይጎዳ፣

ሐ. የሚተዋወቀው ምርት/አገልግሎት እውነተኛ ባህሪ/ጥቅም፣ ጥራትና መሰል መረጃዎችን የሚገልጽ መሆን አለበት፣

መ. የሌሎችን ሰዎች ምርት ወይም አገለግሎት የማያንቋሽሽ፣

ሠ. የአገርን ክብርና ጥቅም የሚጠብቅ፣

ረ. የሙያ ሥነ ምግባርን የሚያከብር ይዘትና አቀራረብ ያለው መሆን አለበት፣

ሸ. ለየት ያለ ባህሪ ያላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ህብረተሰቡን የማይጎዳ መሆኑን ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማረጋገጫ መቅረብ አለበት፣

2. የሚከተሉት የውጭ ማስታወቂያዎች ሕግን ወይም መልካም ሥነ-ምግባርን የሚጻረር ይዘት ወይም አቀራረብ እንዳላቸው ሆነው ይቆጠራሉ፥

ሀ) ቋንቋን፣ ዕታን፣ ብሔር ብሔረሰብን፣ ሙያን፣ ሐይማኖትን፣ እምነትን፣ ፖለቲካዊ ወይም ማህበራዊ አቋምን አስመልክቶ የሰው ልጅን ስብዕና፣ ነጻነት ወይም እኩልነት የሚጻረር ምስልን የያዘ፣

ለ) የግለሰብን፣ የብሔር ብሔረሰብን ወይም የህዝብን መልካም ሥነ ምግባር ወይም ሰብአዊ ክብርን እንዲሁም የድርጅትን መልካም ስምና ዝና የሚያጐድፍ፣

ሐ) ብሔራዊ ወይም የክልል ሰንደቅ ዓላማን፣ አርማን፣ ብሔራዊ መዝሙርን ወይም ገንዘብን የሚያንቋሽሽ ወይም የሚያዋርድ፣

መ) የአካል ጉዳተኛን፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደሙ ውስጥ ያለበትን ወይም በሌላ ህመም የተያዘ ሰውን ክብርና ሥነ ልቦና የሚነካ፣

ሠ) በጎብረተሰቡ መካከል አመጽ፣ የሀይል ተግባር፣ ሽብር፣ ግጭት ወይም የፍርሃት ስሜት እንዲፈጠር የሚያነሳሳ፣

ረ) የጎብረተሰቡን አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነት ወይም ደህንነት ለጉዳት የሚያጋልጥ ድርጊት እንዲፈፀም የሚያነሳሳ፣

ሰ) አግባብነት ያለው የመንግሥት አካል የሚወሰነውን የድምጽ መጠን በመተላለፍ በማናቸውም ዓይነት የድምጽ ማጉያ አማካይነት አካባቢን በከፍተኛ ድምጽ በመበከል የሚነገር፣

ሸ) ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ የጽሁፍ መልዕክት፣ ምስል፣ ሥዕላዊ መግለጫ ወይም መሰል አቀራረብን የያዘ፣

ቀ) የግለሰብን ስም፣ ምስል ወይም ፎቶግራፍ ግለሰቡ ሳይፈቅድ የሚጠቀም ወይም በህግ ጥበቃ የሚደረግለትን የኪነ-ጥበብ ወይም የፈጠራ ሥራ የሚመለከተው ሰው ሳይፈቅድ የሚጠቀም፣

በ) ለትራፊክ ደህንነት ወይም ለአካባቢ ጥበቃ ተጻራሪ የሆነ፣

ተ) የመከላከያ ሠራዊት/የፖሊስ የደንብ ልብስን ወይም ምልክትን በመጠቀም የሚቀርብ የንግድ ማስታወቂያ፣

የውጭ ማስታወቂያ አሰጣጥ፣ አከፋፈል ማስፈጸሚያ መመሪያ እና ሲታ ማርክ ቁጥር 01/2015

ቸ) በሌላ ህግ የተከለከለ ይዘት ወይም አቀራረብ የያዘ ወይም ማንኛውም ህግ እንዲጣስ የሚያነሳሳ የውጭ ማስታወቂያ፣

3. የሚከተሉት ይዘት ያላቻው ማስታወቂያዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፥

ሀ) አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በአደንዛዥ ዕጽነት የተመደበን ማናቸውንም ዕፅ የሚመለከት፣

ለ) ያለሐኪም ትዕዛዝ የማይሰጥ ወይም በጥቅም ላይ የማይውል መድሀኒትን ወይም የህክምና መገልገያን ተጠቃሚው በቀጥታ እንዲጠቀም የሚገፋፋ፣

ሐ) ናርኮቲክ መድሐኒትን ወይም ሳይኮቴራፒክ ንጥረ ነገርን የሚመለከት፣

መ) የጦር መሳሪያ ማስታወቂያ፣

ሠ) የቁማር ማስታወቂያ፣

ረ) የህገ ወጥ ምርት ወይም አገልግሎት ማስታወቂያ፣

ሰ) የአራጣ አበዳሪ ማስታወቂያ፣

ሸ) የጥንቆላ ማስታወቂያ፣

ቀ) የሲጋራ ወይም የሌሎች የትምባሆ ውጤቶች ማስታወቂያ፣

በ) የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ ከተመዘገበ አካል ውጭ የሚደረግ የፖለቲካ ግብ ያለው ማስታወቂያ፣

ተ) የጫት፣ የሺሻ ማስታወቂያ፣

ቸ) የአልኮል ማስታወቂያ፣

ኀ) ሌሎች በህግ የተከለከሉ ማስታወቂያዎች።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8(3)(በ) የተደነገገው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት የሚያሰራጨውን የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅት የሚያሠራጨውን የአድራሻ ለውጥ፣ የሰብሰባ ጥሪ እና መሰል ማስታወቂያን የሚከለክል አይሆንም።

5. የሰነዶች አቀራረብ

ማንኛውም የውጭ የማስታወቂያ ሠሌዳ ወይም ቢል ቦርድ ወይም በኤሌክተሮኒክስ ስክሪን በተንቀሳቃሽ ምስል ለሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ ጠያቂ ለጥያቄ ሲቀርብ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በዋናነት ማሟላት አለበት

ሀ. የማስታወቂያ ሠሌዳ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የተሟላ የዲዛይን ንድፍ፣

ለ. የማስታወቂያ ሠሌዳ ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብ ከማመልከቻው በተጨማሪ በኤሌክትሪክ የሚጠቀም ከሆነ የኤሌክትሪክ ምንጩንና መጠኑን በመጥቀስ መቅረብ ይኖርበታል፣

ሐ. የሚተዋወቀው የውጭ ማስታወቂያ የጽሁፍ፣ የምስል ወይም የቅርጽ ንድፍ፣

መ. ስለሚተዋወቀው ምርት ወይም አገልግሎት ወይም የድርጅት መልክት ሙሉ ይዘትየሚገልጽ ማመልከቻ፣

ሠ. የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርድሮች የተመዘገቡበትን የምዝገባ ወረቀት እና የታደሰ የስራ ፈቃድ ማቅረብ አለባቸው፣ ማስታወቂያውን ለማሰራጨት የተለየ ማረጋገጫ ፈቃድ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተለው አካል ማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል።

1.7 የውጭ ማስታወቂያ ቋንቋ እና ፊደል አጠቃቀም

በማናቸውም መንገድ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ፥

1. በአገር ውስጥ ቋንቋ ወይም ፊደል የተጻፈ መሆን ይኖርበታል፣

የውጭ ማስታወቂያ አቀራረብ፣ ስርጭት እና የክፍያ ማስፈፀሚያ መመሪያ እና ሲታንዳርድ ቁጥር 01/2015

2. በውጭ ቋንቋ ወይም ፊደል ጭምር የተጻፈ ከሆነ የአገር ውስጥ ቋንቋው ወይም ፊደሉ ከውጭው ቋንቋ ወይም ፊደል አስቀድሞ ወይም ከላይ ሆኖ የተጻፈ መሆን አለበት፣

3. በውጭ ቋንቋ ተተርጉሞ የቀረበ የውጭ ማስታወቂያ አቻ ትርጉም ከሕጋዊ ተርጓሚ ተቋም መቅረብ አለበት፣

4. ከውጭ ቋንቋ የተወሰደው ቃል ማስታወቂያው በተሰራጨበት የአገሪቱ ቋንቋ ፍቺ ከሌለው በቀር የሀገር ውስጥ ቋንቋ ከውጭ አገር ቋንቋ ጋር በማቀላቀል በውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት የተከለከለ ነው። ሆኖም ይህ ድንጋጌ የንግድ ስምና ምልክትን በውጭ ቋንቋ ከመጠቀም የሚያግድ አይደለም፣

5. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 1-4 የተመለከተው ድንጋጌ፣

   ሀ) በተባዙ የበራሪ ወረቀት ማስታወቂያዎች ወይም በብሮሸር፣ በሊፍሌት፣ በፍላየር ወይም በወረቀት ላይ በሚሰራጭ ማስታወቂያ፣

   ለ) በምርት ማሸጊያ ወይም መያዣ ላይ በሚሰራጭ ማስታወቂያ፣

   ሐ) በዲፕሎማቲክ እና መሰል አለም አቀፍ ተቋማት በሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

ክፍል አምስት

የውጭ ማስታወቂያ የጥራት ደረጃና ብቃት፣ ስርጭት እና የአገልግሎት ክፍያ

1.8 የውጭ ማስታወቂያ የጥራት ደረጃና ብቃት

ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ከመሰራጨቱ በፊት በደንቡ የተቀመጡትን ህግጋትና ባለስልጣኑ በስታንዳርድና በመመሪያ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል።

1.9 የውጭ ማስታወቂያ የቆይታ ጊዜ

1. በመሬት፣ በሕንፃ፣ በንግድ ድርጅት፣ በአጥር ወይም በማናቸውም መሰል አካል ላይ የሚተከል፣ የሚለጠፍ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ የቆይታ ጊዜ ማስታወቂያው የተዘጋጀበትን መሳሪያ እና የተጠቀመውን ግብአት መሰረት በማድረግ ይሆናል፣

   ሀ. ለዲጅታል ስክሪን እና አዲስ ቴክኖሎጂ ለሚጠቀሙ እስከ 6 (ስድስት አመት)፣

   ለ. በመብራት የሚሰሩ ትልልቅና መካከለኛ ቢል ቦርዶች እስከ 4 (አራት አመት)፣

   ሐ. ከመካከለኛ በታች ለሆኑ ቢል ቦርዶች በጨረታ ለተሰጠ 3 (ሶስት አመት)፣

   መ. በግል ይዞታ ለሚሰጥ በየአመቱ ማደስ ከተቻለ ገደብ አይኖረውም፣

   ሠ. የመንግስት ህንፃ እና ሌሎች የውጭ ማስታወቂያ እስከ 2 አመት፣

2. ከአንድ ወቅታዊ ሁነት ጋር በተያያዘ ለአጭር ጊዜ የሚተከል፣ የሚለጠፍ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ወቅታዊ ሁነቱ ከመከናወኑ በፊት ከአንድ ወር በላይ እንዲሁም ወቅታዊ ሁነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከሰባት ቀናት በላይ መቆየት የለበትም፣ የማጠናቀቂያ ጊዜ ካለቀ የማስታወቂያ አሰራጩ አካል ማስታወቂያውን በማንሳት ቦታውን የማስረከብ ኃላፊነት አለበት፣

3. በዚህ አንቀፅ 10(2) የተደነገገው ድንጋጌ ለትርፍ ያልተቋቋመ የመንግስት መሥሪያ ቤት በሚያሰራጨው የሕዝብ ማስታወቂያ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

1.10 የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ የቆይታ ጊዜ

አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶችን በመጠቀም የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ ማሰራጨት ይችላሉ፣

በዚህ አንቀፅ 11(1) መሰረት የሚሰራጭ የምርጫ ውድድር የውጭ ማስታወቂያ፣

   ሀ) የቆይታ ጊዜው በሚመለከተው አካል በምርጫ ወቅት የሚወሰነው የምርጫ የቆይታ ጊዜ ይሆናል፣

ለ) የተወሰነው የምርጫ ቆይታ ጊዜ በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ማስታወቂያው መነሳት ይኖርበታል፣

ሐ) ማስታወቂያው ሌሎች ሕጎችንና የምርጫ ሕግን አክብሮ መሰራጨት ይኖርበታል።

1.11 የአገልግሎት ክፍያ እና የሚከፈልበት ጊዜ

1. የውጭ ማስታወቂያ በማናቸውም መንገድ ከመሰራጨቱ በፊት ለፈቃድ ሰጪው የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፣
2. የአገልግሎት ክፍያ ተመን የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ የአገልግሎት ክፍያ ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 117/2013 እና ደንቡን ተከትሎ በሚደረጉ ማሻሻያ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፣
3. በፈቃድ ወቅት ለአገልግሎት ክፍያ የተተመኑትን ክፍያዎች መሰብሰብ የፈቃድ ሰጪው ኃላፊነት ይሆናል፣
4. በምስልና በፅሁፍ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ የክፍያ ተመን በማስታወቂያ ሰሌዳው ስፋት በሜትር ካሬና በቆይታ ጊዜው የሚሰላ ሲሆን፣ በድምፅ የሚተዋወቅ የውጭ ማስታወቂያ በሚወስደው ጊዜ (በቀን ብዛት) የሚሰላ ይሆናል
5. የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ዓመቱን ጠብቆ የአገልግሎት እድሳት ማድረግ ይኖርበታል።

1.12 ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ስለመሆን

1. የሃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የዲፕሎማቲክ መስሪያ ቤቶች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለእምነት ወይም ለዓላማ ማስፈጸሚያ እንዲውሉ በተፈቀዱላቸው ቦታዎች ወይም ንብረቶች ላይ የማስተዋወቅ ሥራ ቢያካሂዱ ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ናቸው፣
2. የፖለቲካ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ድርጅት፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና የመሳሰሉት ለአላማ ማስፈጸሚያ እንዲያውሉ ከተፈቀዱላቸው ቦታዎች ወይም ንብረቶች ውጭ የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ ለማካሄድ ሲጠይቁ፣

   ሀ) በህግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ በምርጫ ወቅት ምርጫን ለመወዳደር፣ የስብሰባ ጥሪ እና መሰል ማስታወቂያዎች ለማሰራጨት፣

   ለ) መንግስታዊ ድርጅቶች ወይም ለትርፍ ያልተቋቋሙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ማስታወቂያዎች ለማሰራጨት፣

   ሐ) ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች ለህበረተሰቡ ወይም አለም አቀፋዊና አህጉራዊ ህብረትን ወይም ግንኙነት ለማጠናከር የሚውል የውጭ ማስታወቂያ ለማስተላለፍ ሲፈልጉ ለአጭር ጊዜ ባለስልጣኑን በማስፈቀድ ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ይሆናሉ፤

3. በበጎ ፈቃደኝነት አካባቢዉን ያለማ ድርጅት ወይም ግለሰብ ባለማዉ አካባቢ ያለማውን መንከባከብ እንዳለ ሆኖ ስለ ድርጅቱ ወይም ሥራዉ የውጭ ማስተዋወቂያ የማሰራጨት ፈቃድ አውጥቶ ከከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ጋር በሚያደርገው የውል ስምምነት የጊዜ ገደብ ድረስ ሲያሰራጭ ከክፍያ ነጻ ይሆናል፤ በዚሁ መሠረት፡-

   ሀ) በበጎ ፈቃደኝነት ያለማው ሰው ቦታው ላይ ሌላ ሰው እሱን ተክቶ ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ሊወክል ወይም አሳልፎ ሊሰጥ አይችልም። ድርጅቱን ወይም ስራውን ለማስተዋወቅ የሚጠቀምበት ሰሌዳ ከሁለት ካሬ ሜትር መብለጥ የለበትም

   ለ) የግንባታ፣ የውሃ የኤሌክትሪክ፣ የቀለምና መሰል ስራ ተቋራጮችና አማካሪዎች ግንባታው በሚከናወንበት ሕንፃ፣ ቦታ ወይም መሳሪያ ላይ ስማቸውንና ስራቸውን ለማስተዋወቅ የሚያስቀምጡት የውጭ ማስታወቂያ፣

   ሐ) በባለሥልጣኑ ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ እንዲሆኑ የተወሰነለት ሰው የሚያሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ ከክፍያ ነፃ ይሆናል

1.13 የአገልግሎት ክፍያ ስለመክፈል

የዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ድንጋጌ ቢኖርም ድርጅቶቹ ለዓላማ ማስፈጸሚያ ባልተፈቀዱላቸው ይዞታዎች ወይም ንብረቶች ላይ የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ቢያካሂዱ የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባቸው

1.14 የክፍያ ውሳኔ ማሳወቂያና ክስ አቀራረብ

1. ፈቃድ ሰጪው የአገልግሎት ክፍያውን ላልከፈለ ሰው የአገልግሎት ክፍያ ውሳኔ ማሳወቂያ እንዲደርሰው ማድረግ ይኖርበታል፣
2. በፈቃድ ሰጪው በደረሰው የአገልግሎት ክፍያ ውሳኔ ማሳወቂያ መሰረት የውሳኔ ማሳወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ የሚፈለግበትን ክፍያ አጠቃሎ ያልከፈለ ወይም በ10 ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ቅሬታ ያላቀረበ ሰው ማስታወቂያው እንዲነሳ በማድረግ የአገልግሎት ክፍያውንና ማስታወቂያውን ለማንሳት ያወጣውን ወጪ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቅርቦ መጠየቅ ይችላል፣

ክፍል ስድስት

የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ አዘጋጅና አሠራጭ ግዴታና ኃላፊነት

1.15 ስለ የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ግዴታ

1. ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ አሰራጭ ወይም የራሱን ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት በውጭ ማስታወቂያ በማናቸውም መንገድ እንዲሰራጭ በማስታወቂያ አስነጋሪው የቀረበለትን መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፣
2. የሚሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት ሥነ-ምግባርን የሚጻረር ይዘት ወይም አቀራረብ የሌለው መሆኑን ባለሥልጣኑ ያዘጋጃውን የግዴታ ቅጽ በመፈረም ያረጋግጣል።

1.16 ስለ ውጭ ማስታወቂያ ሪከርድ ወይም ቅጂ

ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ አዘጋጅ አሰራጭ ወይም አስነጋሪ፡-

1. የአንድን የተተከለ፣ የተለጠፈ ወይም በማናቸውም መንገድ የተሰራጨ የውጭ ማስታወቂያን ቅጅ ወይም ሪኮርድ ቢያንስ ለ6 ወራት ይዞ ማቆየት አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተያዘውን የማስታወቂያ ሪኮርድ ቅጅና መረጃ ከዚህ መመሪያ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ምክንያት አግባብ ያለው የመንግሥት አካል እንዲቀርብለት ሲጠይቅ በራሱ ወጭ ማቅረብ አለበት።

1.17 ቁጥጥር እንዲደረግ ስለመፍቀድ

ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ አሰራጭ ወይም አስነጋሪ በአዋጁ፣ በደንቡና በዚህ መመሪያ መሰረት ለሚደረግ ቁጥጥር የአገልግሎት መስጫ ድርጅቱን ከፍት ማድረግና የሚጠየቀውን ሰነድ የማቅረብ ግዴታ አለበት

1.18 የውጭ ማስታወቂያ አሰራጭ እና አስነጋሪ ኃላፊነት

የደንቡንና የዚህ መመሪያ ድንጋጌን በመተላለፍ የተሰራጨ ማስታወቂያ በውጭ ማስታወቂያ ሥራ አዘጋጅ እና አሰራጩ ፈቃድ እንደተሰራጨ ተቆጥሮ እንደ ኃላፊነታቸው መጠን በአንድነት ወይም በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ።

ክፍል ሰባት

በቅንጅትና በትብብር ስለመስራት

1.19 በቅንጅት ስለመሥራት

1. ይህን መመሪያና ደንቡን ለማስፈጸም ባለሥልጣኑ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣ መንገዶች ባለስልጣን፡ የኮሚኒኬሽን ቢሮ፣ ደንብ ማከበር ባለሥልጣን እና አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በቅንጅትና በትብብር የመስራት ኃላፊነት አላባቸው፣
2. በዚህ አንቀጽ 27(1) የተጠቀሱት አስፈጻሚ አካላት ለውጭ ማስታወቂያ መትከያ ቦታዎች ዝግጅት፣ ለይዘትና አቀራረብ ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ በሕግ በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነትን ማከናወን ይኖርባቸዋል፣

3. በዚህ አንቀጽ 27(1) ከተገለጹት አስፈጻሚ አካላት በተጨማሪ ለቅንጅት ስራው አስፈላጊ መሆኑ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ በትብብር ጥምረቱ ውስጥ በጋራ ይሰራል፣

4. የቅንጅት ስራውን የሚያስተባብር ባለሥልጣኑ ይሆናል።

ክፍል ስምንት

/ስለ ውጭ ማስታወቂያ ስታንዳርድ/

የማስታወቂያ አይነቶች

የውጭ ማስታወቂያ ዓይነቶች በሁለት ምድቦች ይከፈላል። እነሱም ቋሚ (fixed) እና ተንቀሳቃሽ (mobile) ናቸው።

1. የማይንቀሳቀሱ ወይንም ቋሚ (Fixed) የውጭ ማስታወቂያ አይነቶች

ሀ. ቢልቦርዶች፣ ባነሮች፣ ዲጂታል/ ኤሌክትሮኒክስ ስክሪኖች፣

ለ. የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣

ሐ. በህንፃ ላይ የሚለጠፉ፣

መ. ጣሪያ ላይ የሚሰቀሉና ሌሎችም

2. የሚንቀሳቀሱ /Mobile Signs/ የውጭ ማስታወቂያ አይነቶች

ሀ. በመኪና ወይም በተሸከርካሪ ነገሮች ላይ የሚሰራጭ ማስታወቂያ፤

ለ. በተነታች መረጃ የሚያስተላልፉ ሆነው አስፈላጊ በሆነ ቦታ ላይ ጎትቶ በመውሰድ በማስቀመጥ የሚሰራጭ የማስታወቂያ፤

ሐ. በአየር ላይ የሚንሳፈፍ ፊኛና መሰል ነገሮች ላይ የሚሰራጭ ማስታወቂያ፤

መ. በድምፅ ካሴት መሳሪያ የሚሰራጩ ማስታወቂያዎች፤

1.20 የውጭ ማስታወቂያ የሚከለከልባቸዉ ቦታዎች

የትምህርት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የመንግስት ተቋማት፣ ኤምባሲዎች፤ አለም ዓቀፍ ድርጅቶች፣ ቤተመንግስት እና የመሳሰሉት ተቋማት አካባቢ ምንም አይነት የውጭ ማስታወቂያ መለጠፍ መስቀል እና ማንጠልጠል የተከለከለ ነው።

1.21 ስታንዳርዶች እና ማስፈፀሚያ ስልቶች

የዉጭ የማስታወቂያ መለጠፊያዎችን ወጥነት ባለዉ መልኩ ደረጃዉን የጠበቀ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ግልጽ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም ለከተማዋ ተጨማሪ ዉበትን በሚያላብስ መልኩ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በዚህ ስታዳርድ የታቀዱ የውጭ ማስታወቂያ መለጠፊያ አይነቶች በሚዘጋጁበት ወቅት ሊያሟሉ የሚገባቸዉን ዝርዝር መስፈርቶች (Guide line & Standards) ከዚህ ቀጥሎ በቀረበዉ መልኩ ተዘጋጅቷል።

1.22 አጠቃላይ ዋና ዋና ስታንዳርዶች

1.22.1 ማንኛውም የማስታወቂያ ሰሌዳ በሚተከልበት ወይም በሚገነባበት ቦታ በቂ የፀሐይ ብርሃንና መተላለፊያ ያለው፣ የእግረኛና የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ የማይከለክል፣ የማያውክ፣ የማይገድብ እና ነጻ መሆን አለበት፣

1.22.2 ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ አስነጋሪ ድርጅት/ተቋም/ በአንድ በቦታ ላይ በተሰጠው ፍቃድ ሌላ አከባቢ/ቦታ/ መትከል አይቻልም፣

1.22.3 ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ከተሰቀለበት ሰሌዳ ወርድና ቁመት መትረፍ የለበትም፣

1.22.4 ለፈቃድ የሚቀርቡ የውጭ ማስታወቂያ ይዘቶች በሀገሪቱ የስራ ቋንቋ መቅረብ አለባቸው፣

1.22.5 የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳ መጠኖች በሜትሪክ ሲስተምና በግራፊክ ስታንዳርድ መቅረብ አለባቸው፣

1.22.6 የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳ በመስታወት የሚሰራ ከሆነ የመስታወቱ ውፍረት 6 ሚሊ ሜትር ሆኖ ቢሰበርም የማይረግፍ መሆን አለበት፣

1.22.7 በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ዲጂታልና ባለብርሀን ማስታወቂያ ሳጥን /Light box/ የራሱ የኤሌክትሪክ መስመርና መቆጣጠሪያ ያለው መሆን አለበት፣

1.22.8 የመሰረተ ልማት አውታሮችን በማይጎዳና አግባብ ባለው አካል የተዘጋጀ የስትራክቸራል ውቅር ንድፍ በሚያቀርበውና በሚያዘው መስፈርት መሰረት ይወሰናል፣

1.22.9 የወረቀትና ወረቀት ነክ ማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርዶች ላይ ብቻ ካልሆን በስተቀር በሌላ ቦታ ምንም አይነት ማስታወቂያ መለጠፍ አይቻልም፣

1.22.10 በመኪና፣ በባቡር እና በእግረኛ መሸጋገሪያ ድልድይ ምሰሶዎች ላይ ምንም አይነት የውጭ ማስታወቂያዎች መስቀል የተከለከለ ነው፣ ነገር ግን በድልድዮች ላይ መስቀል ይቻላል፣

1.22.11 ውበቱ ሲጓደልና የውል ጊዜው ሲያልፍ በጨረታው ያሸነፈው ድርጅት ውሉን ካጠናቀቀ በኋላ ማስታወቂያውን አንስቶ ላዋዋለው አካል ማስረከብ አለበት፣

1.22.12 በማንኛውም ዘዴ የሚሰራጩ የውጭ ማስታወቂያዎች ከይዘት አኳያ ማናቸውንም ሕግ ወይንም መልካም ስነ ምግባር የማይፃረር፣ አሳሳች ወይንም ተገቢ ካልሆነ አገላለፅ ነፃ የሆነ፣ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ እሴት የሚያከብርና የሸማቹን ህጋዊ ጥቅም የማይጎዳ፣ የሚተዋወቀውን ምርት ወይንም አገልግሎት እውነተኛ ባህሪ፣ ጥቅም፣ ጥራትና መሰል መረጃዎችን የሚገልፅ ፣ የሌሎችን ሰዎች ምርት ወይንም አገልግሎት የማያንቋሸሸ፣ የአገርን ክብርና ጥቅም የሚጠብቅ እና የሙያ ስነምግባርን የሚያከብር ይዘትና አቀራረብ ያለው መሆን አለበት።

1.22.13 በህንጻ የውጭ መስታወት በር፣ መስኮት እና የግንባታ ማጠናቂያ ቁሶች ላይ ምንም አይነት የውጭ ማስታወቂያ ማስተላለፍ አይቻልም፣ ሆኖም ግን በህንፃ ውስጥ ባሉ የፓርቲሽን መስታወት በር፣ መስኮት እና የግንባታ ማጠናቂያ ቁሶች ላይ በአከፋፈል ደንብ ቁጥር 117/2013 መሰረት በማስከፈል መፈቀድ ይቻላል፣

1.22.14 በድምፅ ማጉያ መሳሪያ ወይም በድምፅ ካሴት በመጠቀም ምርትንና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጠን በኩል የድምፅ ስታንዳርድ ይሁንታ ሲያገኝ ፈቃድ ይሰጣል፣

1.22.15 የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ የማስታወቂያ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀጽ 21/3 የውጭ ማስታወቂያ በአገር ውስጥ ቋንቋ ወይም ፊደል የተጻፈ መሆን ወይም በውጭ ቋንቋ ወይም ፊደል ጭምር የተጻፈ ሲሆን የአገር ውስጥ ቋንቋው ወይም ፊደሉ ከውጭው ቋንቋ ወይም ፊደል አስቀድሞ ወይም ከላይ ሆኖ የተጻፈ መሆን አለበት።

1.22.16 በስፖንሰር የሚቀርቡ የውጭ ማስታወቂያ በ0.3ካ.ሜ. ስፋት የስፖንሰር አድራጊው ስም፣የንግድ ምልክቱ ወይም ሎጎና ለስፖንሰሩ የሚቀርብ ምስጋና ከመግለጽ ውጭ የስፖንሰሩ ምርት ወይም አገልግሎት እንዲሸጥ ወይም እንዲከራይ መተዋወቅ ወይም መቀስቀስ የለበትም።

1.22.17 በአንድ ገጽ በኩል ብቻ የሚሰራ የማስታወቂያ ሰሌዳ ጀርባው የከተማውን ውበት በማያበላሽና ንጹህ በሆነ ቁስ የተሸፈነ መሆን አለበት።

1.22.18 ማንኛውም የማስታወቂያ ሰሌዳ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሰሌዳ መትከያ ቦታውንም ሆነ የሰሌዳውን ንጽሕና የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

1.22.19 የሚተከል ወይም የሚገነባ ወይም የሚሰቀል የውጭ ማስታወቂያ የህውልት ወይም ማንኛውንም ቅርስ እይታን የሚጋርድ መሆን የለበትም።

1.22.20 ማንኛውም ማስታወቂያ ብልጭ-ድርግም የሚሉ እንዲሁም የመንገድ ተጠቃሚውን እይታ በሚረብሽ መልኩ የሚያንፀባርቁ መሆን የለባቸውም፡ ነገር ግን በምሽት እንዲነበቡ ተደርገው የብርሀን ብክለት በማያስከትል ሁኔታ መሰራት አለበት።

1.22.21 በማስታወቂያው የታችኛው ጠርዝ ላይ (ምሶሶው ላይ) 0.3 ካሬ ሜትር ባልበለጠ ቦታ የማስታወቂያ ወኪል ስምና አድራሻ፣የፈቃድ ቁጥሩ፣ፈቃዱን የሰጠው አካልና ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ ከመሬት ላይ በሚታይ መልኩ መፃፍ አለበት።

1.23 በአደባባይ ዙሪያ ባሉ ክፍት ቦታዎች የሚተከሉ የውጭ ማስታወቂያ ቢልቦርዶች

በአደባባይ ዙሪያ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች ከአንዱ ማስታወቂያ ጠርዝ እስከ ሁለተኛው ማስታወቂያ ጠርዝ ያለው ዝቅተኛው ርቀት ሶስት ሜትር ሊሆን ይገባል። ሶስት ሜትር ላይ ማስታወቂያውን ለማስቀመጥ የማያስችል ነባራዊ ሁኔታ ሲገኝ እስከ አራት ሜትር ድረስ ሊጠበቅ ይችላል ሆኖም ግን ከሶስት ሜትር ርቀት በታች ማስታወቂያዎችን መትከል አይቻልም።

ማስታወቂያዎች ከሦስት ሜትር በላይ ርቀት እንዲጠብቁ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች መካከል፡-

1.23.1 ለአካባቢ ውበት ተብለው የተተከሉ አጽዋት ማስታወቂያው ሊተከልበት በታሰበበት ቦታ ላይ ሲገኙ፤

1.23.2 ስልጣን ባለው አካል የለሙ ቦታዎች ሲገኙና ቦታው ለማስታወቂያ ሲውል የሚያስከትለው ጉዳት አመዝና ከተገኘ፣

1.23.3 በአካባቢው ላይ በመንግስት ወጪ ለልማት ተብለው የተገነቡ መሰረተ ልማት አውታሮች ካሉ

ለምሳሌ፦ የቆሻሻ መጣያ፣ የመንገድ ዳር ምሰሶዎች



1.23.4 በዋና ዋና መንገድ አደባባይ ላይ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች ከእግረኛ መንገድ ጠርዝ አንድ ሜትር እንዲርቁ ይደረጋል።

1.23.5 በአደባባይ ዙሪያ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች እንደ አስፈላጊነቱ ከ6 ሜትር ወርድ ስፋት በላይ ያልሆኑ ማስታወቂያዎች መተከል አለባቸው።

1.23.6 በአደባባይ መሃል ምንም ዓይነት ማስታወቂያ ሰሌዳ መትከል፣ መለጠፍ ወይም ማንጠልጠል አይቻልም ሆኖም አደባባዮችን የሚያለማ ባለሀብት ምርቱንና አገለግሎቱን ለማስተዋወቅ የሚፈቀደው አደባባዩ በሚፈቀድለት ቴክኒካል መስፈርት ወይም ስታንዳርድ መሰረት ቅርጻ ቅርጾችን፣ ሀውልቶችን፣ ፋውንቴኖችን እና ሰው ሰራሽ ወንዞችን መገንባት ይችላል። እንዲሁም የሚያለማ ባለሀብት የማስተዋወቅ ስራ ለማከናወን በአደባባይ ዙሪያ ከ2 ካ.ሜትር ያልበለጠ ስሌዳ መጠቀም ይችላል።

1.23.7 በአደባባይ ላይ የሚሰቀሉ ተከታታይ ማስታወቂያዎች እስከ 6 ሜትር ወረድ ያልበለጡየውች ማስታወቂያዎች የሚተከሉ ቢሆንም አንዱ ማስታወቂያ ከሌላው ማስታወቂያ ቢቻል በተመሳሳይ ምጣኔ ማለትም ወርድ እና ቁመት ካልሆነ ግን አንዱን ምጣኔ እንዲጠብቅ ይደረጋል ይህም የእይታ ወጥነትን እንዲፈጠር ታሳቢ የተደረገ ነው፣

1.23.8 በአደባባይ ዙሪያ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች የቦታ ተደፋት ልዩነት (Slope) ልዩነት ሲኖራቸው ጎን ለጎን የሚተከሉ ማስታወቂያዎችን ቁመት ለማስታረቅ እንደ አስፈላጊነቱ የቋሚ ቁመት ከ2.5 ሜትር ሊበልጥ ይችላል፣

1.23.9 በአደባባይ ዙሪያ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች ማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የሚያስችል አንድ ክንውን ከማስታወቂያው ጎን ለጎን ማካተት ይጠበቅባቸዋል፣

1.23.10 ለምሳሌ፡- ቆሻሻ መጣያ ፣ የሊስትሮ መቀመጫ ቦታዎችን

1.23.11 በአደባባይ ዙሪያ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች አንደኛውን ገጽ ለማየት አዳጋች የሆነ ሁኔታ ከሌለ የማስታወቂያ ቦታዎችን ብክነት እና ምጣኔያዊ አጠቃቀም ለመጠበቅ ሲባል በሁለቱም (ገጽታ) በኩል ማስታወቂያዎችን እንዲሰቀል ይዳረጋል።

1.23.12 በአደባባይ ዙሪያ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች በሁለት ተከታታይ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች መካከል ያለው ርቀት ቢያንስ 3 ሜትር መሆን አለበት

1.24 በዋና ዋና እና መጋቢ መንገዶች ላይ የሚተከል የውጭ ማስታወቂያ መስፈርቶች

ከ25 ሜትር ስፋት እና በላይ (PAS፣ SAS እና RR)

1.24.1 በዋና ዋና መንገዶች ላይ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች ለዋና ዋና መንገዶች ተብለው የተጠቀሱትን የማስታወቂያ ልኬት አማራጮች በመውሰድ በ50 ሜትር ርቀት ውስጥ የሚተከሉ ይሆናል።

1.24.2 ሆኖም በ50 ሜትር ርቀት ውስጥ ማስታወቂያ ለመትከል የማያስችል ሁኔታ ቢገኝ፣

ለምሳሌ፡- የማስታወቂያው በስተጀርባ የሚከለል ህንፃ ቢኖር፣ ኢምባሲ ቢኖር፣ የህዝብ መገልገያ ፓርክ ቢኖር ከ 50 ሜትር ሳያንስ ክፍት ቦታ እስኪገኝ የሚቀጥል ይሆናል፣

1.24.3 በዋና ዋና መንገዶች ላይ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች የእግረኛንም ሆነ የአሽከርካሪን እይታ በማይጋርድ ከ2.5 ሜትር ከፍታ ላይ መተከል ይኖርባቸዋል፣

1.24.4 ማንኛውም በከተማዋ ዋና ዋና መንገዶች ላይ የሚገኙ ክፍት ቦታዎች ላይ ከሚመ"ለከተው አካል ተገቢውን አዎንታ ሳያገኙ ማስታወቂያ መትከል በተጠቀሰው የውጭ ማስታወቂያ በመመሪያ ዘ17/2013 ደንብ መሰረት ቅጣቱ ተፈፃሚ ይሆናል፣

1.24.5 በዋና ዋና መንገዶች ላይ መስቀለኛ አቋራጮች ሲገኙ ከእያንዳንዱ የመንገዱ ጠርዝ 12 ሜትር ርቀት ድረስ ማስታወቂያ መትከል አይቻልም፣

1.24.6 ዋና ዋና መንገዶች ላይ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች ማስታወቂያውን ለመትከል በቂ ያልሆነ ቦታ ከሆነ ለመንገዱ ትይዩ እንዲሆን ይገደዳል፣

1.24.7 ሆኖም በቂ ቦታ ከተገኘ የእግረኛን እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ ለእግረኛው ትይዩ (ፊት ለፊት) በሆነ አቅጣጫ ከ2.5 ሜትር ከፍታ ላይ የእግረኛን እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ ሊተከል ይችላል፣



የውጭ ማስታወቂያ ቁጥጥር አዋጅ መመሪያ እና ቴክኒክ ሰነድ ማስፈጸሚያ ደንብ ቁጥር 01/2015



6.0 ሜትር * 3.0 ሜትር

የመንገድ ቅርጻቸው ከሁለት አቅጣጫ እይታን በሚፈቅዱ ቦታዎች ላይ ሁለት ማስታወቂያዎችን ለእይታ በተመጠነ አንግል ሊቀመጡ ይችላሉ፣





3.5 ሜትር * 6 ሜትር

2.5 ሜትር * 4 ሜትር



የመንገድ ቅርጻቸው ከሶስት አቅጣጫ እይታን በሚፈቅዱ ቦታዎች ላይ ሶስት ማስታወቂያዎችን ለእይታ በተመጠነ አንግል ሊቀመጡ ይችላሉ፣

6 ሜትር * 6 ሜትር

5 ሜትር * 5 ሜትር



1.25 መጋቢ መንገዶች ላይ የሚተከል የውጭ ማስታወቂያ መስፈርቶች

15-20 ሜትር ስፋት (Collecter Road)

1.25.1 በሁለት ተከታታይ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች መካከል ያለው ርቀት ቢያንስ /ሃምሳ/ ሜትር መሆን አለበት፣

1.25.2 በማስታወቂያ ምሰሶው ላይ 0.3 ካሬ ሜትር ባልበለጠ ቦታ ላይ የማስታወቂያ ወኪሉ ስምና አድራሻ፣ የፈቃድ ቁጥሩ፣ ፈቃዱን የሰጠው አካልና ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ በሚታይ መልኩ መፃፍ ሲኖርበት፤ የማስታወቂያ ፈቃድ ባለቤቱ መረጃው ተሟልቶ መቀመጡን ይከታተላል፣

6ሜትር*3.5ሜትር
4ሜትር*2.5ሜትር
3ሜትር*1.8ሜትር
2ሜትር*1.5ሜትር



4ሜትር*2.5ሜትር
3ሜትር*1.8ሜትር
2ሜትር*1.5ሜትር



1.26 በውስጥ ለውስጥ መንገድ የሚተከል የውጭ ማስታወቂያ ቢልቦርድ

ከ10 ሜትር ስፋት እና ከዚያ በታች (local streat)

1.26.1 በማስታወቂያ ምሰሶው ላይ 0.3 ካሬ ሜትር ባልበለጠ ቦታ ላይ የማስታወቂያ ወኪሉ ስምና አድራሻ፣ የፈቃድ ቁጥሩ፣ ፈቃዱን የሰጠው አካልና ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ በሚታይ መልኩ መፃፍ ሲኖርበት ፤ የማስታወቂያ ፈቃድ ባለቤቱ መረጃው ተሟልቶ መቀመጡን ይከታተላል።

ባለአንድ ገጽ ከሆነ፤

- ቋሚው ከመሬት በላይ ያለው ከፍታ በያንስ 2.50 ሜትር በላይ መሆን አለበት።
- በሁለት ተከታታይ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች መካከል ያለው ርቀት ቢያንስ 2 ሜትር መሆን አለበት።

ባለ ሁለት ገጽ ማስታወቂያ ሰሌዳ ከሆነ

- ጥያቄው በሚቀርብበት ጊዜ ቦታው የሚያመች መሆኑ በፈቃድ ሰጪው አካል አስተያየት መረጋገጥ አለበት፤ በፈቃድ ሰጪው አካል አስተያየት ቦታው የሚያመች ሆኖ ከተገኘ ባለሁለት ገጽ የማስታወቂያ ሰሌዳ መትከል የሚቻል ሲሆን ፤
- ቋሚው ከመሬት ያለው ከፍታ ከ2.5 ሜትር በላይ መሆን አለበት።
- ሁለት ተከታታይ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች መካከል ያለው ርቀት ቢያንስ 10 ሜትር መሆን አለበት።

0.4ሜትር*0.7ሜትር
0.5ሜትር*0.8ሜትር
0.6ሜትር*0.1ሜትር



1.8ሜትር*1.4ሜትር
1.4ሜትር*0.8ሜትር



1.27 መካከለኛ የውጭ የማስታወቂያ መለጠፊያ ሠሌዳ

ይህ የማስታወቂያ መለጠፊያ በሰዉ ቁመት ሊነበብ የሚችሉ የማስታወቂያ አይነቶችን የሚይዝ ሲሆን የማስታወቂያወቹ ሰሌዳ አይነትም በህትመት የሚለጠፉ (Hard Copy Display) ወይንም ዲጂታል ስክሪን ላይ የሚተላለፉ ሊሆን

ይችላል። በዲጅታል ስክሪን የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች ማስታወቂያዉ ከሚሰራጭበት ጣቢያ ጋር በገመድ አልባ ኔትዎርክ አማካኝነት በማገኛኘት የሚተላለፍ ይሆናል። ይሁን እንጅ የሁለቱም የሰሌዳ አይነቶች ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘረዉ ስታንዳርድና መመሪያ መሰረት የሚዘጋጁ ይሆናል።

- ✓ የማስታወቂያ ሰሌዳዉ የሚቀመጥበትን ቦታ ከግምት ዉስጥ በማስገባት
  - ባለአንድ ወይም ባለሁለት ገጽ ሊሆን ይችላል
  - ከሚኖረዉ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ብዛት አንፃር እስከ ሁለት የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ጎን ለጎን ሊገነቡ የሚችሉ ሲሆን በሁለት ማስታወቂያዎች መካከል ቢያንስ የነሜትር ክፍተት መሆን ይኖርበታል።
- ✓ ይህ የማስታወቂያ መለጠፊያ አይነት ሶስት ክፍሎች የሚኖሩት ሲሆን እያንዳንዳቸዉም የተለያዩ የማስታወቂያ ሁኔታዎችን (የአገልግሎት ሰጪ፣ የጨረታ፣ ማሳሰቢያና የስራ ማስታወቂያዎችን) የሚይዝ ሲሆን ከ5ካ.ሜ ያነሰና **ከ6ካ.ሜ** በላይ መሸፈን የለበትም (Maximum permitted Area = 6m2).



- ✓ የማስታወቂያ ሠሌዳው ቁመት 125 ሳ.ሜ እና ወርዱ 225 ሳ.ሜ
- ✓ ከመሬት የሚኖረዉ ከፍታ 90 ሳ.ሜ
- ✓ የግንባታ ግብአት
  - ግብአት (Material)፡ የማይዝግ ብረት (ስቴንለስ ስቲል)
  - ቋሚ ምሰሶ /Post/፡ ብዛት 4 መጠን (10*15 ሳ.ሜ)
  - ቋሚ ምሰሶዉ ከምድር ጋር በብሎን የሚታሰር ይሆናል።
- ✓ **መስታወት**፡ ቀለም የሌለዉ 100% ብርሀን አስተላላፊ ፖሊካርቦኔት ወይም የማይረግፍ መስታወት መሆን አለበት
- ✓ ከፋይበር መስታዉት የሚሰራ 100ሳ.ሜ ስፋት ያለዉ የዝናብና የፀሀይ ነፀብራቅ መከላከያ አብሮ የሚሰራ ይሆናል።
- ✓ የማስታወቂያ መለጠፊያዉ በር ፍሬም ባለ 10ሳ.ሜ

- ማጠፊያ ከላይ ሆኖ ወጥ በር የሚዘጋጅ ሲሆን በሩም ወደላይ ተከፋች ይሆናል
- የበሩ ድጋፍም ባለ ተንቀሳቃሽ ስፕሪንግ ይሆናል

✓ **መብራት፡** ከማስታወቂያ መለጠፊያዉ ላይ የሚቀመጡት የLED መብራቶች ሲሆኑ አንባቢዉን በቀላሉ ወደሚፈልገዉ የመረጃ አይነት የሚመሩ የማስታወቂያ አይነቶችን አርዕስት የሚያመላክት ፅሁፎች የሚይዝ ይሆናል።

✓ የአንባቢዉን ምቾት (Comfort) ለመጠበቅ ያስቻላል ዘንድ የማስታወቂያ ሰሌዳዉ አቀማመጥ የፀሀይን እንቅስቃሴን (Sun Orientation) ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል።



የጎን እይታ (Side Elevation)

የወጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ እና ክትትል ማ... ሂደት መመሪያ እና ስታንዳርድ ቁጥር 01/2015





1.28 የተቀናጀ የማስታወቂያ ቦርድ

ይህ የቦርድ ማስታወቂያ አይነት መካከለኛ ቢል ቦርድን ከመካከለኛ የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ ጋር ተቀናጅቶ የሚዘጋጅ ሲሆን ከስር የሚገነባዉ ለመካከለኛ የማስታወቂያ ሰሌዳ ተብሎ በተቀመጠዉ ስታንዳርድ መሰረት የሚገነባ ሲሆን ከላይ ተቀናጅቶ የሚገነባዉ የመካከለኛ ቢል ቦርድ የማስታወቂያ መለጠፊያ ከዚህ ቀጥሉ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፣

ይህ የማስታወቂያ መለጠፊያ ቦርድ የታተሙ ማስታወቂያዎችን ወይንም በዲጂታል ስክሪን የሚዘጋጅ ይሆናል፣

1.28.1 ወርዱ ከመካከለኛ ቢል ቦርድ የማስታወቂያ መለጠፊያ ወርድ (225ሳ.ሜ) ጋር እኩል መሆን ያለበት ሲሆን ቁመቱ ደግሞ ከ225ሳ.ሜ መብለጥ የለበትም፣

1.28.2 በተተከለበት መሬትና በማስታወቂያው የታችኛው ጠርዝ መካከል የሚኖረው ከፍታ ከ305 ሳ.ሜ ማነስ እና ከመሬት የሚኖረው አጠቃላይ ከፍታ 530 ሳ.ሜ መብለጥ የለበትም፣

1.28.3 ከላይ የሚገነባዉ የመካከለኛ ቢልቦርድ የማስታወቂያ ሰሌዳ እንደሚኖረን ሶስት አይት አቀማመጥ (ትይዩ፣ የመንታ መጋጠሚያ /V Shape/ እና ባለ ሦስት ገፅ) ሊኖረዉ ይችላል፣ ከእነኝህ ዉስጥ በባለ ሦስት ገጽ የሚዘጋጅ የተቀናጀ የማስታወቂያ ቦርድ በሶስቱም አቅጣጫ ማስታወቂያዎችን ለማስተላለፍ የሚያስችል መሆን አለበት፤

1.28.4 ራሱን ችሎ መሀከል ላይ የሚቆም በመሆኑ ከሌሎች የማስታወቂያ ሰሌዳዎች አቀማመጥ አንፃር ትልቅ ቦታ (ከ15ካ.ሜ ያላነሰ ቦታ) ይፈልጋል። በመሆኑም የሚዘጋጀዉ ዲዛይን የሚኖረዉን የቦታ ስፋትና አስፈላጊነቱን ከግምት ዉስጥ ማስገባት ይኖርበታል።



1.29 በመንገዶች ዳርቻ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች

1.29.1 የእግረኛን እንቅስቃሴ የማያውኩ መሆን ይኖርባቸዋል፣

1.29.2 የእግረኛን እንቅስቃሴ ታሳቢ በማድረግ የእግረኛ ፍሰት በማይበዛባቸው ቦታዎች ብቻ መተከል ይኖርባቸዋል፣

1.29.3 በመንገዶች ዳርቻ የሚተከሉ ማስታወቂያ ከኋለኛው እግረኛ መንገድ ጠርዝ ድንጋይ /Back curbe stone/ በኋላ አነስተኛው ርቀት 0. ሜትር መሆን አለበት፣





1.30 በህንጻ ላይ የሚሰቀሉና የሚለጠፉ ማስታወቂያዎች

1.30.1በህንፃ አናት ወይም ጣሪያ ላይ

- በሕንጻ አናት ወይም ጣሪያ ላይ የሚሰቀል ወይም የሚለጠፍ የውጭ ማስታወቂያ በምንም መልኩ ወደ ጣሪያው ጠርዝ መጠጋት የለበትም።
- የህንጻው ባለቤት የማስታወቂያ ወኪሉን ስምና አድራሻ፣ የፈቃድ ቁጥሩ፣ ፈቃዱን የሰጠው አካልና ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል።
- የፈቃድ ጊዜው ያለፈበትን ማስታወቂያ እንዲወርድ ወይንም እንዲያሳድስ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ይህን አለማድረጉ በህንፃው ላይ የማስታወቂያ ስራ እንዳያከናውን ከመታገዱም በላይ አስተዳደራዊ መቀጮ ይጣልባቸዋል።



- በሕንጻ አናት ወይም ጣሪያ ላይ የሚሰቀል ወይም የሚተከል የዉጭ ማስታወቂያ ቁመቱ ከ3 ሜትር መብለጥ የለበትም።
- ሆኖም ከዚያ በላይ ጥያቄ ሲቀርብ የአካባቢው የህንጻ ከፍታ ደንብ በጠበቀ መልኩ ሆኖ የህንጻው ውቅር /Structure/ የሚፈቅደው መሆኑ መረጋገጥ አለበት። የህንጻው ውቅር ትንተና /Structural Analysis/ መቅረብ አለበት።

1.30.2 በሕንጻው ግድግዳ ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚሰቀል የማስታወቂያ ሰሌዳ፤

- የማስታወቂያ ሰሌዳው የህንፃውን የመስኮት፣ የበር፣ ወይም የአደጋ ጊዜ መውጫን የሚጋርድ መሆን የለበትም፣ በሕንጻው የጎን ገጽ ላይ ከአንድ ማስታወቂያ በላይ መለጠፍ አይቻልም፣
- የሚሰቀለው የማስታወቂያ ሰሌዳ ከሕንጻው ጠርዝ መትረፍ የለበትም፣
- የሚሰቀለው የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳ ሊለጠፍበት ከታሰበው የጎን ግድግዳ ገጽ ብቻ 70% ፐርሰንት መሆን አለበት፣ ነገር ግን የህንጻውን ውበት እና አርክቴክቸራል (Façade) ተከትሎ እና ከሌሎች ህንጻዎች ጋር የተናበበና የማይቃረን መሆን አለበት፤



- የውጭ ማስታወቂያው ቀለም ከህንፃው ማቴሪያል ጋር መዋሀድ(Harmonized) እና መልካም እይታ መፍጠር አለበት፣
- የህንጻዉን ዉበት(Façade) ከመጠበቅ አንጻር በህንጻዎች የፊት ለፊት ገጽ ላይ የሚሰቀሉ የውጭ ማስተወቂያዎች፡-
  - ✓ በከተማዋ ከሚገኙ Old city ውስጥ ፒያሳ ላይ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት የተሰቀሉ የውጭ ማስተወቂያዎች ቁመታቸው ነ ሜትር ሆኖ የህንፃውን ዉበት (Façade) እና ድግግሞሽ (Rhythm) በጠበቀ መልኩ የተሰሩ በመሆኑ በጥሩ ተሞኩሮ ሊወሰድ በመቻሉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስታንዳርዶች ተዘጋጅተዋል፣



✓

✓ **በህንፃዎች ፊት ለፊት** ላይ የሚሰቀሉ የሚለጠፉና የሚንጠለጠሉ የውጭ ማስታወቂያዎች

- የህንፃው የበረንዳ መደገፊያዎች(Handrail) ላይ እና የህንጻዉ Facade ተከትሎና pattern ጠብቆ በሜትር ቁመት መለጠፍ፣ ማንጠልጠል ወይም መሰቀል ይኖርበታል።



1.30.3 በህንፃ ላይ ባሉ ገፆች ላይ በፅሁፍ የሚሰቀል ማስታወቂያዎች

- በህንፃ ውጫዊ አካል ላይ ለሚለጠፉ የህንፃውን ስም የሚገልፅ ፅሁፎች መጠናቸው ጉልህ የሆነና በጥራት መታየት አለበት፣
- የእያንዳንዱ ፅሁፍ የቁመት ምጣኔ ከአንድ ሜትር ከሀምሳ ያልበለጠ እና ከሰማንያ ሳንቲ ሜትር ያላነሰ መሆን አለበት፣



1.30.4 በሕንጻው ግድግዳ ላይ ወጣ ብሎ የሚሰቀል የማስታወቂያ ሰሌዳ፤

- ይህ የሰሌዳ አይነት ወርዱ ከ80 ሳ.ሜ ያልበለጠ እና ከህንጻው አካል ጋር ያለው ውቅር የጠበቀ እንዲሁም ክብደት ከሌላቸው ቁሶች የሚሰራ በተጨማሪም የእግረኛን እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ ከመሬት ቢያንስ 3 ሜትር ከፍታ ሊኖረው ይገባል፣



1.30.5 በህንጻዎች ፊትለፊት የሚቀመጡ ማስታቂያዎች

- የውጭ ማስታወቂያው የሚቀመጡበት ቦታ ከ0.6 ሜትር ስኩዌር የማይበልጥ ሆኖ የማስታወቂያው ቦርዱ ስፋት 1.00 ሜትር x 0.6 ሜትር መብለጥ የለበትም፣

የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ

➢ እነዚህ ማስታወቂያዎች የእግረኛ መንገድ ላይ መቀመጥ አይችሉም፣ ሆኖም በህንፃ እና በእግረኛ መንገድ መካከል ባሉ ክፍት ቦታዎች እና ህንፃው በተዋቸው ክፍተቶች ላይ ብቻ የሚቀመጥ ይሆናል፣



1.31 በድልድዮች ላይ የሚሰቀሉ ማስታወቂያዎች

1.31.1 ቁመታቸው ከአንድ ሜትር ከሀያ መብለጥ የለበትም፣

1.31.2 የውጭ ማስታወቂያው ወርዳቸው እንደ ድልድዩ መጠን ቦታ ላይ በማስታወቂያ ፈቃድ ሰጪው አካል የሚወሰን ይሆናል፣

1.31.3 የአሽከርካሪዎችን የእይታ መዘበራረቅ ለመግታት በአንደድ ድልድይ ላይ በአንድ አቅጣጫ ከአንድ በላይ ማስታወቂያ መስቀል አይቻልም፣



1.32 አስገዳጅ በሆነና አትክልቱ እስኪያድግ ድረስ አካፋይ መንገዶች ላይ እና የአረንጎዴ ቦታዎች መከለያ ላይ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች

1.32.1 የአጥር ቁመታቸው 0.75 ሜትር መብለጥ የለበትም፣

1.32.2 አካፋይ መንገዶች ላይ እና የአረንጎዴ ቦታዎች ለመከለያ የሚሆን ቦታ ላይ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች በየ20 ሜትር ርቀት መለጠፍ አለባት፣

1.32.3 የአንዱ ማስታወቂያ ስፋት ወርዱ 40 ሳንቲ ሜትር ሆኖ ቁመቱ 60 ሳንቲ ሜትር መሆን አለበት፣

የወ-ማ-መ-ፈ-ቃ-ሰ-ማስታወቂያ እና ሰ-ሌ-ሃ-ዳ-ር-ቁ-ጥ-ር 01/2015



1.33 በአጥር ላይ የሚሰቀሉ ማስታወቂያዎች

1.33.1 የግለሰቦች አጥር

- ✓ የማስታወቂያ ፍቃድ ወቶበት ለሚለጠፍ ወይም ለሚሰቀል ማስታወቂያ የበሩን ተካፋች ሳይነካ ከቀሪው ድፍን ግድግዳ /solid wall/ ግሪል ያልሆነውን የአጥር ክፍል ላይ ሰማንያ ፐርሰንቱን (80%) ብቻ መሸፈን ይኖርበታል፣

1.33.2 የተቋማት አጥር

- ✓ የበሩን ተካፋች ሳይነካ ከቀሪው ድፍን ግድግዳ /solid wall/ ግሪል ያልሆነውን የአጥር ክፍል ላይ ሰማንያ ፐርሰንቱን (80%) ብቻ መሸፈን ይኖርበታል፣
- ✓ ለአካባቢ ልማት የሚለሙ አትክልቶችን በማይነካ መልኩ ከመሬት ሰባ ሳንቲም ከፍታ ላይ መቀመጥ ይኖርበታል፣



1.34 በመንገድ ዳር የመቀመጡ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ላይ የሚለጠፉ ማስታወቂያዎች

• በመንገድ ዳር በመቀመጡ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ላይ የሚለጠፉ ማስታወቂያዎች ለማስታወቂያ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ሙሉ ለሙሉ መሸፈን ይኖርበታል። በተጨማሪም ከሚያስተዳድረው አካል የአምንታ ደብዳቤ ያስፈልጋል።	

1.35 በአውቶቢስ እና በባቡር መጠበቂያ ቦታዎችየሚለጠፉ ማስታወቂያዎች

• በአውቶቢስ እና በባቡር መጠበቂያ ቦታዎች ላይ ባሉ የተሳፋሪ መቀመጫዎች ላይ የሚሰቀሉ ማስታወቂያዎች ለማስታወቂያ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ ላይ ሙሉ ለሙሉ መሸፈን ይኖርበታል። በተጨማሪም ከሚያስተዳድረው አካል የአምንታ ደብዳቤ ሊቀርብላቸው ይገባል።	

1.35.1 የአውቶብስ መጠበቂያ መጠለያዎች ላይ የተዘጋጁ የማስታወቂያ ቦታዎች

የማይዝግ ብረት (ስቴንለስ ስቲል) የአውቶብስ መጠበቂ መጠለያዎች ላይ አላማቸው ለማስታወቂያ ማሳያ ተብለው የተሰሩ ባለብርሀን የማስታወቂያ ሳጥኖች (Light Boxes) ሲኖሩ እነዚህም ሁለት አይነት መጠን ያላቸው ናቸው።

ዓይነት 1

- ✓ የሳጥን ስፋታቸው ፡ 1.7 ሜትር በ 1.8 ሜትር ሲሆኑ
- ✓ የማስታወቂያ ማሳያ መስታወት ስፋታቸው ፡ 1.6 ሜትር በ 1.7 ሜትር፣

የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ እና ተያያዥ ማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 01/2015

- ✓ የሀይድሮሊክ ተከፋች በር እና ከታች ለመቆለፊያ የሚሆኑ ሁለት የማይዝግ ብረት ቁልፎች (Stainless steel lock) ያላቸው፣
- ✓ የብርሀን ሰጪ LED መብራቶች ያላቸው (ከመንገድ ዳር መብራቶች ሀይል ተስቦላቸው)፣

ዓይነት 2

- ✓ የሳጥን ስፋታቸው ፡ 1.05 ሜትር በ 2.1 ሜትር ሲሆኑ በዐይነት 1 መጠለያዎች ላይ ብቻ የሚገኙ ሲሆን ከመጠለያዎቹ በቀኝ ጎን በኩል ይገኛሉ፣
- ✓ የማስታወቂያ ማሳያ መስታወት ስፋታቸው 1.6 ሜትር በ1.7 ሜትር፣
- ✓ የሀይድሮሊክ ተከፋች በር ያላቸው እና ከታች አንድ የማይዝግ ብረት ቁልፍ (Stainless steel lock) ያላቸው
- ✓ የብርሀን ሰጪ LED መብራቶች ያላቸው (ከመንገድ ዳር መብራቶች ሀይል ተስቦላቸው)፣



1.36 በተንቀሳቃሽ አካላት ላይ የሚሰቀሉ ማታወቂያዎች

1.36.1በተንቀሳቃሽ አካላት የላይኛው ክፍል ላይ የሚሰቀሉ ማታወቂያዎች:

- ✓ የመኪናን እንቅስቃሴ በማያውክ መልኩ በቀላል ቁስ መሰራት ይኖርባቸዋል፣
- ✓ እይታን እንዳይጋርዱ ቁመታቸው ወደላይ ከ ሀምሳ ሳንቲም መብለጥ የለበትም፣

1.36.2 በተንቀሳቃሽ አካላት ከጎን የሚሰቀሉ ማስታወቂያዎች

- ✓ መኪናው ላይ ለእይታና ለብርሀን ተብለው የተቀመጡትን ተካፋቾች መሸፈን የለበትም፣
- ✓ ከተካፋቾች ውጪ የመኪናውን አካል ሰባ በመቶ ብቻ እንዲሸፍኑ ይፈቀዳል፣





1.36.3 በተሸከርካሪ ዉስጥ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች

በተሸከርካሪዎች ውስጥ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች የሚሞሪ ካርዶች፣ ፍላሽና መሰል ኤሌክትሮኒክስ መረጃ አስተላላፊዎችን በመጠቀም መልእክት በስክሪኑ በማስተላለፍ ምርትንና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ ይረዳል።

የማስታወቂያ ማስነገሪያው ወይም ማሳያ ስክሪን መጠንም (15 inch, 17 inch, 18.5 inch, 19 inch, 22 inch, 24 inch, 26 inch, 32 inch ወዘተ) መሆን ይኖርበታል።



1.37 በኤሌክትሮኒክስ ስክሪን ለሚሰራጭ ማስታወቂያ

- ✓ ስክሪኖቹ ከእግረኛ ማቋረጫዎች እንዲሁም ከመስቀለኛና አደባባዩች 20 ሜትር መራቅ አለባቸው፤
- ✓ በሁለት ስክሪኖች መካከል ቢያንስ የ1 ሜትር ርቀት ሊኖር ይገባል፤
- ✓ ውቅር /Structure/ የሚፈቅደው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፣
- ✓ የድጅታል ማስታወቂያው ውቅር ትንተና /Structural Analysis/ መቅረብ አለበት /ለትልልቅ ስክሪን/፣
- ✓ ዴሲቤል በላይ ድምፁ የማይረብሽ እና ዝቅተኛ የኃይል ፍጆታ ሊኖረው ይገባል፤
- ✓ በቀላሉ ለጥገና አመቺ መሆን አለበት፤
- ✓ እጅግ በጣም ጥሩ የምስል ጥራት እና ተመጣጣኝ የብርሃን መጠን ሊኖረው ይገባል ፤
- ✓ ለተጠቃሚ ምቹ የሆነ እና የተለያዩ የፈጠራ ቅርጾች ያካተተ ቢሆን፤

ዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ ማለት የግለሰቦችን ወይም የድርጅቶችን የማይንቀሳቀስ ወይም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በማስታወቂያ በከፍተኛ ጥራት ግራፊክስ የሚያሳይ የኤሌክትሮኒክስ የዉጭ ማስታወቂያ ሚዲያ አይነት ነው። ዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ ማስቀመጥ ሲፈለግ /ሲመረጥ/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት።

1.37.1 ለአካባቢዉ ተስማሚ መሆናቸውን በተመለከተ

ዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ የት እንደሚገኝ ለመወሰን በሞቃት ወይም በቀዝቃዛ የአየር ሙቀት፣ እንዲሁም በዝናብ፣ በበረዶ፣ በነፋስ፣ በአቧራ ወይም በእርጥበት ሁኔታ እንዴት እንደሚሰራ ማጤን ሊኖርብን ይገባል። እንዲሁም የስክሪን ዲዛይን እና ማቀፊያው ለኤልኢዲዎች ቀጣይ ስራ እና ረጅም ጊዜ መቆየቱ ወሳኝ ነው።

1.37.2 የእይታ ጥራት በተመለከተ

የዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ የተመልካቹን ትኩረት የማይረብሽ እና ስለምርቱ መልእክት ብቻ የሚያስተላለፍ መሆን አለበት። እንዲሁም ብሩህ፣ እይታን የማይረብሽ እና ቀለሞችን በትክክል ማሳየት የሚችል መሆን ይኖርበታል። የፒክሰል መጠን በRGB ፒክስሎች መካከል ያለው ቦታ ሲሆን የፒክሰል መጠን በጣም ትልቅ ከሆነ የእይታ ጥራትን ይቀንሳል።

1.37.3 የብርሃን መጠን በተመለከተ

ዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ እስከ 5,000 nits (ስክሪኑ በእያንዳንዱ ካሬ ሜትር ሊያወጣ የሚችለዉ የሻማ መብራት) የሚመከር ሲሆን በቀጥታ የፀሐይ ብርሃን ላይ ላሉ ደግሞ 5,000+ nits ይመከራል።

1.37.4 ለደህንነት ትኩረት ከማድረግ አንጻር

የዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ ድምቀቱ ዋና የደህንነት ስጋት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም በጣም ደማቅ የሆነ ስክሪን አሽከርካሪዎችን ትኩረቱን ሊከፋፍል እና በምሽት ለመንዳት አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል የLED ማሳያዉ በአካባቢዉ ባለው ብርሃን መሰረት የስክሪኑን ብሩህነት እና ድምቀት ዝቅ ለማድረግ፣ ለምሳሌ በምሽት ላይ ያለውን ደማቅነት ለመቀነስ LED በራሱ የማደብዘዝ አቅም ያላቸዉ መሆን አለባቸዉ።

1.37.5 ጥገና እና አገልግሎት በተመለከተ

የዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ ሲሰራ ሁል ጊዜ ጥሩ መስሎ እንዲታይ እና በተቻለ መጠን ረጅም ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ መደበኛ ጥገና ወሳኝ ነው።

1.37.6 ስፋትና መጠንን በተመለከተ

- ✓ የኤሌክትሮኒክስ ዲጂታል የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች የማይለዋወጡ ኤሌክትሮኒክስና የታተሙ ምልክቶችን ይተካሉ፣
- ✓ ሙሉ በሙሉ በኮምፒዩተር ቁጥጥር ስር ያሉ፣ ዲጂታል ቢልቦርዶች ምስሎችን፣ ቪዲዮና አኒሜሽን ማሳየት ይችላሉ። እንዲሁም ለተመሳሳይ የማሳያ ስርዓት ለብዙ አስተዋዋቂዎች እቃዎችን እና አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ መልእክታቸውን ሙሉ በሙሉ በመለዋወጥ ይቀርባሉ።
- ✓ ምስሎችን በመለዋወጥ የተለያዩ የውጭ ማስታወቂያዎችን ማስተላለፍ ይችላል። እነዚህ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች በዋነኛነት በውጭ ማስታወቂያ ህግ ለሕዝብ አገልግሎት ዓላማዎችም ሊያገለግሉ ይገባል።
- ✓ ዲጂታል ቢልቦርዶች ለማስታወቂያዎች ከፍተኛ ትውስታን እና የሸማቾችን አወንታዊ አመለካከቶች ያመነጫሉ።

የዲጂታል ስፋት= የአንድ ዲጂታል ፓኔል ስፋት ነሜxነሜ ተገጠጥሞ ዲጂታል LED የውጭ ማስታወቂያ የሚሰራ በመሆኑ እንደጠያቂው ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል፣

ከመሬት በላይ ቁመት= 3.0 ሜትር

የመሸፈኛ ቁሳቁስ= የብረት መዋቅር፣ galvanized Plate እና ጠንካራ የፓነል መስታወት





በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥና አተገባበር በስታንዳርድ ባለመመራቱ እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትና የመንግስት ተቋማት ባለ መቀናጀታቸውና ሚናቸውን ባለማወቃቸው በዘርፉ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም። በዚሁ መሰረት የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን በተመለከተ ከዚህ በታች የተገለፀ ተቋማት ተቀናጅተው መስራት እንደሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነታቸው ተቀምጧል።

1.38 በተሸከርካሪ ላይ በድምጽ፣ በምስል ወይም በስዕል የሚተላለፍ የውጭ ማስታወቂያ

1.38.1 በተሸከርካሪ ላይ የሚለጠፍ ማስታወቂያ

1. ማንኛውም ሰው በንግድ ተሸከርካሪው ላይ የራሱን ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቅ ይችላል
2. ለሕዝብ አገለግሎት በሚውሉ ተሸከርካሪዎች ላይ ማስተዋወቅ የሚችለው የማስታወቂያ ወኪል ብቻ ነው
3. በተሸከርካሪ ላይ የሚለጠፍ የውጭ ማስታወቂያ እይታን በማይከልልና ብርሃን አስተላላፊ በሆነ ቁስ መሆን አለበት። ሆኖም በተሸከርካሪው ፊትና ኋላ መስታወት ላይ መለጠፍ የተከለከለ ነው።
4. በተሸከርካሪው ውስጥ የማስታወቂያ ወኪሉ ስምና አድራሻ፣ የፈቃድ ቁጥሩ፣ ፈቃዱን የሰጠው አካልና ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ ሁልጊዜ መያዝ ያለበት ሲሆን በተጠየቁ ጊዜ ማሳየት አለባቸው።
5. ከተከፋቾች ውጭ የመኪናውን ሰባ በመቶ ብቻ እንዲሸፍኑ ይደረጋል

1.38.2 በተሸከርካሪ ላይ በድምጽ የሚተላለፍ ማስታወቂያ

1. በዚህ መንገድ ማስተዋወቅ የሚቻለው ወቅታዊ ጉዳይን በተመለከተ ለሰሚናር፣ ለኤግዚቢሽን፣ ለሙዚቃ ኮንሰርት፣ እና ለምርጫ ቅስቀሳ እንዲሁም ሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ሲሆን ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው። ሆኖም በህመም ምክንያት በተሸከርካሪ በድምጽ እርዳታ የሚጠይቁ ከሆነ ከሆስፒታል በሚያመጡት ማስረጃ መሠረት በልዩ ፈቃድ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል።
2. በተሸከራካሪ ላይ በድምጽ የሚተላለፍ ማስታወቂያ ማስተዋወቅ የሚቻለው ከጧቱ 2፡00ሁለት እስከ ቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት(12፡00) ድረስ ብቻ ነው።
3. በትምህርት ቤቶች፣ በሆስፒታሎች፣ በፍርድቤቶች፣ ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላት በሚካሂድበት አካባቢ ወይም ከፍተኛ ድምጽ ያውካቸዋል በሚባሉ ተቋማት አካባቢ ማስተዋወቅ አይፈቀድም።
4. የድምጹ መጠን ከ50 ዴሲቤል መብለጥ የለበትም።
5. በተሸከርካሪ ላይ በድምጽ ወይም በድምጽና በምስል የማስተዋወቅ ስራ የሚሰሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ፈቃድ ማግኘታቸውን እና በተፈቀደው ሰዓትና ቦታ

ብቻ ማስተዋወቃቸውን የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ጽህፈት ቤት ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

6. በተሸከርካሪ ዉስጥ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች

7. በተሸከርካሪዎች ውስጥ በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች የሚሞሪ ካርዶች፣ ላሽና መሰል ኤሌክትሮኒክስ መረጃ አስተላላፊዎችን በመጠቀም መልእክት በስክሪን በማስተላለፍ ምርትንና አገልግሎትን ማስተዋወቅ ይቻላል

1.39 በባለመብራት ሳጥን ስለሚዘጋጅ የውጭ ማስታወቂያ

1. በባለመብራት ሳጥን ተዘጋጅቶ በመሬት ላይ በቋሚ ምሶሶ ወይም በሕንፃ አካል ላይ የሚተከል ወይም የሚቀመጥ የውጭ ማስታወቂያ

   ሀ. በቀላሉ በእሳት በማይያያዝ መሳሪያ መሰራት ይኖርበታል

   ለ. የራሱ የኤሌክትሪክ መስመር፣የኤሌክትሪክ ኮንዳክተር ወይም ኮንዲውትና መቆጣጠሪያ ሊኖረው ይገባል

2. በባለመብራት ሳጥን ተዘጋጅቶ በመሬት ላይ በቋሚ ምሶሶ ወይም መሰል አካል ላይ የሚተከል እና በህንፃ ላይ የሚሰቀል ማስታወቂያ

   ✓ በመሬት ላይ ስፋቱ ከ6 ካሬ ሜትር መብለጥ የለበትም

   ✓ በህንፃ ላይ ስፋቱ ከ4 ካሬ ሜትር መብለጥ የለበትም

   ✓ ቁመቱ ከ1.5 ሜትር ያላነሰ እና ወርዱ ከ3 ሜትር ያልበለጠ መሆን የለበትም

   ✓ በህንፃ ላይ የሚሰቀል ቁመቱ ከ0.5 ሜትር ያላነሰ እና ወርዱ ከ3 ሜትር ያልበለጠ መሆን አለበት

3. በባለመብራት ሳጥን የተዘጋጀ ማስታወቂያ ወይም ማናቸውም ብርሃን የሚጠቀም የማስታወቂያ ሠሌዳ ስፋቱ

   ✓ ከ0.5 ካሬ ሜትር በታች ከሆነ የሚቆመው የብርሃን ሃይል መጠን ከ1000 ሻማ በሜትር ካሬ

   ✓ ከ0.5 ካሬ ሜትር እና 2 ሜትር ካሬ መካከል ከሆነ የሚጠቀመው የብርሃን ሃይል መጠን ከ800 ሻማ በሜትር ካሬ፣መብለጥ የለበትም።

   ✓ በ2 ካሬ ሜትር እና በ10 ሜትር ካሬ መካከል ከሆነ የሚጠቀመው የብርሃን ሃይል መጠን ከ600 ሻማ በሜትር ካሬ መብለጥ የለበትም።

1.40 በጨርቅ ወይም በሸራ ባነር፣ወይም መሰል ነገር የሚዘጋጅ ተንጠልጣይ የውጭ ማስታወቂያ

1. በኤሌክትሪክ ወይም በስልክ ምሰሶ ላይ ባነርን በማንጠልጠል ወይም በመወጠር ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው።

2. በጨርቅ ወይም በሸራ ባነር፣ወይም መሰል ነገር የሚሰቀል ወይም የሚንጠለጠል የባነር ማስታወቂያ ፈቃድ ሲሰጥ

   ✓ ወቅታዊ ሁኔታዎች ብቻ ለማስተዋወቅ መሆን አለበት

   ✓ ለምርትና አገልግሎት ማስታወቂያነት መዋል የለበትም

   ✓ የቆይታው ጊዜ ወቅታዊ ሁኔታው ከመጀመሩ ከአንድ ወር በላይ እንዲሁም ከተጠናቀቀ በኋላ ከአንድ ሳምንት በላይ መቆየት የለበትም፡

   ✓ በአደባባይ ላይ ባነር በማንጠልጠል ወይም በመወጠር ማስተዋወቅ አይቻልም። ሆኖም ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር በሚደረግ ስምምነት ለህዝብ አገልግሎት ለሚውል ማስታወቂያ ሊፈቀድ ይችላል

   ✓ የማህበራዊ ተቋማት የሚሰቅሉት ባነር እስከ አንድ ወር ከ15 ቀን ድረስ በክፍያ መስቀል ይችላሉ

የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ እና ክትትል መስፈርት ለመሬሪያ እና ሲታንዳርዱ ቁጥር 01/2015

1.41 በበራሪ ወረቀቶች የሚሠራጭ የውጭ ማስታወቂያ

በፓስተር፣ በአነስተኛ ስቲከር፣ በተባዛ በራሪ ወረቀት ወይም በብሮሸር፣ በሊፍሌት፣ በፍላየር፣ በስቲከር፣በወረቀት ማስታወቂ እና መሰል ሁኔታ የሚዘጋጅ የውጭ ማስታወቂያ ሲሆን

1. መለጠፍ የሚቻለው ለዚህ አገለግሎት ተብለው በተዘጋጁ የየውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች ብቻ መሆን አለበት
2. በግድግዳ ላይ ወይም በአጥር ላይ ወይም በአውቶቡስ ፌርማታ ወይም በስልክና በኤሌክትሪክ ምሰሶ ወይም መሰል አገለግሎት መስጫ ላይ መለጠፍ ወይም ማጣበቅ የተከለከለ ነው
3. የተባዙ በራሪ ማስታወቂያዎችን ከአየር ወደ መሬትም ሆነ በመሬት ላይ በመበተን ማስተዋወቅ የተከለከለ ነው
4. በዚህ አንቀጽ 23.2 እና 23.3 የተደነገገው ድንጋጌ ለትርፍ ባልተቋቋመ የመንግስት መሥሪያ ቤት በሚሰራጭ የሕዝብ ማስታወቂያ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም
5. በብሮሸርና መሰል በራሪ ወረቀቶች የሚሠራጭ የውጭ ማስታወቂያ የሚተዋወቅለት ድርጅት ለሚተላለፈው መልዕክት ኃላፊነት አለበት

1.42 በጎዳና እቃዎች ላይ ስለሚቀመጥ የውጭ ማስታወቂያ

በአውቶቢስ ፌርማታ በሚገኙ መጠለያዎች፣ በአትክልት መከለያዎች፣ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ፣ ህዝብ መፀዳጃ ቤትና መሰል የጎዳና እቃዎች ላይ የሚለጠፍ ወይም በማናቸውም መንገድ የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ

- ✓ የእቃዎችን አገልግሎት አሰጣጥ የሚያሰናክል ወይም የሚያውክ ሁኔታ መለጠፍ ወይም መቀመጥ የለበትም
- ✓ የትራፊክ እንቅስቃሴን በሚገታ ወይም ደኅንነቱን በሚቀንስ ሁኔታ መሰራጨት የለበትም
- ✓ የሚለጠፍ ወይም የሚሰቀል ማስታወቂያ ስፋት/መጠን/ አዲስ በወጣው ስታንዳርድ መሰረት ይሆናል

1.43 በተንሳፋፊ ፊኛ፤ በኬብል የሚንሸራተትና መሰል ነገር ላይ የሚሰራጭ ማስታወቂያ

1. በተንሳፋፊ ፊኛ፣ ውል ብልቢትና መሰል ተንሳፋፊ ነገር ላይ የተዘጋጀ የውጭ ማስተወቂያ በአየር ላይ እንዲንሳፈፍ ሲደረግ የአውሮኘላን ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥል መሆን የለበትም
2. በተንሳፋፊ ፊኛ፣ ውል ብልቢትና መሰል ተንሳፋፊ ነገር ላይ የተዘጋጀ የውጭ ማሰተወቂያን በአየር ላይ ለማንሳፈፍ የማስታወቂያ አስነጋሪው፣ አዘጋጁ ወይም አሰራው በቅድሚያ አግባብ ካለው አካል የተፈቀደለት መሆን አለበት
3. በተነሳፋፊ ፊኛ፣ ውል ብልቢትና መሰል ተንሳፋፊ ነገር ላይ የተዘጋጀ የውጭ ማስተወቂያን
4. በሚመለከተው አካል ከተፈቀደው ከፍታ በላይ በአየር ላይ ማንሳፈፍ የተከለከለ ነው
5. በሚመለከተው አካል በተከለከለ የአውሮኘላን ማረፊያ ክልል ውስጥ ማንሳፈፍ እና በማናቸውም መንገድ ላይ ሆኖ እንዲንሳፈፍ ማድረግ የተከለከለ ነው
6. በኬብል በሚንሸራተት የሚሰራ ማስታወቂያ
   - ✓ ሌላ የተዘረጋ መሰረተ ልማትን የማያውክ፤ የማይከለክልና የማያደናቅፍ መሆን አለበት
   - ✓ በአካባቢው በሚኖሩ ግንባታወች ላይ ከፍተኛ የእይታ ክልከላ የማያደርግ መሆን አለበት

ማስፈፀሚያ ስልቶች

በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥና አተገባበር በስታንዳርድ ባለመመራቱ እንዲሁም በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትና የመንግስት ተቋማት ባለ መቀናጀታቸውና ሚናቸውን ባለማወቃቸው በዘርፉ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም። በዚሁ መሰረት የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥርን በተመለከተ ከዚህ በታች የተገለፁ ተቋማት ተቀናጅተው መስራት እንደሚገባቸው ተግባርና ኃላፊነታቸው ተቀምጧል።

- ➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሙኒኬሽን ቢሮ፣**

- በከተማዋ የሚተከሉ ማስታወቂያዎች ይዘታቸው ከማህበረሰቡ ባህልና ወግ ጋር የሚጣጣሙ መሆኑን ይከታተላል፤
- የማስታወቂያ ስራ ለመስራት ለሚፈልጉ ማንኛውም ሰው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን፣**

- በስታንዳርዱ መሰረት የማስታወቂያ ፈቃድ ይሰጣል፤
- በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን፣**

- በመንገዶች ዳርቻና ድልድዮች ላይ የሚሰጡ የማስታወቂያ ቦታዎችን በተመለከተ ይገመግማል፤
- በድጋፍ ግንብ ግድግዳዎች እና በድልድይ መሰሶዎች ላይ የሚሳሉ የማስታወቂያ ስዕሎች በተመለከተ ይሁንታ በመግለፅ በባለስልጣኑ በኩል ፍቃድ ይሰጣል፣

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ፣**

- ለማስታወቂያ አግልገሎት የሚውሉ ቦታዎችን በተመለከተ ከይገባኛል ጥያቄ ነፃ መሆናቸውን አጣርቶ በጊዚያዊነት ቦታ ይሰጣል፤

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ፣**

- በከተማዋ የሚሰቀሉ፣የሚለጠፉ እና የሚዘዋወሩ ማስታወቂያዎች ከህበረተሰቡ ባህልና ታሪክ ያፈነገጡ እንዳይሆኑ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ፣**

- በመንገድ ዳር የሚተከሉ ማስታወቂያዊች ከትራፊክ ደህንነት አንፃር አግባብ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
- በተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪዎች የሚነገሩ ማስታወቂያዎች ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ይቆጣጠራል፤
- በድምጽ የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በኩል ይሁንታ ካገኘ በኋላ በኤጀንሲው በኩል ክትትል በማደረግ የቅንጅት ስራ ይሰራል፣
- የትራፊክ ምልክቶች እና የትራፊክ አመላካቾች በትራፊክ ማኔጅመንት ስታንዳርድ መሰረት ያለፈቃድ የሚተከሉ ይሆናሉ፣

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ፣**

- ለአረንጓዴ ቦታነት በተከለሉ ቦታዎች በህገ ወጥ መንገድ የተተከሉ ማስታወቂያዎችን በተመለከተ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ቁጥጥር ያደርጋል፤

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፣**

- በተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪዎች የሚነገሩ ማስታወቂያዎችን የድምፅ ብክለት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ፣**

- የአውቶብስ መጠበቂያ መጠለያዎች ላይ የሚገኙ የውጭ ማስታወቂያ መለጠፊያ ሳጥኖችን ላይ የሚለጠፉ ማስታወቂያዎች በግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ፈቃድ በማግኘት አገልግሎት እንዲውል ይደረጋል፣

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ፣**

- የማስታወቂያ ስራ ለመስራት ለሚፈልጉ ማንኛውም ሰው የንግድ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ይጠይቃል፣ሲያሟሉ ፈቃድ ይሰጣል፤

የወጣ የማስታወቂያ ፈቃድ አዋጅ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ማስታወቂያ መለጠፊያ እና ስታንዳርድ ቁጥር 01/2015

➢ **የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን፣**

- በህገ ወጥና ከስታንዳርድ ውጪ የተተከሉ ማስታወቂያዎች ላይ እርምጃ ይወስዳል፤
- ጊዜያቸው ያለፈባቸውን እና ባለቤት የሌላቸው ማስታወቂያዎች ከሚመለከታቸው አካላቶች ጋር በመሆን እንዲነሱ ያደርጋል፤
- ባልተፈቀዱ ቦታዎች የሚተከሉ ማስታወቂያዎች የከተማዋን ገፅታ ስለሚያበላሹ ተከታትሎ አግባብ ባለው ህግ እርምጃ ይወስዳል፤

➢ **ፍትህ ቢሮ፣**

- በህግ አግባብ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
- ህገወጥ የወጭ ማስታወቂያ የሚለጥፉ እና የሚሰቅሉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ተጠያቂ እንዲሆኑ ከህግ አስከባሪ አባላት ጋር በመሆን ክስ በመመስረት ተባባሪ ሊሆኑ ይገባል፣

➢ **ቀላል ባቡር ኮርፖሬሽን**

- የውጭ ማስታወቂያ አስነጋሪ ተቋማት በቀላል ባቡር ውስጥ እና በባቡሩ የውጭ ገፅታ ላይ እንዲሁም በባቡር መጠበቂያና ሀዲድ ድልድዮች ላይ ማስተዋወቅ ሲፈልጉ ከግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ፈቃድ ማውጣት እንዳለባቸው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፣

➢ **የኢትዮጵያ ማስታወቂያ ስራ ማህበር**

- የማስታወቂያ ስርአትን በጠበቀ መልኩ ስራዎች እንዲከናወኑ ለአባላቶቻቸው የግንዛቤ ስራ ማከናወን እና ያለፍቃድ ማስታወቂያዎች እንዳይሰቀሉ እንዳይለጠፉ ወይም እንዳይንጠለጠሉ በማህበሩ በኩል ክትትል ያደርጋል፣

ክፍል ዘጠኝ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1.44 የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት።

1.45 የውጭ ማስታወቂያን አለአግባብ ስለማስወገድ

ማንኛውም ሰው ፈቃድ በማግኘት የተተከለ፣ የተለጠፈ ወይም በማናቸውም መንገድ የተሰራጨ ሕጋዊ የውጭ ማስታወቂያን ሆነ ብሎ የማስታወቂያ አስነጋሪውን ለመጉዳት በማሰብ ማስወገድ የለበትም።

1.46 አቤቱታ ስማቅረብ

1. ከውጭ ማስታወቂያ ጋር በተያያዘ የዚህን መመሪያና የደንቡን ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተሰራጨ ማንኛውም ማስታወቂያ መብቱ የተጣሰ ሰው የማስታወቂያው ስርጭት ፈቃድ እንዲታገድለትና ማስታወቂያው እንዲወገድለት ለፈቃድ ሰጪው አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፣
2. የዚህ አንቀጽ 30(1) ድንጋጌ ሥልጣን ላለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብን የሚከለክል አይሆንም።

1.47 ይግባኝ ስለማቅረብ

1. በፈቃድ ሰጪው ስር በየደረጃው ባሉ አስፈፃሚ አካላት በተሰጠው ማናቸውም ውሳኔ ላይ አቤቱታ ያለው ሰው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን በፅሁፍ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፣
2. ፈቃድ ሰጪው የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው ከ30 ቀናት ባነሰ ጊዜ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፣

የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ እና ክትትል ማስፈፀሚያ መመሪያ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቁጥር 01/2015

3. *ሥልጣን ለተሰጠው የመንግሥት አካል ይግባኝ የማቅረብ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለስልጣኑ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።*

1.48 የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. *ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በሕግ መሰረት ፈቃድ ተሰጥቶት እና የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎበት የተተከለ፣ የተለጠፈ ወይም በማናቸውም መንገድ የተሰራጨ የውጭ ማስታወቂያ የደንቡን እና የመመሪያውን ድንጋጌዎች የሚያሟላ ከሆነ በዚህ መመሪያ መሰረት ፈቃድ እንዳገኘ ይቆጠራል፣*

2. *ይህ መመሪያና ደንቡ ከመውጣቱ በፊት ፈቃድ ሳይሰጠው ወይም ፈቃድ ቢሰጠውም የአዋጁን፣ የደንቡንና የመመሪያ ድንጋጌዎች የማያሟላ የውጭ ማስታወቂያ የተከለ ወይም በማናቸውም መንገድ ያሰራጨ የማስታወቂያ ሥራ ወይም አሰራጭ፣*

   ሀ. ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ የውጭ ማስታወቂያው እንዲሰራጭ ማመልከቻውን በፅሁፍ ለባለስልጣኑ ማቅረብ እና የተሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ የዚህን መመሪያና የደንቡን ድንጋጌዎች አሟልቶ ከተገኘ ማስታወቂያው እንዲሰራጭ የተፈቀደለትና የተመዘገበ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ መያዝ እና ለማስታወቂያው የተወሰነውን ክፍያ መክፈል አለበት፣

   ለ. የተሰራጨው የውጭ ማስታወቂያ የዚህን መመሪያና የደንቡን ድንጋጌዎች ባለማሟላቱ እንዲሰራጭ ፈቃድ ካላገኘ ማስታወቂያውን ማንሳት ወይም ማስወገድ አለበት፣

3. *ይህ መመሪያና ደንቡ ከመውጣቱ በፊት ለውጭ አገር ዜጋ በውጭ ማስታወቂያ ሥራ እንዲሰማራ እና የሌሎችን ሰዎች የውጭ ማስታወቂያ እንዲያሰራጭ የተሰጠ ፈቃድ መሰረዝ ይኖርበታል፣*

4. *በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሰረት የውጭ ማስታወቂያ ስርጭት ፈቃዱ የተሰረዘበት የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት ይህ መመሪያና ደንቡ ከመውጣቱ በፊት ተክሎ ለሌላ ሰው የሚያከራየውን የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳ ፍሬም፣ የውጭ ማስታወቂያ መለጠፊያ ሳጥን ወይም ቦርድ ወይም መሰል የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጫ መሳሪያ ወይም ተያያዥ ንብረቶችን በማንሳት መውሰድ ወይም ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ይችላል።*

1.49አስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ቅጣት

በማስታወቂያ አዋጁ ቁጥር 759/2004 የተደነገገው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ፡-

1. *በዚህ መመሪያ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ በሚከፈልበት ጊዜ ውስጥ የሚፈለግበትን የአገልግሎት ክፍያ በሙሉ ያልከፈለ ማንኛውም ሰው ክፍያውን ማጠናቀቅ ካለበት ከመጨረሻው ቀን በኋላ ክፍያውን ላዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር ከሚፈለግበት የአገልግሎት ክፍያ ከመቶ አስር ፐርሰንት መቀጮ እየተጨመረበት ይከፍላል*

2. *የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሳይከፍል ከሁለት ወራት በላይ ከቆየ ግንባታ ፈቃድ ሰጭው የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳውን በማንሳት ይወርሳል፣ ያነሳበትንም ወጪ በህግ ይጠይቃል፣*

3. *የዚህን መመሪያ ወይም ሌሎች ህጐች ድንጋጌ ባለማክበር የውጭ ማስታወቂያ በደንብ ማስከበር ባለስልጣን አማካይነት የተነሳበትና ለዚሁ የወጣውን ወጪ የከፈለ ሰው በከተማው ክልል በማንኛውም ቦታ የውጭ ማስታወቂያ ሥራ ወይም የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ ጥያቄ ቢያቀርብ ለአንድ ዓመት እንዳይስተናገድ ይታገዳል፣*

4. *ለአጭር ጊዜ በፖስተር፣ በስቲከር፣ በባነር ለሚለጠፍና ለሚንጠለጠል እንዲሁም በብሮሸር፣ በሊፍሌት፣ በራሪ ወረቀት የሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ በተጨማሪ ለሚቆየው ለእያንዳንዱ ቀን የአገልግሎት ክፍያው ሁለት እጥፍ ይከፈልበታል። ሆኖም የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ሳምንት የሚበልጥ ከሆነ ባለስልጣኑ በራሱ ወጪ ያነሳዋል፤ ወጪውንም የማስታወቂያዉ ባለቤት እንዲተካ ያደርጋል፣*

5. *ያለፈቃድ ወይም ከተፈቀደለት ሰዓት ውጭ በመኪና ላይ የማስታወቂያ ሥራ ሲሰራ የተገኘ አሽከርካሪ ብር 1,600.00 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ይቀጣል ማስታወቂያው በመኪናው ላይ የተለጠፈ ከሆነ እንዲያነሳ ይደረጋል፤*

6. *ማንኛውም ሰው የዚህን መመሪያና የደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ብር 2,000.00 (ሁለት ሺህ ብር) መቀጮ ይከፍላል።*

7. የዚህን መመሪያና የደንቡን ድንጋጌ በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕጉ መሠረት የሚያስቀጡት ሁኔታዎች ውጭ፣ በአደባባይ ወይም ሕዝብ በሚያየው ቦታ መልካም ሥነ-ምግባርን ወይም መልካም ጠባይን የሚነካ ድርጊት አስቦ የፈጸመ እንደሆነ፣ የተከለከሉ የውጭ ማስታወቂያዎችን ያሰራጨ እና ገድብ የተደረገባቸውን ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ያደረገ ብር 4,000 (አራት ሺ ብር) መቀጮ ይከፍላል።

8. በዚህ መመሪያና ደንብ የተሰጠውን ክልከላና ግዴታ ያልተወጣ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፣

1.50 መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 01/2015 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥቅምት 01/2015 ዓ.ም

ሰጦታው አካለ (ኢ/ር)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር

የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ አሰጣጥ እና ከታገዱ ማስፈፀሚያ መመሪያ እና ሰታንዳርድ ቁጥር 01/2015

በአዲስ አበባ ከተማ
ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን

ADDIS ABABA CITY
BUILDING PERMIT & CONTROL
AUTHORITY

ቁጥር፡- ግፈቁባ/መፈዳ/____/____/2015 ቀን፡- ____/____/2015 ዓ/ም

የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ ምስክር ወረቀት

የባለቤት /አመልካች ስም ____ የድርጅቱ ስም ____ ስልክ ____

አድራሻ፡ ክ/ከተማ ____ ወረዳ ____ የአካባቢው ልዩ ስም ____ /የመንገድ/አደባባይ/ድልድይ/ ____

አካባቢያዊ ኮኦርዲኔት X ____ Y ____

አገልግሎት ዓይነት፡- የውጭ ማስታወቂያው ስፋት ____ የውጭ ማስታወቂያው ዓይነት ____

በግል ይዞታ/ህንፃ ግድግዳ/አጥር ላይ ____ ህንፃ አናት ላይ ____ የሚተከል በብርሀን/በምስልና/ድምፅ/እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ____

በተሸከርካሪ አካል ላይ ____ ቦታ ባለሁለት /ሶስት ምስል ____ በግድግዳና ጣራ ላይ የሚሳል ስዕል ____ የበረንዳ ጥላ/በፌርማታ/በነዳጅ ማደያ ____

የከፈሉት ገንዘብ መጠን ____ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን ____ ቃድ የሚያበቃበት ቀን ____

የማስታወቂያ ይዘት

ማስታወቂያው ይቻላል

በፎቶ ይለጠፍ

++

ሳይት ፕላን

ከ base map 1988,1997, ላይ ማስገባት

ከላይ በዝርዝር የተገለጸው የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድ ጥያቄ ተመርምሮ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል።

ያዘጋጀው	ያረጋገጠው	ያፀደቀው
ስም ----------	ስም ----------	ስም ----------
ፊርማ ----------	ፊርማ ----------	ፊርማ ----------
ቀን----------	ቀን----------	ቀን----------

ማሳሰቢያ፥ ይህ ፍቃድ በሶስት ቅጂ ተዘጋጅቶ ዋናው ለባለቤቱ ሁለተኛው ቅጂ ለዳይሬክቶሬቱ/ለቡድኑ ሶስተኛው ለመዝገብ ቤት ይሆናል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፸፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን 2ሺ3ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 71
ADDIS ABABA 24 th May 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር 2)፸3/2ሺ3
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕንጻ ደንብ ...ገፅ ፭ሺ፰፻፺፩

CONTENTS

Regulation No243. /2011
Council of Ministers Building Regulation …Page5891

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 2)፸3/2ሺ3
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕንጻ ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩//፪ሺ፫ አንቀጽ 5 እና በኢትዮጵያ ሕንጻ አዋጅ ቁጥር 6፻፳4/፪ሺ፫ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1/ አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕንጻ ደንብ ቁጥር 2)፸3/2ሺ3 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2/ ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1/ #ጊዜያዊ ግንባታ; ማለት የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት የሚገነባ እና የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ የሚነሳ የሕንፃ ግንባታ ነው፤

2/ #የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ; MEት በርካታ እና የተለያዩ ተጠቃሚዎችን የሚስብ እንደ ቲያትር ቤት፣ የሕዝብ ቤተ መፃሕፍት፣ መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ መዝናኛ፣ የትምህርት ተቋም፣ የህክምና አገልግሎት መስጫ፣ የገበያ ማእከል እና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ህዝብ የሚገለገልበት ሕንፃ ነው፤

3/ #ትንታኔ; ማለት ፕላን ወይም ዲዛይን ለማዘጋጀት የሚሰራ ስሌት ወይንም እነዚህን ለመደገፍ የሚዘጋጅ ማብራሪያ ነው፤

4/ #የፕላን ስምምነት; ማለት ለሕንፃ ግንባታ እንዲቀርብ ለሚዘጋጅ ኘላን ከከተማው ፕላን ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስችለው መሆኑን በማረጋገጥ የሚሰጥ በአንድ ቦታ ሊገነቡ የሚችሉ

Council of Ministers Regulations No……../2011

This Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.691/2005 and Ethiopian Building Proclamation No. 624/2009.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Building Regulation No. 243/2011".

2. Definitions

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1/ "temporary construction" means a temporary construction erected for a limited period of time and to be demolished at the completion of such period;

2/ "public building" means any building such as a theatre hall , public library, conference hall, a recreational place, academic institution, a medical center, or a market or any other similar building serving the public ;

3/ "analysis" means a mathematical computation worked out so as to prepare the plan or a description to support the same;

4/ "planning consent" means a document verifying the compliance of a proposed construction plan

ወይም ለቦታው ያልተፈቀዱ የአገልግሎት አይነቶችን፣ ለቦታው የተፈቀደ የሕንፃ ከፍታን፣ በቦታው አካባቢ የሚያልፉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን፣ ነባራዊ እና የታቀዱ መጠኖችን ወይም ስፋቶችን የሚያሳይ የኘላን መረጃ ነው፤

5.# "የፕላን ማሻሻያ" ማለት በነባሩ ፕላን ለሕንፃው ምድብ የተጠየቁ ፕላኖችን ትንታኔ ሙሉ ለሙሉ መከለስ ሳያስፈልግ የሚደረግ ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ነው፤

6. "ሪል እስቴት" ማለት ለሽያጭ፣ ለኪራይ ወይም ለሊዝ አገልግሎት እንዲውል የተገነባ ሕንፃ ነው፤

7. "የአገልግሎት ለውጥ" ማለት አንድ ሕንፃ ያለውን ነባር አገልግሎት በሌላ ዓይነት አገልግሎት መለወጥ ነው፤

8. "የግንባታ ፈቃድ" ማለት አንድ የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ ለሚፈልግ አካል ሕንፃውን ለመገንባት የሚያስችሉት ዝርዝር መስፈርቶች እንደተሟሉ በከተማው ሹም ተረጋግጦ ግንባታ እንዲካሄድ ፈቃድ መሰጠቱን የሚገልጽ ማስረጃ ነው፤

9. "ማስታወቂያ" ማለት በሕንጻ ዲዛይን እና ግንባታ ወቅት የከተማ አስተዳደር፣ የተሰየመ አካል ወይም የሕንፃ ሹም ለሕንፃው ባለቤት ወይም የሕንፃው ባለቤት ለተጠቀሱ አካላት የሚያቀርበው የጥያቄ፣ የትእዛዝ፣ የመረጃ፣ የማስጠንቀቂያ ሠነድ ነው፤

0. "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የህንፃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፬/፪ሺ፩ ነው።

ክፍል ሁለት

አስተዳደር

3. ማመልከቻና ፕላን ስለማቅረብ

1. በአዋጁ አንቀፅ 4 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ

ሀ) የአመልካቹን ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ለ) ሕንፃው እንዲሰጥ የተፈቀደለትን አገልግሎት፣

ሐ) ሕንፃው የሚገነባበትን ቦታ፣

መ) የሕንፃውን ወለል ጠቅላላ ስፋት የሚገልጽ ሠንጠረ ¡ ፣

ሠ) የፕላን ስምምነት ማስረጃ፣

ረ) የኮንክሪት ጣሪያ ላላቸው የምድብ "ሀ" ህንፃዎች የአርኪቴክቸር፣ የስትራክቸር እና የኤሌክትሪክ ፕላን፣

with that of the plan, the type of permitted buildings and services prohibited , permitted heights of buildings to be constructed in a given topology, or indicating the adjacent infrastructures, as well as the size of existing and planned buildings on the area;

5/ "plan revision" means an expansion or revision of an existing plan without causing full revision of the requirements and descriptions thereof;

6/ "real estate" means a building built for the purpose of sale, rent or lease services;

7/ "alteration of service" means changing of the existing service of a certain building;

8/ "construction permit" means a document verifying the permission give to a person to construct a building upon fulfillment of necessary requirements of the plan;

9/ "notice" means a letter of request, an order, information, or waiting which the urban administration, designated organ, or a building officer produces to the owner of a building or vise versa;

10/ "Proclamation" means the Ethiopian Building Proclamation No.624/2009.

PART TWO

ADMINISTRATION

3. Submission of Application and Plans

1. Application submitted as per Article 4 of the Proclamation shall contain:

a) full name and address of the applicant,

b) permitted service for the building,

c) location of construction,

d) table showing the total area of the floors,

e) planning consent,

f) architectural, structural and electrical designs for buildings of Category "A" having concrete roofing,

ሰ) የኮንክሪት ጣሪያ ለሌላቸው የምድብ "ሀ" ህንፃዎች የአርኪቴክቸር፣ እና የኤሌክትሪክ ፕላን፣

ሸ) ለሕንፃ ምድብ "ለ" የአርኪቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካል ፕላን እና የአፈር ምርመራና ስትራክቸር ትንታኔ ሪፖርት፣

ቀ) ለሕንፃ ምድብ "ሐ" ለህንፃ ምድብ "ለ" ከተጠየቁት በተጨማሪ የእሳት አደጋ መከላከያ ፕላን፣

በ) ሊፍት እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን የሚጠቀሙ ህንፃዎች የኤሌክ ትሮ-መካኒካል ፕላኖች እና ትንታኔዎች፣

ተ) በአዋሳኝ ቦታዎች የሚገኙ ግንባታዎች ከመሬት በላይ እና በታች ያላቸው የወለል ብዛት እና ከጋራ ወሰን ያላቸው ርቀት፣እና

ቸ) የሕንፃውን ፕላን ያዘጋጁ የተመዘገቡ ባለሙያዎች ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና ፊርማ ያረፈበት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ኮፒ፣

ጋር ተያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ተ) ላይ የተገለፀው የአዋሳኝ ቦታዎች መረጃ በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚዘጋጅ ቅፅ አጐራባቾን በማስሞላት የሚቀርብ ይሆናል፡፡

3. የግንባታ ፈቃድ በተጠየቀበት ይዞታ የአጐራባች ቦታ ላይ የሚገኝ ባለይዞታ ይዞታውን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰውን ቅጽ የመሙላት ግዴታ አለበት፡፡

4. የሕንጻ አገልግሎት ለውጥ ወይም ማሻሻያ ለማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በአገልግሎት ለውጥ ወይም ማሻሻያ ከሚገኘው የሕንጻ ምድብ ጋር ተመሳሳይ ለሆነ አዲስ ሕንፃ የሚጠየቁትን ፕላኖች ከትንታኔያቸው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ የሕንጻው ፕላኖች ከሌሉ የነባሩ ሕንፃ ልኬት ተሰርቶ ከተለካበት አግባብ እና ከትንታኔአያቸው ጋር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

4. <u>የኘላን ስምምነት</u>

1. የኘላን ስምምነት ለማግኘት ገንቢው የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሚያዘጋጀው ቅፅ ሊገነባ ያቀደውን ሕንፃ ከፍታና የአገልግሎት ዓይነት ገልፆ በመሙላት የይዞታውን ካርታ ዋናውንና ኮፒውን በማያያዝ ጥያቄ ማቅረብ አለበት፡፡

g) architectural and electrical designs for buildings of Category "A" which have no concrete roofing,

h) architectural, structural, sanitary, electrical designs and soil test and structural analysis report for buildings of Category "B",

i) in addition to the plans required for buildings of Category "B", fire safety plans and descriptions thereof shall be submitted for buildings of Category "C",

j) electro-mechanical designs and analysis for buildings using lifts and artificial ventilation,

k) number of floors of neighboring buildings below and above ground level and their distance from the boundary lines, and

l) full name, address, signature and a copy of registration certificate of professionals who prepared plan of the building.

2/ The information relating to neighbors referred to in sub article (1) (k) of this Article shall be submitted by making such neighbors to fill the form prepared by the urban administration.

3/ Possessors of the lands adjacent to the area for which a building permit is requested are under obligation to fill the form mentioned in sub article (2) of this Article.

4/ The request for any alteration of services or renovation shall be as per requirement stated for the new category of building to which it belongs. Where the building plan does not exist, the request shall be submitted with as built drawings and analysis.

4. <u>Planning Consent</u>

1. The owner of a building shall fill the form prepared by the urban administration by showing the height and the type of service of the building to be constructed and submit his application attached with the original and a copy of the title deed in order to obtain a plan consent.

2/ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል አዲስ ህንፃ ለመገንባት ለተጠየቀ የኘላን ስምምነት፡-

ሀ) የይዞታ ካርታ፣ እና

ለ) የተፈቀደውን የሕንፃ ከፍታ እና አገልግሎት ዓይነት የሚገልጽ፣

የኘላን ስምምነት ይሰጣል፡፡

3/ ነባር ሕንፃን ለማሻሻል ወይም አገልግሎት ለመለ ወጥ ለተጠየቀ የኘላን ስምምነት የከተማው አስተዳደር፡-

ሀ) የይዞታ ካርታ፣ እና

ለ) የተፈቀደውን የሕንፃ ከፍታ እና የአገልግሎት ዓይነት የሚገልጽ፣

የኘላን ስምምነት ይሰጣል፡፡

4/ የከተማ ኘላን በሌላቸው ከተሞች የሕንፃ ከፍታ እና የአገልግሎት ዓይነት አወሳሰን እና የኘላን ስምምነት አሰጣጥ ክልሉ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

5/ የሕንፃ ሹመ በአዋጁና በዚህ ደንብ ውስጥ የተቀመጡትን የሕንፃ ምድብ መለያዎችን መሠረት በማድረግ ለማምገማ የሚቀርቡለትን ሕንፃዎች ምድብ ይወስናል፡፡

6/ የሕንፃ ሹመ ለኘላን ስምምነት የቀረበለትን ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ ከከተማው ኘላን ጋር የሚጣጣም ወይም የማይጣጣም ስለመሆኑ ምክንያቶቹን በመዘርዘር ከሦስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ መልስ ይሰጣል፡፡

5. ኘላን ስለማስፀደቅ

1/ በአዋጁ አንቀፅ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጎሉ ያልሆኑ ግድፈቶችን ለማረም በኘላን ላይ የሚሰፍሩ አስተያየቶች፡-

ሀ) የኘላኑን ተነባቢነት የሚቀንሱ መሆን የለባቸውም፤

ለ) ባልደበዘዘ፣ ከኘላኑ ሊጠፉ በማይችል ሁኔታ እና ኘላኑ ኮፒ ሲደረግ በኮፒው ላይ በሚወጡበት ሁኔታ መስፈር አለባቸው፡፡

2/ የጎሉ ያልሆኑ ግድፈቶች ዝርዝር በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ ከግንባታ ፈቃድ ጋር በግንባታ ቦታ ተቀምጦ ለግንባታ ክትትል የሚውል "ለቁጥጥር አገልግሎት ብቻ የሚያገለግል" የሚል ማህተም ያረፈበት የፀደቀ ኘላን ኮፒ ለገንቢው ይሰጣል፡፡

6. የኘላን መገምገሚያ ጊዜ

1/ ለአንድ የሕንጻ ዓይነት የተዘጋጁ ኘላኖችን ለመገምገም የሚያስፈልገው ጊዜ፡-

2/ The urban administration shall, in case of a request for plan consent to build a new building, grant:

a) title deed and

b) a plan information describing the height and the permitted type of service.

3/ In case of a request of plan consent for a renovation of a building, the urban administration shall grant:

a) title deed, and

b) a plan information describing the height and the permitted type of service.

4/ For urban centers having no urban plan, the height, the type of services of buildings and the issuance of consent shall be determined by directives to be issued by the respective regions.

5/ The building officer shall determine the category of buildings submitted for his approval in accordance with the criteria set within the Proclamation and these Regulation.

6/ The building officer shall decide the compliance or non- compliance of the application with the urban center and notify the applicant his decision and the reasons thereto, in writing, within three working days.

5. Approval of Plans

1/ Without prejudice to Article 6 of the Proclamation comments referring to minor non-compliance shall not:

a) be made in a manner that reduces the legibility of the plan:

b) be dull and easily removable and shall appear on the copy when the plan is copied.

2/ The lists of minor non-compliance shall be determined by directives to be issued in accordance with this regulation.

3/ A building owner shall be issued with a copy of such plan stamped with "For Inspection Purpose Only" together with the construction permit to be displayed at the site.

6. Plan Review Period

1/ The time needed for review of plans shall not exceed:

ሀ) ከሪል እስቴት ውጪ ላለ በምድብ "ሀ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከአምስት የሥራ ቀናት፤

ለ) በምድብ "ለ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች መገምገሚያ ጊዜ ከ7 የሥራ ቀናት፣ እና

ሐ) በምድብ "ሐ" ስር ለሚካተት ሕንፃ እና በምድብ "ለ" ውስጥ ለሚካተቱ የሪል እስቴት ህንጻዎች ኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ፳፩ የሥራ ቀናት፣
የበለጠ መሆን የለበትም።

2/ በአንድ ሰው የሚቀርቡ እና በአንድ የፕሮጀክት ቦታ የሚገነቡ የሕንፃ ዓይነቶች ከአንድ በላይ ከሆኑ ለፕላን ግምገማ የሚያስፈልገው ጊዜ እን ደየሕንፃ ዓይነቱ ለአንድ ህንፃ የሚያስፈ ልገውን ጊዜ ብዜት ሆኖ የጠቅላላው ፕላን መገምገሚያ ጊዜ ከ፳፩ ቀናት መብለጥ የለበትም።

3/ ለየምድቡ የተሰጠው የፕላን መገምገሚያ ጊዜ የሚቆጠረው ፕላኖቹ ከቀረቡበት ጊዜ አንስቶ ነው።

4/ ከፕሮጀክቶቹ ስፋት ወይም ውስብስብነት የተነሳ ተጨማሪ የመገምገሚያ ጊዜ ለሚሹ ሥራዎች የሕንጻ ሹመ- ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል በማቅረብ ተጨማሪ ቀናት መጠየቅ ይችላል።

7. ፕላን ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

1/ የግንባታ ሥራው ሳይጀመር የጊዜ ገደቡ ያበቃ የፀደቀ ፕላን የፈቃድ ጊዜውን ለማራዘም የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው በወቅቱ ለሕንፃ ሹመ- ግንባታው ያልተጀመረበት ምክን ያት በጽሑፍ ተገልፆ እንደሆነና ይኸውም ምክን ያት በሕንፃ ሹመ- ተቀባይነት ሲያገኝ ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው ግንባታው ሳይጀመር የቀረው፦

ሀ) ከወሰንተኛ ጋር የተፈጠረ ግንባታ መጀመር የማያስችል የድንበር አለመግባባት ሲፈጠር፤ ወይም

ለ) ለግንባታው የሚያስፈልጉ በከተማው አስተ ዳደር በኩል መሟላት የሚኖርባቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች አለመሟላት፤ ወይም

ሐ) ለግንባታው መጀመር መነሳት ያለባቸው ነባር የመሠረተ ልማት አውታሮች ሳይነሱ መቅረት፤ ወይም

መ) በቦታው ላይ አከራካሪ የይዞታ ይገባኛል ጥያቄ ሲቀርብ፤ ወይም

a) five working days for plans of Category "A" building excluding real estates:

b) seven working days for plans of buildings of Category "B"; and

c) twenty one working days for plans of buildings of Category "C" and real estates of Category "B".

2/ Where buildings of different types are to be built on a project area belong to one person, the time taken for the review shall be the multiple of the number of categories of such buildings and the time fixed to review a single building. However, the total time for review of all plans shall not exceed 21 days.

3/ The time for a review of each category shall begin to be counted from the time of submission of the plan.

4/ The building officer may request the urban administration or the designated organ additional time to review huge or complex projects.

7. Validity Period of Plans

1/ The request for extension of validity period of a plan whose validity has been expired before the commencement of construction may be accepted where the reasons for the delay were timely reported to the building officer in writing.

2 The request for extension of validity period of a plan mentioned in sub article (1) of this Article may be accepted:

a) there exists a border conflict preventing the construction activity; or

b) the urban administration failed to fulfill the necessary infrastructure to begin the new construction; or

c) the urban administration failed to clear the existing infrastructure which prevented the construction; or

d) there exists a conflict of possession right over the construction site; or

ሠ) በአገር አቀፍ ደረጃ በግልጽ የታወቀ የግንባታ ግብዓት አቅርቦት እጥረት ሲከሰት፤ ወይም

ረ) ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሌሎች ምክንያቶች የተከሰተ፤

መሆኑ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

3/ ግንባታው ተጀምሮ ሥራው ሳያልቅ የጊዜ ገደቡ ላበቃ የፀደቀ ፕላን ፕላኑ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ ለማራዘም የሚቀርብ ጥያቄ በሚከተሉት እና በወቅቱ ለሕንፃ ሹሙ በቀረበ የጽሁፍ ሪፖርት ምክንያቶች ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል፡-

(ሀ) በአገር አቀፍ ደረጃ በግልጽ የሚታወቁ የግንባታ ግብዓቶች እጥረት መከሰቱ ሲረጋገጥ፤

(ለ) በዲዛይን ወቅት ባልታዩ እና በግንባታ ወቅት በታዩ የዲዛይን ስህተቶች ምክንያት የዲዛይን ማሻሻያ ሲያስፈልግ፤

(ሐ) የግንባታው ማጠናቀቂያ ከአምስት ዓመት በላይ እንደሆነ ሲታመን፤

(መ) የፍርድ ቤት ውሳኔ የሚጠይቁ ነገር ግን ውሳኔ ያላገኙ በእንጥልጥል ያሉ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ፡፡

4/ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ተቀባይነት ባገኙት ምክንያቶች ተጨማሪ ጊዜ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ፕላኑ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ፕላኑን ለመገምገም ከወሰደው ተጨማሪ ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

8. የግንባታ ፈቃድ

የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ተከታታይ የኮድ ቁጥር ያለው፣ የተሰጠበትን እና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን ጊዜ የሚገልፅ ይሆናል፡፡

9. በግንባታ ወቅት ፕላንን ስለማሻሻል

1/ በግንባታ ወቅት ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለውጡ ከመደረጉ በፊት ለውጡ የሚመለከተው የማሻሻያ ፕላን ተዘጋጅቶ በህንፃ ሹም መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

2/ የፀደቀው የማሻሻያ ፕላን በመጀመሪያ የፀደቀው ፕላን አካል ሆኖ ያገለግላል፡፡

3/ በግንባታ ወቅት በህንፃ ሹሙ መፅደቅ ሳያስፈልጋቸው መሻሻል የሚችሉ የፕላን አካላት እና ዓይነቶች ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

4/ የህንፃ ግንባታ ተጠናቆ የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት የተደረጉ ለውጦችን ያካተተ ጠቅላላ ፕላን ተዘጋጅቶ በህንፃ ሹም መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

e) there exists an apparent lack of construction materials at national level; or

f) there exist other causes of force majeure, which attributed delay of the construction activity.

3/ The request for extension of validity period of a plan whose validity has been expired before completion of the construction may be accepted for the following reasons if they were timely reported in writing to the building officer:

a) if there exists an apparent lack of construction materials at national level:

b) where a revision in the design was necessary during construction period resulting from an error which was unforeseen during design period;

c) where the completion of such construction takes more than five years;

d) where there exists pending court case that prevents the construction work.

4/ Where the reasons specified in Article 6 Sub-article (4) of this Regulation justify the extension of the validity period of a plan, the period so extended shall be equivalent to the time taken by the respective reason.

8. Construction Permit

A construction permit shall have a serial number showing the date of issuance and validity period.

9. Modification of Plan During Construction

1/ Where need arises to modify the original plan during construction, the modified plan shall be prepared and submitted to the building officer for approval prior to implementation.

2/ The approved modified plan shall remain part of the original plan.

3/ The type of plans or a part thereof which could be modified during construction without the approval of the building officer shall be determined by directives to be issued in accordance with this Regulation.

4/ A consolidated plan comprising modifications of a completed building shall be submitted to building officer for approval before an application for occupancy permit.

0. የሕንጻ ሹም

1/ በከተማ አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል የሚሾም የሕንፃ ሹም፣ በአርክቴክቸር፣ በሲቪል ምህንድስና፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ እና በኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡ ዝርዝር መመዘኛ መስፈርቶቹ በመመሪያ ይገለጻሉ፡፡

2/ የሕንጻ ሹም በአዋጁ አንቀጽ 01 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት አዋጁ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተገነባና አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንበት የተደረገ ሕንፃ፡-

ሀ) ሕንፃው አደጋ ሊያደርስ ስለመሆኑ መረጃ ሲደርሰው፤

ለ) በሕንፃው ላይ በግልጽ የሚታይ የመሰንጠቅ፣ የመስመጥ ወይም የመዘመም ሁኔታ ሲስተዋል፤

ሐ) ሕዝብን ለአደጋ ያጋልጣል ተብለው የሚገመቱ ሌሎች ሁኔታዎች ሲታዩ፤

ሕንፃው እንዲመረመር ማድረግ ይችላል፡፡

3/ የሕንፃ ሹሙ በሕንፃው ላይ በተደረገው ምርመራ ሕንፃው በሰውና በንብረት ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ሲያምንበት በሙሉም ሆነ በከፊል እንዲፈርስ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግለት ሊያዝ ይችላል፡፡

01. አገልግሎትን መግዛት

1/ የሕንፃ ሹሙ በአስተዳደሩ ውስጥ አንድን የተወሰነ ሥራ ለመሥራት የሚችል ባለሙያ የማይገኝ ሲሆን ይህንን ሥራ ሊሰራ ከሚችል የተመዘገበ ባለሙያ ጋር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በመዋዋል ሊያሰራ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተዋውሎ የሚሠራው ባለሙያ ሥራውን በአዋጁ፣ በዚህ ደንብና እና በውሉ መሠረት የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

3/ የሕንፃ ሹሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተዋውሎ የሚሠራው ባለሙያ ኃላፊነቱን በሚገባ መወጣቱን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

02. ትዕዛዝን አለማክበር

1/ የግንባታው ባለቤት በገባው ውለታ መሠረት የጊዜ ገደቡ ያበቃለትን ጊዜያዊ ግንባታ እንዲያፈርስ የተሰጠውን ትዕዛዝ ካላከበረ የከተማው አስተዳደር ግንባታውን በማንሣት ያወጣውን ወጪ ከባለንብረቱ በሕግ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

10. Building Officer

1/ A building officer to be appointed by the urban administration shall be a professional in architecture, civil engineering, construction technology and construction management, or in other related disciplines. The particular requirements shall be determined by directive

2/ A building officer is empowered to order inspection of exempted buildings in accordance with Article 11 sub article (5) of the Proclamation where:

a) he is informed that the building is likely to cause damage;

b) a visible crack, sink or tilt is observed on the building;

c) there exist some other defects which could put public safety at risk.

3/ Where the building officer is convinced that, upon examination of the building, the building is likely to cause damage to life and property, he may order the demolition or rectification of such building wholly or partly.

11. Outsourcing Professional Service

1/ Where the building officer is unable to find a professional within the administration to carry out a specific work, he may procure the service of a registered professional in accordance with the relevant law.

2. The professional engaged in accordance with sub-article (1) of this Article shall be responsible to carry out the work in accordance with the provisions of the Proclamation, this Regulation and the outsourcing contract.

3/ The building officer shall be responsible to follow up and ascertain that the professional who is undertaking the work under sub-article (1) of this Article properly discharges his responsibilities.

12. Non-compliance

1/ Where an owner of a temporary building fails to comply with the order of the urban administration to demolish such building at the end of the time prescribed by the agreement made at its erection with the urban administration, the latter may demolish the building by its own expense and claim the reimbursement of such cost from the owner.

2/ የሕንጻ ሹመ- ከጸደቀ ፕላን ውጪ የተከናወኑ ሥራዎች የሚስተካከሉበትን አግባብ ለሕንፃው ባለቤት በጽሁፍ ገልያለት የማያስተካክል ከሆነ የሕንፃ ሹመ- ግንባታውን ማስቆም ይችላል፡፡

3/ ከፀደቀ ፕላን ውጪ የተከናወኑ ሥራዎች እንዲስተካከሉ ከሕንፃ ሹመ- ትእዛዝ የደረሰው ሰው የማስተካከያ ሥራውን በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ማከናወኑን ለሕንፃ ሹመ- በፅሁፍ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡

03. <u>ማስታወቂያ</u>

1/ ማንኛውንም በምድብ "ለ" እና "ሐ" የሚገኝ ሕንፃ ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የየሥራው እርከን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስታወቂያ የሥራ እርከኑን ከመጀመሩ 5 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ለሕንፃ ሹመ- በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ ለአዲስ ግንባታ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው የሚገባ የሥራ እርከኖች ቅደም ተከተል ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡-

ሀ) የመሠረት ሥራ ለመጀመር የሚያስችል የቅየሣ ሥራ ሲያጠናቅቅ፤

ለ) የመሠረት ኮንክሪት ሙሌት ከመጀመሩ በፊት፤

ሐ) በየደረጃው ያለ የወለል ኮንክሪት ሙሌት ሥራ ከመጀመሩ በፊት፤

መ) የመጨረሻው የኮንክሪት ሙሌት ሥራ ከመጀመሩ በፊት፤

ሠ) የውሃ አቅርቦት፣ የሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ተጠናቆ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ፤

ረ) እንደ ሥራው ዓይነት እና የአሠራር ዘይ በሕንፃ ሹመ- የሚጠየቁ ተጨማሪ እርከኖች፡፡

3/ ለነባር ግንባታ ማሻሻያ ወይም ማስፋፊያ እና ለማፍረስ ማስታወቂያ ሊቀርብባቸው የሚገቡ የሥራ እርከኖች ከግንባታ ፈቃድ ጋር ለገንቢው በጽሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

4/ የግንባታ ሁኔታቸው እስከፈቀደ ድረስ ለማሻሻያ ወይም ለማስፋፊያ ሥራ ማስታወቂያ የሚቀርብባቸው የሥራ እርከኖች ለአዲስ ግንባታ የሚቀርቡ የሥራ እርከኖችን መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

5/ ማስታወቂያ በሚቀርብባቸው የሥራ እርከኖች የህንጻ ሹመ- በግንባታ ቦታው ላይ በመገኘት ግንባታው በተሰጠው ፈቃድ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን ይቆጣጠራል፡፡

6/ ማንኛውም ዓይነት ማስታወቂያ ወይም ትዕዛዝ በጸሐፍ መሆን ይኖርበታል፡፡ በቃል የሚሰጥ ትዕዛዝ ተቀባይነት የለውም፡፡

2/ If the owner of a building fails to rectify the condition under which construction works carried out beyond the approved plan, after receiving notice in writing, the building officer may suspend such construction works.

3/ A building owner who has received an order to rectify a construction work made beyond the approved plan shall notify in writing to the building officer, his completion of the work in compliance with the order.

13. <u>**Notice**</u>

1/ Any person who has an approved plan for category ''B'' and ''C'' buildings shall notify to the building officer , in writing , the starting date of each stage of work before five working days of such starting date.

2/ The stages of work for which an advance notice is required in case of new construction shall be in the following order:

a) on completion of surveying work for the foundation;

b) before starting concrete cast for grade beam;

c) before starting floor concrete works at all levels;

d) before starting final concrete works;

e) during testing of completed sanitary, electrical and electro mechanical Installations;

f) other stages of work required by the building officer based on the type and method of construction;;

3/ The stage of works for which an advance notice is required in cases of alteration, extension, and demolition of existing buildings, shall be disclosed, in writing, to the building owner at issuance of the construction permit.

4/ The notice to be given for the alteration and extension of existing buildings shall follow the same order with that of a new construction where the nature of the existing building so permits.

5/ The building officer shall inspect the site and ensure that the construction of such stage is in compliance with the permit.

6/ Any order or notice shall be given in writing. An order given orally is invalid.

04. ቁጥጥር

1/ ግንባታ የሚያካሂድ ማንኛውም ሰው በግንባታ ቦታ የግንባታ ክትትል መረጃ መዝገብ ማዘጋጀት አለበት፡፡

2/ የግንባታ ሥራው ወደተጠናቀቀ ወይም በግንባታ ላይ ወደሚገኝ ህንጻ የገባ ተቆጣጣሪ ስለገባበት ዓላማ እና ስለተመለከተው ሁኔታ በግንባታ መረጃ መዝገብ ላይ ማስፈር ይኖርበታል፡፡

3/ የግንባታ ማስቆሚያ ትዕዛዝ የሚሠጠው በግንባታ ክትትል መረጃ መዝገብ ላይ በማስፈር ወይም የቁጥጥር ሪፖርት ቅጽን በመሙላት ይሆናል ፡፡

4/ የማስቆሚያ ትዕዛዙ ቅጽ የግንባታውን አድራሻ፣ የግንባታውን ባለቤት ስም፣ የግንባታውን ፈቃድ ቁጥር፣ ከፈቃድ ውጪ የሆነው ግንባታ ያለበትን ደረጃ እና የተቆጣጣሪውን ሙሉ ስም ያካተተ መሆን አለበት፡፡

5/ የሕንፃ ሹሙ ከህንፃ ተቆጣጣሪዎች ሪፖርት እና የማስቆሚያ ትዕዛዝ ሲቀርብለት በህንፃው ሥራ ላይ የተጣሱትን የህግ ድንጋጌዎች በመዘርዘር ህንፃው የሚስተካከልበትን ወይም የሚነሣበትን ወይም የሚፈርስበትን ጊዜ በመወሰን በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለህንፃው ባለቤት በጽሑፍ እንዲደርስው ማድረግ አለበት፡፡

05. የሕንፃ ቁሳቁስ ጥራት ስለማረጋገጥ

1/ **የሕንፃ ሹም** በግንባታ ሥፍራ የተቀበጠ ወይም በሕንፃው ሥራ ላይ የዋለ ግብዓት በናሙና ፍተሻ ውጤቱ ተቀባይነት ካጣ እንዲወገድ ወይም በአጠቃቀሙ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

2/ በግንባታ ግብዓት ጥራት ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም አደጋ ወይም ጉድለት የግንባታው ባለቤት ሃላፊነት አለበት፡፡

06. የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ

1/ በምድብ "ሐ" የሚመደብ ሕንፃ የግንባታ ሥራ ሲጠናቀቅ የሕንፃው ባለቤት የመጠቀሚያ ፈቃድ በማመልከቻ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ ለሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ የሚቀርብ የማመልከቻ ቅጽ፡-

ሀ) የግንባታውን ባለቤት ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ለ) ግንባታው የሚገኝበትን አድራሻ፣

ሐ) የህንፃውን የአገልግሎት ዓይነት፣

መ) የግንባታውን ፈቃድ ቁጥር፣

ሠ) ግንባታው የተጀመረበትንና የተጠናቀቀበ ትን ቀን፣እና

ረ) ህንጻው በፕላኑ መሠረት ስለመሠራቱ ቁጥጥሩን ያደረገው የተመዘገበ ባለሙያ ያረጋገጠበትን ማስረጃ፣

ማካተት አለበት፡፡

14. Inspection

1/ Any person who is carrying out a construction work shall keep a site book on the construction site.

2/ An inspector visiting a site of a completed or building under construction shall record the objective of his visit and the findings thereof on the site book.

3/ Stop orders shall be issued by recording on the site book or the inspection report form.

4/ The stop order form shall comprise the location of the building, owner's name, construction permit number, stage of the illegal construction and the supervisor's full name.

5/ The building officer shall, upon receipt of the report and the stop order of the inspector, specify the provision of the laws so violated, the period within which the rectification, removal or demolition of such building is to be carried out and communicate the same to the owner in writing within five working days.

15. Ascertaining Quality of Building Materials

1/ If a material used or destined for construction made subject to sample testing is found to be defective or below standard, the building officer may order its removal or adjustment in its use.

2/ The owner of the building is responsible for any damage due to use of substandard materials of construction.

16. Occupancy Permit

1/ The owner of a Category "C'' building, shall apply for an occupancy permit upon completion of construction. The application form for occupancy permit shall indicate:

a) full name and address of the owner;

b) location of the building;

c) type of service of building;

d) construction permit number;

e) date of starting and completion of construction , and

f) the document verified by the registered professional who carried out the inspection as to the compliance of the construction with the plan.

2/ የሕንፃ ሹመ· የቀረበለትን ማመልከቻና ሰነዶች መርምሮ በ0 የሥራ ቀናት ምላሽ ይሰጣል፡፡

3/ የሕንፃ ሹመ· የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖረው በምድብ "ሐ" ሕንፃ መጠቀም በጀመረ በማናቸውም ሕንፃ ባለቤት ላይ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፵4 መሠረት የገንዘብ መቀጫ የመጣል ወይም ሕንፃው የመጠቀሚያ ፈቃድ እስከሚያገኝ ጥቅም ላይ እንዳይውል የማድረግ ወይም ሁለቱንም እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፡፡

4/ የማሻሻያ ወይም የማስፋፋት ግንባታ ፈቃድ የሚያስፈልገው በምድብ "ሐ" ሥር የሚመደብ ህንጻ ግንባታው ሲጠናቀቅ በግንባታ ፈቃዱ መሠረት መከናወኑ እና ፈቃድ ለተጠየቀበት አገልግሎት ብቁ መሆኑ ተረጋግጦ የመጠቀሚያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት የመጠቀሚያ ፈቃድ ማግኘት የሚገባቸው ሕንፃዎች ፈቃዱን የሚያገኙት ከአዲስ ሕንጻዎች የመጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ይሆናል፡፡

07. ጊዜያዊ ግንባታዎች

1/ ጊዜያዊ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ጊዜያዊ ግንባታ ለማካሄድ የፈለገበትን ቦታ ለጊዜያዊ ግንባታ ለመጠቀም የሚያስችል ፈቃድ ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል ማግኘት ይኖርበታል፡፡

2/ የጊዜያዊ ግንባታ ለማከናወን ቦታ የተፈቀደለት ሰው ለሚያከናውነው ጊዜያዊ ግንባታ ከሕንጻ ሹም ጊዜያዊ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

3/ የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ለሕንፃ ሹመ· የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ) የግንባታውን አገልግሎት የሚገልጽ ማብራሪያ

ለ) የግንባታ ቦታውን በጊዜያዊነት ለመጠቀም ከከተማው አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል የተሰጠውን ማስረጃ፣

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) የተጠቀሰውን ቦታ ለጊዜያዊ ግንባታ ለመጠቀም የተሰጠው ፈቃድ ሲያበቃ በምን መልክ እንደሚያስረክብ የተስማማበትን ሰነድ፣

መ) ለሕንፃ ምድብ "ሀ" የሚጠየቁ ማስረጃዎችን እና የፕላን ዓይነቶችን፣

ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

4/ ለሕዝብ መገልገያነት እንዲውል ለሚጠየቅ ጊዜያዊ ግንባታ በምድብ "ሐ" ለሚገኝ ህንፃ የሚጠየቁ የግንባታ ፈቃድ ፕላኖች ወይም ዲዛይኖች በዚህ ደንብ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ (1) (ቀ) መሠረት መቅረብ አለባቸው፡፡

2/ The building officer shall respond within 10 working days after receipt of the application.

3/ The building officer may charge fines in accordance with Article 44 of this Regulation where a Category "C" building is found to have begun rendering service without occupancy permit, or suspend its service until such permit is obtained or it may take both measures simultaneously.

4/ A Category "C" building with extension or alteration shall be approved for compliance with the construction permit and use intended to be issued occupancy permit.

5/ The buildings mentioned in sub article (4) of this Article shall follow the same procedure to obtain occupancy permit like that of the new buildings.

17. Temporary Constructions

1/ Any person who wants to construct a temporary building shall apply to the urban administration or the designated organ to obtain a temporary construction permit.

2/. A person who has a temporary land permit shall obtain a temporary construction permit from the building officer.

3/ The application for a temporary construction permit shall specify or attach:

a) the intended service of the building;

b) the permit obtained from the urban administration or the designated organ for temporary use of the land;

c) the agreement made with the authorities specified in (b) of this on the conditions under which the site is to be handed over at the expiry of the permit;

d) documents and types of plans required for building Category "A" buildings.

4/ Where an application to obtain a temporary construction permit relates to public buildings, it shall be accompanied by plans and designs required for Category "c'' buildings under Article 3 sub article (1) (i) of this Regulation.

5/ ጊዜያዊ ግንባታዎች የቋሚነት ይዘት በሌላቸው በቀላሉ ሊነቃቀሉ እና ሊነሱ በሚችሉ ቁሳቁሶች መገንባት አለባቸው፡፡

6/ በሕንፃ ሹመ- የሚሰጠው ጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ የሚያገለግለው ቦታው ለጊዜያዊ ግንባታ እስከተፈቀደበት የጊዜ ገደብ ድረስ ነው፡፡

7/ ቦታን ለጊዜያዊ ግንባታ ለመጠቀም የተሰጠ ፈቃድ እስከተራዘመበት ጊዜ ድረስ በቦታው ላይ ለተሰራው ግንባታ የተሰጠው የጊዜያዊ ግንባታ ፈቃድ ጸንቶ ይቆያል፡፡

8/ የጊዜያዊ ግንባታ የፈቃድ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ጊዜያዊ ግንባታው መነሳትና ቦታው በጊዜያዊነት በተሰጠበት ወቅት በተደረሰው ስምምነት መሠ ረት መስተካከል እና ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

08. <u>የአገልግሎት ለውጥ፣ ማስፋፋት ፅድሳት ወይም ጥገና ስለማድረግ እና ስለማፍረስ</u>

1/ ማንኛውም ሰው አንድን ህንፃ አገልግሎቱን ለመለወጥ፣ ለማስፋፋት፣ ለመጠገን ወይም ለማፍረስ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2/ አንድን ህንፃ አገልግሎቱን ለመለወጥ፣ ለማስፋፋት ወይም ለመጠገን የሚቀርብ የፈቃድ ማመልከቻ ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ፤

ለ) አዋሳኞቹን የሚያሳይ ፕላን፤

ሐ) የህንፃ አዋጭ ተፈጻሚ ከሆነ በ|ላ የተሰራ ህንጻ ከሆነ የግንባታ ፈቃድ፤

መ) የሕንፃውን የቀድሞው ፕላን እና የተሻሻለውን ፕላን፣

ሠ) ለህንፃ ምድቡ የሚጠየቁ ፕላኖች እና ትንታኔዎች፡፡

3/ አንድን ህንፃ ለማፍረስ የሚቀርብ የፈቃድ ማመልከቻ ከሚከተሉት ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡-

ሀ) የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ፤

ለ) የህንጻው ፕላን፤

ሐ) ህንጻውን ለማፍረስ የታሰበበትን ምክንያት፤

መ) በአጎራባች ይዞታዎች የሚገኙ ህንጻዎች ከፍታና ከሚፈርሰው ህንጻ ወሰን ያላቸውን ርቀት፤

ሠ) የኤሌክትሪክ፣ የውሃ፣ የፍሳሽ፣ የቴሌፎን እና የሌሎች የመሠረተ ልማት መስመሮች በሚመለከታቸው ተቋማት እንደሚቋረጡ የተደረሰበትን ስምምነት የሚገልጹ ማስረጃዎች፤

5/ Temporary constructions shall be built up with materials having no permanence nature and which are easily removable.

6/ The temporary construction permit to be issued by the building officer shall be valid only for the duration of the land permit.

7/ The extension of time for the land permit shall be valid to the temporary building permit.

8. Upon completion of the time limit, the temporary construction shall be removed and the site shall be cleared and handed over in accordance with the agreement made during the issuance of the land permit.

18. <u>Alteration of Use, Extension, Repair or Demolition</u>

1/ Any person who intends to alter the use of a building or to extend, repair or demolish a building shall obtain a permit.

2/ An application to alter the use of a building or to extend or repair a building shall be accompanied by the following documents:

a) title deed;

b) plan displaying adjoining sites;

c) construction permits, if the building is built after the coming into force of the Proclamation;

d) the previous and the modified plans of the building;

e) plans and analyses of the building based on its category.

3/ The application to demolish a building shall be accompanied by the following documents:

a) title deed;

b) plan of the building;

c) statement of reason for demolishing;

d) height of neighboring buildings and their distance from the border of the building to be demolished;

e) agreement made with the respective authorities to interrupt power, water, sewerage, telephone and other infrastructures;

ረ) የጥንቃቄ አወሳሰድ ዘዴዎችንና የማፍረሱን ሂደት ቅደም ተከተል የሚያሳይ ትንታኔ፡፡

4/ የማፍረስ ሥራ ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጅ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት መከናወን አለበት፡፡

5/ የአገልግሎት ለውጥ አንድን ነባር ሕንፃ ሙሉ ለሙሉ የሚያፈርስ ከሆነ የሚሰጠው ፈቃድ ስለአዲስ ግንባታ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

6/ የአገልግሎት ለውጥ፣ ማሻሻያ ወይም ማስፋፋት የተደረገበት ሕንጻ በምድብ "ሐ" ሥር የሚመደብ ከሆነ ሕንጻው ለአገልግሎት ከመዋሉ በፊት የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊያገኝ ይገባል፡፡

7/ የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት፣ የማደስ፣ የመጠገን ወይም የማፍረስ ሥራ ሲከናወን ለሥራው በሚመጥን የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ መከናወን ይኖርበታል፡፡

09. <u>የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር</u>

1/ አርክቴክቱ የሚያስተባብረው በአንድ ፕሮጀክት የዲዛይን ዝግጅት ወቅት በተለያዩ የተመዘገቡ ባለሙያዎች የተሰሩ ዲዛይኖች እርስ በርሳቸው እና ህንጻው ሊሰጠው ከታሰበው አገልግሎት አንጻር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይሆናል፡፡

2/ ማንኛውም ሰው የሕንፃ ዲዛይን ሥራ ለማሰራት ሲያቅድ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ለምድቡ የሚጠየቁ ፈቃዳቸው ለሥራ ዘመኑ የታደሰ የተመዘገቡ ባለሙያዎች መቅጠር አለበት፡-

ሀ) ለምድብ "ሀ" ለአርክቴክቸር እና ለኤሌክትሪክ፤

ለ) ለምድብ "ለ" ለአርክቴክቸር፣ ለስትራክቸር፣ ለኤሌክትሪክ፣ ለሳኒተሪ እና ለአፈር ምር መራ ሥራ፣ እና

ሐ) ሊፍት እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን ለሚጠቀሙ ህንፃዎች ለኤሌክ ትሮ ሜካኒካል የዲዛይን ሥራ፤

የተመዘገቡ ባለሙያዎች መቅጠር አለበት::

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ለምድብ "ሀ" ሕንፃ ስታንዳርድ ፕላኖች በተመዘገቡ ባለሙያዎች አዘጋጅቶ ለገን ቢዎች በተመጣጣኝ ክፍያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4/ የሕንፃ ዲዛይን የሚያዘጋጁ የውጭ ሀገር አማካሪዎች ህጋዊ ሰውነት፣ የሥራ ፈቃድ፣ የሚፈቀድላቸውን የፕሮጀክት መጠን እና የዋስትና ሽፋናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

5. የሕንፃ ፕላን ዝግጅት እና የቁጥጥር ሥራ ለማከናወን የሚቀጠሩ የተመዘገቡ ባለሙያዎች ደረጃ የሕንፃውን ምድብና የፕሮጀክቱን ግምት ታሳቢ በማድረግ በሚዘጋጅ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

f) analysis of safety methods to be applied and the sequence of activities to be carried out.

4/ Demolition shall be carried out in compliance with detail procedures indicated in the directives to be issued in accordance with this Regulations.

5/ If alteration of use requires the demolition of the whole building, the permit to be given shall be similar to the permit given for a new building in accordance with Article 3 of this Regulation.

6/ Where the alteration of service, modification or expansion relates to a Category "C" building, such building shall obtain an occupancy permit before it is put for use.

7/ Any work of alteration of service, expansion, renovation, maintenance or demolition of a building shall be carried out by competent registered contractor.

19. <u>Employment of Registered Professionals</u>

1/ The coordination activity of the Architect shall be confined to assuring the designs prepared by different registered professionals are fit to each other with respect to the intended service of the building.

2/ Any person who is planning to have a building design shall employ registered professionals who have a renewed licenses and qualified for the building category as stated below:

a) for Category "A" buildings, registered professionals in architecture and electrical design works;

b) for Category "B" buildings, registered professionals in architecture, structure, electric, sanitary and soil test; and

c) electro-mechanical professionals for buildings using lifts and artificial ventilations.

3/ Without prejudice to sub article (2) of this Article, the urban administration or the designated organ may prepare standard designs for Category "A" buildings by registered professionals and provide to users with reasonable price.

4/ Expatriate consultants who prepare building designs shall submit certificates of legal personality, work permit, the project sizes to which they are licensed and their insurance coverage.

5/ The level of registered professionals employed for designs and inspection shall be determined by directives to be issued in accordance with this Regulations on the basis of project prices and building categories.

6/ የህንፃ ዲዛይን ለማከናወን ውለታ የሚወስድ የተመዘገበ ባለሙያ ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ህንፃዎች ለሚያዘጋጀው ዲዛይን በአዋጁ አንቀጽ ፶6 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚያቀርበው የዋስትና መጠንና አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ተ.ቁ	የሕንጻ ምድብ	የፕሮጀክት ግምት /ብር/	የዋስትና መጠን (የፕሮጀክቱን ግምት)	የዋስትና መጠን ጣሪያ /ብር/	የዋስትና ጊዜ	የዋስትና አቀራረብ
1	ከሪል እስቴት ውጪ ያሉ የምድብ "ለ" ህንጻዎች	5,000,000	10 በመቶ	500,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
2	ለሪል እስቴት እና ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች	2,500,000	20 በመቶ	500,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
		10,000,000	15 በመቶ	1,500,000		
		20,000,000	10 በመቶ	2,000,000		

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው የመድን ሽፋን በፍትሐብሔር ህጉ ስለማይን ቀሳቀስ ንብረት የሥራ ውል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚነካ አይሆንም፡፡

8/ ለዋስትና መጠን ስሌት የሚሆነው የፕሮጀክት ዋጋ ግምት የሚሰላው በህንጻው ጠቅላላ ስፋት እና የህንጻ ሹመ አዘጋጅቶ በሚያቀርበው እና በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚጸድቀው የየምድቡ የካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡

፳. የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮችን ስለመቅጠር

1/ በአዋጁ አንቀጽ ፶7 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የምድብ "ሀ" ህንጻዎች ግንባታ ከሚመለከተው አካል የክህሎት የምስክር ወረቀት ባገኙ መለስተኛ ባለሙያዎች ሊገነባ ይችላል፡፡

2/ የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮችን አቀጣጠር መስፈርት ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ በህንፃ ግንባታ ሥራ ለመሳተፍ ለዘመኑ የታደሰ የንግድ እና የሥራ ተቋራጭነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

4/ የተመዘገቡ ሥራ ተቋራጮች ሊሳተፉ የሚችሉ ባቸው የፕሮጀክት መጠኖች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

6/ In accordance with sub article (3) of Article 26 of the Proclamation, the form and amount of the guarantee to be produced by a registered professional who has reached agreement to carry on the design of Category "B" and "C" buildings shall be as follows:

No.	Building category	Project cost /Birr/	Guarantee (% of project cost)	Maximum guarantee /Birr/	Duration	Mode of the guarantee
1	Category B buildings excluding real estates	5,000,000	10%	500,000	One year from completion of project	From recognized insurance before commencing project
2	Building Category C and real estates	2,500,000	20%	500,000	One year from completion of project	From recognized insurance before commencing project
		10,000,000	15%	1,500,000		
		20,000,000	10%	2,000,000		

7/ The provisions of the sub article (6) of this Article shall not affect the warranty period provided for in the Civil Code regarding contracts of work and labour relating to immovable.

8/ The project cost estimate for guarantee shall be calculated by multiplying the total area of the project and the construction price for each square meter of the given category of building prepared by the building officer and approved by the urban administration or the designated organ.

20. Employment of Registered Contractors

1/ Without prejudice to Article 27 sub article (1) of the Proclamation, the construction of Category "A" buildings may be carried out by medium professionals certified by authorized bodies.

2/ Requirements to recruit appropriate registered professionals shall be determined by directives to be issued pursuant to this regulation.

3/ A registered contractor shall have a renewed license and a registration certificate to participate in construction contracts.

4/ The project amount in which registered contractors may participate shall be determined by a directive to be issued by the Ministry.

5/ በግንባታ ሥራ ላይ የሚሰማሩ የውጭ አገር ሥራ ተቋራጮች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው መሆኑን፣ የተሰጣቸውን የሥራ ፈቃድ፣ የሚፈቀድላቸውን የፕሮጀክት መጠን እና የዋስትና ሽፋናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

6/ የሕንፃ ግንባታ ለማከናወን ውለታ የሚወስድ ማንኛውም የተመዘገበ የሥራ ተቋራጭ ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ህንፃዎች ግንባታ በአዋጁ አንቀጽ ፳7 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚያቀርበው የዋስትና መጠንና አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ተ.ቁ	የሕንጻ ምድብ	የፕሮጀክት ዋጋ /ብር/	የዋስትና መጠን (የፕሮጀክቱን ግምት)	የዋስትና መጠን ጣሪያ /ብር/	የዋስትና ጊዜ	የዋስትና አቀራረብ
1	ከሪል እስቴት ውጪ ያሉ የምድብ "ለ" ህንጻዎች	10,000,000	20 በመቶ	2,000,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
2	ለሪል እስቴት እና ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች	10,000,000	30 በመቶ	3,000,000	ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት የሚቆይ	ከታወቀ የመድን ድርጅት፣ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት
		15,000,000	25 በመቶ	3,750,000		
		25,000,000	20 በመቶ	5,000,000		

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው የመድን ሽፋን መስጫ ጊዜ በፍትሐብሔር ህጉ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት የሥራ ውል የተመለከተውን ድንጋጌ የሚነካ አይሆንም፡፡

8/ ለዋስትና መጠን ስሌት የሚሆነው የፕሮጀክት ዋጋ ግምት የሚሰላው በህንጻው ጠቅላላ ስፋት እና የህንጻ ሹመ- አዘጋጅቶ በሚያቀርበው እና በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል በሚጸድቀው የየምድቡ የካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ ስሌት መሠረት ይሆናል፡፡

9/ የግንባታ ሥራው የዲዛይን ዝግጅቱን ሥራ የሚያጠቃልል ከሆነ የዋስትና መጠኑ እና አቀራረቡ ለግንባታ ሥራው በተመለከተው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (6) መሠረት ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት

የይግባኝ ሰሚ ቦርድ

፳1. የቦርድ አመሠራረት

1/ የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ ከከተማ አስተዳደር ወይም ከተሰየመው አካል እና ከሚመለከታቸው ተቋማት የተውጣጡ ቁጥራቸው እንደጉዳዩ ውስብስብነት እና እንደ ከተማው ደረጃ የሚወሰን ሆኖ ከ5 እስከ 7 አባላት ይኖሩታል፡፡

5/ Expatriate contractors who carry out construction works shall submit certificates of legal personality, work permit, the project sizes to which they are licensed and their insurance coverage.

6/ Any contractor who has reached agreement to construct Category "B" and "C" buildings as per Article 27 sub article (2) of the Proclamation shall produce guarantee and the amount and procedure of production a guarantee on basis of categories of building shall be as follows:

No.	Building category	Project cost Birr	Guarantee (% of Project cost)	Maximum guarantee (Birr)	Duration	Mode of the guarantee
1	Category B buildings excluding real states	10,000,000	20%	2,000,000	one years from completion of project	From recognized insurance before commencing project
2	Building Category 'C' and real estates	10,000,000	30%	3,000,000	one years from completion of project	From recognized insurance before commencing project
		15,000,000	25%	3,750,000		
		25,000,000	20%	5,000,000		

7/ The provisions of sub article (6) of this Article shall not affect the guarantee period provisions of the Civil Code regarding contracts of work and labour relating to immovable.

8/ The project cost, for insurance purpose, shall be calculated by taking in to account the total project area and the price of the construction per square meter which is to be prepared by the building officer and approved by the urban administration or the designated organ.

9/ Where the construction contract includes design and build /a turn-key contract/ the method and the amount of guarantee to be produced shall be determined pursuant to sub article (6) of this Article.

PART THREE

APPEALLATE BOARD

21. Formation of the Board

1/ The urban administration or the designated organ shall set up an appellate board which consists of 5 to 7 members drawn from relevant bodies depending on the complexity of the case and the level of the urban center.

2/ የቦርዱ የሥራ ዘመን ከከተማ አስተዳደሩ የሥራ ዘመን ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

3/ የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አባላት ስብጥርና የሥራ ድርሻ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ) የከተማው አስተዳዳሪ .....ሰብሳቢ

ለ) የሥራ ተቋራጮች ማህበር ተወካይ ....አባል

ሐ) በከተማው ከሚገኝ የፍትህ አካል ወይም ከተመሳሳይ ተቋም የሚወከል የሕግ ባለሙያ .....አባል

መ) በከተማው ከሚገኙ የሠራተኛና የመምህራንና ወጣቶች ማኅበራት እና ከከተማ ነዋሪዎች የሚመረጡ ተወካዮች.....አባላት

ሠ) የከተማዉ አስተዳደር ተወካይ ..... ጸሐፊ

4/ ማንኛውም ሰው በሕንፃ ሹመ በተሰጠ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ቅሬታ ካለው_የህንፃ ሹመ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ በደረሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ቦርድ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

ፅ2. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

በአዋጁ አንቀፅ 03 ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1/ የይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አቤቱታ በደረሰው በአሥራ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የሚመለከትበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በመወሰን ለአመልካቹ ከአምስት የሥራ ቀናት በፊት ማሳወቅ ይኖርበታል፤

2/ ቦርዱ ለሚቀርብለት የይግባኝ አቤቱታ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም የጉዳዩ ባህሪ ተጨማሪ ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ ለአንድ ተጨማሪ ወር ሊያራዝም ይችላል፤

3/ ቦርዱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሌሎች ባለሙያዎችን እገዛ መጠየቅ ይችላል፤

4/ ቦርዱ በቀረበለት ይግባኝ ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ለአመልካቹ እና ለህንጻ ሹመ በጽሁፍ ያሳውቃል፤

5/ የከተማው አስተዳደር ለቦርዱ አባላት አበል ሊከፍል ይችላል፤

6/ ቦርዱ ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ይሆናል፡፡

ፅ3. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

2/ ማንኛውም የቦርዱ ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ይሰጣል፣ ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል በሆነ ጊዜ ሰብሳቢው የሚደግፈው ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

2/ The term of office of the Appellate Board shall be equivalent to the term of office of the urban administration.

3/ The composition and duties of the Appellate Board shall be as follows:

a) administrator of the urban administration ..……Chairperson

b) a representative of Contractors Association ……member

c) a legal professional representing the justice organ or a similar institution of the urban administration … member

d) representatives to be elected from the workers, teachers and youth associations urban dwellers ……members

e) a representative of the urban administration ……secretary

4/ Any person who has a complaint against the decision or order of the building officer may appeal to the Board within five working days from the date he has received such order or decision.

22. <u>Powers and Duties of the Board</u>

Without prejudice to Article 13 sub article (2) of the Building Proclamation:

1/ the Board shall, notify the appellant the venue and date of hearing within fifteen working days after its acceptance of the appeal and five working days prior to the date of hearing;

2/ the Board shall decide on the appeal within one month. This period may be extended to a maximum of one additional month if the nature of the case demands;

3/ the Board may request professional support of any kind to decide a case;

4/ the board shall notify its decision to the appellant and the respective building officer in writing;

5/ the urban administration or the designated organ may arrange allowances to Board members;

6/ the Board shall be accountable to the urban administration.

23. <u>Meeting of the Board</u>

1/ There shall be a quorum where a majority of the members of the Board are present.

2/ Decisions of the Board shall be passed by a majority vote, in case of a tie, however, the chairperson shall have a casting vote.

3/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

ክፍል አራት

የአገልግሎት ክፍያዎች

፳4. የፕላን ስምምነትና መገምገሚያ ክፍያ

1/ ለሁሉም የህንጻ ምድቦች የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል፡፡

2/ የፕላን ስምምነት ለማግኘት ጥያቄ ሲቀርብ የከተማው አስተዳደር የአገልግሎት ክፍያ ብር ፫፻ በማስከፈል ስምምነቱን ይሰጣል፡፡

3/ ለግንባታ ጥቅም ላይ የሚውሉት ፕላኖች በከተማው አስተዳደር ተዘጋጅተው የሚሰጡ ስታንዳርድ ፕላኖች ከሆኑ ፕላኖቹን ለማግኘት የሚፈጸመው ክፍያ እንደ ፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይቆጠራል፡፡

4/ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሠረት የሚሰላ ሲሆን የፕሮጀክት ግምት የሚሰላው የሕንጻዎቹን ጠቅላላ የወለል ስፋት በካሬ ሜትር የግንባታ ዋጋ በማባዛት ይሆናል፡-

ተ.ቁ	የፕሮጀክት ግምት /በብር/	የፕላን መገምገሚያ ክፍያ
1	እስከ 2,500,000	የፕሮጀክቱን ግምት $\frac{1}{2000}$
2	2,500,000⁺ እስከ 5,000,000	1250 + $\frac{1}{2500}$ (የፕሮጀክት ግምት – 2,500,000)
3	5,000,000⁺ እስከ 10,000,000	2250 + $\frac{1}{3000}$ (የፕሮጀክት ግምት – 5,000,000)
4	10,000,000⁺ እስከ 20,000,000	3920 + $\frac{1}{3500}$ (የፕሮጀክት ግምት – 10,000,000)
5	20,000,000⁺ እስከ 50,000,000	6770 + $\frac{1}{4000}$ (የፕሮጀክት ግምት – 20,000,000)
6	ከ50,000,000 ብር በላይ	14270 + $\frac{1}{5000}$ (የፕሮጀክት ግምት – 50,000,000)

5/ የሕንጻ ሹም ከተማው ከሚገኝበት ክልል የግንባታ ዋጋ በመነሳት ለፕሮጀክት ግምት ስሌት የሚሆን የየህንጻ ምድቡን የካሬ ሜትር ዋጋ በማዘጋጀት ለከተማው አስተዳደር ወይንም ለተሰየመው አካል አቅርቦ ያፀድቃል፡፡ የተዘጋጀው የካሬ ሜትር ዋጋ እንደ አስፈላጊነቱ ሊከለስ ይችላል፡፡

6/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ 01 ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት በግዥ በተገኘ የተመዘገበ ባለሙያ አገልግሎት ሲሆን የፕላን መገምገሚያ ዋጋ አሸናፊው ባቀረበው ዋጋ መሠረት ይሆ ናል፡፡

7/ ለፕላን ግምገማ የቀረቡ የሕንፃ አሀዶች ተመሳሳይ ከሆኑ የፕላን መገምገሚያ ክፍያ የሚሰላው የአንዱን ሕንፃ የግንባታ ሙሉ ዋጋ እና የሌሎቹን አሀዶቹ ጠቅላላ የግንባታ ዋጋ 0 በመቶ በመደመር ይሆናል፡፡

3/ Without prejudice to the provisions of this Article the Board may draw up its own rules of procedure.

PART FOUR

SERVICE FEES

24. Planning Consent and Review Fees

1/ A plan review fee shall be paid for building of all categories.

2. A planning consent shall be obtained from the urban administration upon request and payment of a service fee of birr 300.

3/ If the applicable building plans are standard plans prepared by the urban administration, payments made to obtain the plan shall be considered as if they were made for the review of the plan.

4/ The plan review fee shall be calculated as indicated in the Table below while the project cost shall be the product of the total area of

No.	Project Estimate (Birr)	Plan Review Fee
1	Upto 2,500,000	$\frac{1}{2000}$ of the project Estimate
2	From 2,500,000⁺ upto 5,000,000	1250 + $\frac{1}{2500}$ (Project Estimate 2,500,000)
3	From 5,000,000⁺ upto 10,000,000	2250 + $\frac{1}{3000}$ (Project Estimate – 5,000,000)
4	From 10,000,000⁺ upto 20,000,000	3920 + $\frac{1}{3500}$ (Project Estimate – 10,000,000)
5	From 20,000,000⁺ upto 50,000,000	6770 + $\frac{1}{4000}$ (Project Estimate – 20,000,000)
6	Above 50,000,000	14270 + $\frac{1}{5000}$ (Project Estimate – 50,000,000)

5/ The building officer shall prepare average current unit price per meter square for each category of buildings on the basis of the construction price prevalent in the specific urban center and submit to the urban administration or the designated organ for approval. The price quoted per meter square may be reviewed as necessary.

6/ Where the plan review is made by the service obtained by a registered professional in accordance with Article 11 sub article (1) of this Proclamation, the plan review fee shall be the fee awarded by the winning bidder.

7/ Where there are identical building blocks, the plan review fee shall be the sum of the building cost of one of the blocks and ten per cent of the total building cost of all other blocks.

8/ ውድቅ የሆኑ ፕላኖች ተስተካክለው እንደገና ለማፀደቅ በሚቀርቡበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያው ክፍያ፡-

ሀ) ለምድብ "ሀ" ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ ግማሽ፤

ለ) ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ ፭5 በመቶ፤

ይሆናል፡፡

9/ ፕላኑ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ቀደም ሲል ይኸው ፕላን ውድቅ በተደረገበት ጊዜ ሳይታይ በታለፈ ግድፈት ምክንያት ከሆነ ተስተካክሎ የሚቀርበውን ፕላን ለመገምገም ክፍያ አይጠየቅም፡፡

0/ የፕላን ማሻሻያ ክፍያ ስትራክቸራል ፕላኑን እንዲለውጥ የሚያስገድድ ከሆነ ክፍያው በአዲስ ፕላን መገምገሚያ አከፋፈል መሠረት ይሆናል፡፡ ለሌሎች የፕላን ማሻሻያዎች የሚከፈለው የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ለአዲስ ፕላን መገምገሚያ የሚጠየቀው ክፍያ ፭5 በመቶ ይሆናል፡፡

፳5. <u>የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ</u>

ለሁሉም የሕንፃ ዓይነቶች የፕላን ማስፀደቂያ ክፍያ መጠን ለፕላን መገምገሚያ የተከፈለው ክፍያ 0 በመቶ ይሆናል፡፡

፳6. <u>የቁጥጥር ክፍያ</u>

1/ ለሕንፃ ግንባታ የሚደረግ የቁጥጥር ሥራ በዚህ ደንብ አንቀጽ 03 ንዑስ አንቀጽ (2) ለተመለ ከቱት ሕንፃዎች በተቀመጡት የሥራ ደረጃዎች መሠረት ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት ለሚደረግ የቁጥጥር ሥራ ለየምድቡ የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ፤

ሀ) ለምድብ "ለ" ህንፃ ብር ፬፻፤

ለ) ለምድብ "ሐ" ህንፃ ብር ፰፻፤ ይሆናል ፡፡

፳7. <u>ተመላሽ ክፍያዎች</u>

1/ ተመላሽ ክፍያ የሚባለው አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ወይም ክፍያ የተፈፀመበት አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ወይም አገልግሎቱ ከሚጠይቀው በትርፍነት የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡

2/ አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ እንዲመለስለት የሚጠይቅ ሰው ጥያቄውን ክፍያው የተፈጸመበትን የአገልግሎት ዓይነት እና ክፍያው ተመላሽ እንዲሆን የተጠየቀበትን ምክንያት በመግለጽ ክፍያ ከተፈጸመበት ደረሰኝ ኮፒ ጋር በማያያዝ ማመልከት አለበት፡፡

3/ የተመላሽ ክፍያ አፈፃፀም በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ይከናወናል፡፡

8/ Where rejected plans are re-submitted for approval, additional review fee shall be charged as follows:

a) for Category "A" buildings, half of first payment;

b) for category "B" and "C" buildings, 25% of the first payment;

9/. If the plan was rejected due to overlook in the review of the previous plan, no plan review fee shall be charged to review the resubmitted plan.

10/ The review fee for modified plans shall be 25% of the payment made for a new plan. However, where the plan modification requires changing the structural plan, the plan review fee payable for the modified plan be equivalent to that payable for a new plan.

25. <u>Plan Approval Fees</u>

The plan approval fee for all categories of buildings shall be 10% of the plan review fee.

26. <u>Inspection Fees</u>

1/ Inspection of construction works shall be carried out on buildings specified in sub article Article 13 sub-article (2) f this Regulation and as per the stages of work therein.

2/ The fee payable at each inspection visit and one stage of inspection in accordance with sub article (1) of this Aarticle shall be:

a) Birr 400 for Category "A" building; and

b) Birr 800 for Category "C" building.

27. <u>Refunds</u>

1/ Refund is payment for which no service is rendered or payment made remains unnecessary or excessive.

2/ A person who requests a refund of payment shall specify the type of service for which payment is made, the reason for the refund and apply the same, in writing , with attached copy of the receipt of payment.

3/ The shall be made in accordance with relevant provisions of financial administration regulation and directive.

ክፍል አምስት

የመሬት አጠቃቀም፣ ተጓዳኝ ጥናቶች እና ዲዛይኖች

፳8. ዲዛይኖች

1/ ለየሕንፃ ምድቡ የሚዘጋጁት ፕላኖች ወይም ዲዛይኖች እንደሚከተለው ይሆናሉ፡-

ሀ) ለምድብ "ሀ" ህንፃዎች፣

1/ የኮንክሪት ጣሪያ ላላቸው የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር እና የኤሌክትሪክ ፕላን፤

2/ የኮንክሪት ጣሪያ ለሌላቸው የአርክቴክቸር፣ እና የኤሌክትሪክ ፕላን፡፡

ለ) ለምድብ "ለ" ሕንፃዎች የአርኪቴክቸር ፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ እና የኤሌክትሪካል ፕላን፤

ሐ) ለምድብ "ሐ" ሕንፃዎች ለህንፃ ምድብ "ለ" ከተጠየቁት በተጨማሪ የእሳት አደጋ መከላከያ ፕላንና ማብራሪያ፤

መ) ሊፍት እና ለአየር ዝውውር ሰው ሰራሽ አማራጮችን ለሚጠቀሙ ህንፃዎች የኤሌክትሮ ሜካኒካል ፕላኖች እና ትንታኔዎች፡፡

2/ የምድብ "ሐ" ሕንጻዎች ፕላን ለአካል ጉዳተኞች የሚያመቹ የየወለሉ መዳረሻዎች ለአካል ጉዳተኞች የተመደቡ የመኪና ማቆሚያዎች እና በየወለሉ ለአካል ጉዳተኞች የሚመቹ መጸዳጃ ቤቶች ያሏቸው ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡

3/ ከፍታቸው ከሃያ ሜትር በታች የሆኑ እና ለአካል ጉዳተኞች አገልግሎታቸውን ተደራሽ ማድረግ የሚችሉ የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ሊፍት ሳያስፈልጋቸው ሊገነቡ የሚችሉበት ሁኔታ በመመሪያ ይዘረዘራል፡፡

4/ የባለመስታወት ግድግዳ ለሚገጠምላቸው ሕንፃዎች ነፀብራቁ በነዋሪው ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፳9. በግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች

የአዋጁ አንቀጽ ፴1 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1/ ማንኛውም የሕንፃ ባለቤት አዲስ የሕንፃ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት፣

ሀ) በአካባቢው ቀደም ብሎ የተሠሩ ሕንፃዎችን እና የመሠረተ ልማት አውታሮችን አገልግሎት የሚያውክ፤

ለ) የአካባቢውን ወይም አዋሳኙን ደህንነትና ጤንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ ፤ እና

ሐ) የትራፊክ ፍሰትን የሚያስተጓጉሉ፤

ሁኔታዎችን ማስወገድና ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፡፡

PART FIVE

LAND USE, RELATED STUDIES AND DESIGNS

28. Designs

1/ The plans or designs which shall be prepared for each category of building shall be as follows:

a) for Category "A" buildings:

(1) architectural, structural and electrical designs for buildings having concrete roofing;

(2) architectural and electrical designs for buildings without concrete roofing.

b) for Category "B" buildings, architectural, structural, sanitary and electrical designs;

c) for Category "C" buildings, in addition to the regulations for Category "B" buildings, fire safety plans and the analysis thereof;

d) buildings using lifts and artificial ventilation shall have electro-mechanical designs and analysis.

2/ Designs of Category "C" buildings shall have suitable access to stairs, parking lots, and lavatories accessible for people with disability.

3/ The conditions under which public buildings of below twenty people with meters of height shall be accessible to disability without having lifts shall be stipulated by directives.

4/ For buildings having glass walls it shall be ascertained be fore hand that the performance terminal shall be comfortable to the public.

29. Precautionary Measures during Construction

Without prejudice to the provisions of Article 31 of the Proclamation:

1/ a building owner shall, prior to construction of any new building:

a) avoid disturbances to the safety and services of existing buildings and infrastructures;

b) avoid conditions which may endanger the safety of adjoining properties and health of the community; and

c) remove any obstacle which might hinder the traffic flow in the area.

2/ በምሽት የሚከናወን ግንባታ አካባቢውን የማያውክ እና ለሌሊት ሥራ አመቺ አደጋ የማያስከትል ስለመሆኑ እየተረጋገጠ ከሕንፃ ሹመ ፈቃድ ሊሰጠው ይገባል፡፡

3/ በአዋጁ አንቀጽ ፴1 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ለሚሠሩ ግንባታዎች የሕንፃው ባለቤት የሚከተላቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች በጽሁፍ እንዳስፈላጊነቱም በዲዛይንና በዝርዝር ትንታኔ በማስደገፍ ለሕንፃ ሹመ በማቅረብ ይሁንታ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

4/ አጎራባቹ የቴክኒክ ዕውቀት ካለው በራሱ ከሌለው ደግሞ በሚወክለው ባለሙያ ገንቢው የሚያደርገው የቅድሚያ ጥንቃቄ ዝግጅት ንብረቱን ከአደጋ መከላከል መቻሉ እንዲገለጽለት መጠየቅ እና በግንባታም ወቅት ከግንባታው ባለቤት ጋር በመነጋገር መከታተል ይችላል፤

5/ ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት ጉዳት እንዳያደርስ፡-

ሀ) የግንባታ ሥፍራውን ተቀባይነት ባላቸው ቁሶች መክለል፤

ለ) በቁፋሮ ወቅት ከመሬት በታች ሊኖሩ የሚችሉ የመሠረተ ልማት መሥመሮች እንዳይጎዱ፤

ሐ) በአካባቢው የትራፊክ እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል፤

መ) ተቀጣጣይነት ያላቸውን የግንባታ ቁሳቁሶች በአያያዝ ጉድለት ለእሳት አደጋ እንዳይጋ ለጡ በማድረግ፤

ሠ) በግንባታ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሠራተኞ ችና ጐብኚዎች የደህንነት መጠበቂያዎችን በማሟላት፤

ረ) ለግንባታ የሚውሉ የኬሚካል ውጤቶች በአጠቃቀም ወቅት በሰው ሕይወትና ንብ ረት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ፤ እና

ሰ) ብናኝ ጭስና አንጸባራቂ ጨረር የመሳሰሉ አዋኪ ነገሮች አካባቢውን እንዳይረብሹ ፤

ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፤

፴. <u>በግንባታ ቦታ ላይ ስለሚከናወኑ ሥራዎች</u>

1/ በአዋጁ አንቀፅ ፴2 ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት የተሰጠው ትዕዛዝ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ባይከበር የከተማ አስተዳደሩ ወይም የተሰየመው አካል በራሱ ወጪ የግንባታው ቁሳቁስ ወይም ተረፈ ግንባታ እንዲነሳ በማድረግ ወጪው እንዲተካለት በሕግ ይጠይቃል፡፡

2/ማንኛውም የግንባታ ወይም የማፍረስ ሥራ የሚያከናውን ሰው ለሚያከናውነው ሥራ፡-

ሀ) የእቃ ማከማቻ፤

ለ) የሠራተኞች መፀዳጃ፤

2/ if a construction activity is to be carried out at nights, it shall be permitted by the building officer that such activities do not cause nuisance to the public and could be carried out safely and conveniently;

3/ for buildings carried out according to Article 31 sub article (2) of the Proclamation the building owner shall support precautionary measures by written document, designs and specifications and shall obtain approval from the building officer;

4/ the neighbor has the right to be notified of and to ensure by himself, if he has the technical knowledge, or by represented technical professional that the safety measures taken by the building owner are satisfactory to prevent danger to his properties and to follow up during construction in consultation with the owner;

5/ in order to prevent the occurrence of any danger during any construction work, the owner of the building shall take the following measures:

a) cover the construction site with acceptable materials;

b) protect utility lines in the ground from being damaged during excavation;

c) ensure the well being of the traffic flow around the site;

d) prevent the exposure of inflammable construction materials to fire;

e) provide safety wears for site employees and visitors;

f) take precautionary measures to avoid danger on the life of human being and property which may be caused by the misuse of chemical products for construction purpose; and

g) employ appropriate mechanisms which protect any mote of dust , smoke, ray, and other similar elements from causing nuisance and pollution to the area.

30. <u>Building Site Operations</u>

1/ If the owner of the construction fails to comply with the notice mentioned in sub article (3) of Article 32 sub-article (3) of the Proclamation within the given time, the urban administration or the designated organ shall remove materials and residues and claim costs incurred thereby to be refunded.

2/ Any person carrying out an erection or demolition of a building shall fulfill the following temporary facilities on site prior to commencing:

a) store;

b) lavatory for employees;

ሐ) የሠራተኛ ልብስ መቀየሪያ፤

መ) የቢሮ አገልግሎት፤ እና

ሠ) የሠራተኛ መመገቢያ ወይም ጊዜያዊ መጠለያዎችን፤

በቅድሚያ ማሰራት አለበት፡፡

ፀ1. <u>አርክቴክቸር</u>

1/ የአርክቴክቸር ፕላኖች በመሪ ፕላን እና በዝርዝር የአካባቢ ፕላኖች የተቀመጡ መስፈርቶችንና የአጎራባች ሕንፃዎችን ያገናዘቡ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል፡፡

2/ ማንኛውም የሕንጻ ፕላን የአካባቢውን የአየር ፀባይ ሁኔታ ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡

3/ የማንኛውም ሕንፃ አርክቴክቸራል ዲዛይን ለኃይል ቁጠባ አጠቃቀም ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጥ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ፀ2. <u>የኤሌክትሪክ መሥመር ዝርጋታ</u>

1/ የኤሌክትሪክ መስመር ፕላን ተከላና ዝርጋታ ተቀባይነት ባላቸው ኮድና ስታንዳርዶች እንዲሁም የሚመለከተው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

2/ ለሕንጻው አገልግሎት የሚውል በቂ የኃይል አቅርቦትና የተገልጋዩን ደህንነት ከስጋት ነጻ የሚያደርግ ደረጃውን የጠበቀ የአደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች መገጠም ይኖርባቸዋል፡፡

3/ በምድብ "ሐ" የሚካተቱ ህንጻዎች ከዋና የኃይል አቅርቦት መስመር ከሚገኘው ኃይል በተጓዳኝ ለዋና ዋና አገልግሎቶቻቸው የሚሆን አዋጪ በሆነበት ለታዳሽ የኃይል አቅርቦት ቅድሚያ በመስጠት አማራጭ የኃይል አቅርቦት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ፀ3. <u>ሊፍቶች</u>

ሊፍቶች፡-

1/ ያለማቋረጥ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ከዋና የኃይል አቅርቦት መስመር በተጨማሪ የመጠባበቂያ ኃይል አቅርቦት ሊኖራቸው፤

2/ በድንገተኛ የኃይል መቋረጥ ምክንያት ተገል ጋዩን ወደ ሚቀጥለው ወለል የሚያደርሱ እና በሮቻቸው እንዲከፈቱ የሚያስችል ባትሪ ሊገጠ ምላቸው፤

3/ የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ተገልጋይ ለአጠቃቀም ምቹ መሆን፤

4/ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት እንዳያቋርጡ እና አስተማማኝ አገልግሎት እንዲሰጡ በተ ገቢው ባለሙያ ክትትል፤ በተመሰከረለት ድርጅት ወቅታዊ ምርመራ፤ ጥገና እና ዕድሳት ሊደረግላቸው፤

ይገባል፡፡

c) dressing room;

d) office; and

e) dining rooms or temporary sheds as may be necessary.

31. <u>Architecture</u>

1/ Architectural designs shall take into consideration the requirements of the master plan, the local development plan and surrounding buildings.

2/ Any building design shall consider the weather condition of the specific area.

3/ Any architectural design shall take into consideration energy efficient mechanisms.

32. <u>Electrical Installations</u>

1/ Electrical designs and installations shall be carried out in accordance with acceptable code and standards and directives to be issued by the concerned body.

2/ A building shall have sufficient power supply, a standardized security and fixed controlling devices to avoid the likelihood of danger and ensure safety of users.

3/ Designs of Category "C" buildings shall give priority to cost effective renewable alternative power supply system within their installations in addition to the main power supply, for their essential services.

33. <u>Lifts</u>

Lifts shall:

1/ have alternative power source in addition to the main power supply to provide service without interruption;

2/ have batteries which enable users to reach the next floor and to open their doors in cases of unexpected power interruptions;

3/ be suitable for all users including people with disabilities;

4/ have continuous professional follow up, timely inspection and maintenance by a certified entity so as to prevent their interruption as a result of defects and ensure the reliability of its service

፵4. ለአካል ጉዳተኞች የሚደረጉ ዝግጅቶች

1/ ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ወይም የሕንፃ ክፍል የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ የሚገታ ወይም የሚገድብ መሆን የለበትም፡፡

2/ በማምረቻ ህንጻዎች ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች የሚያመች የልብስ መቀየሪያ፣ መታጠቢያ እና ሌሎችም አገልግሎቶች መሟላት አለባቸው፡፡

3/ በከፊል የተጠናቀቁ የሕዝብ መገልገያ ሕንፃዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ሲፈለግ መሟላታቸውን ከሚያረጋግጡ ሁኔታዎች አንዱ ለአካል ጉዳተኞች የሚያመቹ መሆናቸው ይሆናል፡፡

4/ በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ውስጥ አካል ጉዳተኞችን በየመዳረሻዎቹ ከእንቅፋት የሚጠብቋቸው እንዲሁም በመኪና ማቆሚያነት የተያዙላቸውን ስፍራዎች የሚያመለክቱ ዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው ምልክቶች መደረግ አለባቸው፡፡

ክፍል ስድስት
የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን

፵5. የውሃ አቅርቦት

1/ ለሰዎች አገልግሎት የሚውል ማንኛውም ሕንፃ የውኃ አቅርቦት እና ጥራት አገሪቱ የተቀበለ ቻቸውን ዓለም አቀፍ እና በአገር ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን ኮድና ስታንዳርዶች ያሟላ መሆን ይኖርበታል፡፡

2/ ለማንኛውም ህንፃ የሚዘጋጁ ዲዛይኖች የውሃ አቅርቦት መስመሮች እና የመጠቀሚያ ቁሳቁሶች ቁጠባዊ የውሃ አጠቃቀምን መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፡፡

3/ የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖችና የስርጭት መስመሮች ለቁጥጥር እና ለጽዳት ተደራሽ ሆነው መገንባት አለባቸው፡፡

፵6. የፍሳሽ አወጋገድ

1/ ማንኛውም የፍሳሽ ቆሻሻ መውረጃ መስመሮች ፕላን በአዋጁ እና ተቀባይነት ባላቸው የህንጻ ኮድና ስታንዳርዶች መሠረት በተመዘገበ ባለሙያ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

2/ በአካባቢው ተስማሚ የሆነ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ካለ የሚገነባው ህንጻ የፍሳሽ ቆሻሻ መሥመር ከአካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት ይኖርበታል፡፡

3/ ማንኛውም ህንጻ በአቅራቢያው ተስማሚ የሆነ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ከሌለው በከተማ አስተዳደሩ ወይም በተሰየመው አካል ተቀባይነት ባለው ሌላ መንገድ ፍሳሹን ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

4/ በግቢ ውስጥ የሚደረግ የፍሳሽ አወጋገድ እና ግንባታ የሚመለከታቸውን አካላት ያወጡትን መስፈርቶች እንዲያሟላ መደረግ አለበት፡፡

34. Facilities for Disabled Persons

1/ Any public building or a part thereof shall not prevent or hinder the movement of disabled persons.

2/ Manufacturing buildings shall fulfill suitable dressing rooms, bathrooms and other facilities for persons with disability.

3/ Suitability for persons with disability shall be one of the criteria to be considered in giving an occupancy permit for partially completed public buildings.

4/ In any public buildings, international standard signs shall be posted at junctions to keep persons with disability from any obstacles and to indicate parking lots allocated for them.

PART SIX

WATER SUPPLY AND SANITATION

35. Water Supply

1/ The supply and quality of water for human use shall fulfill the local and international codes and standards which the country has adopted .

2/ Designs of water supply system for all buildings and the sanitary fixtures and appliances installed thereto shall be efficient in water saving.

3/ Water reservoirs and supply systems of any building shall be accessible for inspection and cleaning.

36. Sewerage

1/ Any sewage disposal design shall be prepared by registered professional in accordance with the Proclamation and acceptable codes and standards.

2/. Where in the vicinity of any building a suitable means of sewage disposal is available , the sewage line of such building shall be connected with the existing sewage line.

3/ Where any building has not suitable sewage disposal system in the vicinity, it shall use any other means acceptable by the urban administration or the designated organ to discharge sewage.

4/ Any sewage disposal and its construction in a compound shall satisfy the requirements set for the same by the concerned bodies.

፴7. ተቀባይነት የሌላቸውን ፍሳሾች መቆጣጠር

1/ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ከመፀዳጃ የሚወጣን ፍሳሽ ከጎርፍ ማስወገጃ ቦይ ጋር እንዳይቀላቀል የሚከለክሉ ህጎች መከበራ ቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

2/ የጎርፍ ውሀ መስመር ወደ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ ወይም ማጠራቀሚያ ውስጥ እንዳይገባ የሚቀመጡ የጥንቃቄ መንገዶች መከተላቸውን የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

፴8. የኢንዱስትሪ ዝቃጭ

1/ ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይሰጠው የኢንዱስትሪ ዝቃጭ ያዘለ ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር ወደ ማንኛውም ፍሳሽ ፣ ወንዝ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መልቀቅ ወይም መጣል የለበትም፡፡

2/ ከኢንዱስትሪዎች ወይም ከፋብሪካዎች የሚወጡ ዝቃጮች ብክለትን እንዳያስከትሉ የአከባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሊዘጋጅላቸውና ግምገማው በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

3/ ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሠራ የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በተፅዕኖ ግምገማ መሠረት በአግባቡ ስለመገንባቱ አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

፴9. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ

የአዋጁ አንቀፅ ፵3 እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1/ ለደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያነት የሚመረጠው ቦታ ለቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎች ተደራሽ መሆን ይኖርበታል ፤

2/ መርዛማ ደረቅ ቆሻሻ የሚያመነጩ የማምረቻ ተቋማት የተለየ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የማጠራቀሚያ እና የአወጋገድ ዘዴ መጠቀም አለባቸው፡፡

፵. የጎርፍ ውሀን ስለማስወገድ

1/ የማንኛውም ይዞታ ባለቤት የጎርፍ ውሀ ለማስወገድ ለዚሁ ተብሎ ወደተገነባ ዋና መስመር ማገናኘት ይኖርበታል፡፡

2/ የማንኛውም ይዞታ ባለቤት ከዝናብ ውሃ የተወሰነው በይዞታው ውስጥ ሠርጎ እንዲቀር ከከተማ አስተዳደሩ ወይም ከተሰየመው አካል የወጡ ህጎችንና በጥናት የተደገፉ ዘዴዎችን መጠቀም አለበት፡፡

ክፍል ሰባት

እሳት መከላከልና የእሳት ማጥፊያ ተከላ

፵1. ጠቅላላ መስፈርት

1/ ማንኛውም ሕንፃ በህንፃው ላይ ሊደርስ የሚችልን የእሳት አደጋ ለመከላከል የእሳት አደጋ መከላከያ ሠራተኞች መዳረሻ ሊኖረው ይገባል፡፡

37. Control of Objectionable Discharge

1/ The urban administration or the designated organ shall ensure that the rules and regulations prohibiting the mixing of toilet waste sewage with flood lines are strictly observed.

2/ The urban administration or the designated organ shall control and follow up that the flood line shall not enter to sewage line or reservoir.

38. Industrial Effluent

1/ No person shall release any industrial effluent or solid matter to any sewage, river or solid waste removal sites without obtaining permission from the concerned body.

2/ Impact assessment of industries or factories having residues shall be conducted in order to prevent environmental pollution and such assessment shall be approved by the concerned bodies prior to any release.

3/ A construction of a sewage disposal or treatment shall be approved by the concerned body prior to commencement of the service to ensure that it is carried out in accordance with the impact assessment and acceptable standards.

39. Solid Disposal

Without prejudice to Article 43 of the Proclamation:

1/ the area allocated for storage of solid disposal shall be accessible to waste disposal vehicles;

2/ manufacturing buildings generating toxic solid wastes shall have different storage and disposal methods which qualify international standard.

40. Disposal of Flood Water

1/ Any owner of site shall join the flood water discharge line to the main flood water line which is built for the same purpose.

2/ The owner of any site shall use suitable means which is in compliance with directives of the urban administration or the designated organ for part of the rain water to be absorbed within the site.

PART SEVEN

FIRE PROTECTION AND FIRE FIGHTING INSTALLATION

41. General Requirement

1/ Any building shall have an access for fire fighters to get into in case of fire accident

2/ በምድብ "ሐ" ለሚገኙ ሕንፃዎች የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ እና በራሱ የሚሠራ የእሳት ማጥፊያ ሥርዓት ሊገጠምላቸው ይገባል፡፡

3/ በምድብ "ሐ" ለሚገኙ ሕንፃዎች በአደጋ ጊዜ የማምለጫና የመውጫ አመላካቾች በግልጽ ቦታ እንዲታዩ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡

4/ ተቀጣጣይነት ባሕሪ ያላቸው የኬሚካል ውጤቶች ተገቢ ማከማቻ ቦታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

5/ ከአምስት ወለል በላይ ከፍታ ላላቸው ሕንፃዎች ከዋናው መወጣጫ ደረጃ በተጨማሪ ከአደጋ ነፃ ወደሆነ መሬት የሚያወርድ የአደጋ ጊዜ ማምለጫ ደረጃ ሊኖር ይገባል፡፡

6/ የአደጋ ጊዜ ማምለጫ መስመር በአደጋ ጊዜ በቀላሉ ማግኘት የሚቻልና ዓለም አቀፍ ምልክቶችን የሚጠቀሙ፣ የኃይል አቅርቦት በተቋረጠ ጊዜም የሚሰሩ የብርሃን አቅጣጫ ጠቋሚ አመልካቾች የተገጠሙለት እና ከመሰናክል ነፃ መሆን አለበት፡፡

፵2. <u>የእሣት ማጥፊያ መሣሪያ ተከላ</u>

1/ የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ ተከላ የሥራ ፈቃድና የሙያ ምስክር ወረቀት ባለው ሰው መከናወን አለበት፡፡

2/ የእሳት ማጥፊያ መሥመሮች እና መሳሪያዎች በቀላሉ ለተጠቃሚ የሚታዩ እና አጠቃቀማቸውን በጉልህ የሚያሳዩ መግለጫዎች በአጠገባቸው የሚገኝ መሆን አለባቸው፡፡

3/ የሚገጠሙት የእሳት ማጥፊያ መሣሪያዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ስለመሆናቸው በሚመለከተው አካል የተረጋገጡ እንዲሁም በየጊዜው አስተማማኝነታቸው ፍተሻ የሚደረግላቸው መሆን አለባቸው፡፡

4/ በማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ውስጥ ያለ የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ በማንኛውም ጊዜ ለአጠቃቀም ዝግጁ መሆን አለበት፡፡

5/ ማንኛውም የምድብ "ሐ" ህንፃ ባለቤት የእሳት ማጥፊያ ወይም መከላከያ መሣሪያዎችን ደህንነት እና የዕድሳት ጊዜ የሚያመለክቱ መረጃዎችን መዝግቦ በመያዝ ለሚመለከተው አካል ቁጥጥር ዝግጁ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፵3. <u>የእሳት መከላከያ የውሃ አቅርቦት</u>

የእሳት አደጋ መከላከያ ውኃ መርጫ ቱቦ ተቀባይነት ያለው የግፊትና የአቅርቦት ደረጃ ያሟላ መሆን አለበት፡፡

2/ Category "C" buildings shall have installed their own fire alarm and automatic fire extinguisher system.

3/ Category "C" buildings shall have installed their own emergency escape routes and exit signs in a conspicuous place so as to be visible at all times.

4/ There shall be a suitable storage for inflammable chemicals.

5/ In buildings having more than five floors, there shall be safe escape route for emergency cases besides the main staircase.

6/ The emergency escape route of a building shall be easily accessible and shall have international standard exit signs posted to indicate the escape route in case of emergency and shall also have alternative power supply for illumination during power interruptions.

42. <u>Installation of Fire Extinguishing Instruments</u>

1/ Fire extinguishing instruments shall be installed by licensed persons having professional certificate.

2/ Fire extinguishing instruments and lines shall be placed in a position where they can be easily seen and with their user manuals.

3/ The fire extinguishing instruments shall meet the standard, approved for same by the concerned body, and shall be regularly inspected.

4/ A fire extinguisher installed in a public building shall be made ready at all times for its purpose.

5/ The owner of a Category 'C' building shall keep a record of the maintenance of fire- extinguishing and protection equipment available for inspection by the concerned body.

43. <u>Supply of Water for Fire Protection</u>

The fire fighting water hose shall meet acceptable standards of water pressure and supply.

ክፍል ስምንት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፵4. አስተዳደራዊ መቀጮ

1/ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ኃላፊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁን ወይም ይህንን ደንብ በሚተላለፍ የግንባታ ባለቤት ላይ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል እንደ ሕንፃው ደረጃ ከዚህ በታች የተመለከተው አስተዳደራዊ መቀጮ መጣል ይችላል፡-

ተ.ቁ	የጥፋት ዓይነቶች	የህንፃ ምድብ እና አስተዳደራዊ ቅጣት መጠን (ብር)		
		ምድብ ሀ	ምድብ ለ	ምድብ ሐ
1	ፍቃድ የተሰጠበት ፕላን ማመልከቻ ኮፒ በግንባታ ቦታ አለመገኘት	----------	2000	3000
2	የውስጥ አደረጃጀት /የግንባታ ቅድመ ዝግጅት/ ሳያሟሉ ሥራ መጀመር	----------	2000	3000
3	የተሰጡ የማስተካከያ ትእዛዞችን ካጠናቀቁ በኋላ አለማስታወቅ	1000	2000	3000
4	የተሰጡ ትእዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን	1000	2000	3000
5	ከግንባታ ክልል ውጪ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሠረት አለማንሳት	1000	2000	3000
6	ካለተቆጣጣሪ ማሰራት	----------	3000	5000
7	ካለማስታወቂያ ሥራ መጀመር	----------	2000	4000
8	ያለፈቃድ ዕድሳት ማድረግ	2000	3000	5000
9	ያለፈቃድ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን	2000	3000	5000
10	ያለፈቃድ የማፍረስ ሥራ ማከናወን	2000	3000	5000
11	በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃ ዎች አለመውሰድ	……	3000	5000
12	የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ መጠቀም	……	3000	5000

2/ ከዚህ በላይ በተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ያልተመለከቱ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ የህንፃ ሹመ እንደጥፋቱ ክብደት በሠንጠረዡ ለየህንፃ ምድቡ ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ ተመጣጣኝ ነው ብሎ ያመነበትን ቅጣት ይጥላል።

3/ የተፈጸመው ጥፋት በአዋጁ በተመለከቱት የወንጀል ድንጋጌዎች ስር የሚወድቅ ሆኖ ሲገኝ የሕንፃ ሹመ ተገቢ ነው ብሎ የሚወስደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጥፊው ላይ የወንጀል ክስ እንዲቀርብበት ለሚመለከተው አካል መምራት አለበት።

PART EIGHT

MISCELLANEOUS PROVISIONS

44. Administrative Fines

1/ Without prejudice to criminal and civil liabilities, urban administration or the designated organ may impose the following administrative fines on persons who violate the provision of the Proclamation or this Regulation depending on the category of the building:-

No	Types of breaches	Building Categories and amount of fine		
		Category A	Category B	Category C
1	Failure to display copy of plan permit at construction site	……..	2000	3000
2	Commencing construction works without fulfillment of preliminary works or facilities	……..	2000	3000
3	Failure to notify completion of rectification orders	1000	2000	3000
4	Failure to effect orders within the given time limit	1000	2000	3000
5	Failure to remove construction materials or residues out of site in accordance with the given written notice	1000	2000	3000
6	Working without inspector	----------	3000	5000
7	Starting construction without notification	----------	2000	4000
8	Renovating without permit	2000	3000	5000
9	Carry out an expansion work without permit	2000	3000	5000
10	Demolish without permit	2000	3000	5000
11	failure to take safety measures during construction	……	3000	5000
12	Failure to obtain occupancy permit	……	3000	5000

2/ Where a breach which is not specified in the above table is committed, the building officer shall impose fine displayed in the table which he considers reasonable to the breach committed.

3/ Where the breach committed is one which falls under the criminal provisions stipulated in the Proclamation, the building officer shall refer the case to the relevant body for prosecution besides taking any legal measure he considers appropriate.

4/ u²ÉI ›"kî ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) SW[ƒ ¾T›×M ¾Ñ"²w Skà Øó}—¨‹" u²ÉI Å"w ¾} SKŸ~ƒ" ŸSðìU ¨ÃU uŸ} T¨‹ ›e}ÇÅ` ¨ÃU u}c¾S¨‹ ›"M ŸT›¨cÆ የማስተካከያ ርምጃዎች ነፃ ›ÁÅ`Ñ¨‹U::

፵5. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1/ ከአዋጁ መውጣት በፊት በሥራ ላይ የነበሩ ኮድና ደረጃዎች ይህንን ደንብ እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ ደንብ መሠረት እንደወጡ ተቆጥረው አዋጁ በሚመለከታቸው ህንፃዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ከአዋጁ እና ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ የኮድና ደረጃዎች ድንጋጌዎች ተሽረዋል፡፡

፵6. መመሪያ ስለማውጣት

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይህንን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፵7. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን 2ሺ3 ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

4/ The fines imposed on the basis of sub article (1) and (2) of this Article may not relieve the offender from complying with the requirements of this Regulations and other additional corrective measures to be taken by the urban administration or the designated organ.

45. Transitory Provisions

1/ The codes and standards which have been in force before the promulgation of the Proclamation are deemed to have been issued under this Regulation and are applicable to all buildings on which the provisions of the Proclamation apply.

2/ Notwithstanding sub article (1) of this Article, the provisions of the codes and standards which contradict with the provisions of the Proclamation and this Regulations are hereby repealed.

46. Power to Issue Directives

The Ministry of Urban Development and Construction may issue directives to implement these Regulations.

47. Effective Date

This Regulations shall enter into force as of the date of publication in the Federal Negarit Gazetta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of May, 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ፪ሺ፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 31
ADDIS ABABA 6th May, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፬/፪ሺ፩ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ... ገጽ ፬ሺ፮፻፸፫
ማረሚያ ቁጥር ፬/፪ሺ፩ .....ገፅ ፬ሺ፯፻

CONTENTS

Proclamation No. 624/2009

Ethiopian Building Proclamation .....Page 4673
Corrigendum No. 4/2009 …….. Page 4700

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፬/፪ሺ፩

የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ

የሕዝብ ጤንነትና ደህንነት እንዲረጋገጥ ለማድረግ የሕንፃ ግንባታ ወይም የሕንፃ ግንባታ ማሻሻያና የአገልግሎት ለውጥን በተመለከተ በሀገሪቱ በአጠቃ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ዝቅተኛውን ደረጃ ለመወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ /፫/ የፌደ ራል መንግሥቱ የጤና፣ የትምህርት እንዲሁም የሳይ ንስና ቴክኖሎጂ ሀገር አቀፍ መመዘኛዎችንና መሠረ ታዊ የፖሊሲ መለኪያዎች የማውጣትና የማስፈፀም ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ /፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፬/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

PROCLAMATION NO. 624/2009

ETHIOPIAN BUILDING PROCLAMATION

WHEREAS, it has been found necessary to determine the minimum national standard for the construction or modification of buildings or alteration of their use in order to ensure public health and safety;

WHEREAS, sub-article (3) of Article 51 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia empowers the Federal Government to establish and implement national standards and basic policy criteria for public health, education, as well as science and technology;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Building Proclamation No. 624/2009".

ፀሸጀደፀፀ

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካል ሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

፩/ "ሚኒስቴር" ማለት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው፤

፪/ "ሕንፃ" ማለት ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለፋብሪካ ወይም ለማናቸውም ሌላ አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ነው፤

፫/ "የሕንፃ ሹም" ማለት ይህንን አዋጅ እንዲ ያስፈጽም በከተማ አስተዳደር ወይም በተ ሰየመ አካል የተሾመ ሰው ነው፤

፬/ "የተመዘገበ ባለሙያ" ማለት ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በዲዛይን ወይም በኮንስትራ ክሽን የባለሙያነት የምሥክር ወረቀት የተሰ ጠው ሰው ወይም በዲዛይን ወይም በኮንስት ራክሽን የአማካሪነት የምዝገባ ምሥክር ወረ ቀት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፭/ "የተመዘገበ የሥራ ተቋራጭ" ማለት ሥል ጣን ባለው አካል ተመዝግቦ የሥራ ተቋራ ጭነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰ ጠው ድርጅት ነው፤

፮/ "ምድብ 'ሀ' ሕንፃ" ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ፯ ሜትር ወይም ከዚያ በታች የሆነ ባለአንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም ማናቸውም ከሁለት ፎቅ በታች የሆነ የግል መኖሪያ ቤት ነው፤

፯/ "ምድብ 'ለ' ሕንፃ" ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ከ፯ ሜትር በላይ የሆነ ወይም ባለሁለት ፎቅና ከሁለት ፎቅ በላይ የሆነና በምድብ 'ሐ' የማይሸፈን ሕንፃ ወይም በምድብ 'ሀ' የተመደበ እንደሪል ስቴት ያለ የቤቶች ልማት ነው፤

፰/ "ምድብ 'ሐ' ሕንፃ" ማለት የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ፣ የፋብሪካ ወይም የወርክሾፕ ሕንፃ ወይም ከመሬት እስከ መጨ ረሻው ወለል ከፍታው ከ፲፪ ሜትር በላይ የሆነ ማናቸውም ሕንፃ ነው፤

፱/ "ግንባታ" ማለት አዲስ ሕንፃ መገንባት ወይም ነባር ሕንፃን ማሻሻል ወይም አገል ግሎቱን መለወጥ ነው፤

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Ministry" means the Ministry of Works and Urban Development;

2/ "building" means a permanent or temporary construction used for the purpose of dwelling, office, factory or for any other purpose;

3/ "building officer" means a person appointed by an urban administration or designated organ to enforce this Proclamation;

4/ "a registered professional" means a person who is issued with a certificate as a design or construction professional or a juridical person which is issued with a certificate as a design or construction consultant by the relevant body;

5/ "a registered contractor" means a juridical person who is registered and issued with a work permit by the relevant authority as a contractor;

6/ "category 'A' building" means a one story building with a span of 7 meters or less between two reinforced concrete, steel or other structural frames or any dwelling house not exceeding two stories;

7/ "category 'B' building" means a building with a span of more than 7 meters between two reinforced concrete, steel or other structural frames or of two or more stories not covered in category 'C' or a real estate development of category 'A';

8/ "category 'C' building" means any public or institutional building, factory or workshop building or any building with a height of more than 12 meters;

9/ "construction" means the construction of a new building or the modification of an existing building or alteration of its use;

10/ "dangerous building" means a building that is structurally unsafe or constitutes a special fire hazard or health risk;

፲/ "አስጊ ሕንፃ" ማለት ግንባታው አስተማማኝ ያልሆነ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ለእሳት አደጋ የተጋለጠ ወይም ለጤና ጠንቅ የሆነ ሕንፃ ነው፤

፲፩/ "የተሰየመ አካል" ማለት ይህ አዋጅ ከከተማ ክልል ውጪ ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ አዋጁን እንዲያስፈጽም በክልሉ የሚሰየም አካል ነው፤

፲፪/ "ሰነድ" ማለት ከሕንፃ ዲዛይንና ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚያስፈልግ ወይም የተዘጋጀ ፕላን፣ ሪፖርት፣ የዋጋ ግምት ወይም ማንኛውም የቴክኒክ ጉዳይን የሚያስረዳ ሰነድ ነው፤

፲፫/ "የግል መኖሪያ ሕንፃ" ማለት ለአንድ ቤተሰብ መኖሪያነት የሚያገለግሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎችና የመፀዳጃና የማብሰያ አገልግ ሎቶች ያሉት ሆኖ በመኖሪያው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ የመኪና ማቆሚያንና ለመኖሪ ያነት የሚውሉ ከዋናው ቤት የተነጠሉ ክፍሎ ችን ሊጨምር ይችላል፤

፲፬/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፭/ "ፕላን" ማለት የአንድን ሕንፃ መጠን፣ ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃው የሚሠራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴን የሚያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ የሜካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችን ንድፍ ሊያካትት ይችላል፤

፲፮/ "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአ ዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፯/ "የማስቆሚያ ትዕዛዝ" ማለት በአንድ የሕንፃ ግንባታ ቦታ የሚካሄድ ሥራ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም በሕንፃ ሹም ወይም በሕንፃ ተቆጣጣሪ የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው፤

፲፰/ "ፎቅ" ማለት በሁለት ወለሎች መካከል ወይም ከላይ ሌላ ወለል ከሌለ በወለሉና በኩርኒስ መሃል ያለው የሕንፃ ክፍል ነው፤

፲፱/ "የከተማ አስተዳደር" ማለት በሕግ ወይም በሚመለከተው መንግሥታዊ

11/ "designated organ" means an organ appointed by the concerned Regional State to enforce this Proclamation in areas outside of urban centers to which this Proclamation is applicable;

12/ "document" means any plan, report, estimate or any other technical presentation required or prepared in connection with the design and construction of a building;

13/ "private dwelling building" means a house containing one or more habitable rooms with sanitary and cooking facilities for the use of a single family and may include any garage and other domestic outbuildings within its site;

14/ "person" means any natural or juridical person;

15/ "plan" means any drawing or model showing the extent, nature and size of a building and the materials and method of assembly to be used, and it may include architectural, structural, sanitary, electrical, mechanical, fire protection and other drawings;

16/ "Regional State" means any regional state established in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

17/ "stop order" means any order given by a building officer or by a building inspector to discontinue activities on a building construction site;

18/ "story" means that part of a building which is situated between the top of any floor and the top of the floor next above it, or if there is no floor above it that portion between such floor and the ceiling;

19/ "urban administration" means an organ to which powers and duties of administering an urban center have been given by law or delegated by the concerned government body;

20/ "urban center" means any locality having a municipal administration or a population size of 2,000or more inhabitants, or which at least 50% of its labour force has, primarily, engaged in non –agricultural activities.

አካል ውክ ልና የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግ ባር የተሰጠው አካል ነው፤

፳/ "ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመ በት ወይም ፪ሺ ወይም ከዚያ በላይ የሕ ዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ ቢያንስ ፱ በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝ በት አካባቢ ነው፡፡

፫. የተፈጻሚነት ወሰን

፩/ ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፤

ሀ/ ፲ሺ እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ባሏ ቸው ከተሞች፣

ለ/ የነዋሪዎቻቸው ቁጥር ከ፲ሺ በታች በሆነና ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው በሚ መለከተው ክልል በሚወሰኑ ሌሎች ከተሞች፣

ሐ/ ከከተማ ውጭ በሚገኙ ህዝብ የሚገ ለገልባቸው ሕንፃዎች፣ የኢንዱስትሪ ወይም የዘመናዊ እርሻ ተቋሞችና የሪልስቴት ሕንፃዎች፡፡

፪/ ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፣

ሀ/ አዋጁ በፀናበት ቀን ወይም ከዚያ በፊት በተጠናቀቀ ሕንፃ፣

ለ/ አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተሰጠ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ በመካሄድ ላይ በሚገኝ በማናቸውም ሕንፃ፣

ሐ/ ከሀገር ደህንነት ጋር በተያያዘ እና በሌሎች ምክንያቶች አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ሕንፃ፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪/ለ/ ድንጋጌ ቢኖርም፣

ሀ/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በወጣ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ መሠረት በመ ካሄድ ላይ የሚገኝ ሆኖ ግንባታው ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ከሆነ፣

3. Scope of Application

1/ This Proclamation shall apply to:

a) urban centers that have 10,000 or more dwellers;

b) other urban centers that have less than 10,000 dwellers and to which this Proclamation shall be applicable in accordance with the decision made by the Regional State concerned;

c) public buildings, or buildings which could be used for industrial or commercial scale agricultural occupancy or real-estate out side of urban centers.

2/ This Proclamation may not apply to any building:

a) completed on or before the effective date of this Proclamation;

b) which is under construction with a building permit issued before the effective date of this Proclamation;

c) exempted by the decision of the Council of Ministers for reasons related with national security and other purposes.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article 2(b) of this Article, the urban administration or the designated organ may apply this Proclamation to:

a) a building under construction with a building permit issued before the effective date of the Proclamation if such construction is not completed within three years of the effective date of the Proclamation;

b) in order to ensure the compliance of a building for which alteration of service is required with the service such building is sought to render;

c) a building to which a renovation is required.

ለ/ የአገልግሎት ለውጥ ጥያቄ የሚቀር ብለት ህንፃ ሕንፃው ሊሰጠው ከታ ሰበው አገልግሎት አንፃር ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ሐ/ የእድሳት ፈቃድ ጥያቄ በሚቀርብለት ህንፃ ላይ፣

የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ይህ አዋጅ ተፈጻሚ እንዲሆንበት ማድረግ ይችላል፡፡

፬ሺ፩፻፫፯

ክፍል ሁለት
አስተዳደር

፬. ማመልከቻና ፕላን ስለማቅረብ

፩/ የግንባታ ሥራ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛ ውም ሰው ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ ሕንፃን ለመገንባት የሚቀርብ ማመልከቻ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ለዚሁ ብሎ ባዘጋጀው ቅፅ መሠረት ሆኖ ይህም እንደ ሕንፃው ምድብ አይነት ዲዛይንና ሪፖርት የያዘ መሆን አለበት፡፡

፫/ ከማመልከቻው ጋር በአዋሳኝ ባለ ስፍራ ዎች የሚገኙ ዋና መንገዶችንና የታወቁ ቦታዎችን ስም የሚገልፁ መረጃዎች መቅ ረብ ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ አመልካቹ ሕንፃ በሚገነባበት ቦታ ወይም በንብረቱ ላይ የይዞታ መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበ ታል፡፡

፭/ የሚቀርቡት ሠነዶች በዚህ አዋጅና በሌ ሎች ሕጐች የተመለከቱት መሟላታቸውን ለማረጋገጥ በበቂ ሁኔታ የተሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፭. የፕላን ስምምነት

፩/ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ከማቅረቡ አስቀድሞ የፕላን ስምምነት ማግ ኘት ይኖርበታል፡፡

፪/ የሕንፃ ሹሙ ለፕላን ስምምነት የቀረበለትን ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ ከከተማው ፕላን

PART TWO
ADMINISTRATION

4. Submission of Application and Plans

1/ Any person intending to carry out construction shall submit an application to the urban administration or designated organ.

2/ The application to carry out construction shall be made on an application form prepared by the urban administration or designated organ and shall consist of a design and report according to the category of building in question.

3/ The application shall be accompanied with a reference to main roads and names of prominent places.

4/ The applicant shall submit proof of possession rights to the land or property on which the construction will take place.

5/ The documents to be submitted shall be sufficiently complete to determine compliance with this Proclamation and other laws.

5. Planning Consent

1/ Any person intending to carry out construction shall secure a planning consent prior to submitting application for construction permit.

2/ After having received an application for a planning consent a building officer shall grant a written declaration for compliance or non-compliance with the urban planning of the urban center.

6. Approval of Plans

1/ A building officer shall check submitted plan documents to ensure compliance with the provisions of this Proclamation and other laws. Approval of plans shall not be withheld on account of requirements not included in this Proclamation or other laws.

ጋር የሚጣጣም ወይም የማይጣጣም ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

፮. ፕላን ስለማስፀደቅ

፩/ የሕንፃ ሹሙ የቀረበለትን የፕላን ሠነድ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋ ገጥ ይኖርበታል፡፡ በዚህ አዋጅ ወይም በሌ ሎች ሕጎች ያልተካተቱ መመዘኛዎችን ምክ ንያት በማድረግ አንድ ፕላን እንዳይፀድቅ ማድረግ ፡ ይችልም፡፡

፪/ የሕንፃ ሹሙ የሚሰጠው አስተያየት የጐሉ ግድፈቶችን የሚመለከት ካልሆነና ተፈላጊው ማስተካከያ በሥራው ሂደት ወቅት በቀላሉ ሊደረግ የሚችል ከሆነ አስተያየቱን በማከል ፕላኑን ሊያፀድቀው ይችላል፡፡

፫/ የፀደቀ ፕላን በላይ ላይ "ፀድቋል" የሚል ማህተም የተደረገበት፣ የምዝገባ ቁጥርና የፀደቀበትን ቀን የያዘና የሕንፃ ሹም ፊርማ ያረፈበት መሆን ይኖርበታል፡፡

፬/ ከፀደቀው ፕላን ጋር አብረው የቀረቡት የማ መልከቻ ቅፆች በቅፆች ውስጥ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ "ፀድቋል" የሚል ምልክት ተደርገባቸው የምዝገባ ቁጥ ርና የፀደቀበት ቀን ይሠፍርባቸዋል፡፡ አስተ ያየት ካለ ለዚሁ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ሰፍሮ በሕንፃ ሹሙ ይፈረምበታል፡፡

፭/ ፕላን ከፀደቀ በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አን ቀጽ /፫/ መሠረት ማህተምና ፊርማ ያረፈ በት የማመልከቻ ቅፅና በአባሪነት የተያያ ዘው ፕላን አንድ ቅጅ ለአመልካቹ ይመለስ ለታል፣ ሌላው በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ዘንድ ይቀመጣል፡፡

፮/ ፊርማና ማህተም ያለበት የፀደቀ ፕላንና ማመልከቻ ቅጅ በሕንፃው መሥሪያ ቦታ በግልፅ እንዲታይ ሆኖ ይቀመጣል፡፡ የፀደ ቀውን ፕላንና የማመልከቻውን ዋናዎቹን ቅጅ በጥሩ ሁኔታ እንዲቀመጥ ማድረግና ግንባታው ከመጀመሩ በፊት ወይም ግንባ ታው በሚካሄድበት በማናቸውም ጊዜ በከተ ማው አስተዳደር፣ በተሰየመው አካል፣ በሕ ንፃ ሹሙ ወይም ሥልጣን ባለው

2/ A building officer may approve plans with comments provided that the comments refer to minor non-compliance and if the required rectification work can easily be carried out during construction.

3/ Approved plans shall be stamped **"APPROVED"** and shall bear a registration number and date of approval and shall be signed by a building officer.

4/ Application forms submitted with approved plans shall be stamped "APPROVED" in the appropriate space provided and shall bear a registration number and date of approval. Comments, if any, shall be entered on the form in the space provided and shall be signed by a building officer.

5/ Upon approval, one set of application form and accompanying plan, as stamped and signed in accordance with sub-article (3) of this Article, shall be returned to the applicant and the other set shall be retained by the urban administration or designated organ.

6/ A copy of the signed and sealed application form and approved plans shall be permanently displayed at the building site. All original approved application forms and plan shall be kept in good condition and presented at any time, before and during construction, upon the request of the urban administration or designated organ or the building officer or an authorized inspector.

7. Plan Review Period

A building officer shall review documents submitted and approve or reject within the time limit. The time limit shall be determined by Regulation to be issued for the implementation of this Proclamation.

8. Rejection of Plans

1/ Building plans that do not comply with the provisions of this Proclamation and other laws shall be rejected by a building officer.

ተቆጣጣሪ ሲጠየቅ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፮. <u>የፕላን መገምገሚያ ጊዜ</u>

የሕንፃ ሹም የቀረበለትን ሠነድ በመገምገም ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማፅደቅ ወይም ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

፯. <u>ፕላን ውድቅ ስለማድረግ</u>

፩/ ከዚህ አዋጅና ከሌሎች ሕጐች ጋር የማይጣጣም የግንባታ ፕላን በሕንፃ ሹ.ሙ. ውድቅ ይደረጋል፡፡

[illegible]

፪/ ፕላኑ ውድቅ የሚሆን ከሆነ የህንፃ ሹ.ሙ. በማመልከቻው ላይ ባለው ክፍት ቦታ የተጣሰውን የህጉን ድንጋጌ በአጭሩ መግለፅ ይኖርበታል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ ማብራሪያዎች በተለየ ወረቀት በመፃፍ ማያያዝ ይችላል፡፡

፫/ በሕንፃ ሹ.ሙ. ውድቅ የተደረገ ማመልከቻና ፕላን "ውድቅ ተደርጓል" የሚል ምልክትና ቀን እንዲሁም የሕንፃ ሹ.ሙ. ፊርማ ይሠፍርበታል፡፡

፬/ የቀረበው ፕላን ውድቅ ሲደረግ የሕንፃ ሹ.ሙ. ፊርማ እና ማህተም ያረፈበት ማመልከቻ አንድ ቅጅ እና የፕላኑ ሁለት ቅጂዎች ለአመልካቹ የሚመለስ ሲሆን የህንፃ ሹ.ሙ. ፊርማ እና ማህተም ያረፈበት የማመልከቻ ቅፅ አንድ ቅጂ በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ዘንድ ይቀመጣል፡፡

፱. <u>የግንባታ ፈቃድ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት የፀደቀ ፕላን በግንባታ ፈቃድነት ያገለግላል፡፡

፲. <u>ፕላን ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

፩/ የግንባታ ሥራው ካልተጀመረ አንድ የፀደቀ ፕላን የሚፀናበት ጊዜ የሚያበቃው ፕላኑ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ካበቃ በኋላ ይሆናል፡፡

፪/ የግንባታ ሥራው ፕላኑ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ

2/ Upon rejection of submitted plans a building officer shall state in brief which provision of the law is not complied with, in the space provided on the application form. Further detailed explanations may be written if necessary on separate sheets and attached to the form.

3/ An application and plan rejected by a building officer shall be stamped "REJECTED" and shall bear the date and signature of the building officer.

4/ Upon rejection of submitted plans a building officer shall return one copy of the duly signed and sealed application form and the two copies of the duly signed and sealed plans to the applicant and the urban administration or designated organ shall retain one copy of the duly signed and sealed application form.

9. <u>Construction Permit</u>

A plan which has been approved in accordance with Article 6 of this Proclamation shall constitute a construction permit.

10. <u>Validity Period of Plans</u>

1/ The validity of approved plans shall expire after six months from the date of issuance where construction work has not been started.

2/ The validity of approved plans with which construction work has been started within six months from the date of issuance shall expire after five years from the date of issuance, if the construction work has not been completed.

3/ Upon expiry of the validity period as set out in sub-articles (1) or (2) of this Article an application for extension of the validity period of approved plans shall be submitted for re-approval of plans in accordance with this Proclamation.

11. <u>Building Officers</u>

1/ Every urban administration or designated organ shall appoint a building officer, with the required educational and professional qualifications to enforce, on its behalf, the provisions of this Proclamation and other laws.

የተጀመረና ሥራው ያልተጠናቀቀ ከሆነ የፀደቀው ፕላን ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃው ፕላኑ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ አምስት ዓመት ካበቃ በኋላ ይሆናል።

2/ A building officer shall receive all applications for approval of plans and issue approved plans after ascertaining full compliance with this Proclamation and other laws.

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ወይም /፪/ በተገለፀው መሠረት ፕላን ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ ጊዜው እንዲራዘም በዚህ አዋጅ መሠረት ፕላኑን እንደገና የማፀደቅ ጥያቄ መቅረብ ይኖርበታል።

3/ A building officer shall inspect all buildings under the territorial jurisdiction of the urban administration or designated organ to ascertain conformity with this Proclamation and other laws.

፲፩. የሕንፃ ሹም

፩/ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል አስተዳደሩን ወይም አካሉን በመወከል የዚህን አዋጅና የሌሎችን ሕጐች ድንጋጌዎች ለማስፈፀም የሚያስችል አስፈ ላጊው የትምህርትና ሙያ ዝግጅት ያለው የሕንፃ ሹም ይሾማል።

4/ A building officer may be assisted by staff of the urban administration or designated organ in the discharge of his duties; provided, however, that he shall be responsible for the ruling on applications for approval of plans and inspection reports.

፪/ የሕንፃ ሹም ፕላን እንዲፀድቅ የሚቀርብ ማመልከቻን በመቀበል ከዚህ አዋጅና ከሌሎች ሕጐች ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ያፀድቃል።

5/ A building officer is empowered to order inspection of exempted buildings erected before the effective date of this Proclamation and to order the demolition or rectification of such buildings if public safety is at risk.

፫/ የህንፃ ሹም በከተማው ክልል ወይም በተሰየ መው አካል አስተዳደር ክልል ውስጥ ያሉ ሕንፃዎች ከዚህ አዋጅና ከሌሎች ሕጐች ጋር የሚሰማሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደረጋል።

6/ A building officer is empowered to order rectification work if plans are approved by error; provided, however, that he must have adequate justification for ordering such rectification work.

፬/ የህንፃ ሹም ተግባሩን ለመወጣት በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመው አካል ሌሎች ሠራተኞች ሊታገዝ ይችላል። ሆኖም ፕላን ለማፀደቅ በሚቀርቡ ማመልከቻዎችና የም ርመራ ሪፖርቶች ላይ ውሳኔ መስጠት የእርሱ ኃላፊነት ይሆናል።

7/ Without prejudice to his criminal liability, the building officer shall bear civil liability for any damage he causes to third parties in the course of implementing this Proclamation and the regulation and directives issued there under as a result of his own fault.

፭/ የህንፃ ሹም ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰሩና አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆ ንባቸው የተደረጉ ሕንፃዎች እንዲመረመሩ የማድረግና ለሕብረተሰቡ ደህንነት አስጊ ሆነው ከተገኙ እንዲፈርሱ ወይም እንዲ ስተካከሉ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል።

8/ Without prejudice to the provision of sub article (1), the city administration or the designated body shall make good the damage incurred by third parties where such act of the building officer is regarded as a professional fault. In such cases, the city administration or the designated body shall have the right to reimburse from the building officer to the extent it has paid to third parties.

፮/ የህንፃ ሹም በስህተት በፀደቀ ፕላን መሠረት የተገነባ ህንፃ እንዲስተካከል የማዘዝ ሥል ጣን ይኖረዋል፣ ሆኖም የማስተካከያ ሥራ ውን ለማዘዝ በቂ ምክንያት ሊኖረው ይገባል።

፫/ የህንፃ ሹሙ ይህ አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡት ደንብና መመሪያዎች የጣለበትን ኃላፊነት በግል ጥፋት ምክንያት በአግባቡ ባለመወጣት በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በወንጀል ተጠያቂ የሚ ሆንባቸው ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች መሠረት በግል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፬/ የህንፃ ሹሙ ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሕንፃ ሹሙ የፊጸመው ጥፋት በፍትሐብ ሔር ድንጋጌዎች መሠረት የሥራ ጥፋት ነው ሊባል የሚችልበት ምክንያት ያለ እንደሆነ በሶስተኛ ወገኖች ላይ ለደረሰው ጉዳት የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል በሕግ መሠረት ተገቢውን ካሣ ከፍሎ አጥፊውን መልሶ ለመጠየቅ መብት አለው፡፡

፴ሺ፩፻፹፩

፲፪. ውክልና

፩/ የህንፃ ሹሙ ከፕላን ግምገማ ጋር በተያያዘ ራሱ በሙሉም ሆነ በከፊል ሊያከናውነው ያልቻለውን ሥራ ለሌላ አካል ወይም ለዚሁ ተግባር ለተሰየመ ሰው በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ የህንፃ ሹም የተመሩለትን ማመልከቻዎች በተመለከተ በፅሑፍ አስተያየቱን ለከተማው አስተዳደር ወይም ለተሰየመው አካል ይል ካል፣ እንዲሁም ተያይዘው በቀረቡት ሠነ ዶች ላይ ይፈርማል፣ እንዳአስፈላጊነቱም ማህተም ያደርጋል፡፡

፫/ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል የፀደቁትን ወይም ውድቅ የተደረ ጉትን ሰነዶች በህንፃ ሹሙ ስም ይሰጣል፡፡

፬/ ፕላኖችን ለመገምገም የሚሰጠው ውክልና የቁጥጥር ተግባራትንም እስከማከናወን ድረስ ሊሰፋ ይችላል፡፡

፲፫. ስለ ይግባኝ

፩/ እያንዳንዱ የከተማ አስተደደር ወይም የተ ሰየመ አካል በዚህ አዋጅ መሠረት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ተገቢው ሙያያላ

12. Delegation

1/ A building officer may delegate another body or an approved person to carry out duties in connection with review of plans for which he is incapable of undertaking fully or partially.

2/ A building officer shall make written recommendations to the urban administration or designated organ on application referred to him and shall sign all attached documents and stamp the same where appropriate.

3/ The urban administration or the designated organ shall issue the approved or rejected documents under the name of its building officer.

4/ The delegation for review of plans may be extended to cover inspection duties.

13. Appeals

1/ Each urban administration or designated organ shall establish a board of appeal which shall have members with the relevant qualification to enable them to decide cases in accordance with this Proclamation.

2/ The board of appeal shall have the power to hear, and decide on, decisions taken by building officers regarding construction. The decision of the board on technical matters shall be final.

14. Non-compliance

1/ A Building officer may order a building constructed without approved plans to be demolished, if the plans utilized to construct such building does not comply with the provisions of this Proclamation or other laws.

2/ In the event that the owner of a building who has been ordered by a building officer to demolish or remove his building fails to comply with the order, the urban administration or designated organ may demolish or remove the building and claim the incurred expenses from the owner.

ቸው አባላት የሚገኙበት የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ያቋቁማል፡፡

፪/ ቦርዱ ግንባታዎችን በተመለከተ በህንፃ ሹም በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ቦርዱ ቴክኒክ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

፲፬. ትዕዛዝን አለማክበር

፩/ የህንፃ ሹም ባልፀደቀ ፕላን ለተገነባ ህንፃ ጥቅም ላይ የዋለው ፕላን የዚህን አዋጅ ወይም የሌሎች ህጐችን ድንጋጌዎች የሚጥስ ሆኖ ከተገኘ ህንፃው እንዲፈርስ ያደርጋል፡፡

፪/ በህንፃ ሹም ህንፃውን እንዲያፈርስ ወይም እንዲያነሳ የተሰጠውን ትዕዛዝ የህንፃው ባለ ቤት ያላከበረ እንደሆነ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ህንፃውን በማፍ ረስ ወይም በማንሳት ያወጣውን ወጪ ከባለ ንብረቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፬/

፫/ ተፈላጊው ማስታወቂያ ሳይሰጥ የተሰራን ሥራ ወይም የሥራውን የተወሰነ ክፍል ለም ርመራ እንዲከፈት፣ እንዲነሳ ወይም በህን ፃው ላይ ጉዳት በማያደርስ ሁኔታ እንዲፈ ርስ የህንፃ ሹም ሊያዝ ይችላል፡፡

፬/ የህንፃ ሹም የህንፃ አካልን ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ የፀደቀ ፕላን ሳይኖር የተሰራን ሥራ እንዲስተካከል ማዘዝና ባለንብረቱ በትዕዛዙ መሠረት እስኪያስተካክል ድረስ በህንፃው ላይ የሚካሄድ ሌላ ሥራ እንዲቆም ማገድ ይችላል፡፡

፲፭. ስለ ማስታወቂያ

፩/ በምድብ 'ለ' ወይም 'ሐ' ሥር የሚወድቅ ህንፃ ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው ግንባታው የሚካሄድበትን ጊዜ የሚያሳይ ማስታወቂያ ለሚመለከተው የህንፃ ሹም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በቀረበ ማስታወቂያ ላይ ህንፃ ሹም የሚሰ ጠው ውሳኔ የጊዜ ገደብ ይህን አዋጅ ለማ ስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

3/ A building officer may order any work or parts thereof to be opened for inspection, removed or, without causing damage to building, demolished if such work has been carried out without the required notice being given.

